- እኔ ወዴት እንደሚሄዱ አላውቅም ለጊዜው እኔ ሹፌር ነኝ ታዛዥ ስለሆንኩ ያው ወደቤት ውሰደኝ በማለት ወደቤት እየወሰድኩት ነው እንጂ ወዴት እንደሚወስድ እኔ አላወቅኩም
- ዋና ጥያቄ አበቃን
- እሺ ዋና ጥያቄ አብቅቷል መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ የተከሳሽ ጠበቆች
- ምስክርዎ የድርጅቱ ሰራተኛ ነን ብለዋል ስለድርጅቱ የሚያውቁት አለ የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ ማስረጃ ሰነድ አንብበዋል?
- እኔ ከገባሁ እዛ ድርጅት ውስጥ 14 ቀኔ ነው እኔ ብዙም ስለድርጅቱ ያወቅኩት ነገር የለም
- ድርጅቱ ቦርድ እንዳለውም አያውቁም ድርጅቱ የሚተዳደረውም በቦርድ እንደሆነም አያውቁም አደል?
- አዎ እኔ ብዙም እዛ ውስጥ ጠለቅ ብዬ አልገባሁም
- ሼህ ሱልጣን ተጠሪነታቸው ለማን እንደሆነም አያውቁም?
- አላውቅም አዎ ተሸከርካሪው የድርጅቱ ነው ያሉት ከምን ተነስተው ነው ?
- እ?
- ቅድም ይዘውት የነበረው ተሸከርካሪ ንብረትነቱ የማን ነው?
- ንብረቱማ የመንግስት መሆኑን ነው እኔ የማውቀው
- ምስክር ከርል አደባባይ ፖሊሶች ሲፈትሹ ጥቁር ፌስታል ተገኘ ብለዋል ስለፌስታሉ ምንም የተናገሩት ነገር የለም ሲናገሩ የሰሙት ነገር የለም አደል?
- አልሰማሁም
- እርስዎ ማንበብ መፃፍ ይችላሉ እንዴ?
- እችላለሁ
- አማርኛ ያነባሉ?
- አነባለሁ አዎ
- ስለዚህ አንብበው ነው ምን እንደሚል የተረዱት?
- አዎ ያን ሰዓት እኔ መንገድ ዘግቻለሁ መኪኖች ቆመዋል ግዴታ ደግሞ ያው
- ግልጽ ነው ጥያቄው ምንድን ነው አንብበውታል ወይ ነው እሷን ብቻ ይመልሱ?
- ወረቀቱን አንብበውታል አላነበቡትም?
- እኔ ወረቀቱን ለጊዜው አላነበብኩትም እነሱ እያነበቡ ነበረ ፖሊሶቹ ያን ሰዓት እኔ ቆመው ከፌስታል ውስጥ አንድ ፍሬ አውጥተው ወረቀቱ የት እየወሰድክ ነው በማለት ይሄ ወረቀት ተፈላጊ ነው
- እኮ እና ሲያነቡት ሰምተዋል በድምጽ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይሄ ሰማሁ ያው አሁን የሰማኋት እኮ ነው አሁን የተናገርኳት
- ስለዚህ ሲያነቡ ነው የሰሙት እንጂ እርስዎ አላነበቡም?
- እኔ አላነበብኩም
- ቅድም ሲያነቡ አልሰማሁዋ ብለው ነበር አደል ስለ ፌስታሉ ስለ ጥቁሩ ፌስታል ፖሊሶቹ ሲናገሩ አልሰማሁም ብለው ነበር አደለ?
- ሲያነቡ አልሰማሁም ሳይሆን አንድ ፍሬ አውጥተው እያነበቡ ነበር?
- እኮ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ነበር የሚያነቡት ወይስ ለራሳቸው ነበር የሚያነቡት?
- አደለም ሙራድ ሽኩር አጠገብ ያው ይሄ ወረቀት ከየት አመጣህ በማለት እያነበቡ ነበር
- እነሱ እያነበቡ ነበር እንጂ እርስዎ አልሰሙም?
- እኔ አላነበብኩም ሰምቻለሁ እንጂ ስለሰማሁ እኮ ነው
- እሺ ሙራድ ሽኩር ጠርተዎት ወደቤቱ ነበር አደለም እየወሰዱት የነበረው ድርጅቱ አላዘዞትም አደል ሙራድ በግሉ እንጂ ድርጅቱ አላዘዞትም ?
- ምክትል ሥራ አስኪያጅ ስለሆነ ግዴታ ያው በኔ በእሳቸው በኔ ትእዛዝም ትንቀሳቀሳለህ እኔ የማዝህን ትእዛዝ ትሞላለህ በማለት ነው
- እኮ እሱ ስላዘዞት እንጂ ?
- እኔ መኪናውን አሳስቼ አልወጣሁም
- በኔ ትእዛዝ ትንቀሳቀሳለህ ብለህ ቆመሃል እና እሱን ጨርስ በኔ ትእዛዝ ትንቀሳቀሳለህ የሚል ነገር ስትናገር ነበር አደል አሁንም ?
- በነዳጅ /ግልጽ ያልሆነ/ ያው ምክትል ስራ አስኪያጅ ስለሆነ ሲያዘኝ እኔ እዛ ቦታ ሂድ እዛ አድርሰኝ ወደዚህ እንሂድ ሲል እኔ እሄዳለሁ ከዛ ውጪ ያው እሳቸው ሃጂ ሱልጣን ሲያዙኝ በነሱ ሁለቱ መስረተ ነው የምሄደው
- ሙራድ ምክትል ስራ አስኪያጅ ነው እያሉ ነው ?
- አዎ
- በምን አወቁ ይሄን የስራ ድርሻ ድርሻዎን በምን አወቁ?
- ያው ነግረውኛላ እኔ ነኝ የማዝህ ወይ ሃጂ ሱልጣን ወይ እኔ ነኝ የማዝህ ብለውኛል
- አይ ምክትል ሲሉ አሃ እኔ ነኝ የማዝህ ስላሉህ ነው ምክትል ሥራ አስኪያጅ ያሉት?
- ያው ምክትል ስራ አስኪያጅ ማለት ስገባም እዛ ድርጅት ውስጥ ስገባም ያው ሁለቱ ናቸው እኔ ዋና ስራ አስኪያጅ ነኝ ሙራድ ምክትል ስራ አስኪያጅ ነው በማለት ነግረውኛል
- ጣሃ ቅድም ስትመስክር አንዱን ወረቀት ብቻ ነው ሲያወጡ ያየሁት ብለሃል አንዳን ፍሬ ?

1689 103

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ይሄን ብቻ ነው ያየኸው አደል?
- ሌላው ውስጥ አለ ፌስታል ውስጥ ፌስታል ውስጥ ያለው ከዚህ ወረቀት ጋር አነድ ይሁን ሌላ ይሁን የምታውቀው ነገር አለ በዛት ነው ወረቀቱ ወረቀቱ ፌስታል ውስጥ የነበረው ብዛት ነው ብዛት ያለው ወረቀት ነው
- ስለዚህ ይሄ ወረቀት ከዚጋር ይመሳሰል አይመሳሰል የምታውቀው ነገር አለ ወይ ነው ጥያቄዬ
- እሱን አላውቅም
- አቶ ጣሃ በዚህ መኪና አንተ ለድርድቱ ስራ አስኪያጅ ስትሰራ ለሌሎች ሰራተኞችም የሰርቪስ አገልግሎት ትሰጣለህ አደለም?
- ሸጣሃ ነው እንዴ ስሙ?
- አይ አቶ ጣሃ ነው ያልኩት
- ጣሃ ከተቀጠርክበት ቀን ጀምሮ ለሌሎች ሰራተኞችም በዚሁ መኪና የሰርቪስ አገልግሎት ትሰጣለህ አደል?
- አዎ እሰጣለሁ እነሱ ሲያዙኝ ነው ሁለቱ ካዘዙኝ ነው ሰርቪስ የምሰጣቸው
- እኮ ለሙራድ ሸኩርም ከዚህ በፊትም በተመሳሳይ እቤቱ የማድረስ የሰርቪስ አገልግሎት ትሰጥ ነበር?
- ሙራድ እና ሃጂ ሱልጣን ሲያዙኝ ነው ለሌሎቹ ሰርቪስ የምሰጠው
- አይ ለሙራድ ለራሱ ?
- ለሙራድ ለራሱ እዛ ውሰደኝ እዚህ ውሰደኝ ሲለኝ እኔ ነኝ የማመላልሰው
- በዛን እለት ሚያዝያ 4 ቀን 2004 በመደበኛ ስ ራህ ነው እየሄድክ የነበረው አደለም?
- አዎ
- ጨርሰናል
- ድጋሚ ጥያቄ ካላችሁ አቃቤ ሕግ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ጣሃ በድርጅቱ የቀጠሩኝ ሙራድ እና ሃጂ ሱልጣን ናቸው ብለሃል?
- አዎ
- ደሞዝስ ማን ነው የሚከፍልህ?
- ደሞዝ ሰራተኛ አለች ቢሮ
- ከዘው ድርጅት ነው የምትወስደው አደል?
- አዎ ከቢሮ ነው የምወስደው
- መኪና ያስረከበህ ማን ነው?

1690 04

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መኪናው ያስረከበኝ ሃጂ ሱልጣን ናቸው
- እሺ ይሄንን መኪና ሲሰጡ የማን መኪና ነው ብለው ነው የሰጡት ?
- መኪናውን ሲሰጠኝ የድርጅቱ ነው ብለው ነው የሰጡኝ
- ስለዚህ ቅድም መኪናው የማን ነው ስትባል የመንግስት ነው ብለሃል ተተደጋጋሚ እና ስለዚህ ይሄ መኪና የድርጅቱ ነው ማለት ነው ?
- አዎ ያው የድርጅት ነው እና 35 ቁጥር ነው የመንግስት ነው
- 35 ቁጥር ስለሆነ ድገመው አሁን ያልከውን ነገር ጮክ ብለህ?
- 35 ማለት እኔ ያው የመንግስት ብዬ ነው የወሰድኩት
- ሙሉ ታርጋውን ንገረን ?
- **35** ያልከው ምኑን ነው?
- 35 ያው የእርዳታ ድርጅት
- ሌላው እነዚህ ወረቀቶቹን አንዱን ወረቀት አውጥተው አይቼዋለሁ ብለሃል ሌላም ወረቀት አለ ብዙ ነው ውስጥ ያለው ወረቀት ብዙ ነው ብለሃል ውስጥ ያለውን አይኸዋል እንዴ?
- አላየሁትም
- ሳታየው እንዴት ብዙ ነው አልክ ?
- ያው ፌስታሉን ከፍቶት ነበር
- ከፌስታሉ ተከፍቶ አልወጣም እንዴ?
- እንዳለማ አላወጡትም
- ፌስታሉን ከፍተው ስትል ሲከፈት ምን አየህ ?
- ሲከፈት ወረቀቶች አሉ ውስጥ
- ምን አይነት ወረቀቶች?
- ነጭ ነጭ ወረቀቶች ውስጥ አሉ
- እነዚህ ወረቀቶች ከመሃላቸው አንድ ከወጣው ጋር አንድ አይነት አደሉም እንዴ?
- እኮ ያው አንድ አይነት ይሁን ምን ይሁን ብቻ እነሱ አንድ ፍሬውን አውጥተው ነው ያነበቡት
- እሺ ሌላ ምን አንተ የፈረምክበት ምናምን ወረቀት የለም የዛን ቀን?
- እዛ ድርጅት ውስጥ ?
- አይ የተያዘ ቀን ወይንም በማግስቱ ?
- የለም እኔ ወደ ጣቢያ ነው ቀጥታ የወሰዱኝ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ተመሳሳይ አገልግሎት ሌላ ጊዜም ለአቶ ሙራድ እሰጣለሁ ብለዋል በዛ በምሽት ሰዓት ማታ አንድ ሰዓት ላይም ትወስደው ነበር ሌላ ጊዜ?
- ያው ሰዓቱ
- ተቃውሞ አለ
- አንድ ሰዓት አላልንም የተከበረው ፍ/ቤት አስራአንድ ሰዓት ላይ አብነት ቀጠረኝ አሉ እንጂ አንድ ሰዓተ ላይ አላሉም ስለዚህ ወይም ጥያቄውን በዚህ መልክ ያስተካከሉት
- መልስ እንስጥ
- እሺ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ በዋና ጥያቄም በመስቀለኛ ጥያቄም የተያዙበትን ሰዓት ሲገልፁ ምሽት አንድ ሰዓት ላይ ካርል ኢደባባይጋር እንደተያዙ ገልፀዋል እና በዛ ምሽት ሁል ጊዜ ትንቀሳቀሱ ነበረ ወይ የሚል ነው የእኛ ጥያቄ እና ተቃውሞ ያለ አግባብ ነው
- እሺ ይቀጥሉ ልክ ነው
- እናመሰግናለን እሺ ጥያቄውን ልድገም ወይስ ግልጽ ነው ጥያቄው
- አንድ ሰዓት የተባለው ለጊዜው ሰዓቱ መንገዱ ተዘጋግቷል ፍተሻ ነበር በፍተሻው ሰዓት ያው እየተጠባበቅን ነው የምንሄደው ቀስ እያልን ነው አንድ መኪና ተፈትሾ ሲያልፍ ነው
- ሁል ጊዜ እንደዛ ታመሻላችሁ?
- አይ አናመሽም
- ምስክር እነዚህ በጥቁር ፌስታል አንዷን ብቻ ነው ያየሁት ብለዋል ወረቀቶቹን ሌሎቹ የት ሄዱ መለሱላችሁ ፖሊሶች ?
- አልመለሱም
- የት ቀረ?
- ያው እንዳለ ወደ ወረዳ 23 ጣቢያ
- ስለዚህ የፖሊስ ኤግዚቢት ሆኗል?
- አዎ ፖሊሶቹ ይዘውት ሄዱ
- አበቃን
- እሺ ምስክር እናመሰግናለን ጨርሰዋል
- **የዛሬው ችሎት በዚሁ ተጠናቅል ቀሪ የአቃቤ ሕግ ምስክሮችን ለመስማት ለጥር 28 ቀን 2005 ዓ.ም. ተቀጠረ።።**

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

4ኛ ወ/ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

ጥር 28 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች :- ብሰራት ተህልቁ

ባህር ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሳሽ :- አቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድምአገኝ ፣ቴዎድሮስ ጌታቸው ፣ዘረሰናይ ምስግና ቀርበናል

ተከሳሾች:- እነአቡበክር አህመድ የቀረ ተከሳሽ አለ ዛሬ ሁሉም ቀርቧል እሺ ተከሳሾች ቀርበዋል የተከሳሽ ጠበቆች ባህሩ መካንጋ ፣ አዲስ መሃመድ ፣ሃሊማ ሰኢድ ፣መሃመድ አብደላ ፣ዳዊት ነጋሽ 28ኛ ተከሳሽ አህመድ ጀማል

- እሺ የተከሳሽ ጠበቆች በፊት ከነበሩት አስር ጠበቆች 5 ጠበቆች ስማቸውን ጠቅሰው ቀርበዋል የ28ኛ ተከሳሽ ጠበቃ ቀርበዋል መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ቀሪ የአቃቤ ሕግ ምስክሮችን ለመስማት ነበር ስለዚህ አቃቤ ሕግ ምስክር መጥቷል አቅርባችኋል
- መጥተዋል ቀርበዋል የተከበረው ፍ/ቤት
- የምናመለክተው አለ የተከበረው ፍ/ቤት
- በጽሁፍ ይዛችሁታል
- አዎ
- አቅርቡታ ጽሁፉን /ግልጽ ያልሆነ/ እየታየ እስከዛ አንድ ምስክር እንሰማለን

1693 107

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም ምያለሁ
- እሺ ምስክር አማርኛ ቋንቋ ይችላሉ?
- አዎ
- ስለዚህ ለምስክሮች ደህንነት ሲባል በዝግ ችሎት እየታየ ነው የናንተም ከመጀመሪያ ስማቸው በስተቀር የአድራሻ እና የስራ ቦታ አይገለጽም ይሄንን አውቀው የመጀመሪያ ስሞን ይነግሩ ስንት ነው አቃቤ ሕግ?
- 68ኛ
- እሺ በፍ/ቤቱ 18ኛ ተራ ቁጥር ነው በአቃቤ ሕግ መዝገብ ቁጥር 68ኛ የተጠቀሱት የአቃቤ ሕግ ምስክር ተማም ብለው ቀርበዋል እዚህ የመጡት ለምንድን ነው በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?
- ያሲን ኑሩ
- ሌላ?
- በድሩ ሁሴን
- አቤት?
- በድሩ ሁሴን
- ሌላ?
- መሃመድ አባተ ፣አቡበክር አህመድ ፣ኑሩ ጦኪ
- እነዚህን ሰወች ታውቃቸዋለህ አሁን የጠቀስካቸውን?
- አዎ
- ልታሳየን ትችላለህ?
- እችላለሁ
- እስቲ አንዴ አሳየን ማን ነው ያሲን ነህ እሺ 3ኛ ተከሳሽን ምስክሩ ለይቶ አሳይቷል
- እሺ ከነዚህ ሰወችጋ ፀብ ወይም ዝምድና አላችሁ?
- የለንም
- እሺ ካሉ በኋላ በአቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ

1694/05

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ምስክር የመጣሁት ለምስክርነት ነው ብለዋል 5 ሰወችን ጠቁመው አሳይተዋል እነዚህ የጠቆሟቸውን ሰወች የት ነው የሚያውቋቸው?
- አንዋር መስኪድ
- ምን ሲያደርጉ?
- ሐምሌ 7 በነበረው አንዋር መስኪድ
- ሐምሌ 7 መቼ የትኛው ሐምሌ 7 ?
- 2004
- ሐምሌ 7 ቀን 2004 አንዋር መስኪድ ስንት ሰዓት ነው?
- አራት ሰዓት ተኩል አካባቢ
- እሺ አሁን በዝርዝር ይንገሩን ምንድን ነው ያዩት የሰሙት?
- አራት ሰዓት ተኩል አካባቢ እስፔሻሊ ያሲን ኑሩ አንዋር መስኪድ ውስጥ ያው ቅስቀሳ ሲያካሂድ ነበር
- ምን እያለ?
- ቅስቀሳው እንኳን ደስ ያላችሁ አህባሾች እንኳን ደስ ያላችሁ አህላል ሱኒዎች ወንድሞቻችን ተገደሉላችሁ የሚል ቅስቀሳ ሲያካሂድ ነበር ከዝሁር በኋላ ሰላት እልጀናዛ እንሰግድላቸዋለን ለወንድሞቻችን ሲል ነበር
- ለነማን?
- ለሞቱት
- የት ነው የሞቱት?
- ሐምሌ 6 አወልያ በመንግስት ኃይሎች ተገለዋል ነው ያሉት ይሄንን ቃል እራሱ ሲናገር ሰምቼዋለሁ ሰው ተገሎ ነበር?
- የተገደለ የለም
- ታዲያ ለምንድን ነው የሚለው ያሲን ኑሩ ለምንድን ነው ይሄንን የሚለው?
- እንግዲህ የሃሰት ቅስቀሳ ነው
- እሺ ወንድሞቻችን ተገደሉላችሁ ስለዚህ ምን ይሁን?
- እንግዲህ በመንግስት መጥፎ እርምጃ ያው ሲጀምርም መሰለኝ ያደምጣል ጣልቃ እየገባ ነው ጣልቃ ከመግባት አልፎ

1695 109

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማን?
- ያሲን ኑሩ
- ማን ነው ጣልቃ የገቡ በምን ውስጥ ነው ጣልቃ የገቡት?
- በኃይማኖታችን ውስጥ ጣልቃ ገብቷል
- ማን?
- መንግስት ይሄን በማለት ሲቀሰቅስ ነበር ከዚህ በተረፈ ያው አርብ አወልያ ት/ቤት አካባቢ በተደረገው አሰቃቂ ድርጊት የመንግስት ኃይሎች ሙስሊም ወንድሞቻችንን ገለዋቸዋል የሚል ቅስቀሳ ነበረ ሲቀሰቅስ የነበረው መፍትሄ አፈላላጊ ነን ከሚሉት ኮሚቴዎች አንዱ መሆኑን አውቃለሁ
- ምንድን ነው መፍትሄ አፈላላጊ የሚባል ኮሚቴ አለ?
- አወልያ ግቢ ውስጥ 17 ሆነው የተመረጡ አሉ ከነዛ ውስጥ አንዱ ነው
- ጥሩ እሺ ?
- ስለዚህ ያው በዛ ንግግር ላይ አንዳንድ ተረት አዘል ነገሮችም የተናገራቸው ነገሮች አሉ
- ለምሳሌ?
- ለምሳሌ ስለአይጥ እና ድመት ነበር የገለፀው አይጦችን በጣም እየበላባቸው አንድ ድመት አለ እና ይሄ ከዚህ ድመት ለመዳን ሲሉ ውይይት አደረጉ አይጦች ተሰባስበው እና አሁን ከዚህ ድመት እንዴት ነው መዳን የምንችለው መትረፍ የምንችለው ተባብለው ሲነጋገሩ አንደኛው ብልህ አይጥ አንገቱ ላይ ደውል በማሰር ከሱ ልንተርፍ እንችላለን የሚል ሃሳብ ሰጠ እና ሃሳቡን በማድነቅ ሁሉም በመስማማት ሃሳቡን ተቀብለው አፀደቁት ነገር ግን ይሄንን ደውል የሚያስረው ማን ነው ሲባል ሁሉም እርስ በእርስ ነው የተያዩት ነገር ግን ኢሽ አላህ እኛ ይሄን ደውል ለማሰር ዝግጁ ነን የሚል አስተያየት በመደምደም የተናገረበት ሁኔታ አለ
- እኛ የሚለው ማንን ነው?
- እንግዲህ ኮሚቴዎቹን ይሆናላ እራሱን ጨምሮ
- ጥሩ እሺ ሌላስ ?
- ያው ይሄንን ንግግር ያደረገው አራት ሰዓት ተኩል አካባቢ ነው ግን ፕሮግራሙ ቀጥሎ ነበረ ፕሮግራሙ ሲቀጥል ከዛረም በኋላ እረጅም ሰዓት እስከ አስር ሰዓት ድረስ አንዋር መስኪድ ውስጥ ነበር በዚህ ፕሮግራም ላይ መሃመድ አባተ እንደመድረክ መሪ ነበረ

1696 110

http://ethcriminalawnetwork.com/

ፕሮግራሙን አድማቂ በድሩ ሁሴንም ከሙስሊም መጅሊሶች ጋር በተያያዙ እማይመስሉ ነገሮች ለረጅም አመታት እኛ በቁፋር በሆኑ መጅሊሶች እየተመራን ነው የሚል ታሪካዊ

- ምን ማለት ነው?
- ለምሳሌ በ19
- ቁፋር ምን ማለት ነው?
- ያው ሙስሊም ያልሆነ ማለት ነው እና በነሱ እየተመራን እንደውም አንዱ በ19 ስድሳዎቹ ውስጥ የነበረ የመጅሊስ አመራር መጅሊስ ለ3 ዓመት ከመራ በኋላ ሲሞት በቤተክርስትያን ነው ሄዶ የተቀበረው ስለዚህ ሁል ጊዜ የእኛ መጅሊሶቻችን ሙስሊም ሳይሆን ከሙስሊም ውጪ ነው የሚመራው የሚል ዓይነት ቅስቀሳዎች አሁንም እንደዚህ አይነት ድርጊቶች እየተደረገብን ነው የሚል አይነት ሃሳቦች ሲሰጥ ነበር
- ማን ነው ይሄንን የሚለው?
- በድሩ ሁሴን
- እሺ
- አቡበክር አህመድም እዛው ፕሮግራሙ ላይ ነበረ የሰጣችሁንን አደራ እስከ መጨረሻው እንጠይቃለን መንግስት የሚያደርጋቸውን በደሎች እስከ መጨረሻው ጠይቀን መልስ እናገኛለን እርግጠኛ ነን መንግስት ተገዶም ቢሆን ይሄንን ያደርግልናል የሚል ሃሳብ አቡበክር አህመድም እዛው ፕሮግራሙ ላይ ስለነበረ ያቀርብ ነበር ኑሩ ቱርኪ ግቢ ውስጥ የነበሩት ሙስሊሙን ሕብረተሰብ ዳቦ የማከፋፈል ስራዎች ዳቦ እየገዙ ዳቦ የማከፋፈል ስራ ሲሰራ አይቼዋለሁ
- አሁን ስትገልጽ አቡበክር አህመድ መንግስት ተገዶም ቢሆን የምንለውን ያደርጋል ብሏል ብለሃል እንዴት ነው ተገዶ ማለት ምን ማለት ነው?
- የጠየቅነውን መልስ ያው የሚጠየቁ ጥያቄዎች መጀመሪያ ያው ከመጅሊስ ምርጫ ጋር ነበረ የዛ ሰዓት ላይ ግን እስፔሻሊ መንግስት ተገዶ ምርጫችንን እኛ በምናዘው መሰረት ይመልስልናል የሚል ሃሳብ ነበር ሲያቀርብ የነበረው
- ባያደርግስ መንግስት ምን እንሁን ነው?

1697

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንግዲህ ቅድም እንዳልኩት የሃሰት ፕሮፓጋንዳዎች እየተነፉ ነው ስለዚህ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ እዛ አካባቢ ላይ የነበሩት ስሜታዊ ነበሩ በጣም ተክቢር የሚባል ነበር ተደጋጋሚ
- ምን ማለት ነው?
- አላህዋክበር ይባል ነበር እንዳልኩህ ቅድም በአራት ሰዓት ተኩል ላይ የተሰጠውም ቃል ከዝሁር በኋላ ሰላት የሰባት ሰዓት ሰላት ከተሰገደም በኋላ ከከሰዓት በኋላ ግን የማስተባበያ ቃላቶች መሰጠት ነው የተጀመሩት ለምሳሌ ሰላት ኤልጀናዛ እንሰግድላችኋለን ተብሎ ነበረ አልተሰገደም
- ለነማን ?
- ለሚቾቹ ሰላት እልጀናዛ ከዝሁር በኋላ እንሰግድላቸዋለን ብሎ ነበረ ያሲን ኑሩ ዝሁሩ ከተሰገደ በኋላ በተባው ቃል መሰረት የሞተ ሰው አለ ለሞቱት ሰወች ሰላት ይሰገዳል ማለት ነው ሰላት ኤልጀናዛ ማለት ለሙታን የሚሰገድ ሰላት ነው ስለዚህ ከዛ በኋላ ከከሰዓት በኋላ ግን በነበሩት ፕሮግራሞች ትላንትና ማታ መንግስት ባደረገው አሰቃቂ እርምጃ ወንድሞቻችን ቆስለዋል ተደብድበዋል ሞተዋል ይባላል ነገር ግን ማረጋገጫ የለንም የሚል ማስተባበያ ቃላቶች ደግሞ ከከሰዓት ተጀመረ
- እሺ ቅድም ስትገልጽ መሃመድ አባተ መድረክ ይመራ ነበረ ብለሃል የሚናገረው ነገር ነበረ በወቅቱ መሃመድ አባተ ?
- አሁን የገለጽኩልህ ማለት ነው
- ምን ይል ነበር?
- ያው ወንድሞቻችን ተደብድበዋል ቆስለዋል ሞተዋል ይባላል ነገር ግን እስከ አሁን ማረጋገጫ አልደረሰንም የሚል ቅስቀሳዎች ይሄ ተቃውሚችን ይቀጥላል መንግስት የጠየቀውን ጥያቄ መልስ እስካልሰጠ ድረስ ተቃውሚችን እስክ ሕይወት ፍፃሜያችን ይቀጥላል የሚል እንደዚህ አይነት መፈክር አዘል
- እንዴት ነው የሕይወት ፍፃሜ ማለት?
- እስከሚሞቱ ድረስ እንታገላለን ነው
- እሺ አቶ ተማም ከሰዓት ማስተባበያ የሚመስል ነገር ተናገሩ ብለሃል በምን መነሻ ነው ይሄ ማስተባበያ የመጣው?

1698 112

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያው አራት ሰዓት ላይ እንዳልኩህ ሰላት ኤልጀናዛ ይሰገዳል ተብሎ በጣም ሙስሊም በጣም በዛ ሰዓት ላይ የነበረው ሰው በጣም ስሜታዊ ሆኖ አጠቃላይ ማለት ይቻላል ሲያለቅስ ነበር ወንድሞቻችን ሞተዋል ሲባል ማለት ነው ያ ደግሞ መጥፎ ስሜቱ ውስጥ የሚክት አይነት አለቃቀስ ነበር ለመንግስት እልህ የሚያይዝ ነገር ግን ከሰዓት ያ እውነት ከነበረ ሰላት ኤልጀናዛ ነው ቀጥታ የሚሰገደው ነገር ግን ያ ሳይደረግ የሞተ ሰው የለማ በማውቀው ምንም የሞተ ሰው የለም
- ስለዚህ ለቅስቀሳ
- ስለዚህ እነሱም የሞተ ሰው እንደሌለ ስለሚያውቁ ከከሰዓት ማስተባበያው ቃላት መሰጠት ተጀመረ ምክንያቱም ሰው ሰላት ኤልጀናዛውንም ይጠብቅ ነበር
- እሱን ይጠብቅ ስለነበረ ነው?
- አዎ
- ጨርሳችኋል እሺ መስቀለኛ ጥያቄ የተከሳሾች ጠበቃ
- አቶ ተማም ቅድም ሲመሰክሩ ተከሳሾች ንግግር እንዳረጉ ገልፀዋል እርስዎ ፕሮግራሙ ሲጀመር ጀምሮ ነበሩ እንዴ ፕሮግራሙ ስንት ሰዓት ነበር የተጀመረው?
- ፕሮግራሙ ሲጀመር አልነበርኩም ነግር ግን ከሦስት ሰዓት ጀምሮ እኔ እዛ ግቢ ውስጥ ደርሼ ስከታተል ነበር
- ጥሩ ግቢ ውስጥ ሲደርሱ ሁኔታው ምን ይመስል ነበር?
- ግቢ ውስጥ ስደርስ ያው ግቢ ውስጥ የተወሰኑ ሙስሊም ህብረተሰብ ነበር
- ማለት ጥቂት ነበር የተወሰነ ሲሉ ?
- አዎ
- እርስዎ የትጋ ሆነው ነበረ የሚያዳምጧቸው ?
- መጀመሪያ ግቢ ውስጥ ነበርኩ
- አሁን ተከሳሽ ያሲን ኑሩ ሲናገር እርስዎ ግቢ ውስጥ ነበሩ?
- አዎ
- ስለዚህ ድምፁን ነው የሰሙት ማለት ነው እሱ የት ሆኖ ነበረ የሚናገረው?
- እሱ የአንዋር መስኪድ ዋና መግቢያ ደረጃ ላይ ሆኖ ነው
- አሃ ግቢ ውስጥ ማለት ነው?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ግቢ ውስጥ በሰዓቱ ማብራት ጠፍቶ ነበር ስለዚህ ይቺ ትንሿ ማይክ የለችም በሷ ነበረ ሲነጋገር የነበረው
- አሃ ስለዚህ ሲናገርም በአካልም እያዩት ነው የተናገረው?
- አዎ
- ምን ቆሞ ነበረ ወይስ ቁጭ ብሎ ነበር?
- ቆሞ
- አለባበሱን ያስታውሳሉ?
- አስታውሳለሁ
- ምን ነበረ የለበሰው?
- ሱፍ
- ምን አይነት ?
- ውሃ ሰማያዊ ነገር ከለሩ ወደዛ የተጠጋ
- እነዚህን ቃላት ተናግሮ ነው የተቀመጠው አሁን የጠቀስካቸውን ሲናገር የሰማኸውን እነዛን ብቻ ተናግሮ ነው የተቀመጠው?
- ያው አንዳንድ ለምሳሌ እስላማዊ ቃላቶች ሃሰቦ መሆን የአላህ ወኪል የሚል አላህዋክብር የሚል ተክቢሮች ሲያስብል ነበር
- አሃ ምን ማለት ነው ይሄ ቅድም ያሉን አስቡን አላህ ያሉት ምን ማለት ነው?
- ያው በአላህ ነው የምንተማመነው ነው
- ሌላስ ሕዝቡ እንዲረጋጋ የተናገረው ምንም ነገር የለም?
- ምንም የለም
- ምክንያቱም እርስዎ አሁን ከመሰከሩት ውጪ ሌሎች ቃላትንም እንደተነጋገረ ነው የሚያውቁት ስለዚህ የሚያውቁትን ሁሉ እንዲነግሩ ደግሞ ይጠበቃል እና እስቲ አሰብ አድርገው ሌሎች ነገሮችስ እነዚህን ብቻ ተናግሮ ቁጭ አለ?
- እነዚህን ነው አሁን ያልኩትን ቃላቶች ነው ከዚህ ውጪ ሲያረጋጋ የሚችል ቃላቶች አልተናገረም
- ያሲንን ከዛ በፊት ያውቁታል እንዴ?
- በሲዲ አስተምሮቶቹን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ያሲን በአወልያ ከተመረጡት አስራሰባቱ አንዱ እንደሆነ አውቃለሁ ብለዋል በምን አወቁ ይሄን ?
- ከዛ ቀደም ብሎ መንግስት ሲያነጋግራቸው በሚዲያም ስላየሁ በሚዲያ አይቻለሁ ሰምቻለሁ በራዲዮ መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ ነን
- አሃ ሚዲያ ሲሉ በቴሌቪዥን ማለቶ ነው ?
- አዎ በቴሌቪዥን እና በራዲዮን ምስላቸውን የአስራሰባቱንም አይተዋል ?
- የአስራ ሰባቱንም አላየሁም
- ማን ማንን አይተዋል?
- ለምሳሌ ያሲን ኑሩ ፣ አቡበክር አህመድ ከዛ ፣አህመዲን ጀበል ፣ በድሩ ሁሴን ፣ ካሚል መከተ ይበቃል ለጊዜው
- ጥሩ ቅድም አይጦች እና የድመት ተረት ተናገረ ብለዋል እና በመጨረሻ ይሄን ደውል የምናስረው እኛ ነን ምን ማለት ነው ይሄን እርስዎ እንዴት ተረዱት የድመቱን የአይጡን ተረት ሁሉንም ተከታትለዋል አደል?
- አዎ
- እሱ ስለድመቶች ነው ወይስ ስለ አይጦች ሆኖ ነው እናስራለን ይል ነበረው?
- እሱ ስለ አይጣቹ ሆኖ ነው
- ምንድን ነው እስቲ ከዚህ ንግግር ምን ማለት ነው አሁን ድመት እና አይጥ ተነግሯል ያሲን ኑሩ ስለ አይጦች ሆኖ ነው እና ምን ማለት ነው እንዴት ተረዱት እርስዎ ?
- ግልጽ ነው ምናልባት አንተ ስላልተረዳኸው ለአንተ ልንገርህ አይጥ ማለት እነሱ ናቸው ለብዙሃኑ የሚያስብ የሚመስሉ የነሱ ሰለባዎች ለሆኑ ጥቂቶቹ ማለት ነው የአይጦቹ ደፋር ደግሞ እኛ ነን እያለ ነው መሪ ነው እሱ ድመት ደግሞ እያለ ያለው በሰላም አገር ውስጥ ሰውን የሚበላ እያጠፋ ያለ አይጦችን የሚጨርስ እያለ ነውያለው ስለዚህ ድመቱ ማን እንደሆነ አይጡም ማን እንደሆነ ደፋሩ አይጥ ማን እንደሆነ ግልጽ ይመስለኛል
- ጥሩ ሰው ምንድን ነው አልሳቀም እንዴ እንደዚህ ሲል?
- ስሜቱ ውስጥ ያለ ሰው በዛ ሰዓት ላይ
- ቆይ እስቲ ምንድን ነው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማለት አሁን ያው ቀጥታ አሁን በዛ ወቅት የተደረገውን ንግግር ነው የተናገሩት ምስክሩ አሁን ከዚህ በኋላ የምስክሩን አሁን ትንታነውን ሰው ስቋል ወይ ምንድን ለማለት ነው የተፈለገው ምናምን የሚባለው አሁን የእሳቸውን አረዳድ ነው አሁን እየተጠየቁ ያሉት አሉ የተባሉትም ኮት አርገው ተናግረዋል ይሄንን ፍ/ቤቱም የሚረዳው እዛ ያለ ሰው በተረዳው መጠን ነው የሚረዳው ስለዚህ ሰው ስቋል ወይ ምን ለማለት የተፈለገ ነው አይጡ ማን ነው ድመቱ ማን ነው የሚለው ከዚህ በላይ የተፈለገው ፍ/ቤት ሃራስመንት ነው የሚሆነው
- ምንድን ነው ምስክሩ እዛ ከነበሩት ሰወች ከሦስት ሰዓት ጀምሮ እስከ አስር ሰዓት የነበረ ነው ቃሉ ተነግሯል ቃሉ ደግሞ ለምን እንደተነገረም ተገልጿል ስለዚህ የሕዝቡ ስሜት ምን እንደነበረ እዛው ከተመለከቱት ነገር ነው የጠየቅናቸው ስለዚህ እሳቸውም ከሕዝቡ ከዛ ከነበሩት አንዱ ስለሆኑ በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ደግሞ መመስከር የዚሁ የመስቀለኛ ጥያቄ አካል ነው ስለዚህ በአግባቡ ነው የቀረበው እኛ የግላቸውን የጠየቅነው ቅድም ሲናገሩ ተረቱን ከነእንትኑ ገልፀው ስለነበረ እሱን ለማብራራት ነው ቀጥሎ ያለው ግን በቦታው አለሁ ስላሉ ምስክሩ መኖር አለመኖራቸዉን ጭምር ለመጠየቅ ስለሆነ በአግባቡ ነውና መቃወሚያው ውድቅ እንዲደረግ እና ጥያቄውን እንድንቀጥል ይፈቀድልኝ
- ብይን ሰጥተናል እንግዲህ የግራ ቀኞችሁ ክርክር አንደግመውም ያው ይታወቃል ፍ/ቤቱ የተመለከተው ጥያቄው ተገቢ ነው ተገቢ አደለም የሚል ነው ስለዚህ ጥያቄው በመሰረተ ሃሳብ ስህተት የለውም ምልባት አጠያየቁ ሕዝቡ ይስቅ ነበር አይስቅም ነበር የሚል ነገር ነው ስለዚህ ምንድን ነው ፍ/ቤቱ የወሰደው እነሱ ሰወቹ ከተናገሩ በኋላ የሕዝቡ ምላሽ ምን ነበር ወደሚል መደምደሚያ ስለሆነ በዚህ መንገድ ጥያቄያችሁን ቀጥሉ
- ጥሩ አቶ ተማም ያሲን ኑሩ ይሄንን ተረት ከተናገረ በኋላ የሕዝቡ ስሜት ምን ይመስል ነበር?
- በተክቢር ነው የተቀበሉት
- ተክቢር ማለት ምን ምንደን ነው ትርጉሙ?
- አላህዋክብር ማለት ነው
- ቅድም መንግስት ተገዶም ቢሆን መልስ ይሰጠናል ብለዋል አቡበክር ይሄን ተናግሯል ብለው ለፍ/ቤት ተናግረዋል ማለት ቅድም ሲመሰክሩ እንደዚህ ብለዋል ትክክል ነኝ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- እንዴት ተገዶ እንደሚሆን ግን አልገለፀም አደል መንግስት ተገዶም ቢሆን መልስ ይሰጠናል ነው እንጂ ዝርዝሩን አላብራሩም አደል?
- አስረግጠው ተገድለዋል ነው ያሉት ተገድለዋል ከማለት አልፎም ሰላት እልጀናዛ እንሰግድላቸዋለን መሞት አረጋግጦ ነው ይሄንን የሚናገረው
- ቅድም አቡበክር ተናገረ ብለው ሲገልፁልን መልስ እናገኛለን መንግስት ተገዶም ቢሆን መልስ ይሰጠናል ብሎ ሲናገር ሰምቼዋለሁ ብለዋል ይሄንን አላሉም ?
- ብሏል ጥያቄውን ጠይቁት ችግር የለውም
- እርስዎ አቡበክር የት ሆኖ ነበረ ይሄንን የሚናገረው?
- አቡበክር ውስጥ
- የት ውስጥ ማለት ነው?
- ከሰዓት በኋላ ነው ውስጥ ማለት መስኪድ ውስጥ
- እርስዎ የት ነበሩ በዛኔ ?
- እኔ በዛ ሰዓት ግቢ ውስጥ ነበርኩ
- አሃ ድምፁን ነበር የሚሰሙት ማለት ነው?
- አውቀዋለኋ
- ድምፁን ነበረ የሚሰሙት?
- ድምፁን በአስተምሮቱ ሙስሊም ስለሆንኩኝ አስተምሮቶቹንም ስለምሰማ አውቀዋለሁ ድምጹን
- ጥሩ አቡበክር እንዴት ነበረ የጀመረው ሲጀምር ?
- ቅድም ገለጽኩት መሰለኝ
- የለም መስቀለኛ ጥያቄ ላይ ስለሆኑ መመለስ አለቦት
- ይኸውሎት አሁን ጠበቃ ምስክሩ የሚችሉ ከሆነ መመለስ ነው የማያስታውሱት ከሆነ አላስተውስም ማለት ነው ጠበቃም ጥያቄውን ለይታችሁ አቅርቡ ምክንያቱም አጀማመሩ ምን ነበር የተባለው ነገር አለ ተነስታችሁ መርታችሁም ቢሆን ያልተባለ ከሆነ ያልተባለ መሆኑን መርታሁ እንትን ማለት ትችላላችሁ አሁን ጠቅላላ ከሆነ ዋና ጥያቄ ይሆንና እንደገና እረኸም ዝርዝር ነው የሚሆነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ድምፁን ስለማውቀው ነው በሱ ነው የለየሁት ብለዋል የድምጽ መመሳሰል አይኖርም እንዴ?
- ምክንያቱም አቡበክር አህመድ ቅድም እንዳልኩህ መድረክ አስተዋዋቂ መድረክ መሪ መሃመድ አባተ አለ ስለዚህ አሁን ቀጥሎ የሚናገሩት የኮሚቴዎቹ ሊቀመንበር አቡበክር አህመድ ብሎ ነው ያስተዋወቀው
- ጥሩ በለቱ ጠዋት እርስዎ ከተገኙበት እስከ አስር ሰዓት ድረስ አስተዋዋቂው መሃመድ አባተ ነበረ አደል?
- አዎ
- እሺ ምስክር ቅድም ሲመሰክሩ መሃመድ አባተ ደረጃው ላይ ሆኖ መድረክ እየመራ ነበር ብለዋል የትኛው ደረጃ ላይ ነው የነበረው ?
- እንዳልኩት ጠዋት ላይ ነው ደረጃው ላይ የነበሩት ምክንያቱም መብራት ጠፍቶ ነበር
- የትኛው ደረጃ ላይ?
- የአንዋር መስኪድ ዋናው ደረጃ መግቢው የዋናው መስኪድ መግቢያ
- እሱ ሙሉውን ጠዋት ነው መድረክ ሲመራ የነበረው?
- አዎ
- እሱ እያስተዋወቃቸው ነው ሌሎች ንግግር ሲያደርጉ የነበረው?
- ከዛ በኋላ ፕሮግራም እስፔሻሊ ከዝሁር በኋላ በተገቢው እሱ መድረኩን እየመራ ነበር ጠዋት ላይም ግን ነበረ
- እኮ አሁን ግልጽ እንድታደርግልን የምንጠይቅህ እዛው ደረጃው ላይ ሆኖ እሱ እያስተዋወቀ እየጋበዛቸው ነበር ንግግር ላይ ሲያደርግ የነበረው ሌሎቹ ንግግር ሲያደርጉ የነበረው?
- አንዳልኩህ መብራት ጠፍቶ ስለነበረ እየተቀባበሉ ነበረ የሚነጋገሩት
- እኮ እዛው
- እኮ ስማኝ
- እሺ
- እዛው ውጪ ላይ በነበረበት ሰዓት ትንሽዬ ማይክ ነች እየተቀባበሉ ሲነጋገሩ የነበረው ያሲን ኑሩ የተናገረውን ነግሬሃለው ከዛ በኋላ ግን በተለይ መብራቱ ከመጣ በኋላ ወደ ውስጥ ገቡ ዝሁር ሳይሰገድ ዝሁር ሃዛን ሳይል ማለት ነው

1704 118

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ ስለዚህ ወደ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ሁሉም እዛው ሆነው
- ሁሉም እዛው አልነበሩም
- ማን ማን ነበረ?
- በዛ ሰዓት ላይ የነበሩት ከኮሚቴዎቹ ያሲን ኑሩ ብቻ ነው
- ያሲን ኑሩ ቅድም ተናገረ ያልከውን እዛ ሆኖ ነው የተናገረው ?
- አዎ
- ሲናገር የነበረው በምንድን ነው ?
- ቅደም ገልጨዋለሁ
- እኮ በምንድን ነው በትንሿ ማይክ ነው ሲናገር የነበረው?
- ገልጨዋለሁ እሱን
- እስቲ እሱ ምንድን ነው ግለፀው ደግመህ እነሱ እረስተውትም ሊሆን ይችላል የገለጽከውን ነገር ስለዚህ አስታውሳቸው
- ትንሿ ማይክ ነች ብያለሁ ይቺ በእጅ የምትንጠለጠለው
- መብራት የሄደለው ከሰዓት ነው ጠዋት ነው?
- ጠዋት
- መብራት ስለሄደ ነው ደረጃውጋ የመጡት?
- አዎ
- ከዛ በፊት የት ነበሩ?
- ከዛ በፊት ውስጥ ነበሩ
- አንተ ውጪ ሆነህ ይሄን ሁሉ ትከታተል ነበር?
- ውስጥ ሆኜ እየተከታተልኩ ሰዓት ነበር በተለይ ዝሁር ልሰግድ ገብቼ ነገር ግን ብዙም ሳልቆይ ወጥቻለሁ እዛ አካባቢ ላይ የነበሩትን ሰወች አይቻለሁ ከዚህ በተረፈ ግን መብራት ጠፍቶ ውጪ ሲወጡ ውጪ ነበርኩኝ ብያለሁ ሦስት ሰዓት አካባቢ ነው እኔ እዛ ግቢ የደረስኩት ስለዚህ ለሁሉም ሰው የሚታይ ግልጽ ቦታ ላይ ስለነበረ ፊት ለፊቱ አይቻቸዋለሁ
- እሺ በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥም ውጪም እየገባህ እየወጣህ ነበር የምታየው አንተ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማብራቱ ከመጣ በኋላ እነሱም ሲገቡ ሰዓቱ ወደ ዝሁር እየደረሰም ስለሆነ እኔም ለመስገድ አብሬ መስኪዱ ውስጥ ገብቻለሁ
- ከዛ በፊት ውጭ ነበርክ?
- ውጭ ነበርኩ ፕሮግራሙ ውጪ ነበር
- ስለዚህ አሁን ጠዋት ከመውጣታቸው በፊት የነበረውን ፕሮግራም ውስጥ ሳይሆን ውጪ ሆነህ ነው የተከታተልከው ?
- ድገመው እስቲ
- ሃሳቡ ግልጽ ነው የተነገረው ነገር ግልጽ ነው አሁን የእሳቸውን ክሬዲቴቢሊቲ ከሆነ ኩዊስጅን እያረጉ ያሉት ጠበቃው ቦታውን እዚህ አደለም ወይ ሁኔታዎቹን በግልጽ እየተናገሩ እንትን ይበሉ አሁን ግን ዝም ብሎ ማምታታት ሆነ ውስጥ ነው ውጪ ነው መብራት ጠፋ ከመጣ በኋላ ነው ገባህ ወጣህ የሚባል ሳይሆነ በፍሬ ነገር ኩዊስጅን ያርጓቸው ማለት ክሬዲቴቢሊቴያቸውን የእሳቸውን መፈተን ከሆነ የተፈለገው ይጠይቋቸው ቦታውን እሳቸው የሚያውቁት ከሆነ ከዛ ውጪ ግን ውስጥ ውጪ ማይክ ጠፋ መብራት ጠፋ ምናምን ቢባል አሁን ምን ሴንስ ሆነ ማለት አሁን እኛ መረዳት አልቻልንም በመስቀለኛ ጥያቄ መልክ ጥያቄው ቢጠየቅ ነው ተገቢ የሚሆነው
- ምላሽ ስጡበት
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የቃል አጠቃቀማችን ላይ የተከበረው ፍ/ቤት ከዚህ በፊት የነገረን እሱ አሁንም አቃቤ ሕግ ያንን እንዲያከብሩ ነው እማሳስበው ፍ/ቤቱም ይሄንን ይንገርልን ሲጀመር ነን ሴንስ የሚባል መስቀለኛ ጥያቄ ላይ የለም እኛ ይጠቅመናል ብለን እስከጠየቅን ድረስ አቃቤ ሕግ ነን ሴንስ የሚሉበት ምክንያት አይኖራቸውም አገላለፃቸውም ትክክል አደለም ከዛ ውጪ እኛ አሁን ለምስክሩ እረፍት ይውሰድ ብለው ጣልቃ እየገቡ ካልሆነ በስተቀር አቃቤ ሕግ 1ኛ የተቃወሙት ነገር ግልጽ አደለም ምንን እንደተቃወሙ እራሱ በግልጽ አላስረዱም 2ኛ የሚቃወሙበትም ነጠብ እራሱ የለም እና የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄያችንን እንድንቀጥል ይፍቀድልን ጥያቄያችን ይመልሰው
- የተቃወሙበት ምንድን ነው 1ኛ ጥያቄያቸው ግልጽ አልሆነልንም ለእኛ ለመቃወሙም ምን ለማለትም ጥያቄው ግልጽ አደለም ምስክሩ ላይ ድግግሞሽ አለ አይነት ነገር ነው

1200 120

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ ጥያቄችሁን ግልጽ አርጉ ካሉን ግልጽ እናረጋለን የተከበረው ፍ/ቤት አሁንም ጥያቄያችንን ግልጽ እናረጋለን ለምስክሩ ግን ነን ሴንስ ነው የሚጠየቀው በሚል ጥያቄ ማደናቀፍ ተገቢ አደለም እያሉ ነው
- እሺ ብይን ሰጥተናል የተነሳውን አዳምጠናል በመጀመሪያ ደረጃ አቃቤ ሕግ ምናልባት የቃሉ አጠቃቀም ካልሆነ በስተቀር ነን ሴንስ የሚለው ክርክርን የሚያሻክር ነው ስለዚህ እንዲህ አይነት ንግግሮችን ባለፈውም በተደጋጋሚ ነግረናል ስለዚህ ወደፊትም እንዲህ አይነት ተቃራኒ ወገንን አፕሴት የሚያደርግ ነግግሮች አስተካክሉ በሌላ መንገድ ጠበቃ አሁን የታዘብነው ነግር ከጥያቄውም በጣም ድግግሞሽ አለ እሱን አሁን ለምሳሌ የት ነበርክ ውስጥ ነበርክ ምናምን የሚለው እሳቸው በደምብ ጠይቀዋል የት ላይ ነበርክ እንዴት ነበርክ ብለው ጠይቀውታል ስለዚህ እሱን መድገም ተገቢ አደለም ስለዚህ እሱን ጥያቄ በጥያቄ መልክ ግልጽ አድርጋችሁ ግልጽ እናረጋለን ያላችሁ ስለሆነ በሱ መሰረት ቀጥሉ
- ከጠዋቱ ፕሮግራም ላይ ውስጥ ነበርኩ ነው ያሉት በጠዋቱ ፕሮግራም ላይ መስኪድ ውስጥ ነበሩ?
- ውስጥ ላይ ነበሩ ውስጥ ላይ ነበርኩ ብለው ገልፀዋል ይሄንን
- ስንት ሰዓት ነው መብራት የሄደው ?
- መብራት ስንት ሰዓት እንደሄደ ለጊዜው አላውቅም ነገር ግን እኔ ግቢው ውስጥ ሦስት ሰዓት ስገባ ፕሮግራማቸውን ጀምረዋል ስለዚህ ከነበሩት ሰወች ስጠይቅ ውጪ ለምንድን ነው ስል መብራት ስለጠፋ እዚህ ላይ እያካሄዱ ነው
- ቅድም አራት ሰዓት ተኩል ገባሁ ብለው ነበር ቀየሩት አሁን?
- አልቀየርኩትም ሦስት ሰዓት ነው የገባሁት ነው ያልኩት ምናልባት ለአንተ አራት ሰዓት ተኩል ሰምተህ ከሆነ በደምብ አጣርተህ ስማ
- ሦስት ሰዓት ተኩል ምን ሊሰሩ ገቡ ወደ መስኪድ?
- እንግዲህ ቅድም እንዳልከው የኔ እዛው አካባቢ ነኝ ብዙም አልርቅም ስለዚህ አንዋር መስኪድ እንደዚህ አይነት ፕሮግራም የአመጽ ፕሮግራም እያዘጋጁ ነው ሲባል ለማየት ሄድኩኝ
- እሺ ቅድም ሲመሰክሩ እሚያለቅሱ እና ስሜታዊ ሰወች ነበሩ ብለዋል እና የዱአ ፕሮግራም ወይም የፀሎት ፕሮግራምስ አልነበር?

121

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የዱአ ፕሮግራም በምርቃት ጀምርህ በምርቃት እምትጨርሰው ነው ቅድም ግን እያልኩ ያለሁት ለአመጽ የሚያነሳሳ ሰውን ወደ ኢሞሽኑ ውስጥ የሚከት ቃላቶች በተነገሩ ቁጥር ስማታዊ ሆኖ ሰው እያለቀሰ ነበር ይሄ ደግሞ ዱአ አደለእ አመጽ እንጂ ሰውን ማነሳሳት መቀስቀስ
- የተከበረው ፍ/ቤት እየተቸገርን ነው መስቀለኛ ጥያቄ ለመጠየቅ አዎ ወይም አደለም የሚል ነው እና ምስክሩ የሚሰጡት ማብራሪያ ወይም የሚገልፁት ሃሳባቸው ይበልጥ እኛ ሌላ ጥያቄ በምንጠይቅበት ጊዜ እየተቸገርን ነው እና ለጥያቄያችን አጭር መልስ እንዲሰጡን ወይ በፍ/ቤቱ ቢነገርልን የግል ሃሳባቸውን ነው እየተናገሩ ያሉት
- እንግዲህ ምንድን ነው መሪ ጥያቄ አጭር ከሆነ እንደተባለው አዎ ወይም አደለም ብሎ ማለፍ ይቻላል ነገር ግን ሁል ጊዜ ነው ማለት ብሎ ማለት አይቻልም ምስክሩ በገባው መጠን የጠየቃችሁትን ጥያቄ መልስ መመለስ እሱ አይከለከልም ዋናው ነገር ለፍ/ቤቱ የሚገነዘበው ነገር ይጠቅማል አይጠቅምም የሚለውን ነው እንጂ እናንተ እንዲህ አይነት ይጐዳናል ብላችሁ የምታስቡትን አስተካክላችሁ መጠየቅ ነው የሱ ምላሽ ምን ሊመልስ እንደሚችል
- ዱአ ወይም ፀሎት ነበረ ወይ ለሚለው አሁን ይሄ ሁሉ ማብራሪያ የምስክሩ ሃሳብ ነው እና አሁን እኛ ነፃ ሆኖ እየሰጡ ነው ወይ የሚለውን
- ቆይ እሱን ተውት እኛ ነን የምንመዝነው አሁን ነፃ ናቸው ነፃ አደሉም እየመዘነው ነው ያለው አጠቃላይ ይመዝናል ስለዚህ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም ሲመሰክሩ በአወልያ ምርጫ ተደርጐ ነው የተመረጡት ብለዋል እርስዎ ሰመረጡ ነበሩ?
- አልነበርኩም
- በምን አወቁ መመረጣቸውን?
- ቅድም ገልጨዋለሁ በሚዲያ የተመረጡ የተወከልን ኮሚቴዎች ነን የሙስሊሙን ጥያቄ እናድርስ የሚል
- መሃመድ አባተ ደረጃላይ ሆነው መድረክ ሲመሩ ነበረ ብለዋል ምን አይነት አለባበስ ነበረ የለበሱት ?
- እሱ ጥያቄ አልተጠየቀም ቀደም ብሎ ?
- የመሃመድ አባተ አልተጠየቀም የተከበረው ፍ/ቤት የያሲን ነው የቋጠየቀው

1708 / 22

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ
- ጅንስ ሱሪ ነው ወደ ብሉ ብላክ የሚወስድ ጅንስ ሱሪ እና የሆነ ጃኬት ነገር አድርጓል ከላይ ከፊቱ ላይ ግን ጥምጣም ጠምጥሟል
- እሺ ያሲን ኑሩ በሲዲ ኃይማኖታዊ ትምህርት ሲያስተምሩ አውቃቸዋለሁ ብለዋል ካዩት ውስጥ አንዱን ይነግሩናል ?
- የያሲን ኑሩን
- ይሄ ነገር ይጠቅማችኋል ?
- ይጠቅመናል በትክክል ያውቋቸዋል የሚለውን ለመለየት ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- ቢታለፍ ነው የሚሻለሁ
- እሺ ትተነዋል ያሲን ኑሩ በሲዲ የሚያውቁ ከሆነ ሌሎቹንስ በምንድን ነው በሲዲ ነው የሚያውቋቸው?
- አዎ
- ሁሉንም?
- አደለም አንዳንዶቹን በአካል አውቃቸዋለሁ
- ለምሳሌ በአካል ማንን ያውቃሉ?
- መሃመድ አባተን
- በሲዲስ ማንን ያውቃሉ?
- ኑሩ ቱርኪ አቡበክር አህመድን በሲዲ አውቃለሁ
- ኑሩ ቱርኪን በሲዲ ያውቁታል?
- አይ በአካል አውቀዋለሁ
- አቡበክር አህመድ ቅድም ሲመሰክሩ ብዙ ጊዜ አስተምሮቱን ስለምከታተል አውቀዋለሁ ብለዋል አስተምሮት ያሉት የትኛውን አስተምሮት ነው?
- በሲዲ የሚለቁት እስላማዊ ትምህርቶች አላቸው
- ኃይማኖታዊ ትምህርት ማለት ነው?
- አዎ
- አቶ ተማም ከሐምሌ 7 ቀን ከሦስት እስከ አስር ሰዓት እላ እንደነበሩ ገልፀዋል የአየሩ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን?
- የአየሩ ሁኔታ ዳመናማ ፀሐያማ ?
- ፀሐያማ ነበረ ከሰዓት አካባቢ የሆነች ትንሽዬ ካፊያ ዝናብ ዘንቧል
- ጥሩ አስር ሰዓት የተጠናቀቀበት ጊዜ ነው ?
- ሃስር ለመስገድ ሃዛን ሲባል እኔ ከዛ ወጣሁኝ
- አሃ ከመስኪድ ወጡ?
- አዎ
- ቅድም ያሲን ሲናገር በኃይማኖታችን መንግስት ጣልቃ ገብቷል በምን አግባብ ነበረ ገብቷል ብለው የገለፁት የገለፀበት መንገድ ካለ በዚህ መንገድ ብለው ይግለፁልኝ ከሌለ የለም ብለው?
- የገለፀበት አግባብ ልግለጽልሽ መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ መግባት ብቻ ሳይሆን የዋኘበት ነው ቃል በቃል ይሄንን ነው ያለው መንግስት ደግሞ በኃይማኖት ጣልቃ አይገባም ኃይማኖት በመንግስት ጣልቃ እንደማይገባ በሕገመንግስት ስለማውቅ ነው
- እሺ ቅድም የሞተ ሰው የለም ብለዋል ሰላት አልጀላና ስላልተሰገደ ነው የሞተ ሰው የለም ያሉት በዚህ ነው ያረጋገጡት?
- በነሱም ቃላቸው ማስተባበያ ብለዋል ብዬሻለሁ
- እኮ ስላልተሰገደ ነው እንጂ ሌላ ያወቁበት መንገድ አለ እንዴ?
- ማስተባበያቸው ነው
- በቃ በዚሁ ነው
- ሰላት አልጀናዛ አንድ አልተሰገደም
- እስኪ ጠበቃ ማለት የሞተ ሰው ካለ በግልጽ እከሌ አልሞተም ወይ ብለው ይጠይቁ ምናልባት ቅድም ገልፀዋል አሁን ማለት በግልጽ ነው የገለፁት
- የሞተ ሰው የለም ብለዋል ሰላት ስላልተሰገደ ነው ወይ የሞተ የለም ያሉት ነው የተለየ ማርጋገጫ አሎት ነው እኔ ጥያቄዬ
- ማስተባበያ ሰጥተዋል እያሉ ነው ቅድምም የገለፁት እሱ ላይ ተነሱና ግልጽ ይሁን መረጃ የለንም ብለው ያም ሳይደረግ ቀርቷል ነው ስለዚህ ተነሳሁ ያሉ
- እሺ ጥቂት ደጋፊ አላቸው ብለው ነበር ምን ያክል ያን ቀን የነበረው ሰው ብዛት ነበር ትንሽ ነበር?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቢያንስ ከሦስት መቶ እስከ አምስት መቶ የሚደርሱ
- ማን ነበር ማስተባበያውን የሰጠው ቅድም ማስተባበያ ተሰጥቷል ብለዋል ማስተባበያውን የሰጠው ማን ነበር?
- ማስተባበያውን የሰጡት ቅድም እንዳልኩሽ አንደኛ መሃመድ አባተ ነው 2ኛ እራሱ ያሲን ኑሩ
- እሺ ጨርሻለሁ
- ያው በተቻለ መጠን ሳይደገም
- ቅድም ሲመሰክሩ የሞተ አለመኖሩን አረጋግጫለሁ ብለዋል ትክክል ነኝ ?
- ጠበቃ ግልጽ ነው አሁን ይሄ
- እሺ የቆሰለ መኖሩን አረጋግጠዋል?
- የቆሰለ መኖሩንም የሰማሁት ከነሱ ነው እንጂ እኔ አላየሁም እነሱ ግን የቆሰለ ሰው
- ይበቃል
- እሺ ምስክር ያሲን ኑሩ ሙስሊሞች ተገደሉላችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ ሲል የተናገረው የሃሰት ንግግር ነው ብለዋል አደለም?
- አዎ
- ይሄን እንዴት ሊያውቁ ቻሉ እንዴት አወቁ?
- ይሄም ተመልሷል ይኸውሎት ተጠይቆ እኔ እራሳቸው ማስተባበያ ሲሰጡ ነው ምናልባት ቅድም እንዳልኩት መርታችሁ ወይ የሞተ ሰው ካለ ወይ እንዲህ አይነት ነገር ካለ ቀጥሉ
- ይሄንን ንግግር ያደረገው መስሎት እንዳልሆነ በወቅቱ በተናገረበት ጊዜ የሞተ ሰው ያለ መስሎት አለመሆኑን በምን አይነት ?
- እስቲ ጥያቄው ግልጽ አደለም ጥያቄው
- ሆነ ብሎ የሃሰት ንግግር ነው የተናገረው ስላሉ ሆነ ብሎ ሳይሆን መስሎት በወቅቱ የሞተ ሰው ያለ መስሎት እንዳልሆነ በምን አወቁ እሳቸው ያውቁ ነበረ ወይ በወቅቱ?
- ግልጽ አደለም ጥያቄው
- እሺ የሃሰት ንግግር ነው የተናገረው ብለዋል ሆነ ብሎ የተናገረው
- አሁን ምንድን ነው የተነጋገርነው ይሄ ጥያቄ በተደጋጋሚ ተጠይቋል ከዚህ በላይ መደጋገም ስለሚሆን ሌላ ጥያቄ ይጠይቁ ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ከሰዓት በኋላ ማስተባበያ ሲሰጥ ያሲን ኑሩ አብሮ ነበረ አደለም ?
- አዎ
- ስለዚህ ማስተባበያው የጋራ ሃሳባቸው ነው ማለትነው?
- አንግዲህ በግል ደረጃ እየተናገሩ ስለነበረ መድረኩ አካባቢ ሁለት ሰው ስለተናገረ እንደዛ ብለህ መውሰድ ትችላለህ እኔ ግን ነጥዬ እየነገርኩህ ነው ያለሁት
- ስለዚህ ጠዋት ያንን ተናገረ ከሰዓት በኋላ ደግሞ ማስተባበያ ሰጠ ይህ ማለት ጠዋት መስሎ
- ይህ ማለት የሚለው የእናንተን ኮንክሉዥን ተውት አሁን እሱ ይመልስላችሁ ጥያቄያችሁን መንጥራችሁ ጠይቁ የሱን መልስ ነው እኛ የምንፈልገው የጠበቃ ወይም የአቃቤ ሕግ መልስ እኛ አንፈልግም
- ጠዋት የተናገረው ማስተባበያ ተሰጥቶሃል ነው በጋራ አብረው የተገኙበት ማስተባበያ ሰጥቷል አደለም ?
- አሁን ነገርኩህ
- አቡበከር የሰጠንን አደራ እንወጣለን መንግስት ተገዶም ቢሆን ምርጫችንን ይቀበላል ያለው?
- ይሄንንም ቅድም ገልጨዋለሁ
- እሱም ተጠይቋል ጠበቃ
- እሺ ስለዚህ ተገዶም ቢሆን መብታችንን ያከብርልናል ማለታቸው ነው አደለም?
- ይሄ ቅድም በገለጽኩት አነጋገር መሰረት የራስህን ትርጉም መውሰድ ትችላለህ እኔ ግን ቃል በቃል የተናገርኩት
- መንግስት ተገዶ ይቀበላል ያሉት ምኑን ነው?
- እንግዲህ የነሱ የተለያየ ጥያቄዎች አላቸው ጥያቄዎቻቸው ሲያነሱት የነበሩት ጥያቄዎች አሉ
- የመብት ጥያቄዎች?
- ጥያቄ ተጠይቋል ነገር ግን ምን አርገን እናስገድዳለን የምትለው ጠይቆ አልተመለሰም እሱን የምትጠይቅ ከሆነ ጠይቅ ይሄኛው ግን ተጠይቋል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ አቶ ተማም ቅድም መስኪድ ውስጥ ያለውን ማለት እዛ ግቢ ውስጥም መስኪድም ውስጥ ያለው ስም ገምቷል ከሦስት መቶ እስከ አምስት ይሄ ማለት ግቢው ሞልቶ ነበረ መስኪዱ ሞልቶ ነበረ ማለት ነው ምን ማለት ነው?
- ግምት እያስቀመጥኩልህ ያለሁት
- ቆይ ቆይ ግምት ያስቀመጠ ስለሆነ ለእኛ ብዙም ግልጽ ነው ምን መጠየቅ ፈልጋችሁ ነው?
- አይ ለፍ/ቤቱ ምን ማለት ነው አሁን መስኪዱ አለ የሚይዘው አቅም አለው በገላጭ መልኩ እሳቸው እዛው ስለነበሩ ይሄ ማለት መስኪዱ ክፍት ነበረ ቦታ አለው ሰው ነበረው አልነበረውም የሚለውን ከሦስት እስከ አምስት መቶ የመስኪዱ ካፓሲቲ ነው አደለም የሚለውን ፍ/ቤቱ ስለማያውቀው ቀደም ሲል የተሰጠ ምስክርነት ስላለ ከዛጋር ጭምር እያነፃፀርን ነው ለዚህ ፍ/ቤት ተመሳሳይ
- የምታውቁት ከሆነ ይሄን ያህል ሰሰው እንዴት ይይዛል ብላችሁ ጠይቁት ቦታውን እናንተ የምታውቁት ከሆነ መጥበቡን ሰማችሁን መጥበቡ እና መስፋቱን የሚይዝ እና አለመያዙን የምታውቁት ከሆነ አናንተ ይሄ ጠባብ ነው ስለዚህ እንዴት ይሄን ያህል ሰው ሊይዝ ይችላል ብላችሁ እሱን ጠይቁት በቀጥታ
- ቦታውን የሚያውቅ ጠበቃ ካለ መግለጽ ይችላል
- በቃ ይበቃናል
- ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ አቃቤ ሕግ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ለቅድሙ ቃላት አጠቃቀም ይቅርታ እጠይቃለሁ ችሎቱን ኮንቴክስቹዋሊ ፖዘቲቭሊ ነው ነን ሴንስ ያልኩት ተደጋግሚል በሚል ማለት ነው በኃይል ተገዶ ምላሽ ይሰጠናል ያለውን በምንድን ነው የተረዳኸው አንተ?
- እንግዲህ ያው ቅስቀሳ ነው እየተካሄደ ያለው በሰላማዊ መንገድ ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ የሚሰጠን ምላሽ አጥጋቢ ባይሆን የምንፈልገው ጥያቄ እስኪመለስ ድረስ በዚህ አመጽ እንቀጥላለን እኔ የተረዳሁት ትርጉም ይሄ ነው
- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ምስክር እናመሰግናለን ጨርሰሃል
- በእውነት ለመመስከር
- በእግዚአብሔር ስም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምያለሁ
- እሺ ምስክር ለእናንተ ደህንነት ሲባል ስሞን ብቻ እና ሌሎቹን ሳይጠቅሱ ስሞን ብቻ ነው እንዲጠቅሱ ነው ፍ/ቤቱ የፈቀደው ስለዚህ ስሞን ማን ይባላል የመጀመሪያ ስሞ?
- አባተ
- ለምንድን ነው እዚህ የመጡት?
- ለምስክርነት
- እሺ በፍ/ቤቱ 19ኛ በአቃቤ ሕግ ክስ መሰረት 87ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሱ የአቃቤ ሕግ ምስክር ናቸው እሺ በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?
- በአካል ለይቼ የምመሰክርበት ሰው የለም አለ አጠቃላይ በተፈጠረው ያው በወቅቱ የተፈጠረውን ሁኔታ ለማስረዳት ነው
- ይሄንን ሊያስረዱ ነው?
- አዎ
- እሺ ካሉ በኋላ በአቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ
- እሺ አሁን እንደገለፁት በአጠቃላይ በወቅቱ ስለተፈጠረው ሁኔታ ብለዋል እና ይሄ ድርጊት መቼ እንደተፈፀመ ጊዜውን ሰዓቱን ቦታውን በማስታወስ አጠቃላይ ዛሬ ከመጡበት ምስክርነት ጋር በተያያዘ በዝርዝር እንዲገልፁ ነው የምጠይቀው እና መጀመሪያ ጊዜው መቼ ነበረ ወቅቱ ወሩ አመተምረቱ?
- ጊዜው 14/11/2004 ነው
- ትንሽ ድምጽ
- መቼ ነው ያሉት ጊዜው?
- ቀኑ ሐምሌ 14/1/2004 ዓ.ም ነው ከቀኑ ስምንት ሰዓት
- ቦታው የት ነበር?
- አንዋር መስኪድ
- እሺ በዚህ እለት ምንድን ነው እርስዎ ያዩት ምን አዩ ምን ይሰሩ ነበር ምን አዩ?
- በሰዓቱ እኔ ቢሮ ስራ ላይ ነበርኩኝ እና መስኪድ ላይ ችግር እረብሻ እየተነሳ ነው ከቢሮ ውጡ ተባልን ከዛ ብዙ አባሎች ሆነን ወደ መስኪድ ሄድን ከዛ እዛ መስኪድ ስንደርስ የተወሰኑ ሰወች ያው ወደ ውጭ ሰው እንዳይገባ አጥረው ከውስጥ ጩኸት ነበረ ከዛ ጩኸቱ እየባሰ እየተባሰ መጣ ከዛ አላህዋክበር አላህዋክበር እየተባለ ከውስጥ የሊስትሮ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

እቃ ዲንጋይ ምናምን መወርወር ተጀመረ ከዛ እኛም ትንሽ ወደ ኋላ እያፈገፈግን ኃይሉ እንትን ሲል ከዛ በኋላ ላይ ያው ፌደራልም መጣ የአዲስ አበባ ፖሊስ ቋሚ እና ተወርዋሪ ኃይሎችም መጡ ልክ ኃይል እየበዛ ሲመጣ የመበታተን ሁኔታዎች ተፈጥረዋል

- አዎ ማለት ቅድም እርስዎ የሊስሮ እቃ ሌሎች ሲወረወር ነበር እና ከየት ወዴት ነው የሚወረወረው በወቅቱ የደረሰስ ምን ነገር አለ የደረሰ?
- ከውስጥ መስኪድ ውስጥ የሊስትሮ እቃ ዲንጋይ ምናምን ሲወረወር ነበር በሰዓቱ እኛ ቀረብ ስለነበረ ያው በተወረወረ ዲንጋይ ጉልቤን ተመትቻለሁ ስለዚህ በሰዓቱ ማለት ነው ጉልበቴን ተመትቻለሁ
- ሌሎች አባሎችስ ሌላስ የደረሰ ጉዳት ነበር?
- ሌላ በሰዓቱ ያው ባንክ ተሰብሯል የተፈነከተም አበል አለ የተጐዳ ወደ ሕክምና የሄደ አባል አለ በሰዓቱ ያው ሁሉም ነው የተጐዱት ጀርባውንም የተመታ አለ ብዙ አባሎችም ተጐድተዋል በሰዓቱ
- ስንት ሰዓት አበቃ ምን ያህልጊዜ ቆየ ?
- እኔ ከስምንት ሰዓት ጀምሮ ነው ከዛ በፊትም ውስጥ ነበሩ ከስምንት ሰዓት ጀምሮ ነው እዛ ቦታ ላይ የደረስኩት እስከ አስራአንድ ሰዓት አስራሁለት ሰዓት ድረስ ግርግሩ ነበረ ያው እስከ አስር ሰዓት እስከ አስራአንድ ሰዓት አካባቢ በእርግጥ አላውቀውም ሰዓቱን
- የዚህ አጠቃላይ ምን ነበር የወቅቱ ችግር ወይም ደግሞ የዚህ ሁኔታ አነሳሱ ምን እንደነበረ ተረድታችኋል?
- በውስጥ አነሳሱን አላወቅንም ውስጥ መስኪድ ውስጥ ነው ወደ ውስጥ መግባት አንችልም እኛ በር ላይ ነበርን ውስጥ ሆነው ነው አለህዋክበር እያሉ ሴቶችም ወንዶችም ነበሩ በብዛት ሲሉ ነው የነበረው እንጂ በምን ሁኔታ እንደተነሳ አላወቅኩም
- በወቅቱ መስኪዱ ውስጥ የነበሩት ሰወች ማለት ነው አንዋር እንዴት ወጣ ሰው በዚህ ውርወራ ኃይል ነበር እና እንዴት እንዴት ብሎ ወጣ?
- በወቅቱ በቃ ድንጋዩ እኛ በመጀመሪያ ብዙም ይሄን ያህል የከፋ እንትን ይነሳል ብለን በሙሉ አልጠበቅንም ነበረ ከዛ ድንጋዩ ምናምን ሲሸሽ እኛ ወደኋላ ለቀቅን ከበሩ ወደታች ወደ አሜሪካን ግቢ እኛ እየወረድን መጣን ዲንጋዩ ምኑም እየተበራከተ ሲመጣ በዛ መሃል ነው በቃ የመሯሯጥ ምናምን ሁኔታዎች የተፈጠሩት

129

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እና ሰው እዛ ውስጥ የነበረውም በዚህ በኃሉ ውስጥነው የወጣው ?
- እ?
- ውስጥ የነበረው ሰው በዚህ በግርግር መሃከል ነው?
- አዎ በግርግርነው የወጣው
- ጨርፊናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ
- ምስክር እርስዎ ወደ አሜሪካን ግቢ አካባቢ እንደሸሻችሁ ገልፀዋል ሕዝቡ ታዲያ እንዴት እንደወጣ በምን አወቁ?
- እኛ ያው ፊት ለፊት ድንጋይ እየተወረወረ ስለነበረ ያው ዲንጋዩን እየሸሸን ነው ወደ ኋላ እያፈገፈግን ይሄ ይታይ ነበረ በጀርባው በባንኩ በኩል ስለነበርን ይታይ ነበረ
- አሜሪካን ግቢ ማለት አሜሪካን ግቢ ሆኖ አንዋር መስኪድ ይታያል?
- አይ ወደ አሜሪካን አስፋልቱን እንዲህ እያየን ወደታች ወረድን ወደ አስፋልቱ አራት መንታ መንገድ አስፋልቱን ዝቅ እያልን መጣን እንጂ ቅያስ ምናምን የለውም
- ጥሩ ፖሊሶች መጡ ብለዋል ፖሊሶች መጥተው ምን አደረጉ?
- ያው እነሱ መጋጫ ያለው መከላከያ ያለው ነበር የያዙት እነሱን ሕዝቡን እንደዛ እየተከላከሉ እየተጠጓቸው እየተከላከሉ ነበረ የሄዱት እና ከነሱ ኋላ ሆነን ሌላውን ሰው ወደዛ ወደዛ ማሸሽ ጀመርን ማለት ከዛ ሊቀላቀሉ የሚመጡ ሰወች ስለነበሩ እኛን ወደሌላ እያሸሸን እነሱም እየተጠጉ ሲመጡ እኛ ወደኋላ ተመለስን
- ጥሩ ሕዝቡ በየት በኩል ነበረ የሚወጣው አንዋር መስኪድ በሮች እንዳሉት ያውቃሉ ?
- እኛ የነበርነው በዚህ በባንኩ በኩል ያለው በር በኩል ነበርን በሲኒማ እራስ ባለው በር በኩል ነበርኩኝ እኔ በዛ በኩል የወጣውን ነው የማውቀው
- የሕዝቡ አወጣጥ ምን ይመስል ነበር ማለት እየሸሸ ወደቤቱ እየሄደ ነበረ ወይስ ምን እያረገ ነው?
- በቃ ከዛ እየተወረወረ የሚወረውሩም አሉ ቆመው የሚሯሯጡም የሚሸሹም የሚሮጡም አሉ ወደየአቅጣጫው ወደ ሱቆችም በዛ ሰዓት የተወሰኑ ሱቆች ክፍት ነው ወደ ሱቆቹም የሚገቡ ሰወች ነበሩ እንደዛ ነው
- እርስዎ ከደረሱ በኋላ ድንጋይ ስንት ሰዓት ነበር ሲወረወር የነበረው?

1716 /30

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኛ ያው ስምንት ሰዓት አካባቢ ነው ከዛ በኋላ ነው ድንጋይ ከውስጥ መወርወር የጀመረው ስምንት ሰዓት ከአስር ከሃያ አካባቢ ይሆናል ሰዓቱ
- ሰውስ በስንት ሰዓት ከመስኪድ ወጣ?
- ሰው በቃ ከዛ ልክ አሁን በውል ሰዓቱን ባላውቅም ከድንጋዩ እረብሻው ከተነሳ ጀምሮ ትንሽ እኛ ወደኋላ መለስ ስንል ከውስጥም በብዛት ወጡ ከዛ መወርወር ጀመሩ ውስጥም ድንጋዮችም መወርወር ተጀመረ ከዛ ሰዓት ጀምሮ ነው ሰው እየወጣ የነበረው
- አድማ በታኝ ፖሊሶች ነበሩ አደል?
- አዎ ፌደራል እና ልዩ ኃይሎች ሲመጡ ነው እኛም የሸሸነው እነሱ መከላከያ ስለነበራቸው
- አስለቃሽ ጭስም ተተኩሶ ነበር ?
- በወቅቱ አላየሁም እኔ ሲተኮስ
- እርስዎ የት ነው የነበሩት?
- እኔ ሲኒማ እራስ ነበርን እኛ ወደ ሲኒማ እራስ ወረድን
- መጀመሪያ ማለት አሁን ድንጋይ ሲወረወር እግን ተመታሁ ብለዋል ሲኒማ እራስ ሆነው አይመቱም መቼስ?
- እኔ መጀመሪያ አንዋር መስኪድ በሩ ላይ ነበርን ባንኩ በሩጋ ነበርን እኛ የደረስነው ባንኩጋ ሆነን ከዛ በኋላ ድንጋይ ምናምን ሲወረወር ማፈግፈግ ጀመርን የዛ ሰዓት ላይ ልክ ባንኩ በታች ወደታች ወርደን ነው ያሚር እንትን የሚሸት አለ ፎጣ ምናምን ሱቆች አካባቢ ነው የተመታሁት በድንጋይ
- እሺ አሁን ይሄ ነገር ካለቀ በኋላ እርስዎ ወደሚሰሩበት ቦታ ወይም ወደ ቢሮዎት በየት አቅጣጫ ነው የሄዱት ?
- እኛ በዛ ሄድንና
- በመስኪዱ በኩል አልፈው ነው የሄዱት?
- በመስኪዱ በኩል አደለም በሲኒማ እራስ በቲያትር ቤቱ በኩል አርገን ወደ 18 ጣቢያ ነው ወደዛ ነው የሄድነው በቃ እኛ እዛ አካባቢ ሲረጋጋ እነሱም ሲረከቡ ወደ ጣቢያ ደግሞ ወደ መርካቶ ጣቢያ ተጠጉ ወደ ጣቢያም እየመጡ ነው ከታች ከ18 ቀበሌ ምናምን እየተመጣ ነው ሲባል እኛ ወደ ጣቢያ ተመለስን እኛ ደግሞ የተወሰኑ ኃይሎች ወደ ጣቢያ ሄድን

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም እግሬን ዲንጋይ ተወርውሮ ተመታሁ አሉ የቱጋ ነበሩ እርስዎ?
- ስመታ ከመስኪዱ በሩ አደል ከመስኪዱ ወረድ ብሎ ቢያንስ ቅርብ ነው የሃምሳ ሜትር ያህል
- ያው የመስኪዱ በር አካባቢ?
- በር አካባቢ ላይ ሆኜ ነው የተመታሁት
- እሺ አሁን መጋጫ የያዙት ፖሊሶች ደግሞ ነበሩ ብለዋል እነሱስ የት ነው የነበሩት?
- ልክ እነሱ ዲንጋይ እና እንትኑ ሲወረወር
- ከእርስዎ ፊት ነው ከኋላዎት ነው የነበሩት?
- መጀመሪያ ሲወረወርማ እኛ ነበርን ፊት ለፊት የነበርነው እየተወረወረ ሲመጣ እኛ ወደታች እያፈገፈግን መጣን እኛ ዲንጋዩ እና እንትኑ ሲበዛ
- እነሱ ወደበሩ ሄዱ?
- ከዛ አነሱ መጡ እነሱ ሲመጡ እ ኛ ለቀን እነሱ ከፊት ያን እየተከላከሉ ወደነሱ ሲሄዱ እኛ ደግሞ ከታች የሚመጡ ነበሩ ከሌላ አቅጣጫ ከታች ከሲኒማ እራስ ከአሜሪካን ግቢ እሚመጡ ኃይሎች ነበሩ ወደዛ ወደ መስኪድ ማለት ነው እነሱን እያሸሸን
- እሺ ይበቃል
- ከመስኪድ ሰው እየወጣ በአውቶብስ ሲጫን አላዩም?
- አላየሁም እሱን
- ከ14/11/2004 በፊት በነበረ ፕሮግራም የተፈጠረ ችግር አለ ያውቃሉ እዛ ፕሮግራም የነበረ ስለመሆኑ እዛ አካባቢ ነኝ ስላሉ ማለት ነው?
- ማለት አርብ ለሊት እዛ አካባቢ እኔ በሰዓቱ ለሊት ላይ እረብሻ እንደተነሳ እና አለቃችን በድንጋይ የግራ አይኑ ላይ እንደተመታ ያው በማግስቱ
- አይ እኔ አሁን የጠየቅኩት ከ14/11/2004 በፊት አንዋር መስኪድ ስለነበረ ፕሮግራም የሚያውቁት ነገር አለ?
- ከዛ ያው ሁሌ በዚህ ግርግር ከተነሳ ጀምሮ መች እንደተጀመረ አላውቅም ያው ሁሌ እስታንድ ባይ ነን እኛ
- ከዛ በፊት ስላለው ነው የጠየቅኩት አሁን ከ14/11/2004 እሺ 11/14/2004 መቼ ነበር ቀኑ ምን ቀን ላይ ነው የዋለው?
- ቅዳሜ እለት ነው የዋለው

1710 132

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከዛ በፊት ሰለነበረ ፕሮግራም የሚያውቁት ነገር አለ እዛ መስኪድ ውስጥ ፕሮግራሞች ነበሩ?
- ማለት ፕሮግራም ማለት ይሄ ግርግሩ ሁሌ ነው እኛ ጣቢያችን የራሳችን ጣቢያ ነው መርካቶ 18 አካባቢ ሁሌ ነው እረብሻ የሚነሳው ያው እንደዚህ እረብሻ ባይሆን መጮሆች ምናምን አላህዋክብር የማለት ሁኔታዎች ነበሩ
- ቆይ ቀስ አርገው ምን አይነት ማለት ከዛ በፊት ነበሩ እንዲህ አይነት ነገር ?
- ግርግር ነበር አዎ ከዛ በፊት
- ግርግር ማለት አላህዋክበር የሚሉ ሰወች ነው የነበሩት አድማ በታኝ መጥቶ ያውቃል ከዛ በፊት?
- ከዛ በፊት እንደዚህ አሁን እንዲህ የመወርወር ምናምን ሰዓት ላይ አልነበረም እኛ እዛ እንወጣለን በቃ ጩኸት ያሰማሉ ሶፍት ማውለብለብ ሁኔታዎች አሉ እጃቸውን ምልክት ላይን የማሳየት እና በጣም ጩኸት አለ እንጂ የመወርወር ከዛ የሰላቱ ሰዓት ሲያልቅ ሁሉም ወደየቦታው ይበተናል
- ከሶፍት ውጪ የሚያሳዩት ነገር ነበር?
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለን
- ምንድን ነው መቃወሚያው?
- ያው አሁን
- ትታችኋል ጥያቄውን
- በቃ ትተነዋል
- ትተውታል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም እርስዎ እግርዎን እንደተመቱ ገልፀዋል ምንድን ነው በወቅቱ እርስዎ ላይ ያነጣጠረ ነው ወይስ በአጋጣሚ ነው የተመታው ?
- ያው እንግዲህ እሚወረውሩት እኛ አባሎች ነን ሚሊተሪ ለብሰናል ስራ ላይ ነበርን ወደኛ ነበር ሲወረወር የነበረው እንግዲህ እኔ ተመትቻለሁ ማን እንደመታኝ አላወቅኩም የግድ ያው እኛን ለመምታት ነው ብዙ ልጆች እንደዛ ነው የተመቱት
- ማለት ወደ ግቢ ግብታችኋል እንዴ?
- አልገባንም
- አስፋልት ላይ ነው የነበራችሁት?
- እኛ አስፋልት ላይ በሩ ላይ ነበርን
- ግቢው ዝግ ነበረ እንዴ?
- ክፍት ነበረ
- እናንተ ያደረጋችሁት ነገር ምንድን ነው ለምን ተመታችሁ?
- እኛ ምንም ያደረግነው ነገር የለም ወስጥ ላይ በቃ ሰወች እጃቸውን እንዲህ ተያይዘው በሩን በቃ ከውስጥ እንውጣ የሚሉ ሰወች ነበሩ የተወሰኑ ሌሎቹ ደግሞ እንዲህ ጆርባቸውን ሰጥተው እጃቸውን ይዘው ሰው ከውስጥ ወደ ውጪ እንዳይወጡ ነበር እየከለከሉ የነበሩት
- እኮ እናንተ ሰው እንዲወጣ አልጠየቃችሁም ልቀቁ በሩን ለምን ትዘጋላችሁ አላላችሁም?
- እኛ አላልንም እነሱ ይዘው ብቻ እንዳይወጡ ነበር ሲከለክሉ የነበረው ሰው እንደውም አንዳንዱ እየተጋፋ እጃቸውን እንዲህ እያረገ ሾልኮ እሮጦ የሚወጠ ሰው ነበረ ከነሱ ከዛ በኋላ ነው ከውስጥ ጩኸቱ በዛ ድንጋይ መወርወር ተጀመረ ከዛ እኛም ከበሩ ማፈግፈግ ጀመርን ወደላይ
- ጥሩ እናንተ ከመድረሳችሁ በፊት ሌሎች ፖሊሶች የሉም እንዴ በአካባቢው ዙሪያውን ?
- ሌሎች የተመደቡ አባሎች አሉ እኛ ኃይሉ ሲበራከት ነው እኛ ከጊቢ የተጠራነው እኔ ግቢ ነበርኩኝ ብዬሃለው በሰዓቱ ለዛ ነው ኃይል ይምጣ ተብሎ ነው እኛ ከጊቢ ተነስተን ወደዛ የሄድነው
- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ አቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ
- አባተ

1720 134

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አቤት
- እኛ ተተካን ብለሃል ቅድም ስትጠየቅ ማለት መጀመሪያ እኛ ነበር የደረስነው በኋላ ላይ አድማ በታኝ እና ፌደራል ፖሊስ መጥቷል ብለሃል ?
- አዎ
- ለምንድን ነው ይሄ የሆነው?
- ዲንጋዩ ሲበዛ እኛ ባዶ እጃችንን መከላከል ስለማንችል እነሱ መጋጫ ስላላቸው ነው እነሱ የመጡት
- እናንተ ላይ ድንጋይ መወርወር ለምንድን ነው ያስፈለገው?
- እኛ ከቦታው ዞር እንድንል ይሁን ያው አላማቸውን አላውቅም ግን ያው እየመቱን ነበረ በዛ ሰዓት
- ከአቅማችሁ በላይ ስለሆነ ነው እነሱ የመጡት?
- አዎ እኛ ከአቅማችን በላይ ስለሆነ ነው ያው እኛ ትንንሽ የምንታጠቀው ዱላ ነው የያዝነው መከላከል አንችልም ድንጋዩ ሲብስ ነው እነሱ የመጡት
- ስንት ሰዓት ላይ ነው የመጡት?
- ቢያንስ ከአንድ ሰዓት ምናምን ይሆናል
- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ምስክር ባንኩ ተሰብሯል የሚል ነገር ገልፀሃል እና ምኑ ነው የተሰበረው መስታወቱ ነው የተሰበረው ነው ያልከው?
- መስታወቱ ነው የተሰበረው
- ምን ያህል ይሆናል የተሰበረው መስታወት?
- የዲንጋይ ምት ነው የሰበረው ያው
- እኮ የድንጋይ ምት ማለት አንድ ድንጋይ ነው ብዙ ድንጋይ ነው ጉዳቱ ምን ያህል ነው?
- ያው መጠን የአንድ እንትን መጠን ያህል ይሆናል ክሽ ብሏል በአንዴ
- አቤት?
- በጣም ተሰብሯል የተወሰነ የመስኮት ያህል እንትኖች ተሰብረዋል
- ያረፈበት ድንጋይስ ስንት እንደሆነ በግምትም አይታወቅም?
- አላወቅኩም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ ማለት ለምሳሌ በስፋት ወይ አንድ ሜትር ወይ ሁለት ሜትር ወይ እንዲህ የምትገምተው ነገር አለ?
- አልገምትም
- ምኑ ነው ታዲያ የተሰበረው?
- ያው የባንኩ መስታወት በሩ አለ አደል ለሱ ነው የተሰበረው ድንጋይ የገባበትም የገቡበትም መሃል አለ በስተው የገቡበት
- እንትኑን ስለማናውቀው ነው አሁን ባንኩ ባንኩን እኛ አናውቀውም እርስዎ ስለሚያውቁት ነው እንዲያስረዱን ነው ስለዚህ በሩ ነው የባንኩ በር ነው ወይስ ምኑ ነው የተሰበረው?
- አንድ ብረት የታጠረ አለ ከብረቱ ደግሞ አልፎ መስታወት ነው እንደዚህ መስታወት ነው እንዳለ የበሮቹ ግድግዳው
- በአንድ ግምባር ያለው ሙሉ በሙሉ ነው?
- አይ በአንድ በግራ በዚህኛው በኩል ሳይድ ያለው ነው መሰበሩን ያየሁት ይሄ እራሱ ከአንዋር መስኪድ ጀርባ ያለው
- ማለት የትኛው ባንክ ብዙ ባንኮች አሉ እዛ የባንኩ ስም የትኛው ባንክ ንግድ ባንክ አዋሽ ባንክ?
- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነው
- በየት በኩል ያለው ነው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አንዋር መስኪድ ዙሪያም ብዙ አሉ በየት በኩል ያለው ነው?
- የራሱ ግድግዳ በሲኒማ አራስ በኩል ያለው ነው
- ፊት ለፊት ያለው?
- አዎ
- እሺ ጉዳት በሰው ላይም ደርሷል የሚል ነገር አስቀምጠሃል የአንተ ጉዳት ምንድን ነው ምን ሆነ ?
- እኔ ጉልበቴን ነው በድንጋይ የተመታሁት
- እኮ ምን ጉዳት ደረሰብህ?
- ትንሽዬ አብጣለች
- ሌላስ የተጐዳ ሰው አይቻለሁ ብለሃል?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላው እዚህ አሸናፊ የሚባል አለ ኮንስታብል አሸናፊ ተፈንክቶ እሱ ደም በደም ሆኖ ሆስፒታል ወዲያው ሄዷል
- ሆስፒታል ሄደ ወድቆ ነበር?
- ወድቋል አዎ እራሱን ስቶ ነበር
- ሌላስ?
- ሌላ ትከሻውም የተመታ አለ
- እኮ ማን ነው እሱ?
- አሁነ ዋ/ሳ ተስፋዬ የሚባልም አለ የተመታ
- እነሱ ምን እያደረጉ ነው የተመቱት?
- ያው በሰዓቱ አብረን ነው የወጣነው እዛው ስራ ላይ እያሉ ነው
- አሃ ስራ ላይ የነበሩ ናቸው?
- አዎ
- ጨርሰሃል
- የተከበረው ፍ/ቤት አንድ እንድገም እንደአሁኑ አይነት አለ አንድ እንድገም ሰላሳ ደቂቃ ስላለ
- በእውነት ለመመስከር
- በእግዚአብሔር ስም
- ምያለሁ
- እሺ ምስክር
- አቤት
- ያው እንግዲህ ለምስክሮች ደህንነት ሲባል የመጀመሪያ ስሞን ብቻ እንዲገልፁ ነው ፍ/ቤቱ የፈቀደው ስለዚህ የመጀመሪያ ስሞ ማን ይባላል?
- ሞላ
- እሺ ለምንድን ነው እዚህ የመጡት?
- እዚህ የመጣሁት የማውቀውን ነገር ማለት በመርካቶ ላይ በነበረው ባለፈው ክረምት ላይ
- እነማን በተከሰሱበት?
- ስማቸውን አላውቅም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ ምንድን ነው የሚያስረዱት?
- በዛ ሰዓት በነበረ ብጥብጥ ነበር እሱ ጉዳይ ላይ ለማስረዳት ነው ፍ/ቤት ለማስረዳት ነው
- እሱ ጉዳይ ምንድን ነው እሷን ይንገሩን ?
- ፍ/ቤት ለማስረዳት የመጣሁት እዛ መርካቶ ስራ ላይ እያለሁ
- አሃ የተፈፀመ ድርጊት ?
- የተፈጠረውን ድርጊት ለማስረዳት
- እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ስማቸው 61ኛ ተራ ላይ የተጠቀሰ ነው
- እሺ ምስክር በፍ/ቤቱ 20ኛ ተራ ቁጥር ነው በአቃቤ ሕግ ክስ ላይ 61ኛ የተጠቀሰው የአቃቤ ሕግ ምስክር ናቸው የቀረቡት ይቀጥሉ
- እሺ እ/ሳ አሁን ከመጡበት አጠቃላይ ምስክርነትጋር በተያያዘ ቅድም እንደገለፁት ቀኑ መቼ እንደሆነ ድርጊቱ የት ቦታ እንደተፈፀመ የት ክ/ከተማ የት አባቢ እንደነበረ እና አጠቃላይ በወቅቱ ምን እንደነበረ ያዩትን የሚያውቁትን ሁሉ ለተከበረው ፍ/ቤት በዝርዝር እንዲገልፁ ነው የምጠይቀው ቀኑ መቼ ነበር?
- ቀኑ ሐምሌ ላይ በ14
- አመተ ምረቱ መቼ ነው?
- 2004
- ስንት ሰዓት አካባቢ ነበር?
- ስምንት ሰዓት አካባቢ ይሆናል
- እሺ የት አካባቢ ነው?
- መርካቶ መስኪድ ወደዛ አለፍ ብሎ ጣና አካባቢ ማለት ነው
- እስቲ በዚህ እለት ሰዓት ጊዜ ምንድን ነው አርስዎ ያዩት ምንድን ነው የገጠማችሁ ምን ተከሰተ እንዴት ነው የተከሰተው እስቲ የሚያውቁትን ሁሉ በዝርዝር ይግለፁ እስቲ?
- በዛን ሰዓት እኔ ስራ ላይ ተመድቤ ነበረ ስራ ላይ እያለሁ ያው እኔ ያየሁት በዛን ሰዓት በጋራ ተሰብስበው ከኋላም ከፊትም ብዙ ድንጋዮች እየተወረወሩ ነበረ እየተጮኸ ነበረ አላህዋክበር እያሉ እየጮኹ ነበረ አንፊራም ወደፊት እንጂ ወደኋላ አንልም እያሉ አላህዋክብር እያሉ ድንጋይ እየተወረወረ ነበረ ድንጋይ ወርውረው ባንክ ላይም ሲሰበር ነበረ ባስም ሲሰበር ነበረ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስቲ ቆይ እሱ ላይ በኋላ እንዳንመለስ እነማን ናቸው ማለት ከየት የመጡ ሰወች ናቸው እንደዛ የሚሉት?
- ማለት ከየት እኔ በራሴ በመስኪድ የወጡትም አሉ በመስኪድ በኩል ማለት ነው ከውስጥም ከውጭም አደለም በውስጥ በመስኪድ በኩልም የመጣ አለ ከላይ በኩልም የመጣ አለ በበዙ አቅጣጫ መጥተው እኔ ግን በአንድ ላይ ነው የተሰበሰቡት ጣና አካባቢ ማለት ነው ጣና አካባቢ በጋራ ሆነው እየጮሁ ድንጋይ እየወረወሩ እኔ ላይም ጉዳት አድርሰውብኛል ታክሜ ህክምና ሄጃለሁ
- ቅድም ሲገልፁ እስቲ መጀመሪያ ባሱ ላይም ጉዳት ደርሷል ብለዋል ሌሎች ንብረቶች ላይም ጉዳት ደርሷል ብለዋል እስቲ ንብረት በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳይ ምን ምንድን ነው የደረሰ ጉዳት?
- በዛን ሰዓት ባስ መስታወት ላይ ሲሰበር ነበረ እዛ ጣና የነበረ ማለት ብርሃን ባንክ የሚባልም መስታወቱን ስብርብር አርገውታል የዛን ሰዓት ወርውረው ማለት ነው
- እሺ አውቶብሱ ወይም ባስ ያሉት አውቶብስ ምን አይነት አውቶብስ ነው?
- የከተማ ባስ ነው አምበሳ ባስ
- ቁጥሩን ማስታወስ ይችላሉ?
- ቁጥሩን አላስታውሰውም
- ምን ያህል ስንት አውቶብሳች ናቸው ጉዳት የደረሰባቸው?
- የተሰበረው እኔ በዛ ሰዓት ያየሁት አንድ ባስ ነው
- ሌላስ ቅድም እርስዎ እንዳሉትር ጉዳት ደርሶብኛል ብለዋል እና በእርስዎም በሌሎች ላይም ካለ እሚያስታውሱት ካለ ምን ላይ ነው ጉዳት የደረሰቦት እርስዎ?
- እኔ ላይ እግሬ ላይ በድንጋይ ተመትቻለሁ ብዙ ድንጋይ ነው የተወረወረብኝ ድንጋዩን ብዙ እንትን ብዬ ለመደበቅ እንትን ብያለሁ ግን አንዱ ድንጋይ እንምንም ብሎ እግሬን መቶኛል
- እሺ ሌሎቹስ?
- ሌሎቹ ጓደኞቼም የተመቱ ነበሩ የዬዱም አሉ ያልዬዱም አሉ በዛን ሰዓት የተመቱም አሉ የማስታውሳቸው ከኔጋ የነበሩ
- እስቲ የት የት ላይ ተመቱ እነሱ?
- እስቲ መጀመሪያ የእርስዎን ጉዳት?

1726 139

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ ላይ እርግራን ነው
- እስቲ በጉዳቱ ምን ሆኑ ?
- በቃ ተመታሁ አነከስኩ ብርድም ነበረ ዝናብም ነበረ ህክምና ላይ ነው የሄድኩት መርገጥ አልቻልኩም መቋቋም አልቻልኩም ሕክምና በአምቡላንስ ነው ይዘውኝ የሄዱት የፖሊስ አምቡላንስ መጣ ይዞኝ ሄደ
- ሌሎችስ በሌሎች አባላት ላይ የደረሰ ጉዳት የሚያስታውሱት አለ ልክ እንደ እርስዎ?
- አጠገቤ የነበረ አንድ ጓደኛዬ ተመቷል እጁ ላይ እንደዚህ ተመቶ አብጦ አብሮኝ ነው አሽቼ አስተካክልኩለት ሕክምና ይሂድ አይሂድ አላስታውስም
- ይሄ ቅድም የገለፁት ባንክ የት አካባቢ ነው የሚገኘው ጉዳት የደረሰበት ባንክ ማለት ነው ስሙን የጠቀሱት ማን ነው ስሙ?
- ብርሃን ባንክ
- ምንድን ነው እሱ ጉዳት የደረሰው ባንኩ ላይ?
- ማለት ብርሃን ባንክ መስታወት ነው ፎቅ ላይ ስለሆነ መስታወት ነው እሱ በድንጋይ የተመታው
- ከየት አቅጣጫ መጥተው ነው ይሽው የነኚህ አሁን ቅድም ያሏቸው ስብስብ እየጮሁ ድንጋይ ውርወራ የጀመሩት ከየት አቅጣጫ ነው የመጡት?
- የሚሯሯጡት ከላይም ከታችም በኩል ነው
- ማለት ቦታው በተለይ ቦታው?
- መአከላቸው ጣና ነው እኔ እዛ ሴንተር ላይ ነበርኩ ከዛ በዛ በኩል ነው ወደዚህ የሚወረውሩት
- ከየት አቅጣጫ ነው የመጡት እነሱ?
- እኔ በመስኪድ በኩል ነው ያለሁት አቅጣጫ እነዛ ወደ ምእራብ ሆቴል አካባቢ ማለት አቅጣጫ ወደ 7ኛ አቅጣጫ እና ወደዚህ ለመምጣት ነው እየወረወሩ ወደኛ ነው የሚወረውሩት ወደፖሊሶቹ
- ከወደ መስኪድ ነው የመጡት ነው የምትሉት?
- ወደ ፖሊሶች ነው የሚወረውሩት ወደኛ ነው የሚወረውሩት
- እኮ መነሻቸው ከየት ነው ማለቴ ነው እየመጡ ያሉት ወደ ጣና ሲጠጉ ከየት ከየት አቅጣጫ ነው ወደናንተ እየመጡ ያሉት?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- /ማልጽ ያልሆነ/
- በጣም ጥሩ እሺ ምንደን ነው ሲወረውሩ የነበረው ?
- ድንጋይ ነው ሲወረውሩ የነበረው
- ምን ያህል ይሆናሉ ብዛታቸውን ማወቅ ይቻላል ግምቱን ?
- አይ
- በርካታ ናቸው?
- አዎ
- እሺ
- በወቅቱ ታዲያ ከዚህ በኋላ ማለት ነው ከዚህ ከሁከቱ በኋላ የተወሰደው ምንድን ነው ለመከላከል ማለት ነው ለመከላከል የተወሰደው እርምጃ ምን ነበር?
- እኔ የወሰዱኩት እርምጃ
- አይ በአጠቃላይ ለመከላከል ሕግን ለማስከበር የተወሰደ ነገር አለ እንዴ ?
- እኛ ምንም አልተጠጋናቸውም እራሳችንን ለመከላከል ነው ድንጋይ እንዳይመታን ራሳችንን ለመከላከል ነው ስንራ የነበረው ከኔጋ የነበሩትም እንዳይመጡ እራሳችሁን ጠብቁ እያልኩ ነበር ሲወረወር ነበረ እራሳችንን እየጠበቅን ለማረጋጋት ነው ሰወቹን ለመለየት በአይን ለመለየት ነበረ ግን ለመለየት አልቻልንም
- ሁኔታው ከአቅም በላይ ነበር ?
- ማለት በጣም እየበዙ ድንጋይም እየወረወሩ ወደኛም እየተጫኑ ሲበዙ በርካታ ኃይል ከእኛ ከጀርባ ሲመጣ ደንግጠው ነው የተበተኑት
- ጨርሰናል የተከተረው ፍ/ቤት
- እሺ የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ
- ምስክር ቅድም አህን ሲናገሩ ከ7ኛ አካባቢ ሰወች ፖሊሶት ወደናንተ ይመጡ እንደነበረ ገልፀዋል ትክክል ነኝ ከምእራብ አካባቢ ወደ ጣና አቅጣጫ ነበረ የሚመጣው ሰው?
- አቅጣጫ ወዴት ነው በዚህ ነው በላይ ነው ብለው ምእራብ ወደዛ ስላለ በምእራብ በኩል ነው አቅጣጫው የማሉት ጣና አካባቢ ነው
- እስኪ መነሻዋ ምእራብ መስዝቅ ለማለት የሆነ መነሻ ይኖራል መነሻውን ይንገሩን እኛም እንድናውቀው ለምሳሌ ከዚህ ከተነሳሁ ወደዚህ ምእራብ ማለት አያቅተኝም ስዚህ እርስዎ የት ላይ ሆነው ነው ምእራብ ምስራቅ የሚሉት?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ መአከል ላይ ነበርኩ ጣናጋ ነው
- ጣና ገበያ ማእከል?
- ጣና ገበያ ማእከል ላይ አደባባይ ላይ ነበርኩ
- እሺ ቀጥሉ
- ስለዚህ እርስዎ ጣና ሆነው ነበረ ከምእራብ ወደ ጣና አቅጣጫ ወደናንት የሚመጣ ሰው ነበረ ነው ያሉት?
- ማለት የሚወረውሩት ድንጋይ ማለት ነው
- እ?
- ማለት አልገባኝም
- ቅድም ሰው ከየት መጣ ተብለው ሲጠየቁ ከአንዋር ከላይ ብለው ገለፁና ከታች ደግሞ ከምእራብ በኩልም ወደ ጣና በኩል ድንጋይ የሚወረውር ሰው ነበረ ብለዋል ትክክል ነኝ ?
- ልክ ኖት
- ከአንዋር አካባቢ ሰው መምጣት እርስዎ ጣና ሆነው ነው የሚያዩት አደል የሰውን አቅጣጫ?
- ጣና ነው ያለሁት እኔ
- ስለዚህ ከአንዋር አቅጣጫ እንጂ ከአንዋር ይውጣ አይውጣ በምን ያውቃሉ አቅጣጫውን ብ ቻ ነው አደል መግለጽ የሚችሉት?
- ትክክል እኮ ነው እንደዛ ነው የመለስኩት እኔም
- እኮ እሷን ምንድን ነች ከአንዋር የወጣ ሰው ከአንዋር ይውጣ አይውጣ እንዴት አወቅክ አረጋገጥክ ?
- አቅጣጫውን ነው አደለ የገለፁት?
- በአንዋር በኩል እና በላይ በኩል በታች በኩልም መጥተው ተሰባስበው እዛጋ ሰብስበው በጣም ኃይል ጨምረው እኛ ላይ እየወረወርን ነበረ በላይም በታችም በብዙ አቅጣጫ መጥተው እዛ ነው መሃከል ያረጉት እኔም እዛ ነበርኩ
- ጥሩ በጣና እና አንዋር መካከል ያለውን ርቀት መገመት ይችላሉ?
- መገመት አልችልም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ሲመሰክሩ በድንጋይ የተመታ አንደ ባስ አይቻለሁ ብለዋል ባሱ የቱጋ ነው የተመታው?
- ፊት ለፊት መስታወቱ
- እኮ የት አካባቢ የቆመ ነው የሚሄድ ነበረ ?
- እዛ የቆመ መኪና
- የት አካባቢ የቆመ?
- ባስ መቆሚያ አካባቢ
- ባስ መቆሚያ ሲባል?
- ጫፉ ላይ ማለት ነው ወደ ጣና መታጠፊያ ላይ እዛጋ
- በጣና እና በምእራብ መሃል ማለት ነው?
- መሃል ላይ ማለት ነው ባስ ማቆሚያው ማለት ነው
- ስለዚህ አሁን ቅድም ሲናገሩ ከምእራብ አቅጣጫ ሰወች መጥተው ድንጋይ ይወረውሩ ነበረ ብለዋል መስኪዱ ደግሞ ያለው ከእርስዎ በጀርባ በኩል ነው ማለት ነው ከእርስዎ በተቃራኒ ሳይድ ነው ማለት ነው?
- በጀርባዬ በኩል ነው ያለው
- እሺ ሌላ ተጨማሪ ኃይል መጥቶላችሁ ነበር እንዴ?
- በጣም የበዛ ሰው ሲመጣ ከአኛ በጀርባ ኃይል ሲመጣልን ተበተኑ እነሱም እየተበተኑ እየተመናመኑ ወደዛ እየሮጡ
- ወዴት ሄዱ?
- ከምእራብ በኩል በቃ ብትንትናቸው ጠፉ በቃ ወደ እንትን ነው የጠፉት እዛ አካባቢ ሲደርሱ ብትንትን ብለው ነው የጠፉት
- የመጣው ኃይል አስለቃሽ ጭስ ተኩሰው ነበረ እንዴ?
- አስለቃሽ ጭስ አልተካሰም እኔ ያለሁበት
- ከእርስዎ በፊት የመጡትን ምስክር አቶ አባተን ያውቋቸዋል?
- አዎ አንድላይ ነው የምንሰራው አንድ ጣቢያ ነን
- አብራችሁ ነበራችሁ የዛን ቀን?
- በዛን ሰዓት አላስታውሰውም እኔ ላይ የነበሩት ሌሎች ቲሞች ናቸው ማለት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አቶ አባተ ስራ ላይ ነበር ?
- እምልህ በዛን ሰዓት እኔ አላስታውስም ሁሉም ስራ ላይ ነው ሁሉም አባል እስታፍ ስለሚሰሩ ድጋፍ ነው የእኛ ነው የሚሰጡት የሆነ ነገር ሲኖር በዛ ነው የሚሰጡት
- ጓደኛዬ እጁላይ ተመቶ አብጦበት አሸቼለት ሄደ አሉ ?
- አዎ
- ከዛ ወደ ስራው ገባ?
- ስራውን ለቋል
- ማለት ካሹለት በኋላ ወደ ስራው ተሰማራ?
- አሸሁለት ስራ እኔጋ አብሮ እየሰራ ነበር መጨረሻ ነው የተጐዳው ሄድኩ ወደ ህክምና
- እርስዎ ከተመቱም በኋላ እየሰሩ ነበር?
- ማን?
- እርስዎ በድንጋይ ተመታሁ ብለው ነበር ከተመቱም በኋላ እዛው ለማረጋጋት እየሰሩ ነበር?
- ቆይ እስቲ እኔ እንደተመታሁ ሄድኩ ነው ያሉት
- አካባቢውን ለቀው ሄዱ ወይስ ስራ ላይ ቆይተዋል?
- ከተጐዳሁ በኋላ በአምቡላንስ ሄጃለሁ
- ከዛ በኋላ የደረሰቦት ጉዳት አለ እንዴ ቋሚ የሚባል ጉዳት አልደረሰቦትም አደል?
- በቃ ለሦስት ቀን ለአምስት ቀን እስከ አምስት ቀን ድረስ ያው እረፍት ምናምን
- እረፍት ተሰጦት?
- ወሰድኩና እንትን አልኩ
- ወደስራዎት ገቡ?
- አዎ
- በንብረት ላይ ስለደረሰው ጉዳት ሲገልፁ አንድ የባንክ መስኮት መስታወት ተሰበረ እና አንድ ባስ ላይ ጉዳት ደረሰ ነው ያሉት አደል?
- አዎ ብለዋል ቀጥሉ
- በባሱ ላይ የደረሰውን ጉዳት መጠን ሊያስረዱን ይችላሉ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መጠኑ ፊት ለፊቱ መስታወት በድንጋይ ተመቷል ስብርብር ብሏል እንደዚህ ወደ ውስጥ እንትን ብሏል ያው ሌላ እንትን
- መስታወት ብቻ ተሰበረ?
- መስታወቱን ነው ያየሁት እሱን ነው
- በባስ ላይ የደረሰው ጉዳት መስታወት ብቻ ነው?
- መስታወት መሰበር በዛን ሰዓት ሹፌሮቹም የሉም እሮጠው ሄደው አምልጠዋል እዛ አካባቢ የነበረው ሰውም ሄዷል የለም
- በባንክ ላይም መስታወት ብቻ ነው ?
- በባንክ ላይም ያየሁት መስታወት ነው በአይን ያየሁት ሲወረወር እና የተመታው ማለት ነው
- በተወረወረ ድንጋይ ብቻ ፎቅ ላይ ነው ?
- ፎቅ ላይ ነው መስታወቱ
- የቆመው ባስ ሲመታ ሌሎች ባሶች አልነበሩም እንዴ?
- ብዙ ባስ ነበረ
- ከዛ ውስጥ አንዱ ነው የተመታው?
- እኔ ያየሁት አንድ ነው በኔ በኩል የነበረው ማለት ነው
- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ አቃቤ ሕግ
- በምን ምክንያት ነው አሁን ተገኘሁበት ያልከው እረብሻ በምን ምክንያት ነው የተነሳው?
- ምክንያቱ እኔ ግልጽ አልሆነልኝም በቃ ጩኸት እና ውርወራ ሲሆን ነው
- እኮ ምን ተረዳህ እዛ በምን ምክንያት የተነሳ እረብሻ ነው?
- ምክንያቱን እኔ የማውቀው ነገር የለኝም
- እኮ እዛ ከደረሳችሁ በኋላ የሚናገሩት ነገር የለም እንዴ?
- አላህዋክብር አላህዋክበር ወደኋላ አንልም እያሉ ነው የሚወረውሩት እነሱ በብዛት እንደዛ እያሉ የሚጮሁት
- ተቃውሞ አለን
- እሺ ምንድን ነው ተቃውሞ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኚህ ምስክር የተከበረው ፍ/ቤት ያዩት ነው እንጂ የመሰከሩት ንግግር ወይም ሌላ ነገር አልመሰከሩም በዋና ጥያቄ ላይ አልተጠየቀም አሁን አቃቤ ሕግ የዋናውን ጥያቄ አሁን ነው እየተጠቀሙ ያሉት ያለፈ እድላቸውን ነው እና እኛም በመስቀለኛ አላነሳነውም በዋና ጥያቄም አልተጠየቀም ስለዚህ
- ተመልሷል ይሄ ጥያቄ አሁን
- አዎ የተከበረው ፍ/ቤት እንዲፈቅድልኝ እንደ ማሳሰቢያ አሁን በተለይ
- አሁን ምን ማለት ነው ከተመለሰ ሳይመለስ ከሆነ ሳይመለስ ከቆያችሁ ግን በግራ ቀኙ የሚታሰበው ምንድን ነው ፈቅደዋል ነው
- ተቃውሞ ብለን ስንነሳ የተከበረው ፍ/ቤት እስኪሰማን ድረስ ባለው ሙመንት ወይ አቃቤ ሕግ እኛን ሰምተው ዝም ካላሉ ምስክሩን የሚጠይቁ ከሆነ ያው ምስክሩ ይምልሰዋል እና በዚህ አይነት ሁኔታ የእኛ ተቃውሞም እየታለፈ ጠሚሄድበት እድል ስላለ ይሄ ቢስተካከልልን ወይ ደግሞ ምስክሩ ምስክርነቱን ሲጀምር አቁም ካልንህ ቶሎ አቁምልን ተብሎ ቢነገረው
- እሱ ቶሎ ከተነሳችሁ ተቃውም ቅድሚያ ነው የሚሰጠው ለማንኛውም ለአቃቤ ሕግም ይሁን ለእናንተም ይሁን ተቃዉሞ ፍ/ቤቱ ነው የሚያስቆመው የመጀመሪያው ስለሆነ እሱ ምናልባት እንደተባለው ወይ ሳናያቸው ቀርቶ እንደሆነ ተቃውሞ አለን ማለት ከፍ አድርጎ መናገር ይቻላል ተቃውሞ አለን ከዛ ትርፍ ከተቃውሞ በኋላ ነው ከተቃውሞ በኋላ ሳይፈቀድ የሚቀጥለው ነገር ነው የሚያበላሸው እንጂ ተቃውሞ አለን ማለት በቃ ፍ/ቤቱን የሚያስቆም ስራ ነው ይሄ የእኛ ሳይሆን በሕጉ ላይ የተቀመጠ ግዴታ ነው ፍ/ቤቱም አቁሞ ማዳመጥ አለበት ስለዚህ ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ መጠየቅ ነው የአሁኑ ተጠይቋል አቃቤ ሕግ ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- እሺ ምን ነበረ ሲባል የሰሙት?
- አላህዋክበር እያሉ ወደኋላ አንልም እያሉ ነው የሚወረውሩት
- እኮ ከየት አቅጣጫ ነው ተደጋግሞ ስትጠየቅ ባሉ የት ነው የተመታው ሰወቹ ከየት ነው የመጡት ይሄንን አሁን ያልከውን ንግግር የሚናገሩት ከየት ነው የመጡት ስትባል ተደጋጋሚ ጥያቄ ተጠይቀሃል እነዚህን ሰወች እናንተ በዛ ወቅት አሁን ተመታሁ ያልክበት ድርጊት የተፈፀመበት ምንድን ነው መነሻው እዛ አልጠየቅክም አንተ ከዛ በኋላ የተረዳኸው ነገር የለም በምን ምክንያት?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማለት በቃ እኔ በወቅቱ እዛ ስለነበርኩ በቃ በጣም ምን እንደሆነ እኔ የማውቀው ነገር የለም
- በቃ
- እሺ በፍ/ቤቱ ማጣራየ ጥያቄ
- በወቅቱ እየተከላከልን ነበር የሚል ነገር አንስተሃል ምን መከላከያ ነገር ይዛችሁ ነበር እንዴ?
- እኔ የያዝኩት ዱላ ነው የፖሊስ ዱላ
- ሌላስ መከላከያ የያዘ ነበር?
- እኔጋ የነበሩ ቲሞችም የያዘ የለም እኔ የዛ ቲም አስተባባሪ ነበርኩ ምንም ዱላ ብቻ ነው የያዙት ከኔጋ የነበሩት
- ሌላ መሣሪያስ ይዛችሁ ነበር?
- መሣሪያ አልያዝንም ዱላ ብቻ ነበር
- እሺ እናመሰግናለን ጨርሰሃል ከሰዓት በፊት ያለውን በዚሁ እናጠናቅቃለን ከሰዓት በኋላ ስምንት ሰዓት ላይ እንገናኛለን ማለት ነው
- ያው ከሰዓት በኋላ ያለው ችሎት ቀጥሏል ከሰዓት በኋላ የተቀጠረው ሁለት ስራዎችን ለመስራት ነው አንደኛው ቀሪ የአቃቤ ሕግ ምስክሮችን ለመስማት ነው ሁለትኛው የተከሳስ ጠበቆች ያቀረቡትን አቤቱታ መርምሮ ተገቢውን ትእዛዝ ለመስጠት ነበር ስለዚህ ጠዋት የነበሩት ዳኞች አልተለወጡም ቀኑም አልተለወጠም ከሳሽ አቃቤ ሕጎችም ጠዋት የነበሩት ቀርበዋል ተከሳሾች ያልቀረበ ተከሳሽ አለ ተከሶች ከ29ኛ ተከሳሽ በስተቀር ሌሎቹ ቀርበዋል እሺ ጠበቆች ጠዋት 5 ጠበቆች ቀርበው ነበር እኔ ቀርቤያለሁ ሃሰን ሁሴን እሺ ጠዋት ከነበሩት ከ28ኛ ተከሳሽ ጠበቃ በስተቀር አምስቱ ጠበቆች አሉ ተጨማሪ ሃሰን ሁሴን የተባሉ ሰውቀርበዋል
- እሺ በመጀመሪያ ደረጃ አቤቱታው ጠበቆች የቀረበው አቤቱታ ትእዛዝ ተሰጥቷል እንሰማለን አቃቤ ሕግ ምስክሮቻችሁን አቅርቡ
- እሺ ምስክር ቃለ መሃላ ፈጽሙ
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም
- ምያለሁ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ቁጭ በሉ
- ምስክር ያው ለምስክሮች ደህንነት ሲባል የመጀመሪያ ስሞን ብቻ ነው የሚተላለፈው ስለዚህ ስሞ ማን ነው ?
- ጊማ
- ስንተኛ ተራ ቁጥር ናቸው አቃቤ ሕግ 31ኛ
- እሺ በፍ/ቤቱ 21ኛ ተራ ቁጥር ናቸው በአቃቤ ሕግ ክስ ደግሞ ተራ ቁጥር 31 ላይ የተጠቀሱት ምስክር ቀርበዋል
- ለምንድን ነው እዚህ ፍ/ቤት የመጡት ?
- ለምስክርነት ነው
- በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?
- በ6 ሰወች ላይ ነው
- እሺ እነማን እነማን ናቸው?
- 1ኛ ሣቢር ይርጉ፣2ኛ አቡበክር አህመድ፣3ኛ ያሲን ኑሩ፣ 4ኛ አህመዲን ጀማል ፣ 5ኛ ሙባረክ
- ሙባረክ ማን ናቸው?
- የአባቱን ስም አላውቅም
- ሌላ
- ጀማል ያሲን
- እነዚህን ነው የሚያውቁት?
- አዎ
- እሺ እነዚህን ተከሳሾች ያውቋቸዋል?
- አውቃቸዋለሁ
- እሺ ሊያሳዩን ይችላሉ?
- እችላለሁ
- እስቲ ይነሱና ቢፈልጉ ቁጭ ብለው እንዳሉ ካለዩዋቸው ደግሞ እንዲነሱ አድርገው መለየት ይችላሉ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ 1ኛ ተከሳሽን ጠቁመው አሳይተዋል 2ኛ ተከሳሽን ጠቁመው አሳይተዋል ፣ 7ኛ ተከሳሽን ጠቁመው አሳይተዋል እስቲ ጀማል እርስዎ ኖት እሺ 19ኛ ተከሳሽን አሳይተዋል ማን ናቸው ሙባረክ 20ኛ ተከሳሽን ለይተው አሳይተዋል ጨረሱ እሺ ቁጭ ይበሉ ካሉ በኋላ በአቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ
- እሺ ሃጂ ጊሳ
- አቤት
- ለምስክርነት ነው የመጡት የመጡበትን ጉዳይ በዝርዝር ያስረዳሉ ከጊዜው ይጀምራሉ ጊዜው መቼ ነው?
- እሺ ቢስሚላ መጀመሪያ በሳቢር ይርጉ ላይ በጥር 11 ቀን 2004 እለቱ ጁመአ ነው ሰባት ሰዓት ተኩል ላይ መጅሊስ አይወክለንም የመጅሊስ አመራሮች አይወክሉንም መጅሊሶች የዲንም ሆነ የአካዳሚ እውቀት የላቸውም እንኳን ሙስሊሙን ሊወክሉ እራሳቸውን አይወክሉም አወሊያ የሙስሊሙ ብቸኛ ተቋም እንደመሆኑ መጠን ማንኛውም አካል እጁን ከአወልያ ላይ እንዲያነሳ እንጠይቃለን ሌላ በልዩነት አወልያ የሙስሊሙ ብቸኛ ተቋም እንደመሆኑ መጠን መጅሊስ እስከ መጨረሻው ለቆ እንዲወጣ የመጅሊስ አመራሮች እንኳን እኛን እንኳን ሙስሊሙን እራሳቸውን መምራት አይችሉም አቂዳቸውን ዲናቸውን በፍርፋሪ የሸጡ አቂዳቸውን በገንዘብ የለወጡ ሕዝበ ሙስሊሙን ሊወክሉ አይችሉም የሚል ለተሰበሰበው ሕዝብ ሲናገሩ ሰምቻለሁ
- ጥሩ ይሄ ያሉት አሁን ጥር 11 ቀን 2004 ዓ.ም ነው ከዚህ ቀን በፊት የተጀመረ ነገር ነበረ ወይ ?
- ከዚህ ቀደም የተጀመረ ነገር ቢኖር ቀደም ሲል ወደ ታህሳስ 16 አካባቢ ይመስለኛል በግምት ከአስር የማይበልጡ ሴቶች ነበሩ
- የት ?
- አወልያ ቅጥር ግቢ ውስጥ
- እሺ አሁን ከአወልያ መስኪድ አሁን ከሚሉት ከታህሳስ ጀምሮ ያለውን ነገር በጊዜ ቅደም ተከተል እንዲያስረዱን ነው እምፈልገው እኔ ስለዚህ የምጠይቆትን እየሰሙ በዚህ የጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ያስረዳሉ ማለት ነው?
- በዛን እለት ከ10 የማይበልጡ ሴት ተማሪዎች
- የምን ተማሪዎች ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የአወልያ ተማሪዎች እና ኢማማችን ይመለሱ የታገዱ አስተማሪዎቻችን ይመለሱልን የተዘጋው ቁርአን ት/ቤት ይከፈትልን የሚል ጥያቄ ነበረ አንስተው ሲጮሁ የነበሩት
- እሺ ከዛስ?
- በዛን ወቅት በአጋጣሚ ለቤተሰቦቻቸው ምን የሚል መልእክት ይላካል የአወልያ ተማሪዎች በፖሊስ ታግተው ምግብ ወደቤት እንዳንመጣ ተከልክለን በፖሊስ ታግተን በሚል ለቤተሰቦቻቸው የሞባይል ስልክ ይደውላሉ
- ማን ነው ይሄን የሚያደርገው?
- ይሄን የሚያደርገው መጀመሪያ አቡበክር አህመድ ከመጣ በኋላ ነው ይሄ ስልት የተነደፈው
- ጥሩ አሁን እረጋ ይበሉና መጀመሪያ ከአስር የማይበልጡ ሴት ተማሪዎች ቅድም ያሏቸውን ጥያቄዎች አንስተው እንቅስቃሴ ጀመሩ አሁን ደግሞ አቡበክር መጣ እያሉ ነው መቼ ነው የመጣው አቡበክር ለመጀመሪያ ጊዜ?
- አቡበክር በዛ በ16 ወደ አምስት ሰዓት ገደማ ላይ ነው የመጣው
- ከቀኑ ነው?
- ከቀኑ ማለት ነው እና እሱ ሰብስቦ ካናገረ በኋላ ሴቱ ብቻ ምን አለበት ወንዱስ ለምን አይቀላቀልም እና ድምፁን አያሰማም አመፁን አይደግፍም የሴቶች ብቻ ነው ወይ ዲኑ በሚል ሁኔታ
- ማን ነው ይሄን የሚለው?
- አቡበክር አህመድ አሁን በዚህ ወቅት ወንዱም ተነሳ
- አቡበክር አህመድ ተማሪ ነው እንዴ እዛ ግቢ?
- አቡበክር አህመድ ተማሪ አደለም በወቅቱ የማውቀው ዳኢ መሆኑን ነው የማውቀው
- ዳኢ ምን ማለት ነው?
- ዳኢ ማለት የኃይማኖት ትምህርት አስተማሪ ማለት ነው
- ታዲያ ለምን መጣ እንቅስቃሴ ሲጀመር ለምን መጣ አቡበክር?
- እንግዲህ አቡበክር የመጣው ያው የአወልያ ተማሪዎች ምግብ እንዳይገባላቸው በፖሊስ ታግደው በረሃብ እያለቁ ነው የሚል ስሞታ ደርሶኝ ነው የመጣሁት ነው የሚለው በዛን ወቅት ይሄ ሁኔታ ከመጣ በኋላ ቤተሰቦቻቸው ይሄን አይነት መልእክት እንዲያስተላልፉ
- ይሄ መግብ የለም ታግተዋል የሚለው?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምግብ የለም በፖሊስ ታግተናል እንዳንወጣ ታግደናል የሚል መልእክት ለቤተሰቦቻቸው እንዲያስተላልፈው
- እናንተ ምግብ እንዳይገባ አርጋችኋል እንዴ?
- እኛ ምግብ እንዳይገባ የከለከልንበት ምክንያት እንዲወጡ አልከለከልናቸውማ ያገዳቸው ሰው የለም ፖሊስ በግቢው ወደ ሁለት መቶ ሜትር መቶ ሜትር እርቀት ውጪ ነው ያለው እኛ በዘበኛ ኃይል በጥበቃ ኃይል ያ ሁሉ ተማሪ ምግብ እንዳይገባ ልንከለክል ነው 2ኛ ከውጪ የሚመጣው ምግብ የተመረዘ ሊሆን ስለሚችል እና እኛ ደግሞ ስላልከለከልናቸው ሄደው መመገብ ይችላሉ ያሰራቸው የከለከላቸው ሰው የለም የሚል ሁኔታ ነው የተናገረው ይሄ እንዳትቀበሉ ይሄን ሁኔታ አቶ አቡበከር አህመድ በግቢው ውስጥ ለሚገኘው ካፍቴሪያ የሦስት በሬ ሂሣብ ዋጋ በመክፈል እስከመጨረሻ ድረስ ጥያቄያቸው መልስ እስከሚያገኝ ድረስ የናንተ ጥያቄ የአወልያ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን አገር አቀፍ ጥያቄ ነው መልስ እስኪያገኝ ጊዜ ድረስ እምትፈልጉትን ያው እስፖንሰር አድርጌላችኋለው ለስላሳውም ኃይላንዱም ምግቡም አለ በሚል ሁኔታ በማበረታታት አሁን ለወላጆች ድጋሚ ጥሪ ይደረጋል ጥሪ በሚደረግበት ጊዜ ጥሪ ይደረጋል ጥሪው ምንድን ነው ልጆች ናቸው ተማሪዎች ናቸው እላ አመፁን ያፋፍሙ የነበሩ ናቸው ለቤተሰቦቻቸው ስልክ የሚደውሉት እና መውጣት ስላልቻልን አሁንም የለሊት ልብስ ይዛችሁልን ኑ ከዛ በኋላ በቃ አጠቃላይ ከ12 ሰዓት ጀምሮ እስክ ምሽቱ 2 ሰዓት ድረስ ሕዝቡ ሲጓዝ ብርድልብስ ጋቢ ይዞ ይመጣል ጋቢ ብርድልብስ ከለከልናቸው ስንከለክል አይ ይመልሱና ቀጥታ የዛ ት/ቤት የአዳር ተማሪዎች ብርድልብስ ፍራሽ ነበር እሱን እየተሸከሙ መስኪዱን ጢቅ አርገው ሞልተውታል እና ያ የታረደው በሬ ያደረው ሕዝብ ሁሉ ሲመገብ ነው ያደረው ማለት ነው
- እሺ ይሄ ማለት ታህሳስ ወር 2004 ዓ.ም. ነው ከዛስ?
- ከዛ ያው ሕዝቡም ሰውም እየጨመረ አመፁም እየተፋፋመ መጣ በማግስቱ በሚቀጥለው በጥር 11 አካባቢ እለቱ ጁምአ ነው በመጀመሪያ ደረጃ ሳቢር ቅድም የገለጽኩትን ቃል ሊሕዝቡ ገለፃ አደረገ በመቀጠል ጥር 11 ቀን 2004 ያሲን ኑሩ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሹፌር በሌለው መኪና ውስጥ ይገኛሉ ሹፌሮቹ ወይም መንጃ ፍቃድ የላቸው የፎርጂድ መንጃ ፍቃድ ሙስሊሙን አሳፍሮ እያጋጨት ይገኛሉ
- ማን ናቸው ሹፌር የሚላቸው ያሲን ኑሩ ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንግዲህ እራሳቸው ሊፈቱት ይቻሉ አቶ ያሲን ኑሩ መጅሊሶችን ይመስለኛል የመጅሊስ አመራሮችን ይመስለኛል ከዛ በኋላ ያው እያጋጨት ይገኛሉ እኛ ሕዝባችንን መንግስታችንን በካርድ እንደመረጥን ሁሉ መጅሊሳችንን የመምረጥ እድል ይሰጠን የሚል ለሕዝቡ ይቀሰቅሱ ነበር እነ ቢላል ሐበሺ ለዲኑ ሲል በጠራራ ፀሐይ በአሸዋ እየተጎተተ ሕይወቱን ያሳለፈው ለዲን ሲል ነው
- ምን የሆነው?
- ለእምነቱ ለዲኑ ሲል ነው ሕይወቱ ያለፈው በጠራራ በአሸዋ ላይ እየተጎተተ
- ስለዚህ?
- ስለዚህ የሱን ፈለግ መከተል አለብን የሚል ቅስቀሳ ነውአሁንም ከታህሳስ 19 ቀን 2004 እንጮሃለን በደል በዝቶብናል መጅሊሳችንን ተነጥቀናል መሰብሰቢያችንን አጥተናል ለሁለት የኢትዮጵያ ታላላቅ ሚኒስሮች መልእክት አስተላልፌያለሁ የአክሱም ሃውልት ለኢትዮጵያውያኖች እንደተመለሰ ሁሉ መጅሊሳችን ለእኛ እንዲመለስልን ኢትዮያ የሚጠቅማት ጥሬ እቃ እንጂ ሃበሽን አደለም ኤክስፖርት የምታደርገው ይሄ ሁለቱ ቃላቶች ለሁለት ታላላቅ ሚኒስትሮች አስተላልፌያለሁ የሚል ለሕዝቱ ሲናገር ነበር
- እሺ አህመዲን ጀበልስ?
- አህመዲን ጀበል በጥር 19 ቀን 2004 ያልወከልናቸው የመጅሊስ አመራሮች አይመሩንም ከመጅሊስ ብዙ ጊዜ መጅሊሶች የሚጽፉት ደብዳቤ ከሦስት መቶ ገጽ በላይ አንብቤያለሁ በእጄም ይገኛል ብዙ ጊዜ የሚጽፉት ደብዳቤ መድረሳዎች ይዘጉልን የቁርአን ውድድሮች ይቁሙ ለእከሌ ምን የፖለቲካ ስም ሰጥተን እናሳስረው የሚል ደብዳቤ አንብቤያለሁ 2ኛ መጅሊስ ሙስሊሙን እንመራለን ብለው የተቀመጡ የመጅሊስ አመራሮች እንኳን ሙስሊሙን ሊመሩ አይደለም እድር መምራት የማይችሉ ምርጫችን በመስኪዳችን ይሁን የመንለው የተደራጁ ወሮ በሎች ቦዘኔዎች እንደ አሁኑ መጅሊስም ስልጣን ላይ ጉብ እንዳይሉ በመፈለጋችን ነው የሚል ነው ሌላ ሃበሽ በተለያየ አለማት በተለይ በሳኡዲ ኡለማዎች ቁርአን የአላህ ቃል አደለም ማለቱ አጋልጦታል ነው የሚለው ሃበሽ የተቋቋመው በእስላም ጠላት ሃገሮች ገንዘብ ነው ጉቦ መብላት ጉቦ መስጠት ይፈቀዳል ይወደዳልም ብሎ የሚቀሰቅስ ነው የሚል በግልጽ ሲናገር ሰምቻለሁ
- አህባሽ የሚባል ኃይማኖት አለ እንዴ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አህባሽ የሚባል ኃይማኖት የለም እስከ አሁን ድረስ አልሰማሁም ከነሱ ቃል ነው የሰማሁት
- ጥሩ ወደ ጀማል ያሲን እንሂድ ቅድም ጀማል ያሲንን አውቀዋለሁ ብለዋል ምን ሲያደርግ ነው የሚያውቁት?
- ጀማል ያሲንን አውቀዋለሁ ሲናገር እንኳን አልሰማሁትም ልክ እረኛ ከብቶችን እንደሚነዳ ወይ ፍየሎችን አንደሚረዳ ተማሪዎች ላለማመጽ ላለመረበሽ ሁኔታው አስፈራርቷቸው በሚደበቁ ጊዜ ከተደበቁበት ያወጣቸዋል ትንሽ /ግልጽ ያልሆነ/ እንዳይወጡ ይከለክላል እና እየገፋፋ ያው
- የት ነው ይዜንን የሚያደርገው?
- እዛው አወልያ ቅጥር ግቢ ውስጥ
- አንድ ቀን ነው እንደዚህ አያረገው?
- ያው ዘወትር ነው በዚህ በጁመአ ወቅት ነው እንግዲህ ሌላ ጊዜ ሳይሆን በጅምአ
- ጁምአ ማለት ?
- ጁምአ አርብ ማለት ነው በአርብ ከሰላት በኋላ ነው
- ዘወትር አርብ አሁን የተናገሩትን ነገር ይፈጽም ነበር ጀማል ያሲን ምንድን ነው ጀማል የሲን?
- ጀማል ያሲን ብዙም ከመጅሊስ ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ከዋና ቢሮ በተቀያሪ ጥበቃዎች ተቀይሬ ለአጭር ጊዜ ስለሄድኩ ሲወራ የምንሰማው አስተማሪ ነው የሚል እሰማለሁ
- ጥሩ ቅድም በስም ከጠቀሷቸው ሰወች መሃል አንደኛው ሙባረክ ነው ?
- ሙባረክ ብዙ ጊዜ የተማሪዎች አስተናጋጅ የሚል ታፔላ እዚህ ላይ ይለጥፋል እኛ ሰወችን ተቆጣጥረን ችግር እንዳይፈጠር ሰወችን በተርታ እየተቆጣጠርን በአንድ በር ለማስገባት በምናደርግበት ወቅት አራቱም በር እንዲከፈት ያስደርጋል አራቱን ትላልቅ በሮች
- ለምን?
- በቃ ሁሉም ሰው እንዲገባ ምክንያቱም የአመፁ ብዛት እንደሚሆን ይመስለኛል በአራቱም በር እንዲገባ ስንከለክል ከእኛጋር ግብግብ ነው የሚፈጥረው ጁምአ ተሰግዶ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚቀሰቅሰው ተቀስቅሶ ሰው ጁምአ ተሰግዶ ሕዝቡ ሊወጣ ሲል አራቱም በር እንዲዘጋ ያደርገዋል

- ለምን?
- ሰው እንዳይወጣ
- ወደ ውጭ?
- ወደ ውጭ እንዳይወጣ
- ውስጥ ሆኖ ምን እንዲያደርግ ?
- ወደ ውጭ እንዳይወጣ ሰው ይከለክላል ሚስጥሩ ይመስለኛል ያው ሰው ሳይወድ በግድ መውጫ ስለሌለው ቁጭ ብሎ የነሱ የሚደረገውን ቅስቀሳ የሚደረገውን የአመጽ እንቅስቃሴ እንዲሰማ እና ተባባሪያቸው እንዲሆን ለማድረግ ይመስለኛል
- ሌላስ?
- ሌላ በከፍተኛ ደረጃ ያው ግቢ ውስጥ ተማሪውን በመወከል የሚንቀሳቀስ አንዳንድ ሕገወጥ ጽሁፎች እንዲገቡ
- ምን አይነት ጽሁፎች ?
- አህባሽ አይወክለንም መጅሊስ ይውረድ መጅሊስ የእስራኤል ፍርፋሬ ዳቦ ለማኝ ነው ዳቦ ለቃቃሚ
- የማን?
- የእስራኤል የአይሁድ ቅጥረኞች ናቸው አይወክሉንም የሚል አንዳንድ ፋንፍሌቶች በጨርቅም በወረቀትም ይበተናል ይሰጠናል ያ ሁኔታ በሱ አማካኝነት ነው እንዲገባ የሚደረገው
- ጥሩ በወቅቱ አወልያ ላይ በነበረው እስካሁን በዘረዘሯቸው እንቅስቃሴዎች ከእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት የመጡ ሰወች ነበሩ ?
- በአንድ ወቅት የዚህ የሕዝቡን ጩኸት የመንገድ በተለይ በአርብ በተለያየ በአርብ ወቅት የመንገድ መጨናነቅ የሕዝብ በጣም መብዛት ስለሚበዛ ያ ሁኔታ ለማርገብ ከፖሊስ የተወከሉ መኮንኖች እነ ከመስተዳደር አካላት ከጠቅላይ ምክር ቤቱ ፀጥታ እና ሰላምቢሮ የተውጣጡ ሰወች ተማሪውን ሰብስበው ሲያናግሩ እናንተ አይመለከታችሁም በእኛ በዲናችን ጉዳይ አይመለከታችሁም እኛ የምንፈልገው የመጅሊስ ባለ ስልጣን ብቻ
- ከመጅሊስ የመጣው ማን ነበር በወቅቱ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በወቅቱ የመጣው የመጅሊሱ ዋና ፀሐፊ አቶ መሃመድ ሃጂ መሃመድ ሲራጅ የሚባሉ መጥተው
- ምን አረጉ መጥተው ?
- በተጠራው በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት መጥተው ሊያነጋግሩ ሲሉ ገና መድረክ ላይ ሲወጡ ውረድ ጥርስህ ያምራል ጥርስህን ልታሳየን ነው የመጣኸው ለካ ቀደም ሲል በዚህ በዋና ፀሐፊው ላይ እገታ ሊካሄድ የተጠነሰሰ ሴራ አለ እኛ አላወቅንም ቀጥታ ከመድረኩ ሲወርድ አንድ በመልክ ነው የማውቀው ስሙን የማላውቀው ሽርጥ ይዟል በሽርጡ አንገታቸውን ሊያንቅ ሲል እኔ ሱልጣን የሚባል ጥበቃ ተባብረን ያ ሱልጣን ሲስጥለው ሱልጣን ላይ ሲረባረቡ እኔ ዋና ፀሐፊውን ጉትቼ ወደ ውጭ አውጥቼዋለሁ አውጥቼ
- ምን ሊያረጉት ነበር ዋና ፀሐፊውን?
- ሊያንቁት ነዋ ሊያግቱት ነው ቀደም ብሎ ደግሞ ሳናውቀው አራት መኪና ነው ግቢ ውስጥ ያለው አራቱን ጉማ አተንፍሰውበታል መኪናው ከአንድ ሳምንት በኋላ
- እነማን ናቸው መኪናውን ያተነፈሱት?
- በቃ እዛ አካባቢ ያሉ እነማን እንደሆኑ እኛ ከተነፈሰ በኋላ አራቱም ጉማ መሬት ከያዘ በኋላ ነው ያየነው
- ማን ነው ያለው ግቢ ውስጥ?
- ግቢ ውስጥ እኛ ጥበቃዎች ነን ያለነው ሌሎች እነዚሁ አመፁን የማያፋፍሙ ወጣት ተማሪዎች እና ወጣት ሴቶት ነበሩ
- ሁሉም ተማሪዎች ናቸው ?
- ተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ከተለያየ ቦታ የመጡ ከአለም ባንክ ከአየር ጤና ከመርካቶ ከተለያየ ቦታ የመጡ ሰወች አሉባቸው ተማሪም ያልሆኑ ሰወች ነበሩ ግቢ ውስጥ
- ጥሩ ይሄን ጉማዎች ያተነፈሰው ተማሪዎች ናቸው ከውጭ የመጣው ሰው ነው?
- እንግዲህ ማን እንዳተነፈሰው ያው እዛ ያሉ ተማሪዎች ናቸው ያተነፈሱት
- ጥሩ የተማሪዎችን እንቅስቃሴ የሚመራው ታዲያ ማን ነው?
- የተማሪዎችን እንቅስቃሴ የሚመራው አቡበከር ነው አመራሩን የሚሰጠው አቡበከር አህመድ ነው አመራር የሚሰጠው ግን ከሱ ስር ተቀጽላ እየተከተለ እግር በእግር ትእዛዛቸውን የሚያስፈጽመው ሙባረክ ነበረ ሙባረክ እና ጓደኞቹ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን ጠቁመው ያሳዩት ሃያኛ ተከሳሽ ነው?
- አዎ
- ኤኬ እነ አቡበከር በዚህ በተማሪዎች እንቅስቃሴ ላይ ጣልቃ ገብተው ቅድም እንደገለፀት እስፖንሰር ያረጉ ነበር ቅስቀሳ ያረጉ ነበር ብለዋል ምንድን ናቸው እነአቡበከር ምንድን ነን ነው የሚሉት?
- ያው እነአቡበከር እንግዲህ የሚሉት ቅድም ያው በንግግራቸው ላይ በገለጽኩት አቡከር ለምሳሌ ጥር 19 ቀን 2004 መጅሊስ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ወይም መጅሊስ የኡማ ውክልና የለውም
- አዎ ገባኝ እሱን ቅድም ገለፁልኝ ምንድን ነን ነው የሚሉት እነአቡበከር ለምንድን ነው የተገኙት ምንድን ነን ነው የሚሉት?
- እነአቡከር እንግዲህ ያው የሚያገኙት ጥቅም ይኖራል በአመፁ የሚያገኙት ጥቅም ሊኖር ይችላል
- ምን አይነት ጥቅም?
- ያው ለምሳሌ በአመፁ ወቅት የሚነሱ ፊልሞች አሉ ቪዲዮዎች አሉ እና ያው እርዳታ ለመሰብሰብ ይሄን ያክል አመጽ አካሂደናል ይሄን ያክል እንቅስቃሴ አርገናል
- እሺ ምንድን ነው ተቃውሞ ቆዩ ?
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ ያዩትን ወይም የሰሙትን እንዲናገሩ እንጂ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ አደለም የመጡት አቃቤ ሕጉ ግን አሁን አስተያየት ነው እየጠየቃቸው ያሉት ምስክሩም እየመለሱ ያሉት አስተያየት ነው እና ቀጥታ ወዳዩት እና ወደሰሙት እንጂ ወደእሳቸው ሃሳብ እንዳይሆን ጥያቄውን እንዲስተካከል ብለን ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ምላሽ ስጡበት
- ያው ምስክር ተደጋግሞ እንደተገለፀው በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ ከሰማው እና ካየው የተረዳውን ነው የሚናገረው ምስክር የተረዳውን እንዲናገር ያየው እና የሰማውን ብቻ ሳይሆን የተረዳውን እንዲናገር ሕጉ ያዛል እሱ አደለም ክልክልነቱ ክልክል የሆነው ባለፈው ፍ/ቤቱ ብይን እንሰጠው ምስክሩ ማጠቃለያ እንዳይሰጥ ነው እንጂ የተረዳውን ከሚያረጉት ነገር የተረዳውን መናገር ክልክል አደለም ይሄን ነው ዋናው ምስክር

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚፈለግበትም አንደኛው አላማ የተረዳውን እንዲያስረዳ ነው ስለዚህ በተከሳሽ ጠበቃ የቀረበው አቤቱታ ተቃውሞ ውድቅ እንዲደረግልን ነው

- ብይን ሰጥተናል ጥያቄዎቻችሁን አልደገምንም ያው ጊዜ ስለሚፈጅ ጥያቄው ተገቢ ነው ብለናል ነገር ግን ምስክር ሲጠየቁ ያዩትን ያላዩ እንደሆነ ደግሞ የሰሙትን እና በግሉ ያለውን ነገር እየተው ወደ ሰሙት እና ወዳዩት ነገር
- ያየሁት ነው
- እሺ ቀጥሉ አቃቤ ሕግ
- እሺ ምስክር ካቆምንበት ይቀጥሉ እረሱት
- አሳስቧቸዋል
- እሺ ቅድም እስከ አሁን በዝርዝር ሲያስረዱ እነአቡበከር እነያሲን ኑሩ እያሉ እንዲህ እንዲህ ብለዋል እያሉ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ነገር አስረድተዋል መጀመሪያ ቅሬታ የተነሳው በተማሪዎቹ ነው እያሉ ነው እነአቡበከር ምንድን ነን ነው የሚሉት እዛ መጥተው ?
- እነአቡበከር እንግዲህ ያው በዚህ በተማሪው እንቅስቃሴ የሚያገኙት ጥቅም ይኖራል የሚል ግምት ይኖረኛል እኔ
- እሱን ቅድም አስረዱን
- አዎ
- ምንድን ነን ነው የሚሉት እነአቡበር ለራሳቸው የሚሰጡት ስም አለ?
- እነአቡበር ያው እጃችን ተጠምዝዞ የአህባሽን አመለካከት አንቀበልም ነው የአጥምቆት ስርዓትን አንቀበልም ነው መንግስት እጁ እንዳለበት አህባሽን በማስገባት እጁ እንዳለበት መገለጫዎች አሉን ነው የሚሉት
- ጥሩ አወልያ መስኪድ ላይ ብዙ መድረኮች ነበሩ አደለም ?
- ልክ ነው
- በነዛ በተደጋጋሚ መድረኮች ሌላው ሙስሊም ለምን እየወጣ መድረክ አይመራም ለምን እነአቡበር እየወጡ ይመራሉ?
- እንግዲህ እነአቡበከር የሚመሩበት ምክንያት የራሳቸው የግል ፍላጐት ይኖራቸዋል አመፁን ለማፋፋም ሁለተኛ ያው ምንድን ነው አንድ ነገር አለ አሁን በአገራችን ውስጥ ልማት ዲሞክራሲ አለ ይሄ ልማት ዲሞክራሲ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሃጂ ጊሳ ቆይ ያቁመ ሕዝቡ የመረጠው ሰው አለ ?
- የለም
- ተመረጥኩ የሚልስ አካል አለ?
- ያው ተመራጮች ነን ነው የሚሉት ማን እንደመረጣቸው ግን አናውቅም
- እነማን ናቸው እንዲህ የሚሉት?
- ያው አሁን የጠቀስኳቸው እነአቡክር
- ጥሩ እነአቡክር ተመራጮች ነን ይላሉ?
- አዎ
- የት ነው የተመረጥነው ይላሉ?
- የት እንደተመረጡ እኔ
- አደለም እነሱ የሚሉት?
- ምርጫ ካርድም ሲታደል አላየንም ሁሉንም ሲቀመጥ አላየንም
- በቃ ይበቃል ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- ዋና ጥያቄ አበቃን
- እሺ የተከሳሽ ጠበቆች
- እሺ ክላ በፊት እስቲ ማን ማን ናችሁ
- አዲስ እና ሃሊማ
- አዲስ ማን ናቸው?
- አዲስ መሃመድ እና ሃሊማ ሰኢድ
- ለምንድን ነው የምታውቁት ነገር አላችሁ?
- እዚህ ትእዛዙን በማድረስ በኩል የምንረዳው ነገር ካለ በሚል ነው
- ትእዛዙ እኮ በቃ በፍ/ቤት በኩል እንደሚደርስ ትእዛዝ ተሰጠ 1ኛ ከዚህ በኋላ አስፈቅደው ነበረ መሄድ የነበረባቸው ሌላኛው ተከሳሾች ዝም ስለሚሉ ነው እንጂ ተከሳሽ ጠበቃ ካቆመ አንድ ቀንም ቢሆን ሳይቀር ጉዳያቸውን ተከታትሎ ነው መንቀሳቀስ ያለበት ክላ ውጪ እዚህ የሚመጡት ለክርክር ሳይሆን ለሌላ ምክንያት እንደሆነ ነው የሚያሳየው አንዴ መውጣት አንዴ መግባት ይሄ ተገቢ አደለም ኤኒሃው ለማንኛውን ሲመጡ ምላሽ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ይሰጡበታል ሁለት ጠበቆች አቋርጠው ሄደዋል ለምን እንደሄዱ አልታወቀም እናንተ ያላችሁት ቀጥሉ

- ምስክር ቅድም ያሲን ኑሩ ቢላል ለዲኑ ሲል በአሸዋ ተጐተተ ይል ነበረ ብለዋል ስለየትኛው ቢላል ይናገር እንደነበረ ያውቃሉ?
- ቢላል ሃበሺ እያለ
- እርስዎ ያውቁታል ስለየትኛው ቢላል እንደሆነ?
- ቢላል ሃበሺ እያለ ነው አዎ ቢላል በሁላችንም ዘንድ እንደምናውቀው የእርስዎ ሰላዋላሰለም መዋዚል ነበረ ሳባ የሃበሻ ተወላድ ነበረው ነው ቢላል አራያ አርጐ ነው ሲናገር የነበረው
- ጥሩ ስለሱ በብዛት ሁሉም ብዙ ሙስሊም ያውቀዋል አደል?
- ስለማ?
- ስለቢላል ?
- ሁሉም ያውቀዋል
- ጥሩ ስለ ቢላል ተጐተተ ነው ያለው ለዲኑ ሲል ተጐተተ ነው ያለው አደል ?
- በጠራራ ፀሐይ በአሸዋ ላይ
- እሺ ቀጥሉ
- እሺ አቶ ጊሳ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ቅድም ሲያስረዱ የተባረሩ መምህራን ይመለሱልን የተዘጋ የቁርአን ቤት ይከፈትልን የሚለው ጥያቄያቸው መቼ ነው የተጀመረው ተማሪዎቹ?
- መቼ ነው የተጀመረው ነው ይደገምልኝ ጥያቄው
- ቅድም ሲያስረዱ የተባረሩ መምህራን ይመለሱልን የተዘጋ ቁርአን ቤት ይከፈትልን የሚል ጥያቄ አንስተው ነበረ ብለዋል ይሄን ጥያቄ መቼ ነው የጀመሩት?
- ከታህሳስ 10 ቀን እስከ 16 ባለው ጊዜ ውስጥ ጀምሮ ከዛ በኋላ ወደ መጅሊስ ጥያቄ ቅድም ሲያስረዱ መጅሊስ ነው የምሰራው በጊዜያዊነት ወደ አወልያ ተመድቤ ነበር ብለዋል እና እርስዎ ወደ አወልያ ከመሄዶ በፊት ወይም ከሄዱ በኋላ ተማሪዎቹ ወደ መጅሊስ ምን ያህል ጊዜ ጥያቄ ለማቅረብ እንደሄዱ ያስታውሳሉ?
- አላውቅም

159

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተማሪዎቹ ጥያቄያቸውን ማቅረብ ከጀመሩ በኋላ ወላጆች መጥተው የነሱን ጥያቄ ይዘው ወደ መጅሊስ መሄዳቸውንስ ያውቃሉ?
- አላየሁም
- እሺ የአካባቢው አወልያ ውስጥ ምን ምን እንዳለ ለፍ/ቤቱ ያስረዱልን መስኪድ አለ አደለም?
- አወልያ ውስጥ መስኪድ አለ
- መስኪድ አለ መስገጃ መስኪድ አለ ት/ቤትም አለ?
- አዎ
- አንድ ሰው ከቃሊቲም ይምጣ ከካራ ቆሬም ይምጣ አወልያ ሄዶ መስገድ አይችልም እንዴ?
- መብቱ ነው ይችላል
- ቅድም አቡበከር አህመድ እና የሚመሰክሩባቸውን ሰወች በዝርዝር አስረድተዋል አቡበከር አህመድን የት ነው የሚያውቁት?
- አቡበከር አህመድ የመጣው በጁምአ እለት ሳይሆን ከጁምአ ከሰላት ውጪ
- ምን አሉ?
- በጁምአ ቀን ሳይሆን እነዛን ተማሪዎችን ጥያቄያቸውን እንዲያፋፍሙ እና አመፁን እንዲያጋግሉ በጁምአ ቀን አደለም የመጣው ከጁምአ ውጪ ነው የመጣው
- እርስዎ የት ነው የሚያውቁት አቶ አቡበከርን?
- አቡበከር ብዙ ጊዜ ከመጅሊስጋ መጅሊስ ይመጣል መጅሊስ አየዋለሁ ጥሩ ግብብነትም ነበረው ከመጅሊስጋር
- እሺ መጅሊን ነው የሚያውቁት አቶ አቡበከርን ቅድም ሲያስረዱ ለተማሪዎቹ የሚሆን የምግብ መግዣ ወይም በሬ ብለው አስረድተዋል እና ይሄንን ሲሰጥ አይተዋል እርስዎ እራሶ በአይኖ አይተዋል ለበሬ መግዣ ብሎ ሲሰጥ አይተዋል ?
- እሱም እራሱ ነግሮኛል
- የት አግኝቶ ነገሮት?
- በር ላይ ተገናኝተን 2ኛ የካፍቴሪያው ምግብ አቅራቢ እና ባለ ካፍቴሪያው ይዜን ሁኔታ ተናግሯል ይሄ ደግሞ አገር ያወቀው ሕዝብ ያየው ፀሐይ የሞቀው ነው
- አቡበከር ለካፍቴሪያዎች ሲሰጥ እርስዎ አይተዋል?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- 3 በሬ እስፖንሰር አድርጌያለሁ ነው ለአወልያ ተማሪዎች እና በካፍቴሪያው በኩል እንዲመገቡ ለካፍቴሪያው ተነግሮታል
- ቅድም ሲመሰክሩ አሁን የሚመሰክሩባቸው ሰወች ላይ የተናገሩት ነገር አለ ለምስሌ ሳቢር ይርጉ አቡበክር አህመድ ያሲን ኑሩ አህመዲን ጀበል እስቲ ለምሳሌ ሳቢር ይርጉ ጥያቄያችን ሰላማዊ ነው የሚል በተመለከተ የተናገረውን የሰሙትን ለፍ/ቤቱ እስቲ ቢያስረዱልን የሰሙት ነገር ካለ?
- ጥያቄያችን ሰላማዊ ነው ሲል የሰማሁት ነገር የለም
- ሌሎችስ ከሳቢር ይርጉ ውጪ ያሉት ጥያቄያቸው ሰላማዊ እና የእምነት ጥያቄ ስለመሆኑ የተናገሩት ነገር የሰሙት የለምሳሌ ቅድም የእኛ ጥያቄ መጅሊስ ልክ የመንግስትን በካርድ እንደመረጥነው መጅሊስንም በነፃ ምርጫ እንምረጥ የሚል ነው የሚል ሲነገር ሰምቻለሁ ብለዋል ከዚህ ውጪ ሌላ ተመሳሳይ ነገር ጥያቄያቸው የመጅሊስ ምርጫ የተመለከተ ስለመሆኑ ሲናገር የሰሙት ካለ ማለት ነው?
- ለምሳሌ አቶ ያሲን ኑሩ አገራችን ከማንም በላይ እንወዳታለን ሲል ሰምቻለሁ እና ለአገራችን እንቆረቆራለን ሲል ሰምቻለሁ
- ሌሎችም ሲሉ የሰሙት ካለ ለምሳሌ አቡበክርስ ምን ሲል ሰምተዋል?
- ባልደግመው ቆንጆ ነው ቅድም የተናገርኩትን ነው አቡበክር ሲናገር የነበረው
- አይ አሁን እርስዎ ለፍ/ቤቱ ከተናገሩት ውጪ ጥያቄው የመጅሊስ ምርጫነ የተመለከተ ስለመሆኑ እና ጥያቄው ሰላማዊ እና ግልጽ የሆነ ጥያቄ ስለመሆኑ የጠየቀው ነገር ካለ የሰሙት ካለ እንዲነግሩ ነው ለፍ/ቤቱ ?
- የለውም ያው መጅሊስን
- አይ የሰሙት ከዚህ የተለየ ካለ ቅድም ገልፀውታል እሱን ከዚህ የተለየ ሰላማዊ ንግግር ካለው ነው የመጅሊስን ምርጫ ነው እያነሱ ያሉት እንጂ
- አወልያ ውስጥ እርስዎ ብቻ ኖት እንዴ በጥበቃነት የሚሰሩት?
- የጥበቃ ክፍል ኃላፊ ነኝ የቀጠናውን ኃላፊነት በኃላፊነት የተረከብኩት እኔ ነኝ የበላይነት የምቆጣጠረው አጠቃላይ ጥበቃ አወልያ ዙሪያ
- ከሰኞ እስከ አርባ እዛ ይገኛሉ እርስዎ?
- 12 ሳምንቶች ሁሉ እዛ ነበርኩ እኔ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ለምሳሌ 13 ሳምንቶች እዛ ከነበሩ የወላጅ እና ተማሪዎች ለመጅሊስ ጥያቄ አቅርበው የተሰጣቸውን መልስ በተመለከተ የሰሙትን ነገር ለምን አይነግሩንም?
- እሱ ከኔ አቅም በላይ ነው እሱ አይመለከተኝም እኔ ቀጠናውን ሁሉ ስለምቆጣጠር እንጂ ሌላ ሁኔታ ውስጥ ገብቼ የምቆጣጠረው ነገር የለም
- አሁን እኮ ለፍ/ቤቱ የተሟላ ምስል ነው መስጠት ያለቦት ቅድም የሰማኋቸው ብለው የተናገሩት አለ እና እነዚህን ተመሳሳይ ነገሮች ሁል ጊዜ አስራሦስቱን ሳምንት እዛ ከነበሩ ፍ/ቤቱ የተሟላ ምስል እንዲኖረው ሌሎች ተጨማሪ የሰሙትንም ነገር ቢነግሩ ለፍ/ቤቱ እይታ ይጠቅማል በሚል ነው
- ጥያቄውን አስተካክሉት አንደኛ አልሰማሁም እያሉ ነው አላየሁም እያሉ ነው ይሄ ግልጽ ነው ወደፊት ግን ስትጠይቁ ጠቅለል ያለ ከሚሆን የምትጠረጥሩትን ነገር ይሄ ነገር አልተደረገም ወይ ብላችሁ ለይታችሁ በዚህ ቀን ብላችሁ መርታችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ እኛ አሁን ጠቅላላ ከሆነ የሰሙት የለም ወይ እንደው ከዛ በፊት በ13 ወር ውስጥ የሚባል ከሆነ 13 ወር ሙሉ ሊያስታውሱ ነው ማለት ነው
- እሺ በአወልያ ግቢ ውስጥ 13 ወር አለሁ ስላሉ ነው የምጠቅሰው
- እኮ ይሽውሎት አሁንም ያው እንዳይደገም 13 ወር ቢኖሩም ሰው 13 እያንዳንዱን ቀን ካላሳሰቡት እንዴት ያስታውሳል ስለዚህ 13 ወር እዛ ውስጥ መርጣችሁ በዚህ ቀን እንዲህ አልተደረገም ወይ ብላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ሁሉም ጁምአዎች ላይ ነበሩ አርብ ቀን ሁሉም ጊዜ ይኖራሉ እዛ ይገኛሉ ?
- ምንጊዜም እዛው እገኛለሁ
- ተማሪዎች ጥያቄያቸውን ከጀመሩ ጀምሮ እዛ ይገኛሉ እሺ አወልያ ላይ የተሰበሰው ሕዝብ ጥያቄያችን ይሄ ነው ለመንግስት አድርሱልን ብለው በእጅ ጽሁፍ የሰው ስም ጠቅሶ ኮሚቴ ብሎ ሲመርጥ እርስዎ አልነበሩም አልሰሙም የዛኔ?
- አልሰማሁም አልመረጠም
- እግዲህ ሕዝብ ሁሉ የተከታተለው ሚዲያውን እሺ ልጠይቆት የዶ/ር ሽፈራው የፌደራል ጉዳዮች ሚ/ር እነዚህ ሰወች የሙስሊሙን ጥያቄ ይዘው መጥተዋል እና መልሳችን ይሄ ነው ብለው የሰጡትንም አልሰሙም?
- አለሰማሁኝም

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምስክር ሳቢር ጥር 11 ንግግር ሲያደርግ እርስዎ የትጋ ሆነው ነበረ የሚያደምጡት?
- እኔ አስኮ በር ላይ ነበርኩኝ ዋና በር ላይም ነበርኩኝ
- ማለት የግቢ በር ነው አስኮ በር ማለት?
- እኔ ተንቀሳቃሽ ነኝ የጥበቃ ዙሪያ ግቢውን ስለምቆጣጠር እየተሽከረከርኩ ነው ግቢውን የምቆጣጠረው ዋና በር እቆማለሁ ይሄ እኮ ንግግር የሚደረገው በትልቅ እስፒከር ፀሐይ በሞቀው በአደባባይ እኮ ነው በእስፒከር እኮ ነው የሚለቀቀው
- እሺ ጥሩ ማለት አሁን ተናገረው ብለው የጠቀሱት ነገር አለ እነዚህ ነገሮች በሚነገሩበት ሰዓት በትክክል የትጋ ወይስ አየተንቀሳቀሱ ነው የሰማሁ ማለቶ ነው ወይስ አንድ የሆነ ቦታ ቆሜ ነበር ያንን ማወቅ ፈልጌ ነው?
- ቆሜያለሁ እስፒከሩ እዛው በሬ ላይ ነው ያለው እሚለቁበት እስፒከር ላውድ እስፒከር እዛው አካባቢ ነው ያለው
- አስኮ በር ያሉት ነው አስኮ በርጋ?
- አስኮ በር ላይም በዋና በር ላይም አለ እስፒከሩ
- የትጋ ሆኖ ነበረ የሚናገረው ሳቢር?
- ሳቢር የሚናገረው ውስጥ መስኪድ ውስጥ ሆኖ ነው
- ስለዚህ ድምፁን ነው የሰሙት?
- ድምፁን ነው የሰማሁት ሲገባም እናንተ መጅሊሶች አጠፉም እያለ ነው እየሰደበን ነው እንደውም የገባው
- አሃ ምን አይነት ልብስ ነበረ የለበሰው ?
- በወቅቱ የለበሰውን ልብስ አላስታውስም
- ሳቢር ከግቢ ያው ተሳድቦ ገብቷል ብለዋል ውስጥ ገብቶ ግን ሳቢር ስለመናገሩ በምንድን ነው የሚያውቁት እርስዎ ውጪ ነው ያሉት?
- በእስፒከር አሁን ይሄን ንግግር የሚያደርግላችሁ እከሌ ነው እየተባለ በማስ ሚዲያ እያስተዋወቁ ነው የሚናገሩት የጃቢርን ድምጽ ደግሞ በይበልጥ አብረን ብዙ ጊዜ መጅሊስ ከእኛጋራ ስለሰራ ድምፁን በደምብ አውቀዋለሁ ይረዳኛል
- ሳቢርን ማን ነው ያስተዋወቀው ሳቢር ከመናገሩ በፊት ያስተዋወቀው ሰው አለ?
- ያስተዋወቀው ሰው የለም
- እራሱ እኔ ሳቢር ነኝ አለ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ፆሚቀጥለውን ንግግር ያደርግላችኋል የሚል ከውስጥ የሆነ ሰው ድምጽ
መሪ ሲያስተዋውቅ ሰምቻለሁ-

በምንድን ነው እለያለሁ ያሉት?

ቡር ፍ/ቤት የተደጋገመ ጥያቄ

ቢርን ድምጽ በተመለከተ 1ኛ ያው /ግልጽ ያልሆነ/ 2ኛ የሚያስተዋውቅ
ብዙ ቆይተናል ድምፁን ጅውቀዋለሁ ለይቼ ብለው ተመዝግቧል

ነ አቡበከር ሲናገር የት ሆነው ነው ያዩት?

: እንደውም ወደ ጀናዛ ማጠቢያው አካባቢ ነበርኩኝ የዛኔ እስፒከሩ እዛ
ል የአቡበከርን ድምጽ ብዙ ጊዜ በቁርአን በአዲስ በተለያየ ነገር
ና የአቡበከርን ድምጽ ለይቼ ስለማውቀው በመጅሊስም ሲመጣ ጥሩ
ን የሱን ድምጽ ለይቼ አውቀዋለሁ

ነው የሰሙት?

ነማሁት

ይን አላዩትም?

ኑ ያው አቡበከር የሚቀጥለውን ንግግር ያደርግላችኋል በጥሞና አዳምጡ
.

ታህሳስ ባስነሱት ጥያቄ መጅሊስ አይወክለንም ይውረድ የሚል ነገር
አደል?

ን አላነሱም መጅሊስ አይወክለንም መጅሊስ ይውረድ የሚል ድምጽ
ድም ከተጠቀሱት ተከላሾች

ነስ 16 ወደ አምስት ሰዓት መጥቶ ተማሪዎችን ሰብስቦ ሲያናግር እንዳዩ
ል እርስዎ እዛ ስብሰባው ላይ ነበሩ እንዴ?

ይ ነኝ ዋና ቢሮ የአወልያ ማስተማሪያ ቢሮ መድረክ አድርገው
ነበረው ፊት ለፊታችን ነው የሚታየን ማን እንደሚናገር ማን ምን
ያያለን የአወልያ ማስተባበሪያ ቢሮ ዋና ቢሮ ሆኖ አደለም ?
ቃል ከበሩ እርስዎ ካሉበት እስከ ማስተባበሪያ ቢሮ ?

: አይርቅም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በምን ነበረ የሚናገረው በእስፒከር ነው?
- በቃል አዎ እስፒከር የለውም
- ከ25 ሜትር ላይ ሆነው ለተማሪዎች የሚናገረውን በጆሮ ሰሙ?
- በሚገባ ሰምቼዋለሁ አዳምጨዋለሁ
- ቅድም እነዚህ ተማሪዎች ማደር ሲጀምሩ ከግቢ እንዳይወጡ አልከለከልንም ከውጭ የሚመጣው ምግብ ግን ሊመረዝ ስለሚችል ከልክለናል ብለዋል ከተሳሳትኩ ያርሙኝ ?
- ልክ ነው እያሉ ነው ጨረሳችሁ እሺ
- አቶ ጊሳ ቅድም ሲጠየቁ እነአቡበከር መመረጣቸውን አላውቅም ነበር ብለዋል መጅሊስ ስለመመረጡ ያውቃሉ በህዝብ?
- በደምብ አርጌ አውቃለሁ አንዱ መራጭ እኔ ነኝ
- መቼ?
- ከህዝበ ሙስሊሙ
- ቆዩ መቼ?
- መቼ እሱ ምን ያረግላችኋል መቼ እንደሆነ
- አይ ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ
- የተከረው ፍ/ቤት እኛ መቃሚያ አለን
- መጅሊስ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ምርጫ ያልተመረጠበት ጊዜ የለም የመረጥን ነው እየተመረጠ ነው
- መቃወሚያ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ምንድን ነው መቃወሚያው
- ያው በዋና ጥያቄ ፍ/ቤቱም እንደተከታተለው እኛ ስለመጅሊስ ምርጫ አልተወራም ምስክሩ ተከሳሾች በሕዝ እንዳልተመረጡ አውቃለሁ ሲል ጠበቃው ያንን ገልብጠው መጅሊስ በህዝብ እንደተመረጠ ያውቃሉ ወይ የሚል መጠይቅ 1ኛ ቶታሊ በዋና ጥያቄ በፍፁም ያልተነሳ ነው ስለዚህ መታለፍ ያለበት ጥያቄ ነው
- ለነገሩ ቢከፊልም ቢሆን ምስክሩ መልሰዋል ወደ ኋላም ሄዶ ያን ያህል ከእንትኑ ጋ የሚገናኝ ስላልሆነ ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- እሺ ቅድም ተማሪዎች ዋና ጥያቄ ብለው 3 ነገሮችን ተናግረዋል ከዛ ውስጥ አንዱ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

መጅሊስ አይወክለንም ያለው

ኮማሪዎችን ጨየቁ ብለው ነበረ ከላጋር አያይዘው
ተማሪዎች አላሉም ነው ያሉት

ጋል በለዋል እንዴ?

ስ በሁለት መቶ ሜትር እርቀት ላይ ነበር ብለዋል ፖሊስ ለምን

መጣም ከትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ በሁለት መቶ ሜትር እርቀት
ሩ ነው ያለው ፖሊስ
?
ሩ ለመጠበቅ
ያውቃሉ?
ነኔ አላውቅም ያው ፖሊስ ነው ይምለከተዋል በቀጠናው ለሚደረገው
ጥኖ የመድረስ የፖሊስ ግዴታ ነው
እንዳይገባ ተከለከልን ብለው ደወሉ ብለው ነበረ ለቤተሰብ ይሄን
ነው ብለዋል ወይስ ጆሮዬ ነው ማን ነው የተናገረው ለቤተሰብ?
ተማሪዎችን ሰብስቦ ከቀሰቀሰና እና አድማውን እንዲያፋፍሙ ካደረገ
በምን አይነት ማገት አለበን በሚል ሁኔታ ላይ በሚነሳ ነው እንግዲህ
ምግብ እንዳንወጣም ምግብ እንዳይገባልን ተከልክሏል ብለው
ንዲደውሉ ነው የተደረጉት
ውል ያደረገው በምን አወቁ ነው ጥያቄው?
ን እርስዎ ሲደውል አይተዋል?
አላልኩም የደወሉት ተማሪዎች ናቸው ለየቤተሰቦቻቸው ተማሪዎች
ፖሊስ እንዳገዳቸው እና እንደከለከላቸው ለማስመሰል
ለአወልያ ጥበቃ ሄድኩ ብለው ነበረ ልክ ነኝ ?

166

175

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከእርስዎ በፊት የነበሩት የት ሄደው ነው ነበሩ?
- ማን
- ጥበቃዎች የአወልያ ?
- ከኔ በፊት የነበሩት ጥበቃዎች ለሦስት ወር ኮርስ ወደ መጅሊስ ሄደው ነበረ
- የምን ኮርስ ነበረ?
- ወታደራዊ
- እሱ ምንም አይጠቅማችሁም
- እርስዎ እዛ ጥበቃ ስለነበረ ኢማሙ መባረራቸውን አያውም በሚል የአወልያ በመጅሊስ መባረራቸውን አያውቁም?
- አላውቅም
- 23 የሚሆኑ የኮሌጅ ተማሪዎች መባረራቸውን አያውቁም?
- አላወቅም
- ትምህርት ቤቱ ወይም ኮሌጁ መዘጋቱን አያውቁም ?
- አላውቅም
- ቅድም ሲናገሩ አቡበከር ዳኢ ነው እዛ አውቀዋለሁ ብለው ነበር እቲ ምን ሲያስተምር ያውቃሉ በዳኢነቱ ?
- እኔ አላስታውስም ያው ዳኢ መሆኑን ሃዲስ ይናገራል
- ሌላስ ከሃዲስ ሌላ?
- በቃ ከሃዲስ ሌላ የማውቀው ነገር የለም
- ምን አይነት ሃዲስ ሲናገር ሰምተዋል ምን አይነት ሃዲስ?
- የሚያስተምሩት የሃይማኖት ትምህርት እንደሆነ ለእኛ ግልጽ ነው
- እሺ በዚህ በሃዲስ በሚያስተምሩበት ሰዓት ቁርአን እና ሃዲስን ትጠቅሱ ነበር ?
- እ
- የሃዲስ ቁጥሮችን ይጠቅስ ነበር?
- ይጠቅሳል
- በሚያስተምሩበት ሰዓት መጥፎ ነገር ሲያስተምር ሰምተው ያውቃሉ?
- አልሰማሁም

161 187

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም አህመድ መሃመድ ሲራጅን ሊመቱት ሲሉ ያው እርስዎ እንዳዳኑት ነግረውን ነበረ መሃመድ ሲራጅ በነበረበት ስብሰባ ላይ ስብሰባው የተረበሸው ከዛ በፊት ጀማል የሚባል የመጅሊሷ ተወካይ መጥቶ ያባረርኳቸውን ተማሪዎች እመልሳቸዋለሁ ካለ በኋላ አደለም?
- እነጀማልንማ አንቀበልም ካሉ በኋላ ነው
- ምኑን አንቀበልም አሉ?
- ከመጅሊስ ባለስልጣናት ከፕሬዝዳንቱ ወይ ከዋና ፀሐፊው ውጪ ማንኛውንም መስተዳድሩንም ፖሊስንም የስራ እና ፀጥታ ኮሚቴዎችን አንቀበልም ነው ያሉት
- ጀማልን ነው ያልኩት እነሱም ብለዋል ቅድም ነግረውናል በምስክርነቶ ጀማል መጥቶ ቃል ከገባ ወዲህ ለሕዝቡ መሃመድ ሲራጅ መጥቶ ያን ቃል ሊያጥፍ ሲል አደል ሕዝቡ አልቀበልህም ያለው ?
- መሃመድ ሲራጅ ንግግርም ደህና ንግግር ከመጀመሩ በፊት ጥርስህ ያምራል ለምን ትስቅብናለህ ውረድ ከመድረክ ብሎ ነው ያስወረዱት
- ስንት ሰው አወረደው ከመድረክ ላይ?
- እንዳለ የዙህ ሲሰበሰብ የነበረው ሴቱም ወንዱም
- ምን ያህል ሕዝብ ይሆናል እስቲ አጠቃላይ ሰው መጀመሪያ አወልያ ውስጥ የተገኘው በዛን ጊዜ ?
- በወቱ እኔ ሰው አልቆጥርም ይሄን ያክል ነው ብዬ ቆጠራ ላይ አልነበርኩም
- አወልያ ሙሉ ነበር?
- አይሞላም በወቅቱ ያው ተማሪዎች እና ያው መምህራኖች ናቸው
- ቅድም ደጋፊ ከአየር ጤናም ከሌላ አካባቢ ይመጣል ብለው ነበር ያ ሁሉ ሕዝብ መጥቶ ነው ግማሽ የሚሆነው ?
- ክቡር ፍ/ቤት ጥያቄው አይደጋገም
- ይኸውሎት ምስክር ያው ሲደጋግም እኛ እናስቆመዋለን አሁን ምንድን ነው ግልጽ ለማድረግ ይገባናል ድካም አለው እረዥም ጊዜ ነው ስለዚህ ምንም ነገር ውስጡን ስሜት ውስጥ ሳይገቡ ቀስ ብለው የሚጠየቁትን ያው ለትክክለኛ ፍርድ ነው ሌላ ነገር አደለም
- ከአየር ጤና ከአለም ባንክ ከተለያየ ቦታ የመጡ ጁምአ በሚሆን ሰዓት በጁምአው ወቅት ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ በጁምአ ወቅት ሰው ይሞላ ነበረ ወይ ይሞላል ካሉ ይሞላል
- በየትኛው ቀን ነወ እስቲ
- የተለያየ ጥያቄ ላስከትል እያልኩ ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- ስለተመለሰ
- ቅድም ስለ አርብ አልነበረም ስለ ሌላ ቀን ስለተናገሩ ነው አሁን ደግሞ ጁምአ ጁምአ እራሳቸው ስላሉ ፍ/ቤቱ እንዲጠይቃቸው ነው ጁምአ ጁምአ ሕዝብ መሙላት አለመሙላት
- ቅድም ከተመለሱት ቀን ውጪ ከሆነ ያው ግልጽ አርገው ይጠይቁ
- አዎ የተከበረው ፍ/ቤት ማለት የፈለግኩት ስለ ጁምአ አልነበረም የጠየቅኪቸው አሁን ግን ጁምአ ወይም አርብ አርብ በሰላት ሰዓት ሰው ግቢውን አልፎ መንገድ አይደርስም ነበር ወይስ ግማሽ ነበረ ነው?
- በጅምአ መንገድ አልፎ አስፋልት ሁሉ ይዘጋጋ ነበረ
- እርስዎ የጀመሩ አካባቢ ይሄን ያህል ነበረ ሕዝቡ እርስዎ ስራ ሲጀምሩ ከመጅሊስ ወደዛ ሲሄዱ ሕዝቡ ይሄን ያህል መስኪዱን ሞልቶ መንገድ ሁሉ ያልፍ ነበር?
- አያልፍም ከአካባቢው ሕዝብ በስተቀር ሌላ ብዙ ሰውም አይመጣም ነበር ያው መስኪድ ብቻ
- አሁን ታዲያ ለምን መሙላት ጀመረ?
- ያው በተደረገለት በተለያየ ሁኔታ ሕዝቡ ይጠራል በዚህ ምክንያት ነው እንግዲህ
- ሕዝቡ እየደገፈ ነው የሚመጣው ?
- አየደገፈ አደለም ያው ይጠራል የመጅሊስ መርዶ የመጅሊስ መውረድ መስራች ይነገራቸዋል ተብሎ ያው በተለያየ ነገር ይጠራል ሕዝቡ ዝም ብሎ ይመጣል
- እሺ ያው የመጅሊስ መውረድ ነው ያኔ የነበረው መጅሊስ አለ አሁን?
- መቼ የነበረው መጅሊስ?
- እርስዎ በመሰከሩበት ወቅት ወይም እርስዎን እዛ የመደቡት መጅሊስ አሁን እዛ አለ?
- አሁን የለም
- የት ሄደ?
- ጊዜውን ጨረሰ ያው ወርዷል
- ጊዜው ስላለቀ ነው ወይስ ስላልተመረጠ ነው የወረደው?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይሄ ጥያቄ ብዙም የሚጠቅም አደለም ሌላ ጥያቄ ጠይቁ ስለመጅሊስ ያው ቅድም እንዳልከን አሁን ከዚህ በኋላ የምንፈቅደውን_የማይደገም ጥያቄ ብቻ ነው
- ሼህ ጊሳ አህባሽ የለም ብለው ነበረ ልክ ነኝ?
- አህባሽ የሚሉት ኧልውቅም እኛ
- አላውቅም ሳይሆን አለ የለም?
- አህባሽ አላውቅም
- አህባሽ ከሌለ ያጣላው ጉዳይ ምንድን ነው ታዲያ?
- ያው እራሳቸው ተከሳሾች የፈጠሩት ስም ይመስለኛል
- እኮ ምን አሉ እነሱ?
- ያው አህባሽ አገራችን ገብቷል ነው የሚሉት አህባሽ ማን ነው እኔ አላውቅም እኔ የማውቀው አንድ እስልምናን ነው የማውቀው
- እኮ በእስልምና ውስጥ ሆኖ ሌላ አደለም ከእስላም ውጪ ነው አላልንም ግን እስልምና ውስጥ ያለ ሌላ ዘርፍ የለም ነው አህባሽ የሚሉት እርስዎ?
- የለም አላውቅም
- ይቆዩ እስቲ አህባሽ በሚሉት ልክ መልስዋል ሌላ ካላችሁ
- እሺ ምስክር ቅድም እነአቡበክር በተለያዩ መድረኮች ሲመሩ ታይተዋል ግን አልተመረጡም ብለዋል
- እስቲ ጥያቄው ግልጽ ያርጉላቸው
- እነአቡበክር በተለያዩ መድረኮች ሲመሩ ታይተዋል ግን አልተመረጡም እያሉ ነበር ይሄን ሁሉ ሲያደርጉ የተቃወማቸው ሰው አለ እናንተ አትወክሉንም በተለያየ ጊዜ እየመጣ ይሰበሰብ የነበረው ሰው እናንተ አትወክሉንም እያለ ተቃውሞ አድርጓል እንዴ ተቃውሟቸዋል ወይ ሕዝቡ ማድረጉን ያውቃሉ ?
- የተቃወማቸውን ሰው አልሰማንም
- እሺ ቅድም በዋና ፀሐፊውም በምክትል ዋና ፀሐፊውም ላይ እገታ ሊደረግ ነበረ እና እገታ ታቅዶ ነበረ ብለዋል ይሄን እንዴት አወቁ እገታ ሊደረግ ታቅዶ እንደነበረ ?
- ይሄን ያወቅኩበት ምክንያት በወቅቱ ያው ይጨርሰዋል
- አደለም በአጭሩ ንገሩኝ እንዴት አወቁ መጀመሪያ እገታ ምንድን ነው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እገታ ማለት ያው አስገድዶ አንድ ቦታ ላይ እንዳይነቃነቅ ማድረግ እና እሚፈልጉትን ለሚፈልጉት አላማ ግለሰቡ ወይም ደግሞ ባለስልጣኑ ማዋል ማለት ነው
- እሺ ታቅዶ ነበረ ይሄ ነገር ታቅዷል አሉ ቅድም ?
- እንደታቀደ ነው ምክንያቱም ከመድረክ ውረዱ ብለው ሲያስወርዱት በፎጣ ሸርጥ የያዘ ሰው መጥቶ ሊያንቀው
- እገታ ማለት እንደዚህ ማነቅ ማለት ነው ?
- ቆይ የእገታ ትርጉም በተረዱት መጠን መልሰዋል አስፈላጊ ከሆነ ማለት ነው ትርጉሙ ነገር ግን አሁን ፋክት ጀምሯል አስጨርሱ ጨርሱ አሁን የጀመሩትን
- አዎ እንግዲህ ያው ለመያዝ መጀመር እና ለማነቅ መሞከር እንደእገታ ነው የምቆጥረው ያን በርብርብ አድነን ዋና ፀሐፊውን አስወጥተናል
- እሺ ስለመታገዱ የሚያውቁት ነገር የለም ማለት ነው
- እሺ ምስክር ቅድም ሲመሰክሩ አቡበከር ሴቶችን ሰብስብ ለምን ሴቶች ብቻ ይሆናሉ ወንዶች ለምን አይቀላቀሉም ብሏል ይሄን የተናገረው የት ሆኖ ነው ?
- ሴቶች ይሄን ጥያቄያቸውን በሚያቀርቡ ጊዜ ወንዱ ፈንጠር ብሎ እንደተመልካች ይመለከት ነበር በመስኪዱ ጥላ ስር
- እኮ እሱ የት ሆኖ ነው ይሄንን የተናገረው?
- እዛው ወንዶች መሃል
- ይሄ ጥያቄ ተጠይቋል
- እሺ ወደ ያሲን ኑሩ ልሂድና ያሲን ኑሩ ለኢትዮጵያ ታላላቅ ሚኒስትሮች መልክት አስተላልፈናል ወይም ጥያቄ አቅርበናል ሲል ነበር ብለዋል ለነማን እንዳቀረበ የተናገረው ነገር አለ?
- የኢትዮጵያ ሁለት ታላላቅ ሚኒስትሮች ሁላችሁም እሱ የራሱን ሊያውቅ ይችላል ለኢትዮጵያ ሁለት ታላላቅ ሚኒስትሮች መልእክት አስተላልፏያለሁ ነው
- እኮ ምን አይነት መልእክት እንዳስተላለፈ ሲናገር ሰምተዋል?
- ያስተላለፈው መልእክት አክሱም ሃውልት ለኢትዮጵያኖች እንደተመለሰ ሁሉ የኢትዮጵያ መጅሊስም ለሙሲሊሞች ይመለስልን
- እሺ ይሄንን ሲል ለማን ነበረ ሲናገር የነበረው?
- ለሕዝቡ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሕዝቡ ምን ብሎ ምላሽ ይሰጥ ነበረ ?
- ሕዝቡማ ያዳምጣል
- እኮ ምንም ምላሽ እየሰጠ አልነበረም?
- አዎ
- የተቃወመውስ ነበረ ይሄን ሲናገር?
- እሱም ተመልሷል
- እሺ አህመዲን ምርጫችን በመስችዳችን በማለት ይናገር ነበረ ብለዋል እሱ ይሄን ካለ በኋላ ምርጫ መስኪድ ውስጥ ተደርጓል እንዴ?
- ተጠይቋል
- ምርጫው የት ነው የተደረገው የመጅሊስ ምርጫ የት ነው የተደረገው?
- ተጠይቆ ስለ ምርጫው በቃ /ግልጽ ያልሆነ/
- የተከበረው ፍ/ቤት በባልደረባዬ ክተነሳው እርእሱ
- ይሄ ተደረገ ማለት ለምርጫ /ግልጽ ያልሆነ/ ታልፏል በዋናም አልተነሳም ለማንኛውም መልሷል ግማሽ ነው ተብሎ በዛው ታለፈ
- ጀማል ያሲን ተማሪዎችን ልክ እንደ እረኛ ከግቢ እንዲወጡ ያደርግ ነበር ብለዋል በኃይል ነበር እንዴ እንዳይወጡ ሲያደርግ የነበረው የግዷቸዋል በሩን በመዝጋት ?
- እንዳይወጡ ያው ጥላ የተቀመጠውን ይመልሰው ነበር ፀሐዩ አቃጥሎት አመፁ ያልጣመው እና ያልፈለገውም ሲወጣ ሲፈልግ እንዳይወጣ ሲከላከል እመለከተው ነበር
- እረብሻ እንዳይፈጠር ያደረገው ነገር ቢሆንስ እርስዎ ይሄንን እንዴት ነው ሊያረጋግጡ የሚችሉት እረብሻ እንዳይፈጠር እያደረገ ቢሆንስ?
- እስቲ አሁን ጥያቄውን አስተካክሉት አሁን እሱ እንደዛ ከሆነ ሃሳባችሁ እንደዚህ ነበረ ወይ ብላችሁ ጠይቁ ሃሳባችሁ እንደዛ ከሆነ ትክክል ከሆነ ማለት ነው
- እሺ የመውጫ በሩን አልያዘም አደል ጀማል ያሲን?
- በሩ ላይማ እኛ አለን
- እኮ አልያዘም አደል?
- አልያዘም
- ተማሪ ከፈለገ መውጣት ይችላል አደል?

172

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከኋላ ሆኖ ይከላከላል ወደ ውጭ እንዳይወጡ
- ተማሪ መውጣት ክፈለገ መውጣት ይችላል አደል ቢፈልግ ኤሱ ከልክሎት ነው የቆመው?
- ያው እንደዛ እንግዲህ እረኛ ከብቶችን ፍየሎችን እንደሚከለክል ነበር እሽ እሽ ሲል የነበው
- እስቲ ምን ያክል ተማሪዎች
- እስቲ ቆይ ግልጽ አርጉት አሁን ከእሳቸው የተረዳነው ምንድን ነው እኛ በሩ ላይ አለን በሩ ላይ የሉም ከኋላ ሆነው ግን ተማሪዎች እንዳይወጡ ይከለክል ነበር አይነት ነገር ነው ስለዚህ ከሱ ተነስታችሁ ጠይቁ
- እሺ ምን ያህል ተማሪዎችን ነበረ እሽ እሽ ሲል የነበረው?
- አልፎ አልፎ ከመሃል የጨኸቱም እንደሁኔታው እየሰለቻቸው ሊሾልኩ የሚፈልጉ ተማሪዎች አሉ እነዛን ይመልስ ነበር
- ጠቅላላ የተሰበሰበው ተማሪ ምን ያህል ይሆን ነበር ቁጥሩ?
- ቁጥሩን አላውቀውም
- ሌላ ጥያቄ
- አዳራሽ ውስጥ ነው የት ነው የተሰበሰቡት?
- ሜዳው ላይ ነው
- ሜዳው ሞልቶ ነበር?
- ቅድም ተጠይቆ መልስ ተሰጥቶበታል
- ጀማል ያሲን ምንም አይነት ነግግር ሲያደርግ አልሰማሁም ብለዋል ቅድም በሰጡት ምስክርነት ተማሪዎቹ እንዳይወጡ ንግግር አላደረጉም ?
- ስም እየጠራ እከሌ ተመለስ ይላል
- ሙባረክ በተመለከተ በት/ቤቱ አስተዳደር የሚታወቅ የተማሪዎች ተወካይ ነው አደለም ?
- አይዞት
- እሺ
- ተወካይ ነው ?
- ማን?

123

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሙባረክ የተማሪዎቹ?
- ባጅ ተወካይነት ባጁን ለጥፎ እዚህ ላይ ያው ተማሪውን እንዳይወጣ ይከለክላል ሕዝቡም እንዳይወጣ
- የተማሪዎች ተወካይ ነበር ?
- አዎ
- አወልያ ስንት መውጫ በሮች አሉት?
- አወልያ አራት መውጫ በሮች አሉት
- ሙባረክ አራቱንም እንዳይወጣ ማድረግ ይችላል እንዴ?
- እየተንቀሳቀሰ ከሱጋር የሚሰሩ በብላይነት የሚቆጣጠሩ ተቆጣጣሪዎችን አመራር ነው የሚሰጠው አንዱን ተው ሲል ሌሎቹን ደግሞ ለሚመድባቸው ሰወች መልክት ይልክ ነበር
- እሺ የመጨረሻ አንድ ጥያቄ ልጠይቆት አወልያ አስራሦስቱንም ሳምንቶች ነበርኩኝ ሕዝብ ይሰባሰብ ነበር ጁምአ ብለዋል ሕዝብ ተሰባስባ በሰላም ነው አደል ሲለያይ የነበረው?
- አዎ በሰላም ነው ሲለያይ የነበረው እሱ
- እሺ አመሰግናለሁ
- ጨረሳችሁ
- ጨርሰናል
- እሺ አቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ ካላችሁ
- አለን
- እንግዲህ አህን ሄደናል በኋላ ፍ/ቤቱ የሚጠይቅላችሁ ካለ አሳስቡ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ፍ/ቤቱ እንዲያጣራልን
- ቆይ ቆይ በኋላ ነው የምታነሱት አሁን አልፈናል ወደ አቃቤ ሕግ
- እሺ
- ሃጂ አሁን መጨረሻ ላይ ሲጠየቁ አርብ አርብ ተሰብስቦ ምእመኑ ይመለስ ነበረ ወይ በሰላም ተብለው ሲጠየቁ አዎ ብለዋል በሰላም ተጠናቀቀ እንዴ ይሄ 13 ሳምንቱ?
- በሰላም አደለም በሰላም ማሉቱ የሰው መደብደብ የድንጋይ መወራወር የሰው ሞት የሰው አደጋ አልገጠመም ግን ከሰባት ሰዓት ጁምአ ሰላት አብቅቶ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ተክቢራ ሲባል መጅሊስ ሲወገዝ ሃበሽ ሲወገዝ ይውላል በጨኸት አካባቢውን የሚደባልቅ ጨኸት

- አሁን ያሉት በሰው አካል ላይ ጉዳት መድረስ በንብረት ላይ ጉዳት መድረስ የደረሰበት አያውቁም ?
- እስከ አሁን በሰው አካል ላይ ጉዳት የደረሰበትን እስከ አሁን አላጋጠመኝም አላየሁም
- እሺ ሃጂ ጊሳ አወልያ ውስጥ በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት አለ አወልያ ውስጥ ?
- አወልያ ውስጥ በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት በየወቅቱ ቧንቧዎች ይሰበሩ ነበር ውሃ ቧንቧዎች 2ኛ በብሎኬት እና በውድ ዋጋ የተሰሩ ግንቦች ላይ ሚስማር እያመጡ የማይረባ ወረቀት ይመታ ነበር የግድግዳው ይሰነጣጠቅ ነበር
- እሱ አሁን በግድግዳ ላይ ተበስቶ በሚስማር የተበሳ ሆን ተብሎ የሚደርስ ጉዳት ነበር የንብረት ጉዳት ?
- ሆነ ተብሎ የንብረት ጉዳት የተደረገ ነገር እስከ አሁን የለም
- እስከ መጨረሻው ድረስ የደረሰ ጉዳት የለም?
- እስከ መጨረሻ የደረሰ ጉዳት አላየሁም አልደረሰም
- እሺ ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ በፖሊስ ታግተናል እምንበላውም አጣን ብለው ስልክ የሚደውሉት ተማሪዎት ናቸው ብለዋል ተማሪዎቹ ይሄን እንዲያደርጉ የሚነግራቸው ሰው ነበር?
- እንግዲህ ተማሪዎች ይሄን እንዲያደርጉ የሚነግራቸው ቀደም ብዬ ገልጬዋለሁ እኔ አቡበከር መጥቶ ከቀሰቀሳቸው እና ከነገራቸው በኋላ ነው ያ ስልት የተነደፈው
- ጥሩ ቅድም በመስቀለኛጥያቄ ሲጠየቁ ከዛ በፊት አወልያ ብዙ ሰው አይመጣም ነበረ አሁን አንደሚመጣው አሁን ግን ግቢውን ሞልቶ አስፋልቱን ይዘጋ ነበር ብለዋል ይህ ሰው ማን ነው ጥሪ የሚያደርግለት ይሄንን በዛ መንገዱንም መስኪዱን የሚሞላው ሰው ማን ነው የሚጠራው ጥሪ የሚያደርገው ማን ነው?
- ምንድን ነው ተቃውሞው
- በመስቀለኛ ጥያቄ ስለጥሪ ምንም ያነሳነው ነገር የለም አሁን የተከበሩ አቃቤ ሕግ በጠየቁት መሰረት እኛ የሕዝቡን ብዛት ነው ለማሳየት የጠየቅነው ከዛ ባለፈ ማን ይጠራል እንዴት ተጠራ የሚል ነገር በመስቀለኛ ጥያቄ አልተነሳም ስለዚህ እሳቸው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አሁን ማን ጠራ እያሉ እየጠየቁ ስለሆነ ይሄ ደግሞ ያው ከእኛ ጥያቄ ውጪ ስለሆነ በድጋሚ ጥያቄ ሊጠየቅ አይገባም የተከበረው ፍ/ቤት

- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት የተከሳሽ ጠቦቆች ያው እኛም እንደመዘገብነው ፍ/ቤቱም ሲያዳምጥ እንደነበው ተከሳሹ ከሌላ ክ/ከተማ ከተለያየ አካባቢ መጥቶ መስገድ መብት አደለም ወይ አም መብት ነው ብዛቱን እንደ ድሮው ነበር ወይ አይ ከድሮው በጣም በብዙ እጥፍ ጨምሯል እርስዎ ከመቀጠሮ በፊት እየተባለ እነዚህ ጥያቄዎች ተደጋግመጡ የሕዝቡ ብዛት ሲነሱ ነበር ያንን መሰረት አርገን የሕዝቡ መብዛት በጥሪ ነው አደለም ወይ ጥሪውን ሲያስተላልፉ ማን ነው ብለን ነው የጠየቅነው ስለዚህ አግባብነት ያለው እና በመስቀለኛ ጥያቄም ሊስተባበል የተነሳ ነጥብ ስለሆነ እኛም ለማጣራት ነው በድጋሚ ያነሳነው
- እሺ ጊዜ ላለማባከን ቀደም ሲል በጠበቆች የተነሳ እና አግባብነት ያለው ጥያቄ ስለሆነ አቅቤ ሕግ ይቀጥሉ ብለናል
- እሺ እናመሰግናለን የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር ማን ነበረ ጥሪውን የሚያደርገው?
- ያው ጁምአ ተሰግዶ መጀመሪያ ጁምአ ተሰግዶ ሕዝቡ ከመበተኑ በፊት ሁሉም ሰው መሰብሰቢያችን አወልያ መሆን አለበት ሁሉም ሰው እንዲመጣ ጦረቤቶቹን ይዞ እንዲመጣ የሚል ከመድረክ እስፒከር ይለቀቅ ነበር
- እነማን ናቸው ይሄን የሚያደርጉት ከመድረክ ይሄን የሚለቁት?
- ከመድረክ እንግዲህ ከነዚህ ማን እንደሆነ ከመድረክ ነው እንግዲህ ጥሪ የሚተላለፈው ሕዝቡ ያን ጥሪ በጠቅላላ ሰላታችን ስብሰባችን አወልያ ላይ ነው የሚል መልክ ነው የሚተላለፈው
- እነማን ነበሩ መድረክ የሚመሩት?
- በወቅቱ ያው ቅድም የጠቀስኳቸው ሰወች ነበሩ እነአሕመዲን ጀማል ነበሩ እነሳቢር ይርጉ ነበሩ እነያሲን ኑሩ ነበረ እነአቡበክር አህመድ ነበሩ
- እሺ ይበቃል ሃጂ ድጋሚ አበቃን
- ቅድም የፈለጉት ነገር ምን እንዲጠይቁ ነው
- ቅድም የተከበረው ፍ/ቤት ስለ ጀማል ያሲን እና መ-ባረክ ስለሚባለው ልጅ መ-ባረክ በር ይዘጋ ነበረ ስላሉ የውጭውን በር ለምን ያህል ጊዜ ሲዘጋ አይተው ነው ስለማለት እና
- የትኛውን በር ነው?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የውጭው ይሄ የመስክ ደቹን ቦር ካጭ የሚሉት የግቢው የትሬኒ በር ከሰ ጌሰ በር ለምን ያህል ጊዜ መጣረክ ሲዘጋ እንዳዩ እንዲገልፁ እና ጀማል ያሲን ደግሞ በየክፍሉ ተማሪዎች ከተደበቁበት ያወጡ ነበረ ስላለ ለምን ያህል ጊዜ ሲወጡ እሳቸው እንዳዩት ይሄን እንዲገልፁልን ነው ጀማል ያሲን እና መጣረክን በተመለከተ
- አንድ በአንድ ግልጽ ከሆነሎት አጠር አጠር ያለ መልስ ስጡ
- መጣረክ በር ይዘጋል ግለቴ ላይሆን መጣረክ ሰወች እንዳይወጡ በር እንዲዘጋ ትእዛዝ ያስተላልፍ ነበር ለየቅርንጫፉ ለሚመራቸው ስነስርዓት አስከባሪዎች እነዛ በር ይዘጋሉ ሕዝብ እንዳይወጣ
- ጊዜውን ያውቁታል ለምን ያክል ጊዜ ነው?
- ለ13 ሳምንታት
- ይሄን ሲያደርግ ነበር?
- አዎ ሲያደርግ ነበር
- እሺ ወደ 2ኛ ይሰፉ ወደ ጀማል ?
- ጀማል ያሲን
- ተማሪዎችን ከተደበቁበት ያስወጣ ነበር ነው አደል ለምን ያክል ጊዜ ይሄን ይፈጽም ነበር ኤሉ?
- ያው እንቅስቃሴው እስካከተመበት ጊዜ ድረስ ያን ስራ ነበረ የሚሰራው
- እሺ ምስክር ጨርሰዋል እናመሰግናለን መመለስ ይችላሉ
- አጭር ምስክር እንደ ቅድሙ 5 ደቂቃ ይበቃናል እንደቅድሞቹ በጣም አጫጭር ምስክርነት ስለሆነ ተመሳሳይ ስለሚሆን
- ጠዋት ይሁን ብሏል ጠዋት ያው ታቀርቧቸዋላችሁ አጭር አጭሮቹን ጠዋት በብዛት ስምተን እንጨርስላችኋለን የዛሬውን በዚህ ጨርሰናል እናመሰግናለን ::

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

4ኛ ወ/ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

ጥር 29 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች ፦ ብስራት ተህልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሳሽ ፦ አቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድምአገኝ ፣ቴምድሮስ ጌታቸው ፣ዘረሰናይ ምስግና ቀርበናል

ተከሳሾች፦ እነአቡበክር አህመድ 29ኛ ተከሳሽ ቀርተዋል ሌሎቹ ቀርበዋል ጠበቆች አህመድ ጀማል ስለ 28ኛ ተከሳሽ ሃሰን ሁሴን እና ባህሩ መኮንጋ ቀርበናል

ECLN

- ከቆምንበት እንቀጥላለን አቃቤ ሕግ ምስክር
- በእውነት ለመመስከር
- በእግዚአብሔር ስም
- ምያለሁ
- እሺ ለምስክርነት ነው የመጣኸው
- አዎ
- ለምስክሮች ደህንነት ተብሎ ምስክሩ ያው የራሱን ስም ብቻ የአባቱን ስም ሳይጨምር ይግለጽ ተብሏል ሌላው አይጠየቅም
- ስምህ ማን ይባላል?
- ባህሩ
- እሺ ስንተኛ ነው አቃቤ ሕግ?

178 1767

http://ethcriminalawnetwork.com/

- 84ኛ ተራ ቁጥር
- እስከ አሁን በቀረቡት ምስክሮች በፍ/ቤቱ 22ኛ ላይ የተመዘገበ ነው በቀረበው የምስክር ዝርዝር ላይ ግን 84ኛ ላይ የተገለፀው ምስክር ቀርቧል
- በነማን ላይ ነው የምትመሰክረው?
- ስማቸውን አላውቃቸውም
- እሺ በስም አታውቅም?
- አዎ
- እሺ ምን ለመመስከር ነው?
- ያው ሐምሌ 14 ቀን አንዋር መስኪድ የነበረው እረብሻ ነበረ ምስክር ቃሌን ለመስጠት ነው የመጣሁት
- እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- እሺ ምስክር የመጣህበትን ጉዳይ በዝርዝር ታስረዳለህ ከጊዜው ትጀምራለህ ጊዜው መቼ ነው?
- ሐምሌ 14 ቀን 2004
- የት ነው?
- አንዋር መስኪድ
- እሺ አህን በጠቀስከው ጊዜ እና ቦታ ምን ሆነ?
- ስምንት ሰዓት ተኩል አካባቢ ያው ከፍተኛ እረብሻ እና ብጥብጥ ነበረ
- መጀመሪያ አንተ የት ነበርክ ምን እያረግክ ነበረ?
- እኔ እዛ ስራ ላይ ተመድቤ ሥራ ላይ ነበርኩ
- ምን አይነት ስራ ?
- ያው ወንጀል መከላከል
- ስምንት ሰዓት ተኩል ላይ ምን ተፈጠረ?
- ስመንት ሰዓት ተኩል ላይ ዙሪያውን በቃ ውስጥም
- የት?
- እዛ መስኪድ ውስጥ
- ምን መስኪድ?
- አንዋር መስኪድ
- ውስጥ ምን ተፈጠረ?
- ከፍተኛ እረብሻ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን አይነት ?
- በወቅቱ ሰግደት ነበረ እየሰገዱ ባለው ሰዓት ላይ መስገዱ ካለቀ በኋላ ሌሎቹ እየወጡ እያለ በቃ እንዳትወጡ ምናምን ብሎ ዘግተው እያሉ
- እነማን?
- እዛ ውስጥ ያሉት
- ከየት ነው የሚወጡት?
- ውስጥ ሰግደው ወደ ውጭ ሊወጡ ሲሉ
- ማን ነው የሚወጣው?
- እዛ ሰግደው የወጡ ሰወች
- እሺ ምእመናኑ ሰግደው?
- አዎ ግማሹ ይወጣል ግማሹ ደግሞ ውስጥ በቃ እንዳትወጡ ምናምን ብለው በቃ ከፍተኛ ጩኸት አሰሙ
- ማን ነው እንዳይወጡ የሚለው?
- እዛ ውስጥ ያሉት ሰወች
- እንዴት አርገው ነው እንዳይወጡ የሚሉት?
- ያው እዛ እኛ አቅራቢያ እያለ እያየን ነበረ እና እንዳትወጡ ብለው ከፍተኛ ጩኸት
- እኮ እንዴት ነው እንዳትወጡ በድምጽ ነው እንዳትወጡ ወይስ እንዴት ነው የከለከሏችሁ?
- በድምጽ
- እንጂ ሌላ ምንም አላረጓችሁም?
- ለላ በድምጽ እንዳትወጡ ምናምን ብለው ሲሉ ከዛን በኋላ ጩኸት በጣም ሲጋጋል ኃይለኛ ከፍተኛ ጩኸት ተሰማ እኛ ዙሪያውን ነበርን አካባቢው ላይ ትንሽ ዝቅ ብሎ ወደ አሜሪካን ግቢ መግቢያ አካባቢ ነበርን ከዛ በኋላ ጩኸት ተሰማ ከዛ በኋላ እኛ በወቅቱ እዛ አቅራቢያ ሆነን ስናይ በውስጥ በቃ ሆነው በቃ ድንጋይ መወርወር ጀመሩ እኛ ላይ
- እናንተ እነማን ናችሁ?
- እኛ እኔጋር ያሉት አባሎችም አሉ የፖሊስ አባሎች ናችሁ የፖሊስ አባሎች ላይ ድንጋይ መወርወር ጀመሩ ?
- ትክክል አዎ
- እሺ?
- እና እዛ ውስጥ ድንጋይ ከውስጥ መወርወር ጀመሩ ከኔጋር የነበሩ ልጆች ሁለት ሰው ተመቷል ተመቶ ከዛ በኋላ እሱን እያነሳን ባለን ሰዓት ላይ ከላይም በቃ ድንጋይ ዙሪያውን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

በቃ ድንጋይ መወርወር ጀመሩ ከዛ በኋላ አንደኛውን በጣም የተጐዳውን ሕክምና መኪና ጠርተን ሕክምና

- ማን ነው እሱ?
- አሸናፊ
- ምኑ ተመታ?
- ግምባሩ
- ምን ሆነ?
- እሱ በጣም ተመቶ በጣም ደም ፈሶ ነበረ ከዛን በኋላ እሱን ወደ ሕክምና ወሰድነው አንደኛው ደግሞ ያው ትከሻው ተመታ በዛን ሰዓት ላይ
- አንተስ?
- እኔም በግራ ወገቤ ተመታሁ
- ምንህን?
- በድንጋይ
- ምንህን?
- ወገቤን
- ምን ሆነ የተመታው ቦታ?
- በወቅቱ ቀስ በቀስ ስሜት እንትን አርጐ ነበር
- ስትመታ እንዴት ነው የተመታኸው ተወርውሮ ነው ወይስ?
- ከውስጥ የተወረወረ ድንጋይ ነው
- ከዛስ ምን ሆንክ ስትመታ?
- ስመታ በቃ እኔ በወቅቱ ያው አካባቢ ላይ በጣም ዙሪያውን ከፍተኛ ጩኸት ነበረ በጣም የተጐዳው ሕክምና እንዲሄድ አረግን ሌላውን ደግሞ ያው እኛ ደግሞ ትንሽ ያው እንትን ስለሆነ እኛ በቃ ወደስራችን ጀመርን
- ወደናንተ የሚመጡ ሰወች ነበሩ እንዴ?
- ወደእኛ ?
- እ የሚመጡ ሰወች ነበሩ ቅድም ድንጋይ ይወረውሩ ነበረ ስላልክ?
- ከውስጥ ነው የሚወረውሩት
- ገባኝ ወደናንተ የሚመጡ ሰወች ነበሩ ወጥተው ውጪ ማለት ነው?
- ከውስጥም ተወረወረ ከውጪም በቃ እየተወረወረ ነበር
- ስለዚህረ በተወረወ ድንጋይ ብቻ ነው የተመታኸው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ትክክል አዎ
- ምን አረግክ ከዛ ምን አረጋችሁ እዛ አካባቢ ያላችሁ የፖሊስ ኃይሎች?
- የትኞቹ
- እዛ አካባቢ ያላችሁ አንተን ጨምሮ እዛ አካባቢ በወንጀል መከላከል ላይ የነበራችሁ ፖሊሶች ምን አረጋችሁ ?
- እኛ በወቅቱ እያለን ከዛን በኋላ ያው ለእኛ በጣም ዙሪያዉን በቃ መርካቶ ዙሪያ አጠቃላይ ያው ሁከት ተፈጠረ ጩኸት እንዳለ በቃ ዙሪያውን ከበው ሲጮሁ ከዛን በኋላ እኛ በወቅቱ ፖሊሶቹ የተጐዱትን ሕክምና እንዲሄዱ አረግን ከዛ በኋላ ሌሎቹ ደግሞ ወደ ጣና አካባቢ ያው ባስ ተሰብሯል ተመቷል
- አይተሃል?
- አዎ በወቅቱ እዛ መንገድ እንዲሰራ የተቀመጠ ኮብልስቶን ድንጋይ በሱ እያነሱ ባሱን ሰብረው
- ምኑን ሰበሩ?
- የፊት መስታወት
- ሌላስ?
- ሌላ ደግሞ እዛ ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ ደግሞ እሱን ደግሞ ሰበሩ
- ምኑን?
- መስታወቱን ከዛ ተሰበረ በዛ ባለ ሰዓት ላይ ደግሞ እያለን ደግሞ እንዳለ እኛ ይሄ ሕብረተሰቡን እንዳለ እዛ አካባቢ ተሰባስበው በቃ እንደዛ እየጮሁ በቃ ሲሄዱ ታች ደግሞ ወደ ሲዳሞ ተራ አካባቢ ደግሞ ፖሊስ ሴንተር ሕዝቡ በቃ ለፖሊስ አገልግሎት እንዲሰጥ የተቀመጠ የተሰራ ፖሊስ ሴንተር ደግሞ መስተዋት የተሰራው ደግሞ እንዳለ በቃ ተመታ የፖሊስ ሴንተሩ
- ምን ሆነ?
- ተመታ
- ተመታ ማለት ?
- መስታወት አራገፉ
- መስታወቱ ምን ሆነ?
- መስታወቱ እንዳለ በቃ ከጥቅም ውጭ ሆነ
- የፖሊስ ሴንተር ነው?
- አዎ ፖሊስ ሴንተር

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ሌላስ?
- ሌላ በቃ
- ከዛ እናንተ መቆጣጠር ቻላችሁ?
- ከዛን በኋላ ፌደራል ፖሊስ በቃ ያው መጥቶ ከበበ ከዛ በኋላ እኛ በቃ ያው
- እናንተ መጀመሪያ በናንተ አቅም ቻላችሁ ?
- እኛ ከአቅማችን በላይ ሲሆን ፌደራል ፖሊስም መጣ እኛ ጣቢያ ካምፕ እያለሁ ኃይልም መጣ እስታፎችም አጋዥ ኃይሎችም መጡ ከዛ በኋላ
- እነማን ናቸው ይሄን ሁሉ እስካሁን የነገርከንን ድርጊት የሚፈጽሙት እነማን ናቸው?
- ያው እነማን እንደሆኑ ለይቼ አላውቅም ግን መነሻው ከመስኪድ የተነሳ ጩኸት ነው በዛ የተነሳ ነው እንዳለ ከተማው ቀውጢ የሆነው
- አዎ ቅድም ስትገልጽ ከመስኪድ ውስጥ ድንጋይ ይወረወር ነበረ ወደ ውጭ ብለሃል?
- አዎ
- እዛ አሁን ያልካቸውን እነዚህ የፖሊስ ሴንተር ባስ ባንኮችን እነዛን ሁሉ የሰበሩት ከመስኪድ የወጡት ናቸው ወይስ ሌሎች ናቸው ?
- አካባቢ ላይ የነበሩ
- ምን ይሉ ነበረ ይናገሩ የነበረው ነገር ነበር?
- አላህዋክብር እያሉ ነው እየጮሁ ድንጋይ ሲወረውሩ ነበር
- አሁን የነገርከን ማለት ምንድን ነው መነሻው መስኪዱ ውስጥ ድንጋይ ይወረወር ነበር ብለሃል ምንድን ነው መነሻው ወይም የሰማኸው ንግግር ?
- መነሻ እንግዲህ አገራቱ ላይ ሕግ የለም መንግስት ኃይማኖታችን ላይ ጣልቃ ገብቷል በሚል ነው ጩኸታችንን እናሰማ ብለው ነው ጮኸው በቃ ድንጋይ ሲወረውሩ ነበር
- ከመስኪድ ወጥተዋል ?
- ከመስኪድ አልወጡም እዛ ውስጥ ሆነው ነው
- ከመስኪድ ብቻ ነው ድንጋይ ሲወረወር የነበረው?
- ከመስኪድ ውስጥም መጀመሪያ ድንጋይ ተወርድሯል ከመስኪድ ውጭም ነው የተወረወረው
- እኮ ከእናንተጋ ምንድን ነው ያጋጫቸው?
- ከእኛጋ ምን እንደሚያጋጫቸው ግን ያው ድንጋይ ስለሚወረውሩ ነው
- ምን ስላረጋችሁ ነው እናንተ ላይ ድንጋይ የተወረወረው?
- እኛን ሲያዩ ነው ድንጋይ እኛ ስንመጣ ነው ድንጋይ መወርወር የጀመረው

183

184

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ ምን ስላረጋችሁ እናንተ ምን ወደ መስኪድ ውስጥ ገብታችኋል ወይስ ያደረጋችሁት ነገር የኃይል ተግባር የፈፀማችሁት ነገር አለ?
- ኃይል አልተጠቀምንም ውስጥም አልገባንም
- ስለዚህ ለምንድን ነው ድንጋይ የተወረወረው ነው?
- ድጋይ የተወረወረበት እንግዲህ ሕግ የለም በሚል ነው መነሻቸው
- እሺ
- ጨረሳችሁ እሺ መስቀለኛ ጥያቄ ካለ
- ምስክር ቅድም ወንጀል ለመከላከል እንደሄዱ ገልፀዋል በእለቱ ምን አረጋችሁ እንዴት ነው የተከላከላችሁት እርስዎ ሊከላከሉ ነው የሄዱት?
- እኛ ያው አካባቢ ላይ ያለን ወንጀል እንዳይፈፀም ያው እዛ እኛ የተመደብን ስራችን ነው ስራ ላይ ተመድበን ነው ስራ ስንሰራ የነበረው
- እኮ በእለቱ እንዴት አድርጋችሁ ተከላከላችሁ አልተከላከላችሁም እንዴ?
- እኛ
- እናንተ አዎ በስራ ተመድባችሁ እዛ ሄዳችሁ ድንጋይ ተወረወረባችሁ ምን አረጋችሁ ዝም ብላችሁ ቆማችሁ አይታችሁ ነው የሄዳችሁት?
- እኛ እንግዲህ በወቅቱ መከላከልም አልነበርንም የሆነ ዱላ ብቻ ነው የያዝነው ይሄ እየሸሸን የነበረው ኃይል እስከሚመጣ ድረስ
- እዛ አንዋር እስክ መጨረሻው ነበሩ ኃይል ሲመጣም ነበሩ?
- ፌደራል ፖሊስ ሲመጣ እኛ በቃ ለቀን ወደኋላ ሄድን
- ፌደራል ፖሊስ ከመጣ በኋላ ስለሆነው የሚያውቁት ነገር የለም ወዴት ሄዱ እርስዎ?
- ፌደራል ፖሊስ ከመጣ በላይ እኛ ወደላይ ሄድን መሃል አካባቢ ገባን መሃል አካባቢ ያው ባስ ተመቷል ሲባል ወደዛ ሄድን
- የት ነው መሃል አካባቢ ?
- መሃል አዳራሽ
- መርካቶ ውስጥ ነው?
- መርካቶ ውስጥ
- መሃል አዳራሽ ማለት?
- ባስ እስቴሽኑ
- እዛ በየት አቅጣጫ ነው እርስዎ የሄዱት ከባሽ እስቴሽኑ?
- እኔ በጣና በኩል ነው የሄዱኩት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከአንዋር ወደ ጣና በሚወስደው መንገድ ?
- አዎ
- እርስዎ ከሌሎች ጋር ነው የሄዱት አንድላይ ከእርስዎ ባልደረቦችጋር?
- አዎ
- እላ በሰላም ደርሶችሁ ባስ እስቴሽኑጋ ሲደርሱ ነው አደል ባስ መሰበሩን ያዩት?
- እላ ጨኸት መረጃ ተገለፀ እላ አካባቢ ቶሎ ድረሱ ተባለ እላ ደረስን ብርሃን ባንክም ተመታች አየን ከዛ በኋላ ሜትሮ ፊት ለፊት ተከምሮ የተቀመጠ ኮብልስቶን ደንጋይ እያነሱ ባሱን ሰብረው እላ ስንሄድ ወደታች ወረዱ
- አዎ ስለዚህ ከአንዋር እስከ ባስ እስቴሽኑ ድረሱ ተባላችሁ ከባልደረባዎቻችሁ ጋር በሰላም እላ ደርሳችኋል እናንተ እላጋስ ድንጋይ ይዋረውር የነበረው ከየት አቅጣጫ ነበረ የሚወረውረው ባሱ ይመታ የነበረው ከየት አቅጣጫ የነበረ ሰው ነወ ይወረውር የነበረው?
- ሜትሮ ሆቴል ፊት ለፊት
- ሜትሮ ሆቴል ማለት ምንድን ነው አሁን አቅጣጫ አለው እላ ባስ እስቴሽኑ ከአንዋር የሚመጣ መንገድ አለው ከምእራብ የሚመጣ አለው ከታች ከሲዳሞ ተራ አለ ከላይ ደግሞ አለ በየትኛው አቅጣጫ ሆኖ ነበር ድንጋይ ሰው ይወረውር የነበረው?
- ሜትሮ ፊት ለፊት
- ሜትሮ ማለት አሁን ባሎት አቅጣጫ የትጋ ነው ያለው?
- እኮ ሜትሮ ፊት ለፊት የሆነ ቅያስ አለች እላ መጨረሻ ባሱ ወደታች የሚቆምበት
- የባሱ የመጨረሻ መቆሚያጋ?
- አዎ
- እሱ አሁን ከሲዳሞ ተራ በኩል ወደላይ ወደ ባሱ ነው የሚወረውሩት?
- አዎ ሜትሮ ከፍ ብሎ ያለው ቅያስ ውስጥ ሆነው ነው እንትን ሲወረውር የነበረው
- የተመታው አንድ ባስ ነው?
- አንድ ባስ ነው
- የተመታው ባስ የትኛው እንደሆነ ያውቃሉ?
- 36 ቁጥር ነው
- የሰሌዳ ቁጥሩን አያውቁትም?
- አላውቀውም እሱን
- የተመታው የፊት ለፊት መስታወት ነው?
- የፊት ለፊት መስታወት ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን ሆነ መስታወቱ እንክትክቱ ወጣ ወይስ እዛው ላይ ተሰባብሮ ቀረ መኪናው ባሱ ላይ ነው ያለው መስታወቱ መመታት ሲባል ወይ መሬት ይወድቃል ወይ ደግሞ እዛው ተሰብሮ ይቀራል?
- ተሰብሮ እዛ ቀረ
- በኮብል እስቶን ተመቶ ማለት ነው?
- ትክክል አዎ
- ይመታ የነበረው ሰው ብዙ ነበር?
- ትንሽ ግሩፕ
- ያ ትንሽ ግሩፕ ምን ሆነ ተበተነ እናንተ ስትሄዱ?
- እኛ ስንሄድ እየጮሁ በቃ ወደታች ወረዱ
- ወዴት?
- ወደ ሲዳሞ ተራ
- ቅድም አንድ የፖሊስ ማቆሚያ ተመታለች ብለዋል መስተወት እረገፈ ብለዋል ተሳስቻለሁ ያርሙኛል ይኸው ሰው በረብሻው የፖሊሶች መቆያ የሆነች ቦታ ተመቷል?
- እንደገና
- የፖሊሶች ሴንተር መስታወቷ በድንጋይ ተሰብሯል ብለዋል ይቺ ትልቅ ነው ወይስ ስንት ሰው ነው የሚያስቀምጠው ሴንተሩ ስንት ፖሊስ ይይዛል ?
- 6 ሰው ይይዛል ቅያስ ውስጥ የተሰራ ነው
- በምንድን ነው የተሰራው በላሜራ?
- ዙሪያው በመስታወት ነው የተሰራው
- ቅድም የተከበሩ አቃቤ ሕግ ሲጠይቆት ሕዝቡ ሕግ የለም መንግስት ጣልቃ ገብቷል በኃይማኖት ብሎ ነው የሚል ነገር ተናግረዋል ይሄንን ሲባል ነው የሰሙት ወይስ እርስዎ የሰሙትን ነው?
- ከውስጥ ሆነው እንደዛ ሲሉ ነው የሰማሁት
- ማን እንዳለ አያውቁም?
- ውስጥ ያው ማን እንደሆነ ለይቼ አላወቅኩም እንዳለ በቃ መስኪድ ውስጥ ሆነው በቃ በብዛት እየጮሁ ነበር
- ባህሩ ቅድም ሲመሰክሩ ጓደኛዬ አሸናፊ ተመታ አሜሪካን ግቢ ሄደ ብለው ነበረ ድንጋይ የሚወረወረው ከአንዋር መስኪድ ነው ብለው ነበረ ከአንዋር የተወረወረ ድንጋይ ነው አሜሪካን ግቢ ሄዶ የመታቸው?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አደለም አሜሪካን ግቢ መጀመሪያ እኔ የነበርኩበት አሜሪካን ግቢ መውረጃ መንገድ አደባባዩን ነበርኩኝ ከዛን በኋላ እዛድንጋይ መወርወር ሲጀመር እኛ እዛ በሩጋ ስንመጣ አባሉ ተመታ
- ኦኬ ወደ አንዋር መስኪድ መጣችሁ እናንተ?
- ፊት ለፊት በሩጋ ሲሙሁ በቃ እኔ በቃ በጣም በከፍተኛ ጩኸት የሰማኛል እዛ ስንመጣ ከውስጥ የተወረወረ ድንጋይ አባላችን ተመታ
- ምን ለማድረግ ነበረ እናንተ የሄዳችሁት?
- ሁኔታውን ለማየት ለማረጋጋት
- ስለዚህ ስትደርሱ ምን አያችሁ ለምን ይጮሁ ነበር?
- ያው ሕግ የለም በሚል
- ሕግ የለም ስላለ ትሄዳላችሁ?
- ጩኸት ተሰማ ከሌላ ቀን ለየት ያለ ጩኸት ነው ሌላ ቀን ጩኸት ምናምን አይሰማም
- እናንት ስትሄዱ ባዶ እጅ ነበራችሁ?
- ዱላ ነው የያዝነው የፖሊስ ዱላ
- ሰው እየመታችሁ ነበረ አደለም የሚጮኸውን?
- እ?
- ሰው እየደበደባችሁ ነበረ የሚጮኸውን?
- ሰው እኛ አልመታንም
- እርስዎ ኖት ያልመቱት ወይስ ሌሎቹ አልመቱም?
- ማንም እኛ ያው እርምጃ አልወሰድንም
- ፌደራል ፖሊስ መጣ ብለው ነበረ ፌደራልስ አልወሰደም አላዩም?
- አላየሁም
- ቅድም ሰላት ከተሰገደ በኋላ ነበር ብለው ነበረ ጩኸት የተነሳው ስንት ሰዓት ነው የተሰገደው ሰላት?
- እንግዲህ ያው ሰላቱ እንግዲህ ሰባት ሰዓት አካባቢ ነው ስግደቱ ካለቀ በኋላ ነው ልክ ያው ስምንት ሰዓት ተኩል አካባቢ ነው ከፍተኛ ጩኸት የተሰማው
- በሩን ፖሊስ ለምን ዘጋው?
- አልዘጋም ፖሊስ
- እንዳይወጡ ከለከለ ፖሊስ ብለዋል ?
- ፖሊስ ሳይሆን እዛ ውስጥ ያሉት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እነማን?
- እዛ ውስጥ ያሉት ሰግደው ከወጡ በኋላ ነው ለምን ትወጣላችሁ እዛ ሆነን ድምፃችንን እናሰማለን
- በሚል ነው ያውወቃሉ እርስዎ በሚል ነው ሲሉ እንዴት ነው?
- ምን አሉ?
- በሚል ነው ለምን አሉ አውቀዋል አይተዋል አትውጡ ሲሉ አይተዋል እርስዎ ?
- እኔ እዛ አትውጡ ምናምን ብለው ውስጥ ይዘው አትውጡ ድምፃችን እናሰማ የሚል ነው እንጂ የሰማሁት እዛ የሰማሁት እንጂ እዛ ያየሁ እንጂ እኔ ለይቼ አላየኋቸውም
- በትክክል አትውጡ ሲሉ አይተዋል ወይ አይተዋል ?
- ድምጽ ነው የሰማሁት ነው የሚሉት
- የት ሆነው ሰሙ ይዜንን ድምጽ?
- የጣና በር በኩል ያለው ዋና በር
- ከታች በኩል አላዩም ?
- አዎ በዛ በኩል አላየሁም
- ይዜኛውን በር ነው የሚያወሩት?
- አዎ
- እሺ መጀመሪያ አሜሪካን ግቢ ነበሩ በኋላ ላይ ደግሞ መሃል መርካቶ ውስጥ ወደ ጣና ሄድኩ ብለው ነበረ እየተሟሟሩ ነበረ?
- አዎ
- ኃይል እስኪመጣ ድረስ ብለው ነበረ ኃይል እስኪመጣ ድረስ ዝም ብለን ቁጭ ብለን ነበር አሉ ኃይል ከመጣ በኋላ ምን ሆነ?
- እኛ ዙሪያውን ብቻችንን ነበርን የተወሰነ ትጥቅ ሰው ነን እኛ እኛ ያው ምንም ማድረግ አልቻልንም እኛ ላይ ድንጋይ ሊወረውር የተመታም ፖሊስ ያው በጣም ደም ፈሷል እሱም ወድቋል ከተመታ በኋላ ወድቋል እሱን እያነሳን ባለ ሰዓት ነው እኛ በወገባችን ተመታን ከኔጋ የነበረው ዋና ሳጅን አለ እሱም ትከሻው ተመታ ያው እዛ ሰዓት ላይ እኛ በኃይል ቶሎ ብሎ እንዲመጣ በቃ እሬዲዮ ገለጽን ከዛን በኋላ በቃ ካምፕ ያለም መጣ እስታፎቹም መጡ ትንሽ እስታፎችም መጡ ፌደራል ፖሊስም ተጭኖ ከመጣ በኋላ ለነሱ አስረክበን ሄድን
- ፌደራል ፖሊስ ምን ይዞ መጣ?
- ያው ሄልሜንት ነው
- ሄልመንት እና ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- /ግልጽ ያልሆነ/
- እሺ ማ ብርሃን ባንክ ተሰበረ ብለው ነበረ መስተዋቱ ?
- ትክክል
- በሩ ነው የተሰበረው መስተዋቱ የትኛው ነው?
- ፊት ለፊት የምታየው
- በሩ ማለት ነው?
- መስተዋቱ
- መስኮቱ ለማለት ነው መስታወት የበር አለ የመስኮት አለ?
- ፎቅ ያለ መስታወት
- እሺ ቀጥል
- የተከበረው ፍ/ቤት ፎቅ ላይ የመስኮትም አለ የበርም ምናልባት ሊኖር ይችላል እሱን ቢገልፁልኝ ብዬ ነው ፎቅም ቢሆን ?
- መስኮት ላይ ሁሉም መስታወት ናቸው እንግዲህ መስታወት ተሰብሯል ነው ያለው
- በሚለው እንሂድ
- ለይተህ የምታውቀው ነገር አለ እስቲ ግለጽ?
- ያው መስተዋት ነው ዙሪያውን በመስታወት ነው የተሰራው
- ትልቅ መስታወት ነው የተሰበረው በጠን እንሂድ ?
- ትልቅ መስታወት ነው የተሰበረው
- ከመስኪዱ ውስጥ ጩኸት ነበረ አካባቢውም ጠቅላላ ጩኸት ነበር ብለዋል?
- ትክክል ነው
- በርካታ ሕዝብ ነበረ ?
- አዎ እንዳለ በቃ ጮኽም በረንዳ ዙሪያውን በቃ ዙሪያውን እየጮኹ ነው ድንጋይ እንዳለ ሲወረውሩ የነበረው
- እርስዎ ስበሩ ፖሊስ ደብድቡ ሲባል የሰሙት ነገር አለ?
- ፖሊስ ደብድቡ ?
- ደብድቡ ስበሩ ብሎ ትእዛዝ የሰጠ ሰው የሚያውቁት አለ?
- የለም

189

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እርስዎ የምን ፖሊስ ኖት የአዲስ አበባ ፖሊስ ኖት የወረዳ?
- እሱ ቢቀርቦት ምክንያት ከገለፁ ፖሊስ ነኝ ካሉ ይበቃል ምክንያቱም ስራቸውን እስከ መጨረሻው መሄዱ ያላቸውን ከለላ የሚያሳሳ ነው የሚሆነው
- እሺ ስንት ሰዓት ላይ አቆመ ይሄ ሁሉ ነገር ?
- አቤት ?
- ስንት ሰዓት ላይ ቆመ ?
- እስከ አስር ሰዓት ነው
- እርስዎ ስንት ሰዓት ላይ ሄዱ ከዛ?
- ከዛ ለአስር ምናምን ጉዳይ ላይ ነው ፌደራል ፖሊስ የመጣው
- ተመተው እስከዛ ሰዓት ድረስ ቆዩ?
- እኔ እንግዲህ በወቅቱ ሕክምና አልሄድኩም ሌላ በጣም የተጐዳ አባል እኔ ኃይል ስለሚያንስ ብዬ እኔ ትንሽ ቆየሁ ከተረጋጋ በኋላ ነው እዛ ጣቢያ ሄጄ ክ/ከተማ አለ እዛ ክሊኒክ አለ እዛ
- ምስክር እስርዎ ወገቦን ተመቱ አሁን ታከሙ ዳኑ አደለም ከዛ በኋላ?
- ትክክል ነው
- ሌሎችስ ቅድም በድንጋይ ሁለት የተመቱ ግንባሩን የተመታ ያሉት በቃ ግንባሩን ተፈነከተ ታከመ አደል ?
- ትክክል
- አሁን ሥራ ላይ ነው?
- አንድ ወር ህክምና ተኝቶ አሁን ሥራ ላይ ነው
- ትከሻ የተመታውም በተመሳሳይ ነው?
- አዎ በወቅቱ ትንሽ ታክሞ ነው ወደ ሥራ የገባው
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ድጋሚ ጥይቄ አላችሁ
- የለንም የተከበረው ፍ/ቤት
- የፍ/ቤቱም ማጣሪያ ጥያቄ የለም ጨርሰዋል እናመሰግናለን
- እሺ ቀጣይ ምስክር
- ከ28ኛ ተከሳሽ ውጪ ለሌሎቹ
- ለሌቹ አዎ
- እሺ እንደዛ ብለው ሙሉውን አስመዝግቡ
- ጠበቃ ዳዊት ነጋሽ ከ28ኛ ተከሳሽ በስተቀር ለሌሎቹ ለሁሉም ቅርቤያለሁ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በእውነት ለመመስከር
- በእግዚአብሔር ስም
- ምያለሁ
- እሺ ለምስክርነት ነው የመጡት ዛሬ አደል?
- አዎ
- እሺ ለምስክሮች ደህንነት ሲባል ምስክሩ ያባቱን ስም ሳይጨምር የራሱን ስም ብቻ ነው የሚጠየቀው
- ዋና ሳጅን አዲሱ እባላለሁ
- እሺ ስንተኛ ነው አቅቤ ሕግ በምስክር ዝርዝር
- 111ኛ
- ከተሰሙት ምስክሮች ውስጥ 23ኛ ላይ ነው በምስክሮች ዝርዝር 111ኛ ላይ
- እሺ በነማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ዛሬ?
- በወ/ሮ ሃቢባ እና በአቶ በሼህ አብዱራሕማን
- ወ/ሮ ሃቢባ እና?
- አዎ ሃቢባ መሃመድ
- እሷ ላይ ብቻ ?
- እና ሼህ አብዱራሕማን
- እሺ ያውቁታል እነኚህን ሰወች ሁለቱን?
- አዎ
- በአካል ያውቃሉ ?
- አዎ አሁን መለየት ይችላሉ ?
- አዎ
- እሺ ይለዩልን እስቲ መለየት ካልቻሉ ያው ተነስተው መለየት ይችላሉ አሁን በተቀመጡትም መለየት ከቻሉ ያው ወ/ሮ ሃቢባ አንድ ብቻ ስላሉ ይታወቃሉ ሌላኛው ሼህ አብዱራሕማን
- ምስክሩ ያው 8ኛ እና 7ኛ ተከሳሾችን አመልክቷል
- አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ሌላ ሰው ላይ የሚመሰክሩት አለ ከሁለቱ ውጪ ?
- የለም
- እሺ ጥያቄው ይቀጥል
- ዋና ሳጅን አዲሱ ለምንድን ነው የመጡት ዛሬ ?

191

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በወ/ሮ ሃቢባ ላይ እና በሼህ አብዱራሕማን ላይ እንድመሰክር
- በምን ጉዳይ ነው እሚመሰክሩት እስቲ የሚመሰክሩትን ይንገሩን?
- የምመሰክረው እኔ ከወ/ሮ ሃቢባ ጋ በሹፌርነት እሷ ጋ መንግስት በመደበኝ እሷ ጋ ስሰራ ነበረ እና አብሬ ብዙ ቦታ እንግሄዳለን በስራ ምክንያት እና ስለሱ ጉዳይ ልመሰክር ነው
- አስቲ የመጡበትን ጉዳይ ይንገሩን አሁን ከእሳቸውጋ የነበሮትን ትውውቅ ወይም ግንኙነት ነግረውናል የመጡበትን ጉዳይ ይንገሩን ዘርዘር አርገው የተለያየ ቦታ ሄደናል ብለዋል እስቲ ዘርዘር አርገው ይንገሩን የተለያየ ቦታ ሄደናል ብለዋል እስቲ ዘርዘር አርገው ይንገሩን ?
- እና በስራ ጉዳይ የምንሄደው አሁን በተባለው በመስኪድ በምታሰራበት ሰዓት አብረን እንሄዳለን አንዳንድ ነገሮች እምትገዛቸው እቃዎች ካለ አብረን ሄደን መኪና ስለምይዝላት ሄደን እንገዛለን መስኪዱ የሚያስፈልገውን ነገር ማለት ነው
- መስኪዱ የት ነው ያለው ምንድን ነው የምትገዙት እቃ?
- የማቴሪያል የግንባታ ማሬሪያል
- ከየት ነው የምትገዙት?
- ከዚሁ ከአዲስ አበባ
- የት ነው ያለው መስኪዱ?
- መስኪዱ ያለው በገጠር ኦሮሚያ ክልል ውስጥ
- የት ?
- ወረዳውን ስሙን በደምብ አላውቅም ግን ወሮታ አካባቢ ነው በአሁኑ ስሙ አላውቀውም ወሮታ ማለት በአሁኑ በአዲሱ ስም ሌጦላ ወሮታ ወረዳ ነው የሚባለው
- ከመቼ ጀምሮ ነው እዛ ቦታ መሄድ የጀመራችሁት ከወር አመተምረቱን የሚያስታውሱት ከሆነ ?
- መስኪዱን ለማሰራት ከ2001 ጀምሮ ነው
- እሺ ምን ያህል ጊዜ ሄዳችኋል ?
- በቁጥር ይሄን ያህል የሚለው አላውቅም ስለምመላለስ እንመላለሳለን መስኪዱ በሚሰራበት ሰዓት በመሃል ላይ ለአንድ ዓመት ተኩል ተቋርጧል መስኪዱ ስራው ማለት ነው ከተቋረጠ በኋላ ሲጀመር ደግሞ እንመላለስ እና እናየው ነበር ምን ላይ ደረጃ እንደደሰ እንዴት እንደሆነ ተመላልሰን እናያለን
- ማን ነው መስኪዱን የሚያሰራው?
- ወ/ሮ ሃቢባ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማለት ማን ነው ማለቴ በገንዘብ በአጠቃላይ ስራውን የሚያሰራው በማን ወጪ እንደሆነ ይሄን የምታውቀው ነገር አለ?
- አዎ እኔ ብዙ ውስጡን አላውቅም ባገኙት ፈንድ ማለት ነው ከሳውዲ አረቢያ ባገኘችው ፈንድ ታሰራ ነበ ከዛ በኋላ
- በምንድን ነው ያወቁት ይሄንን ከሳውዲ አረቢያ በተገኘ ፈንድ ያሉት?
- ይሄን እዛ አብረን ሄደን ባለፈው ከዚህ በፊት የተቀበልነው ሐምሌ 9 ላይ ከዛ ስንወጣ
- መቼ ?
- ሐምሌ 9
- መቼ አመተ ምረት ነው?
- 2004
- የት ነው የሄዳችሁት ?
- ከሱራ በኋላ ነው ከዛ በፊትም እዛ እንገባለን አሁን የት ነው የሄዳችሁት ስንት ጊዜ ነው የሄዳችሁት ዘርዘር አርገው ይንገሩን የት ነው የሄዳችሁት?
- ወደ መስኪዱ ነው?
- ወደ አሁን ያሉት ሳውዲ አረቢያ?
- ሳውዲ አረቢያ አንድ ሦስት አራት ጊዜ የሚሆን ጊዜ ሄደናል
- የት ቦታ ነው የት ነው የሚገኘው ?
- 22 አካባቢ
- እስቲ ሦስቱንም ለምን ተግባር እንደሄዳችሁ በሚያስታውሱት ልክ ይንገሩን?
- ያው ለዚህ ጉዳይ እንሄዳለን
- ምን ምን ፈፀማችሁ?
- ያው እዛ የሚፈፀመውን ነገር ውስጥ የሚፈፀመውን እኔ አላውቅም እኔ መኪና ላይ ነው የምጠብቃት ትገባለች አትቆይም አንድ 20 ደቂቃ ቆይታ ነው የምትወጣው እና ይሄ ነው እዛ የሚያያቆያት ነገር የለም
- ስንት ጊዜ ነው ገባን ያሉት?
- ቁጥሩን አላውቅም አንድ ሦስት አራት
- ለምን ጉዳይ ነው የሚገቡት?
- ለዚሁ ጉዳይ በመስኪዱ ጉዳይ እዛ አንተ ስለምትከታተል ከዛ ፈንድ ስለሚሰጣም
- ምን ስለሚሰጣት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በምንድን ነው ያወቁት ይሄንን ውጪ ነው የምቀመጠው ብለዋል ብር ከዛ እንደሚሰጣቸው በምንድን ነው ያወቁት?
- አንድ ጊዜ አብረን ከዛ ወጥተን ለመስኪዱ የሚሆን ማቴሪያል በሲሚንቶ እነዚህ ቀለም አንዳንድ እቃ ለግምባታ የሚሆኑ እቃዎች ከዛ እንደወጣን ገንዘት ወደዛ ልከናል
- በማን በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ሲባሉ በወ/ሮ ሃቢባ እና በሼህ አብዱራህማን ብለዋል ?
- አዎ
- ሼህ አብዱራህማንን የት ነው የሚያውቋቸው?
- እኔ የማውቃቸው አብረን መስኪድ ምን ላይ እንደደረሰ ለማየት ከእኛጋ አንድ ጊዜ አብረን ሄደናል እኔ የማውቃቸው በዚህ ነው
- የት ነው የሚያውቋቸው ሲባል ?
- አብረን መስኪዱ
- አንዋር መስኪድ ነው ወይስ?
- አደለም
- የተሰራው መስኪድ ?
- የተሰራው መስኪድ ማለት ነው ምን ደረጃ እንደደረሰ
- መስኪዱ ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ?
- አዎ መስኪዱ ሲሰራ በየጊዜው ነው ፈዝ ስላለው በየፈዙ ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰለማየት አንድ 3 ጊዜ አብረን ሄደናል
- የት እየተገናኛችሁ ነው 3 ጊዜ ስትሄዱ ከየት ነው መነሻችሁ?
- እኛ የምንወጣው ከቤት ነው እሳቸው መንገድ ላይ ይጠብቁናል
- የት ነው የሚጠብቋችሁ?
- ወደ አየር ጤና አካባቢ ነው መሃል ላይ ይጠብቁናል በዛ መውጫ አለ መውጫችንም በዛው ስለሆነ በዛው እንወጣለን
- ምንድን ነው አሁን ሂደቱን እሳቸው የሚከታተሉት ለምንድን ነው ቅድም ሲነግሩን ወ/ሮ ሃቢባ ነው የሚያሰሩት ብለውናል ?
- አዎ
- እሳቸው ለምንድን ነው አሁን ሂደቱን የመስኪዱን መሰራት የሚከታተሉት ለምንድን ነው?
- የሚሰጣቸው ብር ፈንድ በትክክል ተሰርቷል ወይ ለማየት ነው እዛ ለሙዋሉ
- እሳቸው ምንድን ናቸው ሼህ አብዱራሕማን?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አላውቃቸውም እኔ በዛ ነው የማውቀው እንጂ ሌላ የማውቀው ነገር የለም
- እኮ አይ ምን ላይ እንደደረሰ ለመከታተል ነው ብለዋል 3 ጊዜ ሄዳችኋል ስለዚህ ምን ስለሆኑ ነው አሁን 3 ጊዜ ከእናንተጋ ሄደው የመስኪዱ ሁኔታ ወይም ያለበትን ሂደት የሚከታተሉት?
- የስራ ኃላፊነታቸው ምን እንደሆኑ አላውቅም ከእኛጋ መሄዳቸውን እንጂ ምን እንደሆኑ አላውቅም
- በምን ምክንያት እዛ እየሄዱ እንደሆነ አያውቁም ?
- አዎ ግን መስኪዱን አብረን አይተን እንመለሳለን
- የት ቦታ ነው የተሰራው መስኪዱ በትክክል ቦታው ማለት በማን ፍቃዱ ተሰጥቶ ፍቃድ ተሰጥቷቸው ነው ስለዚህ የሚያውቁት ነገር አለ ፍቃድ ተሰጥቶ ነው በማን ቦታ ላይ ነው የተሰራው ?
- ቦታው በባለቤታቸው በሃቢባ ባለቤት እናቱ ቦታ ላይ ነው የተሰራው
- ማን እንዴት ነው ያወቁት ይሄንን?
- ይሄንን በምርቃቱ ጊዜ እዛ በተነበበ ማለት ነው
- መቼ ነው የተመረቀው?
- ሐምሌ 8
- ስንት አመተምረት?
- 2004
- ማን ማን ነው ያስመቀረው?
- ባለቤታቸው አሉ እሷም አለች እና የተጠሩ እንግዶች አሉ
- ከየት የተጠሩ?
- ከአዲስ አበባ የተጠሩ አሉ ከአዳማ የተጠሩ አሉ የአካባቢ ነዋሪዎችም አሉ እና በዛ አካባቢ የወረዳ መስተዳድሮችም አሉ የተጠሩ እነዚህ ሁሉ በጣም ብዙ ነው
- ከዚህ ውጪ ከአገር ውስጥ ውጪ የተጠራ ሰው አለ?
- አዎ የሳውዲ አረቢያ ልዩ እንግዳ አለ ለየት ብሎ የሚታየው እሱ ነው በቃ
- የማን ተወካይ?
- የሳውዲ አረቢያ
- የሳውዲ አረቢያ ምን?
- ኤምባሲ ተወካይ እዛ የተገኘ አለ
- ከዛ የተወከሉም ተገኝተዋል ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ሌላ የወሰዳችሁት ነገር አለ ከእሳቸውጋ በሹፌርነት?
- አዎ መስኪዱን አስመርቀን ከዛ እዛ መስኪዱ ላይ ቃል በገቡት መሰረት የሳውዲ አረቢያ ኤምባሲው አምስት መቶ ቁርአን እና ሃምሳ ሺ ብር
- ሌላስ?
- ሌላ የለም
- ከየት ነው ይሄ የመጣው?
- ይሄ ከሳውዲ ኤምባሲ እሱ ሰጥቶን እሱን ይዘን ስንመጣ ነው እኛም ክትትሎች መንገድ ላይ ይዘውን እንትን ያሉን
- መቼ ነው ይሄ?
- ሐምሌ 9 ቀን 2004
- ወዴት ነበረ የምትወስዱት?
- እኛ በቃ ይሄን ተቀብለን ወደቤት ነበረ የምንሄደው ለመስኪዱ ምረቃ ተብሎ ከዚህ ከአዲስ አበባ የተከራየነው እቃ አለ ብረት ድስት ምናምን አንዳንድ ለምርቃቱ የሚሆን እሱን የተከራየነው በዛው ለመመለስ ነበር
- መስኪዱ መቼ የተመረቀ ነው?
- ሐምሌ 8
- እናንተ መቼ ነው የተያዛችሁት?
- ሐምሌ 9
- ታዲያ ለምን ጉዳይ ነበር ለምርቃቱ ነው አሁን እየወሰዳችሁት የነበረው?
- የተከራየነውን እቃ ለመመለስ ነው
- ከየት ነበረ ስትወጡ የተያዛችሁት?
- ምኑ?
- ተያዝን በክትትሎች ብለዋል ?
- አዎ
- ከየት?
- ከዛ ስንወጣ ማለት ነው
- ከየት ስትወጡ ?
- ቁርአኑን መጽሃፉን ቅዱስ ቁርአኑን እና የተሰጣትን እንትን ይዘን ስንወጣ
- ከየት?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከላ ሳውዲ ኤምባሲ
- እኮ የተከራየነው ነው ያሉት ምንድን ነው የተከራያችሁት?
- የተከራየነው ያልከነው ከዚጋር የሚገናኝ አደለም ማለት የተከራየነው እቃ እሱን በዛው ለመመለስ ነው ያልኩት
- እኮ ለያይተው ይንገሩና መጀመሪያ አምስት መቶ ቁርአን እና ሃምሳ ሺ ብር ይዘን ወጣን ብለዋል አደል?
- ከቤት ስንወጣ እቃውን ጭነን ነው የወጣነው ድስቱን ምኑን በዛው በእግረመንገድ ለመመለስ ማለት ነው ከዛው እሱን ስንመለስ በዛው ጉራ አልንና እሱን ተቀብለን ድስቱን እንደዛ በመመለስ ማለት ነው
- አንድላይ በዛው ቀን የተፈፀመ ነው እቃውንም ለመመለስ ከሳውዲ አረቢያም ደግሞ ሃምሳ ሺ ብሩን እና ቁርአኑን ይዛችሁ የወጣችሁበት ቀን ነው?
- እቃውን ይዘን ወጥተን በዛው ሳውዲ ኤምባሲ ጉራ ብለን ቅዱስ መጽሐፉን እና ቁርአኑን እና ብሩን ተቀብለን ይዘን ከወጣን በኋላ በዛው እቃውን በዛው እግረመንገድ ለማድረስ ነው ሁለቴ እቤት ከምንገባ ተባብለን ማለት ነው
- አብቅተናል ዋና ጥያቄ
- መስቀለኛ ጥያቄ ጥያቄ ካለ ቀጥሉ
- እስቲ መስኪዱን ያስገነቡት ተከሳሽ በቤተሰቦቻቸው መሬት ላይ ነው ያለው?
- አዎ
- ይህ መስኪድ ግንባታ ላይ እያለ እንሄድ ነበር ብለዋል ከዚሁ ከአዲስ አበባ ተነስታችሁ ነው አብራችሁ የምትሄዱት?
- አዎ
- በቦታው ላይ በግምባታ ላይ እያለ ተከሳሽ አብራችሁ ስትሄዱ ከማንጋር ይገናኛሉ ከገምቢዎችጋር ይገናኙ ነበር መስኪዱን ከሚገነቡ ሰወችጋር ?
- አዎ
- ሌላ ሰው አለ አብሮ የሚገናኙት ከዚህ ውጪ?
- ከዚህ ውጪ ከማንምጋር አይገናኙም
- ተከሳሽ ለግምባታ ጉዳይ መስኪዱን ለማየት አርሲ ሄጦሳ ወረዳ ነው ያሉን?
- አዎ
- እንሄድ ነበረ ብለዋል ሄዳችሁ ስታዩ ያደራችሁበት ቀን አለ ከዛንድ ቀን በላይ ያደራችሁበት አለ እዛ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በምናይበት ሰዓት አናድርም አይተን ብቻ ቶሎ እንመለሳለን
- መስኪዱ በግምባታ ላይ እያለ ኃይማኖታዊ ስብከት በመስኪዱ ተካሂዶ ያውቃል?
- አያውቅም
- የአካባቢው ሰው እዛ ተሰብስቦ ያውቃል በግምባታ ላይ እያለ?
- አዎ በግምባታ ላይ ለመርዳት
- ለግምባታ ስራ?
- ለግምባታ ስራ እዛ እርዳታ ለማድረግ በጉልበታቸው መጥተው የሚያግዙ አሉ
- ከዛ ውጪ ለኃይማኖታዊ ትምህርት ተሰብስቦ አያውቅም?
- አያውቅም
- በቦታው ላይ ተከሳሽ የግምባታ ሂደቱ ባለቀ ጊዜ ኃይማኖታዊ ትምህርት ሰጥተው ያውቃሉ ?
- አያውቁም
- ምረቃው ሐምሌ 8 ቀን 2004 ነበር ነው ያሉት?
- አዎ
- ወደ ምረቃው ከመሄዳችን በፊት እቃ ተከራይተን ከአዲስ አበባ ሄደናል ነው ያሉት?
- አዎ
- መች ነው የተከራያችሁት?
- እቃውን በውል ባላስታውስ ስለቆየ ሐምሌ 3 ተከራይተን ከአዲስ አበባ እኛ በ4 ወደዛ ሄድን አንዳንድ ነገሮችን ለማስጨረስ ለማሰራት
- ጥሩ እነዚህ የተከራያችኋቸው ወደ አርሲ ሄጦሳ ለመስኪድ ምረቃ ይዛችሁ የሄዳችኋቸው እቃዎች ውስጥ ትልልቅ ብረት ድስቶች አሉ?
- አሉ አዎ
- የእንጨት መክተፊያስ አለ?
- አለ
- የወጥ ጭልፋዎች አሉ?
- አለ
- ጮዳጓዳ ሳህኖችስ?
- አለ
- የምግብ ሳህኖችስ?
- አለ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በምረቃ ፕሮግራሙ ላይ የፌደራል ፖሊስ አባላት ነበሩ?
- አዎ አሉ
- የአካባቢው የመንግስት ባለስልጣናት ነበሩ?
- አዎ
- የወረዳው መስተዳደር አለ
- ከአዲስ አበባ የተጋበዙ ሰወች አሉ ብለዋል?
- አዎ
- ምናልባት የሚያውቁ ከሆነ የአሁኑ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ሊቀመንበር ሃጂ ኪያር መሃመድ አማን አሉ?
- እንግዲህ ያው በወቅቱ ስም ስለማላውቅ እኔ አላዉቃቸውም
- የመጅሊስ ተወካዮች ነበሩ የእስልና ጉዳይ ምክር ቤት ተወካዮችስ ነበሩ በቦታው ላይ?
- የወረዳው?
- እ?
- አዎ
- የሳውዲ ኤምባሲ ተወካይም በቦታው ላይ ነበሩ ብለዋል?
- አዎ
- መስኪዱን ለመርዳት ቃል ገብተዋል ነው ያሉን እዛ ስብሰባው ላይ ምረቃው ላይ?
- ምረቃው ላይ 500 ቁርአን እና ብሩን ለመስጠት
- ቃል ገብተዋል?
- አዎ
- ለምን ጉዳይ ነው ሃምሳ ሺ ብር እሰጣለሁ ብለው ቃል የገቡት?
- ያላለቁ ስላሉ እነሱን እንዲጨርሱበት እና እንዲያልቁ
- ለምስኪዱ ግምባታ ስራ ማለት ነው?
- ለመስኪዱ ግምባታ ስራ ማለት ነው
- 500 ያሉን ቁርአን ነው ቁርአን ማለት ምን ማለት ነው ቅዱስ ቁርአን ነው ያሉት?
- ቅዱስ ቁርአን ነዋ የሚሆነው
- የምረቃ ፕሮግራሙ በዛው እለት እንዳበቃ ወደ አዲስ አበባ ተመለሳችሁ?
- አዎ
- ወደ አዲስ አበባ ስትመለሱ ቅድም ተከራይተን ወደ ሄጠሳ ይዘን ሄድን ያሉትን እቃዎች በሙሉ ይዛችሁ ተመለሳችሁ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- እነዛን እቃዎች በ9 ወደተከራያችሁበት ቦታ ለመመለስ ነው ይዛችሁ የወጣችሁት?
- አዎ
- ከነዛ ቁሳቁሶች ውጪ የያዛችኋቸው ቁሳቁሶች ነበሩ የያዛችሁት?
- ከቤት ስንወጣ የያዝነው ቁሳቁች የለም
- ከዛ ሳውዲ አረቢያ ኤምባሲ እግረመንገድ ነው ጉራ ያላችሁት?
- አዎ
- ሳውዲ አረቢያ ኤምባሲ ገብተው ወጡ ተከሳሽ?
- አዎ
- የት ነው የተያዛችሁት?
- 22 አካባቢ
- ስትያዙ እነዛ ከሄጦሳ ይዛችሁ የተመለሳችኋቸው ቁሳቁሶች አብረው ተያዙ?
- አዎ
- እነዚህ ቁሳቁሶች አዲስ አበባ ውስጥ ከአንዋር መስኪድ እና አወልያጋር በተያያዘ አለመግባባትጋር በተያያዘ ይደረግ የነበሩ ሰደቃ ፕሮግራሞች አገልግሎት ላይ ውለዋል ?
- አልዋሉም
- እነዚህ አብረው የተያዙት ቁርአኖች እና ሃምሳ ሺ ብር መስኪዱን ለመርዳት የተደረጉ ናቸው ማለት ነው በእርስዎ እውቀት ?
- አዎ
- ተከሳሽጋር ቆይቻለሁ በሹፌርነት ብለዋለ ለረጅም ጊዜ?
- አዎ
- ወደዛ ከመምጣቴ በፊት ይቅርታ የምረቃው በአል ቀን እዛ ሄጦሳ መስኪዱ ሲመረቅ ተከሳሽ የሰጡት ኃይማኖታዊ ስብከት አለ ?
- የለም
- ሕዝብን የቀሰቀሱበት መንገድ አለ?
- የለም
- ከተከሳሽጋር ለረጅም ጊዜ አብረን ቆይተናል ብለዋል በስራ ?
- አዎ
- በዚህ በቆያችሁበት ጊዜ ተከሳሽ ለሰላት ጉዳይ መስኪድ ሲሄዱ አይተዋቸው ያውቀሉ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለክብረ በአላቸው ሲሆን ብቻ ወደ እስቴዲየም ሁለት ጊዜ ሄዱ እንጂ ከዛ ውጪ ሄደው አያውቁም
- ስለዚህ አንዋር መስኪድ እና አወልያ መስኪድ አካባቢ ሲሄዱም አይተዋቸው አያውቁም?
- አዎ
- ቅድም ከገለጽነው ኃይማኖታዊ የመስኪድ ምረቃ በስተቀር ተከሳሽ ስለ ኃይማኖት ጉዳይ አዲስ አበባ ውስጥ ተሰብስበው አይተዋቸው ያውቃሉ?
- አላውቅም
- ሰውን ሰብስበውስ አይተዋቸው ያውቃሉ?
- አላውቅም
- ተከሳሽ እንግዲህ ለረጅም ጊዜ ያውቋቸዋል ?
- አዎ
- ስለ ሌላ ሰው አመለካከት ጥላቻ ሲያንፀባርቁ አይተዋቸው ያውቃሉ ?
- አዎ የላቸውም
- አክራሪነትን አይተውባቸው ያውቃሉ ?
- አይ
- መስኪዱ ያን ቀን አገልግሎት መስጠት ሲጀምር መስኪዱ ከተመረቀ በኋላ ሄደው አይተው ያውቃሉ ?
- ከተመረቀ በኋላማ አልሄዱም ከዛ ወዲህ በቃ
- ሄደው አያውቁም ?
- አዎ በቁጥጥር ስለዋልን ሄደን አናውቅም
- ተከሳሽ ወ/ሮ ሃቢባ ከ27ኛ ተከሳሽ ሃጂ አብዱራሕማን ጋር አነድ 3 ጊዜ መስኪዱን ለማየት አብረን ወደ ሄጦሳ ሄደናል ብለዋል?
- አዎ
- ሼህ አብዱራህማን እዛ መስኪድ ላይ ኃይማኖታዊ ትምህርት ሰጥተዋል አበረዋቸው በሄዱበት ጊዜ ?
- አይ አልሰጡም
- ወ/ሮ ሃቢባ አብራችሁ መንገዱን ከመሄድ ውጪ ከወ/ሮ ሃቢባጋር ተለይተው ሕዝብ የሰበሰቡበት ጊዜ አለ ሼህ አብዱራህማን እዛ ቦታ ላይ?
- የለም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስቲ 28ኛ ተከሳሽ ላይ ብቻ የእርስዎ ጥያቄ ለ27ኛ ስላልቆሙ ማለት ነው 2ኛ ደግሞ ኦፒኒየን ጥያቄ እያበዙ ነው
- እሺ አሻሽላለሁ
- ሌላው የ27ኛ አይጠይቁ
- እሺ እዛ ቦታ ላይ ምረቃው ቦታ ላይ መውሊድ መከበሩን ያውቃሉ አሁን መስኪዱ ከተመረቀ በኋላ?
- ከተመረቀ በኋላ ወደዛ ሄጀ ስለማላውቅ
- ተከሳሽ እስላማዊ መንግስት እንመሰርታለን ብለው ሲናገሩ ሰምተው ያውቃሉ?
- አላውቅም
- መቃወሚያ አለን
- ምንድን ነው መቃወሚያው
- ማለት የተከበረው ፍ/ቤት በዋና ጥያቄ አልተጠየቀም አሁን እየተጠየቀ ያለው አሁን የተከበረው ፍ/ቤት ችሎቱም እንዳረመው ኦፒኒየኖቹንም ጭምር አሁንም እየተጠየቁ ያሉት እስላማዊ መንግስት እንደተያዘ እኛ በዋና ጥያቄ አላነሳንም በዚህ ደረጃ የሚጠየቅበት አግባብ አይኖርም
- ምስክሩ የመለሱ ስለሆነ ኦፒኒየን መጠየቁ ለእርስዎ አስፈላጊ አደለም እስቲ እዚህ ላይ /ግልጽ ያልሆነ/ ስለዚህ እሱን እዚህ ላይ እናቆማለን ነገር ግን ከምስክሩ ኦፒኒየን ይውጡ ጥያቄ አይድገሙ
- እሺ ጥያቄ አልደግምም የተከበረው ፍ/ቤት ምናልባት አሁን የምቀጥለው ጥያቄ ኦፒኒየን ሳይሆን በእርግጥ ቀዳሚው በዋና ጥያቄ ያልተነሳ ነው ግን የተከሳሽ ተነጥሎ ይታይ የሚል ክርክር ስናነሳ ተነጥሎ ሊታይ አይገባም አጠቃላይ የተያያዘ ነው የክሱ መንደርደሪያ የሆኑት እስላማዊ መንግስት መመስረት እና የመሳሰሉት ሌሎቹን ያው አልገልፃቸውም በጥያቄ የማስከትል ስለሆነ አንድ ወጥ የተያያዘ ስለሆነ ሊነጠል አይገባም በሚል ሃሳብ አቅርቦ በዛ ተኪዶበታል ይሄ ክስ የቀረበበት የጭብጥ አካል ነው እነዛን ጥያቄዎች ድጋሚ መቃወሚያ ሊያነሱ ስለሚችሉ ከአሁኑ ፍ/ቤቱን ለማስፈቀድ ነው እሚቀጥሉት ጥያቄዎቼ እነዛ ናቸው የሚፈቀድልኝ ከሆነ
- በዋና ጥያቄ ያልተነሱት?
- አልተነሱም ግን የጭብጡ አካላት ናቸው
- አሁን ለተነሳው ጥያቄ ጠበቃው እራሱ ገልጿል በዋና ጥያቄ አልተነሳም እሱን እንዳነሳ ይፈቀድልኝ ብሎ ያቀረበው ምክንያት ከሌሎቹ ተከሳሾችጋ በግብርአበርነት የተከሰሱ በመሆኑ

ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

ክሱን በዛ ምክንያት ያልታየ ስለሆነ ምስክሩ ያላነሱም ቢሆን እንዳነሳ ይፈቀድልኝ ብለው ነው ያመለከቱት ፍ/ቤቱም በዚህ ላይ የአቃቤ ሕግን አስተያየት መቀበል አልተፈለገም ምክንያቱም አልተጠየቀም ሊጠየቅ ይገባል አይገባም የሚለውን ፍ/ቤቱ እራሱ መዝኖ ብይን የሚሰጥበት በመሆኑ እና በዚህ ምክንያት ፍ/ቤቱም ብይን ሰጥቷል መዝገቡ የተያያዘው አብሮ አድኗል በሚል ነው ክሱ የቀረበው ነገር ግን ምስክሩ ስለ አዳማ አላነሱም አሁን የቀረበው ምስክር ስለ አድማ ቢያነሱ ከአድማጋር የሚያያዝ ነገር በዋና ጥያቄ ቢነሳ መጠየቅ ይችሉ ነበር ክስ የቀረበው አድመዋል በሚል ነው ምስክር ስለ አድማ አላነሱም አሁን ስለ ሁለት ሰወች ነው የመሰከሩት እርስዎ የቆሙት እዛ ውስጥ ለአንድ ሰው ነው እና አድማ ካልተያያዘ እዚህ ውስጥ የሚነሳበት ምንም ጥያቄ ስለሌለ በዋና ጥያቄ ያልተነሳውን ነገር በመስቀለኛ ማንሳት አይቻልም ስለዚህ በዚሁ እናበቃለን ሌላ ከሌለ

- እሺ እሱን አልፈዋለሁ አብረው በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ከወ/ሮ ሃቢባጋር 28ኛ ተከሳሽ ጋር ማለት ነው እርስዎ ሹፌር ነኝ ብለዋል ?
- አዎ
- ከእርስዎ ውጪ አብሮ የሚንቀሳቀስ ምን አለ አጃቢ አለ ?
- አጃቢ አለ አዎ
- ስለዚህም እያንዳንዱን የወ/ሮ አሃቢባን እንቅስቃሴ መንግስት ያውቃል ማለት ነው ?
- አዎ
- የመውሊድ በዓል አክብረው ያውቃሉ ወ/ሮ ሃቢባ በቤታቸውም ቢሆን?
- ድጋሚ ነው ይሄ ተደግሟል
- አይ የቤታቸውን የመስኪዱን ነው የቅድሙ?
- የተከበረው ፍ/ቤት
- ቆይ ቆይ የቤታቸው ስላልተነሳ ይሄን ጥያቄ እለፉት የውጪ ከሆነ ቅድም ተጠይቋል ስለቤት አልተነሳም
- እሺ ጨርሻለሁ
- ከጨረሱ እንትኑን አላስመዘገቡም የ28ኛ ተከሳሽ ጠበቃ መሆኑን ጥያቄ ተጠይቀው መስቀለኛ
- እሺ እስከ አሁን መስቀለኛ ጥያቄ ሳቀርብ የነበርኩት የ28ኛ ተከሳሽ ጠበቃ ነኝ አህመድ ጀማል
- እሺ አሁን የ27ኛ የሚቀጥለው እንደዚህ አስመዝግበው ይጀምሩ እንዳይቀላቀል
- እሺ የ27ኛ ተከሳሽ ጠበቃ ሃሰን ሁሴን ነው የሚቀጥለው ማለት ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ቀጥሉ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ዋ/ሳጅን አዲሱ ሼህ አብዱራህማን ገንዘብ በግል ለሃቢባ ሲሰጡ አይተው ያውቃሉ ?
- በእጃቸው በግል ሲሰጡ አይቼ አላውቅም
- በአይኖ አይተው አያውቁም ገንዘብ ሲሰጡ?
- አዎ
- ቅድም መስኪድ መሰራቱን ለመከታተል ይሄዱ ነበረ ብለዋል?
- አዎ
- በዚህ በጉሟቸው ወቅት አንድላይ ስትሄዱ የተለየ የተነገሮት ነገር አለ?
- ምንም የተናገሩት ነገር የለም
- መስኪዱ ላይ መጠቀም አለበት ይሄን አይነት ሰው ነው ብለው ሲናገሩ የሰሙት ነገር የለም?
- እስቲ እንደገና ይደገምልኝ
- መስኪዱ ላይ መጠቀም ያለበት ሰው እንዲህ አይነት ሰው ነው እንዲህ ነው ብለው ሲናገሩ የሰሙት ነገር የለም?
- አይ የለም
- የምረቃው ቀን ነበሩ እና የምረቃው ቀን ሰላት ተሰግዶ ነበር መስኪድ ውስጥ?
- ፕሮግራሙን ሲጀምሩ ይሁን ሲጨርሱ ይሁን አዎ ሁሉም እዛ ያሉት ሰወች ስግደት አርገዋል ስብከት ግን የለም
- ስግደት ሲያደርግ ሁሉም እዛ የተገኘው ሙስሊም ነው የሰገደው?
- አዎ
- የሰው ለውጥ አንተ አትስገድ ይሄ ስገድ የሚባል ነገር የለም?
- የለም
- ሁሉም ሕብረተሰብ ነው ?
- አዎ
- ገንዘብ ስታወጣ ከሳውዲ ኤምባሲ ያሉት ቅድም ከዛ ወጥተን እቃ ስለገዛን ነው አንድ ቀን ብለዋል?
- አዎ
- ይሄ ግምት ነው አደል?
- አዎ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቆዩ እስቲ አንዴ እህ
- ማለት አሁን እሳቸው አሁን አስመዝግበው እየጠየቁ ያሉት ሰሼህ አብዱራህማን ነው አሁን እየተጠየቀ ያለው ደግሞ ስለ 29ኛ ተከሳሽ ነው ስለዚህ በምን ተገናኝቶ ነው በዚህ አሁን በጠየቁት አግባብ ከሆነ በምን ተገናኝቶ ነው እየጠየቁ ያሉት እሳቸው ከእሳቸው ደምበኛ ይለያል አሁን እየጠየቁ ያሉት?
- የተከበረው ፍ/ቤት እኔ ጥያቄውን ያነሳሁት አቃቤ ሕግ ቅድም በግልጽ እንዳስመሰከሩት ምስክሩም እንደገለፁት መስኪዱ ሲሰራ እየሄዱ የከታተሉ ነበር ልክ መስኪዱን እነሱ እንዳሰሩ አድርገው ነው ያስመሰከሩት ስለዚህ መስኪዱ ላይ ያለውን ነገር ከክሱ ጋር ከ27ኛ ተከሳሽጋር የሚገናኝ ነገር ስላለ ነው የጠየቅኩት እና አቃቤ ሕግ ከጠየቁት ዋና ጥያቄ አልወጣንም የተከበረው ፍ/ቤት ስለዚህ ጥያቄዬ ሊታለፍ የሚችልበት ምንም የሕግ አግባብ ስለሌለ እንድጠይቅ እንዲፈቀድልኝ ነው
- ምናልባት ሳውዲ አረቢያ ሄደው እቃ የገዙት 28ኛ ተከሳሽ ነው ምስክሩ የተገለፀው እና እንዴት ከ27ኛጋ ተያያዘ የሚለው ግልጽ አደለም ነው እሱን ግልጽ ያርጉ እስቲ?
- ይኸው የተከበረው ፍ/ቤት 28ኛ ተከሳሽን ሲገልጽ ክሱ ከ27ኛ ተከሳሽጋር አገናኝቶት ነው እዚጋ ክሱን
- አይ የምስክሩ ክሱማ ነው
- አዎ ለዛ ነዋ እኔም ያነሳሁት ለዛ ነው 1ኛ ክሱ ላይ ይገናኛል በክቡ በራሱ 2ኛ ምስክሩ ከተናገሩት በዋና ጥያቄ ከተጠየቀው ነገር ጋር ስለሚገናኝ ነው አሉ
- /የማይሰማ/
- ከምስክሩ ከየትኛውጋር ነው የተገናኘው የተከበረው ፍ/ቤት ብር ከኤምባሲ እኮ ተቀብላ ወጥታለች የሚል ነገር ስላለ ነው ከእሱጋ የገናኘ ጥያቄ ነው
- ያነሱትን ጥያቄ እስቲ እንደገና ያስመዝግቡልን አውጥተው ምን ገዙ ነው እሷን አስመዝግቡ
- ምስክር ሼህ አብዱራህማን ከ28ኛ ተከሳሽ ከወ/ሮ ሃቢባጋር ወደ መስኪዱን ለማየት ሄደዋል ብለዋል?
- አዎ
- የሄዱት እርስዎ በእናንተ መኪና ነው የሄዱት?
- አዎ
- የትጋ ነው ያነሷቸው ማለት የትጋ ነው የሄዱት እነሱ?
- አብረው መስኪዱ ቦታ ማለት ነው ከየት ተነስተው ማለት ነው?
- ከዚሁ ከአዲስ አበባ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከየት ቦታ?
- ከአቃቂ የእሳቸው ከመንገድ ላይ ነው የጠበቁን እዚህ ወደ አየር ጤና አካባቢ ላይ ማለት ነው
- ጥሩ ከአየር ጤና ነው ያነሷቸው ?
- አዎ
- አብረዋችሁ ሄዱ እንጂ መስኪድ ለመቆጣጠር ይሁን አይሁን በምን አወቁ?
- ምን ላይ ደረጃ እንዳለ ለማየት እንዴት ነው ማለት እዛ ሲናገሩ ቆንጆ ደረጃ ላይ ነው ያለው በዚህ ይቀጥል አሁን ደግሞ ከተሻለ ከዚህ ፈጥኖ ይሂድ በሚሉ ሰዓት
- አስተያየት ሰጠ?
- አዎ
- እሳቸው አብረው ሲሄዱ ይታወቃሉ መሄዳቸው አደል በሌላው ክፍል ቅድም መንግስት ያውቃል ወይ ወ/ሮ ሃቢባን እንቅስቃሴ መንግስት ያውቃል ብለዋል ?
- አብሮ መንግስት ያውቃል አብሮ ስትሄድ የተመደበላት አጃቢ አለ የሚያውቀው ክፍል አካል ያውቃል
- ስለዚህ አጃቢው አልተቃወመም?
- አዎ አጃቢ ይሄዳል የቀረም አጃቢ አብሮ ነው የሚሄደው
- አሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ
- አይ አልጨረስንም አንድ ጥያቄ
- በምን ቋንቋ ነበረ የሚያወሩት?
- ቆይ ቆይ ቆይ እርስዎ አሁን መጠየቅ አይችሉም ስሞን አላስመዘገቡም የት እንደሚያውቁ አላወቅኩኝም
- እሺ አዲስ መሃመድ የተከሳሽ ጠበቆች ቀርቤያለሁ አንድ ጥያቄ ስላለኝ ልጠይቀው ፈልጌ ነው
- እሺ የተከሳሾች 2 ተከሳሾች /ግልጽ ያልሆነ/ የ27ኛ በዛው ይቀጥላል
- ቆይ እስቲ ሰምተዋል ግን በትክክል ለአቃቤ ሕግ የተነሳውን ነገር ሰምተዋል?
- እኔ መጠየቅ የፈለግኩት ያው ውስጥ ውስጡን ሲያወሩ ነበር ስላለ በምን ቋንቋ ነው የሚያወሩ የነበረው ነው እኔ የጠየቅኩት
- እሺ የ27ኛ ብለሽ አስመዝግቢና ቀጥይ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ የ27ኛ ተከሳሽ ጠበቃ አዲስ መሃመድ ቀርቤያለሁ ለምስክር ጥያቄ አለኝ በምን ቋንቋ ነበረ የሚያወሩት?
- በኦሮምኛ
- ኦሮምኛ ትሰማለህ አንተ?
- አዎ
- ጨርሻለሁ
- እሺ አቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ
- ዋ/ሳጅን በተደጋጋሚ ይሄን ነገር መንግስት ያውቃል ተብለህ ተጠይቀሃል እናንተ ለመንግስት እሪፖርት ታደርጋላችሁ ?
- እኛ እሪፖርት የምናረገው ለእኛ አለቆች ነው
- ምንድን ነው እሪፖርት የምታደርጉት የሄዳችሁበትን ቦታ?
- የምንሄደው ፊልድ እንሄዳለሁ እዚህ ቦታ እንሄዳለን ብለን እንጂ ያው የሄዳችሁበትን ተግባር አደለም?
- አዎ ፊልድ መውጣታችን ነው እንጂ ይሄን /ግልጽ ያልሆነ/ አላልንም
- እናንተ በወ/ሮ ሃቢባ እና በባለቤታቸው ትእዛዝ ነው የምትነቀሳቀሱት ?
- አዎ
- አጃቢውም በተመሳሳይ የመቃወም ስልጣንም የላችሁም?
- አዎ እኛ እዛ የተመደብነው እነሱ የሚሄዱት የሚፈልጉበት ቦታ ላይ ሲሄዱ
- መሄድ ብቻ ነው?
- አዎ
- መቃወምም ስልጣን የላችሁም?
- አዎ
- በተደጋጋሚ ጊዜ የግል ጉዳያቸውን ተጠይቀዋል ለምሳሌ አክራሪነት አይተውባቸዋል ወይ ተብሏል አላየሁም ብለዋል ይሄን በምንድን ነው ያወቁት ስለዚህ መናገር ይችላሉ?
- አዎ የራሴ ግምት
- ግምት ነው የተናገሩት?
- እኔ በግምት ከራሴጋ ከማንምጋር ስለዚህ ጉዳይ ስታወራ ስላላየሁ ማለት ነው
- ስላልሰሙ?
- ስላልሰማሁ አዎ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ክሌላ ሰውጋ ይገናኙ አይገናኙ የሚያውቁት ነገር አለ ወይ ሲባሉ አይ አልተገናኙም አላውቅም ብለዋል ቅድም በዋና ጥያቄ ሲጠየቁ ሳውዲአረቢያ ኤምባሲ ውስጥ ይገባሉ ከማንጋር እንደሚገናኙ አላውቅም ብለዋል አደል?
- አዎ
- ስለዚህ የትኛው ነው ትክክልሳውዲ አረቢያ በምን ምክንያት እንደሚገቡ ከማንጋር ተገናኝተው እንደሚወጡ ያውቃሉ?
- እዛ ይገባሉ እቤት ነው የሚገቡት
- እኮ እርስዎ ውጪ ኖት አደል?
- እኔ መኪና ይቼ ውጪ መኪና ላይ ነው ቁጭ የምለው ስለዚህ ሲወጡ የወጣውን ነው እቃ ይገፎ የምሄደው
- እኮ እዛ በምን ጉዳይ ተነጋግረው ምን ግንኙነት ፈጥረው እንደሚወጡ ያውቃሉ ወይ?
- አላውቅም
- ሼህ አብዱራህማን የሳውዳረቢያ ኤምባሲ እና ወ/ሮ ሃቢባ ያላቸውንስ ግንኙነት የሚያውቁት ነገር አለ?
- እማውቀው ነገር የለም
- አብረው እዛ መስኪድ ድረስ ከመውሰድ ውጪ የሚያውቁት ነገር አለ ወይ አብራችሁ ከመሄድ ውጪ?
- ከዛ ውጪ የማውቀው ነገር የለም
- ሦስቱን ምን እንደሚያገናኛቸው አያውቁም?
- አይ አላውቅም እሱን
- እሺ ምስክር መስኪዱ ከየት በመጣ ገንዝብ እንደተሰራ ያውቃሉ ?
- አሁን በስተመጨረሻ ላይ ከሳውዲ አረቢያ በተሰጣቸው ፈንድ ማለት ነው መጀመሪያ ላይ ግን በራሳቸው ነው የጀመሩት
- ጥሩ ሼህ አብዱራህማን ይሄን መስኪድ ለምን እንሚከታተሉትስ ያውቃሉ ?
- ለምን አንደሚከታተሉ አላውቅም ግን እዛ ከእኛጋ ይሄዳሉ ለምን እንደተመደቡ አላውቅም ባክግራውንዶቹን
- አበቃን ድጋሚ
- እሺ የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የለም ጨርሰዋል እናመሰግናለን
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምያለሁ
- ለምስክርነት ነው የመጡት?
- አዎ
- እሺ ለምስክሮች ደህንነት ተብሎ ምስክሩ የራሱን ስም ብቻ የአባቱን ስም ሳይጨምር እንዲናገር ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል የራሱን ስም ብቻ
- ሙስሊም
- ስንተኛ ነው አቃቤ ሕግ በዝርዝሩ?
- 14ኛ
- በተሰሙት ምስክር ዝርዝር 24ኛ ምስክር ላይ ደርሰናል በአቃቤ ሕግ የምስክር ዝርዝር 14ኛ ላይ የተጠቀሰ ለምስክርነት ነው የመጣሁት ብለሃል ?
- አዎ
- በነማን ላይ ነው የምትመሰክረው?
- እኔ ማለት ሚያዝያ 11 ቀን 2004 ላይ አወልያ አካባቢ በድምጽ ማጉያ ነው የሰማሁት እና ምንድን ነው 1ኛ ያሲን ኑሩ እነአቡበከር እና ሼህ መከተ
- ያሲን ኑሩ?
- አዎ ያሲን ኑሩ አቡበከር
- አቡበከር እና ሼህ መከተ?
- ሼህ መከተ
- ሦስቱም ላይ?
- አዎ ሙደሲር የሚባል ልጅ አለ አምስት ሰው ላይ ነው ቃል የሰጠሁት
- ሦስት ሰው ነው የሰማሁት?
- አዎ 3 ሰው እና ሙደሲር የሚባል
- አዎ
- አራት ሰው ላይ?
- 4 ሰው ላይ እና በድምጽ ማጉያ ነው የሰማሁት እና ፕሮግራም የያዘው
- ስለዚህ 4 ሰው ላይ ነው?
- አዎ
- እሺ ይሄን አራቱን ሰወች ለይተው ያውቃሉ በአካል?
- በአካል እንኳን በብዛት እኔ አላየኋቸውም
- በአካል ለይተው አያውቁም?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ አላውቃቸውም ያው ውጭ ነበርኩ እኔ ከአጥር ውጪ ነበርን በድምጽ ማጉያ ነው የሰማሁት
- እሺ ይበቃናል አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥል
- እሺ ምስክር አቶ ሙስሊም አሁን ያው የመጣኸው ለምስክርነት ነው ብለሃል?
- አዎ እያንዳንዱ ድርጊት ማለት መቼ እንደተፈፀመ ጊዜው ቦታው ሰዓቱን ማን ምን ሲል እንደነበረ ይዜን በዝርዝር እንድታስረዳ ነው የምጠይቅህ እና እስቲ አሁን ቅድም ካልከው ቀን ቀኑ ወሩ አመተምረቱ መቼ ነው ምን ሲደረግ ነው ያየኸው እና መቀጠል ትችላለህ?
- እኔ ማለት ቀኑ አርብ ቀን ነው
- ወሩ መቼ ነው?
- ሚያዝያ 11 ነው አርብ ቀን ነው ሚያዝያ 11 ስድስት ሰዓት ተኩል አካባቢ
- አመተምረቱስ?
- 2004
- የት አካባቢ ነው ቦታው ?
- አወልያ ግቢ ውስጥ ነበሩ እነሱ በማይክራፎን ፕሮግራም ነበራቸው እና በማይክራፎን ሲያስተላልፉ ነበረ እና ፕሮግራም የያዘው ሙደሲር የሚባል ልጅ ነበረ እና ሰዓት ሰጥቷቸው ያው በሰዓት ተደጋጋሚ ቃላት ሲናገሩ ነበር
- እሺ በዚህ እለት አሁን አወልያ ት/ቤት አሁን ባልከው ቀን ማለት ነው እስቲ መጀመሪያ ስለ ያሲን ኑሩ ንገሩን ወይም ስለ አቡበክር መሃመድ ከአቡበክር ጀምርና አቡበክር ምን ያደርግ ነበር?
- ማለት ያው ሁሉም ተደጋጋሚ ቃል የተናገሩት አንድ አይነት ቃል ነው እና ምንድን ነው ቃሉ የሚለው ያው እኔም ቃል የሰጠሁት እንደሰማሁት ነው እና ምንድን ነው አህባሽ የሚባል ኃይማኖት መጥቷል የእስልምና ጉዳይ ብር ተቀብሏል ቼኩ ተገኝቷል በእጃቸው ላይ እና መንግስትም ተካፋይ ሆኖ ከቨር እያደረገላቸው መሆኑን እና አላህዋክበር በቃ በሉ ሰው ዝም ሲል በተደጋጋሚ አላህዋክብር በሉ ምናምን ነው በቃ ይዜንን ነው የሰማሁት እኔ በአጠቃላይ
- ይዜንን ማን ሲናገር ነው የሰማኸው?
- ሦስቱም ሲናገሩ ነበረ
- ሦስቱም በአንድ ማይክራፎን ነው የሚናገሩት ወይስ ?
- አዎ ፕሮግራሙ እንደዚህ ወደ አስር አስር ደቂቃ የምትሆን ማለት ነው ተከፋፍሎ ሁሉም በቃ በተራ ሲናገሩ ነበር

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን የሚቀጥለው ተናጋሪ ወይም እንደዚህ ይባላል ወይስ አንተ እንዴት አወቅክ እያንዳንዳቸውን እንዴት መለየት አስቻለህ ?
- አዎ ማለት እኔ ሙደሲር የሚባል ልጅ ነበረ እዛው የግቢ ተማሪ ነው እና እሱን እንደውም በአካል አውቀዋለሁ እና ምንድን ነው እሱ ነው ፕሮግም ይዞ ሃጣ እከሌ ፕሮግራሙን እንደዚህ ይቀጥላል እያለ ሰዓት ሰዓት ከፋፈሉላቸው ማለት ነው እና እሱ ነው ፕሮግራም ይዞላቸው በቃ በዛ ነው ሃጣ እከሌ አሁን ይቀጥላል እና አዳምጡ ይባላል
- እስቲ በስም አሁን ያልከውን እገሌ ሳይሆን በስም ማን አቶ እከሌ ወይም ያለውን ተናገር እሱ?
- በቃ ልክ ማለት መጀመሪያ ሲናገሩ አሁን የሃጂ ያሲን ኑሩ ይቀጥላል ይላል ከዛ እሳቸው ሲጨርሱ ደግሞ ቀጥሎ አቡበክር አህመድ ይቀጥላል ይባላል ከዛ በኋላ ሼህ መከተም ይቀጥላል እያሉ እንደዚሁ በብዛት ፕሮግራም ይዞላቸው ተራ በተራ ሲጨርሱ ይናገራሉ
- ምን ነበረ መልክቱ ሕዝቡ እንዴት ነበረ መልክቱ ምንድን ነው አሁን አንተ በተረዳኸው ማለት ነው ?
- ያው መልክቱ በቃ አህባሽ የሚባል ሃይማኖት መጥቷል እና እሱ ይቁምልን መንግስት እሱንም ካላቆመልን ትግላችን እስከ መጨረሻ እንደምንቀጥል ይላሉ ከዛ ሕዝቡ ዝም ሲል አላህዋክብር በሉ ይባላሉ እስቲ በማይክራፎን ሲባሉ ሕዝቡም የነሱን ፈለግ ተከትሎ አላህዋክብር ይላል
- አንተ ይሄንን የምትሰማው የት ሆነህ ነው?
- እኔ ከግቢ ውጪ ነበርኩኝ ያው ለሰላት ሄጄ ማለት ነው
- ለሰላት ነው የሄድከው?
- አዎ እና እኔ ምንድን ነው ትንሽ ቅር የሚለኝ ያው ሕዝቡ ዝም በሚልበት ሰዓት አላህዋክበር በሉ ሲባል ያው ያ ነው በቃ በተደጋጋሚ ትንሽ እኔ ቴንሽን የሚሰርቀው ማለት ነው
- አንተ አሁን ቅድም እንዳየኸው ማለት ነው ለሰላት ሄደህ እንደዚህ አይነት ተግባር ሲፈፀም በተለያየ ጊዜ ለሰላት ትሄዳለህ እና እንደዚህ ነገር ገጥሞህ ያውቃል እዛ አካባቢ?
- አረ በብዛት በቃ ምንድን ነው ሕዝቡ ሰግዶ ቢወጣ እኔም ደስተኛ ነኝ ሰው የፈለገውን ቢያወራ ደስ ይለኛል እሚቀበለውም ይቀበል እማይቀበለውም ዝም ብሎ ይውጣ ግን ምንድን ነው በሉ የሚባለው ትንሽ ውስጤን የሰረቀኝ
- አሁን አንተ ውጪ ነህ እነሱን መለየት የቻልከው በዚህ ቅድም መድረኩን ስያስተዋውቅ በነበረው ሰው አማካኝነት ነው ማለት ነው?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ትክክል አዎ ትክክል
- ስማቸውን ይጠራ ነበረ?
- አዎ ሙደሲር የሚባለውን እኔ በአካልም አውቀዋለሁ የዛ ግቢ ተማሪ ነው ዶርሙም እዛ ነው ያለው ልጁ እና በቃ እሱ አሁን ሃጃ እከሌ ፕሮግራሙን ይቀጥላል ይላል ከዛ በኋላ ልክ ማይክራፎን ሲላቸው እሱ ይናገራል
- ለምን ያህል ጊዜ ነው የቆየው ይሄ ንግግር?
- እ?
- ለምን ያህል ጊዜ ቆየ አንተ ሚያዝያ 11 ?
- 11 አረ እስከ ስምንት ሰዓት ተኩል ቆይቻለሁ እዛ
- እንዴት ተጠናቀቀ የመጨረሻው ማለት ነው?
- መጨረሻውማ በቃ ለሚቀጥለው ሳምንት ያው ቀጣይ መልሱን ከመንግስትም ሆነ ከኮሚያቴያችንም ሆነ መልሱን ይዘን እንቀርባለን ተብሎ በቃ ሕዝቡ በዚሁ ተለያየ
- ኮሚያቴያችን ማለታቸው እነማን እነማ ማለታቸው ነው?
- ኮሚቴዎቹ መጀመሪያ የተመረጡ ኮሚቴዎች ናቸው መሰለኝ ከመንስትጋ ኮንታክት ያላቸው
- ምን ሲባል ነው የሰማኸው?
- አዎ
- ምስክር ስንት ሰዓት ነው ፕሮግራም የተጀመረው?
- ፕሮግራመ የዛን ጊዜ የተጀመረው አምስት ተኩል ነው የዛን ጊዜ
- አንተ ስንት ሰዓት ደረስክ?
- እኔ ስድስት ሰዓት ደረስኩ
- ማን ነው መጀመሪያ ንግግር የጀመረው?
- እሱን እኔ አላየሁትም
- እ?
- ንግግር የጀመረው ያው መጀመሪያ ሙደሲር የሚባል ልጅ ነው
- ሙደሲር ጀመሪያ ማንን ጋበዘ?
- እሱ ትዝ አይለኝም ያው እኔ በድምጽ ብቻ በስማቸው
- እኮ ማን ይመጣል አለ መጀመሪያ ?
- መጀመሪያ እኔ እሱን አለየሁም ግን እኔ እንትን ስለነበር
- እሺ የማን ስም ሲጠራ ሰማህ?
- 1ኛ ያሲን ኑሩ ነው እንግዲህ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ያሲን ኑሩ መጥቶ ምን አለህ?
- ያሲን ኑሩ በቃ ይሄ አህባሽ የሚባለው ኃይማኖት መጅሊስም ሆነ መንግስትም ሆነ ከቨር አያረገላቸው እንደገና ደግሞ ምንድን ነው ቼክ ብር ተቀብለው እጃቸው ላይ እንደተገኘ የሚባል ነው ዋናው በቃ
- ምን ያህል ብር ?
- እሱን እኔ አልተናገሩም እነሱ ቼክ ነው በቃ
- ከማን ተቀበሉ አሉ ?
- ያው እንግዲህ ከእነዚህ ከአህባሽ የሚባለው ኃይማኖት
- እኮ ከማን ተቀበለ መንግስት ?
- መንግስት እና መጅሊስ ያው መጅሊስ አህባሽ ከሚባለው ተቀብሏል ቼኩን እጃቸው ላይ ተገኝቷል እና እንደውም የተገኘውን ፎቶ ብለው ፎቷቸው
- እኮ ምን ያህል ገንዘብ ገንዘቡ ቁጥሩን ሲጠቅስ አልሰማህም?
- አልሰማሁም እኔ
- ማን ቀጠለ ከዛ?
- እኔ እሱ ትዝ አይለኝም በቃ እኔ በአጠቃላይ ይሁን በተራ ግን ተናግረዋል በተደጋጋሚ
- እሺ ቅድም የጠቀስካቸው ያሲን ኑሩ አቡበከር አህመድ ሌላ ማን አለ?
- እና ፕሮፌሰር አህመድ ነው የሚባሉም አሉ መሰለኝ አራት ናቸው
- ሌላስ?
- በቃ እኔ ማለት ያው
- ቆይ አዳምጥ ሙስሊም እያዳመጥክ መልስ እኔ እምጠይቅህን ብቻ መልስ
- እሺ
- ቅድም መጀመሪያ በማን ላይ ነው የምትመሰክረው ተብለህ ስትመጣ የ3 ሰወች ስም ጠርተሃል አደለም?
- ትክክል ነው አዎ
- 1ኛ አቡበከር አህመድ 2ኛ ያሲን ኑሩ 3ኛ ማንን ነው የጠራኸው?
- 3ኛ ኑሩ ቱርኪም ሳይኖር አይቀርም ቃል ሰጠን እኛ
- ቅድም መጀመሪያ ስትጠራ ሼህ መከተ ሙሄ ?
- ትክክል
- አቡበከር አህመድ ?
- ትክክል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እና ያሲን ኑሩን ጠርተህ ነበር?
- አዎ
- ቀጥሎ ደግሞ እረዳት ፕሮፌሰሩን ጠራህ ?
- ትክክል አዎ
- አሁን መጨረሻ ላይ ደግሞ ኑሩ ቱርኪን ጠራህ?
- አዎ ማለት እኔ ስለቆየ ያው የዛን ቀንም በድምጽ ስለሰማሁ ያው ወቅቱም እራሱ እንትን ስላለ
- አሁን እኮ አስታውሰሃቸዋል እኮ የተለየ ነገር እንድትናገር አደለም እኛ የምንጠይቅህን እየሰማህ የምታስታውሰውን እንድትናገር ነው አሁን ባለመረጋጋትህ ሁለት ሰወች ስም አልጠራህም መጀመሪያ?
- ትክክል
- ስለዚህ አሁን እያስታወስክ ነው እረጋ ብለህ የምታስታውሰውን ንገረን
- እሺ
- የያሲን ኑሩን ጨረስን ቅድም አቡበክር አሊ ያልከውን ተኛግረሃል ኑሩ ቱርኪስ?
- አዎ ኑሩ ቱርኪም ሳይኖረው አይቀርም አዎ ትዝ ይለኛል ቃል ሰጥቻለሁ
- አይ ቃል የሰጠሽውን አደለም በወቅቱ የምታስታውሰውን የኑሩ ቱርኪ ስም ተጠርቶ ኑሩ ቱርኪ ንግግር አድርጓል?
- አዎ እኔ ብቻ በአጠቃላይ 5 ሰው ነው እኔ በስነስርዓት የሰማሁት ስማቸውንም በስነስርዓት ባላስታውስ
- ቆይ ምስክር ያዳምጣሉ አሁን አንድ በአንድ እየተጠየቁ ነው ቅድም የሆኑ አራት ሰወች ዘርዝራችኋል አደል
- አዎ
- ያልተጠቀሱትን ቅድም እከሌ እንዲህ አለ እንዲህ አለ እያሉ ያስረዱ ነበር ስለዚህ እነዚህ አራት ሰወች ምንድን ነው ያደረጉት ያዩት እና የሰሙት ነገር ካለ እሱን ብቻ የሚጠየቁትን ብቻ ይመልሱ ስለዚህ አንድ በአንድ ጠይቋቸው
- አሁን ስታስረዳ መንግስት አህባሽ የሚባል ኃይማኖት አምጥቷል ከመጅሊስ ጉን ገንዘብም ተቀብሏል ቼክም ተገኝቷል ይሉ ነበር ብለሃል?
- ትክክል
- እና ምን እናርግ ነው የሚሉት?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በቃ እኛ ምንድን ነው ይሄ አህበሽ የሚባለውን ኃይማኖት ካልቆመ መንግስት ካላስቆመልን ትግላችንን እስከ መጨረሻ እንደምንቀጥል ነው ሲሉ
- እስከመጨሻ እንዴት?
- ያው በቃ እስከ መጨረሻ ትግላችንን እንቀጥላለን አሉ
- ምን ማለት ነው እስከ መጨረሻ ማለት እስከ ምን?
- ያው እስከመጨረሻ ማለታቸው እንግዲህ ያው እኔ የሰማሁትን ነዋ የምናገረው እስከ መጨሻ ትግላችንን እንቀጥላለን ሲሉ ከዛ አላሕዋክበር በሉ ሲባል
- እንዴት ነው እንታገላለን ያሉት?
- እሱን እንግዲህ እስከመጨሻ ነው እነሱ ያሉት
- እንዴት እስከ መጨሻ ማለት እንዴት?
- ምስክር ጥያቄው ግልጽ ይሁንልህ አሁን እስከ መጨሻው ማለት ሌላ የተናገሩት ነገር አለ ወይ ነው?
- እስከ መጨሻው ማለት ያው እንግዲህ እስከ መጨረሻው መንግስት ይሄ ነገር አህባሽ የሚባለውን ኃይማኖት ካላስቆመልን
- በቃ እኮ እስከ መጨሻው ማለት ምን ማለት ነው ተብለህ ስትጠየቅ ከዛ በኋላ ያሉት ነገር አለ?
- ያሉት ነገር አልሰማሁም
- ምስክር አንተ በአወልያ መስኪድ ውስጥ የጥበቃው ክፍል አባል ነህ አደለም?
- አባል ሳይሆን ያው ያኔ ያው ዝም ብዬ ነው ልሰግድ የምሄደው እኔ በፊት ነበረ የተመደብኩት የግቢው ሳይሆን ከሌላ ቦታ የምክር ቤቱ ነኝ
- ይሄ እንቅስቃሴ አሁን ከጠቀስከው ከሚያዝያ ወር በፊት ሲደረግ ተመልክተሃል?
- እንቅስቃሴው
- እ?
- አዎ
- መቼ?
- እሱ ትዝ አይለኝም እንጂ ተደጋጋሚ እረብሻ እንደነበረ እዛ ነበረ አዎ
- በማን አማካኝነት ነው ይሄ እረብሻ ሲደረግ የነበረው?
- ያው አብዛኛውን ተማሪዎች ነበሩ ከዛ በኋላ ከተማሪዎች ውጪ ሰዎች ነበሩ ስማቸው ትዝ አይለኝም እንጂ
- ቅድም የጠቀስካቸው 5 ሰወች ነበሩበት ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከዛ በፊት አዎ በተደጋጋሚ ይገባሉ መሰለኝ
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለኝ
- እሺ
- አቃቤ ሕግ ለ2ኛ ጊዜ ወይም ለ3ኛ ጊዜ እየመሩ ነው ያለው የተከበረው ፍ/ቤት ሌላ ሰው ነበረ እነዚህ ሰወች ነበሩ አምስቱ ሰወች ነበሩ ይሄ መሪ ቀጥተኛ የተከበረው ፍ/ቤት ሰውየው ወይም ምስክሩ ነበረ እረብሻ ብለዋል እነማን ነበሩ ተማሪዎች ብሎ ዘጋ ከዚህ ወዲህ እነዚህ ኮሚቴዎች ነበሩ ማለት ቀጥታ የተከበረው ፍ/ቤት ይሄ መሪ ጥያቄ ስለሆነ ጥያቄው ሊሰረዝ ይገባል
- ምላሽ ስጡበት
- ያው ስንከታተል እንደነበረው
- መሪ ነው ጥያቄው የሚል ተነስቷል መሪ ነው አደለም በሚለው ላይ
- ያው ስንከታተል እንደነበረው ምስክሩ የ5 ሰወች ስም ጠቅሶ እስከ አሁን አውቃለሁ የሚለውን ነገር ሲያስረዳ ነበር አሁን ደግሞ የጠየቅነው ጥያቄ ከሚያዝያ ወር በፊት ምን አይነት እንቅስቃሴዎች ነበሩ ብለን ጠየቅነው ተመሳሳይ እንቅስቃሴዎች ነበሩ አለ መጀመሪያ ማን ነው የጀመረው አልነው ተማሪዎች ነው አለ ቀጥሎስ ስንለው የተለያዩ ሰወች ገብተውበታል አለ አሁን የጠቀስካቸው 5 ሰወችስ ብለን ነው የጠየቅነው ስለዚህ ምስክሩ ቀደም ብሎ ሲናገር የነበረውን ነገር ነው ፍሎውን አሲዘን የመጣነው እንጂ በአዲስ ፋክት ነግረን ምስክሩን እንዲያምን መሪ ጥያቄ አልጠየቅንም
- የመጨረሻ የተነሳው እነኚህ ቅድም የጠቀሱት አምስቱ ሰወች ነበረ በተባለው እንቅስቃሴ ውስጥ ነበሩ ወይስ አልነበሩም ነበሩ ወይ የሚልነው ጥያቄው መሪ ነው የሚል ተቃውሞ ተነሳ ነበሩ ወይስ አልነበሩም የሚለው ግልጽ መሪ ስለሆነ ይሄ ጥያቄ ይታለፍ ብለን ብይን ሰጥተናል ሌላ ጥያቄ ካላችሁ
- ሙስሊም ከመቼ ጀምሮ ነው አሁን የገለጽከው እስከ አሁን የነገርከን እንቅስቅሴ የተጀመረው?
- ማለት ያው እንቅስቃሴው የቆየ ነው በጣም
- እስኪ ንገረን በወራት በግምት?
- እኔ እራሴ ያው እዛ ውስጥ እረብሻ እንዳለ ወደ 2 ወር ያህል እርግጠኛ ነኝ ይሆናል
- ይኸውሎት ምስክር ከመቼ ጀምሮ የሚለውን ነገር እሷን ብቻ መነሻ ይንገሩን
- በወር ያስታውሱታል በስም በወር?
- ግን አትሊስት ያው ከባድ እርብሻ ግን ወደ 1 ወር የሚሆን [illegible] እርግጠኛ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ ምን ወር በስም?
- ያው እንግዲህ ከሚያዝያ ወደዛ ግምቦት ላይ ነበረ
- የነበረው?
- አም ግምቦት እራሱ መጋቢትም ነበረ
- ከባድ ያሉት በምንድን ነው ከባድ ማለት ምን ማለት ነው?
- ማለት ያው ለ15 ቀን እራሱ ውስጥ እያደሩ ማለት ነው ከብት ሁሉ እየታረደላቸው ከብት እራሱ እዛ አወልያ ግቢ ውስጥ እየታረደላቸው ውስጥ እራሱ ወደ 15 ቀን ያህል አድረዋል እርግጠኛ ነኝ እኔ ያየሁት ነገር ማለት ነው
- ከዛስ ውጪ ከባድ እረብሻ ያሉት?
- 15 ቀን ሴቶቹም ወንዶቹም እያደሩ እንደውም ከብት ሁሉ ያው ወደ አወልያ ግቢ ሲከለከል ለክበብ ነው እየተባለ ክበብ ውስጥ እየታረደለት
- ከየት ነው የሚገባው?
- ከውጪ ተገዝቶ
- ማን ነው የሚገዛው?
- አይታወቅም እሱ የክበቡ ነው ተብሎ ወደ 4 በሬ እራሱ ያየሁት ነገር አለ እኔ
- እንደዛ ነው የሚገዛው?
- አም ሲከለከሉ ያው ክበብ ነው ብሎ የክበቡ ባለቤት አለ ተከራዩ እና በሱ ስም ይገባል ይሰራል እራት እራት ያው ይቀርብላቸዋል እዛ ለሚያድሩት ሴቶቹም ወንዶቹም በብዛት እዛ አድረዋል ወደ 15 ቀን የሚሆን
- መቼ ነው ያበቃው መጨረሻ እርስዎ የሚያስታውሱት?
- እኔ በእውነት ያው በዛ ሰዓት ሥራም ውጥረትም ስለሆነ ግርግርም ስለሆነ ያው የሚታየውም ነገር ቆንጆ ስላልሆነ እንደ ኃይማኖት ቦታ ላይ ማለት ነው ያው ቴንሽንም ስለሚሰረቅ እኔ እንደዚህ አይነት ነገር ያው በቃ ያው ወንጀል እንዳይፈጠር ብቻ ነው እኛ እራሳችን
- የተፈጠረ ወንጀል አለ እንዴ?
- የለም ያው መኪና ምናምን ግን የሚሰባበር አለ
- የት ነው የተሰበረው?
- አዛው ግቢ ውስጥ የቆመ መኪና የድርጅቱ
- ቆይ አቶ ሙስሊም
- አቤት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እረጋ ይበሉና እያስታወሱ እንትኖቹን የተፈጠሩትን ነገር እያስታወሱ ለምሳሌ ወንጀል የተፈፀመ የለም ነገር ግን መኪና ተሰባብሯል ብለዋል?
- ትክክል አዎ
- እስቲ እሱን እያስታወሱ መኪናው የት ነው የተሰበረው ቀስ ይበሉ እኛል እንድናዳምጦት ስለዚህ መኪናው የት ነው የተሰበረው?
- አሁን መኪናው እንደውም ከዚህ በፊት ትዝ የሚለኝ መኪና የፀሐፊው መኪና ነበረ እና ለፀሐፊ ጽሕፈት ቤቱ የምክር ቤቱ ፀሐፊ አሊ መሃመድ ሲራጅ የሚባል አንድ ቀን መጣ የዛን ቀን ቀን
- ለምንድን ነው የመጡት?
- ያው እነሱ ያው እንግዲህ እንዳይረብሹ ለማናገር ተመጡ እና ሲመጡ ከዛ በኋላ እሱን ሊደበድቡት ሲሉ አንድ ሱልጣን የሚባል አለ
- ማን ነው የሚደበድበው?
- ሕዝቡ በቃ ግጥም ብሎ በቃ ሕዝቡ
- ለምን?
- ያው በቃ መልሱ አልረካንም ብለው
- የትኛው መልስ?
- ያው እሱ የሆነ እያናገራቸው ነበር አዳራሽ ውስጥ ከዛ በኋላ እሱን ሊደበድቡት ሲሉ ወጣ እሮጦ ወጣ ፖሊስም ነበረ ከዛ እሮጦ በእግሩ ሄደ እሱ ከዛ መኪናው እዛው በቆመበት አራቱንም መኪና ጮማ አተነፈሱት
- እነማን ናቸው ያተነፈሱት?
- አይታወቅም በብዛት ነው ሕዝቡ ያለው እዛ ውስጥ
- ሌላስ?

  እስፖርትም ጮማ ነበረ የሱን እራሱ አተነፈሱት ታርጋ ሁሉ እስከማጠፍ ድረስ ከዛ በኋላ እኛ ባለንበት ነው ማታ ላይ ጮማ ተቀይሮ ምን ተብሎ በሌላ ሹፌር የሄደው
- ሌላ ከዚህ ውጪስ ንብረት ላይ የደረሰ ?
- የቆመ መኪና ነበር እሱ ሁሉ በቃ እስከ መሰባበር ድረስ ደርሷል
- የማን መኪና ነው?
- ያው የድርጅቱ መኪና እዛው የቆመ ነበር
- የማን ድርጅት?
- ያው የአወልያ ድርጅት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለምንድን ነው እሱስ የተሰበረው?
- ያው አይታወቅማ በዛ በግርግር መንስኤው ያው እሚገባው እሚወጣው እሚያድረው ሁሉ አይታወቅም ነበር
- እኮ እዛ ምክንያት አለው አደል መነሻ አለው ይሄ ሁሉ ነገር ሲፈጠር ?
- ያው መነሻማ አህባሽ የሚባለው ነገር በመጣበት ኬዝ ነው
- ይሂድ ነው?
- አዎ
- በዚህ ምክንያት ነው ?
- በዚህ ኬዝ ነው በቃ አህባሽ የሚባል መጥቷል መጅሊስ ይውረድ በቃ ይሄ ነው ዋናው መንስኤው
- ሌላስ ያዩት ከመኪናው ውጪ ሌላ ንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት ?
- ሌላ የለም በኔ ሰዓት የማስታውሰው የለም
- እሺ ጨርሰናል ዋና ጥያቄ የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ መስቀለኛ ጥያቄ ካለ
- አቶ ሙስሊም
- አቤት
- ቅድም ይናገሩ ነበር ያላቸውን ሰወች ከግቢ ውስጥ ሆኜ ነበረ የማዳምጣቸው በስፒከር ነው ብለዋል ?
- ትክክል
- ከግቢው ምን ያህል እርቀው ነበር ?
- ያው እኔ ከመስኪዱ ጮን ነበርኩ ጀርባ ማለት ነው ከስፋልቷ ጮን ግቢዋ እንደዚህ ነው መስኪዱ እንደዚህ ነው ይሄ መንገድ ነው እኔ ያው ለግርግርም ከተነሳ ብዬ ውጪ ነበር የምሰግደው እና እዛ ነበርኩ
- የጠቀሷቸው ሰወች ንግግር መሆኑን የሚያውቁት ሙደሲር የሚባል ሰው ስለገለፀ ነው?
- አዎ ሙደሲር የሚባል ተማሪ ነው እሱ በአካልም አውቀዋለሁ እና እሱ እዛው ዶርም ነው የሚኖረው እና በቃ እንደዚሁ እያስተዋወቀ በተራ እንዲናገሩ ይሰጣቸዋል ማይክራፎኑን
- ቀጥሉ
- እነያሲንን ከዛ በፊት ያውቋቸዋል እንዴ?
- እኔ አላዉቃቸውም
- ሁሉንም ተከሳሾች በስም የጠሯቸውን አያውቋቸውም ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አላውቃቸውም እኔ
- ስለዚህ ሙደሲር የነሱ ድምጽ ነው የነሱ ንግግር ነው ከማለት በስተቀር የነሱ ይሁን አይሁን እርስዎ ማረጋገጥ አይችሉም ?
- እኔ አልችልም አዎ ግን እሱ ግን ሲያስተዋውቃቸው ሃጂ እንደዚህ ይላል ይቀጥላል ይሰጣቸዋል ይናገራሉ ሲጨርሱም እንደዚሁ ቀጣዩን ይናገራሉ
- አቡበከር ማን ነበረ ያሉት?
- አቡበከር አህመድ ነው እሱ ያለው
- የሼህ መከተንስ ያባት ስም ያውቃሉ?
- እሱ ትዝ አይለኝም ግን ተናግረዋል የዛን ቀን ፕሮግራሙ ላይ
- እለቱ ይነገር የነበረው ከመስኪድ የሚወጣ ድምጽ ነው ?
- አረ ከመስኪዱ እዛው በማይክራፎን ይሄ ይሄማ በእርግጠኛ ነኝ
- ቅድም ስብሰባ በእለቱ የተጠናቀቀው ለሚቀጥለው ሳምንት እንገናኝ ተብሎ ይጠናቀቃል መልስም ይሰጠናል ይሉ ነበር ብለዋል?
- ትክክል ነው
- ምን መልስ ነው ከማን ነበር ይሰጠናል የሚሉት?
- ያው በቃ ከመንግስት የሚመጣልንን መልስ ይዘን እንቀርባለን መልስ እስከሚሰጠን ትግላችን ይቀጥላል በቃ አላህዋክበር እየተባባሉ እንደዚሁ ነው ያሉት
- ከዚህ ውጭ ትግላችን ሰላማዊ ነው ሕገመንግስታዊ ነው ሲሉስ አልሰሙም?
- እንዴት ?
- ተከላከሉ
- መቃወሚያ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ
- ማለት በዋና ጥያቄ አልተነሳም በዚህ ጉዳይ ላይ ማለት ነው አሁን በመስቀለኛ ጥያቄ መከላከያቸውን አደለም የሚጠይቁት ሊጠይቁ የሚገባው የምስክሩን ያመሰካከር ኢንኮንሲስተንሲ ከሆነ መጠየቅ የሚገባቸው ያንን መሰረት በማድረግ ይሄ ማለት አደለም ወይ የተናገርከው ነገር ይሄን ለማለት አደለም ወይ እየተባለ ነው ሊጠየቅ የሚገባው እንጂ ዘአዘር ሳይድ ሌላኛው ገጽ ተወስዶ መከላከያቸውን አደለም አሁን መጠየቅ የሚገባቸው በዚህ ደረጃ
- እሺ ምላሽ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ በእለቱ ወሎው እዛ እንደነበረ ገልጿል በእለቱ ያየውን ነገር ደግሞ ለፍ/ቤቱ ምሎ እውነቱን ለመግለጽ መሃላ ስለፈፀመ አንድም በእለቱ መኖር አለመኖሩንም 2ኛ የሰማው ይሄን ብቻ ነው ወይ የሚለውን እውነታውን ሁሉ እንዲገልጽ ነው እንጂ እኛ መከላከያ እያቀርብን አደለም ስለዚህ መቃወሚያው አለ አግባብ ነው
- ብይን ተሰጠ የቀረበው ጥያቄ ቅድም የተጠቀሱት ተከሳሾች ትግላችን ሰላማዊ ነው ብለው ተናግረዋል ወይስ አልተናገሩም የሚል ጥያቄ ነው የቀረበው በዚህ ላይ የቀረበው መቃወሚያ ይሄ በዋና ጥያቄ አልተነሳም የሚል ነው ፍ/ቤቱ ጥያቄው አግባብ ነው ወይስ አደለም ለሚለው ምላሽ ለመስጠት ይሄ ጥያቄ በዋና ጥያቄ ተነስቷል አልተነሳም የሚለውን ነው ያየው በዋና ጥያቄ ላይ የተነሳው እና ምስክሩ የተናገሩት ሙደስር የሚባል ሰው አስተዋዋቂ ነበሩ በሙዳስር አስተዋዋቂነት ቅድም ስማቸው የተጠቀሰው ተከሳሾች የተናገሩትን ነው የሰማሁት ብሎ ተናግሯል ስለዚህ ምስክሩ እየመሰከረ ያለው በዛ በአስተዋዋቂው መሰረት ከተስተዋወቁ በኋላ ወደ መድረኩ ተከሳሾቹ ቀርበው ንግግር ማድረጋቸውን ነው ንግግር ሲባል አጠቃላይ ነው ከንግግሩ ሰላማዊም ሌላም ሊወጣ የሚችል ነው እና በሌላ መልኩ ከተጠየቀ ሰላማዊ ንግግር ውስጥ የሚካተት ስለሆነ በዋና ጥያቄ አልተነሳም ሊባል የሚችል አደለም ስለዚህ ጥያቄው ተገቢ ነው ይቀጥል ብለናል
- ምስክር
- አቤት
- ቅድም ተናገሩት ካሉት ውጭ ተከሳሾች አንዳቸውም ከጠቀሷቸው ሰወች አንዳቸውም ትግላችን ሰላማዊ ነው ሕገመንግስታዊ ነው የሚል ነገር ሲናገሩ አልሰሙም?
- አይ እኔ ይሄን አልሰማሁም
- ጥሩ ቅድም ከብት ሲከለከሉ ለካፍቴሪያው ነው ብለው አስገቡ አሉ?
- ትክክል
- ቀደም ሲል አይከለከልም ነበር በኋላ ነው የተከለከሉት?
- አዎ መጀመሪያ ያው እንግዲህ እኔ ብዙ ባላውቅም በአንድ ኃይማኖት ግቢ ውስጥ እንደ ዶርም ማደሩ በጣም ይከብደኛል እና ምንድን ነው እኛ እንደ ጥበቃም ሆነን እዛ ላይ እንደ ዜጋም ሆነን የማንኛውም እንደው የኃይማኖት ፀሎት ከሌለ ዝም ብለው ጥያቄ ካለው
- ጥያቄው ተመልሷል
- አልተመለሰም ወደ ሌላ ቦታ ነው የሄዱት ምስክር እኔ ያልኮት መጀመሪያ አካባቢ ከብት እንዲገባ እየተፈቀደ በኋላ ነው የተከለከለው ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ በፊት ለካፍቴሪያው ይታረድ ነበረ እዛው ዝግጅት ነበረው ያው ይሸጥ ነበረ እንደማንኛውም ክበብ እና መጨረሻ ላይ ግረግሩ እየከፋ ሲሄድ ማለት ነው ሕዝቡም እንዲወጣ ስለተፈለገ ከፀሎቱ ቦታ እና በቃ ምግብ ከብት እንዳይገባ እንዲወጡ ማለት ነው ብለን ስንናገራቸው እና ለነሱ የመጣው ከብትን ለክበብ ነው ብለው አስገቡ እነሱ ግን መጨረሻ ላይ ያው ለክበብ አደለም ለተጠቃሚው ቀን ቀን ሳይሸጥ ቀርቶ ማታ ማታ ብቻ ነበር ለነሱ የቀረበላቸው
- አዛ መጀመሪያ ክበቡጋ ይታረድ እና ሳይሸጥ ሲቀር ለተከሳሾቹ
- አደለም እዛ ለክበቡ ይሰራል እና ማንኛውም ተጠቃሚ በገንዘቡ እየገዛ ይጠቀም ነበረ ግን ያው ለክበቡ የገባው ከብት ለሌላው ተጠቃሚ ተከልክሎ ለነሱ ብቻ ውስጥ ለሚያድሩት ብቻ ነበረ ከሁለት ሰዓት ተኩል በኋላ ዝግጅቱ የሚደረግላቸው
- ማን ነው የከለከለው ?
- ያው እዛ አካባቢ ያው አባሎቹን በቃ ክበቡም ያው ግርግር በጣም ስላለ እንዳይገባ ምናምን ተብሎ ነበር
- አባሎች ማለት የአወልያ አባሎች?
- አዎ ጥበቃዎቹ ማለት ነው ከዛ በኋላ ጥበቃዎቹ ሲከለክሉ ለክበብ ነው ተባለ ግን ያ ከብት ግን ታርዶ የቀረበላቸው ውስጥ ላደሩ ሰወች ነው
- ውስጥ ያድሩ የነበሩት እነማን ነበሩ?
- አረ በጣም ብዙ ናቸው
- ማለት ተማሪዎች ?
- አይታወቁም ተማሪዎቹም የሰፈር ሰውም ከሌላ የመጣውም በቃ በጣም የተለያዩ ሰወች ናቸው እዛ ሲያድረ በጣም የነሩት
- አሁን ይሄን ያድሩ የነበረው መጋቢት ግምቦት ብለው ነበረ ቅድም በየትኛው አመተምረት?
- ከሚያዝያ ወደዛ ነው የተጀመረው
- ማለት አመተምረቱን ያውቁታል?
- አዎ መጋቢት ማለት ነው
- ወሩን መጋቢት ግምቦት ይሆናል ብለዋል?
- አዎ ወደ መጋቢት አካባቢ ላይ በጣም ሲያድሩ ነበረ
- አመተምረቱ መቼ ነው?
- ያው 2004 ማለት ነው እኔ እዛ ነበርኩ በሚያድሩበት ሰዓት
- እርስዎ ተማሪዎች ተቃውሞ ሲያነሱ ነበሩ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተማሪዎችም ነበርኩ እዛ ተቃውሞ ሲያደርጉ ከዛ በኋላ ደግሞ በዛው ነው ማደር የጀመሩት ብርድ ልብስ ሁሉ እየመጣላቸው ማለት ነው
- በዚህ በግምቦት መጋቢት አካባቢ?
- አዎ መጋቢት አካባቢ አዎ
- ከባድ እረብሻ ሲሉ ምን ማለቶ ነው ቅድም?
- ያው ከባድ እረብሻ ማለት ያው በቃ በጣም የከበደ አስከፊ ነገር ነበር መቼም ያው ከባድ ነገርም የሰው ሕይወትም ባይጠፋ የሰወቹ የተማሪው ጩኸት የተለያዩ የሕዝብ ጩኸት ከባድ ነበር
- እስቲ ቆይ ምስክር ማለት ከባድ ብለው ቅድም ዘርዝረዋል በዋና ጥያቄ ላይ እሱ ላይ ተነስታችሁ እምትጠይቁት ጥያቄ ካለ ድጋሚ ያው እንደ ዋና ጥያቄ መልስ
- አብራርተዋል ከባድ እረብሻ እንጂ መገለጫው ምን ማለት እንደሆነ ድምጽ ጩኸት ነው ዱላ ነበረ ብጥብጥ እንደዚህ ነገር በማለት ይሄንን አላብራሩም?
- ጩኸት ነበር
- ጩኸቱን ነው ካባድ እረብሻ የሚሉት?
- አዎ ጩኸት ነበር እንደገና ደግሞ ይሄ አሊ መሃመድ ሲራጅ የሚባለው የመጣ ቀን ማለት ነው ያው እስከ መደብደብ ነገር ያው ደርሶ ነበር እሱ ሸሽቶ ሄደ እንጂ
- ጥሩ መሃመድ ሲራጅ ላይ ሕዝቡ አንድላይ ነው የተነሳው ወይ ተለይቶ የተነሳበት ሰው አለ?
- በቃ በአጠቃላይ ነው ሕዝቡ ግልብጥ ብሎ የተነሳው ያው አዳራሽ ውስጥ ነበረ እሱ እኛ ውጪ ነበርን እና በቃ ንግግሩን እንዲያቋርጥ አስደርገውት ከዛ በኋላ በቃ እሱ ሸሽቶ እየሮጠ ወጣ
- ስለዚህ እርስዎ ሕዝቡ አንድላይ ሲነሳበት ከጊቢ ውጭ ማለት ግቢ ውስጥ ነበሩ ?
- ግቢ ውስጥ አዎ ወደላይ ነበርን እኛ
- አቶ መሃመድ ሲራጅ አዳራሽ ውስጥ ነበር?
- እሱ አዳራሽ ውስጥ ነበር አዎ
- አላዩም ማለት ነው?
- እኔ አይቼዋለሁ እሱ አዳራሽ ውስጥ ነበረ ከዛ ጩኸቱን ስንሰማው ወደዛ ሄደ ስንሄድ ያው ፖሊሶችም ነበሩ
- የለም መሃመድ ሲራጅ ከአዳራሽ ወጥቶ ሲሮጥ ነው ያዩት?
- ሲሮጥ አዎ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በወቅቱ አቁመው አልጠየቁትም?
- አረ በጣም እንዴ እኛም ያው ስለምንፈራ ወደ መሃል የማንገባበት ሰዓት አለ
- ጥሩ ፖሊስም ነበረ ብለዋል ፖሊስ የትጋ ነበረ የዛን ሰዓት?
- ጊቢ ውስጥ ነበረ በር ላይ
- ማለት ግቢ ውስጥ ገብተዋል?
- ግቢ ውስጥ አዎ በር ላይ ነበሩ ልክ የግቢው በር አለ አደለም እዛ ላይ ነበሩ ከዘ በኋላ እረብሻውን ጩኸቱን ሲሰሙ እሱ ወደርሱ እሮጠ እነሱም ወደነሱ መጡ ከዛ እሱ በመሃል ሄደ ወጣ
- ሰው እሱን አባረረ እና ተመልሶ አዳራሽ ውስጥ ተቀመጠ ?
- በዛው ጩኸት ተነሳ እንጂ
- ምን አይነት ጩኸት?
- ያው በቃ አህባሽ ምናምን ይጥፋ መጅሊስ ይውደም ምናምን ነው እንግዲህ በአረብኛም ስለሆነ አይለይም
- እኮ ግቢው ማለት እሱን አባረሩት እሱ ወደ ፖሊሶች ሄደ ከዛ ወደ ውጭ ወጣ
- ከዛ ሕዝቡ ቅድም ያሉትን አህባሽ መጅሊስ የሚለውን ነገር ተናገረ?
- አዎ በአረብኛም ይናገራል
- ከዛ ያለፈ ነገር የፈፀመው ነገር የለም?
- አዎ
- ፀሐፊውን ሲያናግሩ የነበሩት ተማሪዎች ናቸው ወይስ የአካባቢው ሕብረተሰብ ነበረ ለይተው ንገሩን እስቲ?
- ያው ተማሪዎችም አሉ ያው በብዛት ግን ያው እዛ ብዙ ሰወች ስላሉ አይለይም
- እርስዎ እዛ ነው የምሰራው ስላሉ ነው ማለት ያን ጊዜ ጥያቄውን ሲመልሱላችሁ አዳራሽ ውስጥ ገብተው ነበር ፀሐፊው ብለዋል ማለት ጥያቄ የጠየቀ ማን ነው ለማን ነበረ መልስ የሚሰጡት የአካባቢው ሕብረተሰብ ምን ሆኖ የመጣበት አግባብ ነበር ነው ወይስ ተማሪዎች ብቻ ነው የነበሩት?
- ማለት ያው እዛ ተማሪዎችም አሉ ሌላ ሰውም አለ ሌላ ከተለያየ ቦታ የሚመጡ አሉ
- ሌላ ሰወችም ነበሩ?
- አዎ
- ሙስሊም
- አቤት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ስትናገር አቡበክር ያሲን ሼህ መክተ ኑሩ ቱሪኪ እና ፕሮፌሰር አህመድ ይናገሩ ነበረ ብለሃል?
- አዎ
- እስቲ አቡበክር ምን አለ?
- ማለት ያው በአጠቃላይ የተነጋገሩት
- አቡበክር ያለውን የምታውቀው ከሆነ አውቃለሁ የማታውቀው ከሆነ አላውቅም
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለን አሁን በመስቀለኛ ጥያቄ በድጋሚ ጥያቄ የተጠየቁትን በድጋሚ እንዲደግሙ አደለም መስቀለኛ ጥያቄ ካላቸው በዋና ጥያቄ ያሉትን መነሻ አድርገው መስቀለኛ ጥያቄ ይጠይቋቸው
- መላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት እኔ የጠየቅኩት ጥያቄ እቃቤ ሕግ እራሳቸው በዋና ጥያቄ ማብራራት ያልቻሉት ምስክሩን ጠይቀው በተደጋጋሚ ግልጽ ስላልሆነ ያለፉት ነው አቡበክር ምን አረገ ያሲን ምን አረገ አያንዳንዱን አልዘረዘሩም በደፈናው እንዲህ እንዲህ አሉ በደፈናው ደግሞ በደምበኞቼ ላይ ፍርድ እንዲሰጥ ሕግ አይጠብቅም እና ወንጀል ፐርሰናል ነው አቡክር ለብቻው ምን አረገ ያሲን ለብቻው ምን ተናገረ የሚለውን ነገር ምስክር ካወቁ ማስረዳት በቦታው ላይ ነበርኩ ብለዋል በዋና ጥያቄም ስለተነሳ ጥያቄው ሊፈቀድልኝ ይገባል ነው ስላልተብራራ ግልጽ ስላልሆነ ግልጽ እንዲሆንልኝ
- የቀረበ ጥያቄ አቡበክር ምን አደረጉ የሚል ነው የተነሳው መቃወሚያ ይሄ በዋና ጥያቄ ተነስቷል ዋና ጥያቄውን መድገሙ ተገቢ አደለም የሚል ነው ለዚህ የተሰጠውን ምላሽ በግልጽ ያልተጠየቀ ነገር አለ ለዛ ነው የጠየቅነው የሚል ምላሽ ተሰጥቷል ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል ጥያቄው ተነስቷል አልተነሳም የሚል ክርክር በእርግጥ አልተነሳም ጥያቄው ተነስቷል በግልጽ አልተጠየቀም እኛ እንጠይቅ ነው እያሉ ያሉት ነገር ግን መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ ያለበት ምስክር በግልጽ ያነሱትን ነገር ማስተባበል ማጣራቱ ከዛ በኋላ ያለው የፍ/ቤት ስለሆነ የተነሳው ነገር ላይ ቆመው መጠየቅ የሚፈልጉትን ከውስጥ መርጠው ጥያቄውን በዚህ መሰረት አስተካክለው ያቅርቡ ተብሎ ብይን ተሰጥቷል
- አመሰግናለሁ ሙስሊም
- አቤት
- አቡበክርም ያሲንም ሼህ መክተም አህባሽ አገራችን ገብቷል ብቻ ነው ያሉት?
- አዎ በቃ አህባሽ መንግስትም ተባብሯቸዋል መጅሊስን ብሎ ሁሉም ተደጋጋሚ ቃል ሁሉም ማች ነው ያወሩት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ኑሩ ቱርኪ እና ፕሮፌሰር አህመድም ይሄንን ነው የደገሙት ?
- አዎ ትክክል ነው ይሄንን ነው
- ኑሩም ቱርኪ ይሄንን አሉ?
- አዎ
- ቀድሞ ማን እንደተናገረ ያውቃሉ?
- እሱን አለየሁም
- መጨረሻስ የተናገረውን ያውቃሉ?
- እሱንም አለየሁም ግን እኔ ምንድን ነው በስማቸው ሲጠራቸው በቃ ተደጋጋሚ ቃል ተመሳሳይ ሲናገር ነው
- ይበቃል ሌላ ጥያቄ አዳምጡ ግልጽ ነው እሱ
- ቅድም ሙስሊም ጥያቄውን የጀመሩት ተማሪዎች ናቸው ብለው ነበረ ተማሪዎች እስቲ ምን ብለው ነው የጀመሩት ጥያቄውን?
- ያው መጀመሪያ ተማሪ እረበሸ ከዛ በኋላ በቃ እንደነዚህ አይነት ተመሳሳይ ሰወች ኃላፊዎት እኛም አንዳንዴ እዛ በምንጠብቅበት ሰዓት በምንኖርበትም ሰዓት እየወጡ የሚሄዱበት እየገቡ የሚሄዱበት ሰዓት ነበረ እኛ ባንለያቸው ማለት ነው
- ኃላፊዎቹን?
- አዎ
- የምን ኃላፊዎች ናቸው ?
- ያው ዳይሬክተሩም አለ ያው እንደዚህ በመኪና ፀጉሩ ልውጥ ብቻ በቃ ኤኒ ዌይ እማይታወቁ ሰወች በመኪና ይመጣሉ ሰው ሰግዶ ሲወጣ መስኪዱን ሰገደው ሁሉ እረጅም ሰዓት የሚቀመጡበት ሰዓት ሁሉ ነበር
- ይኸውሎት እኔ የጠየቅኩት ተማሪዎች ነው መጀመሪያ የጀመሩት ብለው ነበር ?
- አዎ
- ተማሪዎች ምን ብለው ጀመሩ ነው ጥያቄው ?
- ያው በቃ እኛ ምንድን ነው እኔ የማስታውሰው ባልታሰበ ሰዓት ወቅት ባላስታውሰውም ጩኸት ተጀመረ ከዛ በኋላ ይሄን ነው እኔ የማስታውሰው ጩኸት እረብሻ ነው የተጀመረው
- ተማሪዎቹ ቀጥታ ወደ ጩኸት ነው የገቡት?
- አዎ
- ተማሪዎቹ ነው ቀድመው የጮሁት ወይስ እነ አቡበከር ነው ቀድመው የመጡት?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ ያኔ እረጅም ሰዓት ነው ከዛ በኋላ ነው እኔ በቃ የማስታውሰው እኔ በስነስርዓት የሚያዝያ 11 ብቻ ነው በቃ እኔ ሆነ ብዬ አዳምጠው የነበረው
- ሚያዝያ 11 ላይ ተማሪዎቹ ነው ቀድመው የጀመሩት?
- ያኔ ተማሪዎች የሱም ሰላት ወቅት ብቻ ነው ያኔ እና በቃ እኔ የዚችን ወቅት ብቻ ነው የማስታውሰው በስነስርዓት
- አወልያ ጥበቃ ነበሩ ተብሏል አሁን በተከበሩ አቃቤ ሕግ አወልያ የት ነው የሚገኘው?
- አወልያ አስኮ ክልል ነው
- ምኑጋ አስኮ ብዙ ነው ክልሉ ?
- ያው አብስኮ ክልል እብነበረድ ኦሊቩ አለ አደለም እንዴ አስኮ ወደዛ በቃ አውቀዋለሁ ከኦሊቫ አልፎ አደባባዩ አለ አደለም ዊንጌት አልፎ ማለት ነው እዛ አካባቢ ነው
- አወልያ ምን ምን ነገር እንዳለ ያውቃሉ ውስጡ?
- ውስጡን ያው ት/ቤቶች አሉ መስኪድ አለ ወደ አራት በር የሚሆን ነገሮች አሉ በጀርባ በኩል ጫካ ነው
- ቅድም መሃመድ ሲራጅ መጣ ብለው ነበረ መሃመድ ሲራጅ አስቀድሞ የመጣባት መኪና አውቀዋል አይተዋታል እርስዎ?
- አዎ አይቻታለሁ
- ስትገባ እንዴት ነበር?
- ስትገባ በበር ነው የገባችው በበር ገባች አቆሟት ይቺ ጤና ክሊኒክ የለችም ይሄ እሬሳ ምናምን የሚታጠብበት ፊት ለፊት ጀናዛ የሚታጠብበት ፊት ለፊት እዛ አቆመ እና ገባ ከዛ ዛሬ መልስ አለ የሚባል ነገር ሰምተናል ከዛ በኋላ አዳራሽም ስብሰባ ነበር ወደዛ ገባ ከዛ ያው ተጋጩ ሲጋጭ ያው መልሱ አለተመቻቸውም መሰለኝ እየሮጠ ወጣ እሱ
- እኮ መልሱ መሃመድ ሲራጅ ይዞ የመጣው መልስ ሰምተዋል እርስዎ?
- እኔ አልሰማሁም ውጪ ነበርኩ እኔ ግቢ ውስጥ ነበርኩ ደ
- የሕዝቡ ጥያቄ መልስ ተሰጥቶ ነበር መሃመድ ሲራጅ ሲመጣ ከተማሪዎቹ ለተነሳው ጥያቄ መጅሊስ ይውረድ አህባሽ አገራችን ገብቷል የሚለውን ነገር በተመለከተ ምንድን ነው ያሉት ?
- ያው እኔ ግቢ ውስጥ ነበርኩ ምን እንደሚነጋገሩ አልሰማሁም ግን መልስ እንደሚያመጣ አውቅ ነበር ተነግሮን ነበር
- እሺ ግቢ ውስጥ ነበርኩ አሉ ?
- አዎ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ እሱን አላዩትም ?
- አይቼዋለሁ ሲሮጥ አይቼዋለሁ መኪና ውስጥ ሁሉ መግባት አቅቶት ቀጥታ እንደውም በታ ወደ ውጭ ነው የወጣው እሱ
- እሺ ከአዳራሹ እሮጦ ሲወጣ አይተውታል?
- አይቼዋለሁ
- እርስዎ ግቢ ውስጥ ነበረ አደለ አሁን እኮ ግቢ ውስጥ ነበርኩ አሉ?
- ይታያላ
- ይታዮታል?
- ግቢ ውስጥ ቢሆንም እኮ ይታያል እንደዚህ እኔ ግቢ ውስጥ ወደላይ ብሆን አዳራሹ እንደዚህ ፊት ለፊት ነው
- ሲወጣ ሲሮጥ አዩት?
- አዎ እንደዚህ ፊት ለፊት
- ሲወጣ ሲሮጥ አዩት?
- አዎ
- ማን ነበረ ሊመታው የሞከረው?
- አይታወቅም እሱ በብዛት ናቸው ወይ ብለው የወጡት
- እሺ ሊያድነው የሞከረ ሰው ነበር?
- ሊያድን የሞከረ ሰው አንድ ሱልጣን የሚባል ነበር ጥበቃ
- ምን አረገ?
- እሱ እንደውም ተመቷል
- ምን አረገው እሱ እንዴት አድርጐ አዳነው ?
- እንዲህ ተከላከለው
- በምን በእጁ?
- በእጁ እረጅም ልጆ ነው እንዲህ ሲከላከለው ሁሉ እሱን ሊመቱ ሲሉ ፎቅ ላይ ወጥቶ ሸሸ እሱ
- ሱልጣን?
- አዎ
- ከዛ እዛ የሆነ በር ነበረ ፎቁ ላይ ለጤና ጣቢያው የተሰራ ፎቅ አለ ተጀምሮ የተቋረጠ እና እዛ ገብቶ በሩን ዘጋ
- መኪናዋ ምኑ ነበረ ረዳት የደረሰባት?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጐማው ብቻ እና ታርጋው አምስት ጐማ ነው የተነፈሰው እስክነ እስክነ እስኮርቱ ጐማ ማለት ነው
- ከፍተውት ነው ወይስ ውጭ ነበር እስኮርቱ?
- አዎ ውጭ ነበር ከዚህ ዋላ በር የለችም
- እ?
- እዛች ላይ ጫፏ ላይ ነበረች
- ማን እንዳተነፈሰ አያውቁም?
- በብዛት አይለይም እንደዚህ አይነት ነገር
- እሺ አወልያ ቅድም ሲናገሩ የቆሙ አወልያ መኪኖች ተመቱ ብለው ነበር ?
- ተመቱ ሳይሆን ተሰባብረዋል እንደዚህ
- መኪኖቹ ነው የተሰባበሩት?
- አዎ
- ምናቸው ነው የተሰባበረው?
- ያው በቃ እነዚህ አለ አደለም መስተዋት
- መጀመሪያ ስንት መኪና ተሰበረ እሺ ?
- ወደ ሦስት መኪና የሚሆን ተሰብሯል የተጐዳ ነው ደህና መኪና ዝም ብሎ ቆሞ ሰርቪስ የሚደረግ አቧራም ቢሆን እና ከላይ ያው ኮፈኑ ደህና ነው እና እነሱ ሁሉ ተሰባብረዋል
- የዛን ቀን ነው የተሰበሩት?
- የዛን ቀን ሳይሆን ከዛ ወደዛ
- የዛን ቀን አልተሰበሩም?
- አዎ
- ስንት መኪና ተሰበረ የዛን ቀን ?
- ወደ ሦስት መኪና ተሰብሯል ብቻ እኛ ያየነው
- ከዛ በፊት?
- ደህና የሆነ መኪና በአጠቃላይ ያው ግቢ ውስጥ አንዳንዱ ስለምንዞርም ደህና መኪናኖች ነበሩ በዛ በግርግሩ ኬዝ 3 መኪና ተሰባብሯል
- ከሚያዝያ 11 በፊት ነው?
- አዎ በቃ ያው ግርግሩ ከተነሳ ወቅት ጀምሮ
- ሚያዝያ 11 የተሰበረ መኪና አለ እርስዎ ያዩት?
- ያኔ የለም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስንት መኪና ተሰበረ ነው የምሎት?
- 3 ብለዋል
- እሺ የትኛው የትኛው መኪና ተሰበረ?
- ያው መኪና ይቆማል በብዛት አለ እዛ አካባቢ ግቢ ውስጥ
- አይነቶቹን የሚያውቃቸው ከሆነ ትልቅ ትንሽ መኪና እያሉ ?
- ያው ላንድ ክሮዘር ናቸው
- ሦስቱም?
- ሦስቱም ያው ላንድ ክሮዘር ናቸው
- መስታወታቸው ነው የተሰበረው?
- አዎ መስታወታቸው እና ያው እነዚህ ከላይ ከጂላቸው ብዙ ፍሬቻ ምናምን ተሰባብሯል
- ቅድም ከብት ታረደ በክበብ አማካኝነት ምናምን ብለው ነበረ ሰው ብርድልብስም ይዞ ይገባ ነበር ብለዋል ትክክል ነኝ?
- ትክክል አዎ
- ይሄ የሆነው አወልያ ምግብ ስለከለከለ እና ተማሪዎችን ስላባረረ ነው አደል?
- ማለት ያው እንዴት ጥያቄው ይደገምልኝ
- ምግብ ከዉጭ መግባት ተከለከለ ?
- እሱ ትዝ አይልኝም
- ጥበቃ ነበሩ እርስዎ?
- አዎ
- ያው ትዝ አይለኝም አላስታውስም ካሉ
- መከልከሉ እኔ ትዝ አይለኝም
- እሺ ምግብ ይገባ ነበር ?
- ምግብ ይገባል እኔ
- ብርድልብስም ይገባል?
- ብርድልብስ ምግብ ኃይላንድ ሁሉ ይገባል
- እሺ ከዚህ በፊት ይገባ ነበረ?
- ከዚህ በፊት ያው ለክበቡ ነው የሚገባው
- እኮ አሁን ለምን መግባት ቻለ?
- አሁንማ መግባት የቻለው ኬዙም እራሱ ብርድልብስ ኃይላንድ አይቻለሁ እኔ እና ምግብ ሁሉ በመኪና ሁሉ አንዳንድ ምግቦች ይመጡና ይገባሉ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ እነዚህ ነገሮች መግባት የጀመሩት?
- መግባት የጀመሩት እዛ ማደር ከተጀመረ በኋላ ማለት ነው
- እዛ የሚያድረው ማን ማን ነው ተማሪዎች ማደሪያ አለ አደል?
- አይታወቅም ተማሪዎች ዶርማቸውን ሁሉ ጥለው መስኪድ ውስጥ ነበረ የሚያድሩት
- ግን ማደሪያ አለ የተማሪዎቹ?
- አዎ የተማሪዎች ማደሪያ ዶርም የሚያድሩ አሉ የተወሰኑት
- ቆይ ተማሪዎቹ ናቸው ለማደር የሚገቡት?
- አረ ከተማሪዎቹ ሌላ ሕዝቡ እራሱ
- ሕዝቡ የት ይገባ ነበር?
- መስኪድ ውስጥ
- ዶርማቸውስ?
- ዶርማቸው ውስጥ እንደውም የሚያድር ሰው አልነበረም ቀርቶ ነበረ
- እርስዎ ማታ ማታ ጠብቀው ያውቃሉ?
- እዛ
- እ?
- አዎ በብዛት እንደውም እኔ ያው ማታማታ ነው የማድረው
- ይቀያየራሉ ከገበሬዎችጋር?
- እ?
- ማን አለ ዘበኛ ከሱልጣን ሌላ እርስዎ ሱልጣን ሌላ ማን አለ?
- ብዙ አሉ እሬድዋን የሚባል አለ እዛው የአወልያ ግቢ
- እሺ ሌላስ?
- በብዛት አሉ እኔ ስማቸውን ባላውም እሬድዋን ትዝ ይለኛል እሬድዋን የሚባል አለ
- ስንት ናቸው ዘበኞቹ?
- እዛ የሚያድሩት ወደ አራት አምስት ናቸው
- ከእርስዎጋር የሚያድሩት?
- አዎ ብዙ የሚያድሩ አሉ አዎ
- ከዛ በፊት የአወልያ ጥበቃ የነበሩ የት ሄደዋል ?
- እሱን አላስታውስም እዛው ሲሰሩ ነበር
- አንድላይ ነበሩ?
- አዎ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ከብቱን ማን እንዳረደ አያውቁም?
- ከብቱን ያው
- በክበብ አማካኝነት ያሉትን ከብት ማን እንዳረደ ያውቃሉ?
- እሱን አላውቅም
- ቅድም
- ጥያቄ እየተደጋገመ ነው
- አልደግምም የተከበረው ፍ/ቤት
- የተደጋገመ አለ እየመዘገብን ነው ያለው የተደጋገመ ነው
- እሺ አስተካክላለሁ
- ቅድም አህባሽ ይጥፋ ሲሉ ነበር ብለዋል አህባሽ ጠፋ እንዴ?
- እኔ አህባሽ የሚባል እነሱ ሲሉ ነው እንጂ የምሰማው እኔ የማውቀው ነገር የለም
- አልጠፋም አለ?
- አረ እኔ እንደውም አህበሽ የሚባል አበሻ ነው የማውቀው እንግዲህ ዜጋችን ያሉው ቅጽል ስማችን ነው እንጂ እነሱ ነው የሚሉት
- ጨረሳችሁ
- ምስክር
- አቤት
- ቅድም ኮሚቴዎች ከመንግስት ጋር ኮንታክስ ነበራቸው የሚል ነገር ተናግረዋል?
- አዎ
- እነማን ነው ኮሚቴዎች የሚሏቸው?
- እንዴት ይደገምልኝ
- ኬሚቴ ማለት ኮሚቴ የሚባሉትን ያውቃሉ?
- ኮሚቴ
- ኮሚቴዎች ከመንግስት ጋር ኮንታክት ነበራቸው ብለዋል ?
- አዎ
- እነማን ናቸው ኮሚቴ ?
- ያው እነሱ የመረጧቸው ኮሚቴዎች ነበሩ
- እነማን?
- ያው እነዚህ ሕዝቡ የመረጣቸው ያው ወደ 11 ነው እንደዚህ ባላስታውስም ወደ 11 ኮሚቴዎች ከሕዝቡ ተመርጦ ተብሎ በየመስኪዱ ማለት ነው እና አብዛኛውም የተመረጠው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ከሸህ ኦጀሌ እና ከአወልያ ክልል ውስጥ ነው እና እነሱ የመረጣቸው መንግስትጋ ሄደው መልስ ያመጣሉ የሚባል ነገር ነበር እና እነሱ ነው ኮሚቴ የሚባሉት እና መጅሊስ እና መንግስት ያው ከቨር እያረገላቸው ነው የተባለው

- ለማን ለኮሚቴዎቹ?
- ለመጅሊስ
- ጥሩ ኮሚቴዎቹ እንዴት ነበረ የተመረጡት እዛ ?
- ያው እራሳቸው ነው የመረጧቸው
- ሕዝቡ?
- ሕዝቡ እዛው በቃ
- እንዴት አርጐ ማለት እየጠቆመ እየፈረመ እንዴት አርጐ?
- ያው በቃ ይፈርማሉ ፊርማም አሰባስበዋል እዛው አወልያ ግቢ ውስጥ ተሰባስበው ፊርማ ሰባስበው ከዛ እከሌ እከሌ ተመርጧል ብለው እንደ ድጋፍ አርገው ነው ያው ኮሚቴ ብለው የሚያረጉት እራሳቸው ማለት ነው
- ከመንግስትጋር ኮንታክት ያረጋሉ ሲሉ በምን መልኩ ?
- ያው ከመንግስት ጋር ኮንታክት አርጐ እየተመላለሱ ነበር ያኔ
- ወደ መንግስት?
- ወደ መንግስት እየሄዱ ጥያቄ ሲጠይቁ ነበረ መሰለኝ እና ያው እነሱ የሚሉት መንግስትጋር ይሄዳሉ በዚህ ቀን ቀጠሮ አላቸው መልሱን አነግራቸዋለን እያሉ ነው የሕዝቡም ሲሸኙ የነበሩት አርብ አርብ ማለት ነው
- መልስስ ተሰጣቸው እንዴ ቅድም መልስ ይሰጠናል ሲሉ ነበረ ብለዋል እርስዎ እዛ ዘበኛ ስለሆኑ?
- አዎ
- መልስ ተሰጣቸው እንዴ?
- ያው በቃ መንግስት ግን ያው መልሱን አልመለሰልንም ብለው ነው ኢንፎርም የሚያረጓቸው ለሕዝቡ እና መንግስት መልሱን ያልመለሰልን ኬዝ መጅሊስም ለነሱ ነው የሚደግፈው እያሉ ነው ሕዝቡን ኢንፎርም የሚያረጓቸው
- ሙስሊም
- አቤት
- የግርግሩ መነሻ የአስተማሪዎች መባረር ነበር ይሄን ታውቃለህ አንተ?
- ጥያቄው ይደገምልኝ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለግርግር አወልያ ለነበረው እንቅስቃቄ መነሻ አንተ እዛ ነው የምሰራው ስላልክ ማለት ነው የተባረሩ አስተማሪዎች ነበሩ የምታውቀው ነገር አለ?
- እኔ በዚህ ነገር የለም
- የለማሽውም የለም?
- የለም አዎ
- ሙስሊም
- አቤት
- እርዎ ቅድም እንዳሉት ያው በተደጋጋሚ ገልፀዋል እዛ ግቢ ጥበቃ አባል ኖት?
- አዎ
- እሬድዋን እንዳለ ገልፀው ነበረ የዛን ቀን ?
- አዎ
- ጊሳ የሚባል ጥበቃ ነበር እንዴ የዛን ቀን?
- ጊሳ ነበር አዎ እንደውም የጥበቃው ሺፍት ኃላፊ ነበር እሱ
- የት ነበር እሱ?
- ጊሳ እንደውም በብዛት እዛ ነው እሱ ያለው
- መሃመድ ሲራጅ ሲሸሽ የት ነበረ እሱ ያስታውሳሉ ?
- እሱ እዛው ነበረ እንደውም
- የት?
- እዛው ግርግሩ ላይ ነበር
- ግርግሩ ላይ?
- አዎ እንደውም እሱ አዳራሽም ሳይገባ አይቀርም መሰለኝ
- ግምት ሳይሆን ያዩትን በትክክል ?
- በወቅቱ እሱ እዛው ዲል ነበረ እሱ እዛው ከግቢም አይወጣም ነበረ በብዛት
- እኮ ግቢ ቦታ ነው እንጂ ያዩት ግርግር ቦታው ላይ አላዩትም ?
- በብዛት ግን እሱ ያው እዛው ነው ግን
- ተቃውሞ
- እዛው ግርግር ላይ ነበር
- አይቼዋለሁ አዎ
- ሁለት ነገር ስለተናገሩ ነው
- ቆይ ቆይ ምስክር

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አንዴ ግቢው ላይ ነበር አሉ አንዴ ግርግር ላይ ነበሩ አንዱን እንዲነግሩን ብዬ ነው የትኛው እንደሆነ የቱጋ ነው በትክክል ያዩዋቸው ነው ?
- በዛ ወቅት በቃ እሱ እዛው ነበር አንድላይ ነበር አዳራሽም ሳይገባ አይቀርም ገብቷል
- ሳይገባ አይቀርም ነው አይተውታል አዳራሽ?
- እይቼዋለሁ
- ምን ሲያረግ አዩት?
- ያው አዳራሽ ውስጥ ገብቶ ሲወጣ አይቼዋለሁ ከግርግሩጋ
- ገብቶ ሲወጣ ነው እንጂ ሌላ ምንም ነገር ሲያረግ አላዩም ?
- አላየሁም አዎ
- በአወልያ ኢማሙ መባረሩን አያውቁም?
- አይ እኔ አላውቅም
- 36 ተማሪዎች ?
- አይ በዚህ ምንም ነገር
- ያኔ የነበረው መጅሊስ አሁን አለ?
- የመጅሊስ ኃላፊዎች ማለት ነው?
- እሺ ኃላፊዎች አሉ?
- የሉም አሁን
- የት ሄዱ?
- ያው ወረዱ በሕዝቡ ምርጫ ወረዱ ሕዝቡ የራሱን መረጠ አዲሶች ናቸውአሁን ያሉት
- በቃ ግልጽ ነው ቀጥሉ
- ስለዚህ ቅድም በሕዝቡ የነበረው ጥያቄ መጅሊስ ይውረድ የሚለው በሱ መሰረት ነው የወረዱት?
- ተቃውሞ አለኝ የተከበረው ፍ/ቤት
- በዚህ ተቃውሞም አናስነሳም ጥያቄው በቃ ተመልሷል በቂ ነው መጅሊሱ እንዴት እንደወረደ ግልጽ እኮ ነው እሱ
- ፍ/ቤቱ ካወቀው እሺ አመሰግናለሁ
- ይኸውሎት አሁን እንዲህ አይነት የስላቅ ንግግሮች ተደጋግመዋል ይኸውሎት በፊትም ቢሆን እንደህ ነው ሲል ይበቃል ሲሎት አዎ ይበቃል አይነት ነገር ቅድምም ሳሳ ሲባል ሳሳ እንዴ እንዲህ አይነት የስላቅ ንግግሮች ፍ/ቤቱ ላይ ያላችሁን ከበሬታና እና ሌላ ነገር ነው የሚያሳየው ከከበሬታ በግልባጭ ማለት ነው ስለዚህ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ ከሰጠ ትእዛዝ ሰጠ ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ከዛ ደግሞ የሆነ የስላቅ ንግግር ነው የሚመስለው ስለዚህ እንዲህ አይነት ነገሮች ቢታረሙ ጥሩ ነው

- ላስተባብል ፍ/ቤቱ በዛ እንዴት እንደተረዳ እንጃ እኔ እሳቸው የተረዱትን መንገድ ፍ/ቤቱ በዚህ መልኩ ከተረዳኝ እሺ እኮ ነው ያልኩት ስላቅ የተከበረው ፍ/ቤት ከኔም አይጠበቅም ላደርግም አልፈልግም እንዴት እንደተረዳ እነጃ እኔ ምስክሩ በዚህ መልኩ ከተረዳው እሺ እኮ ነው ያልኩት ሌላ ነገር የስላቅ
- እሺ እንግዲህ ምናልባት እኔ አንዳንዴ እንደልምዴ ስለሚመስለኝ ነው እንደዛ ከዛ ወጣ ያለ ከሆነ
- ይቅርታ
- ይሄ ከሌለ ጥሩ ነው ካለ ግን ይስተካከል
- አመሰግናለሁ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ድጋሚ ካለ
- እሺ ሙስሊም ቅድም በተደጋጋሚ ስትጠየቅ ሕዝቡ መርጧቸው ነው ብለሃል እራሳቸው የመረጧቸው ብለሃል አንተ መርጠሃል እንዴ?
- አዎ ምርጫውን መርጫለሁ እንደ ዜጋም እንደ ኃይማኖቴም
- አይ የመጅሊሱን አደለም ኮሚቴው ሲመረጥ ተገኝተህ መርጠሃል እንዴ?
- አረ እኔ በብዛት እንደውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘጠና ፐርሰንቱ ይሄን ኬዝ አያውቀውም
- እ?
- እኔ አልመረጥኩም
- እሺ ጨርሰናል
- ምስክር ለምን አለመረጥክም?
- የግርግሩን
- አደለም ኮሚቴዎቹ ሲመረጡ እኔ አልመረጥኩም ብለሃል ለምን አልመረጥክም?
- አካሄድ ቆንጆ እኔ ስላልተመቸኝ አካሄዱም ያው አግባብ ያልሆነ ነገር ስለሆነ አንድ ሰው ያው ነፃነት ባለበት ሰዓት
- የመረጣቸው ማን ነው ታዲያ አንተ ሙስሊም ነህ አደለ ?
- አዎ
- አንተ እዛ ነው ጭራሽ አወልያ ነው የምትውለው ሰራተኛም ነህ ?
- ትክክል
- አንተ ካልመረጥክ ታዲያ ማን ነው የመረጠው?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላ ሰው ነው የመረጠው
- እኮ ማን ምን አይነት ሰው?
- ያው በብዛት በቃ የተወሰነው ያው አስር ፐርሰንት የሚሆን ሃያ ፐርሰንት የሚሆን ነው በራሳቸው ያፈራረሙት
- አሃ በራሳቸው ያፈራረሙት?
- በራሳቸው ነው የሆነች ወረቀት አለች እንደዚህ ቅርጽ የወጣች እና በቃ በሷበቃ ይሰጣል የሚቀርበው ሰው ለሚቀርበው ሰው ይሰጠዋል ይፈርማል ከዛ አብዛኛውን እንደውም እንደውም ወረቀቱ አደራሻም ምናምንም አይኖረውም የሰውየው
- ስለዚህ አንተ አትቀርብም ማለት ነው ?
- ወደዛ አካባቢ እኔ እንደዚህ አይነት ነገር ውስጥ እኔ እንደውም በብዛትም እኔ ለመስገደድም እራሱ ግርግሩን እኔ እንትን ስለማይለኝ አልገባም
- እሺ እርስ በርሳቸው ተፈራረሙ ስትል ሃያ ፐርሰንት የምትላቸው አስር ፐርሰንት የምትላቸው ከምኑ ነው?
- ማለት ያው በብዛት
- ከአጠቃላይ ከምኑ ነው?
- ከአጠቃላይ ከሙስሊሙ ሕብረተሰብ በቃ አስር ፐርሰንት ሃያ ፐርሰንት ነው እንደዚህ ተፈራርጦ መረጥን ያሉት
- ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቅ ሃጂ ጊሳ ግርግሩ አካባቢ ነበር በተረፈ ሌላ ነገር ሲያረግ የተለየ ነገር ሲያረግ አላየሁትም ብለሃል?
- አዎ
- አንተ ሃጂ ጊሳን ትከታተለው ነበር እያንዳንዱን ነገር የሚያረገውን እንዴ?
- አልከታተለውም አረ
- እሺ ድጋሚ ጥያቄ አበቃን
- የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ እስቲ ምስክር ቅድም ሲናገሩ ያሲን ኑሩ አቡበከር ሼህ መከተ እና ሙደስርን ጠቅሰው ነበረ እና ?
- አዎ
- በነዚህ ሰወች ላይ ለመመስከር ነው የመጣሁት አሉ?
- አዎ ትክክል
- የተወሰኑ ሰወች አቡበከር ተናገረ ያሉትን ያሲን ኑሩ እንደዚህ ኑሩ ቱርኪ ብለውም አስመዝግበው እስቲ የሼህ መከተ እና የሙደስር በግልጽ የተናገሩትን ነገር እኛ አልያዝንም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ስለዚህ እስቲ ሼህ መከተ ሁላቸውም የተነጋገሩት ተመሳሳይ ነው እሱን ደግመው ነው የሚል ነገር አንስተዋል ሲናገሩ?

- ትክክል አዎ
- እስቲ ሼህ መከተ የተናገረውን በግልጽ የሚያስታውሱት ነገር ካለ እሱን ይንገሩን?
- ያው እኔ በአጠቃላይ እንደያዝኩት ያው በቃ ይሄ ሃበሽ የሚባል ትምህርቱንም ያው አላቁረጠም እና በቃ ይሄኛው እስከሚቋረጥ ትግላችንን ቀጥለን መልሱን እንደምናመጣ ነው ብለው ነው ተደጋጋሚ ቃል የሚናገሩት ሁሉም
- መልሱን እናመጣለን ?
- አዎ
- ትግላችን በምን መልኩ እንቀጥላለን የሚለውን ነገር ?
- ያው በቃ እስከመጨረሻው ነው የሚሉት
- እስከ መጨረሻው ማለት እስከ ምን ድረስ የተናገሩት ነገር አለ?
- የለም
- እሺ ሙደስርስ ?
- ሙደስር እሱ አስተዋዋቂ ሃጂ እከሌ ይቀጥላል ይላል እሱ ነው ፕሮግራሙን የሚመራው የነበረው እሱ ነው
- እሺ
- አቃቤ ሕግ ዳኞች ጠዋት የነበሩት አልተቀየሩም አቃቤ ሕግ አንድ ብቻ ነው ያሉት
- ዘረሰናይም አለ
- ኦኬ ለጊዜው ያሉት አቃቤ ሕግ ስሞን ያስመዝግቡ
- ብርሃኑ ወንድምአገኝ
- ተከሳሾች ያው ከ29 ውጪ ሌሎቹ አላችሁ መጥቷል እሱ ሁሉም ተሟልቷል እሺ ጠበቆች
- ጠበቆች ሃሰን ሁሴን ባህሩ መካንጋ አዲስ መሃመድ
- ስለ 28ኛ ተከሳሽ አህመድ ጀማል አ
- እሺ የአቃቤ ሕግ ምስክር ይቅረብ
- እሺ ዘረሰናይ ምስግና ቀርቤያለሁ
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም
- ምያለሁ
- ለምስክርነት ነው የመጡት?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ለምስክርነት
- እሺ የአባቶን ስም ሳይጨምሩ የራሶን ስም ብቻ ይገልፁልኛል ?
- እንድሪስ አህመድ
- እሺ አቃቤ ሕግ ስንተኛ ላይ ናችሁ?
- ተራ ቁጥር 66
- እሺ በተሰሙት ቅደም ተከተል 25ኛ ምስክር ላይ ደርሰናል በምስክሩ የማስረጃ ዝርዝር ላይ ግን 66 ላይ የተጠቀሱት ለምስክርነት የመጡት በነማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?
- በሰይድ አሊ እና ባህሩ ዑመር በነሱ ላይ ነው የምመሰክረው
- በሁለት ሰው ላይ?
- አዎ
- እነዚህ ሰወች በአካል ለይተው ያውቃሉ?
- ሰይድን አንድ ቀን እይታ ቢሆን
- እ?
- ባህሩን መለየት አልችልም ሰይደን አንድ ቀንም ቢሆን ካልተለወጠብኝ ልለየው እችላለሁ
- ስለዚህ መለየት ይችላሉ?
- አዎ
- እሺ ከቻሉ ለይተው ያመልክቱ ተነስተው ማየት ይችላሉ ተቀመጡ እንደተመቾት
- ሹራብ የለበሰ ማን ነህ አንተ እሺ 16ኛ ተከሳሽን አመልክቷል ባህሩ ኡመርን መለየት አልችልም ብሏል እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- እሺ አቶ እንድሪስ የመጣሁት ለምፋክርነት ነው የምመሰክረውም በሁለት ሰወች ላይ ነው ስማቸውን ጠቅሰው አንደኛውን ለይተዋል የት ነው የሚያውቋቸው ?
- ሰኔ 29 ቀን ላፍቶ ወረዳ 12 ቢላል መስኪድ ጁምአ ቀን የስግደት ቀን ስነበረ እዛ ቦታ ላይ
- ፊቶትን ወደዚህ አዙሩ እንደተቀመጡ ያው የተጠየቁትን አገናዝበው ይመልሱ
- እና በዛ በስግደት ቀን ጁምአጋ ስለነበረ እዛ ቦታ ላይ ነው የማውቃቸው በሰዓቱ ጁምአ ቀን ነው ጁምአ ቀን እንደመሆኑ መጠን ሰጋጁ ብዛት ነበረው መስኪድ ደግሞ የዛን ቀን አዲስ የተከፈተ ነበር
- የት የሚገኝ መስኪድ ነው ማን የሚባል መስኪድ ነው?
- ወረዳ 12 ቢላላ መስኪድ
- የት ክ/ከተማ?
- ንፋስ ስልክ ላፍቶ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምንድን ነው እዛ ያዩት ወይ የሰሙት?
- ያየሁት በሰዓቱ ጁምአ ቀን እንደመሆኑ መጠን ለስግደት እዛ ቦታ እየሄድኩ ነበር ስራ አካባቢዬም እዛው ስለነበረ ስድስት ሰዓት አካባቢ ላይ ሄድኩኝ በጣም ብዛት ያለው ሰው ተገኝቶ ነበር ከዛ በኋላ ስግደቱ ከተከናወነ እና ሰባት ሰዓት እንደተጨረሰ /ግልጽ ያልሆነ/ ይቃጠል መጅሊስ የሚል መፈክር ተሰማ ከዛ በኋላ ይሄ በጣም እየተስተጋባ ሄደና ጤነኛው ሰው ሽማግሌው ደካማው ሕፃናቱም አንዳንዶችም እየወጡ ወደቤታቸው በሚሄዱበት ሰዓት በግምት ከአንድ ሺ በላይ የሚሆኑ ሰወች እዛ ውስጥ ተከማችተው ቀሩ መስኪድ ውስጥ እና ይሉ የነበረው ሰይድ መልክት አስተላለፈ ከዛ በኋላ ሲያስተላልፍ ሙስሊም ፈሪ አደለም ሙስሊም አይፈራም ደማችን ይፈሳል እንጂ የዚህ መስኪድ ካርታ እና ፕላን ቁልፍ ካልተሰጠን ማንም ሙስሊም ከዚህ እንዳይወጣ የእ ናን መብት እኛ እንጂ የምናስከብረው መጅሊስ እና መንግስት ሊያስከብርልን አይችልም መንግስት እና መጅሊስ ሌባ ነው የሚል መልክት አስተላለፈ ከዛ ሌላውም አስፈላጊ ከሆነ ከውጭ ሌላ ኃይል ይጨመራል አለና እሱ ወጥቶ ሄደ
- ለምን ጉዳይ?
- ለምን እንደሄደ አላውቅም
- አይ ሌላ ከውጪ ካስፈለገ ከውጪ
- ሌላ ኃይል ይጨመራል እንጂ
- ለምን?
- እንግዲህ ያው ከመነሻው እርእስጋር የተያያዘ ነገር ይመስለኛል
- ምን ስለነበረ ነው ተጨማሪ ኃይል ያስፈልጋል እየተባለ ያለው ?
- የመስኪዱ ካርታ እና ፕላን በእጃችን ቁልፍ ካልገባ ከዚህ መስኪድ ማንም ሰው እንዳይወጣ ሙስሊም ሞት አይፈራም እኛ የመስኪዱ ካርታ እና ፕላን በእጃችን እስከሚገባ ድረስ ማንም ሙስሊም ከዚህ እንዳይንቀሳቀስ አስፈላጊ ከሆነ ከውጪ ሌላ የሰው ኃይል እንጨምራለን
- ማን ነው ያሰራው መስኪዱን አሁን ካርታ እና ፕላን በእጃችን ካልገባ ?
- መስኪዱን የሰራው አንድ /ግልጽ ያልሆነ/ የተሰራው በመጅሊስ ስም ነው
- ስለዚህ የማን ካርታ እና ፕላን ነው ታዲያ እጃችን ይግባ የሚባለው ?
- የዛ መስኪድ ካርታ እና ፕላን መጅሊስ ከሆነ የወሰደው ሌላ አካል ከሆነ የወሰደው በእጃችን ቁልፍ እና ካርታውን ፕላኑን ይስጠን ሲባል የነበረው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን ማለት ነው ይሄ ማለት ፕላን እና ካርታው በእጃችን ይግባ የመስኪድ ፕላን እና ካርታ በግለሰብ ነው እንዴ የሚያዘው?
- በእኛ ስር መተዳደር አለበት አይነት ነገር ነው
- እነማን ናቸው እነሱ?
- እንግዲህ እዛ የተሰባሰቡት አሻቢሉዲስ ይቃጠል መጅሊስ መንግስት እና መጅሊስ ሌባ ነው እኛን አይወክለንም እኛ የራሳችንን መብት እኛ ነን የምናስከብረው ሜዳውን ተቆጣጥረናል የሚል መፈክር ይሰማ ነበር
- ሚያዲያ?
- ሚዲያውንም እኛ ተቆጣጥረነዋል
- የትኛውን ሚዲያ?
- እንግዲህ እዛ ያለውን እንጂ ሌላውን አላውቅም በሰዓቱ ያው ማይክ የሚነጥቀው በእጃቸው ነበር እዛ መስኪድ ላይ
- አሁን ያሉት የአማርኛ ሶሎጋን የሚመስል ነገር ምን ማለት ነው ?
- ማለት?
- አሁን ያሉት?
- /ግልጽ ያልሆነ/ ይቃጠል መጅሊስ
- አዎ
- እንግዲህ ያልመረጥናቸው አይገዙንም አይነት ነገር ይመስለኛል
- አረብኛ ነው ምን ቋንቋ ነው?
- አብዛኛውን እኔ እንግዲህ የማየው ዲሽ ላይ ላይ የውጪ እስራኤላውያኖች ወይም ሌሎች መፈክር የሚያደርጉት ነገር ነው የማውቀው እንጂ እዚህ አገር ላይ የምንጠቀመው ቋንቋ ነው ብዬ አልወስደውም
- እሺ አቶ ሰይድን በዚህ መልኩ ይሄን ሲሉ ሰምተዋል ?
- አዎ
- አቶ ባህሩንስ በአካል አናውቃቸውም ብለዋል ስማቸውን እንዴት አወቁ?
- በአካል አላውቀውም ግን
- ስማቸውን እንዴት አወቁ?
- ስማቸውን ያወቅኩት እዛው ካለው ከአንድ ሺ በላይ የተሰባሰቡ እየተደወለለትም ሁሉ የሚጠራ ሕዝብ ሌላም ስለነበረ ምንድን ነው ማን ነው ይሄን መልእክት እንደዚህ የሚያስተላልፈው ብዬ ጠየቅኩ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እየተደወለለት ?
- ከሌላም ቦታ እየተደወለለት እየወጡ እየደወሉ እዚህ ቦታ እዚህ ቦታ ብላችሁ ታክሲ ይዛችሁ ኑ እየተባሉ የሚጠሩ ሰወችም ነበሩ እና ከነዛ መካከል ማን ነው ይሄን መልእክት የሚያስተላልፈው ብዬ ስጠይቅ ይሄን መልእክት የሚያስተላልፈው ሰው ባህሩ ይባላል አካባቢውም ወደ ጀርመን አደባባይ ነው መካኒሳ ሰፈር አካባቢ ነው ከዛ ነው የመጣው
- ለምንድን ነው ስሙን የጠየቁት እርስዎ ከዛ ሁሉ ሰው?
- አካባቢው በጣም ታውኮ ነበር እና ፀጥታው ትንሽ በጣም አካባቢውን በጣም ያናውጣል ጥሩ ሴንስ አልነበረውም በሰዓቱ ስለዚህ ከዛ አንፃር እኔ እንደ ፀጥታ አካባቢው ፀጥታ እንዲኖረው እፈልጋለሁ ማንም ሰው ፀጥታ ተከብሮለት እንዲኖር ማንኛውም ሰው የራሱ ፍላጐት ይሆናል
- ገብቶኛል አሁን የእሳቸውን ስም ለምንድን ነው ማወቅ የፈለጉት ከዛ ሁላ ሰው ?
- በሰዓቱ መልክቱ ጥሩ ስላልነበረ
- መልክቱ ምን የሚል መልእክት ?
- መልእክቱ እንደዚህ ነበረ ማለት መንግስት እና መጅሊስ ሌባ ነው የእኛን መብት እኛ ነን እንጂ የምናስከብረው ማንም ሊያስከብርልን አይችልም ሙስሊም ደም አይፈራም ሙስሊም ሞት አይፈራም ደማችን ይፈላል የሚባል ነገር ነበረ እንግዲህ ሙስሊም ደሙ ይፍሰስ የሚል መልእክት የለም እንደ ኃይማኖታችን ሕግ ሙስሊም አዛኝ ነው ሙስሊም ልማት ነው የሚባል ነገር ነው
- እሺሌላ
- በመልክት መለየት ያልቻሉት ለምንድን ነው?
- በሰዓቱ ውስጥም ስለነበረ ብዙ ሰው ውስጥ ነው ገብቼ ያን ማወቅ ትንሽ እቸገራለሁ
- ውስጥ ማለት እስቲ ይንገሩን አቀማመጡን
- መስኪዱ ውስጥ መስኪዱ በጣም ሰፊ ነው እዛ ውስጥ እንግዲህ ከአንድ ሺ በላይ የሚገመት ሕዝብ ነበር እዛ ውስጥ ለብቻ ግሩፕ ፈጥረው እንትን ያሉት ስግደትም ሲደረግ ለብቻ ነው የተሰገደው ሁለት አይነት ስግደት ነው የተደረገው በዛ መካከል ሰውን ለመለየት ትንሽ ያዳግት ነበር
- ስንት አይነት ስግደት ?
- ሁለት አይነት ስግደት ነው ሌላው ያ እየሸሸ ይሄድ የነበረው ሰው በኋላ መጥቶ ለብቻው ሰገደ እነሱም ለብቻቸው በኋላ ሰገዱ በነዚህ ተከትለን አንሰግድም ተባለ ከዛ ወጥተው እነሱም ለብቻቸው እዛው ለብቻ ይሄኛው ከተሰገደ በኋላ እነሱ በኋላ ሰገዱ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማንን ተከትለን አንሰግድም?
- ይሄ የመስኪዱን ኢማም ተከትለን አንሰግድም እነዚህ ካፊሮች ናቸው ነው የሚሉት እነሱን ተከትለን መስገድ ስለሌለብን ሌላ እኛ ለብቻችን እንሰግዳለን አሉ የመጀመያው ኢማሙ የዛ የመስኪዱ ኢማም አሰገዱ ካሰገዱ በኋላ እነሱ ደግሞ ለብቻቸው ሰገዱ ስለዚህ እዛ ውስጥ ነው ለመለየት ትንሽ ያዳግት ነበር ያለው ብዛት ሰው ትንሽ
- ንግግሩ በምንድን ነበር የሚደረገው ?
- በማይክ ነበር በኋላ መብራት ጠፋ እስከ ምሽቱ ሦስት ሰዓት ተኩል ድረስ ተቆይቷል እስከዛ ሰዓት ድረስ ግን ባህሩ የሚባለው እንዳለ ነው
- አቶ ሰይድን በምንድን ነው የለዩዋቸው የት ሆነው ሲናገሩ ነው ያዩዋቸው ?
- ሰይድ እዛው አካባቢም ተከራይቶ ይኖራል የቄራ ምክትል ኢማም መሆኑንም አውቃለሁ እና በስእል ነበረ የማውቀው የዛን ቀን ግን በአካል ይሄ ነው ስላሉኝ አየሁት ያው እሱ መልክት አስተላልፎ ወጣ
- የት ሆነው ነበር የተናገሩት?
- እዛው መኪድ ውስጥ
- እርስዎ ውስጥ ነበሩ?
- አዎ መስኪድ ውስጥ ነበርኩ
- በአካል አይተዋቸዋል?
- በአካል አይቼዋለሁ
- ዋና ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ መስቀለኛ ጥያቄ ካለ
- ሰይድን በእለቱ አይቼዋለሁ ብለዋል
- ወደኋላ አይዙሩ እንደዚህ ቁጭ ብለው ለጆሯችሁ ብቻ ስሙ
- ሰይድ ምኑጋ ሆኖ ነበር የሚናገረው?
- ኢማው ማሰገጃ ቦታ ላይ
- ምን ቆሞ ነበር ወይስ ቁጭ ብለው ?
- ቆመው
- ምን አይነት ነበር የለበሰው?
- ነጭ ጀለቢያና ነጭ ጥምጣም
- በእስፒከር ነበር?
- በእስፒከር

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም አሻ በዩሪድ ይቃጠል መጅሊስ የሚለው መፈክር ያልመረጠን አይመራንም ማለት ነው ይመስለኛል ብለዋል ትርጉሙ ያልመረጥነው የሚሉት ማንን ነው ያልመረጡት?
- ማንን እንዳልመረጡ አላውቅም
- እርስዎ እንዴት ተረዱት?
- ያልመረጠን አያስተዳድርንም የሚለውን እንዴት ተረዱት መጅሊንስ ማለታቸው ነው?
- እንግዲህ መጅሊስን ይሁን መንግስትን ይሁን አላውቅም መጅሊስ እና መንግስትም ይሁን አላውቅም መጅሊስ እና መንግስት ሌባ ነው እየተባለ ስለነበረ ያልመረጥነው አይገዛንም ነው መፈክሩ ይላል እያሉ የነበረው
- ሁለቱም ተመሳሳይ ቃል ነው እንዴ የተናገሩት ባህሩ እና ሰይድ ተመሳሳይ ቃል?
- አዎ ተመሳሳይ ነው ሌላ ተጨማሪዎች ብዙ ሰወችም እዛው መካከል የሚያስተጋቡ ሰወች ስለነበሩ
- ቀድሞ የተናገረው ማን ነው?
- ሰይድ
- ቅድም ባህሩ የሚባለው ማን ነው ተናጋሪው ብዬ ስል ባህሩ ነው አሉኝ እንጂ ባህሩን አላየሁትም ብለዋል ትክክል ነው አደል?
- ትክክል ነው አላየሁትም ሳይሆን በደምብ ልለየው አልችልም ብዙ ሰው መካከል ስለነበረ
- እኮ እርስዎ አሁን ባህሩ ነው የተናገረው የሚሉት ሰወች ያሉትን ሰምተው ነው ተናጋሪው ባህሩ ነው ስላሉት ነው?
- ባህሩ ነው ብዬ የጠየቅኩት ማን ነው ብዬ የጠየቅኩት ሰው ብዛት ውስጥ ስለነበረ ማንነቱን መለየት ትንሽ እርቀትም ስለነበረው ማን ነው ብዬ ጠየቅኩ ባህሩ ነው አሉኝ ያ ከነሱ ታዳሚ ውስጥ ከነበረው ሰው ነው የጠየቅኩት
- እርስዎ ይሄን የጠየቁት መስኪድ ውስጥ ሆነው ነው ከመስኪድ ውጭ?
- መስኪድ ውስጥ
- ሰፈሩም ጀመርመን አደባባይ ጋር ነው አሉት?
- ወደዛ አካባቢ ነው ሰፈሩ ነው የተባልኩት ቦታውን በግልጽ ይሄ ቦታ ነው ተብሎ ተለይቶ የተነገረኝ ነገር ይሄ ቦታ ባይባልም ጀመርመን አደባባይ አካባቢ ወደ መካኒሳ ነው ቤቱ እዛ አካባቢ ነው
- እነዚህ ሰወች ለብቻቸው የሰገዱት የመጀመሪያ ከኢማሙ የሚሰግደው ሲሰግድ እነሱ የት ነበሩ?
- እዛው ተቀመጡ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዛው መስኪድ ውስጥ?
- አዎ
- ተቀምጠው ሲጨርስ እነሱ ተነስተው ሰገዱ?
- ለብቻቸው ሰገዱ
- በዚህ ምክንያት የተፈጠረ ነገር የለም?
- በዚህ ምክንያት የተፈጠረ ነገር የለም ለብቻ ለምን ሰገድክ የሚል ሰው የለም ማንም ሰው በፈለገው ሰዓት የሚፈልገውን ተከትሎ መስገድ ይቻላል በሰዓቱ አንሰግድም አሉ አንሰግድም ካሉ በግድ ስገዱ ስለማይባል ለብቻችን ነው የምንሰግደው እነዚህ ካፊሮች ናቸው እነዚህን አንከተልም ብለው ተቀመጡ ተሰባስበው
- ይሄንን ያደረጉትን ሰወች በቁጥር ይገምቷቸዋል?
- ማለት?
- ለብቻ የሰገደው ብዙ ነበረ አነስተኛ ነበረ ?
- ከአንድ ሺህ በላይ የሚገመት ሕዝብ ነው ያለው
- ከኢማሙጋር የሰገደውስ?
- የአካባቢው ነዋሪ ብቻ አደለም
- የቱ ይበልጥ ነበረ ከኢማሙጋ የሰገደው ነው ወይስ አልሰግድም ያለው ?
- እሱ እንግዲህ መገመት ይቸግራል ማን ይበልጣል የማወዳደር ስራ አልነበረም እንግዲህ የሰገደው ሰው እኔም እየሰገድኩ ስለነበረ ቆሜ ምን ያክል ሰጋጅ አለ ብዬ ለመገመት ጊዜው አላመቸኝም
- አህለል ኃይር ነው የተሰራው ብለዋል ማለት በዝርዝር ንገሩኝ ምንድን ነወ አህለልኃየር ማለት ግለሰብ ነው ወይስ ድርጅት ነው ይሄ የት ቦታ ያለ እሱን ንገሩን?
- አህለርሃይር ማለት በፍላጐቱ ይሄን አደርጋለሁ ብሎ ማንኛውንም የሚያደርግ ሰው አህለል ሃይር ነው
- እሺ ስሙን ያውቁታል እስቲ?
- ስሙን በውል ለይቼ አላውቅም አረብ ነው ከአረብ አገር ነው የመጣው
- የት አገር ከየት ?
- ሳውዲ አረቢያ መሰለኝ ባልሳሳት
- ሼህ እድሪስ ቅድም አሻብዮሪድ ብለው አረብኛ ቃል ከተናገሩ ወዲህ ርጉም ሰጥተው ነበር መንግስት እና መጅሊስ የሚል ነው ይውረድ የሚለው አሻብ ይውረድ የሚለው ቃል ?
- አሻብ ይውረዲስ ይቃጠል መጅሊስ ከመጀመሪያም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንደሱ ማለት መንግስት ይውረድ ማለት ነው ?
- መንግስት ይውረድ ብሏል ብዬ ለይሻላል አላልኩም የቆረጥነው አይገዛንም ብለዋል ትርጉሙ ምንድን ነው ብዬ ጠይቄያለሁ
- መቃወሚያ አለ ቆይ
- አሁን የተባለውን ትርጉም አላሉም ፍ/ቤቱ እየሰማቸው ስለመሰለን ነው መንግስት ይውረድ የሚል ትርጉም አደለም የሰጡት
- ስለዚህ አልተነሳም ነው ተቃውሞው
- እሺ ምን ማለት ነው ይሄ ትርጉሙ ምን ማለቱ ነው ለፍ/ቤቱ እስቲ ተርጉመው ያስረዱ
- ቆይ ተቃውሞ ተነስቶ እየተነጋገሩ ነው
- /የማይሰማ/ ለፍ/ቤቱ አስረዱ
- አሻም ይውረድ ምንድን ነው ብዬ ጠይቄያለሁ በእርግጥ እኔ ቋንቋውን ላልፈታ እችላለሁ በቂ እንትኑ ስለማይኖረኝ አረብኛ ትርጉም መፍታት ስለማልችል ሊሆን ይችላል ስጠይቅ አሻምይውረዲስይቃጠል መጅሊስ ማለት ያልመረጥናቸው አይገዛንም ብሎ ማለት ነው
- ቅድም እነሰይድ ሚዲያውን ተቆጣጥረናል ብለው ነበረ ምንድን ነው ሲባሉ ያው የመስኪዱ ነው ብለው ነበረ እና ሰይድ ወይም ባህሩ ሲነጥቁ እና ሲናገሩ አይተዋል እርስዎ?
- አዎ አይቻለሁ
- ነጥቀው ሲናገሩ?
- አዎ
- ምን ብለው ተናገሩ ?
- መድገም ካልሆነ
- ድገሙ ችግር የለውም
- እንድደግም ከሆነ የሚፈለገው መጀመሪያ አሻም ይውረዲስቃጠል መጅሊስ የሚል መፈክር ተስተጋባ ከዛ በኋላ ሰይድ ተቀበለ ማይኩን ነጠቀ ኢማሙ በዛው ወደዛ ሾለከ ከዛን በኋላ መስሊም ሞት አይፈራም ደማችን ይፈሳል እንጂ የመስኪዱ ካርታና ፕላን ቁልፍ በእጃችን ካልተሰጠ ማንም ሙስሊም እንዳይወጣ የእኛን መብት እኛ እንጂ የምናስከብረው መንግስት እና መጅሊስ አደለም መንግስት እና መጅሊስ ልጣ ነው
- በቃ
- እሺ ባህሩስ ምን አለ?
- በዚህ ይሄው ተመሳሳይ
- ምን አለ ይሄንኑ ነው ያለው እሱ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እ?
- ይሄንኑ ቃል በቃል ነው የደገመው?
- ይሄንኑ ተጨማሪ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ የማላስታውሳቸው ብዙ ነገሮች
- እሺ ባህሩ የአባቱን ስም ያውቁታል እንዴ?
- ባህሩ ኡመር ነው ያለኝ
- ዑመር ነው የተባሉት?
- አዎ
- ባህሩ ኡመር የሚል ሌላ ሰው የለም ይሄ መሆኑን በምን አወቁ እርስዎ?
- አላውቅም እንግዲህ የአካባቢ የነሱ ታዳሚ የነበረ ሰው ይሄን ከነገረኝ ከሌላው ሰው ማንን እንዲነግረኝ እጠብቃለሁ ታዲያ?
- እኮ እርስዎ በግል ያውቁት ነገር የለም ሰው ተነግሮት ነው እንጂ
- እኮ በሰዓቱ መልእክቱን ሲያስተላልፍ ስለነበረ እሱ ነው ብሎ የተነገረኝ ከዛው ከነሱ ታዳሚ ውስጥ ነው
- ጨርሳችኋል?
- አልጨረስንም የተከበረው ፍ/ቤት
- ቅድም ሲመሰክሩ አሁን ጠበቃው ሲጠይቆት ባህሩም ሲናገር ነበረ ቅድም ግን ውጪ ነበርኩኝ እኔ ባህሩ ሲናገር አልሰማሁም በስልክ ግን እሚጣራ ሰው ነበር ማን ነው ስል ባህሩ ኡመር አለኝ ነው ያሉት እና ለይተው ንገሩን ባህሩ ኡመር በስልክ የሚጣራ ሰው
- ቆይ ቆይ እንደዛ አደለም ያሉት በደምብ ይከታተሉ እራሱ አደለም የተናገረው ሌላ ሰው ጠይቀው ነው የነገራችሁ ባህሩ ኡመር አለኝ አላሉም እሳቸው
- አይ አላልኩም እንደዛ አላልኩም የተከበረው ፍ/ቤት
- ጥያቄውን ተረድቻለሁ እኔ ላብራራው ችግር የለውም እኔ ያልኩት እንደሱ አደለም
- እስቲ ጥያቄሽን ግልጽ አርጊና
- ጥያቄዬን ግልጽ ላርገው ቅድም ሲናገሩ እየተደወለ ሰው ይጠራ ነበር ማን ነው ይሄንን የሚያደርገው ስል ባህሩ ኡመር ነው ብሎ ነገረኝ የሆነ ሰው አሉ አሁን ደግሞ ባህሩ አሁን ጠበቃው ደግሞ ሲጠየቁ ባህሩ ሰይድም ባህሩ ኡመርም ሲናገሩ ነበር እያሉ ነው ሁለቱን እንዲለዩልኝ ነው የፈለግኩት ባህሩ በስልክ እየጠራ ነው ብለው ከሰው ነው የሰሙት ወይስ እርስዎ በአካል አይተውታል ነው?
- ባህሩ ሰው ጠራ ብዬ አደለም ያወራሁት አሁን እሱ ሌሎች ሰዎች የነሱ ታዳሚ የሆነ በስልክ ሰው ይጠሩ ነበር ሌሎቹ እዚህ ቦታ ተሳፍራችሁ እዚህ ቦታ ወርዳችሁ ከዚህ ቦታ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

እዚህ ቦታ ብላችሁ ኑ ቶሎ እዚህ መስኪድ እያሉ ይጠሩ ነበር እና እነዛን ሰወች አብሬ ተከትያቸው ሳናግራቸው መስኪዱ በርአፍ ላይ ሆነው የሚያወሩት ሳናግራቸው ባህሩ በዛ አጋጣሚ እሱ መልእክት ያስተላልፍ ነበር ይሄስ መልእክት የሚያስተላልፈው ማን ነው ባህሩ ኡመር ነው ከየት የየት አካባቢ ነዋሪ ነው እዚህ አካባቢ ነው እንዴ እዚህ አካባቢ አደለም ግን እዚህ አካባቢ አላውቀውም ከጀርመን አደባባይ አካባቢ ነው ቤቱ ወደዛ አካባቢ ነው ጀርመን አደባባይ ወደ መከኒሳ እዛ አካባቢ ሰፈር ነው ሰፈሩ ብሎ ነው የነገረኝ እንጂ ባህሩ በስልክ ሰወችን ይጠራ ነበር አደለም ያሉት

- እሺ እንደዚህ ከነገሮት እርስዎ አላዩትም ማለት ነው በአካል ባህሩን አላዩትም?
- በአካል አለየውም ብያለሁ እኮ መጀመሪያውኑ
- መቼ ነበር ጊዜውስ?
- 2004 ሰኔ 29 ጁምአ ቀን
- አቶ እንድሪስ እንደዚህ ቁልፉን ካርታውን ፕላኑን ካላስረከቡን አንወጣም ብለዋል ብለው ነበር ማን ነበር የያዘው ይሄንን?
- ካርታና ፕላሉን?
- እ?
- በሰዓቱ መጅሊስ ነበር መስኪዱን የሚያስተዳድረው ውክልና ማለት ተዋውሎ ያሰራውም መጅሊስ ነው ቁልፉና ካርታና ፕላኑ መጅሊስ እጅ ነበር
- እርስዎ ስለ መስኪዱ ታሪክ ያውቃሉ እንዴ የዛ ሰፈር ሰው ኖት?
- የዛ ሰፈር ሰው ነኝ
- ስለ መስኪዱ ታሪክ ያውቃሉ?
- ማለት
- መስኪዱ ቅድም አሰራ ከተባለው ጋር የገቡት ውል ስለመኖሩ ያውቃሉ?
- ውስጡን መርምሬ ላላውቅ እችላለሁ ግን በሰዓቱ ሲያስተዳድር የነበረው መጅሊስ እንደሆነና መጅሊስ እንደሆነና መጅሊስጋር ውለታ ፈጽሞ ሰውየው እንደሚሰራ አውቃለሁ
- ይሄ ጥያቄ ለምንድን ነው የተነሳው የአካባቢ ነዋሪ ስለሆኑ ይሄ ያስረክቡን የሚለው ጥያቄ ለምን ተነሳ?
- ለምን እንደፈለጉት አላውቅም
- አሁን ከአንድ ሺ ውስጥ የዛ የአካባቢ ነዋሪም አለ አደል?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሊኖር ይችላል እንግዲህ ሊኖርም ይችላል ላይኖርም ይችላል እሱን እንግዲህ ለይቶ ማወቅ እቸገራለሁ በሰዓቱ ፀጥታው መታወክ እንጂ እኔን ያሳሰበኝ የነበረው ሰወችን የመለየት ሥራ አልነበረም
- ቅድም ከኢማሙጋር አብሮ የሚሰግድ እና የማይሰግድ ብለው ለሁለት ከፍለው ነበር አሁን አንድ ሺ ሰው ካለ ሰው የጠየቀበትን ነገር መገመት አይችሉም ለምን እንደሆነ?
- ሰው ጠየቀ አደለም እሳቸው ያሉት እሱ ሲናገር እንዲህ ብሎ ሲናገር ሰምቻለሁ ነው ያሉት ስለዚህ አሁን ሰው ምን ያህል ቁጥር ነው ይሄን ያህል የተናገረው ምናምን ተብሎ በመስቀለኛ ጥያቄ ሊጠይቁ አይገባም አቶ ሰይድ ሲናገሩ ሰማሁ ብለው ነው የመሰከሩት ወደ አሁን እሳቸው እየጠየቁ ያሉት ወደ ሕዝቡ እዛ ያለው ሰጋጅ እንደጠየቀ አድርገው ነው እየጠየቁዋቸው ያሉት
- እስቲ ግልጽ ያርጉት እንደገና ጥያቄውን
- ጥያቄው ተመዝግቧል ግን አልተነሳም ነው ምንድን ነው እስቲ ግልጽ ?
- ምስክሩ ሲናሩ ማለት መቃወሚያችን ምንድን ነው አላሉም ነው ያላሉትን ነው እሳቸው ኮምፊርም እያስደረጓቸው ያሉት ምስክሩ የመሰከሩት አቶ ሰይድ ፕላን እና ካርታውን እስካላስረከብን ድረስ ብለው ነው የተናገሩት ወርድ ባይ ወርድ እንደዚህ የተናገሩት አሁን እሳቸው ጠበቃው እየጠየቁ ያሉት ደግሞ ምነ ያህል ሰው ነው እንዲህ ብሎ ሲጠይቅ የነበረው ብለው ነው እየጠየቁ ያሉት እኔ በገባኝ መጠን ማለት ነው ስለዚህ እንዲህ ተብሎ በዋና ጥያቄ አልተመሰከረም ነው ያለተመሰከረ ነገር ነው አሁን እንዲረጋገጥላቸው በመስቀለኛ ጥያቄ እየጠየቁ ያሉት
- እሺ ምላሽ
- አቶ ሰኢድ ሲናገሩ አንድ ሺ የሚሆን ሰው ከነሱጋር እንደነበረ አብሮ የዚሁ የነሰኢድ ደጋፊ ሆኖ እዛው እንደነበረ መልክት ያለው ነገር ተናግሯል ስለዚህ ጥያቄው እነአቶ ሰኢድን በመደገፍ እዛው ስለነበረ የአቶ ሰኢድ ጥያቄ ጥያቄ ነው ብለው እነሱን ደግፎ የተቀመጠ ሰው አለ ከሚል ታሳቢ በመነሳት ነው የጠየቅኩት እና ምናልባት በዛ መልክ ይስተካከልም ከተባለ ላስተካክለው እችላለሁ
- ብይን ተሰጥቷል የተነሳውን ጥያቄ በድጋሚ እዚህ ላይ መድገም አያስፈልግም ቅድም ምስክረ የመሰከሩት አንፈቅድም ብለው የተቀመጡ ሰወች ነበሩ ከኢማሙጋር ከመስኪዱ ኢማምጋር የሰገዱ ሰወች ነበሩ ብለው አቶ ሰኢድ የተናገሩት ነገርም አለ ካርታ እና ፕላን ካልተሰጠን ከዛ አንወጣም አንፈራም የሚል ነገር ተናግረዋል የሚል ነበር እና በጠበቃው በኩል አሁን የቀረበው አንድ ሺ ሰወች ያክል እሱን የደገፉ አንሰግድም ያሉ ነበረ ብሎ ከዛ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

መንደርደሪያ ነው የተነሳው እና ምስክሩ በግልጽ እነኚህ ሰወች እሱን ደግፈዋል የሚለውን ነገር ስላልተናገረ አንሰግድም ብለው ለብቻ የተቀመጡት ሰወች አሉ ከሰይድ ጋ የሰገዱት ማለት ነው ከመስኪዱ ኢማም ጋ የሰገዱት አሉ ስለዚህ ጥያቄውን መጨረሻ ላይ አስተካክላለሁ ባሉት መሰረት ስለ ድጋፍ መኖር አለመኖሩ ደምሮ ጥያቄውን አስተካክለው ይጠይቁ

- ምስክር እስከ ምሽቱ 3 ሰዓት ድረስ ቆዩ ያሉት እነ ባህሩ እና ሌሎች ሰወች ነበሩ አደል?
- አዎ
- እነዚህ ቀድም ያሏቸው ሰወች ናቸው ወይስ ሌሎች ናቸው?
- እነዛ
- ቅድም አንድ ሺ ያሏቸው?
- አዎ
- እነዚህ ሰወች ባህሩ እና ሰይድ ያነሱትን ጥያቄ የሚቃወሙ ነበር ወይስ የሚደግፉ ነበር?
- ሳይደግፉ እነሱጋ አብው እዛ አይቆዩም ድጋፋቸውን እያሳዩ ነው
- የሰሙት ወይም ያዩት ካለ ነው?
- በቃ እነሱ የዛኔ የዛ ደጋፊ ሆነው ነው እሱ የሚለውን ነገር እያስተጋቡ አብረው እያሉ
- እኮ ያስተጋባሉ ወይ ይደጋፋሉ ነው ምንድን ነው?
- እየደገፉ ማለት ነው
- እርስዎ አሁን የዛ ነዋሪ ስለሆኑ በተዘዋዋሪም የሚያውቁት ለምንድን ነው ይሄ ጥያቄ የተነሳው?
- እሱን አላውቅም
- እድሪስ ይሄ ፀብ የተነሳው አህለር ከይሩ መስኪዱን አስረክቦ ከሄደ በኋላ በአካባቢው መስኪድ ኮሚቴ እና በመጅሊስ መሃል አደል እንዴ ቁልፉ እኔጋ ይሁን እኔጋ ይሁን በሚል የተጣሉት?
- አቤት አቤት
- ይሄ ፀብ የተነሳው የመስኪዱ ኮሚቴ አለ አካባቢው የለም?
- የመስኪዱ ኮሚቴ አለ
- በመስኪዱ ኮሚቴ እና በመጅሊስ መካከል አደለ እንዴ ቁልፍ አላበረክብም የሚል ክርክር የነበረው አህለል ከይሩ ሰጥቶ ከሄደ በኋላ የዛ ሰፈር ሰው ነኝ ስላሉ ነው?
- አደለም ኮሚቴው እና መጅሊሱ አንድ ነው ዲፈረንስ የላቸውም እሱ ውስጥ ምንም አይነት ልዩነት አላየሁም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ልዩነት ያዩት እነሱጋ ነው?
- ልዩነት የነበረው ቁልፍ ይሰጠን ተብሎ በነ ባህሩ እና በነ ሰይድ የሚመራው ጋንታ ውስጥ ነው
- ቅድም ከኢማሙ ውጭ የሰገዱ ሰወች እንደነበሩ ተናግረዋል ሌሎቹን ሰወች ማን አሰገደ?
- ማን እንዳሰገደ አላውቅም ከነሱ ውስጥ ነው ያሰገደው ሌላው ሰጋጅ ሰግዶ ወጣ
- ማን እንዳሰገደ ግን አያውቁም?
- ማን እንዳሰገደ አላውቅም
- መጀመሪያ ከመስኪዱ ውጪ ነኝ ስላሉ አሁን ደግሞ ሰይድ ማይክራፎን ሲነጥቅ አይቶ አይቻለሁ አሉ ይታይ ነበር በአንድ ሺ ሰው መሃል ከውጭ ወደ ውስጥ ?
- ውጭ አደለም መስኪድ ውስጥ ነው ውጭ ነኝ ቢዬም አልሰጠሁም
- እሺ ውስጥ ካሉ ይታይ ነበር በትክክል ሰይድ ማይክራፎን ሲጠንጥቅ ?
- አዎ እዛው ፊት ለፊት ስለነበረ ይታያል
- ኢማሙ የወጡት ማይክራፎኑ ከተነጠቀ በኋላ ነው?
- አዎ
- ሰላት መቼ ነበረ የተሰገደው?
- ሰኔ 29 ቀን 2004
- አይ ሰዓቱን ነው የጠየቅኩት የምን ሰላት ማለት ነው ?
- የተሰገደበት ሰዓት በግምት ሰባት ሰዓት አካባቢ ላይ
- እርስዎ ከሰባት ሰዓት እስከ 3 ሰዓት እዛው ነበሩ እስከ ምሽቱ ሦስት ሰዓት?
- የስራ ቦታዬ እዛው አካባቢ ነው?
- አረ መስኪድ ውስጥ ነው የምሎት?
- ስራ ቦታዬ እዛው ነው ለሶላት ሰዓት እመጣለሁ እንጂ መስኪድ ውስጥ አልነበሩም ሙሉ በሙሉ?
- መስኪድ ውስጥማ እንዴት እውላለሁ ሰግጄ እወጣለሁ በስግደት ሰዓት እመጣለሁ እሚባለው ነገር ግን እዛው ፊት ለፊት ነኝ
- አሃ ገባ ወጣ እያሉ ማለት ነው ?
- አዎ
- እሺ ጨርሳችኋል
- ጨርሰናል
- እሺ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ አቃቤ ሕግ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቁልፉን እና ካርታውን በተመለከተ በኮማቴው እና በመጅሊሱ ነው ማለት የሰፈር ኮሚቴው እና በመጅሊሱ መሃከል አለመግባባት ስለነበረ አለም ወይ ተብለው ሲጠየቁ አደለም ብለዋል እነሰይድ ወይም እነ ባህሩ እዛ ኮሚቴ ውስጥ አሉ እዛ ሰፈር ውስጥ አሁን የሰፈር ኮሚቴ ውስጥ የተባለው ?
- የሉበትም
- ያውቋቸዋል የኮሚቴ አባሎቹን?
- አውቃቸዋለሁ
- ለምንድን ነው ይሄ መስኪድ የተፈለገው ለምንድን ነው የፈለጉት ማለት እንረከበው የሚሉት ለምንድን ነው?
- ለምን አላማ እንደሆነ አላውቅም ግን
- መቃወሚያ
- እኛ ይሄን በተመለከተ የጠየቅነው ነገር የለም መስኪዱ ለምን ተፈለገ የሚል ነገር አላነሳንም የተከበረው ፍ/ቤት በዋና ጥያቄም አልተነሳም በተመሰረቱ በመስቀለኛም አላነሳንም እና በድጋሚ ሊጠይቁ አይገባም ነው
- መስኪዱ ለምን ተፈለገ
- የሚል ነገር አልተነሳም
- እሺ ምላሽ
- ይሄንን ጥያቄ ሕዝቡ አልደገፈውም ወይ አልጠየቀም ወይ እያሉ ነበር ማለት በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠይቋቸው የነበረው ስለዚህ ይሄ መስኪድ በአሁን በቁጥርም እሳቸውም ምስክሩም በገመቱት ቁጥር የነሱስ ጥያቄ አልነበረም ወይ አልደገፉም ወይ እየተባለ በተደጋጋሚ ጊዜ ጠይቀዋል ስለዚህ ይሄ መስኪድእነሱ እየጠየቁ ያሉት ለምን ጉዳይ ነው ተብሎ የተጠየቀው ጥያቄ ተያያዥነት ያለው ነው በዚህ ደረጃም ለማብራራትም የተጠየቀ ጥያቄ ነው
- ብይን ተሰጥቷል አሁን የቀረበው ጥያቄ መስኪዱ ለምን ተፈለገ የሚል ጥያቄ ተነስቷል በመቃወሚያ የተነሳው መስኪዱ ለምን ተፈለገ የሚለው በዋና ጥያቄም በመስቀለኛም ስላልተነሳ በድጋሚ መነሳት የለበትም የሚል ተቃውሞ ቀርቧል ጥያቄው ተነስቷል ወይ አልተነሳም የሚለውን ፍ/ቤቱ መርምሯል ምስክሩ ከዚህ በፊት የመሰከሩት ጥያቄው የመስኪዱ ካርታ እና ፕላን ካልተሰጠን ከዚህ አንወጣም አንፈራም ሌሎችም ሌሎችም ሲናገሩ ነበረ እነሰይድ ብሎ የሚደግፉ ሰወችም ነበሩ ብሏል ቁልፍ እና ካርታ እና ፕላን ቁልፍ ተፈለገ ማለት መስኪዱ ተፈለገ ማለት ነው ስለዚህ ጥያቄው አልተነሳም የሚያስብል

http://ethcriminalawnetwork.com/

ነገር የለም ጥያቄው ተነስቷል አሁን የነኳው ለምን ተፈለገ የሚለው ተገቢ ጥያቄ ነው ይቀጥሉ ብለን ብይን ሰጥተናል

- አቶ እንድሪስ ያውቁታል አሁን ማለት እዛው የሰሙት ወይም የተረዱት ነገር አለ ለምንድን ነው እነዚህ ሰወች ይሄንን መስኪድ ካርታ እና ፕላን ያስረክበን ይሰጠን እያሉ ያሉት ለምንድን ነው ያው አማኙ እየተገለገለበት ነው?
- አይተገለገለበት ነው
- ስለዚህ እነሱ አሁን እንደ አዲስ መጥተው ለብቻቸው የሚሰግዱ ሰወች እርስዎ በገለፁት መልኩ ማለት ነው ለምንድን ነው ካርታ እና ፕላኑ ቁልፍ ይሰጠን እየተባለ ያለው ለምንድን ነው የተፈለገው ?
- እኔ እንደሚመስለኝ ለግላቸው ለማድረግ ይመስለኛል እንደ ግል መስኪዱ ለምሳሌ ቁራ መስኪዱ በመጅደሊስ ስር የሚተዳደር አደለም እንደዚህ አይነት ነገር ሌሎች ሌሎችም
- ምን መስኪድ?
- ቆራ መስኪማ
- በማን ነው የሚተዳደረው?
- በመጅሊስ ስር አይተዳደርም አሁን እነሱ ያው በራሳቸው የሚተዳደሩ ናቸው እና አሁንም እንደዛ አይነት ሌሎችም መስኪዶች አሉ በስም ልጠራቸው የማልችላቸው እንደዛ እንደዛ አይነት መስኪዶችን ወደ ግላቸው አድርገው የኪራይ ሰብሳቢነትን ለማስፋት ካልሆነ በስተቀር ለሌላ አማኙ አየተገለገለበት ለመዉጣት ከሆነ ምንም የሚያጋጭ ነገር አይመስለኝም የራሴን ግምት ነው
- ያንን ነው የተረዱት?
- ስለዚህ ይሄንን ነው የተረዳሁት እኔ በሰዓቱ
- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ
- አሁን መጨረሻ ላይ የተናገሩት እነ ቁራ መስኪዶች መጅሊስ የሚተዳደሩ አሉ አሁን ክርክር ካርታ ቁልፍ እና ፕላን እንፈልጋለን ያሉትን መስኪድ ለራሳቸው የፈለጉት ለኪራይ ሰብሳቢነት ብለው የተናገሩት ካልፈለጉ በስተቀር ብለው ተናግረዋል እና ይሄ ነገር ከሌላ የተረዱትነገር አለ ወይስ የእርስዎ ግምት ነው?
- በእኔ ግምት እኔ ስገምት እንደዛ ነው
- በእርስዎ ግምት ነው ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በራሴ ግምት ነው ምክንያቱም መስኪዱ ማንኛውም ሰው መጥቶ ይሰግድበታል አማኝ የሆነ ሰው የተከለከለ ሰው የለም የመስኪዱን ካርታ እና ርላን እንደ ግለሰብ ለኔ ይሁን ማለት እንደኔ ስገምት ለግሌ ማረግ ማለት ነው ስፈልግ የማስገባበት ስፈልግ የምከለክልበት ላደርግው ማለት ነው እንደኔ ስገምተው እንደራሴ እንጂ አማኝ የተከለከለ ሰው እስከሌለ ድረስ ካርታ እና ፕላን ቁልፍ ለኔ ይሰጠኝ የሚያሰኝ ምንም አይነት ነገር አላየሁም
- እሺ ይሄንን ነው የፈለግነው ጨርሰዋል እናመሰግናለን
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም
- ምያለሁ
- ለምስክርነት ነው የመጡት
- አዎ
- ያው ለምስክር ደህንነት ተብሎ ምስክሩ የራሳቸውን ስም ብቻ የአባታቸውን ስም ሳይጨምሩ ይግለፁ ተብሏል እና የራሶን ስም እስቲ
- ኑርሁሴን
- እሺ ተራ ቁጥር ስንት ላይ ናቸው አቃቤ ሕግ?
- ተራ ቁጥር 121
- እሺ ምስክሩ ያው በመሰከሩት ዝርዝር 26ኛ ላይ ደርሰናል በምስክሩ ማስረጃ ዝርዝር ላይ 121 ላይ በተጠቀሱት
- እሺ እነማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?
- በነ ዶ/ር ከማል እና በሼህ አብርሃም አሊ ኡስማን
- ሁለት ሰው ላይ?
- አዎ
- እሺ ለይተው ያውቃቸዋል እነኚህን ዶ/ር ከማል እና ሼህ አብዱራህማንን በአካል?
- አዎ አውቃቸዋለሁ
- ማሳየት ይችላሉ አሁን?
- አዎ
- እሺ ከቻሉ ተነስተው ማሳየት ይችላሉ እዛም ቆመው
- እሺ የትኛው ናቸው ዶክተሩ ኮፍያ ያረጉት ኮፍያ ያረጉት ማለት መነጽር ያላደረጉት?
- መነጽር ያላደረጉት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እርስዎ ኖት ዶ/ር ከማል ? እሺ ምስክሩ 27ኛ እና 29ኛ ተከሳሾችን ለይቶ አሳይቷል አሁን ካሳዩን ሰወች ጋር ዝምና ጥላቻ አሎት?
- ምንም የለኝም
- እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- ሼህ ኑር አሁን በችሎት የለዩዋቸውን የት ነው የሚያውቋቸው?
- እኔ በምሰራበት የነበረ ድርጅት
- የት ነው ድርጅቱ ?
- የሳውዲ አረቢያ ኤምባሲ ስር ሆኖ ኃይማኖታዊ አታች ሙልሃቀዲን የሚባል ኃይማኖታዊ ተቋም
- እዛ ነው የሚያውቋቸው?
- አዎ
- በምንድን ነው ትውውቃችሁ?
- ትውውቃችን በቃ የወር ደሞዝ ስንወስድ አብረን በፔሮል እነሱ እዛ ነበሩ እኔ ቅጥረኛ ነበርኩኝ እንደ ጥበቃ ሰራተኛነት ነበርኩኝ እና እዛ ሲወስዱ በየወሩ በፔሮል ዝርዝራቸውም አለ በአካልም እዛ እንተዋወቃለን
- አሁን እስቲ እንትኋን ይንገሩን ደግመው ይንገሩን ምንድን ነው ክፍሏን ይንገሩን
- ሙልሃቀዲ ማለት ኃይማኖታዊ ተቋም ነው በሰዓቱ
- ምን?
- የሳውዲ አረቢያ ኤምባሲ ስር ሆኖ ኃይማኖታዊ ተቋም ሙልሃ ቀዲን ይባላል ስሙ
- የት ነው ቢሮው?
- እዚህ 22 አካባቢ ወርቁ ሕንፃ የሚገኝ
- እኮ ማለት ከኤምባሲውጋር ያለው ምንድን ነው ግንኙነቱ?
- ከኤምባሲ ስር ነው የሚባለው ግን እራሱን የቻለ ቢሮ መሆኑን ነው የማውቀው እኔ ግን ኤምባሲ
- ይሄ የኃይማኖት ትምህርት ያሉት?
- እራሱን የቻለ ቢሮ ነው አዎ
- ምንድን ነው ሥራው?
- ኃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች
- የት ነው የሚንቀሳቀሰው?
- እኮ በአገር ውስጥ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ ይንገሩን ምንምንድን ነው እሚያውቁት ነገር አለ ምን ምን እንደሚሰራ አገር ውስጥ ?
- ማለት መስኪዶች መስራት ትምህርት ቤቶች
- የሚያውቁት አለ የተሰራ መስኪድ ወይም ት/ቤት?
- በቃ ይሄንን ፕሮጀክት እንደሚያካሂዱ ነው የማውቀው
- አሁን የጠቀሷቸውን ሰወች የት ነው የሚያውቋቸው ታዲያ?
- በየወሩ እየመጡ ደሞዝ ይወስዳሉ እዛ ድርጅት ውስጥ
- ኤምባሲ ውስጥ ነው የሚሰሩት የት ውስጥ ነው የሚሰሩት?
- እዛው ኃይማኖታዊ ተቋም መሃል የሚባል በሳውዲ አረቢያ ስም
- ምን ይባላል ነው ያሉት ስሙን?
- ሙልሃቀዲን ይባላል ስሙ እዛ ፔሮላችን አንድ ነው እየመጡ ይወስዳሉ አይቻቸዋለሁ
- ቢሮ አላቸው እዛ ሳምንቱን ሙሉ ወይ በወር ወሩን ሙሉ እዛ ነው የሚሰሩት ?
- አይሰሩም በቃ ከውጭ መጥተው ደሞዝ የሚወስዱበት ቢሮ ነው ነው
- ደሞዝ ለመውሰድ ብቻ ነው የሚመጡት እዛ ቢሮ?
- አዎ
- አሁን የጠቀሱት የኃይማኖት ክፍል ውስጥ አደለም የሚሰሩት?
- በቃ ለደሞዝ ብቻ እዛች በየወሩ ይመጣሉ
- በምን ስራ ነው ደሞዝ የሚከፈላቸው የሚያውቁት ነገር አለ ጠይቀው ወይም የሰሙት ነገር ካለ ምንድን ናቸው ይባላሉ ዝም ብለው ደሞዝ መጥተው ሲወስዱ እናንተ ምንድን ናቸው ብላችሁ ጠይቃችሁ አታውቁም?
- እኛ በቃ የዚሁ ድርጅት ተቀጣሪዎች ናቸው ሲመጡ እንዳትፈትሿቸው የሚል መመሪያ ስለተሰጠን መጥተው ይወስዳሉ ማለት ነው በየወሩ
- ኤምባሲ ውስጥ?
- እዛ ሙልሃቀዲን ኤምባሲ እና ያኛው ይለያያል
- እስቲ አቀማመጡን ቦታው እርቀት ካለው ይንገሩን?
- እኮ ያው ዋናው ኤምባሲ ወሎ ሰፈር አካባቢ የሚገኝ ነው ከኤምፔሪያል ሆቴል ፊት ለፊት ይሄ ደግሞ 22 ወርቁ ሕንፃ አካባቢ ቦሌ ክ/ከተማ ማለት ነው
- አሁን የት/ቤቱ ማለት ነው?
- አዎ የድርጅቱ
- እርስዎ እዛ ዘበኛ ኖት?
- አዎ ለ4 ዓመታት ያህል ሰርቻለሁ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- 4 ዓመት ሙሉ ሲሰሩ እነዚህ ሰወች ቢሮ ይዘው የሚሰሩት ስራ አለ ወይ?
- ኖ ቢሮ አልያዙም እዛ መጥተው ግን ደሞዛቸውን በየወሩ ስም ዝርዝር አለ ፔሮል ሲወስዱ ነው ያየሁት
- ለምን ስራ ደሞዝ እንደሚከፈላቸው አያውቁም?
- እኔ አላውቅም
- ዋና ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ መስቀለኛ ጥያቄ ካለ
- ጠበቃ መሃመድ አብደላ ከ28ኛ ተከሳሽ ውጪ ላሉት ተከሳሾች አቶ ኑርሁሴን ዶ/ር ከማል እና ሼህ አብዱራህማን ሁሴን ላይ ልመሰክር ነው የመጣሁት ለ4 ዓመት አውቃቸዋለሁ ብለዋል እስቲ በምን ጉዳይ እንደሚያውቋቸው ለምሳሌ የኃይማኖት አስተማሪ መሆናቸውን ያውቃሉ?
- የኃይማኖት አስተማሪ መሆናቸውን ያው ዱአት ተብለው ይጠራሉ እኛም ተነግሮናል
- ዱአት ማለት?
- ዱአት ማለት ትምህርት የሚያስተምሩ የሚል ተነግሮናል ስለዚህ ያው የሚያስተምሩበት ቦታ የት መሆኑን አናውቅም ግን ዱአት የሚል ስም መጠሪያ ተሰጥቷቸዋል
- ስለዚህ የኃይማኖት አስተማሪ ናቸው ማለት ነው?
- አስተማሪዎች መሆናቸውን ነው
- ያላቸውን የትምህርት ደረጃ ታውቃለህ?
- ዶ/ር ተብለው ነው የሚጠሩት ያኛው ደግሞ ሼህ ሌላ ጠለቅ ብዬ የማውቀው ነገር የለም
- ዶክተርነታቸው በኃይማኖት ነው?
- ይሆናል መዲና ምናምን ተመርቀዋል ነው የሚባለው
- በዋና ጥያቄ አሁን ስለተከሳሾች የኃይማኖታዊም ሆነ የአለማዊ ትምህርት ኳሊፊኬሽን አልጠየቅኩም ስለዚህ እሳቸው እንዲህ ናቸው ተብሎ ተነግሮናል ከዛ ውጪ የምናውቀው ነግር የለም ብለዋል ከዚህ ውጪ ዶ/ር መሆናቸውን በኃይማኖት ነው ምናምን የሚባለው በዋና ጥያቄ አልተነሳም
- የተከበረው ፍ/ቤት ደምበኞቻችን በተለይ እሳቸው ምስክር የሚመሰክሩባቸው ሁለት ተከሳሾች ያለ ስራ እንደሚወስዱ ተደርጐ ነው በአቃቤ ሕግ ጥያቄ ሲጠየቅ የነበረው እና እኛ ደግሞ የትምህር ደረጃቸውን ያላቸውን እውቀት አስመስክረን ወደ ስራቸው ልንሄድ ነው እና ይሄንን ነው እየጠየቅን ያለነው ሌላ ነገር አደለም ከዚህ ቀደምም ባደረግነው

261

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ክርክር ምስክሩ የሚያውቀውን ከጉዳዩጋር ተያያዥነት ያለውን ነገር ቢጠየቅ ክፋት የለውም ተብሎ ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቶበታል

- መልሰዋል ምስክሩ የሚያውቁትን ከዛ ያለፈ ግን በዋና ጥያቄ ያልተነሳውን ጥያቄ አታንሱ ሌላ በዋና ጥያቄ የተነሳውን የምትጠይቁት ካለ
- አቶ ኑርሁሴን በየወሩ እየመጡ ደሞዝ ሲወስዱ እንጂ ሌላ ስራ እንዳላቸው አላውቅም ብለዋል አደለም
- አዎ ብለዋል ጥያቄውን ጠይቁ
- እሺ በሌላ ቦታ ድርጅቱ ያሰራቸው አያሰራቸው የሚያውቁት ነገር አለ ?
- ማለት ሼህ አብዱራህማን መስኪድ እና መድረሳ ማስፋፊያ ፕሮጀክቶች እንደሚያስፋፉ ነው አገሩም ወደ ደቡብ ነው አብዛኛው ወደ ኦሮሚያ ክልል ምናምን ስለዚህ ፕሮጀክቱ እንዳላቸው እኔ ግንዛቤ አለኝ እዛ ባሉ ሰወች ፕሮጀክት እንደሚነድፉ እና የተለያዩ እንትኖች እንደሚያሰሩ እኛ ግን ያለ ስራ ነው ደሞዝ የሚመስዱ የሚለው
- እሺ ይበቃል
- ቅድም የሙልሃቀዲን ያሉት ድርጅት ስራው መስኪድ እና ት/ቤት መገንባት ነው ብለዋል ይሄን በምን አወቁ?
- እኔ እራሴ እዛ ቁጭ ብዬ የተለያዩ ሰወች መጥተው ብር ሲወስዱ አይቻለሁ ከአፋር ክልል በየክልሉ እየመጡ እንደሚወስዱ እኔ አውቀዋለሁ አረብኛም ስለማውቅ እምሰራበት የነበረው ሰውየም ጠንቅቄ የማውቅ ነው ስለዚህ እዛ ስሰራ ስለነበር እኔ አውቃለሁ እንደውም አንድ ጊዜ ለአንድ ሰውዬ ብር ሲሰጥ ምስክር ሆኜ ፈርሜያለሁ ወደ ትግራይ አካባቢ ትግራይም ስለሆንኩ እኔ ስለዚህ ይሄንን ሙልሃ ቀዲን የተባለ ስሙም የዲን ኃይማኖታዊ ማስፋፊያ ማለት ነው እዛ ነው ተቋሙ በኤምባሲ ስር ሆኖ የሚሰራው ማለት ነው ስለዚህ እኔ ጭብጡ አለኝ 4 ዓመት ከ8 ወር ሰምርቻለሁ በ2004 ነው የወጣሁት እዛ
- የሰራው ት/ቤትስ የት እንደሆነ ያውቃሉ?
- ት/ቤቱን አላውቀውም
- ትምህርት ቤት መስራቱን በግምት ነው?
- ት/ቤቶች ይሰራሉ መስኪዶች ይሰራሉ ይሄ ግን በየክልሉ ነው ይሄንን ብዬ ሄጀ አላየሁም ግን እይወሰዱ ነው ሰወች በጀት እዛ መስሪያ የሚሆን ስለዚህ የኃይማኖታዊ ተቋም ቴምር በተለያዩ ሆኔታዎች ይታደላል ያየሁት ነገረ ነው
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ አቃቤ ሕግ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የለንም የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የለም ምስክሩ ጨርሷል እናመሰግናልን
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም
- እምላለሁ
- ለምስክርነት ነው የመጡት
- አዎ
- ለምስክር ደህንነት ተብሎ ምስክሩ የራሳቸውን ስም ብቻ የአባታቸውን ስም ሳይጨምሩ እንዲናገሩ ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል በዛ መሰረት የራሶን ስም ብቻ ይነግሩናል?
- እድሪስ እባላለሁ
- ስንተኛ ላይ ናቸው አቃቤ ሕግ
- በተመሳሳይ በእኛ ቀርበው በመሰክሩት በተመዘገቡት 27ኛ ላይ ያሉት በአቃቤ ሕግ በክስ ቻርጁ በቀረበው ስር ግን 71ኛ ላይ የተጠቀሱት ምስክር ቀርበዋል
- እነማን ላይ ለመመስከር ነው የመጡት አቶ እድሪስ?
- ከአሁን በፊት በፖሊስ በመርማሪም በአቃቤ ሕግም ተጠይቄ እንትን ያልኩት አለ
- በማን ላይ ሊመሰክሩ ነው የመጡት?
- ዝርዝሩን በኋላ ይቀርባል ግን በነማን ላይ አሁን ወደ 30 የሚሆኑ ሰወች አሉ እና ከነዚህ ውስጥ እነማን ላይ ነው ወይስ ሁላቸውም ላይ እሱን ለማወቅ ነው?
- እኔ እዚጋ በግል የምመሰክርበት ማንም ሰው የለም እዚጋ ምናልባት ክቡር ፍ/ቤት ከፈቀዱልኝ
- ምን ሊያስረዱ ነው የመጡት?
- የተጠየቅኩት ጥያቄ አለ እለቱን በትክክል ባላስታውሰውም አዛል የሚባለው እናንተ መስኪድ በሚል ነው የመጀመሪያ ጥያቄ 2ኛ ሰደቃ የሚለው በሰፊው የተጠየቅኩት
- እሺ አቃቤ ሕግ ጥያቄ ይቀጥሉ
- እሺ አቶ እንድሪስ አሁን ያሉትን ሰደቃ እና አዛን በተመለከተ ምንድን ነው የሚያውቁት እስቲ ይንገሩን ከዛ ጀምረው ?
- በመሰረቱ ከለሊቱ 6 ሰዓት ኦር ከአራት ሰዓት በኋላ ከአምስት ሰዓት አካባቢ ላይ አዛን ሰምቻለሁ እቤቴ ሆኜ አዛን ሰምቼ ወደ መስኪድ መጥቻለሁኝ
- የት ነው መቼ ነው እስቲ ጊዜውን እና እረጋ ብለው ?
- ቀኑን በትክክል አላስታውሰውም

269

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወሩስ?
- ሜይ ቢ ግምቦት አካባቢ ሊሆን ይችላል
- ሰዓቷን ስንት አሉ ?
- ከአምስት ሰዓት በኋላ
- ቀን ነው ማታ?
- ለሊት
- ወሩን ምን ላይ አሉን የሚያስታውሱት ከሆነ?
- ግምቦት አካባቢ ሊሆን ይችላል
- አመተምረቱስ?
- 2004
- የት መስኪድ ነው እርስዎ የት አካባቢ ነው የሰሙት አሁን?
- እኔ አጋጣሚ ወደ ሼህ ወጀሌ አካባቢ ነው የሰማሁት ሼህ ሆጀሌ ብቻ ላይሆን አዛን የሰማሁት በርካታ መስኪዶች ላይ ነው አንድ መስኪድ ላይ ብቻ አደለም አዛን የሰማሁት እና ወደሚቀርበኝ መስኪድ ነው እኔ የሄድኩት በዛ ሰዓት
- ለምን ሄዱ ወደዛ?
- አዛኑን ስለሰማሁኝ ሄጃለሁ
- እሚቀርቦት መስኪድ ማን ነው ያሉት?
- ሼህ አጀሌ ሰፈር መስኪድ
- እሺ ወደዚህ መስኪድ ለምንድን ነው የሄዱት?
- ስለሚቀርበኝ
- ማለት ይሄኛው በኃይማኖት የሚደረግ አዛን ነው በዛ ምክንያት ነው የሄዱት?
- በመሰረቱ 5 የአዛን ወቅቶች አሉ ከአምስቱ ይሄ ለየት ያለ ስለሆነብኝ በዛን ሰዓት ምን ተከሰተ በሚል ሄጃለሁኝ
- ምን ተከሰተ ማለት ምን ማለት ነው ?
- በዛን ሰዓት ጥሪውን ስሰማ ለኔ አዲሴ ስለሆነብኝ ሄጃለሁኝ
- 5 የሃአዛን ጥሪ አለ ብለውናል?
- እሱ መደበኛ ናቸው
- እነማን ናቸው እስቲ ይንገሩን እስቲ?
- ሱቢህ፣ ስሁር ስሁር ማለት ሊነጋጋ አካባቢ ላይ ዙር ስድስት ተኩል ላይ አስር ሰዓት ላይ አስራሁለት ሰዓት ተኩል እና ወደ ሁለት ሰዓት አካባቢ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን የተደረገው አዛን ስንት ሰዓት ላይነው?
- ከአምስት ሰዓት በኋላ ሰምቼዋለሁ
- አሺ ምን ተከሰተ ብዬ ሄድኩኝ አሉ ?
- አዎ
- ምን ተከሰተ ማለት ምን ማለት ነው መስኪድ አዛን ሲባል ምን ተከሰተ ብለው ሄደው ያውቃሉ?
- አዲስ ነገር ስሰማ እሄዳለሁኝ አዎ
- እሺ ምን አዩ ወደቀረቡት ሄደው?
- መስኪድ በምሄድበት ሰዓት በርካታ ሕዝብ ነው ያገኘሁት እዛጋ
- ምን የሚያረግ?
- ግቢ ውስጥ በርካታ ሕዝብ ነው ያየሁት በጣም በርካታ ሕዝብ
- እሱ ምን ተከሰተ ብዬ ሄድኩኝ ብለዋል?
- አዎ
- ምን ተከስቶ ነው ያ ሁላ ሕዝብ የተገኘው ?
- እዛጋ ያገኘሁት ሰው በዛ ሰዓት አወልያ ላይ ችግር አለ እዛ ያሉ ሽንኩርት ሊከትፉ እና ስጋ ሊቆርጡ የሄዱ ሴቶች ስለተደበደቡብን ወደዛ መሄድ አለብን የሚለውን የሕዝብን ድምጽ ሰምቻለሁ
- ማን ነው ይሄን ያለው?
- አጠቃላይ ሕብረተሱ ነው እዛጋ የወጣው
- ምን ያህል ሰው ይሆናል ?
- በጣም በርካታ ሕዝብ ነው ግቢው ሙሉነው ምናልባት ግቢውን ታውቁት እንደሆነ በጣም ትልቅ ግቢ ነው ያ ሙሉ ሕዝብ ነው ያለው
- ሙሉ ሕዝብ አንድላይ አይናገርም ከሰወች ከግለሰቦች ጥሪ በማይክ የተደረገ ንግግር ነው የሰሙት?
- ኖ ማይክ የሚባል ነገር ከአዛን ውጪ ማይክ አልሰማሁኝም የሰው ድምጽ እራሱ የተንጫጫ ሕዝብ ነው ያለው የበርካታ ሕዝብ ድምጽ ነው ያለው ያንድ ሰው ድምጽ የለም
- ምን ተብለው ነው የመጡት ?
- ማ እኔ
- አዎ አሁን እርስዎን ጨምሮ ሌሎቹ በአዛን ጥሪ ተሰብስበዋል አሉ ?
- አዎ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሳ ሲደርሱ አሁን ምንድን ነው ያሉት?
- አወልያ ላይ የነበረ ሽንኩርት ሊከትፉ የሄዱ ሴቶች አሉ ስጋ ሊቆርጡ ለሰደቃ የሄዱ ሰወች አሉ እነሳ በመደብደባቸው ምክንያት ነው የሚል የሰማሁት
- ሄዱ ወደ አወልያ እርስዎ?
- እኔ ትንሽ ህመምተኛ ስለሆንኩ ወደቤቴ ነው የተመለስኩኝ
- ሌላው ሕዝብ ሄደ?
- በርካታ ሕዝቡ እንዳለ ወደሳ ነው ፊቱን ያዞረው እና ያው ከመንግስት ከንገድ ላይ እንደተመለሰ ነው ሕብረተሰቡ የነገረኝ
- እ?
- የሄዱ ሰወች ከመንገድ ላይ ፖሊስ እንደመለሳቸው ነው የነገሩኝ
- ለምንድን ነው የመለሳቸው?
- ፖሊስ ተመለሱ ብሎ መልሶናል
- እኮ በሚቀጥለው ቀን እርስዎ ሕመምተኛ ስለሆንኩ መሄድ አልቻልኩም ብለዋል በሚቀጥለው ቀን አላጣሩም አወልያ ምን ተፈጥሮ ነው ?
- ነገርኩህ እኮ የኔ ወንድም እሳ ያለው ሽንኩርት ሊከትፉ እና ስጋ ሊቆርጡ የሄዱ ሴቶች የሆኑ ወጣቶች ተደብድበውብናል በሚል ነው
- እኮ አይ እሱንማ ሰማን እኮ አሁን የምሎት ምንድን ነው በሚቀጥለው ቀን ይሄንን ነገር አጣሩ ወይ አወልያ የተከሰተውን ነገር እርስዎ አማኝ ኖት አደለ?
- በትክክል
- ስለዚህ አወልያ ያለው ጉዳይ ይመለከቶታል ?
- አዎ
- ስለዚህ ምን ተከሰተ የአሳን ጥሪም ተደርጓል ?
- አዎ
- የማይሆን ነገር ያልተለመደ ነገር ስለሆነና ምን ተከሰተ ብዬ ሄድኩኝ ብለዋል ?
- አዎ
- ስለዚህ በሚቀጥለው ቀን አወልያ ምን ተፈጠረ ብለው አላጣሩም ወይ?
- አጣርቻለሁኝ ሰምቻለሁ ልጆች ብዙ ልጆች ታስረውብናል እንደውም የቆሰሉ ልጆች ሁሉ እንዳሉ አይቻለሁኝ
- በምን ምክንያት ነው ይሄ ሁላ የሆነው ነው?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እላ እንግዲህ ከነበረው ከፖሊስ ኃይል ጋር በተነሳው ግጭት ነው አትግባ ግባ አትግባ በሚል ነው
- ምን ተዘጋጅቶ ነው እላ?
- እላ የነበረው በማግስቱ የሰደቃ ፕሮግራም ነበረ ይምስለኛል እሁድ
- ሰደቃ ማን ነው ያዘጋጀው?
- ሕብረተሰቡ ያዘጋጀው ነው ሕብረተሰቡ
- ሕብረተሱ ማለት እሚያውቁት አለ?
- እዚጋ አጠቃላይ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ ያዘጋጀው ነው አንድ ግለሰብ ያዘጋጀው ማንም የለም
- ሰደቃ በሕብረተሰብ ይዘጋጃል እንዴት ነው የሚዘጋጀው ይንገሩን?
- ሰደቃ ምን ጊዜም የሚዘጋጀው አብዛኛው በሕብረተሰብ ነው
- በሕበረተሰብ ማለት?
- በግልም ይዘጋጃል በሕብረተሰብም ይዘጋጃል
- ስለዚህ ያ ሰደቃ ለምን እንደተዘጋጀ የሚያውቁት ነገር አለ እንዴ?
- እንግዲህ አወልያ የራሱ የሆነ መስኪድ አለው መስኪዱ ኮሚቴ አለው ኮሚቴው ባስተባበረ ቁጥር ሕብረተሰቡ ለዛ ድጋፍ ይወጣል የሚሰራውን ሥራ ይሰራል
- አወልያ ለምን አሁን ሰደቃ በሕብረተሰቡ ያሉትን ሰደቃ ለምን እንደተዘጋጀ ሰምተዋል ወይ አጣርተዋል ወይ አልሄድኩም ብለለዋል ?
- አልሄድኩኝም አዎ
- አጣርተዋል ወይ ለምን እንደተዘጋጀ ሰደቃው?
- ሕብረተሰቡ እንግዲህ በመስኪዱ አስተዳደር በሕዝቡ ጥያቄ ይሄን የመስኪዱ አስተዳደር ነው ያንን ሰደቃ ሊያወጣ የቻለው
- መስኪዱ ነው ያዘጋጀው እርግጠኛ ኖት?
- በትክክል
- ይሄን ሰምተዋል?
- አዎ
- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ መስቀለኛ ጥያቄ ካለ
- እድሪስ
- አቤት

273

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ስለ አዛን በቀን 5 ጊዜ ነው ብለው ወቅቱን ገልፀዋል ?
- አዎ
- ይሄ ብቻ ነው እንዴ አዛን የሚደረገው?
- በመሰረቱ አምስቱ ሕጋዊ መደበኛ አዛኖች 5 የሰላት ወቅቶች በአምስቱ ሰዓታት ላይ አዛን ይባላላ አስቸኳይ ሁኔታ ለምሳሌ እንደ አስቸኳይ ጥሪ ዱአ ለማድረግ ለምሳሌ ለሊት ለመስገድ ከተፈለገ አስቸኳይ የአዛን ጥሪዎች አሉ ዱአ ለማድረግ ከተፈለገ ለምሳሌ እስቲስታ ሌላም ሌላም ለሊት ላይ ተሰግዶ ዱአ ለማድረግ ከተፈለገ አዛን ይደረጋል
- ጥሩ ሕፃን ልጅ ሲወለድም አዛን ይደረጋል አደል?
- በትክክል ጆሮ ላይ አዛን ይባላል
- እራዳሉት አሳሳቢ አስቸኳይ ሁኔታ ሲገጥም አዛን ይደረጋል?
- በትክክል
- አዛን ማለት ምን ማለት ነው?
- ጥሪ ማለት ነው
- ቅድም 5 ጊዜ ነው ብለዋል ?
- አዎ
- ለሊት የንጋት ሰላት ላይ ሁለት ጊዜ አዛን አይባልም እንዴ?
- እኛ አገር ላይ ባይለመድም ከአሁን በፊት ይደረግ ነበረ አሁን በአብዛኛው ላይ የሚታወቀው አንድ የሱቢሽ አዛን ብቻ ነው እና ከዛ በኋላ ኢቃሙ ነው የሚታወቀው ከአዛን በኋላ ኢቃም ነው በፊት ሁለት አዛን ነበረ አንደኛው ቀርቶ እና አገር ላይ በብዛት የሚታወቀው አንዱ ብቻ ነው
- ጁማ ሁለት አዛን የለም?
- ጁምአ ሁለት አዛን አለው አምስት ሰዓት አካባቢ እና ስድስት ተኩል አካባቢ ላይ
- ከቀኑ ነው ከለሊቱ?
- ከቀኑ
- እድሪስ
- አቤት
- ቅድም ሼህ ሆጀሌ መስኪድ አዛን ሰምተው ሲሄዱ ሰው ወይም ሕበረተሰቡ ስጋ ሊቆርጡ እና ሽንኩርት ሊከትፉ የሄዱ ሰወች ተደበደቡ ሲል ነበር?
- አዎ
- በማን ተደበደቡ አለ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በፌደራል ፖሊስ እንደተደበደቡ በፖሊስ ተደብድቡ ነው
- ከዛ ወዲህ በማግስቱም የቆሰለ ሰው ነበር ብለው ነበር ?
- በትክክል አዎ
- በማን ቆሰለ ተባለ?
- እዛው ባሉት ግማሹ ሲሸሽም የቆሰለ አለ መስታወትም የሰበራቸው አሉ መስታወት የቆረጣቸው ማለት ነው
- ከማን ሲሸሹ ?
- ከፖሊስ ሲሸሹ
- ቅድም አሁነ በስራ ባልደረባዬ ሲጠየቁ አንዱ አዛን የሚደረግበት ፕሮግራም እስቲስካ ነው ብለው ነበረ ?
- አዎ
- እስቲ ይሄን ለፍ/ቤት ያስረዱ ምናልባት ቃሉ የተለየ ስለሆነ ምን ማለት እንደሆነ?
- ይህ አጋጣሚ ለምሳሌ ድርቅ ሲከሰት አጋጣሚ አንዳንድ ከባድ ነገሮች እንደ ጦርፍ እንደ ዝናብ መጥፋት ነገሮች ሲከሰቱ ለሊት ተነስቶ ለመስገድ ሕብረተሰቡ ሰብሰብ ብሎ ለመስገድ ሲፈልግ ሌላም አስቸኳይ ሁኔታዎች ሲገጥሙት ድንገታዊ ሁኔታ ሲገጥሙት አዛን ያደርጋል በዛን ሰዓት አዛን የሚያደርገው ዱአ ሊያደርግበት ነው ተሰብስበው ዱአ ሊያደርግ እና ለዛ አስቸኳይ ሁኔታ እንዲደረስለት ነው አዛኑ
- የመጨረሻ ጥያቄ ይሄ አዛን በሉ ብሎ ትእዛዝ ያስተላለፈ ሰው አለ እንዴ?
- ኖ እኔ አልሰማሁም እንደዛ
- የሚያውቁት አካል የለም?
- የለም
- እሺ አመሰግናለሁ
- ድጋሚ ጥያቄ አለ አቃቤ ሕግ
- ጨርሰናል ብለው እስቲ አሁን ምክንያቱም እሳቸው ጥያቄ ጀምረዋል እሚጠየቅላችሁ ነገር ካለ በኋላ በፍ/ቤቱ በኩል ብታስጠይቁ ይሻላል ያዙትና ጥያቄውን
- አሁን መጨረሻ ላይ ሲጠየቁ መስቀለኛ ጥያቄ የቆሰሉ ሰወች አሉ በምን ምክንያት ሲባሉ ከፌደራል ፖሊስ ሲሸሹ ብለዋል አይተዋል እንዴ ይሄንን?
- አይቼ ሳይሆን በማግስቱ ያገኘኋቸው ልጆች የነገሩኝ እና ታሽገው ያገኘኋቸው ጅምናሱል ከፖሊስ ስንሸሽ እና ፖሊስ ሲመታን መስታወት የመስኪድ መስታወት ቆርጠናል
- እዛ ስለተፈጠረው ነገር ያውቃሉ እዛ እረብሻ ይፈጠር አይፈጠር?

ECLN

275

1845

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጩኸት ይሰማ ነበር አልፎ ጩኸቱ እነ ያለሁት ለምሳሌ ሽጦሉ እሩፋኤል መሃከል ላይ ነው ያለሁት እና እዛ ያለው ጩኸቱ ከመስኪዱ
- እኮ ያወልያ መስኪድ ጩኸት ቀጥታ እኛጋ ይሰማ ነበረ ዳይሬክት የሕዝብ ጩኸት
- እኮ እረብሻ ይፈጠር አይፈጠር የሚያውቁት ነገር አለ ወይ ?
- ጩኸቱ አዎ እረብሻ እንዳለ ያስገመግማል
- እኮ በዚህ እረብሻ መሃከል ሕግ በማስከበር አጋጣሚ ሲሸሹ የወደቁ ይሁኑ ፖሊስ ጥቃት አድርሶባቸው ይሁን ይሄን አጣርተዋል?
- ከራሳቸው ከእነሱ ከንደበታቸው ሰምቻለሁ
- ጉዳት ከደረሰባቸው ነው የሰሙት ይሄን?
- ከደረሰባቸው ልጆች አዎ
- ይሄን የሰሙት?
- አዎ
- ከሌላ ሰው አልሰሙም ?
- ከሌላ አልሰማሁም ከደረሰባቸው ነው
- የሰሙት?
- አዎ
- ዱአ ለማድረግ ነው ብለዋል ይሄ ለሊት ላይ የሚደረገው ለድርቅ ለጉርፍ ምናምን ለአስቸኳይ ያሉት ዱአ ተደረገ እንዴ ያን ቀን?
- ዱአው በዚሁ ኬዝ ተቋርጧል
- በምን?
- በነበረው ሁኔታ አለመግባባት የተነሳ
- አይ አደለም አዛን ጥሪ ተደረገላችሁ?
- አዎ
- እርስዎ ወደሚቀርቡት ሄዱ ?
- በትክክል
- ከሄዱ በኋላ ዱአ ተደርጐ ወደየቤታችሁ ተበታተናችሁ ወይ?
- ዱአ አልተደረገም ይሄ ሃዛን የወጣበት ምክንያት አወልያ ላይ በነበሩ ግለሰቦች ላይ ባደሩ ግለሰቦች ላይ ቅድም ለመግለጽ ሞክሪያለሁኝ ሽንኩርት ለመክተፍ ስጋ ለመቁረጥ በሄዱ ሴቶች ላይ በተፈጠረው ሁኔታ ላይ ነው አዛኑ የወጣው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ አሁን እኮ እርስዎ ከነገሩን ኃይማኖታዊ አነጋገር ዱአ ለማድረግ ነው አዛን የሚደረገው በዚ ሰዓት ዱአ ለማድረግ ነው ተብሏል?
- ኢን ጄኔራሊ ሃዛን የሚደረገው ዱአ ለማድረግ ነው
- እኮ ዱአ ተደረገ ወይ ያን ቀን?
- አልተደረገዋ ያልተደረገበት ምክንያት የነበረው ከፖሊስጋር በነበረው አለመግባባት የተነሳ ዱአ አልተደረገም ዱአም አልተደረገም ሕብረተሰቡ እራሱ አዛኑ ሊወጣ የቻለው በዚሁ በፖሊስ በነበረው የመደብደብ ኮንዲሽን ላይ ነው
- እሺ ፖሊስ እዛ መጥቷል እንዴ ሸጐሌ እናንተ የነበራችሁበት መስኪድ ፖሊስ መጥቷል?
- ፖሊስ በትክክል ግቢ ውስጥ አልገባም እረብሻ አልነበረም አካባቢው ላይ ነበረ
- ታዲያ ዱአው በምን ተቋረጠ እናንተጋ?
- በቃ ሰው እሕብረተሰቡ ወደ አወልያ እንሂድ
- ወደ አወልያ እንሂድ ስላለ እንጂ በፖሊስ አማካኝነት ተቋርጦ አደለም?
- ኖ ሼህ ሆጀሌ ላይ በፖሊስ አደለም ያቋረጠው
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት
- በፊት ያለተነሳ ነው ፖሊስ ደበደበ ሲል በዚህ በፍ/ቤትም የያዝነው ነገር የለም ስለዚህ ይሄን ጥያቄ አልተቀበልነውም
- እሺ ጨርሰዋል እናመሰግናለን መሄድ ይችላሉ እርስዎ
- ምስክር የለንም
- የለም ጨርሳችኋል?
- አዎ ማለት 3 ምስክር ነው ለከሰዓት የያዝነው ይበቃል ብለን የገመትነው ምናልባት ከዛ ከተገመተው ሰዓት በፊት ስለሚያልቅ
- ነገ በተለመው ሰዓት እንቀጥላለን ለዛሬ በዚሁ አጠናቀናል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

4ኛ ወ/ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

ጥር 30 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች :- ብስራት ተህልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሳሽ :- አቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድምአገኝ ፣ቴዎድሮስ ጌታቸው

ቀርበናል

ተከሳሾች:- እነአቡበክር አህመድ ከ23ኛ እና ከ29ኛ ተከሳሽ በስተቀር ሁሉም ቀርበዋል የተከሳሽ ጠበቆች መሃመድ አብደላ ፣ባህሩ መካንጋ ሃሊማ ሰይድ ቀርበናል እሺ የተከሳሽ ጠበቆች 3 ጠበቆች ስማቸው ከላይ የተጠቀሰው ቀርበዋል ሌሎቹ አልቀረቡም የ28ኛ ተከሳሽ ጠበቃም አልቀረቡም እሺ የ28ኛ ተከሳሽ ደምበኛ ሌላ ቀጠሮ አለኝ ብለው ሳይቀርቡ ቀርተዋል ብለዋል እሺ አቃቤ ሕግም እኚህን ተከሳሽ በተመለከተ የቀረበ ምስክር ስለሌለ በሌሎቹ ላይ ስለሆነ ቢቀጥል ችግር ስለሌለው እንቀጥል ብለናል ስለዚህ አቅርቡ

- በእውነት ለመመስከር
- በእግዚአብሔር ስም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምያለሁ
- እሺ ምስክር ለምስክሮች ደህንነት ሲባል የመጀመሪያ ስሞን ብቻ እንዲጠቅሱ ነው ፍ/ቤቱ የፈቀደው ስለዚህ የመጀመሪያ ስሞ ማን ነው?
- ሰይፈ ዘመድኩን
- እሺ ስንተኛ ተራ ቁጥር ነው አቃቤ ሕግ?
- 44ኛ ተራ ቁጥር
- እሺ በፍ/ቤቱ ተራ ቁጥር 28ኛ ናቸው በአቃቤ ሕግ 44ኛ ተራ ናቸው
- ለምንድን ነው እዚህ የመጡት?
- ለምስክርነት ነው
- በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?
- በሙባረክ አደም ፣አቡበክር አህመድ ፣ካሚል ሸምሱ
- በነዚህ ነው ?
- አዎ
- እነዚህን ተከሳሾች ታውቃቸዋለህ ?
- አውቃቸዋለሁ
- ልታሳየን ትችላለህ?
- አዎ
- እስቲ አንዴ ተነስና አሳየኝ መለየት ካልቻልክ ይቆሙልሃል አልያም ቁጭ እንዳሉ መለየት እችላለሁ ካልክ ትችላለህ
- እሺ 1ኛ ተከሳሽን ለይቶ አሳይቷል ፣ እሺ 20ኛ ተከሳሽን ሙባረክ ለይቶ አሳይቷል ካሚል ሸምሱ ስንተኛ ተከሳሽ ነህ እሺ 4ኛ ተከሳሽን ካሚል ሸምሱን ለይቶ አሳይቷል ከነዚህ ሰወች አሁን ከጠራሃቸው ሰወች ጋር ፀብ ወይ ዝምድና አላችሁ?
- የለንም
- እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- እሺ ምስክር የሚያውቁትን ነገር በዝርዝር ያስረዳሉ አሁን ጠቀመው ባሳዩዋቸው ተከሳሾች ላይ ከጊዜው ይጀምራሉ ጊዜውን ያስታውሳሉ ?
- ጊዜው አዎ አስታውሳለሁ ጥር ላይ ነው ጥር 2004

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቦታው የት ነው?
- አወልያ ት/ቤት
- እሺ አሁን በጠቀሱልን ጊዜ እና ቦታ ምንድን ነው የሆነው ?
- በወቅቱ እኔ እዛ ነበርኩኝ ማለትም ችግር አለ ተብሎ ከስራዬ አንባር አዛ ሄጄ ነበር ሥራዬም ስለሚፈቅድ ማለት ነው እና እዛ በሄድኩ ሰዓት ጩኸት ነበረ ጊቢው ዉስጥ አወልያ ግቢ ውስጥ ማለት ነው እና በሚጮህ ሰዓት ውስጥ ገባን ምንድን ነው አደባባዩ ላይ ሙባረክ ሰብስቦ
- እነማንን?
- ማለትም ተማሪዎቹን እንዳለ ሰብስቧቸው አላህዋክበር አሻም ሁሪይስቃጠል በማለት ከዛ በኋላ ደግሞ በኃይማኖታችን ድርድር የለም ማንኛውም ሙስሊም ለኃይማኖቱ መታገል አለበት ሙስሊም አይደላችሁ ወይ ሙስሊም ሆይ ንቃ ለኃይማኖታችን እስከ ህይወት መስዋእትነት እንታገላለን መጅሊሱ አይወክለንም መንግስት አረብኛ ትምህርት ሊያስቆምብን ነው የመጅሊስ አሰጋጁ ይመለስልን ማንም ተማሪ ወደ ውጪ እንዳይወጣ እዚህ ሆነን ጩኸታችንን እናሰማለን እና ከዚህም አልፎ ደግሞ የነሱ እኔ አላውቅም በእርግጥ ያው እምነቱን ስለማላውቅ ተወካይ ተብሎ መልስ ሊሰጥ የመጣ ሰውዬ ነበር
- ከየት?
- ከመጅሊስ ነው ያሉት እና እሱ ሰውዬ ለመደብደብ በቃ ያዙኝ ልቀቁኝ በቃ እና አንድ መኪና ነበረችው መኪናዋን ሁሉ ጐማዋን አራቱንም ጐማ አፈነዷት
- ማን?
- በቃ እነሱ ሙባረክ ጓደኞቹ አሉ አውቃቸዋለሁ እንዲህ ባያቸው ማለት ነው ያው በስም ስለማላውቃቸው አፈነዱት ሰውየው በቃ በመሃል እንዴት ያስወጡት ያው እኛም እንትን ማለት ስለማንችል ዝም ብለን እያየን ነው እኛ ከዛ በኋላ በቃ ሁሌ እንትን ይላል
- ምን አረጉት መኪናውን ሌላ ጐማዎቹን አፈነዱ ብለዋል ?
- ጐማው ፈነዳ በቃ መኪናው አይወጣም እስከ ስንት ቀን ሁሉ አልወጣም ሌላ በቃ ሙባረክ ፖሊሶቹን የመገፍተር ውጪ ያሉት ፖሊሶቹን ማለት ነው ፖሊስ እራሱ አንድ ሰው በእኛ ማንም አይመለከተውም አንተን ብሎ መልስ መላሽ ሰውየውን ማለት ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ፖሊሶቹ ምንድን ነው ብለው በር ላይ እራሱ በቃ ማንም አያስገባም ዘበኞቹም አይመለከታችሁም ተብለዋል እና አስተማሪዎች ይመለሱ ዘበኞች ይመለሱ ኢማሙ ይመለስ ኮሌጁ ይከፈትልን በማለት በቃ ይቀሰቅስ ነበር በጣም ብዙ እንደውም ስለቆየ እረስቼ እንጂ ብዙ ነው የሚያወራው

- አንተ በወቅቱ ይሄን ካየህ በኋላ ሙባረክን አላናገርከውም?
- ሙባረክን እንደውም እኔ ሙባረክ እንደኔ ልጅ ስለሆነ ጠየቅኩት ውጭ ሲወጣ ማለት ነው እንዲህ እንዲህ ከምታረግ በአግባቡ ጠይቅ ስለው እሱ የእኛ ችግር ነው እንጂ የአንተ አደለም አለኝ አይመለከትህም ዝም አልኩት እሺ አይመለከተኝም ብዬው
- ይሄ አሁን የገለጽክልን ነገሮች በሙሉ በአንድ ቀን የተፈፀሙ ናቸው?
- እንዴ አረ ተደጋጋሚ ነው የሚለው በቃ ጁማ ጁማ የመጣ ቀን በቃ ይሄ ነው እሱ እራሱ በቃ አሁን ከግቢው ማለት ነው የተማሪ ተወካይ ነው እሱ
- ሰይፈ
- አቤት
- ጁምአ ምንድን ነው?
- አርብ አርብ እንትን የሚባል ማለት ነው ይሰግዳሉ
- ኦኬ ስለዚህ አርብ አርብ ነበረ ?
- አርብ አርብ ብቻ
- የገለጽካቸው ነገሮች እየሆኑ የነበሩት?
- አዎ ሙባረክ አርብም ሌሎች ቀንም ያረጋል ሙባረክ ማለት ነው ሌሎቹ ሌላ ጊዜ ነው በጁምአ በጁምአ ቀን ነው የሚያረጉት
- ኦኬ ቅድም ከጠቀስካቸው ሱወች መሃል ሙባረክ አንዱ ነው ሌሎች ሁት ሰወች በስም ጠቅሰህ ለይተህ አሳይተሃል አንደኛው አቡበከር አህመድ ነው እሱ እሺ ምን ሲያደርግ ነው የምታውቀው?
- አቡበከር አህመድ ይመጣል አስተማሪ እሱ ነው ይባላል እዛ መጥቶ ማለት ነው እና እዛ ይመጣና በቃ አንደኛ የሚያነሳሳቸው እሱ ከመጣ በቃ ሞራሉ ሌላ ነው እኮ ምንድን ነው እሱን ነው የሚናገሩት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ አሁን ልነግራችሁ ነው እኛ መንግስት ቢያስፈራራንም ከመናገር ወደኋላ አንልም አላባሽ እያለ አሸባሪ እያለ ምን እያለ ቢፈይደንም እኛ አሸባሪ እንዳልሆንን እናሳየዋለን ስለዚህ ሙስሊም ሆይ ንቃ ማንም ቁጭ ማለት የለበትም ወዲያውኑ አላህዋክበር ይላል እሱ እነሱም አላህዋክበር ይሉታል ይቀጥሉና ከዛ በኋላ እሱ ይሄን ይናገራል ምላሻችሁን ሁሉ አሁን እናሰጣችኋላን ምላሻችሁ ይምለስላችኋል ስለዚህ አሁንም ትግላችሁ መቀጠል አለበት ማንም ሰው መፍራት የለበትም ለዚህ መታገል አለብን
- እስከምን?
- ከዛ በኋላ እንደዚህ ይላል በቃ እነሱም አላህዋክበር ይላሉ 3 ጊዜ ይባላል አላህዋክበር ከዛ በኋላ ኃይማኖታችንን በግላችን እናደርጋለን አቡበክር ማለት ነው በግላችን እናደርጋለን ማድረግ ያለብንን በኃይለስላሴ ጊዜም ሙስሊም አይታወቅም ነበር በደርግ ሰዓት ትንሽዬ ጭምጭታ ነበረች አሁን በኢሃዲግ ለስሙ በዝተናል ብዛታችንን ግን አላሳየነውም እንዲህ ጭብጥ አርጉ ሲያየን ትንሽ ነው የመሰልነው ስንበተን ያየናል ሲሉ ወዲያውኑ አላህዋክበር ይሉታል
- እና ምን ያህል ነን ነው?
- በቃ እኛ እንደውም እዛ ላይ ያለው ከመቶ ሺህ አንድ ሚሊዮን እንሆናለን አሁን የተሰበሰብነው እዛ ማለት ነው አወሊያ ላይ አንዴ መቶ ሺህ ይላል አንድ ሚሊዮን ማለት ነው በቃ በሚዲያ ላይ ብዙ ነው በቃ እሱ እንትን የሚለው እዛ ይሄ ማይኩ ላይ ማለት ነው
- እና ብዙ ስለሆንን ምን እናደርጋለን ነው?
- የራሳችንን ማድረግ ያለብንን እናደርጋለን
- ምንድን ነው እሱ?
- ኃይማኖታቸውን ማለት ነው ኃይማኖታችንን የራሳችን እናደርጋለን መንግስት ቢጫነንም ምንም ቢለንም ከትግል ወደ ኋላ አንልም በማለት ይናገራል እሱ
- ትግሉ በምን መልኩ ነው?
- ያው እስከ ሕይወት መስዋእትነት እንታገላለን ብለዋል እኮ ቅድምም አሁን ከሙባረክጋር አያይዤው ነግሬዋለሁ እስከ ሕይወት መስዋእትነት እንታገላለን ማንም

1851
282

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ሰው እንዳይፈራ በቃ ወዲያውኑ እንዲህ ሲል መፈክር ነው የሚመስለው አላህዋክብር ይላሉ

- አሁን ስትገልጽ ምስክር ብዙ ነን በጣም በዝተናል እያለ ይናገር ነበር ብለሃል ታዲያ ብዙ ስለሆንን ምን እናርግ ነው?
- ማለትም በቃ የራሳችን እምነት ማንንም አንፈራም በወቅቱ እኮ እኔ እንትኔ ላይ ስላልያዝኩ ነው የተከበረው ፍ/ቤት መዝገቤ ላይ ብዙ አለ በወቅቱ ያለው እና ብዙ ነው ያለው በቃ ከእምነቱጋር ተያይዞ
- እሚያስታውሱትን ይናገሩ
- ጥሩ ወደ ካሚል ሸምሱ እንሂድ ካሚል ሸምሱንስ ምን ሲያረግ ነው የምታውቀው ?
- ካሚል ሸምሱ እኔ ይታሰር አይታሰር አላውቅም መንግስት እየጠራ ቢያስፈራራኝም ቢመክረኝም እኛ እንደሆነ ወደኋላ አንልም ይላል እሱ ሲል አላህዋክበር ይላል ከዛ በኋላ ደግሞ እንደፈለገ ጠርቶ ያስፈራራን ይደብድበን ይግደለን እንጂ እኛ አሁንም ወደኋላ የምንልበት ምክንያት አይኖርም ሲል አላህዋክብር ይባላል ከዛ በኋላ /ግልጽ ያልሆነ/ ብዙም እንትን አይልም እና መልስ የፈለጋችሁት እንትኑን ኮሌጁ ጥያቄያቸው በሙሉ ማለት ነው መጅሊሱም ሁሉ ነገር በእኛው ይስተካከላል ምንም የሚያስፈራችሁ ጉዳይ የለም ትግላችንን ወደፊት መቀጠል አለብን ሲል አላህዋክበር ይባላል
- ምስክር አሁን ስለ ሦስቱም ሰወች ስትናገር እኛ እናስመልሰዋለን ጥያቄያችሁን ወደኋላም አንልም ይሉ ነበር ሦስቱም ሰወች እኛ የሚለው እነማንን ነው?
- እኛ ሙስሊሞች ማለት ነው እኛ ሙስሊሞች ማንንም አንፈራም
- ጥሩ አሁን ለሙስሊሙ እዛ ለተሰበሰበ የሙስሊም ህብረተሰብ ነው አደለም ይሄን ንግግር የሚያደርጉት አይዟችሁ አትፍሩ እኛ ጥያቄያችሁን እናስመልሳለን ይል ነበር ብለሃል ማንን ነው እንደዛ የሚሉት?
- ማለትም መንግስትን
- እሺ ቆይ ተቃውሞ ቆይ ምንድን ነው ተቃውሞ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ ይሄንን ጥያቄ ጠይቀው መልሰዋል አቃቤ ሕግ ምንን ማውጣት እንደፈለጉ እኛ እናውቃለን መናገር ባንፈልግም ይሄን ጥያቄ የተከበረው ፍ/ቤት የተመለሰ ስለሆነ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንዴት እንዴት?
- ደጋግመው እየጠየቁ የተመለሰን ጥያቄ ምስክሩን የመምራት ሥራ እየሰሩ ነው የተመለሰ ጥያቄ ላይ አትኩረው ደጋግመው እንዳይጠይቁ መምራት ስለሚሆን እንዳይጠየቅ ነው የምንጠይቀው የተከበረው ፍ/ቤት እኛ የሚለውን የተከበረው ፍ/ቤት ተጠይቀው መልሰዋል ሙስሊሙን ሕብረተሰብ ብለዋል ምስክሩ ከዚህ በኋላ ሲጠየቁ የመለሱት ጥያቄ ላይ እንደገና ሲጠየቁ ወዴት እንደሚመሯቸው ግልጽ ነው እየመሯቸው ነው ስለዚህ መምራት ነው ጥያቄው ተደግሞ አይጠየቅብን ነው
- እሺ ምላሽ ስጡበት
- እሺ ያው ፍ/ቤቱም ሲከታተለው እንደነበረው ምስክሩ ደጋግመው ስለ ሦስቱም ሰወች ሲገልፁ ጥያቄያችሁን እኛ እናስመልሳለን ችግር የለም እናንተ እስከመጨረሻው እስከ ሕይወት መስዋእትነት ለመክፈል ተዘጋጁ እያሉ ምስክሩ ደጋግመው ሲገልፁ ነበር እኛ የጠየቅነው ሳንመራ ደጋግመህ እኛ እናስመልስላችኋለን ትል ነበር እኛ የሚሉት እነሱ እነማንን ነው ምስክሩ ስላልተረዳ ሙስሊሙን ሕብረተሰብ ነው ስላለ ስላልተረዳ ጥያቄውን ለማስረዳት ነው ያልነው እንጂ የተከበሩ ጠበቃ እንደገለፁት መሪ ጥያቄ ቀደም ብሎ በዚህ ፍ/ቤት ብይን የተሰጠበት ነው መሪ ጥያቄም አልጠየቅንም ምስክሩ አንደርስታንድ ያደረገውን ነገር ያልተረዳውን ነገር ነው ደግመን የጠየቅነው እና መቃወሚያውም በአግባቡ የቀረበ አደለም ውድቅ እንዲደረግ ነው እምናመለክተው
- እሺ ያው ላለመደጋገም የናንተን የሁለታችሁን ላለማንሳት ፍ/ቤቱ ያየው ነገር መሪ ጥያቄ አደለም ነገር ግን አቃቤ ሕግ መደጋገም ይታያል እሱን መደጋገሙን ቀንሳችሁ ጥያቄያችሁን ቀጥሉ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር አሁን በዋና ጥያቄ ሲጠየቅ ደጋግመህ ስትገልጽ እኛ መልሱን እናመጣላችኋለን እናንተ ለመታገል ጽኑ ይሏቸው ነበር ስትል ነበር እነካሚል እነአቡበከር እኛ የሚሉት እነማንን ነው ምን ስለሆኑ ነው እነሱ?
- አዎ እኔ በወቅቱ እኔ ምንም ስላልገባኝ እራሳቸውን አሁን እንደዚህ የራሳቸው እምነት ይኑር ሌላ ይኑር አላውቅም በወቅቱ የሰማሁትን ነው እና እናመጣላችኋለን በቃ አሁን እንደውም አንዱን አላውቀውም አህመዲን ጀበል ነኝ ነው ብሎ እዛ ሲያስተምር የሰማሁት ምንድን ነው በቃ ምንድን ነው የምንፈራው እስከ መቼ ነው የምንፈራው በቃ እንደሚያለቅስ ሰው ሆኖ ነው የሚናገረው እንደዚህ ባላውቀውም ማለት ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አህመዲን ጀበል የሚባለው እና እነሱም ሲያስተምሩ በቃ ሁሉም መውጣት ሁሉ አይፈልጉም በቃ በወቅቱ ማለት ነው እኛ ሲል እኔ እራሴ አልገባኝ ወይ መስኪዱ መጅሊሱ ይመልስላችኋል አላለ ምን አላለ እኛ ነው የሚሉት እራሳቸውን ማለት ነው እና ይሄን ነው የሰማሁት

- እሺ ሌላ ጥያቄ
- ጥሩ አሁን አህመዲን ጀበል ብለሃል አህመዲን ጀበል አወልያ ይመጣ ነበር?
- አዎ ማለትም እኔ እንደዚህ በእንትን አላውቀውም አስተማሪ አህመዲን ጀበል ተብሎ ማለት ነው ቆሞ ቀሩቅ ብዙም እንትን ነው የሚያረገው እንደዚህ ስለማላውቀውም እንደዚህ እስከታች ድረስ ቀሚስ ነው እሱን ነው ያደረገው እሱን ስለሚያደርግ አለየውም እንጂ እሱም በቃ ልክ እንደነሱ ነው የሚያስተምረው
- ምን እያለ ሲያስተምር ሰማህ?
- እሱ እንደውም በቃ አህመዲን ጀበል አስተማሪ ነው ሲባል ጩኸት ነው በቃ የሚነሳው
- ቆይ አይ ምን እያለ አሁን በተደጋጋሚ ጊዜ ጀለቢያ ለብሶ አይቼዋለሁ ብለሃል ሲያስተምር የሰማኸው ነገር አለ ?
- ማለትም እሱም እንደነ ካሚል ማንም ሰው መፍራት የለበትም እሱ እንደውም እያስረገጠ ነው ቀስ እያለ ነው የሚናገረው ማድረግ ካለብን ምንም እናደርጋለን አላህዋክብር ይባላል ገና አንዳንድ ፊደል ሲናገር ሁሉ ለሱ ይጮሃል
- ምንድን ነው ማድረግ ካለብን ሁሉን እናደርጋለን ማለት?
- እኔ እሱን አላውቅም ምን እንደሚያደርግ
- እኮ ያብራራው ነገር የለም?
- ማለትም በቃ እሱ እሱም ቢያስፈራሩንም ብንታገትም በቃ ማለትም ብዙ እንትኖቹን አላውቅም እሱም በቃ እንደዚህ እያለ አህመዲን ጀበል ዛሬ አስተማሪ ነው ከተባለ በቃ እንትን እሱ የሚናገራቸው ቃላት ጭንቅላት የሚነካ ነው የሚባለው እዛ ውስጥ ሁሉ እኔ ስለማላውቅም ነው በእንትን ይናገራል ምንድን ነው አረብኛ ነው ምንድን ነው የሚባለው ስለማላውቀው በሱ ነው በብዛት የሚናገረው
- ሕዝቡ ምላሹ ምን ነበር?
- በቃ ሕዝቡ አላህዋክብር ይልለታል

1854
2555

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይሄ ጥያቄ ተመልሷል
- እሺ ሌሎች አንተ በወቅቱ እዛው አካባቢ በነበርክበት ወቅት ያየሃቸው አስተማሪዎች አሉ አሁን ከጠቀስካቸው ውስጥ ?
- እዛ?
- እ?
- ስሙን አላውቀውም አለ አንድ ጥቁር
- በስም የምታውቃቸው አሉ ጥሩ ቅድም ስለ ሙባረክ ስትገልጽ ሰወች ከግቢ እንዳይወጡ ይል ነበረ በአፉ ብቻ ነው እንዳይወጡ የሚለው?
- አረ በርም ላይም አያስወጣም በቃ
- እንዴት አርጉ?
- በቃ በሩን ይዘጋዋል በሩን ይዘጋዋል ዘበኞቹ ሁሉ እሱን ይፈሩታል ሌላ ሰው ማንንም አይፈሩም ዳይሬክተር ነው ምናምን የሚባለውም እራሱ አይፈራም እሱ ካለ በርም አይከፈትም ምንም አይደረግም በቃ ይዘጋል እሱ ወይ አስተማሪ ወይ በሆነ በሽማግሌዎች እንትን ሲባል መልሶ ግማሾቹ እንሂድ ይላሉ ለኃይማኖትሽም እዚህ መታገል አለብሽ አረ ፀሐይ በጣም አቃጣይ ነበረ እዛ ያቃጥላል በጣም እዛ አስፋልት ላይ ሆኖ እና ያን ያን በማድረግ
- እስካሁን የገለጽካቸው የኃይማኖት አስተማሪዎች እዛ አሉ ያልከውን ነገር ስትናገር ነበር ስለ አላማቸው ይናገራሉ ምንድን ነው የምንፈልገው ይላሉ የሰማኸው ነገር አለ?
- ማለትም የራሳቸውን ይሄ መጅሊሱ እንደማይወክላቸው እና የራሳቸው ማቋቋም እንዳለባቸው
- ምንድን ነው የሚያቋቁሙት?
- እኔ እሱን አላውቅም እና
- አይ የሚናገሩት አንተ የምታውቀውን አደለም ?
- መጅሊሱ እንደማይወክላቸው በመጅሊሱ እንደማይመሩ መንግስት ከእንትኑጋር እንደሆነ ከመጅሊሱጋር መንግስት የላካቸው ናቸው የተቀመጡት የመንግስት ሰወች ናቸው እኛን የሚወክሉ አደሉም እኛን የሚያስተዳድሩም አደሉም በማለት ነበር ይሄን የሚናገሩት

1885
286

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከዚህ ውጭ አላማቸውን በተመለከተ ቅድም የጠቀስካቸው ሰወች ሲናገሩ የሰማኸው ነገር አለ?
- እኔ አላማቸው ምን እንደሆነ አላውቅም እሚሉትን ነው የሰማሁት
- ገብቶኛል አሁን መጨረሻ ላይ ስትመልስ የራሳችንን እናቋቁማለን ሲሉ ሰምቻለሁ ብለሃል ምንድን ነው የሚያቋቁሙት ?
- እኔ እሱን ምን እንደሚያቋቁሙ አላውቅም የራሳቸውን እንትን ያው ቅድምም ተናግሬያለሁ
- ይበቃል ግልጽ ነው
- እሺ ዋና ጥያቄ አበቃን
- እሺ መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ የተከሳሽ ጠበቆች
- አቶ ሰይፈ ቅድም ሙባረክ ከጓደኞቹጋ ነበር ብለውናል የትኛው ጓደኛው ነበር መኪናውን ጉማ ያፈነዳው ?
- እንዲህ በመልክ አውቃቸዋለሁ ስማቸውን አላውቅም
- የትኛው ጓደኛው ነበር?
- እራሱ ያውቃቸዋል የሱ እኩያ ናቸው አንዱ ደግሞ እንትና ይባላል ታጁዲን የሚባል
- ታጁዲን ነበር መኪና ጉማ ያፈነዳው ?
- ታጁዲን የሚባል ሌሎቹ ስማቸውን አላውቅም እንዲህ ግን በመልክ ሁሉንም አውቃለሁ
- ታጁዲን የመኪናውን ጉማ ሲያፈነዳ አይተውታል አይደል?
- ታጁዲንም ነበር አዎ
- የትኛውን የመኪና ጉማ ነበር ታጁዲን ያፈነዳው?
- እንዴት የትኛውን አንድ መኪና ናት የቆመችው
- እኮ ምን አይነት መኪና ነው የመኪናውን አይነት ?
- አይ የተከበረው ፍ/ቤት የትኛው?
- ሰውየው ይዞት የመጣው ማለት ነው ይሄ ተወክዬ ነው የመጣሁት ያለው ማለት ነው እሱ ነው ይሄት የመጣው ያው እኔ የመኪናዋን ስም አላውቅም
- /የማይሰማ/
- አሃ አራት ጉማ እሱ አደሉም ያፈነዱት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስሪ ቀይ እሳቸው ይጠይቁ
- ጥያቄው እንደሱ ከሆነ
- ቀይ እስቲ ጥያቄውን ግልጽ አርጉት
- የትኛውን የመኪና ጐማ ነው ያፈነዳው ታጁዲን የሚባለው ?
- እሺ ማለትም
- አራት ጐማ አለው መኪና አደለም?
- አራት ጐማ ነው ያለው እኮ ላስረዳሽ አሊም ቤቱጋር እንዲህ ነው የቆመችው መኪናው
- ቀይ ምስክር አራት ጐማ አለ አደለም ከአራቱ ጐማዎች የትኛው ነው አንዱን ነው ሁለቱን ነው አራቱን ነው የትኛውን ነው
- አንዱንም እሱ ብቻውን አደለም ብዙ ሆነው እንደዚህ እንትን ሲሉት ነበረ ያየሁት ማለት ነው ሌሎቹ ደግሞ እንደዚህ እንደዚህ በመልክ አውቃቸዋለሁ ቢቀርቡልኝ ሁሉንም ማሳየት እችላለሁ
- እሺ ምን ለብሶ ነበረ መባረክ በዛን ጊዜ?
- በወቅቱ አላውቅም እንትን ግን አስሯል ጨርቅ ነው ምንድን ነው
- ስንት ሰው ነበረ እዛ ግቢ ውስጥ የነበረው ብዙ ሰው ነበረ አደል?
- የዛኔ አይ ወጥተው በዛ ሰዓት ጐማው በሚፈነዳ ሰዓት ብዙ ሰው አደለም ያለው በሩ ላይ ነው እየተከተሉት መጡ ከዛ በኋላ ልክ በር ላይ ሲወጣ ሲል ነው በመኪናው ሲሄድ ሲል እዚጋ እንዳሉ ሁሉም አንቀውት
- አደለም አደለም
- እ
- ግቢ ውስጥ መባረክ ንግግር ያደርጋሊ ሲሉ ብዙ ሰው ነበረ ግቢ ውስጥ አደለ?
- የዛኔ እሱ ሲቀሰቅስ አዎ
- በጣም ብዙ ሰው ነበረ አደለ?
- በጣም ብዙ ሳይሆን የተጋነነ አደለም ተማሪዎች ናቸው መጀመሪያ የሚበዙት የዛ ተማሪዎች አሉ ሴቶች እና ደግሞ ከሱጋር የሱ ጓደኞች አሉ ጽ/ቤት በሩ ላይ ፊት ለፊት ሆነው ነው ይናገር የነበረው
- እሺ መጀመሪያ ሕዝቡ ጥያቄ ጠይቆ ነበር አደለም?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንዴት
- ምላሹን እናስመልስላችኋለን ያሉት መጀመሪያ ሕዝቡ ጥያቄ ጠይቆ ነበር?
- እንደሱ አደለም ሕዝብ ጥያቄ ምናምን ብሎ አደለም የሰማሁት
- ጥያቄያችሁን እናስመልስላችኋለን እያሏቸው ነበር አሉ ቅድም በዋና ጥያቄ ጥያቄያችሁን እናስመልስላችኋለን ሲሏቸው ነበር?
- እሱ አደለም ያለው እሱን
- አይ ሌሎቹ እነ አቡበክር አህመድ ጥያቄያችሁን እናስመልሳለን ብለዋቸዋል አደለም?
- አቡበክር አህመድ
- እ?
- አም
- ሕዝቡ መጀመሪያ ጥያቄ ጠይቆ ነበር ማለት ነው?
- እኔ አላውቅም እሱን
- ምኑን ነው ታዲያ እናስመልስላችሳኋለን ያሏቸው?
- ማለትም አሁን መጅሊሱ እንደማይወክላቸው ይሄ አሁን የተባሉት አረብኛ ትምህርት መንግስት እንዳንማር እያደረገን ነው ኮሌጁ ተዘግቶብናል ይሄ ይሄ እነሱ የጠየቁት ጥያቄ እንደሆነ ነው
- ስለዚህ መጅሊሱ ይመረጥልን ብለው ጥያቄ ጠይቀው ነበር ማለት ነው?
- እሱ ነው ሲናገር የሰማሁት እነሱ ሲጠይቁማ እኔ የት አይቼ አላየሁም እሱ ግን ይሄ የጠየቃችሁት ጥያቄ ሁሉ ማለት ነው
- ግልጽ ነው ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- አቶ ሰይፈ
- አቤት
- ቅድም የጠቀስካቸው ሰወች የተናገሩትን ስትጠቅስ ነበረ ጥር 2004 እንደሆነ ነው አሁን ይሄን ንግግር ሁሉ የሚያረጉት ጥር ውስጥ ነው እንዴ?
- ጥር ውስጥ ነው ወይ ሁሉም የነበሩት?
- ንግግር አረጉ ብለህ እያንዳንዱ የተናገረውን ገልፀሕልናል ?
- አም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሁሉም ንግግር ያደረጉት በጥር ወር ነው?
- እኔ አሁን የሰማሁትን ነው እራሴ ማለት ነው እኔ የሰማሁት ሙባረክ ጥር ላይ ነው እነዚህ አሁን ያልኩህም አራሱ አህመዲን ጀበል ካሚል ሸምሱ አቡበከር አህመድ በዚህ ወር እራሱ መጥተው ማለት ነው በጥር ወር ማለት ነው መጥተው የተናገሩ ናቸው ከጥር በኋላም እያለፈ እየሄደ ማለት ነው ይናገሩ የነበሩ ናቸው
- አሁን ግልጽ እንድታረግልን ይሄንን ንግግር እነሱ እንዲህ ተናገሩ እንዲህ ተናገሩ ብለህ አሁን የመሰከርከውን በጥር ወር ነው ከዛ በኋላ ባለው ነው መቼ ነው የተናገሩት ?
- ጥር ወር ላይም ተናግረዋል ከዛ በኋላ ከጥር በኋላ የካቲት ላይም ተናግረዋል
- እስቲ ግልጽ አርገው ማን ጥር ወር ላይ ማን የካቲት ?
- እኔ አቡበከር ጥር ወር ላይ ተናገረ ብዬ አልፃፍኩም አሁን በወቅቱ የሰማሁት ነው ጥር ወር ላይ ሲናገሩ ማለት ነው የሰማሁት በወቅቱ ከዛ በኋላም እንደነበሩ አውቃለሁ ሲናገሩም እንደነበረ አውቃለሁ
- እኮ ቀኑ እሳቸው የጠየቆት
- ጥር ወር ላይም ተናግረዋል
- እሺ ግልጽ ነው
- እርስዎ አወልያ ምን ያህል ቆዩ ?
- እስካሁንም አለሁ እዛው ነኝ
- ከጥር ጀምሮ እስካሁን እዛው አሉ?
- አዎ ስለ አወልያ በተመደብኩበት ስራ እከታተላለሁ እዛ አዛም አሁን አወልያ ምን ላይ እንዳለች ሁሉ ብትጠይቀው ይነግርሃል ችግር የለውም
- ጥሩ ቅድም ሙባረክን በግል መክሬዋለሁ ብለዋል ሙባረክ ምንድን ነው ክት/ቤቱጋ የሚያገናኘው ነገር ተማሪ ነው ?
- እሱ ተማሪ ነው የተማሪ ተወካይ ነው
- እንደተማሪ ተወካይነቱ ነበር እንዴ የሚነጋገረው?
- እንደተማሪ ተወካይም ሳይሆን እሱ እንደ አምባገነን ነው የሆነው እኔ ባላውቀውም ወንድሜ ማለት ነው እኔ ላይ አልደረሰም ግን ምንደዚህ አትሁን ቀስ ብለህ አስረዳ እንደዚህ ሌላ ነገር ውስጥ ትገባለህ ሁሉ ስለው ሕይወቴን ብሰዋ ማንም ሰው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አይመለከተውም ነው ያለው ሲለኝ ከዛ በኋላ መልስ የለኝም ከሱጋ በቃ እንደውም በአይነ ቁራኛ ነው ማየት የጀመረው እኔን ተውኩኝ ከዛ በኋላ በቃ የዚህን ያህል ነው የመከርኩት

- ጥሩ እንደተማሪ ተወካይነቱ ተማሪ እንግዲህ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ስለነበሩ ተማሪው ያነሳው ጥያቄ አቤቱታ ያቀረበለት ምላሽ የተሰጠበት ሁኔታ መኖሩን ያውቃሉ ?
- ማለትም አንዱ ምላሽ ሲሰጥ ከመጅሊሱ ባላውቃቸውም ስማቸውን ቀይ እረዘም ያሉ ሰውዬ መጥተው ኮሌጁ ይከፈታል እንደዚህ አደለም ሲሉ ማይክ ቀማቸው እሱ ሙባረክ እንደዚህ እንደዚህ አትለፍልፍ ግልጽ ግልፁን አውራ ነው ያለው እንደ ሕፃን ልጅ አሁን ከዛ በኋላ ሰውየው ተሸማቀቁ በቃ እኛ የመጡት የመጅሊስ ተወካይ ተብለው የመጡ ናቸው መልስ ሲሰጡ እና ሲቀማቸው እኛ የጠየቅነው ጥያቄ አግድም ምናምን የሚሄድ አደለም ግልጽ የሆነ ጥያቄ ነው ስለዚህ ትክክለኛውን ጥያቄ መልስልን ነው ያለው በቃ እንደ ሕፃን ልጅ ነው
- እሺ በቃ በቃ እሺ ቀጥሉ
- እነዚህ ቅድም ጮማቸው ተነፈሰ የምትላቸው ናቸው አደል መጅሊስ ያልካቸው ሰው የመኪናቸው ጮማ ተነፈሰ ያልካቸው ሰው ናቸው ?
- ምኖቹ?
- አሁን መጥተው ጥያቄ?
- አደሉም
- ሌላ ናቸው?
- ሌላ ናቸው
- ይሄም በጥር ወር ነው?
- ይሄን ወሩን አላውቅም
- ጥሩ ይሄንን ማይክ ብለሃል የትጋ ነበ ይሄ ንግግር ይደረግ የነበረው ሙባረክ ማይክ የቀማው የት ነው?
- አዳራሽ ውስጥ
- አንተ ውስጥ ነበርክ ወይስ ውጭ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ውጪ ነበርኩ
- ከአዳራሹ ምን ያህል እርቀህ?
- በቃ ከአዳራሹ እርቀቱን በግምት አላውቅም አሁን ውጩ ላይ ሆኜ እሱ ሲቀማ እንደዚህ ቆሞ ስለሆነ እሱ ያለው
- ቆየኝ አዳራሹ አለ እኔ ቦታውን ስለማውቀው ከአዳራሹ በኋላ መስኪድ አለ የለም መስኪድ?
- መስኪድ አለ
- ስለዚህ ከመስኪዱ በኋላ ደግሞ ክሊኒክ አለ ወደ ውጭ መውጫ ግቢ አለ ስለዚህ አንተ አሁን አዳራሹጋ ከአዳራሹ ውጭ የትጋ ነበር የቆምከው?
- በሩ ፊት ለፊት
- አዳራሹ ትልቅ ነው አደል?
- አዎ ትልቅ ነው
- ሰው ሙሉ አልነበረም እንዴ?
- ሰው ሙሉማ ነው ሰው ማለትም በኃይል ባይጠቀጠቅም ወንበሮቹ ሞልተዋል
- አንተ ከውጭ ሆነህ አየህ?
- አዎ
- ከዛ ሰውየው ምን አረጉ?
- በቃ ዝም አለ ሰውየው
- ቁጭ አሉ ?
- ቁጭ ብሏል መጀመሪያም አልተነሳም እኮ ሰውየው
- ማይክ ይዞ ነበር እኮ አልከን?
- እኮ እንደዚህ ማይክ ይዞ ነው እያወራ ያለው ከጉኑ ምን እንደሆኑ ባላውቅም አብረውት ያሉ ሰወች አሉ ትላልቅ ሰወች የሰውየው ከዛ በኋላ ሙባረክ ሰውየው እንዲህ ዞረው በዚህ በኩል ነው እሱ ያለው እንዲህ ነው የቀማቸው በቃ
- ከዛ ሰውየው ቁጭ ብለው ሙባረክን ማዳመጥ ጀመሩ ?
- ሙባረክ መልሱን በአግባቡ ስጥ ወደሌላ ወደሌላ አትሂድ አለው
- ሰውየው ቁጭ ብለው ሙባረክ ይሄን ሲነግራቸው ሰውየው ቁጭ አሉ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሰውየው መጀመሪያም ቁጭ ብሏል እኮ አልተነሳም ሰውየው
- ከዛ ስብሰባው ቀጠለ ማለት ነው አደል ?
- ስብሰባው ወዲያውኑ ሰውየው መልስ እንደዚህ ይከፈታል እንደዚህም ይደረጋል አጠያየቃችሁ በአግባቡ አድርጉት ሲለው ያው ስምምነት አልተደረሰም በቃ በወቅቱ
- እኮ ስምምነት አልተደረሰም እንጂ ስብሰባው ቀጠለ?
- በቃ ስምምነት አልደረሰም እንትና እንደ እንትን ሆነ ተናገደደ ሙባረክ ሙባረክ ተናደደ ያን ሲቀማቸው ምናምን በዚጋም በቃ ወከባ ሆነ ከዛ በኋላ ሌላ ከእሳቸው በላይ እንዲመጣ ተደርጉ ምላሻቸውም አጥጋቢ እንዳልሆነ ማለት ነው የሰውየው
- በእለቱ መጣ ከእሳቸው ሌላ ሰው ከእኚህ ሰውዬ ሌላ ሰው መጣ መልስ ሊሰጥ ?
- አይ ማለትም ይሄኛው ሰውዬ መጥቶ ነበር ይሄ አሁን ጉማው ተነፈሰ ያሉት ሰውዬ
- በእለቱ እሱም ነበረ?
- የለም ነበር ይሄ የመጣው እንደውም ውጪ ላይ ነው
- እሺ ጉማው ስለተነፈሰው ሰውዬ እሱስ በእለቱ በመጣበት ቀን እርስዎ ነበሩ?
- ነበርኩ አዎ
- እሱስ የት ነበረ ንግግር ያረግ የነበረው?
- ማን
- ጉማ የተነፈሰበት?
- ያው ፊት ለፊት ይሄ አወልያን አውቀዋለሁ ካልከኝ ፊት ለፊት ጽ/ቤቱ በር የለም?
- አዎ ግቢ ውስጥ ማለት ነው
- ግቢ ውስጥ ነው?
- ግቢ ላይ አስፋልት ላይ ማለት ነው
- እርስዎ የትጋ ነበሩ ያኔ?
- እኔ ቆሜ ነበር
- የትጋ?
- ከውጪ በሯ መግቢያ የለችም
- ግቢ ሳይገቡ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ በቃ መባረክ ማንንም ሰው አያስገባም በዛ ሰዓት መልስ ሰውየውጋርም እኮ ብዙ አላወሩም በቃ ምንም አላወሩም
- እሺ ሰውየው ሲናገር እርስዎ በማይክ ነበረ የሚናገረው ይሄ ጉማ የተነፈሰበት ሰው?
- ሰውየው በቃ አላወራም መጣ ለመልስ እንትኑ ላይ ወጣ መድረኩ ላይ ምን እንዳለ ብዙም ባላውቅ ሰውየው ጮሁበት ሰውየው ላይ ማለት ነው ሲጮሁበት ሰውየውም እንግዲህ ተናደደ መሰለኝ ምንም እንትን ሊሉት አልቻሉም በቃ
- ምን አደረገ እስቲ አንተ በወቅቱ እዛ ስላለህ ሰውየው ሊያናግሩት አልቻሉም ተናደደ ከዛ ምን ሆነ እስቲ እስከመጨረሻው ንገረን እስቲ?
- በቃ ሰውየው መጣ እስከ መጨረሻው ማለት ነው መጣና መልሱንም ምኑንም አልሰጠም ስላልሰሙት እየጮሁ ተከተሉት እንዳሉ ከዛ በኋላ ግብግብ ያዙት በቃ ትላልቅ ሰወች እንትን ይሉታል እንደዚህ አደለም እያሉ እንትን ሲሉት ወዲያውኑ ገና መኪናው ዞር ሲል እንዳለ እዛ እንትን የሚሉ የነበሩ መድረክ ላይ የነበሩ ልጆች እንትን አሉት ጉማውን አተነፈሱት አራቱንም ሰውየው ምን አረገ?
- በቃ ሰውየው ምንም አላለም ከዛ በኋላ እነዚህ ትላልቅ ሰወች ይዘውት ወጡ ወደ ውጭ ወደ ውጭ ይዘውት መጡ ከዛ በኋላ ሄደ በቃ
- አቡበክር አህመድ ይናገር የነበረው የትጋ ሆኖ ነበር ቅድም የጠቀስካቸውን ነገሮች ሲናገር የትጋ ሆኖ ነበር የሚናገረው?
- ይሄ ምንድን ነው የሚባለው በእናንተ ይቺ መስኪዷ የለችም መስኪዷ ልክ እንደዚህ ከበውት በዚና በዚህ ምንድን ነው የሚባለው እኔ አላውቅም እንደዚህ ፊት ለፊት ነው እሱ በዚህ በጉን በጉን ሰወች አሉ እንትን ላይ አደለም እላይ አልወጣም
- ከመስኪድ ውጪ ነው?
- አረ መስኪዷ ውስጥ ይቺ ምንድን ነው የሚባለው
- ችግር የለም መስኪድ ውስጥ ነው ከመስኪድ ውጭ?
- አደለም ችግር አለው እንትኗ ይሄ
- በሩ ላይ ነው?
- መስኪዷ አለች አሁን የመስኪዷ ፊት ለፊት እንትን አለ ወደላይ ማውጫ
- እኛ አናውቀውም አንተ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ እኔ ያየሁትን ነው እሷጋር ልክ የእንትኖች እንትን አለ
- አሃ ደረጃ ነገር አለ?
- ወደላይ መውጫ አዎ እላይ አይወጣም እንደዚች እንትን ማያ አለት መታያ ማለት ነው በቃ እዛ ላይ ይታያል እሱ ላይ ነው እንትን የሚለው
- ግልጽ ነው
- ግልጽ ስላልሆነ ነው
- የሆነ ደረጃ አለ ነው የሚሉን ከመስኪድ ውስጥ ከዛ ደረጃ ላይ ፊት ለፊት ይታያል ለሰው ነው
- አዎ
- መስኪድ ውስጥ ሆኖ ነው?
- ፊት ለፊት እንደዚህ በሩ ነው
- ቆይ ጥያቄዬን ከመለስክ ቀላል ይሆናል አቡበክር መስኪድ ውስጥ ነበረ ከመስኪድ ውጭ ይሄ ግልጽ ነው ጥያቄው?
- ይኸው ደረጃ አዎ ልክ ነህ ግልጽ ነው ይሄ ደረጃው ተወጣ ትንሽዬ ደረጃ የምትወጣ አለች እዛችጋ እንደሜዳ ነገር ናት
- ደረጃው ወዴት ነው የሚያስወጣው ወደ መስኪድውስጥ ነው?
- መስኪድ አሁን በዚህም ወደላይ ማስወጣ አለው ወደላይ ደግሞ የሚያስወጣ አለ ትልቅ እዚችጋር እንደሜዳ ነገር እምትመስል አለች የመስኪዱ የራሱ
- በረንዳው ማለት ነው የመስኪዱ በረንዳ?
- አዎ እንደሱ ማለት ነው እሷ ላይ ማለት ነው እንደዚህ ፊት ለፊት ይታያል
- እርስዎ የትጋ ነበሩ በዛኔ?
- እኔ መኪኖቹ ወደላይ ማስወጫ ወደ በር ማለት ነው
- ከመስኪዱ ወደ ዋናው ከግቢ መውጫ በር?
- አዎ ወደዛኛውጋ ማለት ነው ?
- አዎ
- ስለዚህ በመስኪዱ እና አሁን በሚሉት በር መካከል አጥር እኮ አለ አደል ?
- እ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አጥር አለ መስኪዱን ከሆስፒታሉ ከክሊኒኪ የሚከፍለው አጥር የለም እንዴ?
- አይ እሱጋ አደለም እሱማ መስኪዱንማ ይከልለዋል
- አሁን ያሉት ደረጃ መውጫውጋ ሰው ከውጭ ከአወልያ ውጭ ሲገባ ወደ መስኪዱ ሲገባ እኮ የሆነ አጥር አለ የሚለየው አጥር አልፎ ነው ወደ ደረጃው የሚያልፈው አደል ?
- አዎ
- ስለዚህ እርስዎ ከአጥሩ ውጭ በሩ አካባቢ ነበሩ?
- አዎ እንደዚህ በዛኛው በኩል መሄጃ ማለት ነው እሱጋ ነበርኩ
- ጥሩ በምን ነበር የሚናገረው በማይክ ነው ያለ ማይክ?
- አረ በማይክ ነው
- ቆመው ነው ቁጭ ብለው?
- ቆመው
- ምን ነበረ የለበሰው?
- አንዴ ሙሉ ሱፍ ጥቁር ነው ያረገው
- ጥሩ አህመዲንስ የትጋ ነበረ የሚናገረው አህመዲን ጀበል ?
- አህመዲን ጀበል እዛው ነው ይሄ እንትን አርጓል እሱ ቀሚስ
- አይ እዛው አሁን ያሉት በረንዳ ላይ ?
- በቃ እዛ ላይ ነው የሚያስተምሩት
- ሁሉም?
- አዎ
- ይሄንን ትምህርት ደጋግመውታል ነው ያሉኝ በጥርም ከዛም በኋላ ባለው ይሄንኑ ነበር የሚያስተምሩት ?
- እንዴት አሁን ይሄን ትምህርት ተደጋግሚል ስልህ ጥር ብቻ ነበሩ ስትለኝ ቅድም ጥር አደለም ከዛን በኋላ ነበሩ ብዬሃለው
- ከዛ በኋላ ያስተምሩ የነበረው አሁን ያለው በረንዳው ላይ ነው?
- በቃ እዛው ላይ ሆነው እነሱ እኮ እንደዚህ በግልጽ በቃ የሚታወቁ ናቸው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቦታው በረንዳው ላይ ነበር እርስዎ ያዩት በሙሉ ጥርም ከዛም በኋላ ያስተምሩ የነበረው ቅድም የገለፁልን የመስኪዱ መግቢያ ደረጃውን ወጥቶ በረንዳው ላይ እዛ ነበር የሚያተምሩት?
- አዎ መስኪድ ውስጥ ሲያስተምሩ አላዩም ?
- መስኪዱ ውስጥ እንዴት አያለሁ አላየሁም
- እሺ ቅድም አሰጋጁ ይመለስ ዘበኞች ይመለሱ አስተማሪዎች ይመለሱ ትምህርት ቤት አረብኛ ት/ቤት ተዘጋብን ወይም መንግስት አዘጋብን ይሄ ነገር ተዘግቶ ነበር እንዴ አሁን ያለት ነገር አስተማሪው ኢማሙ አሰጋጁ ተባረው ነበር?
- ማለትም አሁን በወቅቱ እኔ ስለውስጥ አላውቅም እነሱ ያሉትን ነው የሰማሁት ኮሌጁ እንደተዘጋ አረብኛ ትምህርት እንዳይማሩ እንዳላቸው መጅሊሱ እንደተባረረ አስተማሪዎቹ እንደተቀነሱ ይሄን እራሳቸው ሲያወሩ የሰማሁት ነው እኔ ስለውስጥ መጀመሪያ እንትኑ አላውቅም
- እሺ ምስክር ያው በስራዬ ምክንያት አወልያ እሄዳለሁ ብለህ መስክረሃል ለምን ያህል ጊዜ ነው አወልያ ስትሄድ የነበረው ?
- አወልያ አሁንም እየሄድኩ ነው
- አይ አሁን ሳይሆን ከመቼ ጀመሮ ጥያቄ ከተጀመረ ጀምሮ እስከ አሁን ማለትህ ነው ወይስ ?
- እምሄደው እኔ አወልያ ከመጀመሪያም እሄዳለሁ ፈረንጅ እንትኑ እያለ ማለት ነው
- ስለዚህ እዛ በተደረገው ስብሰባዎች ሁሉ ተሳትፈሃል ማለት ነው ?
- ስብሰባዎች ሁሉ አልተሳተፍኩም
- ስብሰባ ማለቴ እዛ ፕሮግራም ሲኖር አንተ ትኖራለህ ታያለህ ትታዘባለህ ማለት ነው?
- ስብሰባ ፕሮግራም ሲኖር አደለም ችግር አለ ከተባልኩኝ ወይንም እንደዚህ አሁን በማንኛውም ቦታ እውከት ካለ እሄዳለሁ
- እስቲ ምን ያህል ጊዜ ችግር አለ ተብለህ ሄደሃል እሺ?
- አንዴ አስተማሪዎች ደሞዝ አልተሰጠንም ብለው ከዛ በፊት
- መቼ ነው ይሄ የሆነው?
- ከ15 ቀን በፊት ወይ ከወር በፊት ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከዛሬ ነው ወይስ ከየት ?
- ከዛሬ አደለም ከጀመሩበት ቀን 15 ቀን ወይንም ወር ላይ ነው
- አንዴ ከጥር ጀምሮ ነው መሄድ የጀመርኩት ብለሃል ከጥር ወደፊት ነው ወደኋላ ነው አስራአምስት ቀን ?
- እኔ ጥር ጀምሮ ያልኩት እዛ ሁከቷ ስትፈጠር የሰማሁት ነው እዛ እኔ አወልያ ብቻ እኮ አደለም እንትኔ በየቦታው እሄዳለሁ አወልያ አካባቢም ከሆነ እሄዳለሁ ግን ተማሪዎች እራሱ ደሞዝ አልተከፈላቸውም ነበረ
- ተማሪዎች ወይስ አስተማሪዎች ?
- አስተማሪዎች ከመረበሹ በፊት ከዛ በኋላ ሄደን እንደሚስተካከልላቸው እና ይሄ የውስጥ ችግር ነው ተብሎ ያ እንደተፈታ ምናምን አውቃለሁ
- ማን ነው የፈታው?
- ይበቃል ይሄ ጥያቄ
- ስለዚህ አንድ ከ15 ቀን በፊት ያልከው አንድ ይሄንን ሄደሃል
- ቀኑ ያው በተረዳሁት ነው አረብ እያሉም እዛ ነበርኩ ከዛ በኋላም አሁንም አለሁ አጠቃላይ ሁኔታን ከጠየቃችሁ ልነግር እችላለሁ ብለዋል እሳቸው ሲጠይቁ ቅድም እና ስለዛ አካባቢ ጥያቄ በቃ ሌላ ካላችሁ
- እሺ አቡበክር አህመድ እና ካሚል ሸምሱን በቪሲዲ አይተሃቸው ታውቃለህ ?
- በምን?
- በቪሲዲ በተንቀሳቃሽ ምስል አይተሃቸው ታውቃለህ?
- ማለትም እኔ እነሱን የማውቀው
- በተንቀሳቃሽ ምስል አይተሃቸው ታውቃለህ በቪሲዲ በቴሌቪዥን?
- ቆይ እስቲ ተቃውሞ
- የተከበረው ፍ/ቤት ያው ሂደቱን ላለማቆራረጥ ነው እና እኛ አሁን ይሄ ምስክር የአይን ምስክር ነው ሲገልጽ የነበረውም አወልያ ውስጥ የተፈጠረውን ነገር ነው እኛ ስለቪሲዲ አላስመሰከርንም እና በዋና ጥያቄ ያልተነሳ ነው የተከሳሽ ጠበቃ እያነሱ ያሉት እና እንዲታለፍ ነው የማመለክተው
- እሺ ምላሽ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተከበረው ፍ/ቤት በምን መንገድ ምስክሩ ተከሳሾቹን ያውቃቸዋል የሚለው መሰረታዊ የሆነ ጥያቄ ነው መመለስ አለበት መስቀለኛ ጥያቄ እንደመሆኑ መምራት እንችላለን ምስክሩ አደለም ወይም አዎ ማለት መብቱ ነው እና እንድንጠይቅ ይፈቀድልን
- የግራ ቀኙን ተመልክተናል እንግዲህ ጥያቄውን እንደተመለከትነው መስቀለኛ ጥያቄ ነው እና የጥያቄውን መንፈስ የተረዳነው እነዚህን ሰወች በአካል አታውቃቸውም ስለዚህ የምታውቃቸው በቪዲዮ ነው አይነት ጥያቄ ነው የተመለከትነው ተከሳሹ በቪዲዮ አይቷቸው ከሆነ በቪዲዮ ነው የማውቃቸው ይበል ወይ ቀደም ሲል የገለፀውን ማረጋገጥ ከቻለ ያንን ለማረጋገጥ የተጠየቀ ጥያቄ በመሆኑ ይቀጥሉ ብለናል
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር አቡበከርን እና ካሚል ሸምሱን በተንቀሳቃሽ ምስል በቪሲዲ በቴሌቪዥን ወይም በማንኛውም መልኩ አይተሃቸው ታውቃለህ?
- እኔ በአካል ነው ያየኋቸው
- በአካል የት አየሃቸው?
- አወልያ
- አወልያ መስኪድ ውስጥ አደለም አደል ?
- ቅድም ተናግሬያለሁ
- እሱ ተጠይቋል
- እሺ እንዴት አወቅካቸው አወልያ ?
- እስቲ ጥያቄው ምንድን ነው
- አወልያ ውስጥ አውቃቸዋለሁ ነው ያልከው ከዛ በፊት ከአወልያ ውጪ ታውቃቸዋለህ?
- አላውቃቸውም
- መስኪድ ውስጥ ገብተህም አላየሃቸውም እነሱ እነዚህ ሰወች ካሚል ሸምሱ ይሁን አቡበከር አህመድ ይሁን በምን ልታውቅ ትችላለህ?
- እራሱ እኔ ካሚል ሸምሱ ነኝ ዛሬ የማስተምረው ብሎ ካሚል ሻምሱ አሁን እኮ አሳይቻቸዋለሁ እነሱ ካልሆኑ በቃ እኔ ተሳስቻለሁ ማለት ነው
- እሺ ያው እንደምታውቃቸው አስረድተህልናል እነዚህ ተናገሩ የሰማኸው ሰወች ጥያቄያቸው ሰላማዊ ስለመሆኑ እና ጥያቄያቸውንም ለመጠየቅ እየቀረቡ ስለመሆኑ የተናገሩት የሰማኸው ነገር አለ ?

1868 299

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እ?
- ጥያቄያቸውን በሰላማዊ መንገድ እያቀረቡ እንደሆኑ ሲናገሩ የሰማኸው ነገር አለ?
- እ?
- ጥያቄያችን ምንድን ነው አሉ?
- በቃ ጥያቄያችን አሁን ቅድም እኮ እንዳልኩት
- ቆይ ቆይ ጥያቄያቸው ጠበቃው እየጠየቁ ያለው እሚጠይቁት ጥያቄ ሰላማዊ አደለም ወይ?
- ማለትም በቃ እኔ ሲጠይቁ የነበረው ማለት ነው በወቅቱ ሲመልስ የሰማሁት መንግስት ሲያስረንም ቢያስፈራራንም ይሄን ነው ያልኩት በቃ እኔ
- ከሚናገሩት ሰወች ውስጥ ፖሊስ የህዝብ አገልጋይ ነው ፖሊስ የሕዝብ ጠባቂ ነው ስለዚህ ከፖሊስጋር ምንም አይነት ችግር መፈጠር የለበትም የሚል ነገር አልሰማህም ከሚተላለፉ መልክቶች ውስጥ ማለት ነው?
- አሁን ፖሊስ እዛ ውስጥ አይገባም
- አይ ይገባል አይገባም ሳይሆን የሕዝብ ጠባቂ ነው ከውጭም ቢሆን እየጠበቀ ሊሆን ይችላል ነውም ደግሞ አንተም ተናግረሃል ስለዚህ ከፖሊስጋር ምንም አይነት ግጭት መፈጠር የለበትም ጥያቄያችን ሰላማዊነው ፖሊስ የሕዝብ አገልጋይ ነው የሚል ነገር አልሰማህም?
- አሁን እዛ ላይ ስለዚህ አደለም
- ይሄን ሰምተሃል አልሰማህም?
- አልሰማሁም
- በቃ ሌላ ጥያቄ
- መጅሊሱ አይወክለንም እያሉ ነበር ብለሃል ተማሪዎቹ አደል ?
- አዎ
- ማንኛውም ተማሪ ወደ ውጭ እንዳይወጣ ሲል ነበር ስትል እረብሻ እንዳይፈጠር ማለት ነው ሙባረክ ማንኛውም ተማሪ ወደ ውጭ እንዳይወጣ እዚህ ሆነን ጥያቄያችንን እናቀርባለን ሲል ነበር ብለሃል እና እረብሻ እንዳይፈጠር ማለት ነው?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የሱ እንደራሱ ነው እኔ አላውቅም እረብሻ ይፈጠር አይፈጠር በሱ አደለም እሱ እንትን ያለው
- ለምንድን ነው እንዳትወጡ ያለው ለምንድን ነው እሱን መልስ
- ማንም ሰው መውጣት የለበትም እዚሁ ጮኽን ድምፃችንን ማሰማት አለብን ነው ያለው በወቅቱ አሁን ለምን እንደሆነ አላውቅም
- እሺ ሙባረክ አርብ አርብ ነው ንግግር የሚያረገው ሌሎች በሌላ ቀን ይናገራሉ ብለሃል ሙባረክ በሌለበት ቀን የሚያስተባብሩ ሰወች ነበሩ ማለት ነው የሚናገሩ ሰወች ?
- የሱ አሁን ጓደኞች አሉ
- እሱ በሌለበት የሚያስተባብሩ ሰወች ነበሩ ማለት ነው ?
- አሉ የሱ እኩዮች ማለትም እንደዚህ በመልክ አውቃቸዋለሁ በስም አላውቃቸውም እንደዚህ ቢመጡ እኔ እንዳለ አውቃቸዋለሁ
- ሌላ ጥያቄ
- አቡበክር ሲመጣ ሞራሉ ሌላ ነው አህመዲን ጀበል ሲመጣ በጣም ይጮሀል ሕዝቡ ድጋፉን ያሰማል እሚቃወም ነበር እንዴ ከዚህ በተቃራኒ ?
- አይ እኔ ስለሚቃወም ስለማይቃወም ሳይሆን በወቅቱ
- ያየኸው ድጋፉን የሚሰጥ ሰው ብቻ ነው?
- እንዳለ አላህዋክበር ሲሉ
- እኮ የድጋፍ ነው የተቃውሞ ነው በአንተ ባየኸው?
- እኔ እንጃ እኔ አላውቅም እኔ ሲሉ ነው እንጂ ድጋፍ ይሁን ተቃውሞ ይሁን አላውቅም
- እሺ አላህዋክበር እያሉ ሕዝቡ እንደዚህ አይነት ምላሽ ሲሰጥ የነበረው የሚናገሩት ነገር እያሳመናቸው ስለነበረ ነው ማለት ነው?
- እሱ ግልጽ ነው
- እሺ አሸባሪ እንዳልሆንን እናሳያቸዋለን ብለዋል ብለዋል በሰላማዊ መንገድ ጥያቄያችንን እናቀርባለን ማለታቸው ነው?
- እኔ እሱን አላውቅም
- እሺ ምን ማለት ነው አሸባሪ እንዳልሆንን እናሳያቸዋለን ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?
- እኔ እንጃ ያሉትን ነው የሰማሁት እንጂ ምን ማለታቸው እንደሆነ አላወቅኩም

301

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አንቱ ምንድን ነው የተረዳኸው በዚህ ነገር ?
- እኔ ምንም አልተረዳሁም
- ሙባረክ አደባባይ ሆኖ ይናገር ነበር ብለዋል ድምፁ በደምብ ይሰማ ነበር?
- እንዴ የሙባረክ አንደኛ በቃ በጣም ነው የሚሰማው እንደውም
- እሺ ይበቃል
- ያለ ማይክራፎን ነበር የሚናገረው ማለት ነው ማይክራፎን አያስፈልገውም ስላሉ
- ተጠይቋል በቃ
- እሺ የመጅሊስ ሰው ይመስለኛል ያሉት ሰው መኪና ምን አይነት መኪና እንደሆነ አላውቅም ብለዋል ግን ቢያንስ ጉማው መተንፈሱን ስላዩመኪናው ትልቅ ነው ትንሽ ነው የጭነት መኪና ነው የቤት መኪና ነው ይቺን እስቲ መልሱ?
- የቤት መኪና ናት
- ትልቅ ነው ትንሽ?
- አረ ትንሽ ነው ማለትም ስሙን ስለማላውቀው እንጂ እኮ
- ያው የቤት መኪና ከተባለ
- ሙባረክ ንግግር ሲያደርግ አቡበከር እና ካሚል ሸምሱ በቦታው አልነበሩም አደል አውቃቸዋለሁ ስላል ሙባረክ ንግግር ሲያደርግ አቡበከር እና ካሚል ሸምሱ በቦታው አልነበሩም አደል?
- ሙባረክ ንግግር ሲያደርግ
- እነሱ አልነበሩም?
- ሙባረክ እዛ አለ ማለትም በወቅቱ ማለት ነው አሁን ሙባረክ የሌለ ጊዜ ይነገራል መድረኩ ላይ እራሱ
- አደለም አሁን እኔ እየጠየቅኩ ያለሁት መስኪድ ውስጥ ሰወች ተሰብስበው ንግግር ማረግ ከመጀመራቸው በፊት ጽ/ቤቱ በረንዳ ላይ ንግግር ያደርጉ ነበር እነሙባረክ ብለሃል እና እዛ ለተማሪዎች ንግግር በሚያደርግ ጊዜ ሙባረክ አቡበከር ወይም ካሚል አልነበሩም አደለል በቦታው?
- እነሱ የሉም
- መቼ መጡ እነሱ ወደ አወልያ መምጣት መቼ ጀመሩ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- መምጣት የጀመሩት እኔ የማውቀው ማለት ነው ከጥር ጀምሮ እሱ ሲናገር ያሉት ተማሪዎች ነው ሙባረክ ሲናገር ማለት ነው እነ አቡበከር ሲናገሩ ጁምአ ላይ ነው የሚመጡት በዛ ሰዓት ነው በቃ እነሱ አስተምረው የሚሄዱት እንደውም አንዳንዴ ከግቢው ሁሉ አይወጡም
- አይ ቅድም አሁን ስትነግረን ሙባረክ ጁምአ ጁምአ ንግግር ያደርጋል
- በቃ በቃ ይሄ ተመልሷል ሌላ ጥያቄ
- በወቅቱ አንተ እነዚህ አሁን ጥያቄዎች ተጠይቀው ሰው ተሰብስቦ ወደቤቱ ሲመለስ በሰላማዊ መንገድ ነው አደለ ወደቤቱ በሰላማዊ ሁኔታ ምንም ችግር ሳይፈጠር ነው አደለም ወደቤቱ ይመለስ የነበረው?
- ውጪ ሲወጡ
- እ?
- አሻምኑሪእስቃጠል እያሉ ማለት ነው
- ከዚህ ውጪ ሌላ ምንም ችግር የለውም ወደየመጡበት ይመለሳሉ ሰላቱ የተደረገው ፕሮግራም ካለቀ በኋላ?
- አዎ እንደውም አንዴ ካሚል ውስጥ ሆኖ የውሽት እንትን ታሰርኩ ብሎ አውርቷል መሰለኝ ካሚል ታሰርኩ ብሎ የመጮህ ነበረ
- አቶ ሰይፈ አወልያን ለረጅም ጊዜ ስለሚያውቁት ስንት የግቢ መግቢያ በር አለው ዞረው አይተውታል?
- አዎ
- አንድ በር ነው ያለው ወይስ ከዛ በላይ ነው?
- ማለትም ትላልቅ ቢሮች 3 አሉት
- ጥሩ ሙባረክ ቅድም በሩን ይዘጋል ሲሉ የበሩን ብረቱን ይዘጋል ነው ወይስ በእጁ ይከላከላል?
- ሁለቱ በር ይዘጋል ይቆለፋል ትላልቆቹ በር በግራና በቀኝ ያሉት ማለት ነው በቁልፍ ያቆለፋሉ
- ማን ነው የሚቆልፋቸው?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለጥበቃዎች ይነግራል እሱ ይቆለፋል ሰው እንዲወጣ እሚደረገው በዚህ በዋና በር ነው በሱጋ ነው እሱጋ መጥቶ ትእዛዝ ብቻ ነው የሚሰጠው በቃ
- ለጥበቃዎች ?
- አዎ ወይንም እራሱ ማንም ሰው እንዳይወጣ ይላል በቃ ትእዛዝ ነው
- አሃ እንጂ በሩ እይዘጋም ትእዛዝ ሲሰጥ ሰው ይቆማል ?
- በቃ በሩ ይዘጋል እራሱ መጥቶ ይዘጋዋል በቁጣ ነው ሁሉ ነገሩ ሙባረክ ማለት ነው ለሰው እንትንም የለው ፖሊስም ከበሩ ላይ ወደዛ ሂዱልን ብሎ እንትን የማለት
- በቃ ግልጽ ነው ሌላ ጥያቄ
- እሺ ምስክር አቶ ካሚል ሸምሱ አስረው ወደ ደህንነት ቢሮ እንዲያቀርቡ ማን ነበር ያዘዞት ይሄ ፕሮግራም በሚደረግበት መሃል እርስዎ አስረዋቸው ወደ ፖሊስ ወይም ደህንነት ቢሮ አቅረበዋቸው ነበረ ማን ነበረ ያዘዞት ይሄንን እንዲያደርጉ?
- ተቃውሞ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ጥያቄው ግልጽ አደለም መጀመሪያ ጥያቄው ግልጽ ይሁን እና ተቃውሞውን ታቀርባላችሁ
- ማን ነበረ ትእዛዝ የሰጦት አስረው እንዲያቀርቡ ወደ ፖሊስ ጣቢያ አቶ ካሚልን
- እስቲ ቆይ አሁን ጥያቄው ምንድን ነው ተገደዋል ለማለት ነው እንደዛ ከሆነ
- ያው ታስረው ነበር አልነበረም የሚለውን
- ማን ናቸው የታሰሩት?
- የሚመሰክርባቸው አንድ
- ካሚል ሸምሱ
- ካሚል ሸምሱ
- አስረው እንዲያቀርቡ ማን ትእዛዝ ሰጠ ነው?
- ማን ትእዛዝ ሰጠ እርስዎ አላሰሩም ወይ ነው ጥያቄው
- ማ እሳቸው ናቸው ያሰሩት?
- አዎ እሳቸው በቁጥጥር ስር አውለው አላቀረቡም
- እሺ ቀጥሉ ከዚህ ተቃውሞ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተከበረው ፍ/ቤት ያው ይሄን ምስክር ስናቀርበው ጭብጥም ሲያዝ ቅድም እንደገለጽነው አወልያ ውስጥ ምስክሩ በተደጋጋሚ ተገኝቶ ተፈጠረ ያለውን እና ያየነውን ነው የተናገረው የሙያ ምስክር አደለም ወይም በስራው አጋጣሚ ስላከናወናቸው ነገሮች የሚገልጽ ምስክር አደለም ስለዚህ ምስክሩ ባልመሰከረው በዋና ጥይቄ ባልተነሳ እና በጣም ግላዊ የሆነ ከጭብጥም ውጪ የሆነ ጥያቄ ነው እየጠየቀ ያለው እኛ ስለ ካሚል መታሰር አለመታሰር እኔ የማውቀው ነገር የለም የማውቀው የውሸት ታሰርኩ ብሎ ውጪ እረብሻ ሲፈጠር ነው ብሎ ምስክሩ መስክሯል እና አግባብነት ያለው ጥያቄ ስላልሆነ እንዲታለፍ ነው የምናመለክተው
- ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት የተከበሩ አቃቤ ሕግ በጥያቄያቸው ከምስክሩጋር ተቃርነዋል ምክንያቱም ምስክሩ በሙያዬ ወይም በስራዬ ምክንያት ነው ወደ አወልያ የምሄደው ብለው መስክረዋል ይሄ ግልጽ ነው ምንም በግልጽ የተነገረ ነው በችሎት እና አንዱ ይሄ ነው 2ኛ አቶ ካሚል ስለመታሰራቸው በተመለከተ ምስክሩ ተናግረዋል እኛ ከየትም ያመጣነው አደለም ከምስክሩ ቃል የተያዘ ነው እና የእስራቸውን ሁኔታ በተመለከተ ጥያቄ መጠየቃቸው የሚያስነቅፍበት ምንም ምክንያት የለም ጥያቄያችን እንዲቀጥል የተከበረውን ፍ/ቤት እንጠይቃለን
- እሺ ብይን ሰጥተናል አሁን መጨረሻ ላይ የተነሳው ጥያቄ ምስክሩን ካሚል ሸምሱን እርስዎ አስረው ለደህንነት አቅርበው አልነበረም ወይ ማን ነው ትእዛዝ የሰጠው የሚል ጥያቄ ነው የተነሳው በጥያቄው ላይ የተነሳው ተቃውሞ አንደኛው ምስክሩ የሙያ ምስክር አደሉም በዋና ጥያቄ ያልተነሳ ነው የውሸት ታሰርኩ ብሎ እረብሻ ማስነሳቱን ነው ምስክሩ የመሰከረው የሚል ተቃውሞ በአቃቤ ሕግ በኩል ተነስቷል የተሰጠው መልስ ምስክሩ በሙያዬ መሰረት ወደዛ ሄጃለሁ ብሏል ስለዚህ ተናግሯል ሌላው የተነሳውን ጥያቄ ለማጣራት ነው የሚል ምላሽ ቀርቧል ፍ/ቤቱ ጥያቄው ተገቢ ነው ወይስ አደለም የሚለውን መርምሯል ጥያቄው ተነስቷል አልተነሳም የሚለውን በተመለከተ ያው ጥያቄው በዋና ጥያቄ ተነስቷል ምን ተብሎ ነው የተነሳው ብንታሰርም ቢያስፈራሩንም አንፈራም የሚል ነገር በዋና ጥያቄ ተመስክሯል ያው ካሚል ሸምሱ ከነዛ ውስጥ ስለሆነ ተነስቷል ለመነሳት አልተነሳም የሚለው ማለት ነው የሙያ ምስክር አደለም ምስክሩ የሚለው ፍ/ቤቱ በሙያ ምስክርነት አልጠራም ተከሳሽን አሰቃይልጽ

ECHN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ነው ሙያቸው ምን ይሁን ምን ፍ/ቤቱ በሙያ ምስክርነት አልጠራም ምስክሩን በዋና ጥያቄ አልተነሳም የሚለውም ተነስቷል የውሸት ታሰርኩ ብሎ መልሷል የሚለው ነገር ተመልሷል ነገር ግን ፍ/ቤቱ በጠበቃ በኩል የተነሳውም በአቃቤ ሕግ በኩል የተነሳውም ሳይሆን ምስክሩን አስረህ ለደህንነት አቅርበሃል ወይስ አላቀረብክም የሚለው የምስክሩን ሥራ በግልጽ ማጋለጥ ነው ይሄ ደግሞ በችሎት ለምስክርነት የተሰጠውን የምስክር ደህንነት የሚያጣርስ ስለሆነ ምስክሩ ይሄንን ጥያቄ መመለስ የለባቸውም ተብሎ ብይን ተሰጥቷል ሌላ ጥያቄ ካላችሁ

- አቶ ሰይፈ ቅድም አቡበክር አህመድ እኛ መንግስት አያስፈራራንም ከመናገር ወደኋላ አንልም ሲል እንደነበረ ሰምተዋል ትክክል ነው?
- አዎ
- ከዛ ትግላችን መቀጠል አለብን እንዳለ ነግረውናል በየሳምንቱ አርብ አርብ ይመጡ እንደነበረም ነግረውናል ስለዚህ ትግለችን ይቀጥል ማለት እርስዎ የተረዱት በየሳምንቱ በዚሁ መልክ እየመጣን መጮሃችንን መናገራችንን እንቀጥላለን ማለታቸው አደለም እንዴ?
- እኔ እሱን ምን ማለታቸው እንደሆነ አላውቅም
- በእርስዎ አረዳድ እንዴት ተረዱት ትግላችን ይቀጥላል ቅድም ከሰጡን ምስክርነት ተነስተው አንፈራም ትግላችን ይቀጣላል በየሳምንቱ ይመላለሳሉ
- ተመልሷል ጠበቃ እኔ አላውቅም ብለው መልሰዋል
- ቅድም ከመቶ ሺ በላይ ነን ብለዋል ነው ወይስ ነበረ ነው ያሉት?
- አሁን ያለነው በዚህ ሰዓት ከመቶ ሺ በላይ ሕዝብ ነን ማለትም ሙስሊሙን ማለት ነው እዛ ያለው ሙስሊሙን ነው ከመቶ ሺ ሰው በላይ ነን ብሎ እራሱ እዛው መድረክ ላይ ነው የተናገረው
- ጥሩ ሰው ይሰበሰብ የነበረው ሰው መገመት ይችላሉ እርስዎ?
- እኔ አልችልም
- እሺ ግቢው ይሞላ ነበር መስኪዱ ይሞላ ነበረ ከግቢው ውጪስ ሰው ነበረ?
- በወቅቱ
- እርስዎ ባዩት እርስዎ እስከመጨረሻው ስለነበሩ ነው?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በወቅቱ ውጪም መስኪድ ውስጥም ሞልቶ ማለት ነው ያው እንትኑ ላይ ብቻ እንትን እንደማይባል አውቃለሁ ይሄ ሜዳ አለ ውስጥ እሱ አፈር ስለሆነ እሱ ላይ እንትን አይባልም በተረፈ ውጪው ሁሉ ማለት ነው
- ከግቢው ውጭ?
- አዎ ከግቢው ውጭ ሁሉ አስፋልቱ በሙሉ እዛ ድረስ እንደሚደረግ አውቃለሁ
- ይሄንን እነአቡበክር ሲናገሩ ሕዝቡ ቁጭ ብሎ ነው አደለም የሚያዳምጠው?
- ሲናገሩ?
- ሲናገሩ ቆመው ነው በቃ ሰላት እንትን ይባላል መጀመሪያ ትምርት አለ እነሱ የሚያስተምሩት ትምህርት እነአቡበክር ማለትነው እነሱ ካስተማሩ በኋላ መጨረሻ ላይ ይሄ የጁምአው መዝጊያ ፀጥ ተብሎ ይሰገዳል እሱጋ ይሰገድ እና ከዛ በኋላ ይነሳሉ ትምህርቱ በዛው ይቀጥላል
- የነአቡበክር ትምህርት ከጁምአ ሰላት በኋላ ነው?
- ሌላ ነው በቃ የሚያስተምረው እንደ እንትን ነገር ነው እንደምንድን ነው ይሄ አሁን አሻም ኑሪ እያለ በእንትኑ ላይ ሲል እነሱም እያሉ ይወጣሉ ከእንትኑ በኋላ ማለት ነው
- ሁለት ጊዜ ነው የሚያስተምሩት ማለት ነው እነአቡበክር ከጁምአ ሰላት በፊት እና ወይ ከአርብ ስግደት ከፀሎት በፊት እና በኋላ?
- አደለም ልክ ከመጀመሩ በፊት ማለት ነው ይሄ አሁን የሚሰግዱበት ከመጀመሩ በፊት ያስተምራል ልክ እሱ ሲደርስ ይሰገዳል ከዛ በኋላ በቃ ይነሳሉ እንትን ነው የሚያስሙት አላህዋክበር ይሄ ቅድም ያልኩት አሻም ኑሪ እያሉ ይወጣ በቃ መጀመሪያ ነው እሱ የሚያስተምረው ማናቸውም
- ከስግደት በፊት ምንድን ነው የሚያስተምሩት?
- ቅድም የተናገርኩትን ነው ያስተምራሉ ያልኩት
- በየአንዳንዱ ላይ የመሰከሩትን?
- አዎ የተናገርኩትን
- ከስግደት በኋላስ?
- ከስግደት በኋላ በማይክ ይሄ አሻም ኑሪ ይስቃጠል እያሉ እንደ እንትን ነው ሁሉም እሱን አንዳንዴ ይያያዛሉ እጅ ለእጅ ተያይዘው እያሉ ይሄዳሉ እንደዚህ እንደዚህ እያሉ እጅ የማውለብለብ ምናምን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወደቤታቸው ማለት ነው?
- አም በቃ እንደዛ እያሉ ነው የሚሄዱት ከእንትኗ በኋላ ማለት ነው
- እየደጋገሙ ነው ጥያቄ
- እሺ የተከበረው ቤት ጨርሰናል
- አቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ ካላችሁ
- ቅድም ሙባረክ ከመጅሊስ ተወክለው የመጡትን ግለሰብ እሳቸው እየተናገሩ እያለ ያው ማይኩን ቀምቷቸው እውነቱን ተናገር ሲላቸው እንደነበረ ያው ገልፀሃል እና በተደጋጋሚ በኃይል ማለት ነው በወቅቱ ሙባረክ እውነቱን ይህ ነው ብሎ እንዲናገሩ ወይም እውነቱን ይህ ነው ብሎ የተናገረው ነገር ካለ ታስታውሳለህ እሳቸው እውነቱን ተናገር ብሎ ሲላቸው ምንድን ነው እውነቱ ብለው ወይም እሱ እሳቸው እንዲናገሩለት የፈለገው በወቅቱ የተናገረውን ታስታውሳለህ ሙባረክ?
- ማለትም እሳቸው በወቅቱ መልስ ሲሰጡ ማለት ነው ጥያቄያችሁን በአግባቡ አድርጐት ብለው ልክ ሲመልሱ ማለት ነው እና እንትኑ ኮሌጁ ይከፈታል ነበረ ያሉት ገና ሲጀምሩ እሱን እሱን አደለም ብሎ እሱ ማለት ነው ቀማቸው እና እሱን እሱን አደለም ግልጽ ግልፁን በቃ እየተቆጣቸው እንትን ሲል ሰውየው ዝም አሉ በቃ በወቅቱ ማለት ነው ከዛ በኋላ እዚጋር ከእሳቸው ጐን አብረው የመጡ አሉ ትላልቅ ሰወች እነሱም ይናገር ግልጽ ግልጽ ምናምን ብሎ እንትን ሲላቸው ማለት ነው
- እሺ እንግዲህ ይሄ ከሆነ አሁን ቅድም እንደገለጽከው ማለት ነው እነአህመዲን ጀበል የጠቀስካቸው እነአቡከር ከሚል እሱን ጨምሮ አራቱም ሰወች በተደጋጋሚ ጊዜ ያው እዛ ይመጣሉ ቅድም እንደገለጽከው አወልያ እንግዲህ አነሳሱ ተማሪዎቹን ሲሉ የነበረው እና የመጅሊስ ተወካሉ ሊመልሱ የፈለጉትን አቡበከር አለመቀበሉን ገልፀሃል እና እነኚህ እነአቡበከር በየሳምንቱ እየመጡ አሁን ቅድም ያልካቸውን ትግላችንን እንቀጥላለን ምላሽ ይሰጠን ቅድም ያልካቸው የለያዩ ቃላቶችን በተለያየ ጊዜ ሲገልፁ እንደነበረ ገልፀሃል እና ምንድን ነው አሁን ዋናው አንተ ስትረዳው አስተያየት ሳይሆን ከዚጋር በተያያዘ እንኚህ ሰወች ይሄ ጥያቄ ሲነሳ ት/ቤት ይከፈታል ተብሏል ያነሱት ጥያቄ መፍትሄ እንደሚያገኝ ተነግሯቸዋል ቅድም እንደገለጽከው ማለት ነው ይሄ ከሆነ እነኚህ ሰወች ምንድን ነው አላማቸው አላማችን ይሄ ነው ብለው የገለፁበትን ሁኔታ ታስታውሳለህ ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ተቃውሞ
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄ ጥያቄ በዋና ጥያቄ ላይ አልተነሳም እኛም በመስቀለኛ ላይ ምንም ጥያቄ አላነሳንበትም በዋና ጥያቄ ያላነሱትን ነገር አሁን የድጋሚ ጥያቄን እድል ተጠቅመው አቃቤ ሕግ እያነሱት ስለሆነ ሊጠየቅ አይገባም ያለአግባብ ነው እዚህ
- እሺ ምላሽ ይስጡበት
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እናመሰግናለን ይሄማ በዋና ጥያቄም ቅድም እኮ ተጠይቋል በዋና ጥያቄ ቅድም ሲጠየቅ ከሙባረክጋ በተያያዘ የመጅሊስ ተወካይ
- አይ ዋና ጥያቄ ሳይሆን ዋናው በመስቀለኛ ጥያቄ ተነስቷል ወይ ነው
- በመስቀለኛ እኮ ተናገሩ እኮ አሁን አሁን መነሻዬ ምንድን ነው ይሄ ጠየቅኩት አሁን ስጠይቀው መልስ ሰጠኝ ለዚህ መነሻ ቅድም በድጋሚ ስጠይቀው እኚህ ሰውዬ የመጅሊስ ተወካይ ማለት ነው በአጭሩ መልሴ ምን እንደሚሆን ገልፀውታል ይሄ ከገለፁ የነኚህ ሰወች አመጣጥ የነሙባረክ አመጣጥ እዚህ ቦታ ላይ በየሳምንቱ መጥቶ ይሄን መልእክት ማስተላለፍ አላማው ምን ነበረ ነው ይሄን ታስታውሳለህ ወይ ነው ጥያቄው ስለዚህ በዋናም አሁንም ቅድምም በተደጋጋሚ የተገለፀ ጉዳይ ነው
- ብይን ሰጥተናል የነሙባረክ አላማቸው ምንድን ነው ት/ቤት ይከፈታል ሌላም ሌላም እየተባለ አላማቸው ምንድን ነው የሚል ጥያቄ ተነስቷል ይሄ ጥያቄ በዋናም በመስቀለኛም አልተነሳም የሚል ተቃውሞ ተነስቷል በአቃቤ ሕግ በኩል ተነስቷል የሚል አንስቷል በዋና ጥያቄ ተነስቷል አልተነሳም የሚለውን ፍ/ቤቱ መመርመር አስፈላጊ አደለም መጀመሪያውም በዋና ጥያቄ ባይነሳ በዚህ በመስቀለኛ ስለማይነሳ ማለት ነው በዋና ጥያቄ ያው በግልጽ ተጠይቋል ጥያቄው አላማቸው ምንድን ነው ተብሏል ስለ አላማቸው ምስክሩ የመሰለውን መልሷል በዋና ጥያቄ ማለት ነው በአሁን ኢሹ ሆኖ እኛ መመርመር ያለብን በመስቀለኛ ጥያቄ ይሄ ተነስቷል አልተነሳም ነው በመስቀለኛ ጥያቄ ካልተነሳ ድጋሚ ላይ መነሳት ስለሌለበት ማለት ነው በመስቀለኛ ጥያቄ ተጠይቆ ተደጋግሞ የተጠየቀ ነገር አለ እሱም ምንድን ነው ሙባረክ ሌሎች ቀኖችን ያስተባብራል ተማሪዎችን አርብ አርብ ጁምአ ቀን ደግሞ እነአቡበከር መጥተው ያስተምራሉ ሲያስተምሩም ሰወቹ ወደቤታቸው ሲገቡ እንደመፈክር አይነት ሲያሰሙ እሚገቡ አለ ብሎ መልሷል አርብ አርብ ይመጣሉ ሌላ ቀን አቶ ሙባረክ አለ እዛ ተብሏል አሁን እነኚህ ሰወች አርብ አርብ መምጣታቸው ይው እዚህ ላይ ጥያቄው

http://ethcriminalawnetwork.com/

ተነስቷል አርብ አርብ ለምን አላማ መጡ የሚለው ከዚህ የወጣ አደለም ከዚጋ የሚያያዝ ነው ማለት ነው አርብ አርብ መምጣታቸው ይሄን ይሄን ማድረጋቸው በመስቀለኛ ተነስቷል አላማቸው የሚለው የዛ ኤክስቴንሽን ስለሆነ አዲስ አደለም ጥያቄው ተገቢ ነው ይቀጥል ብለን ብይን ሰጥተናል

- የተከበረው ፍ/ቤት አመሰግናለሁ ይሄ አሁን ከተከበረው ፍ/ቤት እንደተገለፀው ስምተሃል እና እነዚህ ሰወች ከአርብ በስተቀር ሙባረክ መድረኩን የመራል እነሱ ደግሞ አርብ አርብ ይመጣሉ ብለሃል እና በአጠቃላይ ያለው ሁኔታ ከአንተ ከምታስታውሰው ምንድን ነው ተልኳችን ወይም አላማችን እንዲህ ነው ብለው የገለፁት ካለ ማስታወስ ትችላለህ ወይ ነው ?
- እኔ በወቅቱ መልሱን እንመልሳለን አሁን እኔ የአላማቸው አካሄድ አላወቅኩም በእርግጥ
- ቀጥሉ ሌላ ጥያቄ
- ምስክር ቅድም ስትገልጽ ሙባረክ እኔንም አያስገባኝም በሮቹንም ይዘጋል እሚወጣውንና እሚገባውንም ሰው በተለይ በር ላይ የነበሩ ፖሊሶችንም ይገፈትራል ስትል ነበር ?
- አዎ
- ተቋሙ ዘበኛ የለውም እንዴ?
- ዘበኛ አለው
- ለምን ታዲያ ይሄን ስራ ሙባረክ ይሰራዋል?
- ዘበኞቹ እሱን ነው እንትን የሚሉት ማለትም በቃ ነው እንደ እንትን ነው ፓወር ነው እንትን የሚለው ዘበኞቹ አይመለከታቸውም በሩን መጥቶ የሚዘጋው እሱ ነው
- ማን ነው አይመለከታችሁም ያላችሁ?
- ማለትም እኔ ለምን እንደማይመለከታቸው አላውቅም እኛ እዛጋ ሲገፈትር እራሱ ሲዘጋ ማንም ሰው እንዳይወጣ ሲል ነው የማውቀው በወቅቱ ማለት ነው
- ጥሩ ቅድም በተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ላይ የተሰበሰበው ሰው ወደቤቱ የሚመለሰው በሰላም ነው ወይ ተብለህ ስትጠየቅ መልሰሃል አንተ ቅድም ከገለጽካቸው ከፈነዳው ከተነፈሰው ጮማ ከተቀማው ማይክ ውጪ አወልያ ውስጥ የደረሰ ሌላ ጉዳት የለም እንዴ?
- እሺ ቀጥሉ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄም በግልጽ በመስቀለኛ ጥያቄ ያልተነሳ ነው ስንከራከርበት የነበረው ነጥብ በመጅሊሱ ሰው መኪና ጐማ ተነፈሰ ነው ከዚህ ውጪ ያለ ነገር በመስቀለኛ አልተነሳም እና አሁንም ዋና ጥያቄ ነው እንደገና በድጋሚ ጥያቄ ላይ እየተነሳ ያለው ሊጠየቅ አይገባም ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ አቃቤ ሕግ ምላሽ ይስጡበት
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እሳቸው ናቸው ጥይቄውን ደጋግመው ሲያነሱ የነበረው በመስቀለኛ ጥያቄ ጥያቄው ሲነሳ ነበር ጥያቄው የተነሳበት አግባብም ህዝቡ ምንም ችግር ሳያደርስ በሰላም ነበረ ወይ ወደቤት የሚሄደው ብለው ደጋግመው ሲጠይቁ ነበር ምስክሩም አዎ አሻቱሪ እያለ የጠቀሳቸው አላህዋክበር ምናምን ይሉ ነበር ብሎ አስረድቷል ይሄንን መስቀለኛ ጥያቄ ላይ ደጋግመው ሲያነሱ ነበረ እና ይሄንኑ ለማስተባበል በድጋሚ ጥያቄ ያነሳነው ስለሆነ አግባብነት ያለው መቃወሚያ አደለም
- እሺ ብይን ሰጥተናል ምንድን ነው ጥያቄው ቀደም ብሎ ተነስቷል በጠበቆቹ ሰው እንዴት እንደወጣ ለተባለው ሰላም እንደሆነ ምስክሩ በዚህ አካባቢ ሲመልሱ ነው የነበረው አቃቤ ሕግም ይሄን መሰረት አርገው ያነሱ በመሆኑ ጥያቄው ከዚህ የወጣ አደለም የሚል ብይን ሰጥተናል አቃቤ ሕግ ይቀጥሉ
- ምስክር ሌላ የደረሰ ጉዳት የለም ወይ አሁን ከጠቀስካቸው ውጪ?
- አንዴ ካሚል ሸምሱ ታሰረ ፖሊሶች ወሰዱት በሚል ውጪ ከፖሊሶችጋር ግብግብ ፖሊስ የመገፍተር የዛ ጣቢያዎች አሉ እነሱን ገፍትሮ እንትን ድረስ የመሄድ ወረዳ 15 ቀበሌዋ አለች በሷ አልፈው ሁሉ በቃ ማንም ሊያስቆማቸው አልቻለም አላህዋክብር እያሉ አስፋልቱን መሄድ ከዛ በኋላ ፌደራል መጣባቸው እነሱ ላይ ማለት ነው ፌደራል መጥቶ ከዛ እንዳይሄዱ
- ቆይ እስቲ ጥያቄው ሰው በሚወጣበት ጊዜ የደረሰ ጉዳት ወይም በአካል ላይ ወይም በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት ነው አቃቤ ሕግ እየጠየቁ ያሉት
- አወልያ ውስጥ የደረሰ ጉዳት እምታውቀው ነገር አለ አንተ ቅድም ከጠቀስክልን ጐማ ተነፈሰ ሌሎች ሌሎች ከጠቀስካቸው ውጪ አወልያ ውስጥ የደረሰ ጉዳት አለ በዚህ ምክንያት ?
- በቃ አስተማሪውን እንትን ሲሉት ነው ይሄ አሁን ተወክሎ የመጣው
- ጉዳት ነው እንዴ እሱ ጉዳት የደረሰ ጉዳት አለ ወይ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የደረሰ ጉዳት ምንም ነገር የለም
- አበቃን ድጋሚ
- የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ
- እስቲ የመጅሊስ ተወካዩ አራት ጉማ የሙባረክ ጓደኞች አፈንድተዋል ብለው ነበረ ቅድም እና ጉማው ሲፈነዳ የሙባረክ ተሳትፎ ነበር ሄዶ ጉማው ሲፈነዳ እዛ ውስጥ ተሳትፎ ከሆነ እሱን የምታውቀው ነገር ካለ?
- ሙባረክ ሰውየውን ይገፈትር ነበረ በወቅቱ
- ሰውየውነ ማለት ተወካዩን?
- ይሄ አሁን ተወክሎ የመጣው እሱ ነው አንደኛ ከመድረክ እንዲወርድ ያደረገው ከመድረክ አስወረደው እንዳሉ አንድ ስድስት ሰባት ይሆናሉ ከበውት ማለት ነው ያዙት ሰውየው ይፈነጫጨራል ከዛ በኋላ ይሄ አሁን ቅድም ያልኩህ ልጅ ታጁዲን እና ሌሎቹም አሉ እኔ አውቃቸዋለሁ እንደዚህ በቃ እንዳለ ጉማውን ሰውየው እንዳይነዳው በቃ ወዲያው ነው እዛው እንትን ሲል ይታያል አጠገቤ ነው በሩ ላይ ነው ከዛ በኋላ ወድያውኑ እንትን አሉት ሰውየውን ይሄ አለቀውም አለ እሱ ማለት ነው እሱ ማለት ነው ሲል ከዛ በኋላ
- ተወካዩን ማለት ነው ?
- ተወካዩን
- ወደ ጉማው ስለማሄድ አለመሄዱ?
- ማለትም እዛጋር ነው በቃ እንትን እንዳለ ይሄኛው አንደኛው እንትን ሲል ሌሎችም አሉ በዚህ በኩል በዛ በኩልም አሉ ልጆች ማለት ነው አሁን እሱ ሰውየውን እንትን ሲለው የነበረው እሱ ነው መጀመሪያ ማለት ነው ለጉማው መንስኤ የሆነው እሱ ነው ልክ እንደተነጋገረ ሰው ማለት ነው
- እስቲ ለጉማው መንስኤ የሆነው እሱ ነው የምትለውን አሱን አስረዳ እስቲ?
- አዎ ሰውየው ልክ ሊነዳ እየገባ ነበር
- መኪና ውስጥ?
- ወደ መኪናው አልገባም ገና ሊገባ ሲል ጉትቶ ሙባረክ ነው ከዛ በኋላ ሌሎችም ጓደኞች አሉት ስድስት ሰባት ሆነው ሲረባረቡበት አንተን ብሎ መልስ መላሽ ምናምን ሲሉት

http://ethcriminalawnetwork.com/

እላጋ እነታጁዲን ሌሎች አሉ እላ የሚያስተናብሩ ምናምን እላ የሚያድሩም አሉ ወዲያውኑ አፈነዳዱት ጐማው እላው ቆመው እንትን አለ ተኛ አራቱም ጐማ

- እሺ ምስክር እናመሰግናለን ጨርሰሃል መመለስ ትችላለህ በጣም አጭር ምስክር አላችሁ መጀመሪያ አንተ ግለጽልን እስቲ ና /የማይሰማ/ ምንድን ነው የምታቀርበው ነገር
- አሁን ስወጣ ማለት ነው አቡበከር ዝም ብሎ ፈገግታ ነው ሰላም ሲለኝ ያኛው ድርሻህን ታገኛለህ አለኝ
- አቡበከር ሰላም አለህ?
- ይሄኛው በቃ በአይኑ ሰላም አለኝ ያኛው ድርሻህን ታገኛለህ አለኝ እኔም ልናገር ስል ዝም ብለህ ሲለኝ ነው የሄድኩት እኔም እንዲህ ብዬ ሳየው ያው ፖሊሶቹ ዝም ብለህ ሂድ አለኝ
- እስቲ ሌላ የሰማ ሰው አለ እላ ፖሊሶች ?
- /የማይሰማ/
- እስቲ ይምጡ እስቲ ምንድን ነው የሰሙት ነገር ዝም ብለህ ሂድ ብለው ?
- /የማይሰማ/
- እሺ አንተ ወጣ በል ማይኩን ስጡት ለተከሳሽ ለምንድን ነው እንደዛ ያልከው መጀመሪያ ስምህ ማን ነው?
- ስም ሰኢድ አሊ 16ኛ ተከሳሽ
- አሊ ማን ነው?
- ሰኢድ አሊ ጁሃር
- እድሜ?
- 30
- ሥራ?
- ኢማም
- የመስኪዱ?
- የመስኪድ
- አሁን አድራሻህ ከዚህ በፊት ዋናው መዝገብ ላይ ስላለ ከዚህ በላይ አይፈለግም አሁን ዋጋህን ታገኛለህ ብሎኛል እያለ ነው ምስክሩ ምን ይላሉ እዚህ ላይ?
- እኔ በፍፁም የምን ዋጋ እከፍለዋለሁ ምንም የማውቀው ነገር የለም አላናገርኩትም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አላልክም?
- እኔ አላልኩም እንደዚህ የሚያስብል ነገር
- /የማይሰማ/
- አይ እሱ ችግር የለውም እሱ የተናገረውን ፍ/ቤቱ ይዳኛል እሚያዝትም ይሁን የሚያስደስት ነገር እንደተናገርኩ የራሴን ስሜት እራሴ
- አይ ችግር የለውም ቆይ ወደ ጀስቲፊኬሽኑ በኋላ እንመጣለን ብለሃል አላልክም ብቻ ነው
- አዎ እኔ አላልኩም ከሱጋራ ምንም አላወራሁም ጭራሽ
- እሺ እሱ ነው ብሎኛል ያልከው አንተ ይነሱ እስቲ ስጧቸው ማይኩን እርስዎስ ሰላም ብለውታል?
- እኔ ፈገግ ብሎ ዞር ብሎ ሲያየኝ በቃ እኔ በአንገቴ እንዲህ አልኩት እንጂ የተናገርኩት ቃል ምናምን የለም
- እሳቸውስ ምን ተናገሩ?
- አልሰማሁም እኔ
- በቃ
- እስቲ ቀይ የለበሱት እዛጋ ያለው እስክሪፕቶ /ግልጽ ያልሆነ/ አንዴ ተነስና አሁን የባለውን ነገር ሰምተሃል አንተጋ ነበር ሲቀመጥ የነበረው እሱ አንተጋ ነው እዛጋ ነው አንተጋ ነበር አደል እሺ የሰማኸው ነገር አለ ?
- /የማይሰማ/
- ስለዚህ ምንም አልሰማህም ቁጭ በል አዎ ተናግረዋል አደል ከእርስዎ በኋላ ያለው ፖሊስ እሺ ስለዚህ ነገር የሰማኸው ነገር አለ እዛው አጠገብ ስለነበርክ ድምጽ የማንን ነው የሰሙት እስቲ ወደ ማይኩ እሺ ፖሊስ ነህ እሺ ምን ሰማህ ቀጥል?
- ማለት ምን አይነት ድምጽ እንደወጣ ለይቼ አላወቅኩም
- ድምፁ የማን ነው?
- በዚህ ሳይድ መሆኑን ነው
- እሺ የማን እንደሆነ አላጣራህም ብቻ ድምጽ ሰማህ?
- አዎ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ከእርስዎ በኋላ ያለው ፖሊስ ኮማንደር ነው ማረጉን በትክክል ስላለየን ነው ይቅርታ ኮማንደር ነው ?
- ም/ኮማንደር
- የሰሙት ነገር አለ አሁን ስለተባለው ነገር እሳው አጠገብ ስለሆነ?
- እኔ ክቡር ፍ/ቤት በጀርባ ላይ ነበርኩ እኔ
- እ?
- በወዲያ ነበርኩ እኔ እዚህ አልነበርኩም
- ኦኬ እሳ ፊት ለፊት ነበርክ
- እሺ የሰማኸው ነገር አለ አሁን የተባለውን?
- አልሰማሁም
- እሺ ያኛውስ?
- አልሰማሁም
- እሺ ተመለስ መልሰው ወደቦታው
- እሺ አሁን ያለውም ጊዜ ምስክር ስላለ ያለችውም ጊዜ አጭር ስለሆነ ይዜን መርምረን በነገው እለት ተገቢውን ትእዛዝ እንሰጣለን
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም
- ምያለሁ
- እሺ ምስክር የአማርኛ ቋንቋ ይችላሉ ?
- አዎ
- ስለዚህ ለምስክሮች ደህንነት ሲባል የመጀመሪያ ስሞን ብቻ ይናገራሉ
- አየነው መሃመድ አሊ
- ለምንድን ነው የመጡት እዚህ?
- ከሳ በፊት አቃቤ ሕግ ስንተኛ ተራ ቁጥር ናቸው?
- በአቃቤ ሕግ ክስ ላይ 94 ተጠቅሶ ይገኛሉ በፍ/ቤቱ 29ኛ ተራ ቁጥር ናቸው ለምንድን ነው እዚህ የመጡት?
- የመጣሁት ኮሚቴ የሚሰበሰብበት ቦታ የማን ነው እሱን ትመስክራለህ
- ምንድን ነው የምን ኮሚቴ ነው?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ 17ቱ
- የሚያውቁት ሰው አለ?
- አዎ
- ያውቋቸዋል?
- ከፊሎቹን አውቃቸዋለሁ በስም ባላውቅ በመልክ
- እሺ ማን ማንን ያውቃሉ?
- በስምም አውቃለሁ በመልክም አውቃለሁ
- እሺ ማን ማንን ያውቃሉ እስቲ ንገሩን?
- ኮሚቴዎቹ ያው አቡበከር ሽምሱን እንደዚህ አውቃለሁ
- አቡበከር ማን ነው?
- የአባት ስም አላውቅም
- ሽምሱ?
- አዎ
- ሽምሱ ማን ነው?
- የባት ስም ሁሉንም አላውቅም
- ሌላ?
- የመጣልኝ የመጣልኝን
- እኮ የሚያስታውሱትን ብቻ
- አዎ ሼህ ጣሂር ሼህ ሱልጣን ሼህ መከተ ሌሎቹ ጠፍተውብኛል ሌሎቹ
- እስኪ ወይ ስማቸው ከጠፋቦትም በአካልም ሊያሳዩን ይችላሉ እነዚህ አህን የጠሩትን እና በአካል የሚያውቋቸውን
- እዛ የነበሩትን ነው?
- እዚህ አሉ እዛ የነበሩት እዚህ ካሉ ይለዩልን ይሽውሎት ያዳምጡኝ መጀመሪያ ተነስተው መጀመሪያ ይመልከቱ ተነስተው ደግሞ እነሱ ተከሳሾቹ ቆመው መለየት የሚችሉ ከሆነ ወይ ቁጭ እንዳሉ ወይ ቆመው መለየት ይችላሉ ይነሱና ሼህ ጣሂር ስንተኛ ተከሳሽ ኖት 21ኛ ተከሳሽን ለይተው አሳይተዋል ጀማል ያሲን ስንተኛ ተከሳሽ ኖት 19ኛ ተከሳሽን ለይተው አሳይተዋል እሺ ቁጭ በሉ
- ከነዚህ ሰወችጋ ፀብ ወይ ዝምድና አላችሁ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ዝምድና የለንም
- ፀብስ?
- ፀብ የለኝም
- እሺ ካሉ በኋላ በአቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ
- ሃጂ የመጣሁት ለምስክርነት ነው ብለዋል አሁን እኚህ እርስዎ ቆመው ያሳዩዋቸው እዛ ውስጥ ያሉት ሰወች መች እንደሚያውቋቸው በምን እንደምታውቋቸው እና አጠቃላይ ከነሱጋር የነበረው ሂደት ምን እንደነበረ እስቲ የሚያውቁትን ለተከበረው ፍ/ቤት በዝርዝር ይግለፁ መቼ ነው የሚያውቋቸው በምን ነበረ የተዋወቃችሁት እርስዎ እስቲ ዛሬ ከመጡበት ጋር በተያያዘ በዝርዝር እንዲገልፁ እጠይቃለሁ እና እስቲ ይንገሩን?
- አዎ እንዚህን ሰወች የማውቃቸው አወልያ ስብሰባ ላይ ነው
- መቼ ነበረ ስብሰባው?
- ወልያ ስብሰባ ላይ የዛሬ ዓመት አካባቢ ነው ቀኑን ባላስታውሰው ወሩን
- ወሩን ያስታውሳሉ ?
- ታህሳስ ይመስለኛል
- ምን ነበር የአወልያ ስብሰባ ዋናው አላማው ምን ነበር እንዴት ተገናኛችሁ?
- አወልያ የተሰበሰብንበት አላማ 3 አላማዎችን ይዘን ነው ሦስቱን ልዘርዝራቸው
- አዎ ይቀጥሉ
- ከሦስቱ አንዱ የመጀመሪያው አወልያ ትምህርት ቤት የሙስሊም ት/ቤት ነው ኮሚቴው /ግልጽ ያልሆነ/ ስላደረገ በገለልተኛ በቦርድ ይመራ ነው ሁለተኛው ጥያቄ መጅሊስ ብዙ ዘመን አድርጓል ለሙስሊምም አልሰራም ሙስሊሙን አዳክሟል በሚል እሱን በምርጫ ምርጫ እናካሂድ ሌላ ሰው እንተካ ነው
- እሺ 3ኛው?
- ሦስተኛው አህባሽ በእኛ እምነት ላይ ጣልቃ አይግባ የራሱን እምነት በራሱ በነፃነት እንደ ሌላው ኃይማኖቶች ያካሂዳል እነዚህ ሦስቱን መንግስት ይፍታልን ብለን ለመንግስት አቤት ለማለት ነበር እዛ የተሰበሰበው
- እሺ ያ ስብሰባው እንዴት ነበረ ይሄ ስብሰባው አሁን የጠቀሷቸው ሰወች ማለት ነው የት እንደምትሰበሰቡ ከዛ በኋላ ምን እንደተባለ ምን ሲደረግ እንደነበረ እስቲ እሱን ዘርዘር ባለ ሁኔታ ይግለፁልን ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስብሰባው ያው እዛው ላይ ሰወች ተመራረጡ ወደ እከሌ ብዬ ባላውቃቸውም ወደ ሃያ አባቢ የሚሆን ሰው ተጠቆመ እነዚህ ሃያ ሰወች ደግሞ እራሳቸው ተመካክረው እዚህ ሃያው ላይ ያለ ወጣት ነው አብዛኛውን ከሽማግሌ እናርግበት በሚል ከምሁርም ከአሊምም እንቀላቅልበት መንግስት ፊት ለይ ስንሄድ ከሽማግሌዎችም አብሮ መታየት አለበት እኛም ብንሳሳት ሽማግሌዎች ይመልሱናል በሚል እንደገና ከዚህ ከሦስቱ አይነት ሰወች እነ እከሌ እነከሌን ጨምሩልን እና እነዚህን ብናረጋቸው ብለው ለተሰብሳቢው አመለከቱን ተሰብሳቢውም ያን ያመጧቸውን ሰወች ተቀብሎ አፀደቀላቸው
- እነዚህ ሰወች አሁን ጠቆመ እንደዚህ ሆነ ያሏቸውን ሰወች ማለት ነው ቅድም
- ከኛ ከሽማግሌዎች አንዱ እኔ ነኝ
- እርስዎም እዛ ተመርጠው ነበረ እንዲገቡ ተደርገው ነው ?
- አቤት
- እርስዎ እንዴት ገቡ?
- ከሽማግሌዎቹ እነዚህ ሽማግሌዎች ይጠቅሙናል ብለው ለሕዝቡ አስታወሱ በዛ መሰረት እኛ ሽማግሌ ልንገባ ቻልን
- እስቲ እሱን በኋላ ይገልፁልናል እና እስቲ ከዚህ ከአወልያ በኋላ ማለት ነው የት የት ነበረ የምትሰበሰቡት ለምሳለ አሁን ሼህ ጣሂርን አንስተዋል ?
- የምንሰበሰበው ነው ድምጽህን ትንሽ
- እሺ ስብሰባው የሚካሄደው የት ነበረ ምንድን ነው የስብሰባው አላማ ምን ነበረ?
- የስብሰባው አላማ ይሄው ነው እኮ ሦስቶች ናቸው ሌላ አላማ የለም የነኚህን ሦስቶችን ዓላማ ለማን ለማን መስሪያቤት እናድርስ ነው ለየትኛው መስሪያቤት ብናደርስ መፍትሄ እናገኛለን በሚል ለጠቅላይ ሚኒስትሩም ፃፍን ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩም ፃፍን ለብዙ መስሪያቤቶች ፃፍን ያንን ተወያይተን አስራሰባቶችም እየፈረምን ቃል በቃል እየተናበብን ያንን እከሌ እና እከሌ ይሄን ደብዳቤ እዚህ ቦታ ይዘው ይሂዱ ያን ደብዳቤ እዚህ ቦታ ያድርሱ እየተባልን ያን ደብዳቤ ወስደን እያደረስን እንከታተል ነበር
- እሺ ከአወልያ ሌላ የት ነበረ ስብሰባ ይካሄድ የነበረው ?
- ከአወልያ ሌላ እንግዲህ እንድእርቀቱ ሰው እንዳይጐዳ አንዱ ወደላይ ወደ እሩፋኤል መስኪድ እንሰበሰባለን ወደታች ወደ ሳርቤቶችም እንሰበሰባለን
- ሳር ቤት የት ነበረ የምትሰበሰቡት?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሳር ቤት አንድ የሼህ ጣሂር ቢሮ አለ እዛ
- ማን የሚባል ነው ቢሮው?
- ቢሮ ውጭ ላይ ነው የተፃፈው እሬክላሙ እስላማዊ ዳዋ የትምህርት ነው የመመካከር ድርጅት ነው እኔ በደምብ አላነበብኩትም
- እሱ ባለቤትነቱ የማን ነው ?
- የማን እንደሆነ አላውቅም
- ግን እዛ ግቢ ትሰበሰቡ ነበረ?
- እዛ እንሰበሰብ ነበረ ለቦታው አንዴ ወደታች አንዴ ወደላይ ስለምናደርገው ለታክቢ እንትን እንዳይል እያልን በየ አራት ማእዘን እንትን እንላለን
- እዛ ስትሰበሰቡ ምን ይቀርብላችሁ ነበር?
- ይኸው ነው
- አይ ስብሰባው ላይ ማለት ነው አሁን ሼህ ጣሂርጋ እዛ አሁን እርስዎ የገለፁት ቦታ ማለት ነው ይሄ የዳባናእውቀት ያሉትን እዛ ማህበር ውስጥ?
- ይኸው ነው 3 አጀንዳ ነው ሌላ አይመላለስም
- አደለም አጀንዳ ሳይሆን ምንድን ነው የሚቀርብላችሁ መስትንግዶ የመሳሰለው ነገር አለው ወይ?
- መስተንግዶማ ውሃ ቆሎ ሻይ ያንን መቼም ሰው ሲገኛኝ መቅመስ አለበተ ያቺን ቡና ሻይ ውሃ ቆሎ
- ማን ነው የሚያቀርብላችሁ እሱን?
- የራሳችን ነው አንዱ ቸር የሆነ አንድ ሁለት ሦስት ጊዜ ይጋብዛል ጥብቅ የሆነ ደግሞ ዝም ይላል እንዲሁ እርስ በራሳችን ነው እንትን የምንለው
- እዚህ ቢሮ ውስጥ አሁን ቸር የነበረው ማን ነው ታዲያ?
- ቸር ከሚባሉት አንዱ እኔ ነኝ
- እዚህ ቢሮ ውስጥ ማለቴ ነው ?
- የት
- ይሄ ቢሮ ማለቴ የሼህ ጣሂር ቢሮ ውስጥ የዳባና እውቀት ማህበር ውስጥ እዛ ማህበር ውስጥ አሁን በወቅቱ ማን ነው ቸር ማን የሆነው እሚያቀርብላችሁ ሎጂስቲክ የመሳሰለው መስተንግዶ ማን ነበረ የሚያቀርበው ማለቴ ነው?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የሚያቀርበው እንግዲህ ያው እዛው በአካባቢ ያሉት ሰወች እዛው ልጆች ይልኩና ይጠሩና ሻይ ቡና አምጣልን ቆሎ ይምጣል ያቺን ቆሎ እየበላን እንመካከራለን
- በዚህ ድርጅት ውስጥ ስንት ጊዜ ምን ያህል ጊዜ ተሰበሰባችሁ እነዳባና እውቀት ማህበር ሌላጋ የምትሰበሰቡበት የነበረ ከሆነ ምን ያህል ጊዜ ተሰበሰባችሁ?
- እንግዲህ እኔ አብዛኛውን ብዙ ጊዜ አልገኝም ብገኝም ያው እዛ ምናልባት አንድ ሁለት ሦስት ጊዜ ተሰብስበን ሊሆን ይችላል
- ከዚጋር በተያያዘ እርስዎ ግን በወቅቱ ማለት ነው እርስዎ አሁን እነሱ መረጡኝ ወይም ደግሞ ጠሩኝ ብለዋል እና እርሱ በቦታው ነበሩ እንዴ እርስዎ እዛ ቦታ ውስጥ ሲከቶት እነሱ?
- መልሰማሆትም
- የኮሚቴ አባል እንዲሆኑ እርስዎን ሲጠይቆት በወቅቱ ነበሩ ወይ?
- እኔ ስመረጥ በጽሁፍ እነእከሌ እነከሌን በዚህ መልኩ እነሱን አርገናል እና አጽድቁልን ብለው ሲናገሩ እዛው ቁጭ ብያለሁ
- አርስዎስ ስለእርስዎ አገባብ እስቲ እርስዎ እንዴት ገቡ ነው ጥያቄው በስልክ ነው የተነገሮት እንዴት ነው የተነገሮት ምንድን ነው?
- አይ በኋላ መጨረሻ ላይ ገና ወደዛ ስሄድ ማለት ነው
- አዎ ገና መጀመሪያ ወደዛ ስትሄዱ?
- እሱማ እኮ እንግዲህ በ15 ቀንም በየሳምንትም እሄዳለሁ አንዳንዴ እሄዳለሁ አንዳንዴ እቀራለሁ አጋጣሚ ሆኖ እዛ እንደሄድኩኝ ደነገጥኩኝ እኔ አቶ ሃጂ አየነው መሃመድ ለዚህ የስፈልጉናል ብለን አርገናቸዋል አጽድቁልን ሲሉ አይሆንም ለማለትም ፈራሁ እሺ ብዬ
- ቅድም እንደገለፁት ልክ እንደ ዳዋ እና እውቀት ሌላ ማለት ነው ሌላ እንደዚህ ማህበር የሆነ እነደዚህ የምትሰበሰቡበት ቦታ ነበረ ሌላ ማህበር ማለት ቅድም እንደገለፁት እንደ ዳዋ እና እውቀት አይነት ድርጅት ውስጥ?
- የለም አላውቅም ሌላ መኖሩን አላውቅም
- እዛ ውስጥስ ሆኖ የተለያየ ቦታ ነበረው የምትሰበሰቡበት ቦታ እዛ የሳርቤቱ ማለት ነው?
- አንድ ብቻ ነው ያለው ወንበሮች አሉ አንድ አግዳሚ ጠረጴዛ አለ ያው ያቺን ይከፍቱልናል እዛች እንሰበሰባለን ቆሏችንን ውሃችንን ጠጥተን ነው ይምንለያየው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስቲ እነማን ናችሁ አሁን የጠቀሷቸው ሰወች በሙሉ ነበሩ ወይስ ማስታወስ ይቻላል ?
- አዎ እንግዲህ ስብሰባ ላይ መቼም ያለ ነው አንዴ ይገኛል ሰው አንዴ አይገኝም እንመካከራለን እንትኑ ሳይሞላ ሲቀር ደግሞ ቀጠሮ እናረጋለን ለዚህ ነው
- እስቲ ይንገሩን የሚያስታውሷቸውን አሁን እዚህ የነበሩት በሙሉ ነበሩ ?
- አሁን ቅድም እከሌ እከሌ እያሉ ከወምበር ተነስተው የጠቆሟቸው ሰወች እዛ ስብሰባ ላይ ይገኙ ነበረ ሁሉም ይገኙ ነበር?
- እንግዲህ የሚገኙት እንደስራው ሁኔታ አሁን ጠቅሼዋለሁኝ የሚገኝም አለ የማይገኝም አለ የግል ሃጃው እንትን የሚለው አለ እና በዛ መልኩ ነው የሚካሄድ የነበረው
- ግን እነኚህ ሰወች ቅድም የጠቀስኳቸው በሙሉ በተለያየ ጊዜም ይሁን ይገኙ ነበር?
- አንዳንዴ ይገኛሉ አንዳንዴ ደግሞ ይጓደላል
- ሃጂ እርስዎ የተመረጡት በነበሩበት ነው እንዴ?
- ቅድም እኮ ተናገርኩኝ አልሰማሽኝም
- እኮ አሁን ጥያቄው ምንድን ነው እርስዎ ሲመረጡ እዛው ነበሩ ወይ?
- አዎ ሲመረጡ ሳይሆን እነ እከሌ እነ እከሌን አንዱን በምሁር በሸማግሌ ከዛ ከዛ እነዚህን
- ልክ ነው ይሽውሎት አሁን ጥያቄው ምንድን ነው እንደዛ ሲባል አጽድቁልን ተብሎ ሲጠየቅ እርስዎ እዛ ቦታ ላይ ነበሩ ወይ ነው ?
- አለው አለሁኝ
- ቅድም አሁነ በዋና ጥያቄ ሲጠየቁ ይሄ እስላማዊ ዳእዋ የሚባለው ማህበር ውስጥ ብቻ ነው የተሰበሰብነው ብለዋል መጀመሪያ ደግሞ ሲጠቁሙ ሼህ ሱልጣን አማንን አውቃቸዋለሁ ብለዋል የት ነው የሚያውቋቸው ሼህ ሱልጣን አማንን?
- የለም የተሰበሰብንበት እኮ አንድ ቦታ ነው አላልኩም
- እሺ ይቀጥሉ እሺ አሁን ስላሉ እኮ ነው እሺ ይቀጥሉ ስንት ቦታ ነው ?
- አንድ ቦታ ነው አላልኩም
- ቆይ ምስክር ምናልባት ወደ ሩፋኤል አካባቢ አንድ መስኪድ አለ አወልያ እንደገና ደግሞ አሁን የጠሩት አለ ብለዋል ከዛ የተለየ አላችሁ?
- አይ ቅድም በባልደረባዬ ሲጠየቁ እስላማዊ ዳእዋ ብቻ ነው የተሰበሰብነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ ብቻ ነው አላልኩም
- እዛም ተሰብስበናል ለማለት ነው ምንድን ነው እዛ ላይ የተነሳው ነገር የሆነች ቦታ እንደጠረጴዛ እና የሆነ ነገር ብቻ ነበር ነው ያለው የቦታውን አቀማመጥ ነው እንትን ያሉት
- ጥሩ ሼህ ሱልጣን አማንን የት ነው የሚያውቋቸው ?
- ሼህ ሱልጣን እዚህ ኮሚቴ ውስጥ
- እሳቸውስ የት ነው ምንድን ናቸው ሼህ ሱልጣን አማን ?
- እንዴት ምንድን ናቸው ?
- በኮሚቴ ውስጥ ምንድን ነው ሚናቸው?
- ያው እንደእኛው ተሰብሳቢ ናቸው
- እሳቸውጋር ትሰበሰቡ ነበረ እንዴ?
- መቃወሚያ አለን
- እሺ ምንድን ነው ተቃውሞው?
- መሪ ጥያቄ ነው በቀጥታ ከሚሆን ምስክሩም መሪ ባልሆነ መንገድ መጠየቅ ይችላሉ ግን እሳቸውጋ ትሰበሰባላችሁ መልሱም ይታታል እኮ የተፈለገውም
- ምላሽ ስጡበት
- ጥሩ አልፈነዋል የተከበረው ፍ/ቤት ይሄን ጥያቄ
- ሌላ ጥያቄ
- ምስክር ሼህ ሱልጣን አማን ምንድን ነው ስራቸው ስራቸውን ያውቃሉ?
- አላውቅም
- ቅድም ቢሮስ ያሉት ቢሮ አላችሁ
- የማን?
- ምንድን ነው ተቃውሞው ቀጥሉ
- የተከበሩ አቃቤ ሕግ ጥያቄውን ትተነዋል ካሉ በኋላ በሌላ ዙር ነው መሪ ይዘው የመጡት እና ወይ ይሄንንም ይተውት ወይ መሪውን ይተውት ከሁለት አንዱ
- እሺ ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄው ሌላስ የት ቦታ ተሰብስባችኋል ቢሆን እንኳን
- ልክ ነው ጥያቄውን ሰምተናል መሪ ነው ብላችኋል አሁን እሱን ምላሽ ይስጡበት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥሩ እሺ
- አለፋችሁት ወይስ
- አሻሽለን እናቅርበው ጥያቄውን የተከበረው ፍ/ቤት
- ይሄን ታልፉታላችሁ?
- አዎ
- ምስክር እሩፋኤል አካባቢ ያለው መስኪድ ሳር ቤት ያለው የእስላማዊ ዳእዋ ማህበር ውስጥ ተሰብስበናል ብለዋል ሌላ ቦታ ተሰብስባችኋል?
- የለም እዚህ እሩፋኤል መስኪድ ተሰብስበናል
- ሌላስ ?
- ሌላ አንድ አራት ቦታ ነው የተሰበሰብነው
- አራቱን ቦታ እስቲ ስማቸውን ይንገሩን የት የት ናቸው ?
- ቆይ እስቲ ቆይ እሩፋኤልን ጠርተዋል ሳር ቤትን ጠርተዋል አወልያን ጠርተዋል አራተኛው ማን ነው?
- አራተኛው ይሄ ኩርቱ ህንፃ እዛ መስኪድ አለችን ኩርቱ ሕንፃ ውስጥ መስኪድ አለችን
- እሺ ቀጥሉ
- ጥሩ ቅድም ሲገልፁ በእያንዳንዱ ስብሰባ እኔ አልገኝም ነበር ብለዋል እማልገኝባቸው ስብሰባዎች ብዙ ነበሩ በብዛት አልገኝም ብለዋል አደለም ?
- እማልገኝበትም አለ እምገኝበትም አለ
- አዎ በማይገኙበት ስብሰባ እሚደረገውን ነገር ያውቃሉ?
- እንግዲህ በማልገኝበት ስብሰባ የተነጋገሩትን ባላውቀውም በሚቀጥለው ስብሰባ ይሄን ይሄን ተነጋግረን ነበረ እና ይሄን ይሄንን ማመልከቻ ልንጽፍ ነው ለመስሪያቤቶች ብለው ታይፕ አርገው ያመጡልናል ያን አንብበን በዛ እንፈራረማለን
- ስብሰባዉን በየምን ያህል ጊዜ ነበር ታረጉ የነበረው ?
- ስብሰባው እንግዲህ የአወልያ ስብሰባ አርብ አርብ ስለሆነ ውጤት እንዳለ እንከታተላለን
- መቼ ነው ታዲያ?
- ሕዝቡ አርብ አርብ ውጤት ይጠይቃል ምን ደረሳችሁ ይላል
- ስለዚህ እናንተ ስብሰባውን መቼ ታረጋላችሁ?
- አቤት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አርብ ሕዝቡ ውጤት ይጠብቃል እናንተ ስብሰባውን መቼ ታረጋላችሁ ?
- እኮ ያገኘነው ውጤት ካለ ያገኘነውን ውጤት እንነግራለን ከሌለ ደግሞ ውጤት እስኪመጣ
- እስቲ ምስክር ይቆዩ እስቲ አንዴ ጥያቄው ስብሰባውን በየስንት ቀኑ ነው የምታደርጉት ነው እሱን ብቻ ይመልሱ?
- እንግዲህ ስብሰባው እንደሁኔታው ነው በሳምንትም እናደርገዋለን
- እሺ በሳምንት ስታደርጉ መቼ መቼ ነው የምታደርጉት ቀኑ መቼ ነው?
- አይ በሚመቸን ነው ተመካክረን ቢዚ የሚሆንበት ቀን
- ከአርብ በፊት ነው ከአርብ በኋላ ?
- ስብሰባውን የምናደርገውማ ከአርብ በፊት ነው
- ለምን?
- ለአርብ ውጤት ያለውን ውጤት ለመንገር ለሕዝቡ እዚህ ላይ ውጤት ደርሰናል ይሄ እንዲህ ነው ውጤት ከሌለ ደግሞ ውጤት አላገኘንም እና ተረጋጉ ውጤት እስከምናገኝ ድረስ በእርጋታ ጠብቁን ተቀጥረናል በዚህን ቀን እያልን እንነግራቸዋለን
- ጥሩ ከአርብ በፊት ስብሰባ ታረጋላችሁ አርብ አርብ ለሕዝቡ ገለፃ ታደርጋላችሁ ?
- አዎ
- አርብ አርብ አወልያ ላይ ችግር ይፈጠር ነበር እሚያውቁት ?
- ችግር አወልያ ላይ አልተፈጠረም እኔ እንደውም በእውነቱ እነዚህ ወጣቶቹ እንዴት አርገው ችግር እንዳይፈጠር እንደሚጠብቁ እኔ ይገርመኛል በእኔ በእድሜ እንደዚህ አይነት አላየሁም ያን ያህል ሕዝብ ተሰብስቦ አንድ ሁከት ሳይፈጠር እንዲህ በሰላም ሲለያይ ሁሉም እንደው ተከታትሎ እንዲህ እንኛ ይነሳል ብዬ የምለው ቀን የለኝም በሰላም ነው የሚለያይ የነበረው
- እስከመጨረሻው?
- አዎ
- እስከ መቼ ነበሩ እርስዎ ከኮሚቴውጋር?
- ከኮሚቴውጋ ያው መጨረሻው ቀን ድረስ
- መቼ ነው መጨረሻው ቀን?
- ቀኑን እንግዲህ ይሄ ነው ብዬ አላውቀውም መታሰር ሲጀምሩ የዛን ጊዜ ቆመ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥሩ እሺ ታዲያ ተከሳሾች መታሰር እስኪጀምሩ ድረስ አወልያ ሁሉም ነገር ምንም ችግር አልነበረም ነው እያሉን ያሉት?
- አዎ በነበርኩበት ሰዓት ችግር አልነበረም
- እናንተ በምትፈልጉት ማለት እናነተ ማለት የኮሚቴ ተሰብሳቢዎች በምትፈልጉት ሰላኩ ነበር ሁሉም ነገር እየሄደ የነበው እስከ መጨረሻው ድረስ?
- አዎ [illegible] ሕዘቡ ከእኛ
- ከቁጥጥራ[illegible]ሳ አልወጣም ?
- አልወጣም እ[illegible]ላሁበት አሁን የምነግርህ እኔ እኔ ባለሁበት ወቅት ከሰብሳቢያችን በሚነገረው ሌላ[illegible]ማም እንዲህ ተጨማሪ በሚሰጠው መመሪያ አካባቢያችሁን ነቅታችሁ ጠብቁ ሌላ[illegible] ባለሁበት ስብሰባ ጊዜ ሁከት[illegible]ስም የሚያጐድፍ እንዳይገባ እያሉ በመምከር እንጂ እኔ
- እሺ ስብሰባው ላይ አሁን በቃል[illegible]ጠረም
- ያጋጥም የነበረው ነገር አንድ አይነትፀው ገለፃ እና በተግባር አርብ አርብ በየመስኪዱ
- እንግዲህ ከዛ ውጭ ያለውን አላውቅም ላያያል?
- ስለዚህ እርስዎ የሚያውቁት በስብሰባ ላይ የነ
- አዎ በስብሰባ ላይ የምንነጋገረውን እና አወልያ ላሉን ብቻ ነው ማለት ነው?
- እርስዎ ለምን ወደ ኮሚቴው እንደተመረጡስ ያውቃሉ ላበውን ነው
- የተመረጥኩት እኔ እንግዲህ የተመረጥኩት መቼም ተፈጥ[illegible]
- አንድ ችግር ሲገጥመኝ አቤት ማለት እወዳለሁ ለምን አንድ [illegible]ላት አቤት ማለት ብሎ እቤት ከተቀመጠ ለችግሩ ደራሽ የለውም አንድ ችግር ሲደ[illegible]ን ይዞ ዝም ለሚመለከተው መስሪያቤት አቤት ስለምል ሰው ስለሚያውቀኝ ይመስለኛ[illegible] ችግር ብለው የጠቆሙኝ
- በጣም ጥሩ ቅድም ሲገልፁ የናንተ ኮሚቴ ከተቋቋመ በኋላ ያረገውን አስረድተውናል የናንተ ኮሚቴ ከመቋቋሙ በፊት የተጀመረ እንቅስቃሴ ነበር ወይ የሚያውቁት ነገር አለ?
- የለም ይገርማችኋል ይሄ እንቅስቃሴ የተጀመረው መቼ እንደሆነ ልግለጽ ይፈቀድልኛል?
- ይግለፁ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ይሄ እንቅስቃሴ የተጀመረው ሐረር ላይ ነው አንድ ጊዜ የእኛ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መጅሊስ ሰብሳቢ ሃረር ላይ የሆነ አንድ ስብሰባ ነበራቸው ያን ጊዜ እሱ አወልያን በቁጥጥር ስር አዋልነው ይላል እሬድዮን አወልያ የሁከት ምንድን ነት ብቻ ብዙ አልያዝኩትም መፈልፈያ ሆኖ ነበረ ተቆጣጠርነው የኛ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መጅሊስ አህመዲን ነው ማን ነው የሚባለው አረንጓዴ ለባሽ እንለዋለን ስሙን በዉል አላውቀውም እና አወልያን በቁጥጥር ስር አዋልነው አለ የዚህን ጊዜ ነው እንግዲህ
- ስለዚህ ከዚህ በኋላ አወልያ ውስጥ የተፈጠረ ነገር አለ አዲስ አበባ ውስጥ ያለውን ነገር ይንገሩን አሁን ካሰፉት በጣም ይሰፋል እና አዲስ አበባ ውስጥ የተጀመረ እንቅስቃሴ ነበር የናንተ ኮሚቴ ከመቋቋሙ በፊት?
- አይ እኔ ማለት የፈለግኩት ይቅርታ ከዛ ጀምሮ ነው
- ጥሩ ሃጂ እሱን እሺ ነገሩን አሁን እኛ ምን ያለውም ጊዜ አጭር ስለሆነ ለዛ ነው እያቋረጥኮት ያለሁት ይቅርታ
- እሺ
- አዲስ አበባ ውስጥ የተጀመረ እንቅስቃሴ ነበረ ወይ እናንተ ኮሚቴ ሆናችሁ እንድትቋቋሙ ምክንያት የፈጠረ?
- እኔ አላውቅም
- ታዲያ ለምን ኮሚቴ ሆናችሁ ምን አስፈለገ ኮሚቴ መቋቋሙ እንቅስቃሴ ከሌለ ለምን ተቋቋማችሁ?
- እንቅስቃሴውማ ይኸው ነገርኩህ እኮ አሁን የአወልያ ተቆጣጠርነው
- እሺ አወልያ ላይ እንቅስቃሴ ነበር?
- አወልያን ተቆጣጠርን ሲል እኔ አወልያ የእስላም ተቋም ነው ምኑን ነው የተቆጣጠረው ይሄ ሰውዬ አህባሽ ተቆጣጠረን የሚል ነው እንግዲህ
- ማን ነው ይሄን የሚለው እሺ አህባሽ ተቆጣጠረን የሚለው ማን ነው?
- እዚህ ላይ አሁንም አበዛባችኋለሁ እንጂ ሌላ እንትን አለኝ
- ይኸውሎት ሃጂ እሁን እርስዎ የሚያውቁትን ማስረዳት የሚፈልጉት ነገር ካለ በኋላ ጠበቆች በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠይቆት ያስረዳሉ አሁን ይሄ የእኛ ጊዜ ነው እኛ የምንጠይቆትን ብቻ ነው የሚመልሱት እኔ እየጠየቅኮት ያለሁት ጥያቄ አዲስ አበባ ላይ እናንተ በኮሚቴ መልክ ከመቋቋማችሁ በፊት አዲስ አበባ ላይ ቅድም አወልያን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ጠቀሱልኝ አወልያ ላይ የተጀመረ እንቅስቃሴ ነበረ ወይ ማንም ይጀምረው ጥያቄው ምንም ይሁን የተጀመረ እንቅስቃሴ ነበረ አልነበረም ?

- አይ የሚወራው አህበሽ የሚባል እምነት ተከታይ እምነታችንን ሊያጠፋ መጥቶብናል ነው
- እሺ ሌላስ?
- ሌላ ይሄን ነው የማውቀው
- ጥሩ የት ነው የተጀመረው ይሄ እንቅስቃሴ?
- እዛው አወልያ ላይ
- በማን ነው የተጀመረው?
- አወልያላይ በተማሪዎች ነው የተጀመረው
- የናንተ ኮሚቴ የተቋቋመው ተማሪዎች እንቅስቃሴውን ከጀመሩት በኋላ ነው?
- በኋላ ነው
- በጣም ጥሩ ዋና ጥያቄ አበቃን
- መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ የተከሳሽ ጠበቆች
- ሃጂ
- አቤት
- ቅድም አህባሽ እምነታችንን ተቆጣጠረ የሚል ነገር ሰምቻለሁ ብለዋል አህባሽ ምንድን ነው የውቃሉ?
- አህባሽ ማለት እኔ እንግዲህ ምንም የለኝም ሰምቻለሁ አህባሽ ማለት የአብደላ ሃረር ያመጣው ሃረር ማለት አገር ነው አብደላ ያመጣብን ትምርት ነው አብደላ ያመጣው ትምህርት ምንድን ነው አላህ ሰማይ ላይ ነው ስንል የት አይተሽዋል የሚል ሰው ነው እኛ ደግሞ ፈጣሪ ከሰባቱ ሰማይ በላይ ነው ከሃርሽ በላይነው ነው የምንለው ዱአ ስናደርግም እንደዚህ ቀና ብለን ነው የምናየው ወደላይ ነው አህበሽ ግን ወደላይ ምን ኃይማኖት አለ ወደላይ የሚባል ነገር የለም ይሄ እናንተ የፈጠራችሁት ነው ነው የሚለው ስለዚህ አህበሽ የሚሉት ቃላት ነው
- ይሽውሎት ለእኛ ይሽው ግልጽ ነው ሁለት ልዩነት አላይተውናል እሷን እንይዛለን ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- ቅድም እሺ ይሄ አሁን ያሉት ነገር እዚህ አገር ውስጥ አለ እንዴ ያውቃሉ ይሄን ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የትኛው
- አሁን አብደለ ሃረሪ ብለዋል የሃረር ሰው ነው ብለዋል እንደዚህ የሚለው እርስዎ ካሉት እኛ ከምንለው ይለያል እጁንም ወደላይ አንስቶ አሳይቷል ይሄንን አስተሳሰብ የሚያራምድ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖሩን ያውቃሉ የአብደላ ሃረሪ አስተሳሰብ ኢትዮጵያ ውስጥ አለ የለም?
- አለ ግን ይሄ ነው ብዬ እኔ አሁን አላውቀውም እንጂ አለ
- ቅድም ሃረር ላይ የፌደራል መጅሊስ አህመዲን ወይም አረንጓዴ ለባሽ የምንለው አወልያን በቁጥጥር ውስጥ አዋልነው ሲል አወልያ የሙስሊም አደለም ወይ እንዴት ተቆጣጠርነው ይላል የሚልነገር ይሄንን እርስዎ በምን ሰሙ ማለቱን?
- እንግዲህ እዚህ ላይ ቃላቱ ጠፋብኝ እንጂ የምን መፈልፈያ ነው ያለው የምን መፈልፈያ ሆኖ ነበረ አወልያ ተቆጣጠርነው ሲል የመጅሊስ ስልጣኑ ይሄን ያህል ዘመን ዝም ብሎ ተቀመጠ ሙስሊም ስልጣን አይፈልግም እንደገና ደግሞ አወልያን ይቺን ልጆቻችን የሚማሩባት እንደገና ደግሞ በሌላ ተረጉመ በሚል ነው የሕዝብ አነሳስ ይመስለኛል የራሴም ይመስለኛል
- ለምንድን ነው አረንጓዴ ለባሽ የሚሉት?
- እንግዲህ ሁል ጊዜ የሚያዘወትረው አረንጓዴ ነው የሚለብሰው ስሙ ስለሚጠፋብን አረንጓዴ ለባሽ አልኩት ይቅርታ
- አወልያ ምን ያህል ይሄዱ ነበረ እርስዎ?
- እሄዳለሁ ብቻ ያዉ እንግዲህ እንደው ሽምገል ስላልኩኝ ፀሐይ ላይ መቀመጥም ስለማልችል እንደው አልፎ አልፎ አንዳንዳን ሳምንት እያሳለፍኩ እሄዳለሁ
- ሄደው ወደኋላ ሄደው ከስንት ሰዓት ጀምሮ ሄደው ስንት ሰዓት ድረስ ይቆዩ ነበር የሄዱባቸው ጊዜ ለናሙና ያህል ቢያሳዩን ?
- እንግዲህ እዛ ውጪ ላለመቀመጥ ብዬ ወደ አምስት ሰዓት ተኩል እሄድና እዛ ሶላት ሰግደን ያው ፕሮግራሙ ከተካሄደ በኋላ እንመለሳለን
- ሲጠናቀቅ ነው የሚመላለሱት?
- አዎ
- አወልያ ላይ ንግግር አርገው ያውቃሉ እርስዎ?
- አላውቅም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ንግግር ሲያደርግስ የሰሙት ሰው አለ?
- ከእኛ ከኮሚቴዎቹ?
- አዎ
- እዛ ንግግር ላይ ቅድም ያነሱት ነገር አለ ሕዝቡ ከእኛ ቁጥርር ውጭ ሆኖ አያውቅም እነዚህ በሕይወቴ ሰላማዊ ሆነው አይቼ አላውቅም ብለዋል ምንድን ነው ሰላማዊ እንዲሆን ያረገው?
- ሰላማዊ ያደረገው እምነቱ ነው
- የሰም አወልያ ላይ የተሰበሰበው ሕዝብ ቅድም ወጣቶች እነዚህ ወጣቶች ሲሉም ነበረ እነማን ናቸው እነዚህ ወጣቶች?
- አወልያን ሰላም ያደረገው እምነቱ ነው እምነት ወጣት አይልም ሽማግሌ አይልም ከሰማ ሰላማዊ ነው የሚያደርገው እስላም ሰላም ነው እንኳን እስላም ይቅርና ሌሎችም ኃይማኖቶች ቢሆን ኃይማኖት ሰላም ነው እምነቱ ይለያያል እንጂ ሰላም ነው ማንንም አይጐዳም እና ለዚህ ነው በሰላም የሚጠናቀቀው ለምን ሰላምን ካናጋ ያኛው አገር ይበላሽብሃል ይለዋል ኃይማኖት
- ቅድም እነዚህ ወጣቶች ያሏቸው እነማን እንደሆኑ ያስታውሳሉ?
- እነዚህን ወጣቶች በሕይወቴ አይቼ አላውቅም
- ተከሳሾችን ማለቶ ነው?
- እነሳሚል ወጣት ናቸው በዚህ በወጣት እድሜያቸው እንዲህ ያለ ሰላማዊ አመራር ሰላማዊ አካሄድ እኔ በእድሜዬ አላየሁም
- ስለ ስላም እስቲ የሚጠቅሱት አለ የተናገሩት ነገር እነሱን አሁን እነዚህ ወጣቶች ሰላማዊ ሲሉ ስለሰላም የተናገሩት አለ ተከሳሾቹ?
- አዎ
- አወልያ ላይ የሰሙት እስቲ ምን አለ?
- ተመራጮቹ እንዴ እንደውም አስቀድሞ ሰላማችንን እንጠብቅ ነው አበክረው ሰላማችን እንዳይናጋ እንዳይገቡብን እኛን መስለው ገብተው እንዳያደፈርሱብን ጥንቃቄ አድርጉ ነው የሚሉት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም እርስዎ ተመርጠው ለሕዝቡ አቅርበው አፀድቀዋል እንዴት ነበረ ያፀደቁት እስቲ ሂደቱን ይንገሩን እንዴት በምን መልኩ ፀደቀ እርስዎ መመረጦን የአገር ሽማግሌ ነኝ ብለው እና ያስመረጦት እዛው ነበርኩ ብለዋል?
- አዎ
- በምን መልኩ ነው የተመረጡት ሕዝቡ እንዴት አፀደቀው?
- እንግዲህ ዝርዝሮች ተነገሩ ዝርዝሮች ሲነገሩ ሰው በተክቢራ ነው የተቀበለው ያው እንግዲህ እስላም ተክቢራ ነው ከፊሉ በጭብጨባ ይገልጣት ከፊሉ ደግሞ በተክቢራ አላህዋክበር በሚል ይገልፃል ተክቢራ ብዙ አይነት ነው ይሄ አገላለጽ እንደየ ሃይማኖቱ ይለያያል
- ሕዝቡ ምን ያህል ነበር?
- ሕዝቡ ብዙ ነው
- ጥሩ ቅድም ስለ ጽሁፍም አውርተው ወረቀት ይበትኑ ነበረ ለማጽደቅ ብለዋል ትክክል ነኝ?
- እ
- ስትመረጡ በወረቀትም ሕዝቡ እንዲፈርም ?
- አዎ ዝርዝር ወረቀት የእኛ እንትን አለና ከዛ እዛ ላይ ዝርዝሩ ተነገረ በዚያ መሰረት ምርጫውን ሕዝብ ተቀበለው እኛ እንግዲህ ሕዝብ ከተቀበለ የእናንተን የዚህ የሕዝቡን ንግግር ወደ መንግስት ማድረስ ነው የመንግስትን መልስ ደግሞ ወደ እናንተ ማምጣት ነው የሚለውን ይዘን ተነስተናል
- ለመንግስት አደረሳችሁ እንዴ?
- አዎ
- የት የት አደረሱ?
- እንግዲህ ብዙዎችን ለመጥቀስ ቢያቅተኝ ለጠቅላይ ሚንስትሩ ቢሮ አግብተናል ብዙ ቢሮ አግብተናል ቢያንስ ቢያንስ ወደ ሰላሳ የሚሆን ከሃያ በላይ የሚሆን ደብዳቤዎች በየ መስሪያቤቱ አስገብተናል
- ጨረሳችሁ
- ሃጂ ቅድም ሲመሰክሩ ሕዝቡ መረጠ ብለዋል እና የምረጡኝ ቅስቀሳ ነበረ እንዴ ምረጡኝ ያለ ሰው ነበረ እንዴ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዚህ ላይ ነው አንዱ ያለው ችግር እስላም ምረጡኝ አይልም እስላም በግድ ተመረጥ ተብሎ ካልተጫነበት በስተቀር ምርጫ እስላም አይፈልግም
- ስልጣን አይበሉ
- ቆይ ምስክር እየሰሙ ነው አሁን የተጠየቁት ምረጡኝ ብሎ የቀሰቀሰ ሰው ነበረ ወይ ነው ካለ አለ ከሌለ የለም
- ምረጡኝ የሚል አልነበረም ያለ የለም
- እሺ በአወልያ ስብሰባ በሚደረግበት ጊዜ እነዚህ ወጣቶች ሰላማዊ እንዲያደርግ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ነበረ ብለዋል እና ከዚህ ተቃራኒ የሆነ ጀሃድን መቀስቀስ ወይም ተመሳሳይ ነገር ያደረጉት አለ እንዴ?
- እሱ ተመልሷል እኮ ቅድም ተጠይቆ ሁሉም ሰላም ነው ተብሏል ሰላም ከሆነ በተረሳቢጠሽ
- ጅሃድ ሲቀሰቅሱ ነበር እንዴ?
- ይሄን ጥያቄ እንቃወማለን የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ምንድን ነው ተቃውሞው
- የምንቃወመው አሁን እሳቸው ቅድም እንደተገለፀው በዋና ጥያቄ በዝርዝር የተናገሩትን መድገም አያስፈልግም ያው የገለፁት እንዳለ አለ ከዚህ ውጪ አሁን በቀረቡት ስለ ጀሃድ ስለምናምን እሳቸው ያሉት ነገር የለም እና ስለዚህ ነው አይ አደለም እንዲባል ነው የተፈለገው ስለዚህ የተከበረው ፍ/ቤት ይሄን ጥያቄ እንዲሰረዝልን እንጠይቃለን
- እስቲ ግልጽ አርጉት ማለት ያልተነሳ ነው ነው በእኛ
- ያልተነሳ ነው የተከበረው ፍ/ቤት እኚህ ምስክር ያው ፍ/ቤቱም እንደሰማው ሲመሰክሩ የነበረው ኮሚቴው እንዴት እንደተቋቋመ የት እንደሚሰበሰቡ ነው እንጂ አወልያ ላይ ስለበው ቅስቀሳ በየመስኪዱ ስለነበረው ቅስቀሳ እኛ አላስመሰከርንም በዋና ጥያቄ ተከሳሾች ተናገሩ የተባው እስካሁን በነበሩ ምስክሮች ሲነገርባቸው የነበረው በተለያዩ መስኪዶች እንጂ ኮሚቴ ውስጥ አደለም ክሳችንም በዛ መልኩ አደለም ፍሬም የተደረገው ስለዚህ ከጭብጡ ውጪ ነው በአጠቃላይ
- እሺመልሱ
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ ከመነሻው ምርጫ የተደረገው አወልያ ስለመሆኑ ሕዝቡ እነዚህ ተወካዮች ያላቸውን ሰው መምረጡ ክዛም እነሱ ሽማግሌ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ተብለን ወደ መንግስትም ጥያቄያችንን እንድናቀርብ ተጨማሪ ተደርገን ሕዝቡ አጽድቆልናል የሚል ነገር ተናግረዋል ከዛ በተጨማሪ እነዚህ ወጣቶች ስብሰባው ሰላማዊ እንዲሆን ያደረጉት ጥረት ያስገርመኛል ብለዋል ይሄ በግልጽ ተነስቷል ስብሰባው ሰላማዊ እንዲሆን ያደ9ጉት ጥረት ነበረ ብለው ተናግረዋል ከዚህ በተቃራኒ ስብሰባው ሰላም እንዳይሆን ደግሞ ከመሃከላቸው ያደረገ ሰው ካለ እንዲያስረዱን ነው የጠየቅነው ይሄ ያልተነሳ አደለም የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ ከተናገሩት ተነስተን ነው እየጠየቅን ያለነው እሳቸው ካነሱት ነው ስለዚህ የሚታለፍበት ምክንያት የለም ፍ/ቤት በቀረበው መቃወሚያ እና መልስ ላይ በእርግጥ ጥያቄው ተነስቷል ዋና ጥያቄ ግን ምንድን ነው ፍ/ቤቱ የወሰደው ከዛ ለየት ያለ ነገር ምስክሩ መለሰዋል በወቅቱ በነበረው ነገር ሰላም ነው ብለዋል ከዛ ውጪ ሌላ ምላሽ እንዲመልሱ እይጠበቅም ስለዚህ ሌላ ጥያቄ ጠይቁ ሰላም ነው ካሉ በቂ ነው

- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም በተለያዩ ቦታዎች ስብሰባ አድርገናል ብለው አስረድተዋል ለፍ/ቤት በነዛ ስብሰባዎች ላይ ማለት የኮሚቴው አባላት በምትገናኙበት ስብሰባዎች ላይ የሕዝቡን ወደ አመጽ ወይም ወደ ብጥብጥ የመምራት ፍላጐት ያለው ሰው አይተዋል እዛ ውስጥ ከስብሰባው ውስጥ ስብሰባ ላይ ስብሰባ በምታደርጉበት ሁኔታ?
- ኮሚቴው ስብሰባ ላይ ነው ?
- ቆዩ እስቲ አሁን የተነሳው ያው ቅድም የተነሳውን ነው ያለው ሂደት በሙሉ ፍፁም ሰላማዊ ነው ብለው መልሰዋል ምስክሩ ጀአድ አለ ወይስ የለም ሲባል አይ ሰላማዊ ነው ካለ ከዚህ በኋላ የለም ተብሎ የታለፈውን ነው አሁንም ወደ አመጽ የሚመራ አለ ወይ ጀአድ የሚለው ትርጉም ተቀየረ እንጂ ያው ስለሆነ ይሄ ታልፏል ሌላ ካላችሁ
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም ምርጫ ተደርጐ እኛን ተጨማሪ እንደሆንን ከሽማግሌዎች በነበሩት ኮሚቴዎች ላይ እንደተጨመርን ለሕዝቡ አስተዋወቁ ገለፁ ብለዋል እዛ ከነበረው ሕዝብ ላይ ይሄን የተቃወመ አለ እንዴ እናንተ ወደ ኮሚቴው ስትገቡ መግባት የለባቸውም ብሎ የተቃወመ አለ ?
- የለም የተቃወመ እንደውም አልመረጥም ነው የሚል ያለው እንጂ ተቃዋሚ የለም
- ይበቃል ሌላ ጥያቄ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሃጂ አወልያ የተሰበሰበው ሰው ብቻ ነው መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ ብሎ የመረጣቸው ወይም ሌሎች የሙስሊም ማህበረሰብ አለ?
- አቤት
- አወልያ የተሰበሰበው የሙስሊም ማህበረሰብ ብቻ ነው ወይስ ሌላ የሙስሊሙ ማህበረሰብ አለ?
- ሙስሊም ነው ይሄማ ጠባቂ አለ እኮ
- አይ አወልያ ውስጥ የተገኘው ሙስሊም ብቻ ነው ወይስ በሌላ አካባቢ ያለ?
- ሙስሊም ነው ብለዋል እኮ
- ሃጂ ቅድም ሳር ቤት ሼህ ጣሂር ቢሮ እስላማዊ ዳእዋ ትሰበሰቡ እንደነበረ ኮሚቴዎች ገልፀዋል ይሄን ቢሮ የሼህ ጣሂር ያሉት ከምን ተነስተው ነው ?
- እንግዲህ እሱ ነው አርሂቡ አርሂቡ የሚለን የሱ ነው በሚል ነው
- እንጂ ይሄ ድርጅት በማን እንደሚተዳደር አያውቁም አደል?
- አላውቅም
- ስለድርጅቱ ከዚህ በላይ የሚያውቁት ነገር የለም?
- የለም
- እዛ ስትሰበሰቡ ሻይ ቆሎ ቡና ከመካከላችን ቸር የሆነው እንደነበረ ገልፀዋል በድርጅቱ ተጋብዛችኋል እንዴ?
- በነማን ?
- እሺ ጥያቄው ስላልገባዎት እተወዋለሁ
- እሺ ሃጂ የሃረሩን ስብሰባ በተመለከተ ስለምን እንደነበረ እሚያውቁት ነገር አለ ስብሰባው የመጅሊሱ ኃላፊ አወልያን በቁጥጥር ስር አዋልነው ብለው የተናገሩበት ስበሰባው ስለምንድን ነበር?
- የለም ይሄ በማስሚዲያ ነው የሰማሁት
- የሃረሩ ስብሰባ ስለምን እንደነበረ የሚያውቁት ነገር አለ?
- እስቲ ቆይ በሚዲያ ነው የሰማሁት ነው ያሉት
- እኮ ስብሰባ ስለመኖሩ በሚዲያ ሰሙ ስለምን እንደሆነ ደግሞ የሚያውቁትን ነገር እንዲያስረዱ ነው የጠየቅኮት
- እዚህ ላይ መቃወሚያ አለ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቆይ እስቲ ተቃውሞ አለ
- እኛ በዋና ጥያቄ ካስመሰከርነውጋ ስለ ሃረር ስብሰባ እሳቸው ቅድም ስለ አብዱላሂ ሃረሪ ብለው ከገለፁትጋር ዝም ብለው ለመግለጽ ካልሆነ በስተቀር ስለ ሃረሩ ስብሰባ አላማ ይዘት ምን እንደነበረ እኛ እሱን ጭብጥ ይዘን ያን መሰረት አርገን በዋና ጥያቄ አላቀረብንም ስለዚህ ይህ ጥያቄ ግልጽ ቢያረጉልን
- የተከበረው ፍ/ቤት አቃቤ ሕግ በእርግጥ ምስክር ሲያመጣ የሚፈልገውን ነገር እንዲመሰክርለት ነው ምስክሩ ከተናገሩት ነገር ተነስቶ መስቀለኛ ጥያቄ ሊጠየቅ ይችላል እና ምስክሩ የተናገሩትን ነገር መሰረት አርገን እንጂ የሌለን ነገር እኛ ፈጥረን አደለም ጥያቄ እየጠየቅን ያለነው በዋና ጥያቄ ላይ ከጠየቁ ምስክሩ ሲያብራሩ ስለ ሃረር ስብሰባ ተናገሩ ሃረር ስብሰባን መሰረት አድርገው የመጅሊሱ ሰው አወልያን በቁጥጥር ስር አደረግነው አሉ የሃረር ስብሰባ ተደጋግሞ ተነስቷል እና ይሄ የሃረር ስብሰባ ስለምንድን ነበር የሚለው ጥያቄ ተገቢ ነው ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ የግራ ቀኙችሁን አዳምጠናል ፍ/ቤቱ የያዘው ነጥብ መጀመሪያ ቀደም ሲል በዋና ጥያቄ ተነስቷል አልተነሳም ነው ምስክሩ መጀመሪያ ሲጠየቁ ልጀምር ብለው ከሃረር ጀምረዋል አቃቤ ሕግም እስቲ ከዛ ጀምሮ ይቀጥሉ በማለት ሃረር ላይ የነበረውን ስበሰባ አንስተዋል ስለዚህ ጥያቄው ተገቢ ነው ቀጥሉ ብለናል
- እናመሰግናለን የተከበረው ፍ/ቤት ሃጂ ሃረር ላይ ስለነበረው ስልጠና ወይም ስብሰባ እስቲ የሚያውቁትን ነገር ለፍ/ቤቱ አስረዱ ምን አይነት ስልጠና ነበር ማን ነው ስልጠናውን ያዘጋጀው ?
- እስቲ ቆይ ጥያቄው የነበረው ቅድም የሃረር ስብሰባ ለምንድን ነው የተሰበሰበው ያውቁታል?
- የእስላማዊ ስብሰባ ነው
- እኮ ያውቁታል?
- መጅሊስ ነው
- መጅሊስ እኮ ለምንድን ነው አጀንዳው ምንድን ነው ያውቁታል ለምን ጉዳይ ነው የተሰበሰቡት?
- ስልጠና ተብሎ ነው
- አብረው ነበሩ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የለሁም
- የሉም እርስዎ?
- እኔ ያለሁት እዚህ ኮተቤ ነበርኩኝ
- የተከበረው ፍ/ቤት ልጠይቅ
- ቀጥሉ
- እሺ የሃረር ስልጠናን ማን እንዳዘጋጀው የሰሙት ነገር አለ ?
- አይ ማን እንዳዘጋጀው አላውቅም ግን ንግግር ያረግ የነበረው ይሄኛው የፌደራል መጅሊስ ጠቅላይ እንትን ነው
- እሺ አወልያ ላይ የተነሱ 3 ጥያቄዎች አሉ ብለውናል ሲጀምሩ አደለም ?
- እኛ ይዘናል ብለዋል እያሉ ነው ከዚህ በላይ ማን ያረጋግጥ
- እሺ የአወልያ ስበሰባዎች ላይ የተነሱ 3 መሰረታዊ ጥያቄዎች አወልያ የሚሰበሰበው ሰው ብቻ ነው ወይስ የአዲስ አበባ ሙስሊም እና የሃገሪቷ ሙስሊም በሙሉ ጥያቄ ነው በእርስዎ እምነት እርስዎ በሚያውቁት ማለት ነው የኮሚቴ አባል ነኝ ስላሉ?
- እንግዲህ በእርግጠኝነት የምናገረው ስብሰባ ላይ ያለውን ሰው ነው
- የኮሚቴዎችን ምርጫ የመረጠው የአዲስ አበባ ሰው ብቻ ነው ወይስ ሌሎች ክልሎች ላይም ተመርጧል ?
- ይሄ ምንድን ነው
- እኮ የኔ ጥያቄ የተከበረው ፍ/ቤት ከአዲስ አበባ ውጭ ያለው ሰው ያለው ሙስሊም ፔቲሽን ፈርሟል ወይ ወይም እነዚህነ ሰወች መርጧል ወይ የሚል ነው ጥያቄው
- ኮሚቴውን ማን ጠየቀ የሚለው ተጠይቋል በእሳቸው
- አዎ እኮ እዛው መስኪድ ውስጥ ነው የእሳቸው ጥያቄ የተከበረው ፍ/ቤት
- ሙስሊም ነው የመረጠው ነው ያለው ሲመልስ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት
- ሃጂ ቅድም ከሦስቱ ጥያቄዎች አንዱ መጅሊስ ብዙ ዘመን አድርገዋል የሚል ነበር ብለዋል ይሄ 3 ጥያቄ ስለሆነ ነው ወይስ እርስዎ የሚያውቁት ነገር አለ አድርገዋል ሲሉ ምን ማለት ነው ?
- እንዴት እንዴት
- መጅሊስ ብዙ ዘመን አድርጓል ከተመረጠ ማለቶ ነው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ወደ 30 መስሪያቤት ብለዋል አሁን ያሏቸው ባለስልጣን ጋር ሄደው ነበረ እንዴ አሁን የጠሯቸው በስም ዶ/ር ሽፈራው ብለዋል ዶ/ር ሽፈራውጋ አቤቱታ አቅርበው ነበር ከኮሚቴጋር?
- አዎ
- ምን ተባሉ እዛ መልስ ተሰጣችሁ?
- መልስ ተሰጥቷል ነው የሚሉት ያን መልስ ግን እኛ አልተቀበልንም
- እርስዎ ነበሩ እዛ መልስ ሲሰጥ?
- አዎ ነበርን
- በእለቱ አልተቀበልንም ብላችሁ ነው የወጣችሁት?
- አዎ
- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- አቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ
- ሃጂ ደጋግመው ስለ ሃረሩ ስብሰባ ሲያነሱ ነበር እርስዎ ሃረሩ ስብሰባ ላይ ነበሩ እንዴ?
- በሬዲዮ ነው የሰማሁት እኔ አዲስ አበባ ነኝ
- አልነበሩም በድጋሚ በመስቀለኛ ጥያቄ ስለ ኮሚቴዎቹ ሕዝቡ የመረጣቸው ክፍለሃገር ነው አዲስ አበባ እንዲህ እንዲህ ያሉ ጥያቄዎች ሲነሱሎት ነበር ከጠበቆቹ እርስዎ ሁለት መልስ ነው የሰጡት በመጀመሪያ አይ ዝርዝሩ ወጥቶ ሕዝቡ አፀደቀ ብለዋል በዋና ጥያቄ እኔ ስጠይቆት አሁን በመስቀለኛ ጥያቄ ደግሞ ስለምርጫ ያነሱ ነበር አሁን ይለዩልን አርስ በእርስ የተመራረጠውን ነው ሕዝቡ ያፀደቀው ወይስ ሕዝቡ በቀጥታ ሲመርጥ ነበር ?
- 2ኛውን ምርጫ ነው ያልኩት እኔ ሁለተኛውን ምርጫ እኛ የተመረጥንበትን ከሽማግሌዎች ከምሁሮች ከኡለማዎች ይጨመርበት ወጣ
- ስለዚህ አሁን እናንተና ወጣቶቹ ተመራርጣችሁ ያቀረባችሁትን ነው ሕዝቡ ያፀደቀው ሕዝቡ በቀጥታ መርጧችኋል?
- እኔ የለሁበትም እኛ መጀመሪያ የተመረጡ ሰወች
- እርስዎማ ነገሩን እርስዎ ማን እንደመረጣትም አያውቁም ተመረጡ ተብለው ተነገሮት ቅድም ?
- አይ እሱ እዛው አለሁ

1906
237

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ብዙ ዘመን አድርጓል ምርጫ አልተካሄደምነው አነሳሳችን ነው የምትለኝ
- እሺ ጥያቄውን ግልጽ ያርጉ ቅድም ያነሱትን ለማንሳት ነው?
- ከሦስቱ ካነሷቸው ጥያቄዎች አንዱ
- ሦስቱን አልዘረዝረውም
- የፈለጉትን ብቻ
- 2ኛ ጥያቄ ያሉት መጅሊስ ብዙ ዘመን አደርጓል ለሙስሊሙም አልሰራም ይውረድ የሚለ ነው ብለዋል ከዚህ ጥያቄ ውስጥ መጅሊስ ብዙ ዘመን አድርጓል ሲሉ ብዙ ዘመን በስልጣን ቆይተዋል ነው?
- ይመልሱት ገብቶታል
- አዎ ገብቶኛል
- እሺ ይመልሱ
- አዎ በስልጣን ላይ ብዙ ዘመን አድርጓል ማለት ነው
- መጅሊስ በስልጣን ሲሉ ምንድን አመራሩን ማለቶ ነው?
- አመራሩ በየአራት አመቱ እንዲመረጥ ነበር መጀመሪያ ስንጀምረው አራት ዓመት ቀርቶ አሁን ሁለት ሦስት አራት ያለፈው
- በዚህን ጊዜ
- ለዚህ ነው ሙስሊሙ የተነሳ የተነሳው
- አሃ ሳይመረጥ ነው ወይስ ተመርጦ ነው አራት ጊዜ ያለፈው?
- አልተመረጠም እዛው ነው የሚመራረጡት
- ሃጂ በሃረሩ ስብሰባ ላይ ከፍተኛ የመንግስት አመራር እንደተገኙ ሰምተዋል አደለ?
- ሰምቻለሁ
- ማን ነበረ የተገኙት?
- ከእኛ ከፌደራል መጅሊስ አመራር ጋራ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ፖሊስ
- አይጨነቁ በቃ ዋናውን ነገር ይናገሩ የሚያውቁት ሰው ከሆነ ሰው ኃላፊ ከሆነ ኃላፊ
- ኃላፊ ናቸው የተገኙት?
- አይ ሰውየውን አቃውቃለሁ እንትኑንም ለመግለጽ ፈልጌ ነው ዶ/ር ሽፈራው ነበሩ
- እሺ ሌላ የተገኘ የሰሙት አለ?
- አላየሁም ሌላ አልሰማሁም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ሲፀድቅ ነበሩ ሲፀድቅ ነበርኩ ብለዋል ?
- አዎ
- ስለዚህ የናንተ የፀደቃችሁም ሰወች ሕዝብ ነው በቀጥታ የመረጣችሁ ወይስ እርስ በእርስ ከተመራረጣችሁ በኋላ ነው አሁን ባሉት ፕሮግራም አወልያ ላይ ያፀደቃችሁት?
- እንግዲህ አወልያ ላይ ስማችን እከሌ እከሌ የሚባሉትን
- ስለዚህ እራሳችሁ እርስ በእርስ ተመራርጣችሁ ማለት ነው ?
- እኔ የለሁም እዛ ላይ
- እኮ እርስዎ ሳይኖሩ ሌሎች ተመራርጠው ነው ያፀደቀው አደለም?
- ቆይ እስቲ አቃቤ ሕግ
- የተከበረው ፍ/ቤት እንግዲህ አቃቤ ሕግ በተሻለ ያውቃሉ ብለን እናስባለን ጥያቄ ተጠይቀዋል ምስክሩ ይመልሱ እየዘለሏቸው ነው እየሄዱ ያሉት እሳቸው የሚፈልጉት የተከበሩ አቃቤ ሕግ እሚፈልጉት ካልሆነ እየገፉ ነው እየሄዱ ያሉት እኛ ስንጠይቅ የተከበረው ፍ/ቤት እያስቆመን ነው ይመልሱ ይጨርሱ እያለ እና የተከበሩ አቃቤ ሕግ ምስክሩን ከጠየቁ እስኪጨርሱ ያድምጡ እና ይጠይቁ እና ይሄ የምስክሩን የሚሰጡት ምስክርነት የተሟላ እሪከርድ ፍ/ቤቱ እንዲኖረው ያስችላል ማለት ነው አለበለዚያ አቃቤ ሕግ ብቻ እየገፉ የሳቸውን መልስ እያለፉ የሚሄዱበት
- ተቃውሞ አደለም ማሳሰቢያ ነው ምንድን ነው ጥያቄው እስቲ ግልጽ አርገን እኛም መጀመሪያ ላይ ሲሉ የነበሩት ምንድን ነው እዛ ስብሰባ ተገኝተን የሆኑ ኮሚቴዎች ሌላ ሰው ይጨመር ተብሎ ከሸማግሌዎቹ ይጨመር ተብሎ ሰው በተሰበሰበበት ሄደን እነ እከሌ እነ እከሌን ጨምረናል አጽድቁልን ብለው ነገሩን ብለው ነው ቅድም የተናገሩት ስለዚህ ምንድን ነው የፈለጋችሁት ይሄን መልሰዋል
- ከዛ ደግሞ በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ በሙሉ ሙስሊም ነው የመረጣቸው ብለው መልሰዋል በመስቀለኛ ጥያቄ ስለዚህ አሁን ይለዩልን ከሁለቱ በምርጫ በቀጥታ በሕዝብ ነው የተመረጡት ወይስ ከተመራረጡ በኋላ
- ቆይ እንግዲያስ ጥያቄው ምንድን ነው ስብሰባው ላይ ያለ ሰው ብቻ ነው ወይስ ውጭ ላይ ያለን ሰው ጭምር ነው ለማለት ነው
- አደለም ሁለት መልስ ነው ምስክሩ የሰጡት አንደኛው ከሁለቱ የትኛው ነው ልክ ይለዩልን ነው

1907
1338

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስቲ አብራሩት ይሄንን ገብቶታል ግልጽ ነው
- እኔ እኮ ተናግሬያለሁ አልተረዳኝ እንደሆነ እንጂ መጀመሪያ ወደ ሃያ የሚሆኑ ኮሚቴዎቹን አወልያ ላይ መረጥን
- ማን?
- ሕዝቡ መረጠ ከዛ በኋላ ስብሰባው ተበተነ እንደገና እነዛ ሃያዎቹ ሲያዩት ወጣት አብዛኛው ሲሆንባቸው ከምሁሩም እናርግ ከሃሊሞችም ከሸማግሌዎችም እናርግ ብለው ይሄን ሃሳብ አፈለቁት እኛ ወጣቶች ብቻ ነን በሚል ያንን ይዘው መጡና እዛ ስብሰባ ላይ ይሄን ሃሳብ አቀረቡ
- በሌላ ስብሰባ ማለት ነው?
- በሌላ ስብሰባ
- ጥሩ ስለዚህ መጀመሪያ ሕዝብ የመረጣቸው ሃያዎቹ ቀጥለዋል እስከመጨረሻው?
- ሃያዎቹ አልቀጠሉም በምን ምክንያት እንደሆነ የቀሩም አሉ
- እሺይበቃናል
- ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ ይሄ የሼህ ጣሂር ድርጅት ምን እንደሆነ አላውቅም ብለዋል ሌላ ስለ ሼህ ጣሂር ድርጅት ዝርዝር ያውቃሉ ወይ ሲባሉ አላውቅም ብለዋል ይሄ ድርጅት የሼህ ጣሂር ነው የመንግስት ይሄን ያውቃሉ ?
- ታፔላ አለ ታፔላዉ የሚለው ማስታወሻ ይፈቀድልኛል
- ይግለፁት ችግር የለውም እሺ ያው እንግዲህ ችሎቱ አልተቀበለም በድምጸ የሚያስታውሱት ከሆነ ይቀጥሉ
- አዎ ቅድም ስሙን ነግረውናል የሚያስታውሱትን እስላማዊ ዳእዋ ምናምን ብለዋል ሃጂ
- እኮ ለመድገም ጠፍቶብኝ ነው
- አይ በቃ እንረዳለን እሱን
- ታፔላ እስላማዊ ድርጅት የሚል አለ ውጭ ነው
- ያ ድርጅት የመንግስት ነው ወይስ የማን ነው?
- እስላማዊ ድርጅት ነው የሚለው
- ተቃውሞ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ተመልሷል
- አበቃን

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጨረሳችሁ
- ጥያቄ የተከበረው ፍ/ቤት ይቅርታ ምስክር አወልያ እርስዎ አርብ አርብ ሁሌ ይሄዳሉ እንዴ?
- አይ ሁሌ አልሄድም
- ስለዚህ ባልነበሩበት ጊዜ ምን ሲባል እንደነበረ አያውቁም ?
- ይበቃል አቃቤ ሕግ
- አበቃን
- አቶ ሽፈራውጋ ሄዳችሁ ነበረ እና የተሰጠ ምላሽ አለ እሱን አልተቀበልንም አሉ ምን ምላሽ ተሰጥቶ ነው ያልተቀበላችሁት?
- ወደፊት ምርጫ ይካሄዳል አለ ወደፊት የሚባለው ቀን ይቆረጥልን እዛው ለሰወች መልስ እየጠበቁ ነው ምን እንደምንል መልሱን ይሄንን /ግልጽ ያልሆነ/ ለዚህ መልስ አልተሰጠንም በዚህ ወጣን እኛም የሄንኑ መልስ አልተናገርንም
- ሌላ የለም ?
- የለም
- እሺ ሌላው ጥያቄ መጨረሻ ላይ ሲጠየቁ 20 ሰወች አስቀድመው ተመርጠው ነበር ከዛ በኋላ በሌላ ቀን እኛ ከምሁርም ከሽማግሌም ከሌላም ተጨምሯል ሃያዎቹ በሙሉ አልቀጠሉም ለምን እንደተውት አላውቅም ብለዋል እና ሃያዎቹ በሙሉ ነው የተቀየሩት በሙሉ አልቀጠሉምሲሉ ወይስ ከሃያዎቹ የተወሰነ ሰው ቀርቷል?
- እንግዲህ እኔ እንደሚመስለኝ ሃያዎቹ በሙሉ ለመስራት ፍቃደኛ ያልሆነ ያለ ይመስለኛል እዛ ውስጥ እነዛም ተጓድለውባቸዋል ሲጓደሉ እንግዲህ ያው ከእኛ ሞልተው ወደ 17 ደረሰን
- ኦኬ ከሃያዎቹ የመጣው ስንት ነው የሚሆነው እስቲ የሚያስታውሱት ካለ የቀረው ስራ ውስጥ ?
- ከሃያዎቹ እንግዲህ ያው ሃያው ይመረጥ እንጂ እከሌ ብዬ የማውቀው የለኝም
- እሺ ሌላው ደግሞ ሃያዎቹን እኛ ነን የመረጥነው ብለዋል እሱ ምርጫ ነው የአወልያ መስኪድ ብቻ ነው ወይስ የሁሉም የሙስሊም ጥያቄ ተብሎ ሲጠየቁ የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ብለው መልሰዋል ቅድም እና እሱን እስቲ እዛ አካባቢ ያለ ነው የክፍለሃገር ምናምን ሲሉ አጠቃላይ?

1909 3ረ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምርጫው በመጀመሪያ ደረጃ የሙስሊሙ ነው አወልያ የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ነው ጥያቄውም የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ነው ፌደራል ማለት ያው ሙስሊም ነው ይሄ መጀመሪያ ይሄን መጀመሪያ ካደረግን በኋላ ክፍለሃገሩን ለማጠቃለል ክፍለሃገሩን የምንጨምር ከሆነ የፊርማ መምጣት አለበት ክፍለሃገሩን ወከለን ፊርማ ይምጣልን ብለን እንደገና የክፍለሃገሩ ፊርማ መጣልን
- እሺ እናመሰግናለን ምስክር ጨርሰዋል ይመለሱ እሺ ያው ሰዓት ትንሽ ሄዶብናል አጭር ምስክር ነው ብላችኋል ስለዚህ ስምንት ተኩል እንገናኝ
- ጠዋት የነበረው ችሎት ያው ከሰዓት በኋላ ቀጥሏል የመዝገቡ ጠዋት የነበረው ነው ቀኑም አልተለወጠም ዳኞች አልተለወጡም ከሳሽ አቃቤ ሕግ ሁሉም አሉ አልተለወጡም ተከሳሾች እነ አቡበክር አህመድ ከሰዓት በፊት የቀረቡት 4ኛ ተከሳሽ ቀርቧል የትኛው ናቸው 29ኛ እሳቸው ናቸው እሺ እነአቡበክር አህመድ 29ኛ ተከሳሽን ጨምሮ ቀርበዋል የተከሳሽ ጠበቆች ከሰዓት በፊት ጠዋት የነበሩት እሉ ከሰዓት በኋላ ሁለት ጠበቆች ተጨምረዋል
- ሃሰን ሁሴን እና አዲስ መሃመድ
- እሺ ቀርበዋል እሺ ጠዋት ከሰዓት የተቀጠረው ቀሪ የአቃቤ ሕግ ምስክር ለመስማት ነው አቃቤ ሕግ ቀሪ የአቃቤ ሕግ ምስክር ያቅርቡ
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም
- ምያለሁ
- እሺ ምስክር እንኳን ደህና መጡ አሁን ያው ለምስክሮች ደህንነት ሲባል የመጀመሪያ ስሞን ብቻ እንዲጠቅሱ ነው የሚፈለገው የመጀመሪያ ስም የአባት የአያት አያስፈልግም ስለዚህ የመጀመሪያ ስሞ ማን ነው ?
- አቶ ሰይድ
- ስንተኛ ናቸው አቃቤ ሕግ?
- እሺ በፍ/ቤቱ 30ኛ ተራ ቁጥር ላይ ነው ያሉት በአቃቤ ሕግ ክስ በቁጥር 117 ላይ የተጠቀሱ ምስክር ናቸው ለምንድን ነው እዚህ የመጡት ?
- ለምስክርነት
- በነማን ላይነው የሚመሰሩት?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንግዲህ እኔ መጀመሪያ ደህንነቶች አነጋገሩኝ
- ቆይ ቆይ እስቲ አሁን የሚመሰክሩት በማን ላይ ወይም እነማን በተከሰሱበት ነው?
- በ3 ሰወች ነው የተነገረኝ
- ማንና ማን ናቸው?
- ሼህ ሱልጣን
- ሼህ ሱልጣን ማን ናቸው የአባታቸው ስም?
- ሼህ ሱልጣን አማን
- እሺ ሌላ?
- ሼህ አብዱራህማን ዑስማን
- ሌላ?
- ዶ/ር ከማል
- ከማን ማን ነው?
- ሃጂ ገለቱ
- ሌላ የለም?
- በቃ
- እነዚህን ሰወች ያውቋቸዋል?
- አዎ አውቃቸዋለሁ
- ሊያሳዩን ይችላሉ?
- አዎ
- እስቲ ይነሱና ያሳዩን ካለዩዋቸው ቆመውም ቢሆን እንዲያዩት ይደረጋል ተቀምጠው መለየት ከቻሉ ሞክሩ ተነስተው ይሞክሩ
- እሺ 17ኛ ተከሳሽን ለይተው አሳይተዋል ሌላ እሺ 29ኛ ተከሳሽን ለይተው አሳይተዋል ሌላ እሺ 27ኛ ተከሳሽን ለይተው አሳይተዋል እሺ ይመለሱ
- ከነዚህ ከጠቀሷቸው ሰወች ጋር ፀብ ወይ ዝምድና አላችሁ?
- የለንም
- እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ
- እሺ የተከበረዉ ፍ/ቤት አቶ ሰይድ አሁን የጠቀሷቸው ሃጂ ሱልጣን አማን ሼህ አብዱራህማን ኡስማን እና ዶ/ር ከማል ሃጂ ገለቱ ዮት እንደሚያውቋቸው መቼ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

እንደሚያውቋቸው እና ምን ሲያደርጉ እንደነበረ ይሄንን የሚያውቁትን እርስዎ የሚያውቁትን የምስክርነት ቃል ለተከበረው ፍ/ቤት በድጋሚ ያው በዝርዝር እንዲገልፁ ነው የምጠይቀው የት ነው የሚያውቋቸው የት ሲሰሩ ምን ሲሰሩ?

- እኔ እንግዲህ የሳውዲ አታች ቢሮ ሰራተኛ ነበርኩኝ የዛሬ ሁለት ዓመት ከምናምን
- መቼ ነው አመተምረቱ?
- እንግዲህ የዛሬ 3 ዓመት በለው የማውቃቸው ሼህ ዶ/ር ከማል
- እሺ ምን ሲያደርጉ ነው የሚያውቋቸው ?
- ቢሮ ባለሁበት ሰዓት ቢሯችን ይመጡ ነበረ
- ምን ሊያደርጉ ነው የሚመጡት?
- እንግዲህ እኔ ቢሮ ነው የማያቸው ነገር ግን እዛ ስሰማ ደሞዝ ሊቀበሉ እንደሚመጡ ነው የምሰማው
- ምንድን ነው የሚቀበሉት ደሞዝ ለምንድን ነው የሚከፈላቸው?
- አስተማሪ ስለሆኑ ነው መሰለኝ
- ምንድን ነው የሚያስተምሩት?
- የሚያስተምሩት ቁርአን እና ሃዲስ
- እሺ ማን ማን ናቸው የሚመጡት?
- ምን አሉኝ
- የሚመጡት እዛ አሁን ያሉበት ቦታ እዚህ ሳውዲ
- የት ነው ያሉት ቦታውን ?
- የሳውዲ አታሼ ቢሮ
- እሚመጡት መቼ ነው ምንድን ነው የሚያስተምሩት ምንድን ነው የሚከፈላቸው ?
- የሚያስተምሩት እንግዲህ እኔ ኤግዛክትሊ ስራቸው ምን እንደሆነ አላውቅም ነገር ግን ሲያስተምሩ ነው የማያቸው
- ማን ማን ነው የሚያስተምሩው?
- ዶ/ር ከማል ሼህ ሱልጣን አልፎ አልፎ ሼህ አብዱራህማንም አልፎ አልፎ
- ይሄ የሚከፈላቸው ክፍያ ስለሚያስተምሩ ነው ወይስ ምንድን ነው ?
- ምን አሉኝ
- ክፍያው ታዲያ እሚፈፀመው እንዴት ነው ማለቴ ነው?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ክፍያው የሚፈፀመውማ ወርሃዊ ነው
- ምንድን ነው ቅጥር ነው ምንድን ነው ነገሩ?
- እንግዲህ ቅጥር መሆኑን ቢሮ ነው የሚያውቀው ቅጥር ነዋ ቅጥር አደለም እኔ እላው ቢሮ አካባቢ ማኔጅመንት አካባቢ አደለሁም
- ግን እርስዎ የሚያውቁት በየወሩ እየመጡ ሲከፈላቸው ነው የሚያውቁት ?
- እንደዛ እሰማለሁ እንጂ ሲከፈላቸው አላየሁም
- ግን እንደሚከፈላቸው ግን ይሰማሉ?
- እሰማለሁ
- ሦስቱም?
- ሦስቱም አዎ
- ከመቼ ወር ጀምሮ ነው የሚከፈላቸው?
- እኔ እንግዲህ እስከማውቃቸው ድረስ 3 ዓመት ነበረ የላሬ ሁለት ዓመት ከምናምን ነው የለቀቁት ቢሮውን እላ ያለው እንትን ሲመጡ ነበር
- እየመጡ በየወሩ ሲወስዱ ነበረ?
- አንዳንድ ጊዜ በየወሩ ይመጣሉ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወሩም አልፎ ሊመጡ ይችላሉ ከዛ በፊትም ይመጣሉ
- አዎ ማለት አሁን ይሄ የሚከፈላቸው ክፍያ ለምን አገልግሎት ለምን እንደሆነ ማን እንደሚከፍላቸው በግልጽ የሚያውቁት ነገር አለ?
- የሚከፍላቸው ሳውዲ ኤምባሲ ነው
- ኤምባሲው እራሱ?
- ኤምባሲ እራሱ ነው በአታቼ በኩል ነው
- ምስክር እነዚህ 3 ሰወች በወር ምን ያህል ብር እንደሚከፈላቸው ያውቃሉ?
- አላውቅም
- ቅድም ሲያስተምሩ አይቻለሁ ብለዋል አስተማሪዎች ስለሆኑ ነው የሚከፈላቸው ሲያስተምሩ አያለሁ ዶ/ር ከማል እና ሌሎቹም ደግሞ አልፎ አልፎ ብለዋል?
- አዎ
- የሚያስተምሩት ነገር ተከታትለው ሰምተው ያውቃሉ?
- ዶ/ር ከማል ሰምቻለሁ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የሌሎቹንስ ?
- የሌሎቹን አልሰማሁም
- ጥሩ እርስዎ አሁን በገለፁልን ተቋም ውስጥ ሰራተኛ ኖት ግን ተቋሙ የት ነው የሚገኘው?
- ተቋሙ የሚገኘው እኔ በነበርኩበት ሰዓት ቦሌ
- አሁንስ?
- አሁን የት እንዳለ አላውቅም
- ለቋል ከቦሌ?
- ለቋል አዎ ድሮ ቢሮ እኔ የነበርኩበት ለቋል ሰምቻለሁ
- ስሙ ማን ነው?
- የማን
- ያ ተቋም
- ያ ተቋም አታቼ ቢሮ ነው ስሙ
- አታቼ ቢሮ ብቻ ነው ?
- እንግዲህ በአረብኛም ከፈለግክ ሙልሃቅ ይሉታል
- ሙልሃቅ?
- አዎ
- አበቃን ዋና ጥያቄ
- መስቀለኛ ጥያቄ አላችሁ የተከሳሽ ጠበቆች
- አቶ ሰይድ ምስክሮችን ከነዚህ ከሦስቱ ከገለጿቸው ተከሳሾች ውጭ ሌሎቹን ተከሳሾች አይተዋቸው ያውቃሉ በአይን ወይም ሌላ የሚያውቁበት መንገድ አለ ?
- ምንም የለም
- ተከሳሾችን አይተዋቸዋል ሌሎቹን ነው የምሎት ?
- ከነዚህ ውጭ ነው የምትለኝ?
- እ
- አዎ አውቃቸዋለሁ
- በምን ያውቋቸዋል?
- ይሄን ጥያቄ እንቃወማለን የተከበረው ፍ/ቤት

1914

345

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ
- በመጀመሪያ ደረጃ እኛ ስለ ሌሎቹ ተከሳሾች አደለም እያልን ያለነው ቅድም እሳቸው በዋና ጥያቄ ስለነዚህ ሰወች ባስያዝነው ጭብጥ ወይም ሊመሰክሩልን ባሰብነው በሚያውቁት አስመስክረናል እንጂ አሁን እያንዳንዱ ተከሳሾች የት ሲያስተምሩ የት ምን ሲሉ እንደነበረ ይሄን በሚመለከት የቀረበው ጥያቄ
- ስለሌሎቹ ተከሳሾች ነው?
- አዎ ሌሎች ተከሳሾች ነው እየጠየቁ ያለው እኛ ስለ ሦስቱ ተከሳሾች ነው ያቀረብነው የተከበረው ፍ/ቤት አሁን የመሰከሩት ማለት ነው ከዛ ውጭ ስላለው ባልመሰከሩበት ሊጠየቁ አይገባም ነው በአጭሩ
- እሺ ግልጽ ነው መልሳችሁን
- የተከበረው ፍ/ቤት እኛ ስለሌሎቹ አደለም አቃቤ ሕግ አልተረዱኝ እንደሆነ አላውቅም ስለ ሌሎቹ ሳይሆን የጠየቅኩት ስለ ሦስቱ ነው የት ታውቃቸዋለህ ከዚህ ውጭ ነው ያልኩት አቃቤ ሕግ አላዳመጡኝ እንደሆነ አላውቅም ስለዚህ ከዚህ ውጭ ሌላ የምታውቅበት መድረክ የለም ወይ እነዚህን ሰወች ነው ዶ/ር ከማል
- እሺ በዚህ መንገድ ከሆነ ቀጥሉ
- ዶ/ር ከማልን ?
- ዶ/ር ከማል መስኪድ ሲያስተምሩን ነው የማየው
- እሺ ሼህ ሱልጣን ?
- ሼህ ሱልጣን ድርጅት አላቸው ገመያታል ብር የሚባል ድርጅት ሼህ አብዱራህማን ኡስማን ያው መስኪድ አካባቢ ነው የምንተዋወቀው
- በሌላ ያወቁበት ነገር የለም እነዚህን ሰወች አሁን በታሰሩበት ጉዳይ የሚያውቁት ነገር የለም ?
- ምንም የለም
- ከነሱጋር ሌላጋ የሄዳችሁበት ቦታ የለም በሽምግልና?
- በሽምግልና ደረጃ የሄድንበት ቦታ የለም
- የሚያውቁትም የለም?
- የለም
- መንግስት መስሪያቤት አልሄዳችሁም ከነሱጋር በሽምግልና ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሼህ ሱልጣን ባሉበት አልሄድንም ግን
- እሺ ማን ባለበት ሄዱ?
- በእንትና ሼህ ሃጂ ባሉበት ሄደናል ሽምግልና
- የት ሄዳችሁ?
- እዚህ ጁነዲን ቢሮ
- መቃወሚያ አለኝ
- እሺ
- ያው ፍ/ቤቱ እንደተከታተለው ያስያዝነው ጭብጥ እኚህ ምስክር ሦስቱ በስም የተጠቀሱት ተከሳሾች ከሳውዲ አረቢያ የሃይማኖት አታሼ ክፍል በየወሩ ገንዘብ ይወስዱ እንደነበረ ይሄ ነው ጭብጡ ይሄንኑ ነው ያስረዳነው ከዚህ ጭብጥ ውጪ አሁን በተከበሩ ጠበቃ እየተነሳ ያለው ጥያቄ ቶታሊ ከምስክሩ ጭብጥ ውጪ ነው ስለ ሽምግልና ስለ መንግስት ቢሮ
- ስለዚህ ያልተነሳ ጥያቄ ነው ነው?
- አዎ በኋላ በመከላከያ ማስረጃ ሊያቀርቧቸው ይችላሉ እንጂ አሁን
- እሺ ግልጽ ነው
- ምላሽ ትሰጡበታላችሁ
- የተከበረው ፍ/ቤት እኔ ምስክሩን መጠየቅ የፈለግኩት አውቃቸዋለሁ ስላሉ በምን በምን መልኩ ነው የምታውቋቸው በተለይ አሁን ፍ/ቤቱ አቃቤ ሕግ በእርግጥ ያስመሰከረው ይሄንን ነው በክሱ ግን ዋና ጭብጥ ያስያዘበት ክስ ከኋላው አለ ስለዚህ ምስክሩ ስለዛ ክስ የሚያውቁትን ነገር እንዲያስረዱነው የጠየቅኩት ጭብጥ ማለት አጠቃላዩን እንጂ እያንዳንዱ ምስክር መጥቶ የመሰከረው ብቻ አደለም ስለዚህ አጠቃላዩን ነገር መጠየቅ የሚከለክል ሕግ የለም ይሄ ደግም መስቀለኛ ጥያቄ ስለሆነ እችላለሁ እያልኩ ነው የተከበረው ፍ/ቤት ሕጉ ስለሚፈቅድልኝ
- እሺ ብይን ሰጥተናል የተነሳውን ጥያቄ ከግራ ቀን አዳምጠናል እንደተመለከትነው የተነሳው ጥያቄ የሽምግልና ጥያቄ ነው ምናልባት መስቀለኛ ጥያቄ ሊነሳ የሚችለው በዋና ጥያቄ የተነሳ ነው ምናልባት ክሱ ብዙ ሊሆን ይችላል ከዛ በላይም ሊሆን ስለሚችል እያንዳንዱ ምስክር ሊመሰክርበት ባሰበበት ነው የሚመጣው ስለዚህ አቃቤ

1916

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ሕግ በዚህ በሽምግልናው ጉዳይ አሁን በተባለው ጉዳይ ያነሳው ጥያቄ የለም ስለዚህ ሌላ ጥያቄ አልተነሳም

- ይሄ የሳውዲ ኤምባቢ አታቼ የተለየ ነው እንዴ ከሙልሃቅ ቅድም ያሉት?
- አንድ ቢሮ ነው ግን ለብቻው ቢዩልዲንግ ነው እንጂ አንድ ነው
- አንድ ናቸው ?
- አዎ
- የሙልሃቅ ያሉት ወይም አታቼ ምንድን ነው አገልግሎቱ እስቲ?
- አገልግሎቱ ከኤምባሲ የማመጡ ዶክመንቶች አንዳንድ ድርጅቶች አሉ ኤምባሲ ሄዶ እርዳታ ምናምን ይጠይቃሉ እርዳታውን ሲጠይቁ ያ ዶክመንት ወደኛ ይላካል ወደኛ ቢሮ ወደኛ ቢሮ ፎርም አለ ፎርሙን ከሱጋ ይላካል ፎርሙ ምንድን ነው የሚለው እነዚህ ድርጅቶች ሕጋዊ ናቸው ከፍትህ ሚ/ር ፍቃድ አላቸው ኤኒዌይ የመንግስትን ዶክመንት ያሚላሉ ወይ ብለው እንጠየቃለን እኛ እኛ ደግሞ ፍቃዳችሁን አምጡ ደውለን ስልክ ስልካቸውን የምናውቅ ከሆነ ፍቃዳችሁን አምጡ የፍትህ ሚ/ር የሰጣችሁ ፍቃድ አስፈላጊ የሆነ ዶክመንትን እንጠይቃቸዋለን እሱን አያይዘን ድጋሚ ወደ ኤምባሲ ይመለሳል በአለቃችን መሰረት
- እሺ እርዳታው ምን ምን ነበር ምን ምንድን ነው የሚያካትተው እርስዎ የሚያውቁት እርዳታ?
- እኔ እስከማውቀው ድረስ እርዳታው ውሃ ጉድጓዶች ይመጣሉ አንዳንድ መስኪዶችም ይመጣሉ ክልሊኒኮችም ይመጣሉ ወላጅ አልባ ሕፃናቶች መርዳት ይመጣል ያም አካባቢ ደግሞ ይሄ ቴምር ጥያቄ ይመጣል አረፋ አካባቢ ይሄ የእርደ ሥጋ ለመጠየቅ ይመጣሉ እነዚህ እነዚህ ናቸው
- ስለዚህ ሙልሃቅ የሚሉት ድርጅት በዚህ በሳውዲ ኤምባሲ ውስጥ ያለው እነ ሼህ አብዱራህማን እነ ዶ/ር ከማል ያሉበት ድርጅት ይሄንን ነው የሚሰራው በዚህ እርዳታ ድርጅት ውስጥ ነው የሚሰራው ?
- እሱን ማጣሪያ ሥራ ብቻ ነው የሚሰራው ሥራውን ዳይሬክት የሚፈጽመው ኤምባሲ ነው
- እነሱ የማጣራቱን ስራ ነው የሚሰሩት?
- አዎ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አቶ ሰይድ ቅድም ደሞዝ ለመቀበል ይመጣሉ ብለዋል ደሞዝ ሲሉ ምን ማለት ነው ክፍያ ይቀበላሉ ለማለት ነው የደሞዝ ትርጉሙን ያውቁታል ?
- ደሞዝ እንግዲህ እኔ የማውቀው ለነገሩ እኔ እንደነገርኳችሁ አላየሁም ሲቀበሉ ብር እንደዚህ ሲቀባበሉ አላየሁም ነገር ግን ትጠይቃለህ እንግዲህ እዛ ሰራተኛ ሆነህ እነዚህ ሼህ እከሌ ለምንድን ነው የሚመጡት ምናምን ደሞዝ አላቸው ትባላለህ ምንድን ነው ደሞዙ እንዴት ነው የማውቀው ነገር የለኝም
- ከነ ዶ/ር ውጪ በዚህ መልክ የሚከፈለው ሰው አለ ከሦስቱ ውጪ ቅድም ድርጅቱ የሚሰራውን ስራ ገልፀዋል?
- አዎ
- ሌሎች የሚከፈላቸው አሉ?
- አሉ አዎ
- ጨረሳችሁ
- አቶ ሰኢድ አሁን ለነዚህ ለሦስቱ ተከሳሾች የሚሰጠው ደሞዝ ብለው ያሉት የእርዳታው አካል ነው አደለም ለነዚህ ሦስት ተከሳሾች ይሰጣል ያሉት ክፍያ ወይም ደሞዝ ቢሮው ወይም ድርጅቱ ከሚሰጠው የእርዳታው አካል ነው አደለ?
- አልገባኝም ጥያቄው
- የእርዳታው አካል ነው ወይ ክፍያው?
- ክፍያውን የሚፈጽመው
- አይ ለነሱ የሚሰጣቸው ክፍያ የእርዳታው ድርጅቱ እርዳታ ብሎ የሚሰጠው የዛ አካል ነው ወይ?
- አሁንም አልገባኝም ጥያቄው
- እሺ ክፍያ ይከፈላቸዋል ያሉት ከርዳታውጋር ተያይዞ ነው ወይ?
- እስቲ ቆይ የምን እርዳታ ነው እሱን ግለፁት እና?
- ድርጅቱ እርዳታ ይሰጣል ውሃ ይቆፍራል የቲሞችን ይረዳል እንዲሁም ክሊኒኮችን ብለው ቅድም
- እና በደሞዝ ሳይሆን በእርዳታ መልክ የሚሰጣቸው ነው
- እንደዛ ነው የጠየቅኳቸው

1918

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይሄ ደሞዝ የሚከፈላቸው በደሞዝ መልክ ሳይሆን በእርዳታ ስም ነው የሚሰጣቸው ነው ጥያቄው እንደዛ ነው ወይ
- ለዚህ እኮ ነው እኔ ደሞዝ ይሁን እርዳታ ይሁን ምን ይሁን ደሞዝ ነው የሰማሁት
- ግልጽ ነው ቀጥሉ ሌላ
- እንጂ ከዚህ ክፍያ ጋር ተያይዞ ይሄን እንሰራላችኋለን
- ጠበቃ ያው ይህ ተመልሱል ግልጽ ነው መድገሙ ምን ያስፈልጋል
- እሺ ከዚህጋ ተያይዞ ግን ሥራ ይህን ትሰራላችሁ ተብሎ አልተሰጣቸውም አደለም?
- አይመስለኝም
- ቅድም በደህንነቶች ተጠይቁ ነበር ያሉትን እስቲ ይንገሩን?
- እንቃወማለን
- ጥያቄው ግልጽ አደለም
- ለምስክሩ ግልጽ
- ለኛም ግልጽ
- ቅድም ምስክርነታቸውን ከመስጠታቸው በፊት እኔ እንግዲህ የመጣሁት በደህንነት ቢሮ ተጠይቁ ነው ስላሉ ይጠቅመናል ብለን ስለምናስብ እንዲያብራሩልን
- ትንሽ ቀየር እናርገው የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ አስተካክሉት
- ምስክርነት በመስጠታቸው የሚሰጉት ነገር አለ የለም የሚለው በዚህ መልክ ?
- ተቃውሞ አለን ለዚህም
- ምስክር በመሆናቸው
- አሁን እዚህ መጥተው በመመስከራቸው ወይም ባለመመስከራቸው በነፃ ፍቃዳቸው ነው ወይስ ተገደው የሚሰጉት ነገር አለ የለም በዚህ መልክ ቢስተካከል
- እሺ ምንድን ነው የናንተ ተቃውሞ
- /ግልጽ ያልሆነ/
- የመጀመሪያው ግልጽ ነው የሁለተኛው ተገደው ነው የመጡት ነው ወይስ ተመልሰው የሚሰጉት ነገር አለ
- አደለም የ2ኛውን ጥያቄ ትተነዋል በመጀመሪያው ላይ ምስክርነት ከመስጠታቸው በፊት
- ኦኬ በመጀመሪያው በደህንነት ቢሮ ተጠይቄያለሁ የሚለው

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ምላሽ ስጡበት በመጀመሪያው ላይ
- የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም ምስክሩ እዚህ እንደተቀመጡ ገና ሳይጠየቁ እንደዚህ ብለው የጀመሩት በደህንነት ብለው የጀመሩት እንደዋና ጥያቄ የሚቆጠር አደለም ምክንያቱም ገና ስማቸውን ተጠይቀው የመጡበትን በነማን ላይ እንደሚመሰክሩ ሲጀምሩ ነው እዚጋ ያቆሙት በእንጂ ይሄንን በዋና ጥያቄ ሆኖ እኛ ይሄንን በጥያቄ መልክም አላቀረብንም እላቸውም ደግሞ ከአቃቤ ሕግ ለቀረበው ጥያቄ ይሄንን በዝርዝር መልስ ነው ብለው አልሰጡም ስለዚህ በአጭሩ በዋና ጥያቄ አልተጠየቀም እና ውድቅ ይደረግልን
- መልስ እንስጥበት የተከበረው ፍ/ቤት
- ጥያቄውን አቀረቡ ምላሽ ተጠሰበት
- የግራ ቀኙን ተቃውሞ አዳምጠናል ምንድን ነው አሁን መጨረሻ ላይ የተነሳው ጥያቄ በአቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ሆኖ አልተነሳም መጀመሪያ ምስክሩ እንደጀመሩ የሆነ ቃል ጀምረው ነበር እሱ እንዲቋረጥ ተደረገና ዋና ጥያቄው ሌላ ነው የተጠየቀው ስለዚህ የዋና ጥያቄ አካል አደለም ስለዚህ ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- አቶ ሰይድ ቅድም ዶ/ር ከማል ያስተማሩትን እንዳዩ ወይም እንደሰሙ ነግረውናል የኃይማኖት ትምህርት ቁርአን እና ሃዲስ እንደሚያስተምሩ ነግረዋል በተለምዶ ከሚሰጠው የተለየ ነገር ያስተምራሉ እንዴ?
- እኔ አልሰማሁም የተለየ ነገር ሁሉም ያለ ነገር ነው የተለየ ነገር አልሰማሁም
- ቁርአን እና ሃዲስ በየቦታው የሚሰጥ ነው አደል የሚለው ትምህርቱ?
- ኤግዛክትሊ እሱ ነው
- አቶ ሰይድ ቅድም ሲመሰክሩ ሼህ ሱልጣን ጀምእየደልብር የሚባል ድርጅት አላቸው ብለዋል ይሄ ድርጅት ምን አይነት ድርጅት ነው ?
- ድርጅቱ እኛጋ የመጣውን እኔ እንትኑን አይቼው ነበር ድርጅታቸው እነሱ የልማት ድርጅት ነው
- የልማት ድርጅት ከሆነ የሚተዳደረው በቦርድ እና በጠቅላላ ጉባዔ ነው አደል?
- ትክክል
- ቅድም ሲናገሩ የዶ/ር ከማል እና ሼህ ሱልጣን አልፎ አልፎ ሲያስተምሩ አውቃለሁ ብለዋል የአክራሪነት ትምህርት አያስተምሩም አደል?
- እኔ አልሰማሁም የአክራሪነት ትምህርት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ዶ/ር ከማል ትምህርት ያስተምራሉ ብለዋል እሳቸው የተማሩት ትምህርት ምን እንደሆነ ያውቃሉ የሳቸው ትምህርት ምን ሆኖ ነው እሳቸው የሚያስተምሩት ወይም ትምህርታቸው ምንድን ነው እሳቸው?
- ትምህርታቸው እኔ አሁን እንግዲህ ቀኑ እረዝሟል ግን
- እሚያውቁ ከሆነ ብቻ ነው አይ ግድ የለም
- ትምህርታቸው ዶክትሬታቸው በምንድን ነው ነው?
- ያውቁታል የትምህርት ደርጃቸውን?
- ዶክተር ናቸው
- በምንድን ነው ዶክትሬትነቱ?
- ዶክተር በእስልምና ኃይማኖት
- እሺ አመሰግናለሁ
- አቶ ሰይድ ቅድም ይሄ ሙልሃቅ ድርጅት እያጣራ የተለያየ እንትኖችን ያጣራል ብለው ነበር እነዚህ ካጣራቸው ውስጥ ከመጅሊስ ድጋፍ ያመጡ ያጣራቸው ወይም ከሌላ ከመንግስት መስሪያቤት ከቀበሌም ሊሆን ይችላል በዚህ መልክ ያጣራችሁት ሰው አለ ወይም ያጣራችሁት ድርጅት አለ?
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለ
- እሺ ምንድን ነው መቃወሚያው
- ቅድምም አቶ ሃሰን ይመስሎኛል እሳቸውም ሲያነሱ ላለማቋረጥ ነው የተውነው ቅድምም ተመሳሳይ ጥያቄ ጠይቀው ነበር ምስክሩ ቅድም ፍ/ቤቱ ብይን በሰጠው መልኩ የመሰከሩት ነገር ግልጽ ነው በቃ የመሰከሩት በቃ የመሰከሩት ነገር ሦስቱ ሰወች ከኃይማኖት አታሼ ክፍሉ ገንዘብ በየወሩ ይቀበላሉ ሲባል ሰምቻለሁ ይሄ ነው አሁን ስለምስክሩ የለት ተእለት ስራ በየቀኑ የምታጣሯቸው ድርጅቶች እነማን ናቸው ከመጅሊስ የድጋፍ ደብዳቤ ያመጡት እነማን ናቸው እኛን አይጎዳም ቢናገሩት ምስክሩ ግን ጊዜንም ይፈጃል አግባብነትም የለውም ከጭብጡም ውጪ ነው በዋና ጥያቄም አልተነሳም
- እሺ ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ ቅድም የኢሰመ[illegible] ሙልሃቅ የሚባል ድርጅት እንዳለ ስራው ምን እንደሆነ ገልፀዋል የሚያጣራበትን ሁኔታ እንዲህ ካጣራቸው ሰወች ውስጥ በዚህ

ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/

መልክ ቅድም በገለጽኩት መልክ ያጣራቸው ሰው አለ ወይ የለም የሚለው ነው ተያያዥነት ያለው ነው እና

- እነማን ነው ያጣሯቸው ቅድም ድርጅቱ ሙልሃቅ የሚባለው አታቼ ምንድን ነው ስራው ሲባል ከዚህ ይሄን ያመጣ ይሄን ሰነድ ያመጣ ይሄን ይሄን ያጣራና ኤምባሲው ክፍያ ይከፍላል ብለው መልሰዋል አሁን እነዚህ ያጣራቸው ሰወች ውስጥ አሁን ማጣሪያ ውስጥ ከሚገቡት ነገሮች ውስጥ ከመጅሊስ ወይም ከመንግስታዊው ከሌሎችም ድርጅቶች በኩል ተጠይቆ በዚህ መልክ ያጣሩት ነገር አለ ወይ ቅድም ከመለሱት ጋር ተያይዞ የቀረበ ነው እና አግባብነት አለው
- ባልደረባዬ ካብራሩት በተጨማሪ ምስክሩ ሙልሃቅ የሚባለው ድርጅት የእርዳታ ድርጅት ነው ወይም እርዳታ ይሰጣል ብለዋል እና ይሄን እርዳታ ለሌሎች ድርጅቶች ለሌሎች ግለሰቦችስ ሰጥቷል ወይ የሚልነው ጥያቄያችን ተያያዥ ነው ከጭብጥ ውጪም አደለም ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- ሁለቱ ግን የተለያየ ጥያቄ ነው አሁን የጠየቀው ሁለት ጥያቄ ነው
- ሦስተኛም ጥያቄ አለ የተከበረው ፍ/ቤት እኛም አካሄድ ላይ
- ቆይ ቆይ እኛ እኮ እያጣራን እኮ ነው ስለዚህ የመጀመሪያውን ብቻ ያው ጊዜ ላለማጥፋት ጠበቃ ያነሱት የመጀመሪያው ጥያቄ ተገቢ ነው ብለናል ተያያዥነት ያላቸው ናቸው በ2ኛ የተነሳው በዚህ ሰበብ የተነሳው ጥያቄ ግን ተገቢ አደለም እንደዚህ አይነት ሁለት ጥያቄ ይዛችሁ መቅረብም ተገቢ አደለም ሁለቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ናቸው ስለዚህ የመጀመሪያውን ጥያቄ መሰረት አርጋችሁ ቀጥሉ
- እሺ አቶ ሰይድ ቅድም የናንተ ሙልሃቅ የሚቀርቡለትን አቤቱታ እያጣራ ከዛ ክፍያ ኤምባሲው እንደሚከፍል ተናግረውናል በዚህ መልክ እናንተ ካጣራችሁት ውስጥ ከመንግስት መስሪያቤት ከግለሰብ ከመጅሊስ በኩል እርዳታ ተጠይቆ ያጣራችሁበት ሁኔታ አለ?
- አልገባኝም ጥያቄው
- ቅድም ሙልሃቅ ምን ይሰራል ሲባል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ማሟላት ያለበትን ነገር እንደምታጣሩ ገልፀዋል እርዳታ የሚጠይቀውን ሰው ሙልሃቅ ይሄን ያጣራና ክፍያውን ኤምባሲ ይከፍላል አላሉኝም ተሳስቼ ከሆነ ያርሙኛል?
- አዎ ትክክል

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ በዚህ ማጣራት ሂደት ውስጥ ከመጅሊስ ወይም ከእስልምና ጉዳይ ድጋፍ ይዘው መጥተው የጠየቁ ከመንግስታዊ መስሪያቤት ወይም ከሕዝባዊ ድርጅቶች ድጋፍ ይዘው መጥተው ጠይቀምት ያጣራችሁበት ሁኔታ አለ?
- መአት አለ
- አቤት
- አለ ብዙ አለ ከመጅሊስ ድጋፍ ይዞ የሚመጣ ከመንግስታዊ ይዞየሚመጣ አለ
- መጅሊስ እራሱስ ጠይቋችሁ ያውቃል?
- መጅሊስ ዳይሬክት ጠይቆ አያውቅም
- ጥሩ በዚህ መልክ ከተጠየቀው ውስጥ ተስተናግዶ ያውቃል የተከፈለው መኖሩን ያውቃሉ በጠየቀው መሰረት?
- መጅሊስ
- በመጅሊስ በኩል በመንግስት በኩል በመንግስት መስሪያቤቶች በኩል ተጠይቆ እርዳታ የተሰጠው ክፍል አለ ?
- አላስታውስም ግን ሃጂ አካባቢ ሃጂ የሚሄዱ ወደ ሃጂ ጉዞ አካባቢ ጠይቀው የተመለሰላቸው አሉ በሼህ አብዱራህማን መዳ ጊዜ
- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ አቃቤ ሕግ
- እሺ አቶ ሰይድ ቅድም ዶ/ር ወይም እነኚህ ገንዘብ የሚከፈላቸው ሰወች ቁርአን እና አዲስ ያስተምራሉ ከአክራሪነት ውጪ ሲያስተምሩ ያውቃሉ ወይ ተብሏል አቶ ሰይድ በተለያየ ጊዜ እነሱ የሚያስተምሩት ቦታ ይከታተሉ ነበር ?
- እኔ አልከታተልም ለምን ምናልባት ሰላት ደርሶ መስኪድ ከመጣሁ አጋጣሚ ቁርአን ምናምን የሚያስተምሩ ከሆነ ቁጭ ብዬ አዳምጣለሁ
- እንጂ ከዚህ ውጪ እነሱ አክራሪነት ያስተምሩ አያስተምሩ ይንን ማረጋገጥ አይችሉም ?
- አይችሉም
- እሺ ከዚጋር በተያያዘ እነኚህ 3 ተከሳሾች የሚከፈላቸው ማለት ነው አሁን ካሉት የዚህ ሳውዲ ኤምባሲ የሚገኘው አታሼ የተባለው የሚከፍላቸው በጐ አድራጐት ስላላቸው ነው ወይስ ይሄን የኃይማኖትም ስለሚያስተምሩ ነው የሚከፍላቸው እርስዎ እንደሰሙት ማለት ነው?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንግዲህ አንዳንድ ድርጅቶች በጐ አድራጐት ነው በጐ አድራጐት ድርጅት ስላላቸው ነው ከነዚህ ሦስቱ2 ሼህ ሱልጣን መሰለኝ በጐ አድራጐት ድርጅት እንዳለው ሆኖ ሼህ አብዱራህማን ኡስማን እና እነ ዶ/ር ከማል ስለሚያስተምሩ ነው የሰማሁት እኔ
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ምስክር የፍ/ቤቱ ጥያቄ አልተነሳም እናመሰግናለን ጨርሰዋል መመለስ ይችላሉ
- እሺ እኔም አመሰግናለሁ
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም
- ምያለሁ
- አሁን ለምስክሮች ደህንነት ሲባል የራሶን የመጀመሪያ ስም ብቻ ይናገራሉ የአባት ስም የአያት አድራሻ አይናገሩም ስለዚህ የመጀመሪያ ስሞ ማን ነው ስሙ?
- ሚፍታህ
- እሺ በፍ/ቤቱ 31ኛ ቋሚ ቁጥር ነው በአቃቤ ሕግ ክስ ላይ የማስረጃ ዝርዝር በተራ ቁጥር 107 ነው እሺ በማን በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት
- ይደገምልኝ
- ለምስክርነት ነው የመጡት አደለም?
- አዎ
- እኮ በማን በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?
- እዜ በግለሰብ የማውቀው የለም በቡሼር መስኪድ ላይ የነበሩ ሁኔታዎችን ለመመስከር ነው የመጣሁት
- በግለሰብ አደለም?
- አዎ
- እ/ላጅን አሁን እንደገለፁት ማለት ነው ይሄ የገለፁት ድርጊት መቼ እንደተፈፀመ ጊዜ ቦታውን አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሆነ የት ቦታ የት ክ/ከተማ እንደሆነ አጠቃላይ የሚያውቁትን ለተከበረው ፍ/ቤት ያው በዝርዝር እንዲገልፁ እጠይቃለሁ እና መቀጠል ይችላሉ ጊዜው መቼ ነበር?
- ጊዜው 11ኛ ወር ቀን 06 ለሊት አምስት ሰዓት
- የት አካባቢ ነው?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንግዲህ አንዳንድ ድርጅቶች በጐ አድራጐት ነው በጐ አድራጐት ድርጅት ስላላቸው ነው ከነዚህ ሦስቱ ሼህ ሱልጣን መሰለኝ በጐ አድራጐት ድርጅት እንዳለው ሆኖ ሼህ አብዱራህማን ኡስማን እና እነ ዶ/ር ከማል ስለሚያስተምሩ ነው የሰማሁት እኔ
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ምስክር የፍ/ቤቱ ጥያቄ አልተነሳም እናመሰግናለን ጨርሰዋል መመለስ ይችላሉ
- እሺ እኔም አመሰግናለሁ
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም
- ምያለሁ
- አሁን ለምስክሮች ደህንነት ሲባል የራሶን የመጀመሪያ ስም ብቻ ይናገራሉ የአባት ስም የአያት አድራሻ አይናገሩም ስለዚህ የመጀመሪያ ስሞ ማን ነው ስሙ?
- ሚፍታህ
- እሺ በፍ/ቤቱ 31ኛ ቋሚ ቁጥር ነው በአቃቤ ሕግ ክስ ላይ የማስረጃ ዝርዝር በተራ ቁጥር 107 ነው እሺ በማን በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት
- ይደገምልኝ
- ለምስክርነት ነው የመጡት አደለም?
- አዎ
- እኮ በማን በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?
- እዜ በግለሰብ የማውቀው የለም በቡሼር መስኪድ ላይ የነበሩ ሁኔታዎችን ለመመስከር ነው የመጣሁት
- በግለሰብ አደለም?
- አዎ
- እ/ሳጅን አሁን እንደገለፁት ማለት ነው ይሄ የገለፁት ድርጊት መቼ እንደተፈፀመ ጊዜ ቦታውን አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሆነ የት ቦታ የት ክ/ከተማ እንደሆነ አጠቃላይ የሚያውቁትን ለተከበረው ፍ/ቤት ያው በዝርዝር እንዲገልፁ እጠይቃለሁ እና መቀጠል ይችላሉ ጊዜው መቼ ነበር?
- ጊዜው 11ኛ ወር ቀን 06 ለሊት አምስት ሰዓት
- የት አካባቢ ነው?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በ18 ጣቢያ አካባቢ ምእራብ ጀርባ የነበረ መስኪድ ላይ የነበረ አመጽ ላይ የነበረውን ለመመስከር ነው የመጣሁት
- ስንት ሰዓት ነበር ይሄ?
- ከለሊቱ 5 ሰዓት ላይ
- እስቲ አሁን በዚህ ባሉት ጊዜ እና ቦታ ሰዓት የገጠሞትን
- ምንድን ነው እስቲ ቆይ ምስክር
- መቃወሚያ አለን ቅድም እኔ ከክስ ውጭ ባለ ነገረ ላይ ስቃወም ተከልክዬ ነበር እና እሱን በማስታወስ አሁን በእኛ ክስ ላይ በቀረበው ክስ ማለት ነው ባዩሽ መስኪድ ወይም ባቡሼ መስኪድ በሙሉ ጥፋት አጠፋ ተብሎ የተከሰሰ ደምበኛ የለንም ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ ሊመሰክር አይገባም ክስ ላይ የለም እንዲህ አይነት ነገር ማየት ይችላል ፍ/ቤቱም እና መመስከር የለበትም ምስክርነቱን እንቃወማለን ክስ ላይ የለም
- እሺ አቃቤ ሕግ ምላሽ ይስጡበት
- ለዚህ የምሰጠው መልስ የተከበረው ፍ/ቤት እኛ አዲስ አበባ ባሉት አጠቃላይ መስኪዶች ሁሉ እያንዳንዱን በዝርዝር የመግለጽ እንትን የለብንም ነገር ግን በነኚህ አመራሮች እና በዋና ግብርአበሮች ተብለው የተከሰሱትን ጨምሮ ከተማ ውስጥ ምን ሲደረግ እንደነበረ እና አጠቃላይ የተፈጠረ ሁከት በሚገልጽ ሁኔታ ክሳችን ላይ
- የተከበረውፍ/ቤት የተከበሩ አቃቤ ሕግ የሚናገሩትን ነገር ምስክሩ እያዳመጡ ነው ስለዚህ ምስክሩ ወይ ወጥተው
- አረ ቆይ እስቲ አሁን እኮ አልሰጠናችሁም
- አኬ የሰጡኝ መስሎኝ ነው ይቅርታ አሁን እያብራሩ ነው ማለት እንዴት እንደጠየቁ ነው እስቲ እኔ አልሰማኋቸውም በደምብ እሺ ቀጥሉ
- ምንድን ነው ክስ ላይ አልተመለከተም ነው እየተባለ ያለው ይሄ እዚህ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሲፈፀም የነበረውን አጠቃላይ እሳቸው ሄደው በወቅቱ በነበሩበት ማዘጋጃ ጣቢያ ላይ ሲፈፀም የተደረገውን ድርጊት በሚመለከት ነው እየገለፁ ያሉት መነሻው ምንድን ነው እንዴት ነበረ እሳቸው የሚያስረዱት ነው ሚዛኑ የተከበረው ፍ/ቤት በማስረጃ አሁንም ሰምቶ የሚያየው ይሆናል ማለት ነው ስለዚህ የክሱ አካል ነው የቀረበው መቃወሚያ አግባብነት የለውም ነው

1926

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የክሱ አካል ነው ብሏል አሁን ምስክሩ ለመመስከር የመጡት መስኪድ እና እንዴት የክሱ አካል እንደሆነ እሷን ፓርት ብቻ ግልጽ አርጉልኝ እንዴት እሷን ባቡሼ መስኪድ ነው መሰለኝ ያሉት ስሙን ከተሳሳትኩ ልተረም ይችላል ያ መስኪድ የክሱ አካል እንዴት እንደሆነ ብቻ
- የተከበረው ፍ/ቤት ያው ምስክሩ እንዳይሰማ እንጂ በክሱ ገጽ 7 በዝርዝር እንደጠቀስነው መግቢያው ላይ በክልል እና በአዲስ አበባ በሚገኙ የተለያዩ መስኪዶች የአንድ የሰደቃ የአንድነት የሰደቃ ፕሮግራም የአንድነት ፕሮግራም እየተባሉ በሚጠሩ እያለ ይቀጥላል እና
- እሺ ልክ ነው ክሱን አትግለፁት እኛን አሳዩን
- እሺ ከዚህ የተለየ ማብራሪያ አለ የምትሰጡት
- የተከበረው ፍ/ቤት አሀን እኮ እዚህ እርግጥ ምስክሩ ስላሉ ነው እንጂ አጠቃላይ እኮ መዘርዘር እንችላለን እያንዳንዱ ሲደረግ የነበረው መነሻው ምንድን ነው የሚለው በክሱ መግቢያ ላይ በዝርዝር አለ ያንን መግለጽ ከተፈለገ ምስክሩ ይሰማሉ መባል ካልሆነ በስተቀር በክስ መግቢያችን ላይ ይሄ
- ቆይ ቆይ ክሱ ላይ የተቀመጠውን ነገር ለምስክሩ መንገር ስለሆነ እሱን አትግለፁት ያለበትን ገጽ ካላችሁ በትክክል ግለፁልን እና እኛ እናነነበዋለን እዚህ
- ከዚህ የተለየ ማብራሪያ ካላችሁ ከሌለ እናያለን ከዚህ ውጪ አለ ከዚህ የተለየ የምትጨምሩት
- እሺ ብይን ሰጥተናል አሁን ምስክሩ የጠቀሱት መስኪድ ላይ ስለተከሰተው ሁኔታ ነው ሊመሰክሩ የመጡት እሱ በክሱ ውስጥ የለም ስለዚህ ክሱ ከተያዘው ጭብጥ ውጪ ስለሆነ ሊመሰክሩ አይገባም የሚል ተቃውሞ ተነስቷል በአቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው የክሱ አካል ነው ብሏል ፍ/ቤቱም የክሱ አካል ነው ወይስ አደለም የሚለውን ለመመርመር ያው ክሱን በሙሉ ለማንበብ ተገዷል በዚህ መሰረት ክሱ ተነቧል ክሱን ስናነብ አላማቸውን ለማራመድ በአዲስ አበባ እና በክልሎች ባዘጋጁት የሰደቃ እና የአንድነት ዝግጅት ብሎ የሚቀጥል ፓርት አለ በአዲስ አበባ እና በክልል ባዘጋጁት የሰደቃ እና አንድነት ዝግጅት ማለት ሰፊ ይዘት ያለው ነው ስለዚህ አሁን የተጠቀሰው መስኪድም አዲስአበባ ውስጥ ያለ ስለሆነ የክሱ አካል ነው ከጭብጥ የወጣ አደለም ትክክል ነው ምስክሩ መመስከር አለበት ብለን ብይን ሰጥተናል ከዛ በፊት ጠበቃው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ያነሱት አግባብ ያልሆነ ነገር አለ እኛ ቅድም አንስተን ተከልክለናል እነሱም መከልከል አለባቸው የሚለው ነገር ማለት ነው ያነሱት ነገር አቃቤ ሕግም ይሁን ጠበቃ ያነሳው በሕጉ አግባብ ከሆነ ይፈቀዳል በሕጉ አግባብ ካልሆነ ይከለከላል ጠበቃ ስለተከለከለ አቃቤ ሕግ ስለተፈቀደ የሚለው የሕግ አካሄድ የለም ቅድም ጠበቃ የተከለከሉበት ግልጽ ነው ምስክሩ ከመሰከሩት ውጪ መስቀለኛ ጥያቄ አይጠየቅም ነው ምስክሩ ከዚህ ሕግ ውስጥ ያ ከዚህ ክስ ውስጥ ያለውን ሙሉውን ጭብጥ ይመሰክራል ተብሎ በጭብጥ ከተያዘ ትክክል ነው ከዛ ውጪም መጠየቅ ይቻላል ሙሉውን ጭብጥ ያውቃል ከተባለ ማለት ነው ምስክር መንድ ጭብጥ ሊያውቅ ይችላል አንድ ክስ ሃያ ጭብጥ ከዛ በላይ ጭብጥ ሊኖረው ይችላል እና በዚህ አግባብ ነበረ መመዘን የነበረበት በዛ አግባብ ከተመዘነ ያ ጥያቄ አግባብ አደለም ስለዚህ ለወደፊት ጥያቄው እንዲታረም ነው የአሁኑ በብይኑ መሰረት ይቀጥል

- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አመሰግናለሁ ብይኑን እንቀበላለን የተከበረው ፍ/ቤት ይሄ የሚለው አሁን የተከበረው ፍ/ቤት የተረጎመው ነገር የሰደቃ እና የአንድነት ፕሮግራሙ ነው አዲስ አበባ እና
- የብይኑን ትንተና
- ትንተናውን አደለም የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄውን እንደገና እንዲያይልን ብዬ ነው ሌላውን ምን ለማለት ፈልጌ ነው የተከበረው ፍ/ቤት ብይኑን ተቀብለናል እኮ ነገር ግን ይሄ አዲስ አበባ ተደረገ የሚባለው የአንድነትን አዲስ አበባ እና ክልሎች ተደረገ የሚባለው የሰደቃ ፕሮግራም ነው እንጂ አሁን ምናልባት ምስክሩ በአዲስ አበባ ከተካተተ የሚመሰክሩት ነገር የሰደቃ እና የአንድነቱን ፕሮግራም ብቻ እንዲሆን ስለ ሌላው ጉዳይ መመስከር የለባቸውም
- አኬ ግልጽ ነው እኛ ትንሿን ብቻ አንብበት ነው ያቆምነው ጊዜ ለማቋረጥ ዝርዝር ነገር አለ ከዛ በኋላ ተደረጉ
- በቃ እሱ ላይ
- ቦታውን ለማሳየት ነው እንጂ የተዘረዘረው ነገር አለ በመሰከረው መሰረት ይሆናል
- እሺ ምስክር እ/ላ ቅድም ባሉበት ጊዜ እና ሰዓት እስቲ እንደገና ጊዜው ወሩ አመተምረቱ እና ቦታው እርስዎ ምን ሲሰሩ እንደነበረ እና ምን እንደገጠሞት የተደረገ አጠቃላይ ድርጊት በዝርዝር እንዲገልፁ ነው የምጠይቀው ቀኑ መቼ ነው ወሩ?

1928

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ቀኑ 11ኛ ወር ለሊት አምስት ሰዓት 06 ቀን 2004 ዓ.ም. ነው እሱም በቡሽር መስኪድ ነው የተከሰተው እሱም ምንድን ነው ሻርፕ ለሊት 5 ሰዓት ላይ አዛን ድምጽ በማሰማቴ ነበር አመጽ ላይ እኔም ቀኝ እግሬ የተጐዳሁበት ሂደት ነው ያለው በድንጋይ ውርወራ አጠቃላይ የነበረበት ሂደት ነው የነበረው እዛ ውስጥ እሱም በግለሰብ ደረጃ እከሌ ነው ብዬ የማስቀምጠው ነገር እስከሌለ ድረስ ይሄ ነው ልመሰክር የመጣሁት የተጐዱ አባሎችም አሉ ከእኛጋ የነበሩ እኔም ተጐድቻለሁ ቀኝ እግሬ ላይ ይሄ ነው የነበረው
- እሺ አዛን የሚሉት ጥሪው እንዴት ነበር እዚህ አካባቢ ምንድን ነው የተከሰተው እርስዎ እንዴት ተመቱ ከእነማንጋር ምንድን ነው የተከሰተው እርስዎ እንዴት ተመቱ ከነማንጋር ምንድን ነው የተከሰተው?
- እሺ አጠቃላይ በወቅቱ ለሊት አምስት ሰዓት ላይ ከዛ በፊት ተሰምቶ የማይታወቅ ድምጽ ተሰማ በቅርብ የነበሩ አለቃችን ትእዛዝ ይዤን በወቅቱ የነበረን አመጽ ለማረጋጋት ገባን እዛ አካባቢ ላይ በተወረወረ ድንጋይ ነው የተመታሁት እኔ በራሴ በኩል ለማለት ፈልጌ ነው
- እሺ እዛ ይሸውሎት አጥር ላይሆን የሚያውቁትን ዘርዘር ያርጉት የተሰማው ድምጽ ምን ነበር ምን ድምጽ ሲሰማ ነው በአለቃችሁ ታዛችሁ ወደዛ አካባቢ የሄዳችሁት ስትደርሱስ በማን እና በማን መካከል ነው ይሄ ውርወራ የነበረው?
- አጠቃላይ ስንደርስ በሉት የሚል ድምጽ ሰማ እዛ መስኪድ ውስጥ ሆዬ በሉት የሚል ሲያሰሙት ነበረ በዛ ወደኛ ድንጋይ ውርወራ ነበረ አጠቃላይ እኔም ተመታሁ መጨረሻ ላይ የነበረው ሂደት ይሄ ነው እኔ ወደ ሆስፒታል የሄዱኩበት ሁኔታ ነው የነበረው ይሄን ማለት ፈልጌ ነው
- ወደኛ ስትሉ ወደነማን ማለቶ ነው ውርወራው?
- ውርወራው ወደ አጠቃላይ የነበረ ፀጥታ ኃይል ላይ ነው
- ምንድን ነው ሲወረወር የነበረው?
- ድንጋይ ነበረ ጠርሙሶችም ነበሩ አጠቃላይ
- እነማን ነበረ የሚወረውሩት ከየት ወዴት የሚመጡ ሰወች ናቸው የሚወረውሩት ?
- ከመስኪድ ግቢ ውስጥ የነበሩ ናቸው

ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወደ ፀጥታ ኃይሉ እየወረወሩ የነበሩት ወደ ውጭ ወጥተው ነው ወይስ ውስጥ ሆነው ነው እየወረወሩ የነበረው?
- ውጭም ውስጥም ሆነው ይወረውሩ የነበሩበት ሂደት ነው የነበረው
- እስቲ በወቅቱ እዚህ በፀጥታ ስራ ላይ በፀጥታ ተግባር ላይ በተሰማሩ ኃይሎች ላይ ምን ምን ጉዳት ደረሰ እርስዎስ ምን ጉዳት ነው የደረሰቦት?
- እሺ በወቅቱ ፀጥታ ላይ የነበሩ አካሎች ላይ የደረሰ ጉዳት እኔ በራሴ በኩል ቀኝ እግሬ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶብኝ ፖሊስ ሆስፒታል ስታከም ቆይቻለሁ በተመሳሳይ አለ እዚሁ ባልደረቦቻችን አብዛኛው ሰው እንደዚህ አይነት ጉዳት የደረሰበት ሂደት ነው የነበረው
- እርስዎ የደረሰቦት ጉዳት ምን ነበረ ከፍተኛ ጉዳት ብለው የገለፁት ማለት ነው?
- እኔ እግሬ ላይ ነው የተመታሁት
- በምንድን ነው የተመቱት?
- በምን እንደሆነ አይታወቅም ድንጋይ ይሁን ምን ይሁን ጨለማ ነው የነበረው ለሊት 5 ሰዓት ማለት እንግዲህ እንደምታውቀው በዛን ሰዓት ነው የደረሰብኝ ጉዳት በድንጋይ ነው የሚመስለኝ እኔ በራሴ በኩል ይሄ ነው የነበረው ሂደት ለማለት ፈልጌ ነው
- ይሄ የደረሰቦትን ከፍተኛ ጉዳት ብለው አሁን ያሉትን ሕክምና አግኝተው ታክሙ?
- አዎ ታክሜያለሁ በአወቅቱ በአምቡላንስ ወስደው በሚገባ ታክሜያለሁ
- ሌሎች አባሎችስ ምንድን ነው የደረሰባቸው ጉዳት?
- እነሱም የተጐዱበት ሂደት ነው ያለው እግራቸውን
- ማ ለምሳሌ ምን ሆነ የሚያስታውሱት ካለ ማለት ነው?
- እሺ የማስታውሰው እ/ሳጅን ካሳሁን አደመ አለ አንድ 2ኛ እ/ሳጅን መሃሪ ገ/መድህንም አሉ መአት ልጆች አሉ በወቅቱ የተጐዱት አባሎች ማለት ነው እዛ የነበረ ስራ ላይ
- ይሄ ጊዜ መቼ ነበር ቀኑ ጉዳቱ የደረሰበት ማለት ነው?
- ቀን 11ኛ ወር 06 ቀን 2004 ዓ.ም. ቅድም እርእሱ ላይ መጥቀስ እንደሞከርኩት
- የት ክ/ከተማ ነው?
- አዲስ ከተማ ክ/ከተማ
- ቅድም ድምጽ ስለተሰማ ነው ብለው ገለፁው ነበረ ያው እናንተ ታዛችሁ የሄዳችሁት እና እዛ ስትደርሱ የሰው ብዛት እንዴት ነበረ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የሰው ብዛት ይሄ ነው ተብሎ የሚገለጽ አደለም በውስጥምሆነው በውጭም በኩል በነበረ ቅያስ ላይ አጠቃላይ የነበረ ሂደት ድንጋይ ውርወራ ነው ከውስጥ ሆነው በድምጽ የሚያሰማ በሉት የሚል ድምጽ ነው የሚሰማው አጠቃላይ ይሄ ነው የነበረኝ
- እዛ አካባቢ የነበረው ሕብረተሰብ ማለት ነው እንዴት እንደተሰባሰበ ይሄንን ማወቅ ችላችኋል እንዴት እንደተሰባሰበ ምን እንዴት ተሰባሰበ ለሊት ነው አምስት ሰዓት ነው እዛ መስኪድ አካባቢ እንዴት ነው የተጠራው ማን ነው የጠራው ይሄንንስ ማወቅ ይችላሉ?
- ይሄን እንግዲህ አጠቃላይ የነበረ ሂደት ምንድን ነው ድምጽ በማሰማት የመሰብሰብ ተግባር እንደተሰራ ነው በወቅቱ እኔ በራሴ በኩል የተረዳሁት ለሊት አምስት ሰዓት ላይ ያልተለመደ አዛን በማሰማት ማለት ነው
- አዛን ባልተለመደ ሁኔታ ነው በአዛን ጥሪ የተደረገው ማለት ነው?
- አዎ ስንደርስ ተሰብስበው ነው ያለው አጠቃላይ ከዛ የተነሳ ነው
- ሕዝብ ወዴት ነበረ እንሂድ የሚለው ከአዛኑ በኋላ እናንተጋ ድንጋይ ውርወራ አለ ከዛ ብዙ ነገር አለ ምንድን ነው የሚለው ሕዝቡ እዛጋ የተሰበሰበው ማለት ነው ?
- አጠቃላይ የነበረው ሕዝብ እንግዲህ እኛ ስንደርስ ወደኛ ነው ድንጋይ ውርወራው የሚፈጽመው ከግራም ከቀኝም ወደኛ ነው የመወርወር ተግባር ነው እኛ ደግሞ በተለመደ የመበተን ተግባር ነው የሰራነው በውጭ ያለን ማረጋጋት ከዛ ውጭ ሌላ ወዴት የመንቀሳቀስ ሁኔታ የተሰማ ነገር የለም ግን ድምጽ በሚያሰማው እንደዚህ አይነት እንትን በሉት የሚል ድምጽ ይሰማል
- ይሄ በሉት የሚለው ግለሰብ ነው ሰው ነው ማን ነው አሱ ይሄን ትእዛዝ የሚሰጠው በለው የሚለው ከውስጥ ነው ከውጭ ነው የቱ ነው?
- ከውስጥ ነው መስኪድ ውስጥ ሆኖ ድምጽ በማሰሚያ እንትን ነው በሉት የሚለው
- ድምፁ እንዴት ይሰማችኋል እናንተ ?
- በማይክራፎን ስለሆነ ሙሉ በሙሉ ይሰማል
- በማይክራፎን ነው የሚያስተላልፈው?
- አዎ
- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ መስቀለኛ ጥያቄ የተከሳሽ ጠበቆች

ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አቶ ወይ ቅድም የተከበሩ አቃቤ ሕግ ሳጅን ብለዎታል በዛ ልበል አቶ ሚፍታ ልበሎት እንትን ስላለን ነው እ/ሳጅን ሚፍታ ቅድም ሕዝቡን በተነው ብለዋል እንዴት አርጋችሁ በተናችሁት?
- ሕዝቡን በተን የሚለው አጠቃላይ የነበረው ሂደት ወደ ፀጥታ ኃይል ድንጋይ ውርወራ ነው የነበረው ከዛ እኛ የማረጋጋት ተግባር ሰርተን ነው ከዛ በኋላ ቦታው ላይ አረጋግተን መጨረሻ ላይ እኛ የተጐዳነው ወደ ሆስፒታል ሄድን የነበሩም አረጋግተው የነበሩ ሁኔታዎችን ወደ ሰላማዊ መንገድ እንደቀየሩ
- ኧሃ ተው አትረብሹ በማለት አረጋግታችሁ ነው?
- አዎ ተው አትረብሹ ይሄ ሕገወጥ ነው እንደዛ አይደረግም በማለት በድምጽ ማሰሚያ ማይክራፎናችን
- አሃ ድንጋይ ይወረውር የነበረው ሕዝብ ይሄን ሲሰማ ተበተነ?
- ምንም አልተበተነም ድንጋይ ውርወራ ነው አጠቃላይ የነበረው ሂደት
- ምን ሆኖ ነው ታዲያ የተረጋጋው?
- እንግዲህ መጨረሻ ላይ የመረጋጋት ሂደት መጣ እንጂ መጀመሪያ ላይ የነበረው አጠቃላይ ወደ 6 አባሎች የተጐዳንበት ሂደት ነው የነበረው
- እኮ ታዲያ አሁን ተው አላችሁ ውጤት አላመጣም ነው በተን የሚለው ቃል በተን ስላሉ ተው አላችሁ ካልቆመ በምን አረጋጋችሁት ታዲያ በመን በተናችሁት?
- እሺ በተኑ የሚለው ቃል ለእርስዎ አገላለጽ ግልጽ ላርግላችሁ ድንጋይ አጠቃላይ ውርወራ ሂደቶች የነበረ ላይ እኛ በአድማ ብተና ጋሽ ኢለመንት ማቴሪያል ስለገባን የነበረን ሕዝብ በወቅቱ አረጋግተን ይሄ ሕገወጥ ነው ይሄ ከእናንተ አይጠበቅም ብለን አረጋግተን የሄድንበት ሂደት ነው ያለው
- እኮ በዚህ መሰረት ሕዝቡ ተበተነ?
- አዎ ወደ ሰላማዊ የሚፈልግ ሰው ወደ ሰላማዊ ኖሮ የተመለሰበት በዚህ መሰረት የተረጋጋበት ሂደት ነው
- ቅድም የተከበሩ አቃቤ ሕግ ሲጠይቆት ነበረ ሕዝቡ ወደ አወልያ እንሄዳለን አላለም ?
- እ?
- ቅድም በእናነተ ላይ ድንጋይ ከመሬት ተነስቶ ነው እንዴ የወረወረው ወይስ ለመሄድ ሲፈልግ እናንተ አገዳችሁት?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኛ ምንም ያገድነው ነገር የለም በወቅቱ እረብሻ አለ ተብሎ በቅርብ አለቃችን ታዘን በቦተው ላይ ሰንሄድ ወደኛ ድንጋይ ውርወራ ነው የተጀመረው እንጂ ወደዚህ መሄድ ወደዛ መሄድ መብታቸው እንደሆነ እናውቃለን ተጠንቅቀን
- ጥሩ መጀመሪያ ያለ ምንም ምክንያት ድንጋይ ተወረወረባችሁ በኋላ ደግሞ ተው ሕገወጥ ነው ሲሉ ሕዝቡ ተበተነ ከዚህ ምንድን ነው የተረዱት?
- ምንድን ነው የተረዱት የሚለው ላይ ይሄ ሕገወጥ ተግባር ውስጥ ሕብረተሰቡ ተግባብቶ ተሰማርቶ ከዛ መቆጠብ እንዳለበት በወቅቱ ተነግሮ ይሄ ድንጋይ ውርወራው መጨረሻ ላይ አጠቃላይ ያ አድማ ብተና ማቴሪያላችን ላይ አርፎ የተጐዳም አባል ተጐድቶ እኔ መጨረሻ ላይ ወደ ሆስፒታል የሄድኩበት ሂደት ነው ያለው እስከ አጨረራረስ ድረስ ያልቆየሁበት ሂደት ነው ያለው እስከ መጨረሻ እኔ ተጐድቼ የወጣሁበት ሆስፒታል የሄድኩበት ነው
- እርስዎ ቀኝ እግሮን ከፍተኛ እንደተጐዱ ገልፀዋል ከፍተኛ ጉዳት ሲሉ ምን ማለት ነው ምንድን ነው የደረሰቦት በተጨባጭ እስቲ ይንገሩን ?
- እኔ የደረሰብኝ የአጥንት መሰበር ነው የደረሰብኝ ቀኝ እግሬ ላይ ማለት ነው
- የትኛው ቦታ ምኑ ላይ?
- ቀኝ እግር ከጉልበት በታች ያለ ላይ
- ለስንት ጊዜ ተኙ ሆስፒታል?
- ሆስፒታል የተመላለስኩት ወደ 15 ቀን የታከምኩበት ሂደት ነው ያለው
- አሁን ተመልሷል አደለም ስብራቱ?
- ይሰማኛል
- ቅድም ለሊት በ5 ሰዓት ላይ አዛን ተደረገ ብለዋል እርስዎ አዛኑ ሲደረግ የትጋ ነበሩ?
- እኛ እንደተለመደ የምንኖረው አንድ ላይ /ግልጽ ያልሆነ/ ስራ ቦታችን ላይ ነበርን ከዛ በነበረ በቅርብ አለቃችን ትእዛዝ ሄደን የነበረን ሁኔታዎች ያረጋጋንበት ሂደት ነው ያለው
- ያው ማለቴ ባዩሽ ነው ብለውታል እዛ መስኪድ እና የእናንተ የስራ ቦታ እርቀት አለው ቅርብ ነው?
- እኛ ያለንበት እርቀት አለው ትንሽ የተወሰነ ሜትሮች
- ከዛ ከባዩሽ ስለመሆኑ እርስዎ የሚያውቁት ነገር የለም አደል አዛን የተባለው?

1933

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ድገሙት እስቲ
- ይሄ ባዩሽ ያሉት መስኪድ እሱ ብቻ ነው ወይስ ከየ አቅጣጫው ነበረ አዛን?
- አዛኑ በወቅቱ የነበረው ከየአቅጣጫው ነው
- እኮ ባዩሽ መስኪድ ለምን ተመረጠ ነው እርስዎ እሩቅ ስለሆነ ባዩሽ መስኪድ አዛን ይባል አይባል የሚያውቁት ነገር የለም አደል ?
- ባዩሽ መስኪድ ለምን ተመረጠ እንደ እኛ ቀጠና ተሰማርተን ፀጥታ የምናስከብርበት ቀጠና አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ከመሆኑ አኳያ ያለን ሂደት ከአመራራችን ጋራ በመነጋገር አስፈላጊ በሆነ ቦታ ተንቀሳቅሰን ፀጥታውን ማስከበር ስለምንችል
- ጥሩ ባዩሽ መስኪድ ከእናንተ የስራ ቦታ እሩቅ እንደሆነ ገልፀዋል ስለዚህ አዛን ተብሎ ካለቀ በኋላ ነው አደል ቦታው የደረሳችሁት?
- አዎ አጠቃላይ ድምጽ ያሰሙ ነው አዛን እየተባለ ነው የደረስነው እዛ ውስጥ እኛ ስንደርስ ድንጋይ ውርወራ ተጀምሯል ብያለሁ ቅድም
- እኮ አዛን እየተባለ ነው ድንጋይ የተወረወረው ወይስ ተብሎ አልቆ እርስዎ ሲደርሱ ጩኸት አለ ድንጋይ ወርውሩባቸው ተባለ ?
- አልሰሙኝም መሰለኝ ቀድሞ አዛን ነው የባለው ከዛ እኛ ስንደርስ ድንጋይ ውርወራ ተጀመረ በሉት በሉት የሚል በድምጽ ማጉያ እንትን ተሰማ ይሄ ነው የነበረው ሂደት ለማለት ነው በአጭሩ
- እሺ ምስክር ቅድም ሲመሰክሩ ግርግሩን ወይም ብዙ ሰው ነበረ ብለዋል የነበሩት ሰወች የተበተኑት እዛው በእንተ ብቻ ነው ወይስ የፌደራል ፖሊሶችም መጥዋል ተጨማሪ ?
- እሺ አጠቃላይ በዛ ዙሪያ እኔም በራሴ በኩል የፌደራል ፖሊስ አባል ነኝ
- አሃ እርስዎ እራሶ የፌደራል ፖሊስ አባል ኖት?
- አዎ
- የሁልጊዜ ምድቦት እዛ ነው ወይስ ለዛን ቀን ነበር እዛ የተመደቡት?
- ምን ግዜም ምድቤ እዛው ኤርያ ላይ ነው አስፈላጊ በሆነ ፀጥታ ሁኔታ ላይ
- እሺ የግርግሩን ለመበተን የአድማ በታኝ ፖሊሶች መጥተው ነበር?
- እኔ እራሴ የአድማ በታኝ ፖሊስ ነኝ ብዬ ቅድም ገልፀዋል አለመስማት ሁኔታዎች ካሉ እንጂ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምስክር አሁን መልሱን ይመልሱ ዝም ብለው እሺምክንያቱም ግልጽ ላይሆንላቸው ይችላል መልሱን ተናግሮ ማለፍነው
- እሺ
- እሺ ቀጥሉ
- እርስዎ ወይም ባልደረባዎ አድማ ለመበተን ይዘውት ወይም ተጠቅመውት ከነበረው ውስጥ አስለቃሽ ጭስ ይገኝበታል አደል?
- እሺ የተጠቀምነው አስለቃሽ ጭስም ሌላም ምንም የተጠቀምነው ነገር እንሌለ ማስቀመጥ እፈልጋለሁ
- በወቅቱ አስለቃሽ ጭስ አልተተኮሰም ወይም አልነበረም ነው የሚሉት?
- አዎ አልተጠቀምንም አልተተኮሰም
- ወደ መስኪዱ ገባችሁ ለማረጋጋት?
- ወደ መስኪዱም የባንበት ሂደት የለም እኛ አጠቃላይ ዙሪያው ላይ ስንደርስ የድንጋይ ውርወራ እንደነበረብን ነው እንጂ መስኪድ ውስጥ እነደማይገባ ተጠንቅቀን እናውቃለን
- እንደው ዝም ብሎ ከመሬት ተነስቶ ለምንድን ነው ድንጋይ ውርወራ የሚኖረው ምንም ነገር ከሌለ?
- እሱን እንግዲህ አጠቃላይ ሲወረወር የነበረን ብንጠይቀው የተሻለ ነው እኛ ሰላሙን ለማረጋጋት ስንሄድ
- ኢኸው ምስክር ምክንያቱን የማያውቁ ከሆነ አላውቅም ነው የሚባለው እንጂ ሌላ ሰው እንዲጠይቁ እርስዎ አይመክሩም እሺ ቅድምም እንደዛ ሲሉ ስለነበር ነው አሁንም ጥያቄዋን ብቻ የሚያውቁ ከሆነ አውቃለሁ የማያውቁ ከሆነ አላስታውስም ግዴታ አደለም ወደኋላ ሄደው እንዲህ አይነት መስጠት ያው እንትኑን ያጓትታል እሺ ቀጥሉ
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ያው ፍ/ቤቱ እንዳለው የሚያውቁት ከሆነ ብቻ ነው ቅድም ጨለማ ነበረ ብለዋል ስለዚህ ማየት አስቸጋሪ ነበር አደል ጨለማ ከነበረ ለማየት ለመለየት ያስቸግራል አደል ?
- እኮ ጨለማ ነው ብሏል እሱጋ የምትጠይቁት ካለ
- እኮ ለማየት እና ለመለየት ያስቸግር ነበር አይደል
- ጥያቄውን ቀጥሉ
- አዎ ስለዚህ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይታያል የሚታይ ነገር አለ?
- በግራም በቀኝም ይወረወር እና የሚወረውሩ ሰወች እንጂ በርቀት የሚታየው ነገር የለም ድንጋይ ውርወራ አለ ከመስኪድ በር ላይ ሰወች ግን ይታያሉ
- እሺ እነዚህ
- እከሌ ነው ብለን ለይቼ ለማስቀመጥ ግን አልችልም
- ቀጥሉ
- እርስዎን ማን ወርውሮ እንደመታዎትም መለየት አይችሉም አደል?
- ማን ወርውሮ እንደመታኝማ ከስኪድ ግቢ ውስጥ በር ላይ የነበሩ ሰወች ናቸው እኛ ፀጥታውን ለማስከበር ስንደርስ ወርውረው የመቱኝ
- እርስዎ ከመስኪዱ ግቢ ምን ያህል እርቀት ላይ ነው የነበሩት?
- በግምት እንግዲህ በሩ እና እኛ የነበርንበት መንገዱ እዛው ቅርብ ለቅርብ ነው እዛው ጋር ነው የተመታሁት
- እዛው አጥሩ ወይም ግቢው አጠገብ ማለት ነው ?
- አዎ ከአጥሩ ውጪ ነው የነበርነው መንገድ ነበረ እዛው የነበረ ድንጋይ ውርወራ ላይ የነበረ ሂደት ላይ ነው የተመታሁት እኔ
- ስለዚህ አሁን እነዚህ ሰወች ጨለማ ከነበረ ከመስኪዱ ውጭ ይምጡ ከመስኪዱ ይምጡ እንዴት በምን ማወቅ ይችላሉ ከመስኪዱ ውጪ የመጡ ሊሆኑ ይችላሉ አደል?
- አይ ከመስኪዱ ውስጥ እንደሆነ በአራት ነጥብ አረጋግጬ አውቀዋለሁ ከምን አኳያ ነው የማውቀው በዚህ አይነት በሉት የሚል ድምጽ ይሄ አዛን የሚያሰማ እንትን በዛ ሲናገር ነበር አንድ ሁተኛ ደግሞ ከውስጥም ሲወረወርብን የነበረበት ሂደት ነው የነበው
- በሉት ያለውን ሰው አይተውታል እንዴ እርስዎ?
- በፊት ያለውን ሰው እኔ እከሌ ነው ብዬ የለየሁት ሰው
- አይ በሉት ያለው ሰው አይታይም አደል?
- ይታያል ድንጋይ ከየት አቅጣጫ እንደሚወረወር በግራ በቀኝ
- አይ የጠየቅኮት ድንጋዩ ሳይሆን አሁን በማይክራፎን በሉት የሚል ድምጽ ነበረ ነው ያሉት አደለም በሉት የሚለው ሰው አይታዮትም አደለ እርስዎ?
- አዎ ውስጥ መስኪድ ውስጥ ስለነበረ በምንድን ነው የሚታየው ታዲያ አይታይም

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ስለማይታይ አሁን ፖሊስን ይሁን ማንን ይሁን ማንን በሉት የሚለው እንዴት ለፖሊስ ነው ብለው ሊይዙት ይችላሉ እርስዎ?
- አጠቃላይ ፖሊስ ላይ በሉት ነው የመጡት በሉ በርቱ የሚል አይዞህ የሚል አካል ስለነበረ ነው ከውስጥ በድምጽ
- ምንድን ነው እስቲ አሁን እዛ ቦታ ሄደው እርስዎ የሰሙት በሉት የሚለውን ድምጽ ብቻ ነው ወይስ ሌላ ጥያቄያችን እንደዚህ ነው እንዲህ ነው ጥያቄያችን የሚል ሰው ነበረ ወይስ በሉት የሚለውን ብቻ ነበረ የሚናገሩት?
- ስለጥያቄ በወቅቱ የሰማሁት ነገር የለም እኔ አጠቃላይ የነበረኝ ፀጥታ ኃይሎች ላይ በሉት የሚል እና ጠርሙስ ውርወራ እና ድንጋይ ውርወራ ነው የነበረው ወደ 6 አባሎች የተጐዳንበት ሂደት ያለ ነው እያስቀመጥኩ ያለሁት
- እርስዎ ከመድረሶ በፊት ምን ያህል ቆይቷል ማለት ሰው ከተሰበሰበ ወዲያው እንደተሰበሰበ ነው ወይስ ቆይተው ነው የደረሱት ?
- እኛ እንግዲህ የሚመለከተው አካል ሲያዘን ነው ወደ ቦታው የምንሰማራው ከእኛ በላይ ያሉ አለቆች ተሰብስበው ከእኛ በፊት የገቡት
- ምስክር የሚያውቁት ተሰብስቦ የቆየ መሆኑን የሚያውቁ ከሆነ እሱን ይጥቀሱ እርስዎ እንደደረሱ ያዩት ከሆነ ደግሞ እሱን ብቻ ይጥቀሱ
- እኔ እንደደረስኩ የነበረው ወደኛ ውርወራ አመጽ ብቻ ነው ያየሁት
- ስለዚህ ከዛ በፊት ስለተፈጠረው ነገር አያቁም ማለት ነው እርስዎ ከመድረሶ በፊት?
- አዎ
- እርስዎ ከመድረሶ በፊትም ሰዎች አሉ እዛ አደለም?
- እንግዲህ እሱን እኔ ከነበርኩበት ሰዓት እና ደቂቃ ጀምሮ ነው ማስቀመጥ የምችለው
- እሺ ምስክር ያኔ ሲወረውሩ የነበሩ ልጆች የተያዙ አሉ የምታውቀው አለ አንተ?
- እኔ በዛ ዙሪያ የማውቀው ነገር የለም እኔ
- ለምክርነት አልቀረብክም ከዚህ በፊት ተይዘው ወረወሩ የተባሉ ልጆች?
- እኔ በወቅቱ ተጐድቼ ወደ ሆስፒታል የሄድኩበት ሂደት ነው ያለው
- በዚህ ጉዳይ የተከሰሱ ሰዎች እንዳሉ ታውቃለህ አታውቅም?
- እዛ በነበረ ላይ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በነበረው ያኔ ተፈጠረ በተባለው ውርወራ የተከሰሱ ልጆች እንዳሉ ታውቃለህ አንተ ወይ ምስክረ ሆነህ ቀርበህ ነበር እምታውቀው ነገር አለ ከዚጋ በተያያዘ?
- እኔ ምስክር ሆኜ ቀርቤ አላውቅም
- ጨርሻለሁ
- እ/ሳጅን እርስዎ አድማ በታኝ ወይም የፌደራል ፖሊስ አካል ኖት ፌደራል ፖሊስ ወይም አድማ በታኝ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ምን ይሰራል ወይም በዛ ሰዓት ምን ልትሰሩ መጣችሁ?
- እስቲ ጥያቄውን ምንድን ነው ይሄ ችግር ተፈጠረ ተብሎ ትእዛዝ ተሰጥቶን ሄድን ነው ያሉት ስለዚህ ከሱ ተነስታችሁ ነው ጥያቄውን መጠየቅ
- አዎ ችግር ሲፈጠር አዲስ አበባ ፖሊስ አልነበረም እሺ በሌላ ምልክ ልምጣ ?
- በቃ እሱን ጠይቁ
- እሺ አዲስ አበባ ፖሊስ አልነበረም?
- ነበረ
- አዲስ አበባ ፖሊስ መቆጣጠር ስላቃተው ነው እናንተ የጠራችሁት?
- አዎ
- ስለዚህ እናንተ አዲስ አበባ ፖሊስ መቆጣጠር ያቃተውን ነገር ለመቆጣጠር ስትመጡ ባዶ እጃችሁን ነበረ የመጣችሁት?
- ጋሽ ኢለመንት መጋጫ የአድማ ብተና ንብረት
- ሄልሜት ምናምን ?
- አዎ
- ሌላ እሺ በዚህ ቀን እዚህ ቦታ እርስዎ ከነበሩ እዚህ ባቦሼ ባዩሽ መስኪድ በአስለቃሽ ጭስ የተጐዱ ብዙ ሰወችን አላዩም እርስዎ በእናንተ በተተኮሰ?
- ቅድም የተጠየቀ ጥያቄ
- ተጠይቋል ይሄ አስለቃሽ ጭስ ተጠቅማችኋል አልተጠቀማችሁም
- የተከበረው ፍ/ቤት
- እዛ ተጠይቆ አስለቃች ጋዝ አልተጠቀምንም ብለዋል
- ከውጭ የመጣ ሌላ ኃይል አስለቃሽ ጭስ ተጠቅሞ የተጐዳ ብዙ ሰው የለም ወይ ነው?
- አስለቃሽ ጭስ የሚባለውን በጭራሽ ያልተጠቀምንበት ሂደት ነው ያለው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላስ አለ የተጠቀመ?
- አልተጠቀምንም የተጠቀመም ኃይልም የለም
- እርስዎ ይሄን የሚያውቁት እስከነበሩበት ሰዓት ነው አደለም ?
- እሱም ተጠይቋል ከመጣሁ በኋላ ያለውን ነው የማውቀው ብለዋል ከዛ በፊት አላውቅም የሚለው ተጠይቋል
- ቅድም ከእርስዎጋር የተጐዱ ሰወችን ገልፀውልኝ ነበር እነእ/ሳጅን ካሳሁን እና መሃሪ ገ/መድህን በእለቱ ከእሱጋር ፌደራል ፖሊስ ሄደው ነበር እነሱ ?
- ከኔጋ የነበሩ ናቸው ሕክምና ሄደዋል ከኔጋ
- ከእርስዎጋር ፌደራል ፖሊስ ?
- አዎ
- ምን ምን ተጐዱ እነሱ?
- እግራቸውን ፊቱጋ የተጐዳበት ሂደት ነው ያለው ሌላውም የተጐዱ ልጆች አሉ እዚህ አንገታቸውም አካባቢ የተጐዱ አሉ
- ስለሁለቱ ነው የጠየቅኩት
- እግር አካባቢ የተጐዳ አለ
- በሉት ማን እንዳለ በትክክል ያውቃሉ እርስዎ ትእዛዝ የሰጠ ሰው ስለመኖሩ አለመኖሩ ያውቃሉ ?
- ከመስኪድ ግቢ ውስጥ በድምጽ ማጉያ ቦታ ሆኖ በሉት በሉት የሚል ሰምቻለሁ
- ይሄ በሉት በሉት
- እሱ ተጠይቋል እኮ አሁን ምክንያቱም እዛ ተጠይቆ ውስጥ ላይ የሆነ ሰው አለ በሉት የሚል አላየውም በድምጽ ነው የሚሰማው የሚል ጥያቄ ተጠይቋል መልሱ ሌላ ካላችሁ
- እሺ በሉት ሲል ፖሊስን ነው
- እሱም ተመልሷል ይኸውሎት ጠበቃ
- የተከበረው ፍ/ቤት እኔ በሱ ተነስቼ
- አላዳመጡም ማለት ነው
- በደምብ አዳምጫለሁ
- ቆይ ቆይ ያዳምጡ መጀመሪያ ተጠይቆ ማንን ነው በሉት የሚለው የሚል ጥያቄ እሳቸው ጠበቃ ጠይቀዋል ጠይቀው ቆይ ጥያቄውን እንዲመጡ ነው በሉት የሚለው

1939

37

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ፖሊስን ነው ብሎ መልሷል ከዚህ ተነስታችሁ ልትጠይቁት የምትችሉት ነገር ካለ ከዚህ ቀጥሉ ካለዚያ ድግግሞሽ ነው የሚሆነው

- እኔ የፈለግኩት የተከበረው ፍ/ቤት በሉት ላለው ሰው ትእዛዝ የሰጠ አካል መኖሩን ያውቃሉ ወይ ነው በሉት ላለው ሰው?
- ውስጥ ላለው ሰው ነው?
- አዎ ይሄ ነው የኔ ጥያቄ የተከበረው ፍ/ቤት
- ይሄን ያውቃሉ?
- ውስጥ ላለው ሰው ብሎት ወደኛ ድንጋይ እንደሚወረውሩ ብቻ ነው የማውቀው እንጂ ማን እንደሆነ አላውቅም ብያለሁ ቅድምም
- መስክር ቅድም ባዩሽ መስኪድ ብለዋል በአካባቢው ሌሎች መስኪዶች አሉ አደል ብዙ መስኪዶች በባዩሽ አካባቢ ያውቃሉ አካባቢውን በደምብ ያውቁታል?
- አዎ በዛ አካባቢ ብዙ መስኪዶች እንዳለ ትልቁ አንዋር መስኪድም አለ
- አደለም በባዩሽ ባዩሽ መሆን በምንድን ነው ያወቁት መስኪዱን?
- መስኪዱን በሚገባ ስለማውቅ
- ምስክር ቅድም ተጠይቀው ሲመልሱ ፖሊሶች እንደተጐዱ መስክረዋል ከአካባቢው ሕዝብስ የተጐዳ የለም እንዴ?
- ሌላ የተጐዳ ሰው አለ ከፖሊሶች በተጨማሪ?
- አዎ የተጐዱ ፖሊሶችን አስቀመጥኩኝ
- ከፖሊሶች ውጪ ማለት ነው የአካባቢው ነዋሪ ወይም አካባቢው ሰው ?
- የተጐዳ የለም በወቅቱ የተጐዳ ፀጥታ አስከባሪ አካል ብቻ ፖሊሶች ብቻ
- እሺ የፀጥታ አስከባሪዎች ከየቤቱ መስኮት እና በር እየሰበሩ ሰውን ሲያወጡ የነበረ መሆኑን ያውቃሉ?
- ያወጣም አካል እንደሌለ ነው የማውቀው አላወጣንም በወቅቱ
- እሺ የፀጥታ አካላት ሰውን መሬት ላይ አስተኝተው ሲደበድቡ እንደነበረ ያውቃሉ?
- የተደበደበም ሰው የለም የደበደበም እንደሌለ ነው የማውቀው እኔ እስከነበርኩበት ድረስ
- እሺ ወቅቱ ዝናብ ነበረ አልነበረም?
- አልነበረም
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ አቃቤ ሕግ
- የለንም የተከበረው ፍ/ቤት
- ምስክር በፍ/ቤቱ ጥያቄ ቅድም ሌላ ሰው የተጐዳ የለም የሚል ነገር አስቀምጠዋት እናንተን ተከትሎ ውጭ ያለ ሰው የመጣ አለ የለም ከፖሊስሶች ውጪ ፖሊሶችን ተከትሎ ከመስኪዱ ውጪ ያለ ማለት ነው እናንተ ስትመጡ አብሮ የመጣ ሰው አለ?
- ማንም የመጣ የለም
- ስለዚህ ፖሊስ ብቻ ነው የነበረው?
- አዎ ፖሊስ ብቻ ነው የነበረው እዛ ውስጥ የነበሩ ወደኛ የሚወረውሩ አካሎች እንጂ ከጭ የመጣ ሕዝብ የለም
- ከውስጥ ነው ሰው የነበረው ?
- አዎ ሆኖ ወደኛ ወደ በሩ አካባቢ ሆኖ ወደኛ ድንጋይ የመወርወር ሁኔታዎች ነው የነበሩት
- እሺ እናመሰግናለን ምስክር ጨርሰዋል
- እሺ
- የዛሬው ችሎት በዚህ ተጠናቋል ቀሪ የአቃቤ ሕግ ምስክሮችን ለመስማት በአዳር ተቀጥሯል ነገ በተለመደው ሰዓት ትቀርባላችሁ።።

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

4ኛ ወ/ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

የካቲት 1 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች :- ብሰራት ተህልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ሰሳሽ :- አቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድምአገኝ ፣ዘረሰናይ ምስግና ፣ቴዎድሮስ ባህሩ ቀርበናል

ተሰሳሾች:- እነአቡበክር አህመድ 5ኛ ተከሳሽ ታመው ሄደዋል ሌሎቹ አላችሁ እሺ ጠበቆች ዳዊት ነጋሽ ፣ተካ ዳባ ፣ ሃሰን ሁሴን ፣ መሃመድ አብደላ ፣ ሞላልኝ መለሰ፣ ባህሩ መካንጋና አዲስ መሃመድ ቀርበናል እሺ 7 ጠበቆች ቀርበዋል የ28ኛ ተከሳሽ አልቀረበም 7 ጠበቃ ቀርቧል

- መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው አንዱን ቀሪ የአቃቤ ሕግ ምስክር ለመስማት ለመቀጠል ነው 2ኛ ምስክር ትላንት አስፈራርቶኛል ዘልፎኛል የሚል አቤቱታ አቅርቦ ነበር እሱ ላይ ተገቢውን ብይን ለመስጠት ነው ሌላው የተሰጠ እግድ አለ ፍ/ቤቱ የሰጠው እግድ ስለ እግዱ ዛሬ ምላሽ ለመጠበቅ ነው 3ኛ በዚህ መሰረት ይሄ ፍ/ቤት የተዘጋጀ ፊልም አለ ዶክመንተሪ ፊልም ሲተላለፍ የተዘጋጀ ፊልሙ ጀሃዳዊ ሃረካት በሚል ስም የተዘጋጀ ዶክመንተሪ ፊልም አለ እንዳይተላለፍ ቢተላለፍ ያው እዚህ ላይ የተዘረዘሩትን ችግር ያመጣል ይታገድልኝ ብሎ አቤቱታ ቀርቧል ፍ/ቤቱ በዛ መሰረት አግዷል ነገር ግን ያው እንደሰማነው ፊልሙ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

በመሃል ተላልፏል ዛሬ ያው የተቀጠረው ለምን ትእዛዙ አልተከበረም አቤቱታ ደርሷል የፍ/ቤቱ ትእዛዝ ደርሷል አልደረሰም የሚሉት እና ተያያዥ ነገሮችን ለማጣራት ነው አንዱ ጭብጥ እሱን በተመለከተ አሁን ፍ/ቤቱ ማጣራት ያለበት ትእዛዙ ደርሷል አልደረሰም ለምን ተላለፈ እና ሌሎችን ማጣራት አለበት በተያዘው ቀጠሮ ነገር ግን እሱን ሳናደርግ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ አለ ትእዛዙ ትላንት ደርሷል በጥር 29 ቀን 2005 የተሰጠ ትእዛዝ ይግባኙ ተሰምቶ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ የስር ፍ/ቤት ጥር 28 ቀን 2005 ዓ.ም. በመዝገቡ ቁጥር 124754 ላይ የሰጠው ትእዛዝ ተፈፃሚነቱ ታግዶ እንዲቆይ ብሎ እግድ ሰጥቷል ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ስለዚህ ከዚህ አልፎ ትእዛዙ ደርሷል አልደረሰም ምን ሆኗል የሚለውን መቀጠል አይቻልም ያ እግድ እስኪነሳ ድረስ ምንም መደረግ ስለማይቻል ደርሷል አልደረሰም ትእዛዙ የሚለውን ፍ/ቤቱ መቀጠል ተገቢ አደለም ለማንኛውም ፍ/ቤቱ ቀጠሮ ይዟል ይርባኙን እሰማለሁ ብሎ ማለት ነው ትጠራላችሁ ከዛ ሄዳችሁ ማጣራት ነው ፍ/ቤቱ የያዘው ቀጠሮ ለየካቲት 6 ይላል እዚህ ላይ አልተፃፈም ይደርሳችኋል ሲደርሳችሁ መከራከር ነው እዚህ ላይ ስለሱ የምናነሳው ጭብጥ የለም ስለዚህ እዚሁ ላይ ይበቃል ማለት ነው ስለ እግዱ ይደርሳችኋል ታዟል ይደርሳችኋል ሲደርሳችሁ ትከራከራላችሁ ኦኬ መዝገቡ በይግባኝ ተብሎ ነው አቃቤ ሕግ ነው ይግባኝ ያለው እዚህ ላይ ባለው እንትን ማለት ነው አቃቤ ሕግ ይግባኝ ብሎ ነው የታገደው ቀጠሮ ለየካቲት 6 ተይዟል ይግባኙን ለመስማት ቀጠሮም ተይዟል ይደርሳችኋል እናንተንም ተከሳሾችንም በጠቅላይ ፍ/ቤት በኩል ማለት ነው ቆዩ ቆዩ ዛሬ አሁን ተጣሰ ለምን አልተጣሰም የሚለው ክርክሩን መቀጠል ነው ክርክሩን እንዳንቀጥል ታግዷል እዛው ተከራከሩና እግዱ ሲነሳ ምናለባት መቀጠል ይቻላል ካልተነሳ ምንም ተጣሰ አልተጣሰ ለምን አልተከበረም ነው ውጤቱ አደለም ለምን አልተከበረም ስትል ትእዛዙ ኢፌክቲቭ ሲሆን ነው ለምን አልተከበረም ብለህ የምትጠይቀው እኮ ክርክሩን መቀጠል ስትችል ነው ክርክሩን መቀጠል ስለማንችል ነው ስለታገደ እዛው ትጠራላችሁ እዛው ተከራከሩ ምናልባት እግዱ ከተነሳ ክርክር ልንቀጥል እንችላለን ላንቀጥል እንችላለን ፍ/ቤቱ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ተመስርቶ ማለት ነው ስለዚህ እሱን ጠቅላይ ፍ/ቤት ይጠራችኋል ያላችሁትን እዛው አቅርባችሁ ትከራከራላችሁ ተከሳሾችም ጠበቆችም

- ግልጽ ነው አደለም የመጨረሻው ትእዛዝ እኮ ግልጽ ነው ቆይ አዳምጡ ይኸውላችሁ ይሄ ትእዛዝ ትእዛዙ ተፈፃሚ እንዳይሆን ማለት የተሰጠ ትእዛዝ አለ ተፈፃሚ እንዳይሆን ማለት

http://ethcriminalawnetwork.com/

ታገደ ማለት ነው ስለዚህ ከዚህ በኋላ መንቀሳቀስ አይቻልም የፍ/ቤት ስልጣን ነው እሱን ስልጣን ማክበር አለብን

- ምስክር ተዘልፈያለሁ ብሎ ነበረ ትላንት እስቲ ድምጽ ቀንሱዋ ጠበቆችም ቢሆን በኋላ ተወያዩ ግልጽ ነው እንትኑ ይደርሳችኋል ግልባጩ የጠቅላይ ፍ/ቤት እስካሁንካልደረሳችሁ ስለሚደርሳችሁ ያንን ተመካክሩና ተከራከሩ ትላንት ምስክር አንድ ከዚህ መስክሮ ሲወጣ ዝቶብኛል ተዘልፈያለሁ ብሎ አቤቱታ አቅርቧል እኛም ትላንት ለማጣራት ባጠገቡ የተቀመጡ ሰወችን ጠይቀናል ያው ሰወቹን ትላንት እንደጠየቅነው እሪከርድም የተደረገው አብዛኞቹ በዛ በኩል ያሉ ፖሊሶችም ተከሳሾችም እኛ ምንም አልሰማንም ብለዋል አንዱ ፖሊስ ድምጽ ብቻ ሰምቻለሁ የማን ከየት እንደሆነ የምን እንደሆነ አላወቅኩም ብሏል ስለዚህ አሁን የቀረበው ነገር ዘለፋው ተፈጽሟል አልተፈፀመም የሚለው ጭብጥ ነው ከተፈፀመ ውጤቱ ምንድን ነው የሚለው ያው የሕግ በግልጽ ተቀምጧል በፀረ ሽብርተኝነት አዋጁ ላይ የምስክር ጥበቃን አልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው ከ5 ዓመት እስከ 10 ዓመት ያስቀጣል ይላል በግልጽ የተቀመጠበት ነገር አለ ችሎት የመድፈር ጉዳይ ብቻ አደለም ይሄ ከዛም በተጨማሪ እስከ ብር ሰላሳ ሺ ያስቀጣል ነው የሚለው የችሎት መድፈር ብቻ ሳይሆን ሌላ ደረቅ ወንጀልም የሚሆንበት አግባብ አለ ስለዚህ ይሄን መሰረት አርገን ተፈጽል አልተፈፀመም የሚለውን ነው ያየነው አሁን ትላንት በሰማነው ማጣሪያ ሰውየው መናገሩን በድምጽ ከምስክሩ በስተቀር ሌሎቹ ምንም ያሉት ነገር የለም ስለዚህ አሁን ባለው በትክክል ምስክሩ ስለመዘለፉ ዛቻ ስለመፈፀሙ ከምስክሩ ቃል ውጪ በሌላ ነገር ምንም አልተጣራም በዚህ ባልተጣራበት ሁኔታ ምንም አይነት ከዚህ ያለፈ እርምጃ መውሰድ ፍ/ቤቱ አይችልም ስለዚህ ይሄን እርምጃ መውሰድ በግልጽ ስላልተጣራ ምንም መውሰድ አይቻልም ነገር ግን ከዚህ በኋላ መስክሮ የሚወጣም ይሁን ምንም ይሁን በምንም አይነት መልኩ ምስክር ላይ የሚደርስ ዛቻ ዘለፋ ካለ በማስረጃ የሚረጋገጥ ከሆነ ሕጉ ግልጽ ነው አሁን የተነበበ ነገር ስላለ እሱን ከግምት ውስጥ አስገብታችሁ ከዚህ አይነት ድርጊት እንድትታቀቡ አሁን ያለው ነገር ስላልተጣራ ምንም የምንለው ነገር የለም ወደፊት እንደዚህ አይነት ሃሳብካለ ከዚህ አይነት እንድትታቀቡ ነው እዚህ ላይ የምንሰማው አስተያየት የለም ስብሰባ አይደለም ችሎት ነው ትእዛዝ ነው እየሰጠን ያለው ስለትላንቱ ምንም የተረጋገጠ ነገር የለም ስላልተረጋገጠ ታልፏል ለወደፊት እንደዚህ አይነት ሃሳብ ካለ ሕጉ ጥብቅ ስለሆነ እሱን አውቃችሁ እንድትታቀቡ ነው አሁን የተባለው ወደ 2ኛውን ጨርሰናል ዛሬ የያዝነውን ሌላው ምናልባት የችሎት አካሄድ ላይ ወደ ምስክር ከመሄዳችን በፊት ከችሎት

http://ethcriminalawnetwork.com/

አካሄድጋር የተያያዘ ከጠበቆችም ከአቃቤ ሕግም አንዳንድ መታረም ያለባቸው የሚታዩ ነጥቦች አሉ እሱን ይዘን ምናልባት ዛሬ በዚህ የያዝነው ዛሬ የመጨረሻ ነው የሚሆነው ከዚህ በኋላ ያለውን አጀንዳ ይዘን ነው የምንቀጥረው ስለዚህ ዛሬም በቀረችው ሰዓት እና በምንቀጥረውም ይዜን አይነት ይዘን ተመልሰን በዚህ አይነት እንትን መገናኘት ስለሌለበት እና ዛሬ መታረም ስላለበት ነው ይዜን የምንናገረው በጠበቆች በኩል የሚታየው ምንድን ነው አንደኛው አብዛኞቹ ጠበቆች አርፍደው መምጣት ይታያል አርፍዶ መምጣት ጠበቃም አንድ ቢሆን ባለጉዳይም አንድ ቢሆን ኖሮ ውጤቱ ይታወቃል በሰዓቱ ካልተገኘ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለው በስነስርዓት ሕጉ በግልጽ ተቀምጧል አሁን ጠበቆች ብዙ ስለሆኑ ያ ስነስርዓት ሕግ ይጣሳል ወይ ግልጽ ነው ውጤቱ ስለዚህ ግልጽ ሕግ እያለ አርፍዶ መምጣት አለ ያን መጣስ ስለሆነ እሱን አስባችሁበት እንድታርሙ ነው ምክንያቱም ጠበቃ አንድ ቢሆን ኖሮ በሰዓት መገኘት አለበት በሰዓት ካልተገኘ ውጤቱ ስለሚታወቅ ማለት ነው በስነስርዓት ሕጉ መሰረት ያ ከሆነ ጠበቃ ብዙ ከሆነ ሌላ ለየት ያለ ስነስርዓት ሕግ የለንም ማለት ነው በዛ ስነስርዓት ሕግ ስለሚመራ እሷን እንድታስተካክሉ ነው ሁለተኛው ሳያስፈቅዱ የሚወጡ ጠበቆች አሉ ይዜ ደግሞ የከፋ ነገር ነው ችሎት ነው ችሎት ሰዓቱን ጠብቀው መግባት አለባቸው ሰዓቱን ጠብቀው መውጣት አለባቸው ይዜ አልተደረገም ሳያስፈቅዱ የሚወጡ አሉ ሰው ነው ችግር ሊያጋጥም ይችላል አስፈቅደ ለምን እንደሚሄድ ግልጽ አርጎ መውጣት ይችላል ይዜም ኤክሰፕሽን ነው ይዜ ይዜን ሳያደርጉ የሚወጡ አሉ ይዜ ስነስርዓቱን የተከተለ አደለም ይታረም ይዜ ሌላው ወደ አቃቤ ሕግ ከአቃቤ ሕግ በኩል አንድ ነጥብ አለ መታረም ያለበት እሱ ምንድን ነው ባለፈው ጥያቄ መጨረሻ ላይ ፍ/ቤት ፈቅዶላቸው ጠበቆች እንዲያነሱ ፍ/ቤት የፈቀደላቸው ጥያቄ ነበር ?

- እሱ ጥያቄ በፍ/ቤት ፍቃድ ሲቀርብ አንድ ፍ/ቤት በምን ግራውንድ ነው ይዜንን የፈቀደው የሚል ነገር አንስቶ ነገ ግን እሱን ነገር በወቅቱብይን ተሰጥቷል ብይኑ የተሰጠው ብይን ምንድን ፍ/ቤቱን ጥያቄው ተገቢነት የለውም ስለተባለ ወደ ሌላ ዝርዝር እንትን ማለት ጊዜ መውሰድ ስለሆነ ወደ ሌላ አላስፍንም ጥያቄው ተገቢነት የለውም ተብሎ በዛው አለቀ አሪዲ የተነሳ ነው ወይ አልተነሳም ብሎ ብይን ተሰጥቶ ስለታለፈ በዛው ታለፈ ለነገሩ ፍ/ቤቱ የተረዳው ግራ ቀኙ ጥያቄያቸውን ከጨረሱ በኋላ ድጋሚ ለጠበቆች የሚፈቀድበት የሕግ ስርዓት አለ ወይ በሚል ነው የተረዳው ፍ/ቤቱ ይዜ ከሆነ ፖዘቲቭ አስፔክት ነው ችግር የለውም እንደዚህ አይነት የሚፈቅደው የሕግ ስርዓት የለም ያ ከሆነ ማለት ነው ሌላም አስፔክት ስላለው ነው ጥያቄው ሌላ አስፔክቱ ምንድን ነው ፍ/ቤቱ ፈቅዶ ሩል ሰጥቷል

1943

376

http://ethcriminalawnetwork.com/

ፍ/ቤቱ ፈቅዶ ሩል ከሰጠ በምን ግራውንድ ሰጠ ብሎ ኩዌስጅን ማረግ ይግባኝ መስማት ያክል ነው የሚታየው ያ ደግሞ ለይግባኝ ሰሚው የሚቀርበው አቤቱታ እና ይግባኝ ሰሚው የሚያየው ነው ነገር የሚሆነው በአንድ አስፔክት በሌላ አስፔክት ፍ/ቤቱ ጥያቄውን የፈቀደው ምንድን ነው 136 ንዑስ አንቀጽ 4 አለ የወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ፍ/ቤቱ ማንኛውንም ጥያቄ በማንኛውም ጊዜ ማንሳት ይችላል ይላል ይሄ ማንኛውም ጥያቄ የሚለው እንግዲህ መሪ ጥያቄም ሊሆን ይችላል ላይሆን ይችላል አሁንም ፍ/ቤቱ ለፍትህ ያግዛል ያለውን ለራሱ የሚጠይቀው ነገር ሊሆን ይችላል ይሄ ለፍትህ የሚያግዝ ነገር ቀርቶብኛል ብሎ ባለጉዳዩ ከግራ ቀኙ የሚያነሳው ነገር ካለ ያ ነገር ለፍትህ የሚያግዝ ከሆነ ማንኛውን ጥያቄ ውስጥ ይገባል በሚል ነው ፍ/ቤቱ ያነሳው ይሄን ትርጉም ማንኛውም ጥያቄ የሚለው ሰፊ ስለሆነ ይሄንንም ያካትታል ነው ይሄንንም ስለሚያካትት በዛ አይነት መልኩ መስተናገድ ስላለበት መታረም አለበት ያልነውም ምናልባት ጥያቄው ካለቀ በኋላ እንዴት ነው ይሄ የሚቀርበው የሚል ከሆነ ችግር የለውም ነገር ግን የቀረበው በዚህ አስፔክት ነው ሰወቹ እራሳቸው ያቀረቡት ሳይሆን ኮንሰርን ነው ብለው ስላነሱ ያ ኮንሰርን ለፍትህ ያግዛል ብሎ ፍ/ቤቱ ካመነበት ከአቃቤ ሕግም ከጠበቃም ወስዶ የማይጠይቅበት ግራውንድ የለም ነው በዛ አንቀጽ መሰረት ማንኛውንም ጥያቄ ስለሚል እስከዚህ ድረስ ሰፍቶ መተርጐም አለበት እስከዚህ ድረስ ብቻ ሳይሆን ከዚህም ያለፈ ሊሆን ስለሚችል በዚህ መሰረት የጠየቀው እና ይሄም ቢታረም የሚለውን ለማንሳት ነው ለወደፊት ታርሞ መቀጠል ስላለብን ማለት ነው ይሄን ካልን በኋላ ምናልባት ሌላ አልተነሳም በሚለው የሚጨመር ካለ ይጨመራል

- እሺ አልተነሳም ሳይሆን ያው ኢምፓሲስ ለመስጠት ነው እና ትንሽ የጨመርነው የምስክሩ ትላንት የነበረው ነገር እሱ ቢረጋገጥ ኖሮ ከባድ ይሆን ነበር ከክብደቱ አንፃር ነው እኛም እስትሪክት ሆነን ጠበብ አድርገን የተረጐምነው ማስረጃውን ስለዚህ ተከሳሾችም ቢሆን ሌላ ችሎት ተከታታይም ቢሆኑ ጠበቆችም ሌላ ይሄ በዚህ ችሎት ችሎት መድፈር አታስቡ ችሎት መድፈር እስከ 1 ዓመት የሚያስቀጣ ነገር ነው እሱ በገንዘብም ሊያስቀጣ የሚችል ነገር ሊሆን ይችላል ይሄ አዋጅ ግን የተለየ ነው የተለያየ ፕሮሲጀር ነው ያለው ስለዚህ በዚህ አዋጅ መሰረት የፍ/ቤቱን ትእዛዝ ያላከበረ በግልጽ ተቀምጧል ስለዚህ ቀለል አድርገን ወደ ችሎት መድፈር ብቻ እንዳንወስደው [illegible] ነው በሌላ መንገድ ጠበቆች ላይ የተነሳው ነገር ባለፈውም አንስተን ነበር አዙን ተፈፃሚ ለማድረግ ሁለቱ ሴቶች ስማቸውን ጠርተን ነው ትላንት ነው መቼ እንደሆነ አንጂ ቀጠሮ ሁሉ ይዘን ነበር የሆነ

1946

377

ETCLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ትእዛዝ ሲሰጥ ምንም አይነት እንቅስቃሴ ሳይደረግ መቼ እንደሄዱም አላወቅንም ወጥተው ሄዱ ይሄ ትልቅ ከጠበቃ ኤቲክስ የወጣ ነው እኛ የምናውቀው እዚህ ውስጥ ያለ ጠበቃ ለተከሳሾች በተገቢው መንገድ ይከራከራሉ ብለን ነው ስለዚህ ክርክራችሁ ያለው እዚህ ነው ፍ/ቤቱ የሰጠውን ትእዛዝ እየተከታተሉ እዚህ የተነሳውን ጥያቄ እየተከታተሉ የህግ ክርክር ነው ጠበቃ የሚያቀርበው ፕሮፌሽናል ኢቲክስ አለው እራሱን የቻለ ስለዚህ እሱን ተከትሎ መሄድ እንጂ የሆነ ነገር ሲደረግ ወጥቶ እንደፈለጉ መግባት እንደፈለጉ እንትን ማለት ከሆነ በስነስርዓት እየተመራን አደለም ቅድም እንደተባለው ተከሳሾችም እየተጠቀሙ አደለም ስለዚህ አሁን እኛ ምንድን ነው ቅድም እንደተባለው ብዙ ስለሆናችሁ ነው ሁለት ሲቀር ሦስት ሲቀር እና ተከሳሾችም ዝም ስለሚሉ ያው እየተነጋገሩ ነው በሚል ግምት እየወሰድን ነው እንጂ ጠበቃ ቀጥ ብሎ ከተዋዋለበት ጊዜ ጀምሮ ተከሳሾቹ እስካሉ ድረስ የሚፈልገውን ነገር እያነጋገሩ ፋክት ከነሱ እየጠየቁ በስነስርዓት መስመር እያስገቡ መጠየቅ የጠበቃ ዋናው ስራ ነው ከዛ ውጪ ግን ብድግ ብሎ ጥሎ መሄድ አልገባንም ምን እንትን እንደሆነ እኛ አልገባንም እሱ ብቻ አደለም አርፍዶ መምጣት ቅድም እንደተባለው መቅረት እየተነጋገራችሁም ስለሚሆን ብዙም ስለሆናችሁ ያን ያህል ችግር የለውም እኛም ትንሽ ገፍተን ስለነበረ የቀጠሮ መደራረብ ይኖራል ሌሎቹ ሌላ ቀጠሮ ሄደው ነው እንዲህ የሚል በውስጣችን ይዘን ነው እኛ ነገር ግን አዚህ መጣችሁ ሌላ ቀጠሮ እኮ የላችሁም እዚህ መጣችሁ እንደገና አቋርጣችሁ የትኛው ፍ/ቤት ቀጠሮ እንደሄዳችሁ ማስረጃ አምጡ ስትባሉ አታመጡም ቆይ ሌሎቹ ደግሞ አርፍዳችሁ ነው የምትመጡት አርፍዳችሁ የትኛው ፍ/ቤት አርፍዳችሁ ነው የምትመጡት ደምበኞቻችሁ እኮ ጉዳዩ ምስክር ተሰምቶ አለቀ ስለዚህ ይሄ ተከሳሾችን የሚጠቅም አደለም ከአንድ ጠበቃ ኤቲክስም የወጣ ነው የሚሆነው ምናልባት አዋጁ የኮድ አፍ ኮንዳክቱ ቢመረመር እዛ ውስጥ አንድ ላይ ሊወድቅ ይችላል ስለዚህ ይሄ ቢስተካከል ነው እዚጋ ሕጉ የተቀመጠ ነገር አለ ያኔም ሲታሰም ይሄ ታሳቢ ተደርጐ ነው ከዛ በፖዘቲቭ አስፔክቱ ለምሳሌ ዳኛ በሕግ መስራት አለበት ልክ ነው ሕግ ሳይጠቅስ የሚሰራ ዳኛ ካለ እሱ ሌላውንም ያስደነግጣት ነገር ግን ቅድም በተነሳው መልኩ ከሆነ ተገቢ ነው ይሄን ሕግ መሰረት ተደርጐ ነው ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ ፊት ለፊት የማይታዩ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ ግን ደግሞ ወደውስጥ ሲገባ ያስገባል አያስገባም ሊያከራክሩ ይችሉ ይሆናል እዚህ ውስጥ አሁን ለምሳሌ አንድ ነገር ብንወስድ ለምሳሌ የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ ይጠይቃል መጨረሻ ላይ የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ ይላል እዚህ ሕግ ላይ የለም ማጣሪያ ጥያቄ የሚል ፎርም የለም ሦስቱ ብቻ ናቸው ያሉት ግን ማጣሪያ ጥያቄ ሆኖ አራተኛ

1947 378

http://ethcriminalawnetwork.com/

ይጨመራል ስለዚህ ይሄ ለምንድን ነው የሚሆነው ይሄ የማናቸውም ጥያቄ የሚለው ነገር ታሳቢ ስለሆነ ሌላውም ፎርም ጨምሮ ስለሚሄድ ነው እና ይሄ መሰረት ተደርጐ ነው የሕግ መሰረት እንዲያዝ መደረጉ ተገቢ ነው ግን ቅድም ዳኛው ቀደም ብለው በገለፁት መንገድ በፖዘቲቭ መንገድ ነው እኛ የወሰድነው ከዚህ ወጣ ያለ ከሆነ ግን እንዲስተካከል ከሚል ነው ያነሳነው ስለዚህ አሁን ካለን ጊዜ አንፃር ወደሚቀጥለው ብንሄድ ነው የሚሻለው

- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ያው ጠበቆች አሏቸው ስነስርዓት ሕጉም ይፈቅዳል ጠበቃው ስላሉ ያው ክርክሩ በዛው መንገድ መሄድ ይቻላል
- /የማይሰማ/ የምታቀርቡት
- በተደጋጋሚ ጊዜ ያው የተከበረው ፍ/ቤት ያው ላለመደጋገም የምናሰማው ለሁሉም ነው የሚመለከታቸው በቀጥታ
- አይ ገብቶናል አሁን ለሁሉም እየሰማን ነው ግን ዋናው ነገር በቀጥታ ዛሬ እሳቸው ላይ የማያርፍ ምስክር ካለ
- አዎ በቀጥታ የሚመለከታቸው የለም ምናልባት የተከበረው ፍ/ቤት ግልጽ ለማድረግ አሁን ሰውየው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው ከዚህ ችሎት የሄዱት በዚህ ያው ስነስርዓት ሕጉን 199 እንደዚሁ ስለሚፈቅድላቸው በዛ መልኩ ቢስተናገዱ በቀጥታ የሚመለከታቸው ምስክር የለም
- እሱ ነው አሁን በፊትም ይታይ እንደበረው በቀጥታ ከሌለ የታመመው ሰው በፊትም ይቀሩ ነበር
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም
- ምያለሁ
- ለምስክርነት ነው የመጡት?
- አዎ
- እሺ ለምስክሮች ጥበቃ ተብሎ ምስክሩ ያው የራሱን ስም ብቻ የአባቱን ስም ሳይጨምር እንዲገልጽ ነው ፍ/ቤቱ ትእዛዝ የሰጠው በዚሁ መሰረት የአባቶን ስም ሳይጨምሩ ይገልፁልንናል ስሞን
- እሺ ስሜ ሃሰን ይባላል
- እሺ ስንተኛ ናቸው አቃቤ ሕግ ?

1988 379

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተራ ቁጥር 76
- እሺ በፍ/ቤቱ 32ኛ ላይ ደርሰዋል በተሰማው ምስክር ልክ በአቃቤ ሕግ 76ኛ ላይ የተጠቀሰው ምስክር ቀርቧል በነማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ዛሬ?
- እኔ በወቅቱ ያው በነበረው ላይ አቡበከር እና ያሲን ኑሩ ላይ ነው
- ሁለት ሰው ላይ?
- አዎ ሌላ በስሙ አላውቅም የነበረውን በአካልም ብዙ ሰው ስለነበረ አለይም አቡበከር እና ያሲን ኑሩን ያውቁታል ?
- አዎ በእለቱ የዛንለታ አይቻለሁ
- እሺ በአካል ነው በስም ነው የሚያውቁት አቡበከር እና ያሲን ኑሩን?
- የዛን እለት በአካል አይቻለሁ በስም ሳይሆን ሁለቱንም
- አሁንም በአካል መለየት ይችላሉ?
- እችላለሁ
- እሺ ስለዚህ ያው ተነስተው እነሱ በተቀመጡበት መለየት ከቻሉ ይለያሉ ካልቻሉም ያው ተነስተውም ማየት ይችላሉ
- አቡበከር ኖት አደለም ጫፍ ላይ 1ኛ ተከሳሽ ማለት ነው መለየት ካቃቶ መቀመጥ ይችላሉ እሺ ከአቡበከር ጋር ዝምድና ጥላቻ አሎት?
- አረ በምንም ነገር የለኝም እኔ ከማንኛውም ዝምድናም ጥላቻም የለኝም
- እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- ቀሃ ብለው ያው እንደዚህ ፍ/ቤቱን እያዩ ለአቃቤ ሕግ እና ለጠበቆች ጆሮ ብቻ ነው የሚሰጡት ሲጠየቁ ያው የሚያውቁት ይመልሳሉ
- ችግር የለም
- እሺ አቶ ሃሰን ዛሬ የመጣሁት ቅድም በጠቀሷቸው ሰወች ላይ ለመመስከር ነው ብለዋል ?
- አዎ
- መቼ ነው የሚያውቋቸው ከመቼ ጀምሮ ነው የሚያውቋቸው እነዚህን ሰወች?
- እኔ ሰወቹን ሳውቅ በአጋጣሚ ለስራ በሄድኩበት 2004 ሰኔ መጨረሻ አካባቢ አስኮ አካባቢ አንድ የኮንስትራክሽን ስራ እሰራ ነበረ በዛ ለእምነቴ ፀሎት ለማካሄድ እዛ አካባቢ አወልያ አካባቢ ፀሎት ላደርግ ሄጀ ነው ያየሁት በፊት ያው ያለውም በሲዲ አውቃለሁኝ ሰወቹን ትክክል ነው ከዛ ውጪ ግን በአካል በምንም አልተገናኘንም የዛን እለት ነው በአካል

1949

350

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ያየኋቸው ስለዚህ እዛ አወልያ በሄድንበት ያው ጁምአ ቀን ነው ቀኑ ከጁምአ በፊት ትምህርት ያስተምሩ ነበረ በሚያስተምሩበት ሰዓት የነበርኩበትን እና የነበረውን ሁኔታ ነው

- ምን የተለየ ነገር ነበ ?
- የነበረው የዛንለታ ብዙ ሕዝብ ነበረ እኔም እዛው አካባቢ ገብቼ እንትን በምልበት ጊዜ መጅሊስ እኛን አይወክለንም መጅሊሱ ይውረድ አህባሽ የሚባል ኃይማኖት አስገብቶ ከመንግስትጋ ሆኖ እኛን እያተራመሰን ነው እና አንፈልገውም መጅሊሱ ይውረድ የሚል ትምህርት ነው ሲያስተምር
- ማን ነው ይሄን ያለው?
- አቡበከር
- ስሙን በምን አወቁ መጀመሪያ ሲገባ ሁስታዝ አቡበከር ገባ ብለው ልጆቹም አብረውኝ አሉ እራሱንም ስሙንም አስተዋውቆናል በግልጽ ስለዚህ ሁለቱም ጐን ለጐን ነበሩ የነበሩት ተራ በተራ ነው የሚናገሩት
- አቡበከር ብቻ ነው ስሙን ያስተዋወቀው?
- አዎ እና ያሲን ኑሩም ነበረ በአካል እዛው ሁለቱም በነበሩበት ሰዓት ከጁምአ በፊት በሚደረገው ከቱባው በፊት ነበረበው ትምህርት ሲያስተምሩም በትክክል የነበረውን አይቻለሁ
- እሺ
- ስለዚህ አህባሽ እኛን አይወክለንም መንግስት ሆነ ብሎ እጁን አስገብቶ መጅሊሱ ይውረድልን አህባሽን አስገብቶ እኛን እያተራመሰን ነው እና ከመንግስትጋር ተጣምሮ መጅሊሱ እኛን አይወክልም መጅሊሱ ይውረድልን የሚል ነው አንዱ ሁለተኛው እነዚህ ያሉ አህባሽ ሰልጠነው የመጡ ኢማሞች ምንም ነገር ቢነግሯችሁ አትስሟቸዉ እኛን ምንም ነገር እናንተም ቢነግሯችሁ አትስሟቸው እምነታቸውን ክደዋል እምነቱን የካደ ሰው ደግሞ ምንም ነገር ቢነግር ልትቀበሉት አይገባም እንደውም ከማዳመጥ ብትገሉትም ጅሃድ ነው እስከመባል ድረስ ያሉበት ሁኔታ ነው ያለው
- ማን ነው ይሄን ያለው ?
- አቡበከርም ያሲን ኑሩ ወደ መጨረሻው ላይ ያለውን ገልፀዋል እና አቡበከር በግልጽ ይሄንን ሲናገር ሰምቻለሁ
- እሹ ሌላስ ምን አለ አቡበከር?
- ሌላ ከዚህም በኋላ እኛ ብንታሰርም ምናልባት ብንሞትም ችግር የለብንም ለዲናችን ነው ለእምነታችን ነው ብንሞትም ይሄንን የጀመርነውን እሳት የሚያቀጣጥል እላህ ያስቀመጠው

1980 384

http://ethcriminalawnetwork.com/

ወጣት ሞልቷል ስለዚህ ምንም ችግር የለብንም አትፍሩ ለዲን ነው መሆን ያለበት ሃቂቃዉን ይዘን ልንሞት ይገባናል የሚል ነው

- እሺ ብንሞትም ለዲናችን ነው ማለት ምን ማለት ነው?
- እንግዲህ ያው ለእምነታችን ነው ማለት ነው
- እሺ ሌላ ያሲንስ ምን አለ?
- እሱ ደግሞ ወደ መጨረሻው ላይ እዚህ ሁላችሁም አሁን በቅርብ ቀን ከአስር ቀን በኋላ በሚደረገው የሰደቃ እና እዚህ አወልያ ላይ ባለው ሁኔታ ላይ ከየአካባቢያችሁ ላይ ጥሪ በምናደርግላችሁ ጊዜ ወደ አወልያ ይዛችሁ እንድትመጡ ሁሉንም ሙስሊም የሆነውን ነው ይዛችሁልን እንድትመጡ በቅርብ ጊዜ እዚህ አወልያ ላይ እንደዚሁ ሰፋ ያለ ማብራሪያ እና ሰፋ ያለ ትምህርት እንሰጣለን ያሉትን ወጣቶች ይዛችሁ እንድትመጡ የሚል ነው ሲያስተላልፍ የነበረው
- እሺ እንዴት ነበረ ሲንቀሳቀሱ የነበሩት ምንን ወክለው ነበረ እዛጋ የነበሩት?
- እነሱ አልገባኝም
- አይ ተከሳሾች ?
- ተከሳሾች ያው ሙስሊሙን ወክለናል እዛ ያለ ሙስሊሙን ወክለን ነው
- እኮ ይሄ ወክለ የሚለው ነገር ምን የተሰጠው ስያሜ አለ ወይ ሲናገሩ የሰሙት ነገር አለ ከዚህ ነው የመጣነው በማለት የገለፁት ነገር አለ?
- ከዚህ ቦታ ነው የመጣነው የሚል የተገለፀውን ነገር አልሰማሁኝም ግን አህባሽ የሚለውን ነገር ብቻ ቢነግራችሁ አትስሙ የሚለውን ነው
- ብቻቸውን ናቸው እንዴ?
- አለ ሕዝብ ሞልቷል ሌሎችም ሰወች አሉ
- አይ መደረክ ላይ የሚያስተምሩት ቦታ ላይ ብቻቸውን ነበሩ ሁለቱ ብቻ ነበሩ ሌሎቹ የሉም?
- አሉ በመድረኩ ላይ ቆመው ሲናገሩ የነበሩት ሁለቱ ናቸው እንጂ ሰው ብዛት አለው ሌሎችም ሰወች አሉ
- እሺ ይሄንን አህባሽን የሚያስተምሩ ኢማሞችን አትቀበሏቸው ብትገሏቸውም ጅሃድ ነው ይሄንን ማን ነበር ሲል የነበረው?
- አቡበክር ነው መጀመሪያ ላይ
- ተደግሟል እንዴ ይሄ ነገር?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተደግሚል ትክክል ሆኖ ያለው እያለ እንዳለ በያሲን ኑሩ ላይ ደግሞ የነበረው ወጣቶቻችሁንም ሁሉንም እስላማዊ የሆነውን ሰው ጥሪ አድርጋችሁ እንድትገኙልን እዚህ ስለዚህ ኡስታዝ ያላችሁ ትክክል ነው እና በዚህ አይነት ሁኔታ ያለውን ነገር በትክክል እንነጋገራለን ለዲናችን ነው የሚል እሱም ደግሞታል
- ለዲናችን ምን አለ ያሲን?
- መሞት አለብን
- ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ
- ምስክር አሁን አቡበከር አለ ያለውን መቼ ነበረ ይሄን ያለው ?
- ሰኔ መጨረሻ ላይ ቀኑን በግልጽ አላውቀውም ብዬ ነው ከዚህ በፊትም እኔ ምስክርነት ቃሌን የሰጠሁት ጁምአ ቀን ነው ሰኔ መጨረሻ ወር ላይ ነው
- የትጋ ሆኖ ነው ያለው ይሄን?
- መድረክ ላይ ነው
- የት መድረክ?
- አወልያ መስኪድ ውስጥ
- እስጋ የት ነበሩ?
- እዛው ነበርኩኝ ከፊት ለፊት ላይ እኔ ቀድሜ ነው የገባሁት ከጠዋቱ ወደ ሦስት ተኩል ላይነው የገባሁት ከጁምአ በፊት ነው ሲነገር የነበረው
- ስለዚህ መድረክ አካባቢ ተጠግተው ነበር ማለት ነው?
- ተጠግቻለሁኝ አጋ ቀድሜ ነው የገባሁት
- ጥሩ ይናገር የነበረው ቆሞ ነው ወይስ ቁጭ ብሎ ?
- ቆሞ ነው
- በማይክ ነው ያለማይክ?
- በማይክ ነው የተነገረው
- ጥሩ እስኪ አወልያ መስኪድ ከውስጥ ቀለሙ ምን አይነት ነው?
- ቀለሙ የቤቱ ?
- የግድግዳው ቀለም?
- የግድግዳው ቀለም ያው ነጣ ያለ ነው
- ወጥ ማለት ነው ከላይ እስከ ታች ነጣ ያለ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አለው ግን አሁን ይሄንን አሁን የዚህን ቀለም እኔ በዚህ እዚህ የምቀመጥበትን ቀለም እዚጋ ፊት ለፊቴ ላይ ያለውን እንጂ ላይ ላይ ያለን ነገር አሁን በዚህን ሰዓት ይሄ ነው ብዬ ላልለው እችላለሁ
- ጥሩ አወልያ ሲገባ እንዴት ነው እስቲ መስኪዱ እንዴት ነው የሚገባው?
- እንዴት አልገባኝም
- ዝም ብሎ አንድ ሰው ከውጪ መጣ እንዴት ነው አወልያ የሚገባው?
- ከውጭ የመጣ ሰው ማንኛው ጁምአ ሲገባ ብዙ ሰው ነን ገብተናል ምንም የተፈተሸንበት ምንም ያልንበት ነገር የለም መስኪድ ሲገባ እንደሚገባው ነው የገባሁት
- ያልኮት መስኪዱ ደረጃ አለው የለውም ወደ መስኪድ ሲገባ?
- ከውጭ ወደ መስኪዱ ሲገባ ደረጃውን ነው
- አለው የለውም?
- አለው
- አቡበክር በወቅቱ ምን አይነት ልብስ ነበረ የለበሰው?
- የለበሰው ጀለቢያ ነው ነፃ ያለ ጀለብያ አድርጓል ኮፍያ አርጓል
- ስንት ሰዓት አካባቢ ነበረ የተናገረው?
- እኔ የገባሁት ሦስት ሰዓት ከምናምን ነው እስከ አምስት ሰዓት ከሃያ አምስት እስከሚሆን ድረስ ንግግር እየተደረገ ነበረ
- አቡበክር የተናገረበትን ሰዓት ያስታውሳሉ ?
- እኔ በምንም ይንንን ሰዓት ብዬ ሰዓት ይገፍ አላየሁትም አላስታውሰውም ግን በትክክል እዛ ድረስ ከዛ በኋላ ወደ ኩትባው እና ወደ ሌላው ነገር ተጀምሯል ይሄንን አውቃለሁ
- ኦኬ ኩትባ ሲሉ ስብከት ማለቶ ነው ኢማሙ የሚያደርገው ስብከት ነው በጁምአ ቀን ?
- እሱ ከመደረጉ በፊት ዩ ኖው ይሄ ትምህርት ሲተላለፍ የነበረው እና ኩትባ እና ይሄ የነበረው ትምህርት ይለያያል ኢማሙ ያስተማሩት ሌላ ነው እነሱ ሲናገሩ የነበረው ይለያል
- ኢማሙ ከማስተማራቸው ቀደም ብለው ?
- በፊት የነበረ ትምህርት ነው ይሄ
- ቅድም ቀደም ሲል በሲዲም አቡበክርን አውቀዋለሁ ብለዋል?
- ያሲን ኑሩን ነው ያልኩት የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ያሲን ከሆነ እሺ ስለያሲን ንገሩን አስቲ ያሲንን በሲዲ ያውቁታል?
- አዎ

1953 3871

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን የሚያስተምረውን አድምጠው ነው?
- እንዴት?
- በሲዲ አውቀዋለሁ ሲሉ ሁስታዝ ነው ሁስታዞች ናቸው ብለዋል በሲዲም ቀደም ብዬ አውቀዋለሁ ብለዋል ?
- አዎ ሲዲውን ገዝቼ አዳምጥ ነበር ትክክል ነው በፊት
- እስቲ ምን አድምጠዋል በሲዲ?
- መንዙማዎችን የአላህን ፍሩ የሚል አንዳንድ ነገሮችን ስለ እምነቱ አዳምጣለሁኝ አዎ
- አሃ አላህን ፍሩ የሚል ከእምነቱጋ የተያያዘ ያስተምራሉ?
- የተያያዘ አዎ ትክክል ነው አዳምጥ ነበር
- በዛ ሲዲ ላይ ወጣ ያለ የተለየ ነገር አለ?
- ከዚህ በፊት እኔ ምንም ያየሁት ነገር የለም በሲዲው ላይ በፊት በነበረው ሲዲ ላይ ያየሁት ነገር የለም
- ቅድም ስልጠና ገብተው የወጡ ኢማሞችን አትስሚቸው ሲል ሰምቻለሁ ብለዋል አቡበክር ምንድን ነው ስልጠና ገብተው የወጡ ኢማሞች አሉ እንዴ?
- እሱን እንግዲህ እነሱ ይወቁት እኔ የሰማሁት እንጂ ምዬ ይሄ ነው ብዬ መናገር አልችልም የሰማሁት ነው እየተናገርኩ ያለሁት
- ምስክር አሁን የምጠይቆት የአወልያ መስኪድ እንዴት እንደሚገባ የተማየየ ማለት ነው የእሺ የአወልያ መስኪድ ከውጭ የሚመጣ ሰው መጀመሪያ የሚያገኘው ምንድን ነው በየትኛው በር ነው የገቡት ወደ አወልያ ?
- ከውጭ የመጣ ሰው በየትኛው እንዴት ይገባል የሚለው ተጠይቋል ሌላ ጥያቄ
- በየትኛው በር የሚለውን ልጠይቅ
- ከውጭ የሚገባ ሰው እንዴት ይገባል የሚለው ተጠይቋል ይሄ ጀነራል ነው ስለዚህ እንዴት ይገባል የሚለው ለማጣራት ስለሆነ ይሄ በቂ ነው ለሱ ሌላ ጥያቄ ካላችሁ
- እሺ ወደ መስኪድ ውስጥ ገብቻለሁ ነው ያሉን ምስክር ከመስኪዱ ስንተኛ ፎቅ ላይ ነበሩ?
- እኔ የነበርኩት መጀመሪያ ላይ ነበር የነበርኩት እና የመጀመሪያው ላይ ነው የነበርኩት
- ስንተኛ ማለት ነው?
- አንደኛው ላይ ነኝ
- ስንት ፎቅ አለው መስኪዱ?
- ፎቆቹን አሁን ቆጥሬ ይሄ ነው ይህ ነው ብሎ ማስረዳት በጣም የሚከብድ ነው

1984
258

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከዛ የሚከብድ ነገር እያስረዱ እኮ ነው አሁን ፎቅ
- የማያስታውሱ ከሆነ
- ስንት ሰዓት ደረሱ እርስዎ ወደ መስኪድ ?
- ነግሬሃለሁኝ ምናልባት ካላዳመጡ
- ስንት ሰዓት ነው ያሉት የነበረው?
- በግልጽ 3 ሰዓት ከ25 ገብቻለሁ አምስት ሰዓት ከሃያ ቆሟል ብዬ ለተከበረው ፍ/ቤት አስረድቻለሁ
- አምስት ሰዓት ከሃያ ቆመ ፕሮግራሙ ?
- አዎ
- ከዛ ምን ቀጠለ?
- ከዛ ሌላ ኢማሙ ተነስተው ባለው ሁኔታ ማስተማር ጀመሩ
- ስንት ሰዓት ላይ አምስት ከሃያ ላይ?
- አደለም አልጀመሩም እሳቸው አምስት ከሃያ ላይ ስድስት ሰዓት ከምናምን ላይ አዛን ተባለ ማስተማር ጀመሩ
- አሁን ፕሮግራሙ አምስት ከሃያ ላይ ቆመ አሉ ስድስት ከምናምን
- ማስተማሩ እሱ የቆመበትን ነው ሁለቱም አስተማሩ ያቆሙበትን ነው እኔ
- ልጠይቆት አሁን ይስሙኝና ጥያቄዬን በደምብ ሰምተው ይመልሱልኛል አምስት ከሃያ ላይ ማስተማሩ ቆመ ስድስት ከመናምን ላይ አዛን ተደረገ በመሃል ምን እየተደረገ ነበር?
- በመሃከል ያው ኩትባ ተደረገ የኩትባውን ስርዓት አዳምጠን ፀሎቱን አድርገን በኢማሞቹ ተለያየን
- አሁን ጥያቄዬ ገብቶት ከሆነ የተከበረው ፍ/ቤት እንዲረዳው ኩትባ የሚባለው ነገር ከአዛን በኋላ ስግደት መሃል ላይ ያለ ነገር ነው አሁን እነዚህ ሲያስተምሩ ነበሩ ያሏቸው ሁለት ሰወች አምስት ከሃያ ላይ ማስተማሩን አቆሙ ብለዋል ስድስት ከምናምን ላይ አዛን ተደረገ ከዛ በኋላ ነው ኩትባ የሚመጣው በአምስት ከሃያ እና በስድስት ከምናምን ላይ ምን ሲደረግ ነበረ?
- ሌላ ውይይቶች ከማይክ ውጪ የነበሩ ውይይቶች ነበሩ ያንን ምንም ነገር ስለማይሰማማ አጠገቡ ያለውን መተረማመስ እንጂ
- ውይይት እንዴት ነበር ሲደረግ የነበረው?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የዚህ የነበረውን እነዚህ ሰወች ቆመው ማይኩ ከተቋረጠ በኋላ የነበረ በግል ሁሉም እንዴት እንደዚህ ሊሆን ይችላል መሆን አለበት የሚል የእርስ በእርስ ነገር ተነስቷል
- እሚቃወም ሰው ነበረ ማለት ነው?
- ነበረ እዛም ይዤንን አይ ትክክል ነው የሚልም ነረ
- ምኑ ትምህርቱን ነው ወይስ?
- አዎ ከዛ አዛን ሲባል አዛን ሰምቶ ሁሉም አቆመ
- እሺ ትክክል አደለምም የሚሉ ነበሩ?
- ነበረ
- ከዛ እርስዎ ምን እያደረጉ ነበረ?
- እኔም እደማንኛውም ኡማ ገብቼ እያዳመጥኩ ነበረ የራሴን ልክ ነው ልክ አደለም የሚለውን የራሴን ወስጃለሁ
- እኮ አሁን እርስዎ ትክክል ነው አደለም የሚሉ ሰወች አይቻለሁ ብለዋል እስቲ እንዴት ነበር በመሃከላችሁ የነበረው ነገር?
- ስለሰወቹ ነው ስለባዮቹ አልገባኝም
- ምን ያህል ሰው ነበረ መስኪድ ውስጥ?
- መስኪዱ ሞልቶ ውጪ መአት ሰው ነበረ አደለም መውጣት የማይቻልበት በጣም እፍንፍን ያለበት
- ማይክራፎን ተዘግቶ የተወሰኑ ሰወች ትክክል ነው የተወሰኑ ሰወች ትክክል አደለም ሲሉ ነበር ማለት ነው?
- ትክክል ነው እንደዛ ነው
- ምን ያህል ይሆናሉ ትክክል ነው የሚሉት ትክክል አይደለም የሚሉት?
- መቁጠር ይከብዳል በዛን ሰዓት በወቅቱ ያለውን መቁጠር ማስታወስ ይከብደኛል አሁን አላስታውሰውም
- 3 ሰዓት ላይ የጁምአ ሰላት ይሰገዳል እንዴ ለምን መጡ እርስዎ?
- እኔ ቀድሜ ጁምአ ለመግባት
- ኮንስትራክሽን ስራ እሰራለሁ ብለዋል የስራው ሰዓት ነው 3 ሰዓም ምን ሊሰሩ መጡ?
- ስለዚህ እኔ አሁን ወደ ስራው ስለሌለ በአጋጣሚ እዛ ገባሁኝ ይህን ደግሞ መስኪድ መግባት ቀድሜ መግባት ስለነበረብኝ ገብቻለሁኝ ገብቼ እዛ በቆየሁበት አጋጣሚ ገባሁኝ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሰው መጣ ትክክል ነው ሌሎችም ልጆች ነበሩ በአጋጣሚ ብንቆይ ይሻላል እዚሁ ሃዲስ እናዳምጣለን የሚል ገባን

- ጥሩ እሺ ሁስታዝ ናቸው ብለዋል ምን ማለት ነው ሁስታዝ ?
- አስተማሪ ማለት ነው
- በመንዙማ ነው የማውቃቸው ብለዋል አቡበክርን ነው ወይስ የያሲንን መንዙማ ነው የሚያውቁት?
- የያሲንን አውቃለሁ
- ምን የሚል መንዙማ አለው ያሲን?
- እሱን እንግዲህ ምናልባት ደግሜ አስታውሼ አሁን አላስታውሰውም አውቀዋለሁ ሲዲውን አውቃለሁ የተለያየ አራት አምስት ሲዲዎች አሉ
- አይ አሁን እኔ የጠየቅኮት የማውቀው የያሲን መንዙማ ነው ብለዋል የያሲን መንዙማ ምን የሚል መንዙማ ነው ያለው ሰምቼዋለሁ አውቀዋለሁ ብለዋል ምን የሚል መንዙማ ነው ያለው?
- አሁን አላስታውሰውም
- ከየት ነው የገዙት መንዙማውን?
- መንዙማውን ማንኛውም ሱቆች ላይ አለ እስላማዊ ቪዲዮ ካሴት ቤቶች አለ
- መንዙማ ምን ማለት ነው?
- መንዙማ ማለት ያው የአላህን የነብዩን ውዴታ የሚገልጽ ነው
- በዜማ ማለት ነው?
- በዜማ ማለት ነው
- ዜማ እያወጡ የሚቀበል ሰው አለ መንዙማ ውስጥ?
- መንዙማ ውስጥ ሃዲስ አለ ሃዲስ እራሱን የቻለ አለ መንዙማ አለ ይሄ ይለያያሉ ሃዲሶች አሉ ቅድም አላህን እንፍራ እያለ የሚላቸው ሃዲሶች አሉ ብያለሁ
- ይበቃል ምስክር
- ምስክር ያሲን እና አቡበክር ሲናገሩ የሚቀርፃቸው ሰው ነበረ እንዴ እላ ?
- አቤት ይቀረፁ ነበር በቪዲዮ በሞባይል በመሳሰሉት የሚቀርጽ ሰው ነበር ከሕዝቡ መሃል?
- አላየሁኝም እኔ ለራሴ ሲቀርጽ ያየሁት ሰው የለም
- ይበቃል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ብንታሰርም ብንሞትም ሃቂቃውን ይዘን እንሞታለን አትፍሩ ብሏል ሃቂቃውን ማለት ምን ማለት ነው ?
- ሃቂቃ ማለት እውነት ማለት ነው እኔ እንደማውቀው በአተረጓጐሙ
- ሰኔ ወር 2004 ነው ቀኑ መቼ እንደሆነ ያስታውሱታል አንድ ሁለት ሦስት?
- መጨረሻ ሰኔ መጨረሳ ላይ ነው አላውቅም ብዬ ቅድምም ነግሬያለሁኝ አሁንም አላስታውሰውም ቀኑን
- ኢማሙ ማን ነበሩ ያሰገዱት በወቅቱ?
- ኢማሙንም ስማቸውን አላውቅም ቁጥባ ሲያደረጉ ሰምቻለሁ ነው ያልኩት
- እሺ አቶ ሃሰን በእለቱ በጣም ብዙ ሕዝብ ነበር ብለዋል በአወልያ መስኪድ እንደው ምን ያህል ሕዝብ እንደነበረ መገመት ይችላሉ ?
- በግምት እኔ ውጭ ላይ ስወጣ ቢያንስ ቢያንስ ከሦስት መቶ ከአራት መቶ በላይ የሆነ ሰው ነበረ ውጪ ላይም ውስጥም ላይ የነበረው ብዙ ሰው ነበረ
- ሲደመር ሦስት መቶ ወይም አራት መቶ ?
- እንደው ይሆናል ብዬ ግምት ነው እኔ እንደዚህ ይሄን ያክል አላየሁትም በጣም ብዙ ሰው ነበር
- እሺ በወቅቱ መጅሊስ አይወክለንም ብለው ሲያስተምሩ ነበር ብለዋል ?
- አዎ
- በሰኔ ወር 2004 ዓ.ም የነበረው መጅደሊስ አሁን በምርጫ ተለውጧል አደለ?
- ተለውጧል
- መጅሊስ አይወክለንም ብለው ሲናገሩ የነበረው መጅሊሱ በወቅቱ በሰኔ ወር 2004 የነበረው መጅሊስ በኃይማኖቱ ሕግ መሰረት የተመረጠ አይደለም በሚል ምክንያት ነው አደለም ?
- እኛ መጅሊሱ አይወክለንም መጅሊሱ አህባሽ የሚባለው ኃይማኖት አምጥቶ ከመንግስትጋር ተጠማምሮ እኛን እያተራመሰ ኃይማኖታችንን የሸጠ አካል ስለሆነ አይወክለንም ብለዋል እያለኩ ነው
- እኮ መጅሊሱ አይክለንም ሲሉ መጅሊሱ አይክለንም ያሉበት ምክንያት በኃይማኖቱ ሕግ መሰረት የተመረጠ አይደለም በሚል ምክንያት አይደለም በሚል ምክንያት አደለም ወይ ነው ያውቃሉ ወይ?
- ይሄንን ምክንያት አውቃሁ ነው ትክክል አይዳለም በሚል ሲያስተምሩ ሰምቻለሁ እያልኩኝ እኮ ነው አይወክለንም

1988

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ አህባሽን አንፈልገውም ሲሉ አህባሽ የሚባል አስተምሮን አንፈልግም ማለታቸው ነው አደል?
- አልገባኝም
- አህባሽም አንፈልግውም ብለው ተናርረዋል ብለዋል አህባሽን አንፈልገውም ማለት አህባሽ የሚባለውን አስተምሮ አንፈልግም ማለት አደለም ወይ ይሄን ማለታቸው አደለም ወይ ማለት ?
- እሱን እነሱ የወቁ እኔ አላውቅም እንግዲህ ያሉት
- እርስዎ እንዴት ነው የተረዱት አህባሽን አንፈልግም ሲሉ የእርስዎ አረዳድ ?
- እኔ ለራሴ እንግዳ ነው የሆነብኝ በእለቱ ስሰማው ምንድን ነው ምን ማለት እንደሆነ አላወቅኩም
- ስለ አህባሽ አስተምሮ የሚያስተምር ይማም የለም አደል?
- እስካሁን እኔ የሰማሁት ኢማም ምንም ምን ማለት እንደሆነም አልገባኝም አሁን
- አህባሽ የሚባለውን ነገር አያውቁትም?
- አላውቀውም ምን ማለት እንደሆነ እኔ አላውቅም
- እሺ እኛ ብንሞትም ለዲናችን ነው ሲሉ ለኃይማኖታችን ነው የምንሞተው ማለታቸው ነው አደል?
- ለዲን ማለት ያው ለኃይማኖት ነው ሌላ ነገር የለውም
- እኛ ብንሞትም ለኃይማኖታችን ነው የምንሞተው ማለታቸው ነው?
- አዎ
- አንድ ሙስሊም ስለ ኃይማኖቱ መጠበቅ እና መከበር መሞት አለብኝ ማለቱ ተገቢ አደለም እንዴ?
- እሱ የኔ እንትን ሳይሆን እኔ ለእምነቴ አዎ አትስገድ አትፁም
- ሲመሰክሩ ይዩት እስቲ እኛን እዩና አቁሙ ስንል ያቆማሉ ይሄ የፍ/ቤት ትእዛዝ ነው ቀጥ ብለው ቀጠሉ እርስዎ ትክክል አደለም ይሄ እና አዳምጡ
- እስቲ መቃወሚያዎትን
- ይሄንን በተመለከተ የተከበረው ፍ/ቤት አሁን በዚህ ደረጃ የግል አስተያየታቸውን የሚጠየቁበት ደረጃ አደለም በመስቀለኛ ጥያቄ ላይ ማለት ነው ስለዚህ እንዲህ ማለት አደለም ወይ ብለው እሳቸው እንዲያጠቃልሉ በዚህ ደረጃ መጠየቅ የለባቸውም በዋና ጥያቄም በዚህ ጉዳይ ላይ የተነሳ ነገር የለም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ምላሽ
- የተከበረው ፍ/ቤት ብንሞትም ለዲናችን ነው የሚለውን ነገር ተከላሾች አስተምረዋል ብለው ተናግረዋል ከዚህ ነው ጥያቄው የተነሳው ስጠይቃቸው ይሄን አስታውሼ ነው የጠየቅኩት እሳቸውም ማለታቸውን አረጋግጠው ነው መመለስ ጀምረው የነበረው ጥያቄው ይሄ ትምህርት ትክክለኛ የእስልምና ትምህርት አደለም ወይ የሚለውን ነገር እንዲመለክሩ ነው እሳቸው አንደኛ ሙስሊም ናቸው 2ኛ በመስኪዱም የተገኙት ደግም የኃይማኖት ትምህርት ለመከታተል እና ከዛም ደግሞ ያለውን የፀሎት ፕሮግራም ለመሳተፍ ነው በዚህ ሂደት ውስጥ ያወቁት እና የተረዱትን ነገር እንዲያስረዱ ነው ጥያቄው ስለዚህ ጥያቄው አግባብነት ያለው ነው
- ብይን ሰጥተናል አሁን የተነሳው በጠበቃ በኩል የተነሳው ጥያቄ እና መቃወሚያ የቀረበበት ለዲናችን ማለት ለኃይማኖታችን ማለት ነው ለኃይማኖታችን እንሞታለን ማለት በእስልምና ኃይማኖት መሰረት ትክክል ነው ለኃይማኖት መሞት በእስልምና ትክክል አደለም ወይ የሚል ጥያቄ ነው የተጠየቀው የቀረበው መቃወሚያ አንድም ይሄን ጥያቄ አልጠየቅንም በዋና ጥያቄ አልተነሳም የሚል ነው ሁለተኛው ይሄ የኦፒኒየን ጥያቄ የምስክሩ የግል አስተያየት ነው ምስክሩ የሙያ ምስክር አደለም ይሄ መቅረብ የለበትም የሚል ሁለት መቃወሚያ ቀርቧል የተሰጠው ምላሽ ጥያቄው ተነስቷል የሚል ምላሽ ሰጥቷል 2ኛ ምስክሩ ሙስሊም ናቸው የሄዱትም ይሄንኑ ለመከታተል ስለሆነ ጥያቄው ተገቢ ስለሆነ ሊፈቀድልን ይገባል የሚል ምላሽ ተሰጥቷል ፍ/ቤቱም ሁለት ነገሮችን መርምሯል አንደኛ ጥያቄው ተነስቷል አልተነሳም ተነስቷል ከተባለ የኦፒኒየን ጥይቄ ነው የኦፒኒየን ጥያቄ ነው መጠየቅ አለበት ወይስ የለበትም የሚለውን ነው ፍ/ቤቱ የመረመረው ተነስቷል አልተነሳም የሚለውን ስናየው በዋና ጥያቄ ላይ እኛ ለዲናችን እንሞታለን ብንሞትም አላህ ያስቀመጠው ወጣቶች አሉ እሚል ነገር አለ ዲናችን ደግሞ ኃይማኖታችን ማለት ነው ተብሎ ተመስክሯል ስለዚህ ለዲናችን እንሞታለን የሚለው በዋና ጥያቄ ተነስቷል አልተነሳም የሚለው በዚህ በኩል የተነሳ ስለሆነ አልተነሳም የሚለውን አልተቀበልንም ወደ ሁለተኛው ስንመጣ የምስክሩ የግል አስተያየት ወይም ኦፒኒየን ጥያቄ ነው ወይስ አደለም የሚለውን ነው ያየነው እሱን ስናይ ጥያቄውበግልጽ ስለ ኃይማኖት መሞት በእስልምና ተገቢ ነው ወይስ አደለም የሚለው ነው በግልጽ የኦፒንየን ጥያቄ ነው የኦፒኒየን ጥያቄ የሚፈቀደው የሙያ ምስክር ላይ ከሆነ ብቻ ነው ከዛ ውጭ አይፈቀድም ምስክሩ ስላዩት ስለሰሙት ፋክት እንዲያስረዱ ነው የተጠሩት የሙያ ምስክር አደሉም እና ኦፒኒየን ጥያቄ

http://ethcriminalawnetwork.com/

አይፈቀድላቸውም ስለዚህ ይሄ ጥያቄ ተገቢ አደለም ጥያቄው ምስክሩ የሰሙትን እና ያየው ላይ አተኩሮ እንዲመልስ ሆኖ ተስተካክሎ ሌሎች ጥያቄዎች ይቅረቡ የአሁኑ ጥያቄ ግን ተገቢ አደለም በዚሁ አልቋል

- እሺ አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት አቡበከር ሲያስተምር ሰምቻለሁ ብለዋል በአወልያ መስኪድ ትክክል ነኝ የሚያስተምረውን ትምህርት ተከታትያለሁ ብለዋል
- አዎ
- አቡበከር እንግዲህ በደምብ ከተከታተሉ ካስተማራቸው ትምህርቶች ላይ ነው የምጠይቆት የሚያስታውሱት ከሆነ ይመልሱልኛል ጥያቄያችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ መጓዝ አለበት ጥያቄያተንን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ይዘን መጓዝ አለብን ብሎ አስተምሯል አደል ?
- አልሰማሁም
- የሕገ መንግስቱን መርሆችን ጠብቀን እንንቀሳቀሳለን ብሎ አስተምሯል አደል ?
- ስለ ህገመንግስት ምንም እዛጋ ሲነሳ የሰማሁትም ያየሁት ነገር የለም
- እሺ ኢትዮጵያ የፍትህ ሃገር ናት ብሎ አስተምሯል አደል?
- የፍትህ አገር ናት ትክክል ነው አስተምሯል ግን ፍትህ አጥተንባታል የሚል ነገር ነው ሲያስተምር እዛው የነበረው
- ግልጽ አርጉ እስቲ የአሁኑን ድጋሚ ንገሩን እስቲ አልያዝንም
- የፍትህ አገር ናት ፍትህ አጥተንባታል
- የፍትህ አገር ናት ሲል የተረዱት እርስዎ ምንድን ነው?
- የፍትህ አገር ናት እንደኔ አረዳድ ያው በሕገ መንግስት
- ይቆዩ ምስክር ይሄም ደተመሳሳይ ነው የእርስዎ አረዳድ ሳይሆነ የሰማው ያየው
- እሺ ጥያቄያችን ሰላማዊ ነው ብለው አስተምረዋል አደል?
- አቤት ይደገምልኝ
- እሺ ጥያቄያችን ሰላማዊ ነው ብሎ አስተምሯል አደል?
- ጥያቄያችን ሰላማዊ ነው ሰላማዊ አደለም የሚልም ነገር አልሰማሁም
- መንግስታችንን በሰላም በካርድ እንደምንመርጠው መጅሊሳችንንም ለመምረጥ እድል ሊሰጠን ይገባል ብሎ አስተምሯል አደለም?
- የዛን እለት በነበረበት ሁኔታ
- አንድ ተጨማሪ ጥያቄ ልጠይቆት ከጁምአ ሰላት በኋላ በቦታው የነበሩት ሰወች በሰላም ነው መአደለም የተበታተኑት?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በሰላም ነው የተበታተኑት ምንም እኔ ሲፈጠር የነበረ በወቅቱ ከጁምአ በኋላ ምንም ያየሁት ነገር የለም ቀድሜም ነው የወጣሁት
- እሺ ከጁምአ ሰላት በኋላ ምንም ፕሮግራም አልነበረም አደል?
- እኔ ልክ እንደተሰገደ ሱና እንኳን አልሰገድኩኝም ወጥቻለሁኝ
- ከግቢ ውጪም ብዙ ሕዝብ ነበረ አደል?
- ብዙ ሕዝብ ነበረ አዎ
- እና እርስዎ እስኪወጡ ድረስ ከግቢው እስኪወጡ ድረስ ምንም ፕሮግራም አልነበረም ማለት ነው አደል?
- ምንም እኔ ያየሁት ከጁምአ በኋላ ያየሁት ነገር የለም
- ሁሉም ሰው ሰግዶ ወደመጣበት ነበር የሚሄደው?
- እሱን ነገርኳችሁ እኔ በሰላም ወደቤቴ ገብቻለሁኝ
- አይ አሁን እርስዎ ሲመለሱ
- መልሰዋል ከጁምአ በኋላ እኔ ወጣሁ
- አዎ ገባኝ የተከበረው ፍ/ቤት እርስዎ ሲመለሱ ሌላውም ሰው እየወጣ ነበረ አደለም?
- ትክክል ነው እየወጣ ነው ከኔጋ የተወሰነ ሰው ወጥቷል ምንም በሰላም ነው የወጣነው
- እሺ ጥያቄ ባይደጋገም ብዙ ተጠይቋል እና ሳይደጋገም
- እሺ ላለመድገም እሞክራለሁ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ሰሚር ቅድም ኮንስትራክሽን ልሰራ ሄድኩ ብለው ነበረ እዛ አካባቢ የማንን ቤት ሊሰሩ እንደሄዱ ያስታውሱታል?
- እኔ የሄድኩት የማንን ቤት የራሴ ስራ አለኝ አጋጣሚ አስታውሳለሁኝ የማስታውሰውን ሰነድ ልሞላ ነው ጨረታ የገባሁት ሄድኩኝ ጨረተ ሰነዱን ተቀብዩ ነው የመጣሁት በዛው ወረቀቱን እጂላይ እንደያዝኩኝ
- የምን መስሪያቤት ነበር ?
- የግለሰብ ነው
- ይሄ ከእንትን የወጣ ስለሆነ አስተያየት ባትሰጡ አስፈላጊ አደለም ኮንስትራክሽን ስራ ላይ ነበርኩ አርፍጀ 3 ሰዓት ሄድኩ ነው የተባለው ከዚህ ያለፈው ከጭብጡጋ የሚሄድ አደለም
- እሺ ቅድም አቡበከር እራሱን አስተዋውቆ ተናገረ ብለው ነበር ያሲን ኑሪም እኔ ያሲን ኑሪ ነኝ ብሎ ሲናገር ነው የሰሙት?
- አዎ ሁለቱም አስተዋውቀውናል እዛው ጐን ለጐን ግራና ቀኝ ነበሩ የነበሩት ሌላም በስተጀርባም ሰወች ብዙ አሉ ሁለቱም አስተዋውቀውናል ትክክል ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በቃ እሺ በጁምአ ሰዓት ኢማሙ በምን ቋንቋ ነው የሚያስተምሩት ወይ የሚናገሩት?
- መጀመሪያ በአረብኛ ይናገራሉ በአረብኛ ነው
- በአረብኛ ነው የሚናገሩት አደል?
- የሚተረጉምበትም በመሃል በመሃል አለ በአረብኛ ነው ኩትባ ሲያደርጉ የነበሩት
- የዛን ቀን ትርጉም ነበረ?
- አላስታውሰውም ምንም የወጣ ነገግ ስለሌለ እኔ ምንም የማስታውሰው ነገር የለም
- ቅድም ሲጠየቁ አቡበክር እና ያሲን ኑሪ የተናገሩት ሌላ ነው ኢማሙ ያስተማሩት ሌላ ነው በለው ነበረ እና አረብኛ ካልቻሉ ኢማሙ ያስተማሩትን ትምህርት እንዴት አወቁ?
- ያስተማሩት ሌላ ነው እነሱ ያሉት ሌላ ነው መጀመሪያ ኩትባ አዛን ከተባለ በኋላ ኩትባ የሚያስተምረው ሌላ አካል ነው ነው አሁንም በግልጽ ያስቀመጥኩት እኔ እነሱ ግን በአማርኛ በትክክል ሲያስተምሩ የነበሩት ሌላ ነው ይሄንን ነው
- እኮ አረብኛውን በምን አወቁ እያልኩ ነው?
- ኩጥባ ነዋ ኩጥባውን እንዴት አላውቅም እምነት ነውና ያው እንደ እምነቴ አውቃለሁኝ
- ስለዚህ አረብኛ ያውቃሉ?
- አዎ ሁጥባው ሲቆጠብ አውቃለሁኝ በትክክል
- ያሲን እና አቡበክር በተከታታይ ነው የተናገሩት ወይስ ሌላ ሰው መሃል ላይ ገብቶ ተናገረ?
- መሃል ላይ የገባ ሰው የለም ብገባ እኔ ምዬ ነው እንትን ያልኩት ለእምነቴ ነው ነገ የመልቃባ ቀመር አለብኝ ብዬነው አላህን ፈርቼ ነው እኔ ለነሱ የምደብቀው ነገር የለም
- ወደ መስኪዱ ሲገባ አልተፈተሸኩም ብለዋል ልክ ነኝ?
- አዎ
- ቅድም ሲጠየቁ ስለ ቀለም ሲያወሩ የታችኛውን ነበረ ያሉት ስለ ፎቁ አንድ አይነት ከለር ነው ያለው ፎቁም ?
- በቃ በቃ
- አይለያይም የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም ስለ ግራውንዱ ነው ያብራሩት
- ይበቃናል ግልጽ ነው ስለ ቀለም ኢሹውም አደለም ምስክሩ እውነት እዛ ሄዷል አልሄደም የሚለውን ለማጣራት ነው የተጠየቀው ያን ለማጣራት ይሄ ጥያቄ በቂ ነው
- ስለ አህባሽ የሚያውቁት ነገር አለ?
- አልገባኝም
- ተመልሷል

394 1963

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ፎቶቹ ሁሉ ሞልተው ነበረ በሰው ?
- ይሄም ተጠይቋል ስለ ሰው ብዛት ተጠይቋል
- ስለ 2ኛ ፎቅ አልተጠየቁም
- የሰው ብዛት ስለ ግቢ ስለ ውጪም ሦስት መቶ አራት መቶ ብለው ገምተዋል ተጠይቋል
- ምስክር አሁን አቡበክር እና ያሲን የተናገሯቸውን አሁን የነገሩን የተወሰኑ ደቂቃዎች ነው የሚፈጁት ይሄን ንግግግ ለማድረግ በመሃል ታዲያ ምን ተደረገ እነሱ ንግግር ይቺን ተናገሩ ቁጭ አሉ ከዛ ምን ሆነ ኢማሙ መጥተው እስኪያሰግዱ ድረስ?
- ተጠይቋል ይሄም ከአምስት ከሃያ ጀምሮ እስከ ስድስት ከምናምን ምን ተደረገ የሚለው ተጠይቋል
- እሳቸው ሦስት ሰዓት ጀምረው ስለነበር ነው
- እሳቸው የጠየቁት ጥያቄ አደለም እንደውም መርተው ማለት እዛ ውስጥ ያለው ስነስርዓት ስለሚያውቁት ይመስለኛል ተጠይቀዋል
- የሕዝብ ውክልና አለን ይሉ ነበር ይሄን ሲሉ ሰምተዋል ?
- አዎ
- ስለዚህ ጉዳይ ውክልና አ ላቸው ሲባል የሰሙት ነገር የለም እርስዎ ሕዝብ መረጣቸው በፊርማ መረጣቸው ሊሆን ይችላል አወልያ ?
- ማ?
- እነዚህ አሁን ይናገሩ የነበሩት?
- እኔ ማንም ይመረጥ ማንም አይመረጥ በዛን ሰዓት እነሱ ዳኢ መሆናቸውን አውቃለሁ እንጂ ሌላ የማውቀው ነገር የለም ብዬ ተናግሬያለሁ
- የለም በዛን ሰዓት ሳይሆን በተዘዋወሪም በቀጥታም ሊያውቁ የሚችሉትን መመስከር ስላለቦት ከዚጋር ከዚህ አወልያ ከሚያስተምሩትጋር በተመለከተ ሕዝቡ መረጣቸው የሚል ነገር አልሰሙም ?
- ወሬ እና በጆሮ መስማት ስለሚለያይ በጆሮዬ የሰማሁት ነገር የለም በወሬ ደረጃ ደግሞ ሰማሁ ማለት አይቻልም
- በወሬ ግን ሰምተዋል?
- ወሬ ሲወራ ወሬ እና መስማት ይለያያል
- ይኸው ምስክር ለምንራ መሰሎት ምስክር ምስክር የሚመስክረው አንድ ስላየው ሁለት ስለሰማው መመስከር ይችላል የሰሙት ነገር ካለ ይቀጥሉ

395 1964

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የለም የሰማሁት የለም ነው ያልኩት
- ቀጥሉ የአወልያ ግቢ ስንት መስኪዶች አሉት?
- መስኪዶቹን ቆጥሬ አላስታውሳቸውም አንድ ብቻ አደለም መስኪዶች አሉ እኔ እንደነገርኳችሁ ከሩቅ መጥቼ ገብቻለሁ በወቅቱ
- ከአንድ በላይ ናቸው ?
- ከአንድ በላይ አለ አዎ መድረሳ አለ መስኪድ አለ
- ሲወጡ እርስዎ መውጣት አይቻልም ብሎ በር የዘጋቦት የለም አደለ?
- መልሻለሁ እኔ በሰላም ነው የወጣሁት በዬ መልሻለሁ
- ተመልሷል
- ሲገቡ ጥበቃዎቹ በመደበኛ የስራ ቦታቸው ላይ ነበሩ አደል?
- መስኪድ ሲገባ እኔ ጥበቃ የትኛው ነው እንትኑ ገባሁኝ ብዬ ተናግሬያለሁ
- ማለት አሁን አወልያ ግቢ ብዙ ተቋም አለው ምናምን ስላሉ ሲገቡ በበር ነው የሚገቡት እና በሩ ላይ ጥበቃዎቹ ቦታቸው ላይ ነበሩ አደለም?
- ነበሩ ቀደም ብዬ ስለገባሁኝ ነበሩ ምንም እኔ ቀደም ብዬ ለስራ በሄድኩበት ስለገባሁ ምንም ያሉኝ ነገር የለም ገብቻለሁ
- እሺ ጥያቄያቸው ኃይማኖታዊ ጥያቄ ስለመሆኑ የሰሙት ነገር አለ በዚህ ንግግር መሃል ምክንያቱም ሦስት አራት አረፍተ ነገር ብቻ አደለም ከዚህ ሁሉ ሰዓት ውስጥ የሚሰሙት እና ጥያቄያችን ኃይኖታዊ ጥያቄ ነው ብሎ አቡበከር ወይም ያሲን ሲናገር ሰምተዋል ?
- የኃይማይኖት ጥያቄ እንደሆነ በወቅቱ ሲነሳ መጀመሪያ የኃይማኖት ጥያቄ እንደሆነ ሰምቻለሁ አልሰማሁም አልልም
- አዎ ምን ምን የኃይማኖት ጥያቄ ነው አሉ?
- መጅሊሱ እኛን አይወክለንም እምነታችንን በትክክል አልመራንም አህባሽ ለሚባል ሽጦ ከመንግስትጋር ተጣምሮ እያተራመሰን ነው የሚል አጀንዳ ነው የተነሳው
- ጥያቄዎቻችን 3 ናቸው የሚል ነገር አልነበረም ሦስት ጥያቄዎች አሉን የሚል ነገር አልነበረም?
- አራት ሦስት የሚል ይዜንን ብሎ አደለም ሰፊ ናቸው እማስታውሳቸውን ከውስጥ ነው የተናገርኩት
- እሺ አሁን ብዙ ሰው ተሰብስቦ ነበር አካባቢው ላይ ብለዋል ሰላማዊ ጥያቄ ነው የምናቀርበው የሚያስተዋውቅ ሰው ነበረ እነሱን?

396 1965

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተጠይቋል
- እሺ ምስክር እስካሁን ድረስ በተናገሩት አህባሽ የሚባል እምነት የለም ይሄን አስተምሮ የሚያስተምረን ኢማም የለም ነው ያሉት አደለም?
- ብሏል ይሄም ተጠይቆ እኮ መልሷል
- ስለዚህ እዛ በነበሩበት ሰዓት የሰሙት በሙሉ ስለ ሌለ ነገር ነው ማለት ነዉ እስከሚያውቁት ድረስ የሌለ ነገር የሚመለከት ነው
- ይኸውሎት ጠበቃ አን ይሄ አለ የለም ከአጠቃላይ ከተመሰከረው ጀጅ የሚደረግ ነው
- የሕግ ጥያቄም ስለሚያስነሳ ነው ይሄ ጉዳይ ምክንያቱም የሌለ ነገርን በተመለከተ የተባለ የተነገረ ነገር በሙሉ ኢምፖሲብል የሆነ
- አዳምጡ መጀመሪያ ይኸውሎት የለም ብለዋል እኮ እሳቸው የለም እኔ አላውቅም እንዲህ አይነት ነገር አልሰማሁም ሲነገር ብቻ ነው የሰማሁት አሉ
- ስለዚህ እስከሚያውቁት ድረስ ይናገሩ
- ቆይ ጠበቃ እስቲ አንዴ ስሙ ያው ሲናገሩ እንደምንሰማ እርስዎም ስሙንና ምስክሩ አህባሽ የሚባል አስተምሮ ስለመኖሩ እኔ አላውቅም ይሄንን የሚያስተምርም ኢማም ስለመኖሩም አላውቅም ነው ያሉት አህባሽ አምጥቷል መጅሊስ አይወክለንም የሚል ነገሮች ንግግር ደግሞ አለ ብለዋል ከዛ በኋላ ምስክሩ ስለሌለ ነገር ሰማ አሰማ ጀጅመንታል ነው ምስክሩ የጀጅመንታል የኦፒኒየን እንዲሰጥ አይጠበቅበትም ኦፒኒየን የሚሰጠው ምስክር ማን እንደሆነ ቅድም ተገልጿል ይታወቃልም ስለዚህ እርስዎ እዚህ ላይ ቆመው የሚጠይቁት ነገር ካለ እሱን መጠየቅ ይሄን መደጋገም ግን ተገቢ አደለም ይለፉት ይሄንን
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ድጋሚ ካለ
- እሺ አቶ ሃሰን ቅድም ለችሎቱ ሲገልፁ አቡበከር እና ሁስታዝ ያሲንን ከዚህ በፊት በሲዲም አውቃቸዋለሁ ብለዋል አደል?
- አዎ
- በሲዲ ሲያውቋቸው በምን አይነት ሲዲ ነው የስብከት ሲዲ ነው አሁን ሲዲው መንዙማም አለው ሃዲስም አለው ብለዋል እነሱን የሚያውቋቸው በሲዲው ላይ ምንሲያደርጉ ነው?
- በሲዲው ላይ እምነቱን ሲያስተምሩ ነው የማውቃቸው
- በማስተማር ብቻ ነው እንጂ በመንዙማ አያውቃቸውም ማለት ነው?
- አዎ በማስተማር ብቻ ነው የማውቃቸው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ሌላውአወልያ መስኪድ ግቢ ውስጥ ስንት መስኪዶች አሉ ተብለው ሲጠየቁ ከአንድ በላይ አለ ብለዋል ይሄንን እንዴት ነው ሊያውቁ የቻሉት እርስዎ ማለት መድረሳዎች ወይንም ሌላ ሌላ ክፍሎችን ነው ወይስ የፀሎት ቦታው እራሱ መስኪዱ ስንት መስኪድ ነው ያለው?
- መስኪድ ሲባል መድረሳ እላ ግቢ ውስጥ አሁን ቤቶች ነው እየጠየቁኝ ያለው እና ቤቶች ምን ያክል አሉ የሚል ከሆነ ብዙ አሉመስኪድ ግን አንድ ግቢ ውስጥ መስኪድ አንድ ነው ግን እላ ዙሪያ ላይ አሉ ነው
- ይበቃናል
- በተደጋጋሚ ጊዜ ስንት ፎቅ አለው ቀለሙ ምንድን ነው ተብለው ተጠይቀዋል ስንት ጊዜ ነው የሄዱት እላ መስኪድ እርስዎ?
- እኔ በአጋጣሚ ሰፈሬ እሩቅ ነው በጣም ያው መግለጽ ስላልተቻለ እንጂ የደረስኩበትን እና የነበረውን እኔ የሄድኩት ሁለት ቀን ብቻ ነው በአጋጣሚ
- መስኪዱን ለሁለት ጊዜ ነው የሚያውቁት?
- አዎ ስለዚህ ለሁለት ጊዜ ስለማውቀው እኔ የደረስኩበትን የነበርኩበት ነገር ላይ ብቻ ነው እንጂ ያየሁት ወደላይ ወጥቼ ከነበረው ሁኔታጋ ይሄንን አገናዝቤ አደለም
- ስለዚህ ግቢውን በአጠቃላይ አቀማመጡን አያስታውሱም ?
- አላስታውስውም
- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ አንዱ ተከሳሽ መንዙማ ያስተምራል ብለው ነበር በመስቀለኛ እና በድጋሚ ሲጠየቁ ግን መንዙማ አደለም ስብከት ነው ብለዋ ልየትኛው ነው ትክክል?
- ስብከት ነው
- በዛ ያልተመለሰው እና በዚህ የተመለሰው ስለሚለያይ ማለት ነው
- ምናልባት የተከበረው ፍ/ቤት ያው
- ማን ነው እሱ ሰውየው ?
- ያሲን ነው
- ስለዚህ የሱ ስብከት ነው ወይስ መንዙማ ነው የተለየ ነገር ስላለ?
- ስብከት ነው ቅድም ያው ከዚህም ከዚህም ሲሆን ብዥ የማለት ሁኔታ ነው ስብከት ነው
- ስለዚህ ትክክለኛ ስብከት ነው?
- አዎ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ጨርሰዋል እናመሰግናለን መሄድ ይችላሉ
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም
- ምያለሁ
- ለምስክርነት ነው የመጡት አደል
- አዎ
- በነማን ላይ ነው የማመስክሩት እርስዎ ከዛ በፊት ስም ይቅርታ ስሞን ያው የምስክር ስም የራስህን ስም ብቻ ነው የምትናገረው የአባትህን ሳትጨምር?
- አቡበከር
- ስንተኛ ላይ ናቸው አቃቤ ሕግ በምስክር ዝርዝሩ 41 ላይ የተጠቀሰ በተሰማው ሊስት 33ኛ ላይ ነው እሺ በነማን ላይ ለመመስከር ነው የመጡት?
- በሙባረክ ላይ
- በአንድ ሰው ላይ ብቻ?
- አዎ
- ሙባረክ ማን ነው?
- ሙባረክ አደም
- ሙባረክ አደምን በአካል ታውቀዋለህ?
- አዎ አውቀዋለሁ
- መለየት ትችላለህ አሁን?
- አዎ
- እሺ ተነስተህ ለይልን ሙባረክን ምን የለበሰ በልብሱ ንገረን ሙባረክ አንተ ነህ ስንተኛ እሺ 20ኛ ተከሳሽን አሳይቷል ከሙባረክ ጋ ጥል ዝምድና አለህ?
- የለኝም
- እሺ ዋና ጥያቄ ይቀጥል አቃቤ ሕግ
- እሺ አቡበከር ሙባረክን ከመቼ ጀምሮ ነው የምታውቀው ?
- ሙባረክን የማውቀው እረብሻ ሲነሳ አካባቢ
- መቼ ነው እረብሻው ማለት መቼ ነው?
- ከታህሳስ ጀምሮ እስከ ጥር መጨረሻ
- የትኛው አመተምረት ላይ ነው ስንተ አመተምረት?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- 2004 ከታህሳስ መጨረሻ እስከ ጥር ድረስ
- እሺ በምን አግባብ ነው የምታውቀው ?
- ያው ልሰግድ ስሄድ ጁምአ ጁምአ የዛን ሰዓት
- የት ነው ስግደት ቦታው ?
- አወልያ
- አወልያ የት አካባቢ ነው የሚገኘው ?
- አወልያ ኮልፌ ቀራንዮ አስኮ አካባቢ
- ምን ሲያደርግ ነው የምታውቀው ተከሳሽን?
- ያው ሲያነሳሳ ነው
- ምንድን ነው ማነሳሳት ማለት ማንን ነው የሚያነሳሳው?
- ተማሪዎቹን
- የምን ተማሪዎችን ?
- የአወልያን ትምህርት ቤት
- ምን እያለ ነው የሚያነሳሳው?
- መጅሊስ አይወክለኝም ሙሳሊም እና እሳት ከነኩት አይፈራም በኃይማኖታችን አንደራደርም በቃ እንዲህ አይነት ነገሮችን
- ሙስሊም እና እሳት ምን አለ?
- ከነኩት አይፈራም
- እሺ ሌላስ?
- ከሙስሊም ተወክለው የመጡት ንግግር ሲያደርጉ
- ከየት ተወክለው የመጡት?
- ከእንትን ይመስለኛል ተወክለው የመጡት ንግግር ሊያረጉ ማለት ነው እነሱን ለማግባባት ተማሪዎችን ለማረጋጋት ማለት ነው እነሱን ምክክር ሲያደርጉ እንትናቸውን በቃ አይወክሉንም እሳቸው የሚናገሩት ነገር ትክክል አደለም ጥያቄያችንን አይመልሱልንም ብሎ ያው በመመነጫጨቅ ሲመልሳቸው አይቻለሁ
- ምን አደረጋቸው አመነጫጭቆ እሳቸው በምን ነበር ሲናገሩ የነበሩት?
- እሳቸው በማይክ ነበረ በቃ ማይካቸውን ነጥቆ
- ማይክራፎኑን ምን አደረገው?

1969

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ነጥቋቸው በቃ አይመልሱልኝም ይሄንን ጥያቄያችንን አይመልሱልንም አይችሉም ብቃት የላቸው ብሎ ያው ተማሪዎቹን ትራት እያረገ ሲያነሳሳ ነበር
- ማይካቸውን ከተቀበለ በኋላ ምን አደረጋቸው እሳቸዉን?
- በቃ እሳቸውን ወደዛ ገፍትሮ በቃ ሙስሊሙን ያው ቅድም ሲል የነበረውን ነገር ከንደገና ማነሳሳት ጀመረ
- ተወክለው ለማረጋጋት የመጡ ሰወችን ወይም ደግሞ ተወካዩን ግለሰብ ገፈተራቸው ነው ያልከውን ወረወራቸው?
- አዎ ማይካቸውን ተቀብሎ በቃ ወደዛ አረጋቸው
- ወደዛ የሚለውን ግለጽልን እስቲ አሁን ፍ/ቤቱ ?
- ገፈተራቸው
- አሁን የምትለው ቃል ስለሚመዘገብ ከምልክቱ ይልቅ በቃላት ብትገልፀው ?
- ገፈተራቸው
- እሺ አንድ ቀን ብቻ ነው እንዴ ያየኸው ሙባረክን ?
- ጁምአ ጁምአ ሁልጊዜ አየዋለሁ
- ስትሄድ ምን ያደርግ ነበር በሌላ ጁምአ ደግሞ ?
- ያው በቃ ይሄንን ተግባር ነው የምፈጽመው ሁል ጊዜ
- ሁልጊዜ ምን አንድ አይነት ተግባር ነው?
- አዎ ያው ከላይ ሆኖ እሱ መድረክ ላይ ሆኖ ታች ያሉ ተማሪዎችን በቃ መጅሊስ አይወክለንም በቃ የተለያዩ ጥቅሶችን በመናገር ትራት ያረጋል ተማሪዎቹ ተነሳሱ
- የተለያዩ ጥቅሶችን ያልካቸውን የምታስታውሳቸው ካሉ ቢመዘገቡ?
- እኮ ያው ነው መጅሊስ አይወክለንም በቃ ሙስሊም እና እሳት ከነኩት አይፈራም በኃይማኖታችን አንደራደርም
- ለመጀመሪያ ጊዜ ያየኸው መቼ ነው ቀኑን ታስታውሰው ይሆን?
- አላስታውሰውም
- የወሩ ስንተኛ ቀን እንደሆነ አታስታውሰውም?
- አዎ
- በወሩ መግቢያ አጋማሽ መጨረሻ ?
- በቃ ከታህሳስ መጨረሻ እስከ ጥር ድረስ
- ስንት ጁምአዎች አይተሃል?

1970

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቢያንስ ከአምስት ከስድስት በላይ
- እሺ ዋና ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ
- በኃይማኖታችን አንደራደርም ማለት ድርድር ነበረ ሌላ የገለፀው የሰሙት እርስዎ?
- ድገሚልኝ እስቲ ከንደገና
- በኃይማኖታችን አንደራደርም ብለዋል እያልክ ነበረ ማለት ድርድር ነበረ ማለት ነው እርስዎ ምንድን ነው የተረዱት?
- እሱን አላውቅም በቃ በኃይማኖታችን ያው ማንም ጣልቃ እንዲገባብን አንፈልግም ለማለት ፈልገው ይመስለኛል
- ሌላ ተጨማሪ ያነሱት ጥያቄ አልነበረም ተማሪዎች ይህንኑ ብቻ ነበረ የሚሉት?
- እሱ ሲል ነው የሰማሁት
- ለማረጋጋት የመጡት ሰውዬ ከየት ነበረ የመጡት?
- አላውቅም
- ከየት እንደመጡ አላወቅክም?
- አዎ
- ለማረጋጋት መምጣታቸውን በምን አወቅክ ታዲያ?
- ያው ለማረጋጋት ተማሪዎች ተረጋጉ ሲናገሩ በቃላት ሲናገሩ ነው የሰማኋቸው
- መናገር ጀምረው ነበር?
- አዎ
- ምን ምን ተናገሩ?
- ያው መድረክ ላይ ገና ሲወጡ ጮሁ
- ስለዚህ አልተናገሩም?
- አዎ ማይካቸውን እንደያዙ መናገር
- አይ ቅድም ሲናገሩ ቸሳቸው የሚሉትን አትስሙ አለ ስላልክ የተናገሩት እና እንዳትሰሙ የተባለው
- ከየት እንደመጡ ያው ከመጅሊስ ስለመጡ ያው የመጅሊስ አመራሮች ደግሞ እኛን አይወክሉንም ማለቴ ከዛ ይመስለኛል የመጡት ያው ከሙስሊም ከእንትን እና እሳቸው ሲመጡ ያው በመጮህ እሱ እንትን አላቸው ያው ሁሉም አየጮኸ እሳቸውም ተመለሱ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኚህ ቅድም ለማረጋጋት መጡ ያልካቸው የትጋ ሆነው ነበረ የሚናገሩት ሊናገሩ የመጡት የትጋ ነበረ?
- ውስጥ አወልያ ውስጥ ካፌው አካባቢ
- ውስጥ ማለት ግቢ ውስጥ?
- አዎ
- ሜዳ ላይ ማለት ነውወ?
- ሜዳ ላይ
- ምን መድረክ ወምበር እንደዚህ ነገር ተዘጋጅቶ ነበረ ወይስ?
- የሆነ ድንጋይ ነገር አለ ደረጃ ነገር
- እዛ አካባቢ ተማሪ ብቻ ነበር እንዴ?
- አዎ
- ስለዚህ ቅድም እሚናገሩት ማይክ እንደነበረ ገልፀሃል ?
- አዎ
- ስለዚህ ሰውም እንዲቀመጥበት ከድንጋይ ውጪ ሌላ ነገር አልነበረም? አልነበረም ያው ማለቴ መድረክ ውስጥ እንዲገቡ ተነገራቸው ተማሪዎቹ አንገባም አሉ ያው በነሱ ትሪት አድራጊነት ማለት ነው ውጭ ላይ ወጥተው ሊናገሩ ፈለጉ አልቻሉም
- ሰውየው ስለዚህ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለው ነበር ?
- ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለው አደለም ቁመው ነው ያልኩት ከተማሪዎቹ ከፍ ብለው ደረጃነገር ነው
- ቆመው ነበር?
- አዎ
- ወደዛ ገፈተራቸው ከዛ ማይኩን ቀምቶ ተናገረ ብለሃል ?
- አስቀምጦ ተናገረ አላልኩም
- ማለት ሙባረክ ከሰውየው ማይክ ቀምቶ እሳቸውን ገፍትሮ ብለሃል ከገፈተራቸው በኋላ ምን ሆነ ምን አደረጉ ሰውየው ተገፈተሩ ከዛ ምን ሆነ?
- ማናገር ስላልቻሉ ወደመጡበት ተመለሱ
- ወደ ውጭ ተመለሱ ?
- አዎ
- አንተ በደምብ እያየህ ነበረ አደለም ሰውየውን?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቆሜ በደምብ እያየሁ ነበር
- ተገፈተሩ ከዛ እራሳቸው ወደ ውጭ ወጡ ጥለው ወጡ ማለት ነው ?
- አዎ
- እስከ የት ድረስ አየሃቸው አንተ ሲወጡ ?
- እኔ እዛው ነኝ አልወጣሁም
- አይ የት ድረስ ሸኘሃቸው በአይንህ ለምሳሌ በአይንህ ሊሆን ይችላል?
- በአይኔ ያው ዞረው ሲሄዱ አይቻቸዋለሁ
- ዞረው እስከበሩ ሲወጡ ምናምን አየህ?
- እስከ በሩ አላየሁኝም ዞረው ተመልሰው ሲሄዱ አየሁ
- ተመልሰው ሄዱ ከዛ ንግግሩ ቀጠለ ሙባረክ ተቀበለና ንግግሩ ቀጠለ?
- አዎ ሙባረክ ያው ቅድም ሲል የነበውን ነገሮች ማረግ ጀመረ
- ሰው ቆሞ ነበረ ወይስ ቁጭ ብሎ ተማሪዎቹ ያዳምጡ የነበረው?
- ቆመው ነው ሁሉም
- ሰውየው ሲሄዱ ቸል አላቸውና የሙባረክን ንግግር ማዳመጥ ቀጠሉ?
- አዎ
- ቅድም በየጁምአው ከታህሳስ መጨረሻ እስከ ጥር ባለው በየጁምአው ለሰላት ወይም ለፀሎት ስትሄድ እንደምታውቀው ገልፀሃል ተማሪዎችም በየጁምአው ነበረ የሚሰበሰቡት?
- ከጁምአም ውጪ ይሰበሰባሉ ላልተወሰነ ሰዓት ከጁምአም ውጭ ይሰበሰቡ ነበር እዛው ግቢ ውስጥ አልወጣም ብለው ላልተወሰነ ሰዓት እዛው እንደሆነም አዉቃለሁ የሰፈሬ ሰው ስለሆነ ማለት ነው
- አንተ የዛ ሰፈር ሰው ነህ?
- አዎ
- ከግቢ አልወጣም ማለት እዛው ማደር ወይስ ቆይቶ መውጣት?
- ማደርም መዋልም
- አንተ ግን የምትሄደው ጁምአ ጁምአ ብቻ ነው?
- አዎ
- ውለው ሲያድሩ ምን እንግዲህ ሰው ውሎ ሲያድር ምግብ ያስፈልገዋል ስለዚህ የሰማኸው ነገር አለ ባትሄድም እንዴት ነበር?
- ስለዚህ አላውቅም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አቡበከር ተማሪዎች ስትል እስካሁን ምን ማለት ነው ተማሪዎች ማለት አወልያ ግቡ ውስጥ ትምህርት ቤት አለ እንዴ?
- አዎ አለ
- የምን ትምህርት ቤት ነው ያለው ?
- ከኢለመንተሪ እስከ ኮሌጅ
- ምን ያህል ተማሪዎች አሉ ታውቃለህ?
- አላውቅም
- እሺ ብዙ ናቸው ግን?
- ብዛት አላቸው አዎ
- ይሄ መጅሊስ አይወክለንም የሚለውን ጥያቄ ተማሪዎች የተማሪዎች ጥያቄ ነው አደል?
- ማለቴ ጥያቄው የማን እንደሆነ ባላውቅም ሲጠይቁ ሰምቻለሁ
- ተማሪዎቹ ይጠይቁ ነበር ?
- አዎ
- ሙባረክ መጅሊስ አይወክለንም ብሎ ሲናገር ተማሪዎቹ ምንድን ነው ያረጉት?
- ያው የሱን ቃል እየሰሙ ያው ያስተጋባሉ እነሱን እንደማይወክላቸው ይናገራሉ
- መጅሊስ አይወክለንም ይሉ ነበረ ተማሪዎቹ?
- አዎ
- እሺ ምስክር ቅድም ለማረጋጋት መጡ ያልካቸው ሰው ስንት ሰዓት መጡ?
- በግምት ከአራት ሰዓት እስከ አምስት ሰዓት
- ተማሪዎቹ ስንት ሰዓት ተሰበሰቡ ከመምጣታቸው በፊት ?
- ከዛ በፊት
- ስንት ሰዓት ነው?
- ከሁለት ሰዓት ጀምሮ ነው የጀመሩት
- አንተ ስንት ሰዓት ገባህ ወደ ግቢው?
- ሦስት ሰዓት ተኩል አካባቢ
- ሁለት ሰዓት መሰብሰባቸውን በምን አወቅክ?
- የተማሪ መግቢያ ሰዓት በዛ ሰዓት
- እና ግምት ነው እንጂ አረጋግጠህ አደለም?
- በትምህርት ሰዓት ገቡ ያው በገቡበት ሰዓት ጀመሩ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አንተ ተማሪ ነህ እንዴ?
- የዛ ሰፈር ሰው ነኝ
- አኬ ምን ልታደርግ ገባህ ታዲያ?
- ሁሉም ነበር ሲጮሁ ምን ተፈጠረ ተብሎ ሁሉም ነው የገባው ማንኛው ሰው ገብቷል ሲቪል ሰው ማለት ነው ከተማሪ ውጪ
- ተማሪው ለምን ይጮህ እንደነበረ የምታውቀው ነገር አለ?
- አላውቅም
- መምህሮቻቸው ተባረው የነበረ መሆኑን ታውቃለህ?
- አይ ይመለሱልን እያሉ ሲናገሩ ነው እንጂ ተባረው መሆኑን አላውቅም
- ይመለሱልን ሲሉ ምን ማለት ነው ተባረው ነበረ ማለት ነው?
- ሜይ ቢ ሊሆን ይችላል
- የቁርአን ት/ቤታቸው መዘጋቱን ታውቃለህ?
- መቃወሚያ አለኝ የተከበረው ፍ/ቤት
- አላውቅም
- በዋና ጥያቄ አልተነሳም አሁን እየተጠየቀ ያለው
- አላዉቅም ብሎ መለሰ
- ንግግር ሲያደርጉ የነበሩት ሰው ከሄዱ በኋላ ተማሪዎቹ ፕሮግራማቸውን ቀጥለዋል ብለዋል ምን ፕሮግራም አደረጉ ከዛ በኋላ ?
- ያው ተሰብስበው ያው ይሄንን ቃል ነው ሲናገሩ የነበሩት ፕሮግራም የላቸውም
- ለምሳሌ ተማሪዎቹ አሰሙ ካልከው መፈክር ውስጥ ኢስላም ሰላም ሲሉ ነበረ አደል?
- እሱን አላየሁም
- የአሸባሪነትን እንቃወማለን ሲሉ ነበረ አደል?
- መቃወሚያ አለን
- እህ?
- ማለት ይሄን በዋና ጥያቄ እኛ ስለ ሽብር ጉዳይ የተነሳ ነገር የለም አሁን እሳቸው የሚፈልጉትን አዎ እንዲሉ ነው በመስቀለኛ ጥያቄ ምን እየተጠየቀ ነው አልገባንም የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ መልስ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተከበረው ፍ/ቤት በእርግጥ በመስቀለኛ ጥያቄ ምን ምንደምንጠይቅ እኛ ነን የምናውቀው የተከበሩ አቃቤ ሕግ አደሉም ነገር ግን ይሄም ሆኖ ተማሪዎች መፈክር ሲሉ ነበረ ብለው በግልጽ ተናግረዋል ምስክሩ እና ካሉት መፈክር ውስጥ እየመራን እነዚህ ይገኛሉ ወይ ስንል ምስክሩ ካወቀ አዎ አውቄያለሁ ካላወቀ አላውቅም ወይም አልተባለም ይላል ስለዚህ ይሄ አልተነሳም የሚያስብል ምንም ነጥብ የለውም እና ጥያቄያችንን ብንቀጥል ይፈቅድልን
- ብይን ሰጥተናል ጥያቄውን ምስክሩ አላውቅም ብለው መልሰዉታል ነገር ግን እየተቃወመ የተናገረ ስለሆነ ተነስቷል አልተነሳም የሚለውን ፍ/ቤቱ አይቶታል በዋና ጥያቄ ላይ ሲጠየቅ ተማሪዎቹ መጅሊሱ አይወክለንም እያሉ ሙባረክ ሲናገር እነሱም ተከትለው ሲናገሩ መፈክር ያሰሙ ነበር ብሎ ተናግሯል የመፈክር አይነቶች ብዙ ናቸው ከዛ ውስጥ መርቶ መጠየቅ የሚችል በመሆኑ ከዋናው ጥያቄ የወጣ አደለም ተብሏል አሁን የተነሳው ጥያቄ ለማንኛውም ጥያቄው ተመልሷል ሌላ ጥያቄ
- እሺ አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄያችን ሰላማዊ ነው ሲሉ ነበረ አደል
- ይሄ ተመልሷል
- እሺ ሙባረክን ታውቀዋለህ እዛ ውስጥ ሙባረክ ምንድን ነው ግቢ ውስጥ የተማሪዎች ተወካይ ነው አደል?
- እሱን አላውቅም
- የሙባረክ አሁን ለስድስት ጁምአዎች እምጣ ነበር ብለሃል ከወላጅ ኮሚቴ ጋር ሲሰባሰብ ነበር አደል?
- በስም ነው የማውቀው ያው ሙባረክ ሲሉ
- እሺ ቅድም ሲጮህ የአካባቢው ሰው ገባ ብለሃል የአካባቢው ሰው ብቻ ነው አደለ የገባው እዛው አካባቢው ላይ የነበሩ ሰወች ድምጽ ሰምተው ብቻ ነው አደለም የገቡት?
- አዎ ሲጮህ ተማሪዎች ሲፎክሩ ሲጮሁ ምን ተፈጠረ ተብሎ ቤተሰብ ስላለ ልጅ ተማሪ ምናምን ተገባ
- ቤተሰብ እና የአካባቢ ሰው ብቻ ነው የነበረው ማለት ነው?
- አዎ
- እሺ ቅድም ንግግር አደረጉ ያልካቸው ሰው ማይክ ተነጠቁ ካልከው ውጪ ሌላ ዝም ብለው ነው አደል በሰላም የሄዱት?
- ተጠይቋል ይሄ
- ሲጮህባቸው ተመለሱ በቃ ተቀባይነት ሲያጡ ተመለሱ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቆይ እኛን እዩ እስቲ እኛን ይዩና አትናገር ከተባለ መቆም አለብህ ስለዚህ ይሄ ተጠይቆ ተመልሷል ሌላ ጥያቄ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት 6 ጁምአዎች ነበርኩኝ ስላሉ ተማሪዎቹ መጅሊስ ሄደው ጥያቄያቸውን አቅርበዋል አደለ?
- ይሄንን አላውቅም
- እሺ የመጀመሪያው ስብሰባ አንደኛው ጁምአ ነው ብንል 2ኛ ጅምአ ላይ ተማሪዎቹ የት ሄደው ምን ጥያቄ እንዳቀረቡ የሰሙት ነገር አለ?
- አላውቅም
- 3ኛ ጅምአ ላይስ?
- አላውቅም
- ስለዚህ አልነበሩም ማለት ነው?
- /የማይሰማ/
- ሰባልደረባዎቼ እሰጣለሁ
- ምስክር በነዚህ 6 ጁምአዎች ውስጥ ከሙባረክ በስተቀር ሌላ ሰው ሲናገር አይተዋል ወይም ሰምተዋል?
- ከሱ ውጪ አልሰማሁም
- ስድስቱንም ጁምአ ተገኝተዋል እርስዎ?
- አዎ
- ያኔ ቅድም ያሏቸው ሲያረጋጉ የመጡት ሰው ተናግረው በወጡበት እለት ሌላ የተፈጠረ ነገር አለ ከእሳቸውጋር በተያያዘ ይሄን የሚያውቁት ነገር አለ?
- ይሄ ተመልሷል
- አሁን በቀረበው መልክ ተጠይቋል የተከበረው ፍ/ቤት
- ተመልሷል እሱን በተመለከተ የተፈጠረው ነገር ተጠይቆ ተመልሷል ምስክሩ በሚያውቁት ልክ
- ጠዋት ሲመጡ ወደ ግቢው ሲገቡ ጥበቃዎች በመደበኛ ቦታቸው ነበሩ አደል?
- እሱን አላስታውስም
- ጨርሰው ሲወጡ አይወጡም ያሉት ሰው አለ እንዴ እርስዎን?
- ድገምልኝ እስቲ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ መውጣት አይቻልም የሚል ሰው የለም አደለ በሩ ላይ ጥበቃዎችም ሆነ ሌላ ሰው የገባውን ሰው መውጣት አይችልም ሲል የነበረ ሰው የለም አደል?
- እሱንም አላስታውስም
- እሺ ሲወጡ እንዴት ወጡ እርስዎ?
- በበር
- በበር ነው አደል የወጡት ክፍት ነበረ አደለ በር?
- አዎ
- ተመልሷል እሱም
- ሰው ይወጣ ይገባ ነበር አደል?
- በቃ በቃ ቆዩ አትግቢ አትውጡ የሚል ሰው አለ ወይ ተባለ አላስታውስም አለ እኮ
- እኮ የተከበረው ፍ/ቤት የእንዱን ጥያቄ በአንድ መንገድ ከመለሰው ሌላ ጥያቄ እንጠይቃለን አሁን አትውጡ አትግቡ አለ የሚል ሰው ነበረ ወይ የሚለው እና በሩ ክፍት ነበረ ወይ የሚለው የተለያየ ጥያቄ ነው ብዬ ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- አንድ ነው አትውጡ አትግቡ የሚል ሰው አለ ወይ ግልጽ እኮ ነው እኔ አላስታውስም ነው ያሉት
- እሺ ልጠይቅ ከዚሁጋ የተያያዘ ተማሪዎቹ ይወጡ ነበረ ወይ ወላጆችም ተማሪዎችም ልክ እርስዎ እንደወጡት ሲወጡ ነበረ አደል?
- ግርግር ስለነበረ ብዙ አላስታውስም
- እኮ አሁን እርስዎ በር ላይ ሲወጡ
- ተማሪ ይውጣ ቤተሰብ ይውጣ
- ግን ሰው ይወጣ እና ይገባ ነበር?
- አላስታውስም ወከባ ስለነበረ
- ትክክል እሺ ወከባ ሊኖር ይችላል ሰው ግን ይገባ ይወጣ ነበረ አደል?
- በር ላይ አልነበርኩም
- አይ ኖ እርስዎ ሲወጡ ሰው ይገባ ይወጣ ነበረ አደል?
- እኔ እንጃ ብዙ አላስታውስም
- /የማይሰማ/
- እኔ ስወጣ ወጥቼ ሄድኩ ሲገባ አይግባ አላስታውስም ወጥቼ መሄዴን አስታውሳለሁ
- እ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ መሄዴን ነው የማውቀው ይውጣ ይግባ
- አታስታውስም?
- በር ላይ ብዙ የለም ውስጥነው የነበረው ግቢ ውስጥ
- ምስክር በነዚህ 6 ጁምአዎች ውስጥ ሙባረክ አሁን ቅድም አነሳሳ ካሉት ውጭ ሌላ ነገር ሲፈጽም ታዝበዋል አይተዋል ?
- ሌላ ነገር አልታዘብኩም
- እርስዎ በነበሩበት ሌላ ነገር ሲፈጽም ወይም ሲያስፈጽም አላዩም አደል?
- አዎ
- ከግቢው ሲወጡ በነዚህ 6 ጊዜ ውስጥ በሩ ላይ ወይም ወደ ውስጥ ፖሊሶች ወይም እንደዚህ ነገር አይተዋል ፖሊስ ማለት ጥበቃው ሳይሆን መደበኛ የከተማ ያለው ፖሊስ?
- አዎ ፖሊሶች ነበሩ
- የት ጋ ነበሩ?
- ከግቢ ውጪ
- ምን ያረጉ ነር ?
- ያው ሰላም ያስከብሩ ነበር ሰው በሰላም ወጥቶ ሰላም እንዲገባ
- ዝም ብለው ይታዘቡ እንጂ በዛን ወቅት ፖሊሶቹ ሰላም ለማስከበር ብለው ሰውን ሲይዙ ወይ የሆነ ነገር ሲያረጉ ያዩት ነገር አለ?
- አላየሁም
- ምስክር እርስዎ በመጡበት 6 ጁምአዎች ተጀምሮ እስኪያልቅ ይቆያሉ አደል እዛው ቆይተው አይተው ነው አደለም የሚሄዱት?
- ሰግጄ ነው የምሄደው
- እኮ ያው ተማሪዎቹ አይተዋቸው ጨርሰው ነው አደል የሚሄዱት?
- ማለት እስከመጨረሻው እዛ ቆይቼ?
- ማለት ያው እርስዎ መቆየት እችላለሁ ያሉት ድረስ ቆይተው ነው ተማሪዎቹ እስኪሄዱ የሚቆዩት አደል?
- አዎ
- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ አቃቤ ሕግ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኚህ ለማረጋጋት የመጡት ሰውዬ የት ነበረ ያነጋገሯቸው ወይም ገና ሲጀምሩ ነው ጩኸት የተጀመረው ብለሃል ቦታው የቱጋ ነው?
- ቦታው ውስጥ ካፌ አካባቢ ነው
- አራሽ ውስጥ ስለተደረገው ነገር የምታውቀው ነገር አለ በተመሳሳይ ?
- ስለተደረገው ነገር አላውቅም
- ቆይ ምስክር ተመለሰ
- ከዚህ በፊትም እንዳለው ምስክሩን ፍ/ቤቱ አቁም ሲለው እንዲያቆም ይነገርልን አሁንም እኛ ተቃውሞ ብለን
- ሰምተውኛል ከተመለሰ በቃ
- አይ እንደማሳሰቢያ ከዚህ በኋላ ላለው ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- ከዚህ በኋላ ያለውን እንከታተላለን አሁን ተመልሷል ቀጥሉ
- መውጣት መግባት ይቻል ነበረ ወይ ብለው በተደጋጋሚ ጊዜ ጠይቀዎታል ተማሪዎቹ እንዳይወጡ ያግድ የበረን ሰው አይተዋል ያስታውሳሉ?
- እሱን አላስታውስም
- እሺ ቀጥል
- ተማሪዎች በተመሳሳይ አሁን በገለፁት ጉዳይ ላይ ከመጅሊስ መጥተው ጥቃት ስለደረሰባቸው ሰው የሚያውቁት ነገር አለ?
- እሺ ተቃውሞ ምንድን ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት በዋና ጥያቄ ላይም በመስቀለኛ ላይም ጥቃት የሚል ነገር አልተነሳም የማይክ ጉዳይ ነው የተነሳው የድጋሚ ጥያቄ ባህሪ መስቀለኛ ላይ የተነሳን ለማፍረስ የሚደረግ ጥያቄ ነው እንጂ ዋና ጥያቄ ላይ አልተነሳም አዲስ ጥያቄ ማንሳት ስለማይቻል ይሄን ጥያቄ ሊጠይቁ አይገባም
- እሺ ምላሽ ስጡበት
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት በተደጋጋሚ በሰላም ነው ወይ አደለ የተመለሱት እስከ በር ሸኝታችኋል አደለ እየተባለ በተደጋጋሚ ጊዜ ተጠይቀዋል አሁን ከዚህ በፊት የመስከሩ ምስክሮችን መነሻ አድርገው ነው ፍ/ቤቱ ኦፍ ኮርስ ፈቅዶላቸው ነው ግን በተደጋጋሚ ከዚህ በፊት የተሰሙትን ምስክሮች ታሳቢ በማድረግ ነው በሰላም ነው ወይ የወጡት እናንተ በሰላም ሸኘሃቸው ወይ እስከ የት ድረስ ከበር ድረስ ሌላ የተፈፀመ ነገር አለ ወይ እየተባለ በተደጋጋሚ ጊዜ ተጠይቀዋል በመስቀለኛ ጥያቄ ማለት ነው ስለዚህ የእኛም ጥያቄ እሳቸው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

አፍ ኮርስ የተናገሩት በዋና ጥያቄ ያስመሰከርነው ይሄንን ነው ነገር ግን ከዛ ከሌሎች ምስክሮች መነሻ በማድረግ ግን የእሳቸውን መውጣት በተደጋጋሚ ጊዜ ጠይቀዋል የእኛም ጥያቄ ከዛ የተነሳ ነው

- እሺ ብይን ሰጥተናል በጥያቄው ዙሪያ ላይ በመስቀለኛ ጥያቄ ላይ ከተነሱት አንደኛው እኛ የመጡ ሰው በሰላም ነው ወይ የሄዱት ምንም ላይሆኑ አስከ የት ድረስ ተከትላችሁ ነበረ ፖሊሶች በአካባቢ ነበሩ የሰላም ጥያቄዎችን በብዛት ይጠየቁ ነበር ስለዚህ ከሰላምጋር ተያይዞ የመጣ ጥያቄ ስለሆነ ጥያቄው ከዚህ የወጣ አደለም ነገር ግን አቃቤ ሕግ ምናልባት በፊት ያሰቡትን ጥያቄ ነው እየጠየቁ ያሉት የሚለውን ነገር እሱ ትክክል አደለም ያን እያሰቡ የሚጠይቁ ከሆነ ምስክሩን ሌላ እያሰቡ የሚጠይቁት ከሆነ እናንተ ያነሳችሁትን የማይጠይቁ ከሆነ ወዲያውኑ ማስቆም ነው ተቃውሞ ብላችሁ ማስቆም ነው እንጂ አሁን ይሄ እየተሰማ ታልፎ ከሆነም ትክክል አደለም ሌላውን ጥያቄ መስቀለኛ ጥያቄ በዚህ ምስክር ላይ የሚያሳርፉ ከሆነም ተገቢ ስላልሆነ ቀድማችሁ ነው ማንሳት የነበረባችሁ አሁን አልነበረም ዞሮ ዞሮ ቅድም ባልነው አግባብ ጥያቄውን ቀጥሉ
- እሺ አቡበክር አሁን አንተ በነበርክበት ቀን ውጪ ተደረገ ከምትለው ውጪ ሌላ ሰው ከመጅሊስ መጥቶ ጥቃት ይፈፀምበት አይፈፀምበት የምታውቀው ነገር አለ?
- እሱን አላውቅም
- እሺ አቡበክር የዛን ቀን በጠዋት ሦስት ሰዓት ተኩል አካባቢ ነው የሄድኩት ብለሃል ሁለት ሰዓት ላይ ተማሪዎቹ መግባታቸውንም ያወቅኩት የተማሪ መግቢያ ሰዓት ስለነበረ ነው ብለሃል እና የዛንቀን በዛ ሰዓት የገባህበትን ሰዓት ስትጠየቅ ጨኸት ስለነበረ ነው ብለሃል እና ምን ሰምተህ ነበረ ወደዛ የሄድከው አንተ?
- ከዚህ በፊት ሰምቼ የማላውቀውንድምጽ ማለቴ ያው ጨኸት ተማሪው ጠቅላላ ማለት ነው
- ምን እያሉ ነበረ የሚጮሁት?
- መጅሊስ አይክለንም
- ማለት ከሩቅ የሰማኸው ሲጮህ የነበረው ማለት ነው?
- መጅሊስ አይወክለንም
- ምን ሰምተው ነበረ የዛን ቀን በጠዋት የሄዱት?
- ጨኸት በቃ
- እርስዎ ከመሄዶ በፊት ስለተፈጠረው ነገር የሚያውቁት ነገር ካለ?
- አላውቅም

4/12

1981

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላው መጨረሻ ላይ ስወጣ በር ላይ ስለነበሩት ሰወች አላስታውስም ምክንይቱም ወከባ ስነከረ ብለዋል የምን ወከባ ነበረ የነበረው?
- ያው ውስጥ ተማሪዎች ይጮሃሉ ቤተሰብ ይሁን መንገድ ለማየት ምን እንደተፈጠረ ይገባል ስለዚህ ወከባ ነበረ በቃ
- እሺ የዛን ቀን ለማረጋጋት አወልያ መጥተው የነበሩት ሰው እስከ በር ሲወጡ በሰላም ወጥተዋል ብለዋል ሲወጡ አይተዋቸዋል እንዴ እርስዎ በር ድረስ ሄደው አይተዋቸዋል?
- በር ድረስ ሄጄ አላየሁም
- አላዩም እሺ ከሙባረክ ውጭ ተማሪዎቹ ምን አይነት ስሜት ላይ ነበሩ የነበሩት?
- ማለቴ ያው ተመሳሳይነው ስሜታቸው እሱ በበለጠ መድረክ ላይ ሆኖ ያነሳሳቸዋል እንጂ ተመሳሳይ ነው
- ሌሎች ተማሪዎች በር ላይ ስለፈጠሩት ነገር የሚያውቁት ነገር አለ?
- እሱን አላውቅም
- እሺ ምስክር እናመሰግናለን ይመለሱ
- እሺ የዛሬውን የችሎት ውሎ በዚሁ አጠናቀናል ለሚቀጥለው ጊዜ ቀሪውን የአቃቤ ሕግ ምስክር ለመስማት ያው ቀጠሮ እንይዛለን ከዛ በፊት ግን ፍ/ቤቱ ብይን ሲሰጥ ተከሳሾቹ የምታሳዩት አክት አለ እሱ ተገቢ አደለም አርማችሁ ኑ ለሚቀጥለው ጊዜ ማለት ነው ፍ/ቤቱ ለእናንተ የሚጠቅምም ብይን ይሰጣል የሚጐዳም ብይን ይሰጣል ሕጋዊ ብይን ነው የሚሰጠው እና ቢጠቅማችሁም ቢጐዳችሁም መቀበል የግድ ነው ስለዚህ ፊሊንጋችሁ ይታወቃል ይታያል እንዴ የሚል ነገር እጅ ማንሳት አለ በዛ በኩል ሁሌ ለእናንተ የሚጠቅምም ብይን አትጠብቁ ሕጉ የሚለው ብይን ነው የሚጠበቀው ከዛም ከዚህም እና ይሄ እንዳለ አውቃችሁ ተረጋግታችሁ ሂደቱ እስከመጨረሻ መከታተል ግዴታችሁ ነው እሱን አስታውሱ የዛሬውን በዚሁ አጠናቀናል ቀሪው ያው ምስክር መሰማት መቀጠል አለበት መቀጠል እንዳለበት ይሰማናል ያም ቢሆን በዛ ሌላም መዝገብ አለ በጣም ብዙ ጊዜ የወሰደና እና ተመልሰን የምናየው አለ ወደ ልደታ ማለት ነው ስለዚህ የናንተን ለመቀጠል የያዝነው ቀጠሮ ከየካቲት 12 እስከ 15 ለአራት ቀኖች በዛ ላይ የተሰማውን ስምተን ከዛ በኋላ ምን ይሆናል የሚለው ያኔ ነው የምንወስነው ስለዚህ በተለመደው ሰዓት እዚህ የምንገናኘው የካቲት 12 ነው ማለት ነው ከየካቲት 12 እስከ 15

ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/

4ኛ ወ.ችሎት

የመ.ቁ 124754

12/6/05 ዓ.ም

ዳኞች:- ብስራት ተልዕቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

አሣሽ:- ዐቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድማገኝ ቀርበዋል 1 ዐቃቤ ሕግ ቀርበዋል

ተከሣሾች:- እነ አቡበከር አህመድ ያልቀረበ ተከሣሽ አለ ተከሣሾች እነ አቡበከር አህመድ ሁሉም ቀርበዋል ከማረሚያ ቤት

የተከሣሽ ጠበቆች ተካ ዳባ፣ ሀሰን ሁሴን፣ መሐመድ አብደላ ፣ ሞላልኝ መለሰ እና ባህሩ መካንጋ ቀርበናል የ 28ኛ ተከሣሽ ጠበቃ አህመድ ጀማል ቀርቤአለሁ

የ 28ኛ ተከሣሽ ጠበቃ እና የሌሎች ተከሣሾች 5 ጠበቆች በመቅረፀ ድምፅ ሰማቸውን ገልፀዋል

- ምናልባት ችሎቱን ከመጀመራችን በፊት ግን አንዳንድ ወደ ፊትም ወደ ኋላም አንዳንድ ነገሮች አሉ እነሱ መስተካከል ያለባቸው ስለሆነ እነሱን እንነግራችዋለን አሁን ይሄ ችሎት ከመጀመሪያ ጀምሮ ማለት እዚህ ቃሊቲ ከመጣን በኋላ ዝግ ይሁን ተብሎ በዝግ እየታየ ነው ያለው ነገር ግን ይሄ የችሎት ውሎ በሚዲያ ላይ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያም ይሁን በጋዜጦች ላይ በብዛት ሲዘገብ ነው የሚውለው ብዙ ነገር ነው የሚዘገበው ይሄ ደግሞ መጀመሪያም ጠበቆችም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሲያመለክቱ የነበሩ ተከሣሾችም ሲያመለክቱ የነበሩት ይሄ ችሎት ኤቭን ተከሣሽ አንድ የማይታወቅ ተከሣሽ እንኳን ሲገባ እየታየ መታወቂያው እየታየ ነው የሚገባው ይሄንን ነው የምናስተናግደው ነገር ግን እነዚህ በጣም በስፋት በጋዜጣ ላይ እየወጡ የችሎት ውሎ እያንዳንዱ ምንም ሳይቀር እየወጣ ያለ ነው ያለው በእርግጥ እዚህ አሁን ከቀረቡት ጠበቆች ላይ ያየነው ነገር የለም በነኛ ጠበቃ የሆኑት አቶ ተማም በሁሉም ሚዲያዎች የችሎቱን ውሎ ይዘግባሉ ይሄ ደግሞ መስተካከል ያለበት ነው በፊት ይሄ ነገር ቅድም እንደተባለው ችሎቱ የተከሣሾችን ጉዳይ የሁሉንም ጉዳይ መርምሮ መጨረሻ እስኪሰጥ ድረስ እዚህ ችሎት ያለውን በሙሉ ማውጣት በኋላ በፍትህ አሰጣጡ ላይ ችግር ያመጣል ይሄ ለማንም ግልፅ ይመስለኛል ስለዚህ ይሄንን ነኛ ጠበቃው ካቋረጡ ቆይተዋል ስለዚህ ለምን እንደዚያ እንደፈለጉ ቀርበው ቢያስረዱን ጥሩ ይሆናል ብለናል ስለዚህ ያው ጠበቆቹ እኚህን ጠበቃ ያው ነግረን እናቀርባለን የሚል ቃል ስለገቡ በእዚያ መሠረት እንዲቀርቡ ብለናል ሌላው ምናልባት በውጪም የሚነገረው ነገር ማለት በእዚህ አሁን በተባለው ሚዲያ የሚባለው ነገር ጠበቆች የተለያየ ተከሣሽ እንደሆኑ አንዱ ለአንዱ ብቻ እንደሆነ እኛ እስካሁን የጋራ እንደሆኑ ነው የምናውቀው ግን የተለያየ በመሆኑ አሁን ፍ/ቤቱ የሁላችሁንም ውክልና ማየት ፈልጓል እሱን ታቀርባላችሁ እናያለን እከሌ የነኛ ጠበቃ ነው እከሌ እንዲህ ነው ምናምን የሚል ነገሮች አሉ እነሱን እናያለን ያው እናንተም ታቀርባላችሁ እሳቸውም ይዘው ይቀርባሉ የውክልና ውላችሁን ለተከሣሾቹ ያደረጋችሁት የውክልና ውል

- ዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ቀርበዋል ስለዚህ ምስክሩን እንቀጥላለን ማለት ነው
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ
- ምስክሩ ቀርበው ቃለ መህላ ፈፅመዋል በፍ/ቤቱ 34ኛ ተራ ቁጥር ላይ ናቸው በዐቃቤ ሕግ 74ኛ ተራ ቁጥር ላይ ነው ስማቸው
- ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሱት ምስክር እንኳን ደህና መጡ አሁን ለምስክሮች ደህንነት ሲባል የመጀመሪያ ስምዎን ብቻ ማን ነው ስምዎት ?
- መሐመድ
- እዚህ የመጡት ለምንድን ነው የመጡት ?
- የምስክርነት ቃል ለመስጠት
- በእነ ማን በእነ ማ ን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- መሐመድ አባተ የተባለ ግለሰብ
- መሐመድ ?
- አባተ
- ሌላ ?
- በእዚህ ግለሰብ ብቻ ነው የምሰጠው
- በአንድ ሰው ብቻ ነው ?
- አዎ
- መሐመድን አባተን ታውቃቸዋለህ ?
- በመልክ አላውቃቸውም
- በመልክ አታውቃቸውም ?
- አዎ
- ካሉ በኋላ በዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ መሐመድ ያው ዛሬ የመጣሁት ለምስክርነት ነው ብለሀል እና መቼ ቀን ስለተፈፀመው ድርጊት አሁን በጠቀስከው ሰው ላይ ምን እንዳየህ እና ምን እንደሰማህ አጠቃላይ የምታውቀውን እውቀት ቀን ሰዓት ቦታው በማስታወስ በዝርዝር መግለፅ እንድትችል ነው እና አሁን መቀጠል ትችላለህ ? መቼ ነበር ጊዜው ?
- ጊዜው ያው በ 7 ነው ዘኛ ወር 2004 አንዋር መስኪድ ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው
- ሰንት ሰዓት ይሆናል
- ሰዓቱ በግምት 4 ሰዓት ገደማ ነው
- ጠዋት ነው ምሽት ነው ?
- ጠዋት
- ምን አየህ የእዚያን ዕለት ?
- በወቅቱ መሐመድ አባተ የተባለ ግለሰብ በ 6/11/2004 አወሊያ ት/ቤት አካባቢ ለሊት ላይ የተፈፀመውን ነገር አንዋር መስኪድ ውስጥ ቅጥር ግቢ ውስጥ በነበሩት የእስልምና እምነት ተከታዮች መንግስት ማን ነው ፖሊስ /ግልፅ ያልሆነ/ ሰዎችን ይዞ በ 200 ብር ለቋቸዋል እንዲሁም ፖሊስ በወቅቱ የነበሩትን የእስልምና እምነት ተከታዮችን ገድሎ ስለነበር አሁን

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ለእነዚያ ለሞቱት ሙስሊም ወንድሞቻችን የሰላት ጀናዛ ወይም ደግሞ የፀሎት ፕሮግራም እናደርጋለን ይሄንንም ተግባር በአሁኑ ሰዓት ላሉት የአፍሪካ ሕብረት አመራሮች መንግስት በደል እየፈፀመብን እንደሆነ በትክክል እናስረዳለን በሚል አገላለፅ በወቅቱ ሲናገር ሰምቼአለሁ

- እስቲ እንዴት በምንድን ነው የሚገልፀው ማለት ቦታው አገላለፁ ሁኔታ ለማን እንደሚገልፅ የሚናገረውስ በምን ነበር ?
- የሚናገረው በማይክ ነበር ሲናገር የነበረው በወቅቱ አንዋር መስኪድ ቅጥር ግቢ ውስጥ ብዙ የእስልምና እምነት ተከታዮች ነበሩ በወቅቱ በአጋጣሚ እዚያ አካባቢ ስለነበርኩኝ እኔም የእምነቱ ተከታይ ስለነበርኩኝ የሚደረገውን ነገር ለማየት ብዬ ገብቼ ስለነበር በእዚህ አጋጣሚ ይሄንን የተደረገውን ንግግር ለመስማት ችዬአለሁ
- ቅድም ይሄ ፖሊሶች እንዲህ ገድለው ገንዘብ 200 ብር እንዲህ እየሰጡ ነው የሚለው የት ስለ ምን ማለቱ ነው የት ስለተፈፀመው ሁኔታ ያንን የሚገልፀው ወይም በእሱ ቋንቋ ማለት ነው እሱ እያለ ያለው ?
- ይህ ነገር አርብ ምሽት ለሊት ላይ በአወሊያ ት/ቤት የእስልምና እምነት ተከታዮች ተቃውሞ እያደረጉ ስለነበረ በእዚያ ተቃውሞ ላይ ፖሊስ ይሄንን ተግባር እንዳደረገ የተገደሉ ሰዎች እንዳሉ በወቅቱ ለነበሩት አንዋር መስኪድ ውስጥ ለነበሩት የእስልምና እምነት ተከታዮች ሲናገር እንደነበረ ነው የማስታውሰው ፣
- ለምን ያህል ጊዜ ቆየ ይሄ የእሱ ገለፃ እና ንግግሩ እንዴት ነው በመጮህ ነው ሕዝቡ ምን ያህል ይሆናል ከእዚያ የሚሰጠው ነገር ምን ያህል ጊዜ ቆይቷል ሰዓት ለምሳሌ ግምት ?
- ያው እኔ ይቺን ነገር የተወሰነች ሰዓት ነው የሰማዋት አጭር ጊዜ ስለቆየሁ ይሄንን ነገር እንደሰማሁ የራሴ የግል ስራዬ ስለነበረ ወደ ስራዬ ሄጃለሁ
- ይሄንን አሁን አንተ እዚያ እያለህ አንዋር መስኪድ የተፈፀመውን ድርጊት ስትሰማ ወይም እሱ ሲናገር ስትሰማ ማለት ነው መሐመድን አባተን ታውቀው ነበር ወይስ እንዴት አረጋገጥክ እሱ መሆኑን ?
- የእኔ ጓደኛ ነበር በወቅቱ በአጋጣሚ የሄድነው ይሄ ጓደኛዬ መሐመድ የተባለውን ግለሰብ እንደሚያውቀው በአካልም በድምፅም ሊያውቀው እንደሚችል ነው የነገረኝ መሐመድ አባተ እንደሆነ በወቅቱም እኔ ያወኩት ይሄ ጓደኛዬ ስለነገረኝ ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አንተ ማን ነው የሚናገረው ብለህ ስትጠይቀው ነው ጓደኛህ የነገረህ መሐመድ መሆኑን መሐመድ አባተ መሆኑን ?
- ግለሰቡ ማን እንደሆነ ለማወቅ ስለፈለኩኝ በወቅቱ መሐመድ አባተ የተባለ ግለሰብ እንደሆነ ነገረኝ
- ብሎ አረጋገጠልህ ሌላ የምታስታውሰው አለህ ?
- ሌላ የማስታውሰው የለም
- ጨርሰናል
- የተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ
- አቶ አህመድ አቶ መሐመድ አባተን እንደማታውቃቸው ገልፀህል ተከሣሽ አውቃቸዋለሁ ያልከው ወይም ስማቸውን የጠራኸው ጓደኛህ ስለነገረህ ብቻ መሆኑን አውቀህል ጓደኛህ የነገረህ ነገር ትክክለኛ እና እውነተኛ ስለመሆኑ የምታውቅበት መንገድ አለ ?
- አይ ጓደኛዬ መሐመድ አባተ የተባሉትን ግለሰብ እንደሚያውቃቸው በአካልም በድምፅም ጭምር ከእዚህ በፊት እንደሚያውቃቸው ስለነገረኝ ነው ግለሰቡ እሳቸው መሆኑን ያወኩት
- ጓደኛህ የነገረህ እውነት መሆኑ ወይም ትክክል መሆኑን የምታውቅበት መንገድ አለ ወይ ነው ?
- ሌላ መንገድ የለም
- ሲናገሩም የሰማኸው ነገር ለሞቱት ሰዎች ፀሎት እናድርግ ነው ያሉት አይደል ?
- አዎ
- በአወሊያ መስኪድ ሐምሌ 6 ቀን 2004 ዓ.ም በፖሊስ እና በመስኪድ ውስጥ በነበሩት ሰዎች መካከል ግጭት የነበረ ስለመኖሩ ታውቃለህ አይደል ?
- ያው በመረጃ ደረጃ ሰምቼአለሁ
- እዚያ ስለነበረው ግጭት የሰማኸው መረጃ ምንድን ነው ?
- ለሊት ላይ የአዛን ድምፅ ሰምቼ ስለነበር
- እኮ አይ የሰማኸው እዚያ የነበረው ግጭት ስለነበረው ነገር በመረጃ ሰምቼአለሁ ስላልክ የሰማኸው መረጃ ምንድን ነበር ዝርዝሩን ንገረን እስቲ የሰማኸውን መረጃ ?

1987

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የሰማሁት መረጃ ጥቂት የእስልምና እምነት ተከታዮች በእነዚህ መሐመድ አባተ በተባለ ግለሰብ እየተመሩ እየተቃወሙ ስለነበር
- መሐመድ እዚያም ያስተባብር ነበር በሚል ነው የሰማኸው ?
- በሚል ደረጃ ሰምቼአለሁ
- ስለደረሰ ጉዳት ወይም ስለተፈጠረ ግጭትስ የሰማኸው ነገር አለ ?
- የሰማሁት ነገር የለም
- ምስክር አንዋር መስኪድ ምን ያህል ቆየህ ?
- አንዋር መስኪድ የቆየሁት ለተወሰነ ደቂቃ ነው የቆየሁት
- ለተወሰነ ደቂቃ ማለት ምን ያህል እስቲ በግምት ምን ያህል ደቂቃ ይሆናል ፍ/ቤቱ እንዲረዳ?
- በግምት ከ 10 እስከ 15 ደቂቃ የሚሆን ቆይቼአለሁ
- ከ 10 እስከ 15 ደቂቃ በቆየህበት ጊዜ ውስጥ መሐመድ አባተ ብቻ ነው ሲናገር የነበረው ?
- አዎ መሐመድ አባተ ብቻ ነበር
- መሐመድ አባተ ቅድም የተናገርኩት ነገር መረጃ ያልደረሰበት ስለሆነ ወይም መረጃ የሌለን ስለሆነ እርግጠኛ አይደለንም ወይም ስህተት ነው ሲል ነበርክ ?
- ይቅርታ ይደገምልኝ
- እሺ አወሊያ በተደረገው ነገር ሰው ሞቷል ብዬ የተናገርኩት ነገር መረጃ ላይ የተመሰረተ ስላልሆነ ወይም ግምት ስለሆነ ይሄ ነገር እርግጠኛ አይደለንም ስህተት ነው ሲል ነበርክ ?
- መጀመሪያ ቅድሚያ እንደተናገርኩት የተናገረውን ነገር ነው የገለፅኩት አወሊያ ላይ
- እስቲ ምስክር ይሄንን ሲል ሰምተዋል አልሰሙም አሁን የተባለውን ጥያቄ ተከሣሹ ይሄንን ሲል ሰምተዋል አልሰሙም ?
- ይሄንን አልሰማሁም
- ሌላ ጥያቄ
- በየትኛው በር ነው የገባው ?
- በሴቶች መስኪድ በኩል ባለው በር ነው የገባሁት
- በሴቶች መስኪድ ባለው በር ሴቶች ነበሩ ስትገባ ?

2/9 1988

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በወቅቱ በሴቶች መስኪድ ሴቶችን አይቼአለሁ
- እኮ እንዴት ማለፍ ቻልክ ሴቶች መስኪድ በኩል ወደ ወንዶች እንዴት ማለፍ ቻልክ ?
- ሁሉ ጊዜ በእዚያ በኩል ስለሚታለፍ በወቅቱ እኔም አለፍኩኝ
- ውጪ ሆነህ ነው ይሄንን ነገር የሰማኸው ?
- ቅርጥ ግቢ ውስጥ ነው ግን ብዙ ሰዎች ነበሩ
- ስትገባ አትገባም ያለህ ሰው የለም ማንም ሰው ይገባ ይወጣ ነበር ?
- ስገባ ተፈትሼ ነው የገባሁት
- ቅድም ግጭት አወሊያ ውስጥ ወይም አወሊያ በ 6 ግጭት የነበረ መሆኑን አውቃለሁ ብለሀል እስቲ ስለግጭቱ ማለት በግጭቱ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሰው ነበር የሙስሊሙ ሕብረተብ ተቃውሞ እያሰማ ነበር ስላልክ በተቃውሞ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው ነበር?
- እሱን አላውቅም
- እስቲ ቆይ ማለት ቅድም ያለው የሆነ ግጭት ነበር ያልከው ከፖሊሶች ጋር ነው ?
- አዎ ከፖሊሶች ጋር
- እንደዚያ ነው የተነሳው የተነሳው ከፖሊሶች እና የሆነ ግጭት አለ ተብሎ ከእሱ ሲነሳ ነው ሌላ ግጭት አለ ብሎ አላነሳም
- ወደ ሌላ ጥያቄ ልሂድ
- የመጀመሪያው እራሱ መታረም ስላለበት መልሷል ነገር ግን የሙስሊሙ ሕብረተሰብ እና ፖሊስ ግጭት ነበር አላለም እሱ
- አይ የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ተቃውሞ ከእዚያ በፊት ከጥያቄው በፊት የተናገረው
- ገባኝ ጥቂት በመሐመድ አባተ የሚመሩ ሰዎች ከፖሊስ ጋር መጋጨታቸውን ሰምቼአለሁ ነው ያለው በእዚያ መሠረት ነው
- እሱ በደንበኛዬ ሲጠየቅ ነው ከእዚያ በፊት ግን የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ጥያቄ ከመጀመራች በፊት ተቃውሞ አወሊያ ሲያሰማ ነበር የሚል ነገር ተናግሯል ያንን መሠረት አድርጌ ነው የጠየኩት አሁን ወደ ሌላ ጥያቄ ልሂድ እና ለ 10 ደቂቃ ለመስማት ነው ወደ አንዋር መስኪድ ሄደው የነበረው ማለት ነው ?
- የራሴ የግል ጉዳይ ስለነበረኝ በወቅቱ የእስልምና እምነት ተከታይ እንደመሆኔ መጠን

420 1989

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የመሐመድ አባተን ብቻ መርጠህ ሰምተህ ሄድክ ?
- አጋጣሚ የደረስኩበት ሰዓት ስለነበር ነው
- መሐመድ አባተን ያስተዋወቀው ሰው የለም አይደል ጓደኛህ ብቻ ነግሮህ ነው ይሄንን ያወከው መሐመድ አባተ መሆኑን ?
- አዎ
- ከእዚያ ውጪ መሐመድ አባተን አንተ አታውቀውም ?
- ተጠይቋል
- ምስክር ቅድም ለፍ/ቤቱ ስትገልፅ /ግልፅ ያልሆነ/ ለሞተ ሰው ሰላት ይሰገዳል ብለህ ነበረ ልክ ነኝ ?
- ልክ ነው
- ሰው ካልሞተ ይሄ ሰላት አይሰገድም አይደል ?
- በእምነቱ አይሰገድም
- የእዚያን ቀን ተሰገደ ?
- የእዚያን ቀን አልተሰገደም ነገር ግን ይሄንን
- በቃ ይበቃኛል ቅድም አወሊያ ስለተነሳው ነገር በእነ መሐመድ መሪነት ለሊት ላይ ግጭት ነበረ ብለዋል መሐመድ ምን አደረገ ተባሉ የእዚያን ቀን ?
- የእሱን ሂደት የሚከተሉ ሰዎች ይሄንን ድርጊት አደረጉ የሰማሁት ይሄንን ነው
- እኮ ምን አደረገ መሐመድ ምን አደረገ ተባሉ በአወሊያው ግጭት ለሊት እዚያ ነበር ብለዋል ምን አደረገ መሐመድ ?
- እሱን አላውቅም
- አወሊያ ሲናገር አይቼዋለሁ ብለዋል አወሊያ የት ጋር ሆኖ ተናገረ ?
- አወሊያ ሲናገር /ግልፅ ያልሆነ/
- አንዋር ይቅርታ የተከበረው ፍ/ቤት አንዋር ንግግር ሲያደርግ እንዳዩት ተናግረዋል እና አንዋር የቱ ጋር ሆኖ ተናገረ ?
- ብዙ ሰዎች ስለነበሩ በወቅቱ ግለሰቡን ለማየት አልቻልኩም

4/24 1990

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቦታውንም አያውቁትም የተናገረበትን መስኪድ ውስጥ ነው ከመስኪድ ውጪ መገመት ይችላሉ ?
- አላውቅም
- የት እንደተናገረም አያውቁም ?
- አላውቅም
- ምስክር ቅድም መጀመጀመሪያ ላይ ሲመሰክሩ የሆነ ስራ ሄጄ ንግግር ያደርጉ ነበር ብለዋል ስለዚህ ንግግር ያደርጉበት የነበረው ቦታ በቀጥታ ያቺን የቆሙበትን ቦታ ሳይሆን መስኪዱ አለ መስኪዱ አጥር አለው ሲናገሩ የነበሩት ከአጥሩ ውጪ መስኪድ ውስጥ ነው ወይስ ከመስኪዱ ውስጥ ነው ወይስ ከመስኪዱ ውጪ ይሄ ነው ጥያቄው ሰምቼአለሁ ብለዋል አይደል እኮ እሱን ነው የሚመልሱ ?
- እንዋር መስኪድ ውስጥ 2 መስኪድ ነው ያለው እና የትኛው መስኪድ መሀል ላይ ትልቅ ቦታ አለ ከእዚያ ጋር በተያያዘ እንዲመልስልኝ ነው 2 መስኪድ ነው አንድ መስኪድ ብቻ
- መጀመሪያ ይሄንን ይመልሱ እና ከእዚያ በኋላ የትኛው ነው
- የትኛው ቦታ ሆኖ ተናገረ ?
- የት ላይ ነው ይሄንን ሰምቼአለሁ ስላሉ ነው ነበርኩ ቶሎ ሄድኩ እንጂ ነበርኩ ስላሉ ነው
- በወቅቱ ሲናገሩ የነበረው ያው በማይክ ነው ማይኩ ደግሞ ያለው ዋናው መስኪድ ላይ ነው የእኔም ግምት ደግሞ ይሄ ነው
- ስለዚህ መስኪድ ውስጥ ናቸው እሳቸው ?
- አዎ መስኪድ ውስጥ
- አቶ መሐመድ በዕለቱ ሐምሌ 7 4 ሰዓት እዚያ ነበሩ አየሩ ምን ይመስል ነበር ፀሀያማ ደመናማ ነፋሻማ እንዴት ነበር ?
- አየሩ በወቅቱ ፀሀያማ ነበር
- ፀሀይ ነበር እርሶ ሲገቡ ቅድም ቲፈትሼአለሁ አሉ ለምንድን ነው የተፈተሹት ?
- እሱን አላውቅም ለምን እንደፈተሹኝ ግለሰቦች በር ላይ ስለነበሩ ሌላው ሙስሊም ሕብረተሰብ ስለሚፈተሽ እኔም ተፈትሼ ገብቼአለሁ
- ማለት አልጠየክም አሁን መስኪድ ስትገባ ተፈትሸህል የተለመደ ነው እንዴ ይሄ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላ ጊዜ አልነበረም
- እኮ ፍተሻ ሲኖር ለምንድን ነው ብለህ ገመትክ አዲስ ነገር ከሆነ ለምን ተፈተሸክ መሣሪያ ወይም ሌላ ነገር መያዝ አለመያዝህን እንትን ለማለት ነው ?
- ሁሉም ሰው ሲፈተሽ ስለነበር እኔም ተፈትሼ ገባሁኝ ይሄንን ነገር አልጠየኩም
- ማን እንደፈተሸስ ታውቃለህ ?
- አላውቅም
- ሰዎቹ እንዴት ዓይነት ነበሩ የሚፈትሹት ?
- አልገባኝም
- ማለት ወጣቶች ናቸው ሽማግሌዎች ናቸው ወንዶች ናቸው ሴቶች ናቸው ?
- ወጣቶች ናቸው ወጣት ወንዶች ነበር ሲፈትሹ የነበሩት
- በምን አወክ ወንዶች መሆናቸውን ?
- ገብቼ ስለነበር
- አይደለም የሚፈትሹ ሰዎች ምን ፊታቸውን እያየህ ነው ወንዶች መሆናቸውን ያረጋገጥክ ?
- ፊት ለፊት እያየዋቸው ስለነበር ወንዶች መሆናቸውን አረጋገጥኩኝ
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ
- ድጋሚ የለንም የተከበረው ፍ/ቤት
- በፍ/ቤቱ ጥያቄ
- መሐመድ ነው አይደል ስምህ መሐመድ አባተ ነው ያልከው ተከሣሹ ?
- አዎ መሐመድ አባተ
- እሱ መሐመድ አባተ መሆኑን ሰው ነግሮኛል ነው ያልከው ?
- አዎ ጓደኛዬ ነግሮኛል
- መቼ ነው የጠየከው ይሄንን ?
- የእዚያኑ የስብሰባው ቀን እዚያው አንዋር መስኪድ ውስጥ
- ማለት እዚያ ሆነህ ሲናገር ነው የጠየከው ከወጣ በኋላ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ እዚያ ሆኜ ነው ግለሰቡ እየታየኝ ስላልነበረ ጓደኛዬ ማን እንደሆነ ስጠይቀው ጓደኛዬ ከእዚህ በፊትም እንደሚያውቀው መሐመድ አባተ የሚባል ግለሰብ እንደሆነ ነገረኝ
- ማለት ንግግር እያደረገ እያለ ነው የጠየከው ?
- አዎ በመሀል ንግግር እያደረገ
- በመሀል ነው የጠየከው እሺ ማን ነበረ ጓደኛህ ?
- ጓደኛዬ ተማም ይባላል
- የነገረህ ?
- ተማም
- ለምስክር ተጠርቷል ሰውዬው ?
- አላውቅም እስካሁን ያለውን ነገር አላውቅም
- ሌላው ቅድም ሰው ካልሞተ ስላተ ጀናጃ አይሰገድም ብለህ ነበር ?
- አዎ
- ነገር ግን ብለህ ነው ጠበቃው ያቋረጡህ አስታወስክ ?
- አላስታወስኩም
- በወቅቱ ስላተ ጀናዛ ይሰገዳል ተብሎ ተገልፆ ነበር ግን አልተሰገደም ብለሀል ?
- አዎ ይቺ ንግግር ላይ ነው እኔ የወጣሁት ይሄ ንግግር ከተጨረሰ በኋላ
- ነገር ግን ብለህ የቆምከው ምንድን ነው ነው ግን አልተሰገደም ነው ያልከው እና ስለመሰገድ አለመሰገዱ እንዴት አወክ ?
- እኔ በነበርኩበት ሰዓት ሰላሰ ጀናዛ አልተሰገደም ከእዚያ በኋላ ግን የነበረው ነገር እንደቀጠለ እና እኔ እንወጣሁ ነው ያለው ከእዚያ በኋላ ምንም ዓይነት መረጃ የለኝም
- ከእዚያ በኋላ ስለሆነው ነገር አታውቅም ?
- አላውቅም
- እኔ እስክወጣ ድረስ አልተሰገደም ማለትህ ነው ?
- አዎ
- እናመሰግናለን ጨርሰሀል
- ሌላ ምስክር ጥሩ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- በተራ ቁጥር 35 በዐቃቤ ሕግ ክስ ላይ
- 108ኛ
- 108 ላይ የተጠቀሱ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ቀርበው ቃለ መሀላ ፈፅመዋል ለምስክሮች ደህንነት ሲባል አድራሻ እና ሙሉ ስም ሳይገልፁ የመጀመሪያ ስምዎን ብቻ ይነግሩናል ማን ነው ስምዎ የመጀመሪያው ?
- ረዳት ሣጅን ካሳሁን እባላለሁ
- ለምንድን ነው እዚህ የመጡት ?
- በ 06/11ኛ ወር በነበረው አመፅ ላይ ያው ቃሌን ለመስጠት ነው የመጣሁት
- /ግልፅ ያልሆነ/
- 2004
- በማን ላይ ነው የሚያስረዱት ?
- በነበረው አመፅ ላይ ነው ላስረዳ የመጣሁት ማለት ነው
- እኮ በማንም ላይ በእከሌ ላይ ብለው የሚያስረዱት የለም ?
- አይ በእዚያ ላይ የማውቀው የለኝም
- እሺ ካሉ በኋላ በዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ
- የተከበረው ፍ/ቤት ረዳት ሣጅን ካሳሁን አሁን ቅድም የገለፁትን ማለት ነው በ 6/11/04 ዓ.ም ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ የሚያውቁትን በዝርዝር ለተከበረው ፍ/ቤት እንዲገልፁ ነው የምጠይቀው እና እስቲ ጊዜው የት ነው ቦታው ሰዓቱ የት አካባቢ እንደነበር እና ምን ነበር የገጠማችሁሰ ?
- እሺ ያው ቀኑ ቅድም እንደገለፅኩት በ 06/11ኛወር 2004 ዓ.ም ላይ ነው ሰዓቱ ከምሽቱ 5 ሰዓት ላይ ነው
- የት ነበር ቦታው ?
- ቦታው ባውሻ መስኪድ ነው የሚባለው ባውሻ መርካቶ ማለት ነው ስለዚህ ያው በመጀመሪያ 5 ሰዓት አካባቢ ላይ እኛ የሰማነው ያው አላህ ክበር የሚል ድምፅ ነው 5 ሰዓት ላይ የሰማነው ከእዚያ በኋላ በቦታው በአለቆቻችን አማካይነት አመራን ስናመራ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ምዕራብ ጀርባ 18 ፖሊስ ጣቢያ አለ እሱ ፖሊስ ጣቢያ አሁን ያው በድንጋይ ፖሊሶች አሉ እነሱን በድንጋይ ጠርሙስም ይወረወራል ድንጋይም ይወረወራል እነሱን ያው እየመቷቸው

- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለ
- እስቲ ምንድን ነው ተቃውሞ ?
- እንግዲህ ለክርክራችን ጭብጣችን የሚሆነው ክሱ ነው በክሱ ላይ አንድም ቦታ ላይ ባዩሻ መስኪድ ስለሚል በመስኪድ እና እዚያ ስለተፈጠረ ነገር የቀረበ ክስም የቀረበ የክስ ምክንያት ምንም የለም ባዩሻ መስኪድ የሚል ነገር የለም ክሱ ዉሰጥ ስለዚህ በክሱ ስላልተገለፀ ነገር ነው እሳቸው እያስረዱ ያሉት እና ከጭብጡ ውጪ ነው ምስክሩ ምስክርነት ቃል እንዳይሰጡ ነው
- መልስ አለን
- አስተያየት /ግልፅ ያልሆነ/ ከሌሎቹ ጋር
- ብይን ተሰጥቷል
- የተከበረው ፍ/ቤት ተጨማሪ ነው ምናልባት ብይን የተሰጠው የእዚያን ቀን ፖሊስ ያስረዳው የሰደቃው ፕሮግራም አዲስ አበባ ውስጥ በሙሉ የሚል ነው የእዚያን ቀን ለፍ/ቤቱም አስታውሼ ነበር መጨረሻ ላይ አዲስ አበባ ውስጥ በሙሉ የሚለው ለሰደቃው ፕሮግራም ብቻ ነው እዚህ ላይ የተጠቀሰው ክሱ ላይ እንጂ አሁን እሳቸው ለሚሉት ጉዳይ አይደለም ባለፈውም ያ ምስክር የመስከሩት ከሰደቃ ውጪ የወጣ ነገር ነው ክሱ ላይ ግን በትክክል የሚለው አዲስ አበባ ውስጥ እና ሌሎች ክልሎች ይላል ምኑን ሰደቃውን አስመልክቶ እንጂ አሁን ሌላውን ነገር አይደለም ዐቃቤ ሕግ የጠቀሰው ባለፈው ምናልባት እሳቸው ያስታውሳሉ መጨረሻ ላይ ነው የታየው አሁን ክሱ ቢታይ አዲስ አበባ ውስጥ የሚለው ክልሎች ውስጥ የሚለው የሰደቃ ፕሮግራምን በተመለከተ ብቻ ነው ምናልባት ፍ/ቤቱ ይሄንን ይይልን እና ብይኑን ያስተላልፍልን
- መልስ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- እዚህ ላይ ዐቃቤ ሕግ አስተያየት ማሰጠት አያስፈልግም ስለ ባዩሼ መስኪድ የሚባለው ያው ባለፈው በብይን ታልፏል ስለዚህ ድጋሚ የሚታይበት ስርዓት የለም ተቃውሞውን በእዚህ መሠረት አልተቀበልንም ኦረዲ የተበየነ ስለሆነ

1998

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ረዳት ሣጅን አሁን በጠቀሱት ቦታው የት ነው ይሄ ባዩሽ መስኪድ ?የት ክፍለ ከተማ ነው ?
- ክፍለ ከተማ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ነው
- ይሄ አሁን ሰዓቱን ቦታውን እንደገና ደግሞ ከየት ወዴት ሲወረወር እንደነበረ በወቅቱ ምን እንደደረሰ እናንተ እንዴት እንደመጣችሁ ምን ሲፈፀም እንደነበረ እስቲ ዘርዘር አድርጉት እና ይግለፁ ?
- ያው ሰዓቱ 5 ሰዓት ላይ ነው ብዬአለሁ
- ቀን ነው ወይስ ምሽት ?
- ሰዓቱ 5 ሰዓት ላይ ነው
- ጠዋት ነው ምሽት ?
- ላይ ከምሽቱ 5 ሰዓት
- ከምሽቱ 5 ሰዓት ?
- አዎ ከምሽቱ 5 ሰዓት ላይ ነው ጣቢያ ደረስን ጣቢያ ስንደርስ ፖሊሶቹ በድንጋይ እየተመቱ ነው የደረስነው እኛ ከደረስን በኋላ ያው ወደ እኛ ዞሩ እኛን ዞረው ወደ እኛ ዞሩ እኛንም በድንጋይ በጠርሙስ ይወረውሩብናል እኛም ያው ባለን ማቴሪያል እየተከላከልን አድማውን ተቆጣጥረነዋል ከእዚያ ላይ ስንቆጣጠረው ግን የነበረው ምንድን ነው አሁን ለምሳሌ በእኔ ላይም ጉዳት ደርሶብኛል
- ምንድን ነው የደረሰቦት ጉዳት ?
- እግሬ ላይ ነው ጉዳት የደረሰው
- ምን ሆኑ እግሮት ምን ?
- በድንጋይ ነው የተመታሁት
- በድንጋይ ተመቱ ?
- አዎ በድንጋይ ተመታሁኝ ጉዳት ደረሰብኝ ሌሎችም አሉ
- ሌሎችስ እነ ማን ለምሳሌ እነ ማን ጉዳት ደረሰባቸው ?
- ለምሳሌ እነ ሚፍታህ የሚባል አለ ሚፍታህ
- ምንድን ነው አሱ አባል ነው የፖሊስ ሕግ አስከባሪ ?

1996

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አባል ነው የፖሊስ አባል ነው እንደገና መሀሪ የሚባል ልጅ አለ እሱም የፖሊስ አባል ነው 3ታችን ላይ ወዲያው ነው ጉዳት ደረሰብን
- ምን ምን ጉዳት ደረሰባቸው እነሱ እነኚህ አባላት ?
- ሚፍታህ ያው ቀኝ እግሩን ነው የተመታው እዚህ ጉልበቱ ላይ ነው ጉዳት የደረሰበት መሀሪ እጁን ነው ግራ እጁን የተመታው ማለት ነው ከእዚያ በኋላ ያው በነበረው ላይ የእኛ አምቡላስ ነበረ ወደ ሆስፒታል ገብተናል ማለት ነው
- እናንተ ከመድረሳችሁ በፊት ቅድም /ግልፅ ያልሆነ/ እናንተ ከመድረሳችሁ በፊት ማለት ነው እናንተ ማለት ቀደም ሲል ከእኛ ፊት የፖሊስ አባላት ነበሩ ድንጋይ ይወረወርባቸው ነበር የጠርሙስ ስባሪ ይወረወርባቸው ነበር ብለዋል እና እነኚያ የት አካባቢ ፖሊሶች ናቸው የት አካባቢ ፖሊሶች ናቸው ?
- የ 18 ፖሊስ ጣቢያ የሚባል አለ ምዕራብ ጀርባ ላይ እነሱ ነው ጣቢያቸው ላይ ነው ድንጋይ ሲወረወርባቸው የነበረው ጣቢያቸው 18 ፖሊስ ጣቢያ
- ፖሊስ ጣቢያው 18 የሚባለው ፖሊስ ጣቢያ ላይ ነበር ሲወረወር ነበር እያሉ ያሉት እናንተ ስትደርሱ ?
- አዎ እኛ ስንደርስ ያው እነሱን ቢድንጋይ ነው በጠርሙስም በድንጋይም ነው ሲመቷቸው የነበረው ማለት ነው እኛ ከደረስን በኋላ ያው ጣቢያውን ለቀቁ እኛ ደረስን ከእኛ ላይ ነው ውርወራ የተጀመረው በኋላ ማለት ነው
- ጣቢያውን ከበውት ነበር እናንተ ስትደርሱ ወርዋሪዎቹ ?
- ጣቢያውን ያው በር ላይ በሩን ይዘው በር ላይ ነው ፖሊሶችም በሩን እየተከላከሉ እያለ ነው በድንጋይ ሲሏቸው የነበረው ማለት ነው
- ምን ነበር ዓላማቸው ወደ ውስጥ ለመግባት ነው ወደ ጣቢያው እንዴት ነበር ?
- እሱን
- ምንድን ነው ተቃውሞ
- የተከበረው ፍ/ቤት የመጀመሪያው ጥያቄም አግባብ አይደለም ቀጥሎ ይስተካከላል ብለን ነው ዝም ብለን ስንጠብቅ የነበረው አሁን ግን በግልፅ የተከበሩ ዐቃቤ ሕግ
- እንደዚህ ብላችሁ ይሸውላችሁ ወደ ፊት ይስተካከላል ብላችሁ መነሳት ያለበትን ነገር አትለፉት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን ዐቃቤ ሕግ ያቀረቡት ጥያቄ ግልፅ የሆነ መሪ ጥያቄ ስለሆነ ሊጠይቁ አይገባም ወደ እዚህ እያሉ አቅጣጫ እየነገሩ ነው እና እንዲህ ዓይነት ጥያቄ መጠየቅ የለበትም ነው
- ምላሽ ስጡበት ዐቃቤ ሕግ
- ምላሽ የተከበረው ፍ/ቤት ፖሊሶቹ 18 ሲገኙ የነበሩት ፖሊሶች ጥቃት የደረሰባቸው ነበረ በጠርሙስ በድንጋይ ሲወረወርባቸው ነበር ብለዋል እነዚህ ሰዎች ፖሊስ ጣቢያው ጋር መጡ እንደፖሊስ እንደሕግ አስከባሪ አባል በወቅቱ ሲደርሱ እነሱ እየተከላከሉ ነበር እና ምን ነበር ዋና ዓላማው እንግባ ነው ወይ ነው ነው ኣይደለም የእሳቸው መልስ ነው እስከእዚህ ድረስ እኮ መጥተዋል አስረድተዋል ማለት ነው
- ጊዜ ላለመጨረስ ዐቃቤ ሕግ መጨረሻ ላይ የተጠየቀው ጥያቄ መሪ ነው ስለዚህ አስተካክለው ይጠይቁ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እናንተ ስትደርሱ እነኚህ አሁን ያሏቸው ሰዎች ከየት ኣቅጣጫ ወዴት ለመግባት ነበረ እየመጡ የነበረው ?
- አቅጣጫው የነበሩት መስኪዱ ከጣቢያው ፊት ለፊት ነው የነበረው ማለት ነው ስለዚህ ከመስኪዱ ያው ተነስተው ነው ወደ ፖሊስ ጣቢያ የመጡት ማለት ነው ያው ከፖሊስ ጣቢያው እና መስኪዱ ፊት ለፊት ነው መስኪዱ ፊት ለፊት ነው ያለው ስለዚህ አሁን መስኪዱ እና ፖሊስ ጣቢያው ይቀራረባል ከፖሊስ ጣቢያው ፊት ለፊት ነው ያለው መስኪዱ ከመስኪዱ ነው ወደ ፖሊስ ጣቢያው የመጡት ማለት ነው
- ፖሊስ ጣቢያው ጋር ስትደርሱ እናንተ ከአንድ አቅጣጫ ነው ወይስ እንዴት ነው እስቲ አሰላለፋቸው ምን ይመስላል ?
- አይ በአንድ አቅጣጫ ነው ያው ፊት ለፊት ብሎክ አለች በእሷ ነው የመጡት
- በአንድ አቅጣጫ ነው ?
- አዎ
- ቅድም ያልካቸው እናንተ አባላት በወቅቱ ያው ሕግ ለማስከበር ሲከላከሉ ማለት ነው ያው ጉዳት ደርሶባቸዋል እና ሕክምና አገኛችሁ ?
- አዎ ሕክምና ወዲያውኑ ያው እኛ ስንጎዳ አንቡላንስ አለ በአንቡላንስ ወደ ሆስፒታል ይዘውን ሄደዋል

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እነ ማን ነበሩ እስቲ ቅደም በድጋሚ እስቲ ንገረን ማን ማን ናቸው አባላቶቹ ማለት ነው ጉዳት የደረሰባቸው እነ ማን ናቸው ?
- አንደኛው እኔ ነኝ
- እርሶ እሺ ?
- 2ኛው ሚፍታህ ነው 3ኛው መሀሪ ይባላል በ3ታችን ላይ ነው ጉዳት የደረሰው
- 3ታችሁም በአንድ አምቡላስ የሄዳችሁት ?
- አዎ በአንድ አምቡላንስ ነው የሄድነው
- ከእዚህ ሌላ ማለት ነው
- እስቲ ቆይ ከእዚያ በፊት ከ2ቱ ከአንተ ውጪ ያለው 2ቱ ሰዎች ጠቅሰሀል እና የደረሰባቸው ጉዳት ምንድን ነው ?
- ቅድም አስቀምጬአለሁ
- እኮ ንገረና
- አሁን ካልካቸው እነኚህ ብቻ ናቸው ሌሎች አሉ ታስታውሳቸዋለህ ?
- አይ ሌሎችም ያው ቀላል ጉዳት የደረሰባቸው አሉ
- የምታስታውሳቸው አሉ ?
- አስታውሳቸዋለሁ
- እስቲ ንገረን ስማቸውን ?
- 1ኛው መብራቱ ይባላል
- ምኑ ላይ ነው ጉዳት የደረሰበት ?
- ይሄ ከንፈሩ ላይ ነው የተመታው 2ኛው ናስሩ ከድር ይባላል እዚህ ላይ ጆሮው ላይ ነው የተመታው 3ኛው ስሞን ዳንኤል ይባላል እሱ እጁን ነው የተመታው
- በምንድን ነው የተመታው በድንጋይ ?
- አዎ በድንጋይ
- እናንተ ሁላችሁም ጉዳት የደረሰባችሁ እንዳለ ተያይዛች ሁላችሁም በአንድ አምቡላስ ነው የሄዳችሁት ?
- 3ታችን ነን የሄድነው ያው፣የእኛ ከባድ ስለነበረ 3ታችን ነው የሄድነው 3ቱ አልሄዱም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ልክ ጉዳት ሲደርስባችሁ አንተ ይሄ ነገር አደጋው እንደደረሰባችሁ ስንት ሰዓት ሆነ ምሽቱ ?
- አደጋው የደረሰብን ቢያንስ ወደ 5 ሰዓት ተኩል አካባቢ ላይ ነው
- ከምሽቱ 4 ሰዓት ተኩል አካባቢ ?
- አዎ ከምሽቱ 5 ሰዓት ተኩል
- እናንተ ከእዚያ ቦታ እስክትሄዱ ድረስ ይሄ ነገር በርዷል ወይስ ገና ነበር ?
- አይ እኛ ወደ ሆስፒታል ነው የሄድነው ከእዚያ በኋላ የነበረውን ሁኔታ አላየሁም
- አታስታውሱም ?
- አላስታውስም
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- የተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ
- ረዳት ሣጅን ከመስኪዱ የወጡት ሰዎች ከፖሊስ ጣቢያው ጋር ግጭት የፈጠሩበትን ምክንያት ያውቃሉ እንዴ ?
- አይ እሱን አላውቅም
- የረብሻውስ ምክንያት ምን እንደሆነ ያውቃሉ ?
- የረብሻው ምክንያት ምን እንደሆነ አላውቅም
- ምስክር ቅድም ለፍ/ቤቱ የነገሩት እናንተ እርሶ ሲደርሱ ሰው በፖሊስ ጣቢያው ላይ ድንጋይ እየወረወረ ነው አይደል ደረስኩ ያሉት ?
- አዎ
- ስለዚህ ሰው እኮ ድንጋዩ ማለት ከመስኪዱ ፊት ለፊት ነው ያሉት ፖሊስ ጣቢያ ምን ያህል ይቅርቃል ከፖሊስ ጣቢያው እና መስኪዱ ?
- አይ በግምት አንድ 100 ሜትር ርቀት ይኖረዋል
- 100 ሜትር ርቀት ?
- አዎ
- ስለዚህ ፊት ለፊት ይበሉ እንጂ ሌላ ብሎክ ወይም ሰፈር ቤት ታልፈው ነው አይደል ፊት ለፊት ቢሆንም በመሀል በፖሊስ ጣቢያውና መስኪዱ እንዲህ ፊት ለፊት እኮ አይተያዩም በመሀል ሌላ ቤቶች አሉ አይደል ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ጥሩ እርሶ እንግዲህ ሰው ይሄንን ሁሉ አልፎ ፖሊስ ጣቢያው ደርሶ ነው የደረሱት እና ከመስኪድ ይውጣ ከሌላ ቦታ ይውጣ በምን ሊያረጋግጡ ይችላሉ ?
- እሺ መጀመሪያ ያው እኛ እንደደረስን ወደ መስኪድ ነው የተመለሱት ወደ መስኪድ ተመለሱ የመጡትም ያው ከመስኪድ ነው
- ግምትዎ ነው ?
- አቤት
- በቦታው ስላልነበሩ እርሶ ፖሊስ ጣቢያ ሆነው አገኙዋቸው ሰዎችን ከእዚያ እንዳሉት ወደ መስኪድ ተመለሱ ስለዚህ ከመስኪድ ወጥተው ሊሆን ይችላል እያሉን ነው አይደል ?
- አዎ ከመስኪድ ነው ያው የመጡት
- ቅድም በነበረን መሣሪያ ተከላከልን ብለዋል እንዴት ነው የተከላከላችሁት ?
- እሺ መሣሪያችን ያው ጋሽ እና ሄልሜንት መጋጫ ይባላል እሱ ምንድን ነው ከድንጋይ የሚከላከል ነው የሚወረወረውን ድንጋይ እና ጠርሙስ የሚከላከል መሣሪያ ነው እሱ መሣሪያው ይሄ ነው
- ስለዚህ በእሱ ብቻ ነው የተከላከላችሁት ?
- በእሱ ብቻ ነው የተከላከልነው
- እሱን ይዛችሁ ወደ ፊት ስትሄዱ ተበተነ ወደ ኋላ ሸሸ ማለት ነው ?
- አዎ እኛ ስንጠጋቸው ወደ ኋላ ነው የተበተኑት
- ወደ ኋላ ተበተኑ ሌላ መሣሪያ ጭስ አልተኮሳችሁም ?
- እሱን አልያዝንም አልተኮስንም
- ቅድም የተጎዱት ከእርሶ ሌላ የተጎዱ አባላት ብለው የጠቀሷቸው አሉ አንዱ አቶ ሚፍታህ ናቸው ሆስፒታል ከገባችሁ በኋላ አንድ ላይ ነው የተኛችሁት ?
- አይ ሆስፒታል ያው ገባን እኔ ራጅ ክፍል ነው የገባሁት ያው ራጅ ተነስቼአለሁ እነሱ ያው ሕክምና ተደርጎላቸው ተመልሰዋል
- በዕለቱ ?
- አዎ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በዕለቱ ተመለሱ ?
- አዎ
- እርሶ ስንት ጊዜ ቆዩ እዚያ ?
- እኔ ያው ያው ራጅ ተነሳሁኝ እዚያው አደርኩኝ በበነጋው መጣሁኝ እዚያው ካምፕ ሆኜ ግን ለ ፣ ወር ያህል ስራ አልተሰማራሁም
- እነ ሚፍታህ በዕለቱ ተመለሱ ካምፕ ተገናኛችሁ ?
- አዎ ካምፕ ተገናኝተናል እነሱም ስራ አልጀመሩም ቢያንስ ይሄ እጁን የተመታው ልጅም በጣም ነው ጉዳት የደረሰበት
- ሚፍታህ ምን ደረሰበት ማለት እግሩን ተጎዳ አሉ ?
- አዎ እግሩ ላይ
- ምን ሆነ እግሩ ?
- እግሩ ላይ ነው ጉልበቱ አካባቢ ላይ ነው የተመተው ያው እብጠት አለው በወቅቱ
- ምን ታሽጎ ነበር ?
- አዎ
- እርሶ አልጠየቁትም እንዴ ምን ሆንክ ጉልበቱ ተመታ በማግስቱ ተገናኛችሁ ከእዚያ ምን ሆንክ በትላንትናው ጉዳት ምን ደረሰብህ ዝም ብሎ ድንጋዩ አቆሰለው ነው ጉልበቱን ስላቆሰለው አመመው ነው ?
- አይ ጉዳት መድረሱን ያው
- አሁን እርሶ ጓደኛ ስለሆኑ ምንድን ነው የሆንከው ድንጋይ አረፈብህ ስለዚህ ጉልበት መጋጠሚያውን ስለመታህ ይሄ የእዚህ ሕመም ስሜት ነው ብለው አልጠየቁትም እንዴ ምንድን ነው የደረሰበት ?
- ያው የደረሰበትን የተናገርኩ መሰለኝ ጉልበቱ ላይ ነው በድንጋይ ነው የተመታው አብጧል ታሽጓል ስራም ሊያሰራውም አልቻለም በወቅቱ
- አይስራ እንጂ በእዚያው ይንቀሳቀስበት ነበር አይደል ?
- ይንቀሳቀሳል መንቀሳቀስ ያው ያነክሳል በወቅቱ ማለት ነው
- ያነክሳል እንጂ በማግስቱ ሲያዩት ይንቀሳቀስ ነበር ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በማግስቱ ያው ታክሞ መጣ ያው ይንቀሳቀሳል ግን ያስነክሰዋል
- ረዳት ሣጅን በወቅቱ ከሚፍታህ ጋር አንድ ላይ ነበራችሁ ?
- አዎ ነበርን
- አንድ ላይ ?
- አዎ
- መስኪድ ምን ተደረገ ከመስኪድ ምን ተደረገ ምን ሲደረግ አዩ መስኪድ ባዩሽ መስኪድ ብለው ነበረ ምን ሲደረግ አዩ ያዩት ነገር አለ ?
- ባዩሽ መስኪድ የነበረው ያው ድንጋይ ውርወራ ነው
- ድንጋይ ውርወራ ?
- አዎ
- ሌላ ነገር የለም ?
- አቤት
- ሌላ ነገር አላዩም ?
- ሌላ አላየሁም ድንጋይ ውርወራ አለ ያው ጠርሙስ አለ ሌላ ደግሞ አላህ ክበር አይዟችሁ አላህ ይረዳችዋል የሚባልም መልዕክት ነበር
- ሰምተዋል እርሶ በትክክል ?
- አዎ ሰምቼአለሁ
- ማን እንዳለ ያውቃሉ ?
- ማን እንዳለ አላውቀውም
- ይሄ ተወረወረ ያሉትን ነገር ማን እንደሚወረውር ያውቃሉ ?
- አላውቅም እሱን
- ማን እንደወረወረ አያውቁም ?
- አላውቅም
- ካላወቁ እሺ ልተወው እና እናንተ የተጠራችሁት የአዲስ አበባ ፖሊስ ጠርቷችሁ ነው ድረሱልን ብሎ ነው ወይስ እንዴት ነበር ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቀጠናው የራሳችን ነው ያው ድምፅ አላህ ክበር የሚል ከምሽቱ ሰዓት ላይ ስንሰማ ነው አለቆች አሉን በእነሱ አማካይነት ነው የወጣነው
- እኮ አዲስ አበባ ፖሊስ ሲያቅተው ነው የተጠራችሁት ዞሮ ዞሮ
- አቤት
- አዲስ አበባ ፖሊስ አቅቶት ነው ወይስ ለምንድን ነው የተጠራችሁት ?
- እሱ አዲስ አበባ ፖሊስ ይጥራ አይጥራ የማውቀው ጉዳይ የለኝም በአለቃችን ምክንያት ነው እኛ የወጣነው
- እስቲ ተመልሷል ግን
- ምንድን ነው
- ያልተመለሰ ነው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ ጉዳይ ነው እንደተቋም ተቋም ነው ስለዚህ ያ ሲያቅት እና ሳያቅት የወንጀል መከላከል ሒደቱ እራሱ አለ እንደአሰራር ማለት ነው ከእዚያም በላይ ሊሆን ይችላል ስለዚህ አገላለፅ ላይ ቋንቋ ላይ አቃተው አላቃተውም የሚባሉ ይሄንን እንትን እንድታርሙ ነው የምንጠይቀው
- እኮ ማለት ተቃውሞ የለም ግን አገላለፅ ሆኖ ነው
- ላስተካክል እና ልጠይቅ የተከበረው ፍ/ቤት ጉዳት ደረሰብኝ ብለው ነበረ ከባድ ጉዳት ነው የደረሰቦት ?
- አዎ ከባድ ጉዳት
- ምን
- እስቲ ቆዩ
- የደረሰባቸው
- አይ ምናልባት የተባለው ነገር ፣ኛ መልስ እየጠበቃችሁ መስሎን ነበር ስለዚህ ምን ለማለት ነው መመለስ ስላለበት ነው ጥያቄው ቀደም ብሎ የተመለሰ ስለሆነ ምናልባት የቋንቋ አጠቃቀም ከሆነ እሱን አስተካክላችሁ ጠይቁ
- የሄዳችሁት የአዲስ አበባ ፖሊስን ለማገዝ ነው ነው አይደል
- አቤት
- የሄዱት የአዲስ አበባ ፖሊስን ለማገዝ ነው አይደል ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኛ ቀጠናችን የራሳችን ስለሆነ ያው ፀጥታውን የማስከበር ኃላፊነትም የእኛ ነው ቀጠናው እራሱ
- ያንን ክልል የሚያስከብረው ማን ነው አዲስ አበባ ፖሊስ አይደል ?
- አዲስ አበባም ፖሊስ ነው ፌዴራልም ይቆጣጠረዋል አለ በጥምር ኃይል ነው የምንሰራው
- ለማንኛውም ነገር ነው የምትሄዱት ወይስ ለእዚህ ነገር ተጠርታችሁ ?
- ለማንኛውም ነገር የምንሄደው
- ስለደረሰቦት ከባድ ጉዳት ምንድን ነው የሀኪም ከባድ ጉዳት የሚል ደርሶታል እጅዎ ላይ ሀኪም ሰጥቶታል ?
- ጉዳቱ አዎ ራጅ አለኝ አዎ
- ራጁን አይደለም የደረሰባቸው ከባድ ጉዳት ነው የሚል ከሀኪም ደርሶታል ?
- የደረሰባቸው ጉዳት ከሀኪም የሚለው
- ደርሶታል
- የደረሰኝ የለም ግን ያው በወቅቱ
- እጅዎ ይሰራል አይደል በትክክል እጅዎ ይሰራል ?
- እኔ እጄን አልተነዳሁም እግሬ ላይ ነው
- ይሰራል እግርዎ በትክክል ?
- ላይ አሁንም ያው ይሰማኛል ግን አሁን ትንሽ ደህና ነኝ
- እናንተ ሕዝቡ ድንጋይ ሲወረውር ምን እያደረጋችሁ ነበር ዝም ብላችሁ ነበር የምታዩት ?
- እኛ ያው እንከላከላለን መከላከያ አለን ያው
- እሱ ተጠይቋል ምናልባት ሌላ ጥያቄ በምን ትከላከሉ ነበር እንዴት ነበር
- እርሶ እስከነበሩ ጊዜ ድረስ ባዩሽ መስኪድ ወይም አካባቢው ላይ ተኩስ አልከፈታችሁም ?
- ምንም ተኩስ የሚባል ነገር አልከፈትንም
- ይሄንን እንዴት አወቁ ?
- የያዝነውም ነገር የለንም
- ከእርሶ በኋላስ ይሄ ስለመፈፀሙ ያውቃሉ ?
- ከእኔ በኋላ ምን እንደነበረ አላውቅም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጨርሻለሁ
- ምስክር ቅድም አዛን ሰማን ሰምተን ነው ወደ ጣቢያ የመጣነው ብለዋል ያስተካክሉኛል ከተሳሳትኩኝ ከየት ነው የሰሙት ይሄንን አዛን ?
- አዛን የሰማነው ከእዚያው ከመስኪዱ ነው
- ከመስኪዱ ?
- አዎ
- በምን ማለት እርሶ ቅድም ርቀቱን ሁሉ ነግረውናል ?
- አዎ
- ከመስኪዱ ይሁን በምን አውቀው ነው ?
- ያው ከእዚያው አጠገብ ስለሆነ ይሰማናል ለእኛ
- ከእዚያ መስኪድ ብቻ ነው የተሰማው አዛን የሰሙት ?
- አካባቢያችን ያለው እሱ ስለሆነ እዚያ መስኪድ ብቻ ነው የሰማነው
- አሁን ባዩሽ ባሉት አካባቢ ሌሎች መስኪዶች የሉም በእዚያው አቅራቢያ በእሱ አቅራቢያ በጣም ቅርብ ?
- አለ አንዋር መስኪድ አለ ከእሱ ግን ምንም ነገር አልሰማሁም
- ከአንዋር ውጪ በእዚያ አካባቢ ሌላ መስኪድ የለም ?
- እነሱን ያው አሉ ግን አላውቃቸውም እነሱን
- ባዩሽ አጠገብ አሉ ?
- ባዩሽ አጠገብ ያሉትን መስኪዶች መስኪድ አለ ግን ማን መስኪድ እንደሆነ አላውቀውም
- ስለዚህ የተሰማው ከባዩሽ ብቻ ነው ?
- ባዩሻ መስኪድ ብቻ ነው የሰማሁት እኔ
- አመሰግናለሁ ቅድም ሲያስረዱ እኛ ወደ መስኪዱ እኛ ስንደርስ ፖሊስ ጣቢያ አካባቢ የነበሩ ሰዎች ተበታተኑ ወይም በተናቸው ብለዋል እንዴት አድርጋችሁ የበተናችሁት ?
- የበተነው ያው እኛ ደረስን ከእኛ ላይ ድንጋይ ወረወረ ያው መከላከያ ስላለን የመጠጋት ስራ ነው የሰራነው
- አስለቃሽ ጭስ አልተጠቀማችሁም ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጭሽ የሚባል ነገር አልያዝንም
- ቅድም በፖሊስ ላይ ደረሰ ያሉትን ጉዳት አስረድተውናል እዚያ አካባቢ ላይ የነበረ ሰው ላይ የደረሰ ጉዳት የለም ?
- ከእዚያ አካባቢ ላይ ማን እንደደረሰበት አላውቅም
- ፖሊስ ሂዱ በማለት ብቻ ነው እንዴ ሰውን የበተነው የተጠቀመው ኃይል የለም ?
- እኛ ምንም ኃይል አንጠቀምም የተጠቀምነው የለንም
- ቀጠይቂል
- እናንተ እዚያ አካባቢ ስትደርሱ መስኪድ ውስጥ ሰው ነበር አይደል ?
- አዎ አለ
- መስኪድ ውስጥ ሰው አለ ?
- አዎ
- ፖሊስ ጣቢያ አካባቢም ሰው አለ ?
- አዎ
- ፖሊስ ጣቢያ አካባቢ ያለው ሰው ከሌላ ቦታ የመጣ ሰው ይሁን አይሁን እርሶ የሚያውቁት ነገር የለም አይደለም ?
- እሱን ከሌላ ይምጣ አይምጣ የማውቀው ነገር የለኝም
- ከመስኪድ ውስጥ አትውጡ ከመስኪድ አትውጡ ውጪ ያላችሁት ከእኛ ጋር አይደላችሁም ሲሉ የነበሩ ሰዎች ነበሩ ሰምተዋል ይሄንን ?
- እሱን አልሰማሁም
- ጨርሰናል
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ
- ቅድም ሣጅን ሲገልፁ በመስኪድ ውስጥ ከመስኪድ ውጪ ማለት ነው ያው ድንጋይ እናንተ ስትደርሱ ድንጋይ ይወረወራል ጠርሙስ ይወረወር ነበር ብለዋል እና በእዚያው ደግሞ ስትሰሙ አላህ ከበር ይል ነበሮ ብለዋል ብለዋል የት አካባቢ ነው ሲል የነበረው የሰማችሁት ?
- ምን ድንጋይ የተወረወረው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሲወረወር አላህክበር ይል ነበር ብለዋል እና የት ነው የቱ ጋር ሆኖ ነው ?
- አላህ ክበር የሚለው መስኪድ ውስጥ ሆኖ ነው
- እየተወረወረ እያለ ነው እንደዚያ ሲሉ የነበረው ?
- እየተወረወረ እያለ አላህ ክበር አይዟችሁ በርቱ አላህ ይረዳችዋል በሏቸው ነው የነበረው መልዕክት
- የነበረው ?
- አዎ
- ታዲያ ቅድም አሁን ሲጠይቆት እነ ማን የሚወረውሩ ሰዎች በግልፅ እያዩዋቸው ነበረ በአካል ያው ትተያያላችሁ አይደል ?
- መጀመሪያ ስንደርስ አካባቢ ያው መብራት አለ ከእዚያ በኋላ ያው ድንጋይ ውርወራ ምናምን ሲሆን ሲበዛ መብራት የለም ነበር በወቅቱ ማለት ነው እንደደረስን መብራት አለ ከደረስን በኋላ ግን መብራት ጠፍቷል
- ስለዚህ እነኚህ ሰዎች ሲወረውሩ የነበሩ ሰዎች ቅድም ሲጠየቁ አይ ከመስኪድ ወጥተው ሊሆን ይችላል ከእዚያ አካባቢ ነው ወይ ሲባሉ አዎ የእርሶ ግምት ነው ወይ ሲባሉ አዎ ብለዋል በእርግጠኝነት ግን እነዚህ ሰዎች አሁን እዚህ ጋር በርቱ የሚል ድምፅ አለ የሚያበረታታ አለ አሁን እንደገለፁት ማለት ነው ከእዚህ ጋር በተያያዘ እነዚህ ሰዎች ከየት ነው የወጡት ማለት ነው
- ምንድን ነው መቃወሚያው ቆይ
- የተከበሩ ዐቃቤ ሕግ እያነሱ ያሉት የእኛን የመስቀለኛ ጥያቄ ሳይሆን ዋና ጥያቄ ነው የራሳቸው ነው ደግመው እየጠየቁ ያሉት እኛ በመስቀለኛ ጥያቄ አሁን ዐቃቤ ሕግ እየጠየቁ ባለው መንገድ አላስረዳንም ወይም እንዲመስክሩ አላደረግንም እርሶ ሲደርሱ መስኪድ ውስጥ ሰው ነበር አዎ ፖሊስ ጣቢያም ሰው ነበር አዎ ይሄንን በተመለከተ ጥያቄ ከመጠየቅ ውጪ በዋና ጥያቄ ያልጠየቁትን ጥያቄ ደርበው እየጠየቁ ስለሆነ ጥያቄአቸውን አስተካክለው እንዲጠይቁ እንዲደረግልን ነው
- ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ግልፅ ያልሆነ አለ ትንሽ ዐቃቤ ሕግ ምላሽ ከመስጠቱ በፊት በዋና ጥያቄ አልተነሳም ነው በመስቀለኛ አልተነሳም ነው እሷን ግልፅ አድርጉ ?
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ዐቃቤ ሕግ እንግዲህ ሁላችንም እናውቃለን ዋና ጥያቄ ጠይቀዋል ዋና ጥያቄ ላይ የተጠቀሙትን ዕድል መልሰው አሁን ድጋሚ ጥያቄ ላይ ደርበው እየተጠቀሙ ነው ነው ዋና ጥያቄ ባህሪ ግልፅ ነው የድጋሚ ጥያቄ ባህሪ ግልፅ ነው እና አሁን እየጠየቁ ያሉት ጥያቄ ዋና ጥያቄ ላይ ያላነሱትን በድጋሚ ጥያቄ ላይ ደርበው
- በመስቀለኛ ጥያቄ ያልተነሳ እየጠየቁ ነው ነው በሌላ አነጋገር ?
- አዎ ደርበው ነው አስጠግተው እየጠየቁ ያሉት ስለዚህ ሊጠይቁ አይገባም እኛ የጠየቅነው ጥያቄ ግልፅ ነው አሁንም መድገም እችላለሁ መስኪድ ውስጥ ሰው ነበር ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ሰው ነበር በተመሳሳይ ጊዜ ስለዚህ ይሄንን
- ጥያቄውን ይዘናል የእናንተ ተቃውሞ ብቻ እንዲገባ ነው
- ይሄንን በተመለከተ ግልፅ የሆነ ጥያቄ ይጠይቁ እንጂ የዋና ጥያቄን እንደገና አሁን ደርበው እየጠየቁ ነው ነው የእኛ
- ምላሽ ስጡበት ?
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አሁን እሳቸው እያሉ ያሉት የራሳቸውን ብቻ ነው ከራሳቸው የቀረበው መስቀለኛ ጥያቄ በአጠቃላይ ግን እንደቡድን አጠቃላይ በእነሱ የተነሱት መስቀለኛ ጥያቄዎችን መሠረት በማድረግ ድጋሚ መጠየቅ እንችላለን ነገር ግን አሁንም ግልፅ ለማድረግ ቅድም ሲጠየቁ ፅዎቹ ከየት ወጥተው ሊሆን ይችላል ግምት ነው ከየት ወጥተው ሊሆን ይችላል የሚል ተጠይቀዋል አይ በእርግጠኝነት ነው ከመስኪድ ወጥተዋል አልወጡም የሚለውን ነገር ሲጠየቁ አይ አዎ የእኔ ግምት ነው ግምት ነው ሲሏቸው አዎ ብለው መልስ ሰጥተዋል ያንን ነው ያንን መሠረት አድርጌ ነው እነዚህ ሰዎች ሲነሱ ከየት ወዴት ነበር የሚለው ግልፅ እኮ ነው ያው እርግጥ በእዚያ ዙሪያ ነው ተነስቷል ምላሹም ግልፅ ነው ይሄንን ለማጥራት ብቻ ስለፈለኩ ነው ከእዚያ ውጪ መስቀለኛ ተጠይቋል
- ያው ጥያቄው በመስቀኛ ጥያቄ ተነስቷል ዐቃቤ ሕግ ቀጥሉ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አመሰግናለሁ ቅድም አሁን ለማረጋገጥ እነዚህ ሰዎች እናንተ ስትደርሱ ጠርሙስ ድንጋይ ይወረውሩ ነበር ብለዋል ከእዚያ ደግሞ ቅድም ያሉት ነገር አለ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

በርቱ እንደዚህ ስለዚህ አሁን ከየት ነው የወጡት ማለት ነው እነዚህ ሰዎች የሚያውቁትን የሚያስታውሱትን ማለት ነው ?

- እሺ እኛ ያው በመጀመሪያ ስንደርስ ከየት ይምጡ ከየት ይምጡ አላየናቸውም ያው ከደረስን በኋላ ነው ወደ ኋላ እየሸሹ ወደ መስኪዱ የተመለሱት ማለት ነው
- ጨርሻለሁ የተከበረው ፍ/ቤት
- በፍ/ቤቱ ጥያቄ የምስክሩ መልስ
- አንድ አሁን የሕክምና ከጉዳቱ በኋላ ወደ ሕክምና ሄጄ ራጅ ተነስቼአለሁ ብለህ ነበር እና በወቅቱ ከባድ ጉዳት ስለመድረሱ በሕክምና የተሰጠህ ማስረጃ አለ ሲባል አልተሰጠኝም ነገር ግን በወቅቱ ብለህ ነው ጠበቃው ያቋረጡህ እና ምን ለማለት አስበህ ነው እሱን ግልፅ አድርግ ?
- ያው የሕክምና ማስረጃ የተሰጠኝ የለም ያው ራጅ ተነሳሁኝ መድሀኒት ምናምን ተሰጠኝ ወደ ቦታዬ ተመልሼአለሁ መድሀኒት ታዘዘልኝ ወደ ቦታዬ ተመልሼአለሁ ወደ ካምፔ ማለት ነው
- ወደ ስራ ተመለስክ ?
- አይ ካምፕ ነው የተመለስኩት እንጂ ስራ ለ ፣ ወር ያህል አልሰራሁም
- ለ ፣ ወር ስራ አልሰራህም ?
- አዎ
- ለምን
- ጉዳት ስለነበረ ያስነክሰኛል አያስለብሰኝም ጫማ
- እረፍት ተሰጥቶሀል ?
- አይ እረፍት አልተሰጠኝም ያለው አመራር ጫማ ስለማያስለብሰኝ አንድ ወር ያህል ያው አሳርፈውኛል
- ለአንድ ወር አልሰራህም ?
- አዎ
- ቅድም ጀመሬ የተውኩት ጥያቄ ነበር 2 ጓደኞችህ ጉዳት የደረሰባቸው አንዱ እጁ ላይ ነው የደረሰበት ነው ያልከን በእሱ ጉዳት ምንድን ነው አሁን ያለው ውጤቱ ?
- ፣ኛው ያው እጁ ላይ ነው የደረሰበት ብዬአለሁ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን ምን ሆኗል
- ከሚፍታህ ጀምር እና ?
- የሚፍታህ ቀኝ እግሩ ላይ ነው ይሄ ጉልበቱ ላይ አለ አይደል እሱ ላይ ነው ጉዳት የደረሰው
- በምን ያህል ጊዜ ወደ ስራ ተመለሰ ?
- ቢያንስ ወደ 15 ቀን ያህል ምናምን ያው እሱም ከእኔው ጋር ነው ነበር የነበረው እረፍት ማለት ነው
- 15 ቀን ?
- አዎ
- የተሰጠው ሕክምና ማስረጃ አለ ?
- እሱን አላውቅም ይሰጠው አይሰጠው
- ለ 15 ቀን አልሰራም ?
- አዎ ያው ባለው አመራር አማካይነት
- በምን አወክ ይሄንን ?
- አብረን ነው ያለነው አንድ ላይ ስለሆን በካምፕ ውስጥ ነው የምንኖረው
- ከጉዳቱ ጋር በተያያዘ ነው ወይስ በሌላ ነው ?
- አይ ከጉዳቱ ጋር በተያያዘ ነው
- ስለመሀሪስ ?
- መሀሪ ያው እጁን ነው የተጎዳው እሱ ግራ እጁን ነው የተጎዳው እሱም አሁን የተሰጠው ውጤት ይኑር አይኑር የማውቀው ነገር የለኝም
- በምን ያህል ስራ ጊዜ ወደ ስራ ተመለሰ ?
- መሀሪ አሁንም ቢሆን ያው እጄን ይሰማኛል ነው የሚለው
- አሁንም ይሰማኛል ይላል ?
- አዎ
- ነገር ግን ያኔ ወደ ስራ የተመለሰው በምን ያህል ጊዜ ነው የምታውቀው ?
- አይ ወደ ስራ የተመለሰበትን ጊዜ አላውቀውም እሱን
- እሱን አታውቅም እናመሰግናለን ጨርሰህል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላ ምስክር ጥሩ
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- በፍ/ቤቱ 36ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር በዐቃቤ ሕግ ክስ ላይ ስንት ቁጥር ነው 180 ላይ የተጠቀሱ ምስክር ቀርበው ቃለ መሀላ ፈፅመዋል ለምስክሮች ደህንነት ሲባል አድራሻ እና ሙሉ ስም አይገለፅም የመጀመሪያ ስም ብቻ ይገለፃል
- የመጀመሪያ ስምዎ ማን ነው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ለምንድን ነው እዚህ የመጡት ?
- በታዛቢነት ያየሁትን ቃል ለመስጠት
- የምን ታዛቢነት ነው በእነ ማን ነው የሚታዘቡት ?
- ሰይድ አሊ
- ሌላ ?
- እና ወ/ሮ ሀቢባ
- ማን ነው ወ/ሮ ሀቢባ ?
- ሀቢባ መሐመድ
- ሌላስ ?
- በቃ
- ያውቋቸዋል እነዚህን ሰዎች ?
- አዎ በአይን
- ሊያሳዩን ይችላሉ
- ሰይድ አሊ
- የትኛው ነው ?
- ጃኬት ያደረገው
- ልክ ነው ለይቷል ስንተኛ ተከሣሽ ነህ እሺ 16ኛ ተከሣሽን ለይቶ አሳይቷል ሌላ
- ወ/ሮ ሀቢባ
- እሺ 28ኛ ተከሣሽን ለይቶ አሳይቷል ቁጭ በል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን ሲደረግ ነው የታዘብከው እስቲ አልገባኝም ታዝቤአለሁ ነው ያልከው ምንድን ነው የታዘብከው ምን ሲደረግ እሱን ብቻ ዋናውን ፍሬ ነገር ንገረን እና ወደ ሌላው እንገባለን የ2ቱ ሰዎች ምን ሲደረግ ነው የታዘብከው ?
- የመጀመሪያው ላይ የወ/ሮ ሀቢባ መሐመድ ላይ ከመንግስት መኪና ውስጥ
- ኣይ የታዘብከው ምንድን ነው እሱን ብቻ አሳጥርልን እና ዝርዝሩን ትገባለህ ይጠይቃሉ ግራ ቀኙ ቃል ስትሰጥ ነው ቤት ሲፈተሽ ነው ወይስ ሌላ ሲደረግ እሱን ነው የፈለግነው እኛ ?
- ኣይ እዚያው ፌዴራል ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ የመጀመሪያው መኪና ሲፈተሽ ነው የታዘብኩት
- መኪና ሲፈተሽ የማንን ?
- የወ/ሮ ሀቢባ
- መኪና ሲፈተሽ ነው እሱን ነው የታዘቡት ?
- ኣዎ
- የኣቶ ሰይድስ ?
- የኣቶ ሰይድ ደግሞ ኮምፒዩተር ላፕቶፕ
- ምን ሲሆን ?
- ውስጥ ያሉ ፋይሎች ሲታይ
- ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ
- የተከበረው ፍ/ቤት እስቲ ከወ/ሮ
- ዐቃቤ ሕግ ከእዚያ በፊት አንድ እነዚህ ሰዎች ጋር ፀብ ወይ ዝምድና አለህ ?
- ኣይ
- የለህም ?
- ምንም ዓይነት ነገር የለኝም
- ዐቃቤ ሕግ ቀጥሉ ዋና ጥያቄ
- እስቲ ምንድን ነው ያየኸው ቆይ ከእዚያ በፊት የኣቶ ሰይድን ኮምፒዩተር ምስክር መጀመሪያ በኣቶ ሰይድ አሊ እንሂድ እና ከኣቶ ሰይድ አሊ መቼ ቀን ምንድን ነው የታዘብከው ምንድን ነው ያየኸው ጊዜው ሰዓቱ ቦታው የት ነበረ እስቲ እሱን በዝርዝር አስረዳ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ አቶ ሰይድ ላይ እንደአጋጣሚ እዚያ አካባቢ ለግል እንትኔ እየተንቀሳቀስኩ ነበረ
- የት አካባቢ ?
- ፌዴራል ፖሊስ አካባቢ አንድ መርማሪ ነኝ
- ፌዴራል ፖሊስ የት ነው፡ ፌዴራል ፖሊስ የት ያለው ?
- ማዕከላዊ አካባቢ 3ኛ አካባቢ ማለት ነው
- ቀኑ መቼ ነበር ጊዜው ?
- ሐምሌ 29 አካባቢ
- ቀኑ እርግጠኛ ነህ ወሩስ ?
- ሐምሌ 19 ክረምት ነበር ሐምሌ 29 ጠዋት ነው 3 ሰዓት ከ 3 እስከ 4 ባለው ጊዜ ውስጥ
- ዓ.ም ?
- 2004
- ሰዓቱስ ?
- 3 ሰዓት
- 3 ሰዓት አካባቢ ምንድን ነው የገጠመህ በእዚህ ዕለት ?
- ጓደኛዬ እዚያ አካባቢ ኬዝ ነበረው እና ከእሱ ጋር መጥቼ ነው መጥቶ እንደዚህ ዶክመንት ከቤት ፈትሸን ያመጣነው ዶክመንት ኮምፒዩተር ስላለ እሱን ስንፈትሽ በታዛቢነት እንድትሆን ብሎኝ ፍቃደኝነቴን ገልጬለት ነው አብሬው የገባሁት ውስጥ ስገባ አቶ ሰይድ ውስጥ ስገባ አቶ ሰይድ ውስጥ ነበሩ እሳቸው የእሳቸው ዶክመንት መሆኑን ተነገራቸው ከእሳቸው ሌላ ቢኒያም የሚባል ልጅ እንደእኔ ታዛቢ የነበረ አብሮ ነበረ ያ ላፕቶፕ ከእሳቸው ቤት የወጣ መሆኑ ተነገረ እሳቸውም አዎ በእኔ ቤት ነው የወጣው የሚለውን ቃላቸውን ሰጡ ከእዚያ ውስጥ ያሉ ነገሮች እየወጡ መታዘብ ጀመርን ማየት ጀመርን ማለት ነው
- በመጀመሪያ ያንን ያ ላፕቶፕ መጣ ከእዚያ እስቲ ምን ቀጣይ ፕሮሰሱ ምንድን ነው የተደረገው እሳቸው ይሄ ነው አሉ እሺ ከእዚያስ ማን ከፈተ እንዴት ተከፈተ ማን ነገረ እሳቸው ምን አሉ አንተ ምን አየህ ?
- አልገባኝም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ላፕቶፑ መጣ በቁጣይ የነበረው ሂደት እንዴት ነበረ እስቲ ሂቱን ንገረን ?
- ላፕቶፑ መጣ የእሳቸው መሆኑን ተገለፀልን እሳቸውም አዎ የእኔ ነው አሉ ከእዚያ ውስጥ ያሉ ፋይሎች ፅሁፍ መውጣት ጀመሩ እነዚያን ፋይሎች እያነበብን ማየቴን ከእሳቸው ፋይል ውስጥ መውጣቱን ያታችንም ፈረምን
- ክእሳቸው ፋይል ውስጥ እያልክ ያለኸው ከላፕቶፑ ማለትህ ነው ?
- አዎ ከላፕቶፑ ውስጥ ማለቴ ነው
- ይሄንን ላፕቶፕ ማን ከፈተ እንዴት ፓስወርዱ ምናምኑ ማን ነገረ እስቲ ይሄንን አልሰማህም እንዴ እንዴት ?
- ፓስወርዱን አላየሁኝም ፓስወርድ የለውም ውስጥ የነበረ ፋይል ነው
- እና ቀጥታ ነው የተገባው ?
- አዎ ቀጥታ ነው የተገባው
- ምን ምን ተገኘ
- እስቲ በኋላ ከምንጠይቅ በእዚሁ ግልፅ ይደረግ እና ከላፕቶፑ ይወጣ ነበር ስለፓስወርድ አንስተሀል እና ከኢሜል ነው ከላፕቶፕ ነው ፓስወርዱ የኢሜል ፓስወርድ ነው ወይስ የላፕቶፕ ፓስወርድ እሱን ግልፅ አድርገህ ግልፅ ነው ጥያቄው የአሁኑ የአሁኑ ?
- ግልፅ ነው አዎ ምንም ዓይነት ፓስወርድ
- ፓስወርድ ታውቃለህ አንተ ?
- አውቃለሁ አዎ ምንም ዓይነት ፓስወርድ አልጠየቀም
- ላፕቶፑ ነው ወይስ ኢሜል የወጣው ዶክመንት ከኢሜል ነው ከላፕቶፕ ?
- የወጣው ዶክመንት የኢሜል እንቅን ነው ግን ዳውን ሎድ የተደረገ የኢሜል እንትን ነው
- ዳውን ሎድ ተደርጎ የተቀመጠ ?
- የተቀመጠ ፋይል
- አስቀድሞ ?
- አስቀድሞ አዎ
- ከእዚያ እሱ ሲወጣ አየህ ምን ምን ነበር የወጣው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፁሑፎቹ የነበሩት ፁሑፎች በግጥም መልክ የቀረቡ ቀስቃሽ የሆኑ እንደዚህ አላህክበር መስኪድ እንደዚህ ዓይነት መስኪድ ላይ እንደዚህ ዓይነት እንትን ስላለ ወደእዚያ እንሂድ እንደዚህ ዓይነት ሕዝቦች ወደ እዚያ እያለቁ ነው እና ጠቅልለን ነገ ጠዋት በአስቸኳይ እንደዚህ ወደ አወሊያ እንሂድ ይሄንን መሴጅ በአስቸኳይ ለእዚህ ሰው በፍጥነት አስተላልፉ አሳቸኳይ ነው እንደዚህ የሚሉ የቀስቃሽ ዓይነት ፁሑፎች ናቸው
- ምን ያህል ይሆናሉ ?
- ከ 27 እንደዚህ 28 /30 እንደዚህ
- እንደዚህ በግምት ይሆናሉ ?
- በግምት አዎ 30 አካባቢ ይሆናሉ
- ከእዚህ ጋር ሌላ የምታስታውሰው አለ የወጡትን ?
- ኡዲዮ ነገር ኡዲዮ ነበረ ይሄንን ይሄንን የሚል ከእዚያ ከውስጡ የወጣ ኡዲዮ ድምፅ ነበረ
- ምንድን ነው እሱ ድምፁ ማለት ?
- እንደዚህ የተለያዩ እንደዚህ ዓይነት እንደፁሑፉ ዓይነት ቅስቀሳ ያላቸው የተለያዩ ድምፆች ማለት ነው
- ለነኚህ አሁን ለጠቃሳይ አሁን ያልካቸው ማለት ነው ከእዚህ ከላፕቶፕ የወጡትን ዝርዝር ምን ያህል ደቂቃ ወይ ምን ያህል ጊዜ ወስደ ሲወጣ ማለት ነው ?
- ከ 3 ሰዓት ጀምረን እስከ 6 እንደዚህ አካባቢ ድረስ እዚያ ቆይተናል
- መጨረሻ ከወጣ በኋላ እስቲ ምን አደረጋችሁ ማለት ስለመውጣቱ ይሄ ነገር ከእዚያ ከላፕቶፕ ስለመገኘቱ ማረጋገጫ ምን ተከናወነ ?
- ያው ቅድም መግቢያው ላይ ለማስቀመጥ እንደሞከርኩት 3ታችንም ፈረምንበት
- 3ታችሁ ?
- 3ታችን
- ማን ማን አንዱ አንተ ነህ ሌላው ?
- እኔ ነኝ አንዱ አንደኛው ቢኒያም የሚባለው ልጅ ነበር አብሮ 3ኛው እራሱ እራሱ
- ማን ?
- አቶ ሰይድ

2016

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አቶ ሰይድ ?
- አዎ
- እሱም እራሱ ፈርሟል ?
- እሱ እራሱ ፈርሟል
- እስቲ አሁን ደግሞ ስለወ/ሮ ሀቢባ ንገረን ወ/ሮ ሀቢባ ምንድን ነው ያየኸው ?
- ወ/ሮ ሀቢባ ላይ የመንግስት ላንድ ክሮዘር መኪናዎች የእሳቸው መሆኑን ነው እንትን የተባለው ሲፈተሽ ማለትም ውስጡ የነበሩ እቃዎች
- መቼ ነበር ጊዜው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ ሐምሌ 9
- ሐምሌ 9 ሲፈተሽ ነበርክ ?
- አዎ
- የት አካባቢ ነበር ?
- እዚያው ማዕከላዊ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ
- እዚያ ቅድም ያልከበት ቦታ ማለት ነው ?
- አዎ
- ስንት ሰዓት ይሆናል ?
- 10 ሰዓት አካባቢ
- ምንድን ነው የተገኘው ላንድክሮዘር ውስጥ ምን ተገኘ ?
- መኪና ውስጥ አረብኛ መፅሐፍ ወደ 440 አካባቢ
- አረብኛ መፀሐፉ ምንድን ነው ስለምን የሚል ነው ?
- እረብኛ ነው አረብኛ ሆኖ እንደ የሙስሊም መፅሐፍ ቅዱስ ቁራን ዓይነት ነገር ነው
- ቁርአን ዓይነት ነው ወይስ ?
- አረብኛ መፅሐፍ መሆኑን ነው እንጂ ቁርአን ያው ስለማላውቅ ነው
- ሊሆን ይችላል ብለህ ትገምታለህ ?
- ሊሆን ይችላል ብዬ እገምታለሁ
- ሌላስ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላ ሳህን ወደ ጋዜጣ አካባቢ /ግልፅ ያልሆነ/ እንደዚህ አካባቢ ሳህን
- እስቲ የምታስታውሳቸውን ያገኘሀቸውን አንተ ግለፅልን ?
- ብረት ድስት
- ስንት ?
- ጎርጓዳ ብረድስት ተልልቅ 2 ጭልፋ መክተፊያ
- ሌላስ ?
- ብር ወደ 50 ሺህ ብር አካባቢ
- ብር ነው ?
- ብር አዎ
- ሌላስ ?
- ዲጂታል ካሜራ እነዚህ ናቸው
- ከየት እንደመጣ አወቀህል ?
- ከየት እንደመጣ ከሳውዲአረብያ ከኃይማኖት ክፍል ወጥቶ በክትትል መሆኑን መጨረሻ ላይ በቃለ ጉባኤ 3ታችንም ሆነን በቃለ ጉባኤ ሲነገር እሳቸውም አምነው በቃለ ጉባኤ /ግልፅ ያልሆነ/
- 3ታችን ተፈራርመናል ስትል መጨረሻ ላይ ማን ማን ናችሁ የተፈራረማችሁት ?ዝ
- ከእኔ ጋር አንድ ታዛቢ ነበር እዚያ ጋር
- ማን ነው ስሙ እሱ ?
- ተመስገን መሰለኝ ባልሳሳት
- ተመስገን ?
- አዎ
- አንተ 3ተኛው ማን ናቸው ?
- ወ/ሮ ሀቢባ እራሳቸው
- ምን አሉ ሲፈርሙ ?
- ቃለጉባኤው ተነበበልን አዎ የሚለውን ነገር እንትን ተብሎ ፈርመናል
- ይሄ የተገኘው የሰሌዳ ቁጥር ትዝ ይልሀል ታስታውሳለህ የመንግስት ላንድክሮዘር ያልከው?

2018 4479

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የመንግስት ላንድ ክሮዘር 4 ቁጥር ነው
- ካስታወስክ ነው ካላስታወስክ ቅድም ከታይማኖት /ግለፅ ያለሆነ/ ከሳውዲ ኢምባሲ ማለት ነው ሲነገር ሰምተህል እና ማን ነው ይሄንን ሲናገር የሰማኸው?
- ቃለጉባኤውን የፃፈልን
- ቃለጉባኤው ላይ ይህ ቃል ከተባለ በኋላ ያው እሳቸው አምነውበት ፈርመዋል ?
- አዎ
- ጨርሰናል
- የተከሣሽ ጠበቆች በመጀመሪያ የሰይድ ጠበቆች
- ምስክር በወቅቱ አንተ በቦታው ላይ የተገኘኸው በግል ጉዳይህ መሆኑን ነው የገለፅከው ሰይድን ከእዚያ በፊት አታውቀውም አይደል ?
- አዎ አላውቀውም
- የተከሰሰ ስለመሆኑም አታውቅም አይደል ?
- የተከሰሰ
- የተከሰሰ ስለመሆኑ አታውቅም አይደል ?
- ያው ከተጠርጣሪ ቤት ላፕቶፕ መሆኑን ስለማውቅ ተጠርጣሪ መሆኑን እንደዚሁ አውቃለሁ
- ተቀጣሪ ስላልሰማውህ ነው በደንብ ንገረን ጥያቄዬ ሰይድን ከእዚያ በፊት አላውቀውም ብለሀል የተከሰሰ ስለመሆኑም አታውቅም አይደለም ወይ ነው ?
- ግልፅ አይደለም እኮ ጥያቄው ለእኛም ግልፅ አይደለም አሁን ነው ወይስ ?
- አይደለም ያኔ በሚያይበት ጊዜ ያኔ በሐምሌ
- በታዘቡበት ቀን ከሆነ እሱን አድርገው አሁን ከሆነ አሁን አድርገው ?
- አይ ሐምሌ 29 ቀን እሳቸው እየመሰከሩ ያሉት ስለ ሐምሌ 29 ስለሆነ ነው ቀን ውስጥ ያልገባሁት ሐምሌ 29 ቀን የተከሰሰ ስለመሆኑ አታውቅም አይደል ?
- ግልፅ ሆኗል አሁን
- እዚያ ቦታ ላይ ያው ተከሶ እዚያ ቦታ ላይ እንዳለ መገመት ይቻላል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የአንተ ግምት ነው እንጂ ስለመከሰሱ አታውቅም በምን ጉዳይ እንደተከሰሰ ፖሊሱ አልነገረህም አይደለም ?
- ኬዙን ምናምን አላውቅም አዎ
- በቢሮ መጀመሪያ የቱ ጋር ሆነህ ነው መርማሪ ፖሊስ አንተን የጠራህ መርማሪ ፖሊስ ነው ያልከው ሰው አንተን የጠራህ አንተ የት ነበርክ መጀመሪያ ?
- እዚያው በሩ አካባቢ
- በሩ ማለት የት ነው በትክክል ንገረን ቦታውን ?
- በሩ በ3ኛ በኩል ባለው በር አካባቢ
- ማለት ከግቢው ከፖሊስ ጣቢያው ግቢ ውጪ ነው የነበርከው ?
- አዎ
- ከግቢ ውጪ ነው ?
- አዎ
- ከግቢ ውጪ ነው ፖሊስ መጥቶ የጠራህ ?
- አዎ
- ያ የጠራህ ፖሊስ ማን ነው የሚባለው ?
- ስሙን አላስታውሰውም
- መርማሪ ነው ብለህል ቅድም መርማሪ መሆኑን በምን አወክ ?
- መርማሪ መሆኑን ገልፆልኛል
- እሱ ነው የነገረህ ?
- አዎ
- እንጂ መርማሪ ስለመሆኑ አታውቅም ?
- አላውቅም አዎ
- ከእዚያ የገባችሁት ምን ውስጥ ነው የገባችሁት ?
- እዚያው ግቢ ውስጥ
- እኮ ግቢ ውስጥ ገብታችሁ ምን ቦታ ነው የሄዳችሁት ?
- ክፍል ገባን የሆነ ቢሮ ውስጥ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን ይላል ቢሮው ቁጥር አለው ስም አለው ቢሮው ?
- ቁጥር አለው ቁጥሩን አላስታውሰውም
- የምርመራ ቢሮ የሚል ነገር አለው ቢሮው የለውም አይደል ?
- ቁጥር ብቻ ነው ያለው
- የምርመራ ቢሮ የሚል ነገር የለውም እዚያ ስትገባ ሰይድ እዚያ ቁጭ ብሎ ነው ያገኘኸው?
- አዎ
- ከየት መጥቶ እዚያ እንደተቀመጠም አታውቅም ?
- አላውቅም አዎ
- ከገባችሁ በኋላ አንተ እና ቢኒያም አይደል በታዛቢነት የተገኛችሁት የእዚያ ቦታ ?
- አዎ
- ለ2ታችሁ ምን ጉዳይ እንደምትታዘቡ አልተነገራችሁም አይደል ?
- ተነግሮናል
- ምንድን ነው የተነገራችሁ ?
- ከተጠርጣሪው ቤት የመጣ ኮምፒዩተር ላፕቶፕ አለ እሱ ሲበረበር እንድትታዘቡ ነው ተብለን ነው ከታዛቢው ቤት የመጣ ላፕቶፕ አለ እሱ ሲከፈት እንድታዩ ነው ተብለናል
- ከእዚህ ሌላ መርማሪው ምንም አልተናገረም ?
- ምንም አላለንም አዎ
- ለሰይድም በላፕቶፕ ውስጥ የሚገኙት መረጃዎች በመረጃነት የሚቀርቡበት ስለመሆኑ እልተነገረውም አይደል ?
- አልገባኝም እኔ
- መርማሪ
- ያኔ ስትገቡ ይሄ ማስረጃ ከላፕቶፕ የሚወጣ ነው ይሄ ደግሞ በሰይድ ላይ ማስረጃ የሚሆን ነው ተብላችሁ ተነግሯችዋል አልተነገራችሁም ነው ጥያቄው ?
- ያው ስንገባ አስተዋውቆናል እነዚህ 2ቱ ታዛቢዎች ናቸው ፋይልህ ሲከፈት የሚያዩ ናቸው ተብሎ ተዋውቀን ነው የጀመርነው እንትኑን
- ጥያቄው እኮ ግልፅ ነው መርማሪው ፖሊስ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከእዚህ ውጪ ምንም ያለን የለም ማለቴ ነው በእዚያ
- ምንም አልተናገረም እሺ ላፕቶፑ የት ጋር ነው የነበረው ስትገቡ ላፕቶፑ ከየት ነው የመጣው እዚያ አሁን ቢሮ ውስጥ ከምን ጋር ተነስቶ ነው እናንተ እንድታዩት የተደረገው ?
- ላፕቶፑ እዚያው ነበር
- እዚያው ስትል ምን ጠረቤዛ ላይ ነው የነበረው ?
- አዎ
- ሰይድ እዚያ ላፕቶፑ አጠገብ ነበር ?
- አዎ እዚያው ነበር
- አጠገቡ ላፕቶፑን የከፈተው ማን ነው ?
- እዚያው ያለ አካል
- ፖሊስ ነው የከፈተው አይደል ?
- አዎ
- ምንድን ነው ቀዝቀዝ አትበል እንጂ በደንብ መልስልን
- ማለት
- ማለት ድምፅህን ነው ሌላ ሳይሆን ድምፅህ በተደጋጋሚ እየነገርንህ ነው ግን ድምፅህ አሁን ሊሰማ አልቻለም ከፍ አድርገህ ተናገር
- እሺ
- ላፕቶፑን የከፈተው ፖሊስ ነው አይደል ?
- ፖሊስ ይሁን ባለሙያ ይሁን አላውቅም እዚያው ያለ አካል ነው ብቻ
- ሌላ ሰው ነው የከፈተው ሰይድ ላፕቶፑን አልነካውም አይደል ሲከፈት ?
- አልነካውም አዎ
- ከእዚያ በኋላ ከላፕቶፕ ውስጥ ፋይሎች ወጡ ብለሀል እንዴት ነው የወጡት ምን ማለት ነው ወጡ ማለት ?
- ፕሪንት እየተደረጉ ወጡ ማለት ነው ከእዚያ ከላፕቶፑ ላይ ያሉት ነገሮች ፕሪንት እየተደረጉ ወረቀት ላይ ወጡ
- ፕሪንት ተደረገ አንተ ወረቀቶቹን አይቼአቸዋለሁ ብለሀል ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ወረቀቶቹ የኢሜል ወረቀቶች ናቸው ብለሀል ሁሉንም ወረቀቶች አይተሀቸዋል ሁሉም የኢሜል ወረቀቶች ናቸው ?
- አዎ 30 ሁሉም ላይ ፈርሜባቸዋለሁ
- ወረቀቶቹ ላይ ወረቀቶቹ የኢሜል ወረቀቶች ከሆኑ አንተ ስለኢሜል በደንብ ታውቃለህ አይደለም ?
- አውቃለሁ አዎ
- ታትመው ሲወጡ የላካቸው ማን እንደሆነ በላዩ ላይ ይገለፃል ይገልፃሉ ?
- ያው እኔ ሞር ያየሁት ፁሑፉን ብቻ ነው
- ማን እንደላካቸው አይገልፅም አይደል ወረቀቱ ?
- ከኢሜል እንትን ውስጥ የወጡ መሆናቸው ያስታውቃል ላኪ ምናምን ሊኖራቸው ይችላል እኔ አላየሁትም እኔ ፁሑፉን ብቻ ነው ያየሁት
- ተከሣሽ ወይም ሰይድ ለሰነዶቹ ምላሽ የሰጠባቸው ወረቀቶች የሉም አይደል ወረቀቶቹን አንብበሀቸዋል ይዘቱን አንብቤአለሁ ብለሀል ለኢሜሉ ሰይድ ምላሽ ስለመስጠቱ ወረቀቶቹ አያስረዱም አይደል ?
- ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ፁሑፎች አላየሁኝም
- የሚያስፈልጋቸው ሳይሆን ሰይድ ምላሽ ስለመስጠቱ አላየህም ወይም አልሰጠም አይደል ለሁሉም ወረቀቶች አይተሀቸዋል ስለዚህ ካየኸው ሰይድ ምላሽ መስጠቱን አያሳይም ወረቀቶቹ አይደል ?
- እነዚያ ያየዋቸው ወረቀቶች የተናገርኳቸውን ብቻ ነው አሁን ከእዚያ ውጪ
- ምስክር ጥያቄዬ ግልፅ ነው ሰይድ ምላሽ መስጠቱን ወረቀቶቹ አያሳዩም አይደለም ወይ አይቼአቸዋለሁ ስላልክ ነው የምጠይቅህ
- ጥያቄውን እንቃወማለን
- ቆይ እስቲ ጥያቄው ምንድን ነው ከዚያ ፁሑፎች ኮምፒዩተር ላይ ነው የወጡት ኮምፒዩተር ላይ
- ተቃውሞ አላችሁ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ የተከበረው ፍ/ቤት ዋናው እዚያ ጋር መቃወሚያችን ይሄ ሰው የእኛ ምስክርም /ግልፅ ያልሆነ/ ብርበራ ላይ የነበረ /ግልፅ ያልሆነ/ የብርበራውን ከእዚያ ከላፕቶፕ የወጣው /ግልፅ ያልሆነ/ ቅድም እንደገለፀው ያንን ነው ከእዚያ ውጪ መቼ ቀን ተፅፎ ማን በኢሜል እነሱ የኢሜል ግኝታቸውን ይገልፃል በሚል ጭብጥ አይደለም እኛ ያቀረብነው ወይም ደግሞ እያንዳንዷ እነሱ ወይ ተጠርጣሪ በኢሜል ሲፅፍ ሲላላክ ሲቀበል ያስረዳልናል ብለን ጭብጥ/ግልፅ ያልሆነ/ በብርበራ ላይ ወይም ደግሞ በዕለቱ የታዘበ ለመታዘቡ ደግሞ የፈረመ ነው ከእዚያ ውጪ ባለፈ እንደሙያ ምስክር ዓይነት ጥያቄ ሊቀርብ አይገባም የሚል ነው
- ማለት ግልፅ አይደለም አልተጠየቀም ነው ወይስ የሙያ ምስክር ነው ?
- ምስክራችን የብርበራ በብርበራ ላይ በወቅቱ ይህ ከኢሜል ከእዚህ ይቅርታ ከላፕቶፕ ሲወጣ ያየ እንጂ በእያንዳንዷ ፅሑፍ ዲቴል ገብቶ ኢሜል በእዚህ ቀን ሲመጣ በእዚህ ቀን እሱ ሲልክ መቼ እንደተቀበለ መቼ ነው በሚል ጭብጥ አስይዘን አይደለም ምስክርነት ያስያዝነው ይሄ በብርበራ ላይ ታዛቢ የነበረ ብቻ ነው ስለዚህ ጥያቄው ማጠንጠን ያለበት ታዛቢን እንጂ ውስጥ ስለእያንዳንዷ ስለወጣው ሰነድ ሁሉ አጠቃላይ እውቀት አለው ብለን አይደለም ያመጣነው እና በእዚያ አግባብ እንዲሄድልን ነው
- ምላሽ ስጡበት እስቲ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አሁን ዐቃቤ ሕግ መቃወሚያቸውን ሲያቀርቡ ያላቋረጥኩት ያው የፍ/ቤቱን ብይን አክብሬ ነው ምስክሩ ምን መመለስ እንዳለበት ነው አሁን ዐቃቤ ሕግ መቃወሚያ ብለው አስረድተው የተቀመጡት ተገቢ አይደለም እሱ ግን ያም ሆኖ ምስክሩን ቅድም እሳቸው ሲጠይቁ እና ሲያስመሰክሩ የደብዳቤዎቹን ይዘቱን አስመስክረዋቸዋል እንደውም ምስክሩ ቀስቃሽ የነበሩ ናቸው ወረቀቶቹ ብለው ስለቀስቃሽነታቸው እና ስለይዘታቸው ዝርዝር ነገር መስክረዋል ወረቀቶቹን በዝርዝር አይተው ስለይዘታቸው ከመሰከሩ እዚያው ይዘቱ ላይ ስላዩት ነገር ነው አሁን እየጠየኳቸው ያለሁት ስለዚህ ጥያቄዬ አግባብ ነው
- ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል የግራ ቀኞችሁ ክርክር ከእዚህ በላይ የተገለፀው ሲሆን ፍ/ቤቱ ይሄ ጉዳይ ተነስቷል አልተነሳም የሚል ነው ቀደም ሲል ወረቀቶቹን አይቼአቸዋለሁ አንብቤአቸዋለሁ የሚል ነገር ገልፆዋል ምስክሩ ስለዚህ ይዘቶቹን ሙሉ በሙሉ አስታወሰ

http://ethcriminalawnetwork.com/

አላስታወሰ የሚያስታውሰውን መመለስ የማያስታውሰውን አላስታውስም የማለት መብት ስላለው የጠበቃ ጥያቄ ተገቢ ነው ቀጥሉ ብለናል

- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ወረቀቱን ስላየኸው የኢሜል ወረቀቶች ናቸው ያልካቸውን ተከሣሽ ወይም ሰይድ ለወረቀቶቹ ምላሽ አልሰጣቸውም አይደለም ወይ ወረቀቶቹ ምላሽ መስጠቱን አያሳዩም አይደለም ወይ ነው ?
- እስቲ ጥያቄውን ግልፅ ለማድረግ እኛ እንደገባን እዚያ ወረቀት ላይ ለማን የተፃፈ ነው ማን ያፃፈው ነው አስተውለኸው ከሆነ አይተኸው ከሆነ ? እንደዚያ ነው ጥያቄው ?
- እሱ ብቻ ሳይሆን ለማን ነው የሚለው ሳይሆን ሰይድ ምላሽ
- ከእዚያ በኋላ ማን ፃፈው ሲባል ለማን ይባላል ከእዚያ ምላሽ ነው ምላሽ አይደለም
- እሺ እንደውም በፍ/ቤቱ አስተካክዬ አመሰግናለሁ ወረቀቶቹ ያየሀቸው ወረቶች ለሰይድ ተብለው በአድራሻ የተላኩ ናቸው ?
- እነሱ ላይ አሁን እኔ ወረቀቶቹ ከእሱ ላፕቶፕ ውስጥ መውጣታቸውን እና ወረቀቶቹ ደግሞ አውት ይሁን ወደ ውጪ የሚተላለፉ መሆናቸውን ብቻ ነው እንዳለ የእዚህ የነበሩ ፁሑፎች የሚተላለፉ መተላለፍ ያለባቸው ፁሑፎች ናቸው
- አይ ጥያቄው ግልፅ እኮ ነው ምናልባት ላኪ እና ተቀባይ ይታወቃል ወይ ከኢሜል የወጣ መሆኑን አውቃለሁ ብለሀል አይደል ከኢሜል የወጣ ወረቀት ነው አስቀድሞ ሴቭ የተደረገ ቢሆንም ከኢሜል የወጣ ወረቀት ነው ብለሀል እና ማን እንደላከ ማን ተቀባይ እንደሆነ ይታወቃል ወይ እሱን አይተሀል ወይ ነው ጥያቄው ካየህ ያየኸውን ካላየህ ደግሞ እሱን መግለፅ ?
- እሱን አላስታውስም
- አድራሻው ለሰይድ ተብሎ የተላከ መሆኑን አታስታውስም ?
- ያው አላስታውስም ብሏል ሌላ ጥያቄ ግልፅ ነው
- ለደብዳቤዎቹ ላይ ሰይድ ማለት ካየሀቸው ኢንተርኔት ወረቀቶች ላይ ሰይድ ላኪ ሆኖ የተገለፀበት ወረቀት አይተሀል ?
- በቃ ይሄ አልቋል እኮ
- አይ ተቀባዩን ነው የጠየኩት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በቃ 2ቱን ጠየቅን እኮ እኛ ማን እንደላከ ለማን እንደተላከ ይታወቃል ወይ ሲባል እሱን አላየሁትም አላውቅም አለ ይሄ አልቋል በእዚሁ
- በኢንተርኔት በትክክል አውቃለሁ አጠቃቀም ብለኸኛል ቅድም በአጠቃላይ ለብዙ ዌብ ፔጆች ላይ እነዚህ ማህበራዊ ድህረ ገፆች በሚሉት ላይ ፖስት የሚደረግ ነገር ፖስት የሚባል ነገር አለ እኔ አማርኛ እውቀቱን ስላላወኩት ነው ፖስት የሚደረጉት ነገሮች እንዴት ፖስት እንደሚደረጉ ታውቃለህ ?
- አላውቅም
- ወረቀቶቹ ይዘታቸው ቀስቃሽ ነው ብለሀል ምን ማለት ነው ቀስቃሽ ማለት ?
- ቀስቃሽ ማለት
- እኮ ቅድም የሆነ የጥሪ ደብዳቤዎች
- የሚያነሳሳ ማለት ነው
- የቅስቀሳ ደብዳቤዎች እኮ የሚነሳሳው ነገር ቅድም የጠቃቀስካቸው ነገሮች አሉ ?
- አዎ
- እነሱን ለማለት ነው እስቲ ግልፅ አድርግላቸው ?
- አሁን አንደኛው የማስታውሰ ነገር አወሊያ ላይ ይሄንን ያህል ሙስሊም እንትኖች እያለቁ ነው እና ወደ እዚያ ሁላችንም እንነሳ ማለት ያው ማነሳሳት መቀስቀስ ማለት ነው
- እንነሳ የሚል ቃል አለው በትክክል አይተሀል ?
- እንሂድ የሚል ቃል አለው አዎ
- እንሂድ ?
- አዎ
- እንሂድን ነው ቅስቀሳ ነው ያልከው ?
- ያው ይሄ ለመመዘን ያው በቂ ነው ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- ስለምን ጉዳይ ነው ቅስቀሳ የሚያደርጉ ናቸው ስትል ስለ ምን ጉዳይ ነው ቅስቀሳው በምን ጉዳይ ላይ ነው ቅስቀሳ የሚያደርጉት የተረዳኸው አንተ ?
- እስቲ ምናልባት አወሊያ ላይ እያለቁ ነው የሚል አለው ይላል እና ወደ እዚያ እንሂድ ነው እኛ የተረዳነው ድረስ ይሄንን መሠረት አድርጋችሁ

FCLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላው ደግሞ ወረቀቱ አለ ሞር አፍ ፕሮሲጀሩ ነው የሚፈለገው ከእዚያ ወረቀቱ ስላለ
- እሺ
- አመሰግናለሁ ፡የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር የኮምፒዩተር አጠቃቀም እውቀትህ ምን ያህል ነው ማለት ኮምፒዩተር በደንብ ትጠቀማለህ የኮምፒዩተር አጠቃቀም እውቀትህ ምን ያህል ነው እስቲ ለፍ/ቤቱ አስረዳልን ኮምፒዩተር በደንብ ትጠቀማለህ ?
- ያው በደንብም ባይሆን ከሞላ ጎደል እጠቀማለሁ
- ኢሜልስ ኢንተርኔት ኢሜል በደንብ ትጠቀማለህ ?
- እጠቀማለሁ አዎ
- ታውቃለህ በደንብ ማለት ነው ?
- አዎ
- ኢሜል ውስጥ ያሉ ባህሪያትን ልታስረዳን ትችላለህ ?
- ስለኢሜል ቆይ ስለኢሜል አረዲ መልሷል በቃ ስለዚህ መንደርደሪያ ወደ እሱ ስለሆነ አያስፈልግም
- ሰይድ ላፕቶፕ ተብሎ ተነገረህ እንጂ የእሱ ስለመሆኑ እርግጠኛ የምታውቀው ነገር የለም አይደል የሰይድ ላፕቶፕ ነው ተብሎ ተነገረህ እንጂ የእሱ ስለመሆኑ የምታውቀው ነገር የለም ከተነገረህ ውጪ ?
- አዎ ተነግሮኛል እሱም የእኔ ነው ብሎኛል
- ከቤቱ ሲያዝ አላየህም ?
- ከቤቱ ሲያዝ አላየሁም
- አሁን እነዚህ ያልካቸው ነገሮች አንድ ሰው ወደ እዚያ ላፕቶፕ ላይ ማስቀመጥ አይችልም ?
- ተቃውሞ አለ የተከበረው ፍ/ቤት
- ግልፅ ነው ማንም ሰው ያስቀምጣል ሴቭ ያደርጋል ግልፅ ነው እዚያ አሁን እሱ እያለ ያለው ሴቭ የተደረገው በፊት ከኢሜል የመጣ ይመስለኛል ሴቭ የተደረገ ነው የወጣ ነው የሚለው እሱ ግልፅ ነው ማንም ሴቭ ያደርጋል አሁን እሱ ያየው እዚያ ደርሶ ይሄ ኮምፒዩተር የእሱ ነው እኔም የእኔ ነው ሲል ሰምቼአለሁ አለ ከእዚህ በኋላ ያለውን ጥያቄ ነው የምትጠይቁት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያየኸው ዳውን ሎድ የተደረገ ነው ያልከው ፋይል ወርድ ፋይል ነበር በምን ፎርማት የተቀመጠ ፋይል ነበር ኮምፒዩተር አውቃለሁ ስላልክ ሲከፈት በምን ፋይል ነው የተከፈተው ?
- አላስታውስም እሱን
- ወርድ ፋይል ታውቃለህ ?
- ያው አላስታውሰውም እያሉ ስለሆነ
- ኮምፒዩተር ላይ ወርድ ፋይል ታውቃለህ ?
- አለቀ ጠበቃ አላስታውስም ብለዋል እና ወርድ ይሁን ፒዲኤፍ ሌላ አላውቅም አላስታውስም ብለዋል
- ሰይድ ያ ኮምፒዩተር የእኔ ነው ሲል
- ተጠይቋል ይሄ
- የተከበረው ፍ/ቤት አንድ ጥያቄ እኮ ቢጠየቅም በተለያየ ሁኔታ ሊጠየቅ ይችላል አሁን ጥያቄዬን ስላልጨረስኩ የተጠየቀ ጥያቄ
- ስለኮምፒዩተር ባለቤትነት ተጠይቋል ሌላ የምትጠይቀው ከእዚያ ውጪ ካለ
- ከእዚያ ውጪ ነው
- ከእዚያ ውጪ ከሆነ መጠየቅ ትችላለህ
- አዎ
- ኮምፒዩተር /ግልፅ ያልሆነ/ እሱ በሚያውቀው መልሷል
- እዚያ የሰይድ ኮምፒዩተር የተባለው ኮምፒዩተር ምን ዓይነት ኮምፒዩተር ነው ?
- ላፕቶፕ ነው
- እኮ ላፕቶፕ ምን ዓይነት ላፕቶፕ ለምሳሌ ከለሩ ምን ዓይነት ነው?
- ከለሩ ጥቁር መሰለኝ ጠቆር ያለ ነው
- ማርኩስ ምን ዓይነት ማርክ ነው ?
- ማርኳን አላስታውሳትም
- አንተ ከኮምፒዩተሩ ላይ እዚያው እስክሪኑ ላይ ነው ያየኸው ወይስ ፕሪንት የተደረገ ነው የሚያሳየው ?
- 2ቱም ላይ ነው ያየሁት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፕሪንት የተደረገም እስከሪኑ ላይም ?
- አዎ
- ቅሰቀሳ እና ማነሳሳት ያልካቸው ነገሮች በእንግሊዘኛ ነው የተፃፉት ?
- በአማርኛ ናቸው
- በአማርኛ ነው የተፃፉት ?
- በአማርኛ ናቸው
- እንትኑ አሁን እነዚህ ፁሑፎች ከእሱ ኢሜል ይሁን አይሁን በምን ልታውቅ ትችላለህ ?
- ከእሱ መሆኑን ያው እሱም አብሮን ሲፈርም ነበር የእሱ ኮምፒዩተር መሆኑን
- እኮ የፈረመው ጫና ተደርጎበት ይሁን ነፃ ሆኖ ይሁን ወይ አንተ ከመምጣትህ በፊት የተደረገበት ጫና ስለመኖሩ የምታውቀው ነገር የለም አይደል አንተ ከመምጣህት በፊት አሁን የሚፈረም ነገር አለ ፈርም ተብሎ ጫና ተደርጎበት ይሁን አይሁን የምታውቀው ነገር የለም ?
- እሱን አላውቅም
- በወቅቱ ወረቀቶቹ ከኮምፒዩተሩ ፕሪንት ተደርገው ከወጡ በኋላ ከኮምፒዩተሩ ፕሪንት ወይም ታትመው የወጡት ወረቀቶች ዝርዝር አልተመዘገበም አይደል ?
- አልገባኝም
- ዝርዝራቸው ከወቀረት ውስጥ የወጡት ዝርዝሮች እናንተ እንድትፈርሙባቸው ከመደረጉ ውጪ ዝርዝራቸው በቃለ ጉባኤ መልክ ወይም በአንድ ወረቀት ላይ ቀናቸው ዓይነታቸው ተለይቶ ዝርዝር አልተፃፈም አይደል ?
- ከእዚያ የወጡት እቃዎች በሙሉ ተፈራርመንባቸው ነው የተለያየነው
- ዝርዝር አልተፃፈም ወረቀቱ ላይ ከመፈረም ውጪ ዝርዝር ላይ አልፈረምክም አንተ አይደል?
- የምታስታውሰው ከሆነ ግለፀው ?
- አላስታውስም
- ያ የወጣው ዓይነት ከኮምፒዩተሩ የወጣው የወረቀቱ ዓይነት የብቻ በዝርዝር ተቀምጧል አልተቀመጠም እሱላይማ ፈመናል ብለህ ቅድም ገልፀሀል እሱን የምታስታውሰው ከሆነ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አላስታውሰውም
- አታስታውሰውም?
- ሙሉ እንትኖቹ ላይ መፈረማችን ከእዚያ ዶክመንቶች ላይ መፈረማችን ብቻ ነው የማስታውሰው
- ሌላ ጥያቄ
- መጀመሪያ የፈረመው ሰይድ ነው ወይስ እናንተ ናችሁ ?
- እሱ ነው መጀመሪያ የፈረመው
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ
- ምናልባት የ 28ኛን
- የ 28ኛ ተከሣሽ ጠበቃ አህመድ ጀማል መስቀለኛ ጥያቄ እንደሚከተለው አቀርባለሁ አጭር ነው ወ/ሮ ሀቢባ መኪና የተባለው ውስጥ የተገኙ መፅሐፎች ነበሩ ብለዋል እነዚህ መፅሐፎች የሙስሊም መፅሐፍ ቅዱሶች ናቸው ነው ያሉን ቅድም በአረብኛ የተፃፉት መፀሐፎች ?
- ይመስለኛል ነው ያልኩት /ግልፅ ያልሆነ/
- ሌሎች ደግሞ ቁሳቁሶች መያዛቸውን የገለፁልን አለ ከእነዚህ ቁሳቁሶች ውስጥ ትልልቅ ብረት ድስቶች ይገኛሉ ትልልቅ ብረት ድስቶች አሉ ?
- አዎ አሉ
- የወጥ ጭልፋዎች አሉ ?
- አሉ አዎ
- ጎድጓዳ ሣህኖች ?
- አሉ አዎ
- ሌላ ቅድም የጠቀሱት ወደ 200 የሚጠጉ ሳህኖች ያሏቸው የምግብ ማቅረቢያ ሳህኖች ናቸው ?
- መመገቢያ ሳህኖች
- መመገቢያ ሳህኖች እነዚህ ቁሳቁሶቹ ለምን ዓላማ እንደዋሉ ያውቃሉ እርሶ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አላውቅም
- የማን ንብረት እንደሆኑስ ያውቃሉ ?
- ያው ከእሳቸው መኪና ውስጥ እንደወጣ ብቻ ነው የማውቀው
- እንዴት መኪና ውስጥ እንደገባስ ያውቃሉ መኪና ውስጥ እንዴት እንደገባ አያውቁም አይደል ?
- መኪና ውስጥ እንዴት እንደገባ አላውቅም ግን ከየት እንደመጣ ያው ቃለጉባኤው ላይ ቅድም ለማስቀመጥ እንደሞከርኩት
- እመጣለሁ ወደ እሱ 50 ሺህ ብርም አብሮ ተይዟል ብለዋል አይተናል ብለዋል ?
- አዎ አይተናል
- ይህ 50 ሺህ ብር ለምን ዓላማ እንደሆነ አያውቁም አይደል ?
- አላውቅም አዎ
- ከሳውዲ ኃይማኖት ክፍል ወጥቶ የመጣ ነው ይላል ቃለጉባኤው ብለዋል ?
- አዎ
- ከሳውዲ ሲሉ ከሳውዲ አረቢያ ሀገር ማለትዎ ነው ወይስ ከሳውዲ አረቢያ ኢትዮጵያ ከሚገኘው የሳውዲያ አረቢያ ኢምባሲ ማለትዎ ነው ?
- ኢምባሲው ማለቴ ነው
- ተከሣሽ ወ/ሮ ሀቢባ በእዚያች እናንተ በነበራችሁበት ሰዓት ምን ተጠየቁ ?
- በቃ እነዚህ እቃዎች ተፈተሹ ቃለ ጉባኤው
- ቃለ ጉባኤው ላይ ካለው ቃል ውጪ ሌላ የተጠየቁት ነገር አለ ?
- የሰማሁት ነገር የለም
- ጨርሻለሁ
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ
- ድጋሚ የለንም
- በፍ/ቤቱ ጥያቄ
- የሆነ መኪና ውስጥ ስትደርስ በ 28ኛ ተከሣሽ ማለት ነው ምንም የተጠየቀችው ነገር የለም ምን ሰማችሁ ምን ስትጠየቅ ሰማችሁ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምንም አልሰማሁኝም
- እኮ ከሳውዲ አረቢያ የመጣ መሆኑን ማን ነገረህ አንተ ከሳውዲአረቢያ ኢምባሲ ማለት ነው ኢምባሲ ነው ያልከን እዚያ የመጣ መሆኑን ማን ነው የነገረህ ?
- መጨረሻ ላይ ቃለጉባኤው ተፃፈ እና ቃለጉባኤው ተነበበልን እሳቸው ባሉበት
- እኮ ቅድም እኮ ከኢምባሲው የመጣ ነው ገንዘቡ ከእዚያ የተላከ ነው እሱን እንዴት ነው ያወከው አንተ ?
- ገንዘቡ ከእዚያ የተላከ ነው
- መፅሐፉ ለምሳሌ መፅሐፉ እዚያ የመጣ ነው ብለህል እንዴት አወክ እሱን ?
- ከእዚያ የመጣ መሆኑን ከቃለጉባው ተፅፏል
- ቃለ ጉባኤው ማን ነው የሚፅፍ የነበረው ቃለ ጉባኤውን ?
- እዚያ የነበረ መርማሪ
- መርማሪ ነው የሚፅፍ የነበረው ስለዚህ ተከሣሽዋ ምን ትል ነበር ያኔ ?
- ምንም አትልም ቃለጉባኤው ተነበበ ቃለጉባኤው ላይ ትክክል መሆኑን አመነች ፈረመች
- እኮ ስታምን ምንድን ነው ያለችው ?
- አዎ ትክክል ነው ብላ ፈረመች
- ማለት ምኑ ነው ትክክል አሁን ለምሳሌ አገላለፅ
- ቃለጉባኤው
- ምን ለማለት ፈልጌ መሰለህ አሁን ለምሳሌ ስምምነት እንዲህ መግለፅ አለ አይደል እራስ በመወዝወዝ ወይም በመግለፅ ምን ምን ነው የገለፀችው ነገር ?
- ቃለጉባኤውን መጀመሪያ መርማሪው ፃፈው ከፃፈው በኋላ አነበበልን ያግባባናል አለ ያው እንደዚህ በውል እንደዚህ በትክክለኛ እንደዚህ እንደዚህ ትበል በቃል ትበል አላስታውስም እሱን ብቻ እዚያ ነገር ላይ ተስማምታ ፈረመች ከእዚያ እኛም ቀጥለን ፈረምን ከሰር
- እናመሰግናለን ጨርሰዋል 8 ከሩብ ላይ እንገናኛለን እዚሁ ችሎት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጠዋት የነበረው ችሎት ከሰዓት በኋላም ቀጥሏል ዳኞች አልተለወጡም ዐቃቤ ሕግ ጠዋት ከነበሩት ፣ ተጨማሪ ዐቃቤ ሕግ ቀርቧል
- አቶ ቴዎድሮስ ባህሩ ቀርቧል
- ተከሣሾች የቀረ ተከሣሽ የለም ተከሣሾች ሁሉም ቀርበዋል ጠበቆች የ 28ኛ ተከሣሽ ጠበቃ አልቀረቡም የሌሎች ተከሣሾች ጠበቆች ጠዋት የነበሩት ቀርበዋል አንድ ተጨማሪ ጠበቃ ቀርቧል ስምዎ ማን ነው ?
- አዲስ መሐመድ ቀርቤአለሁ
- አዲስ መሐመድ ከሰዓት በኋላ ቀርበዋል ሌሎቹ አልቀረቡም በእዚሁ እንቀጥላለን ዐቃቤ ሕግ ምስክር አቅርቡ
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- በፍ/ቤቱ 37ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር በዐቃቤ ሕግ ክስ ላይ ተራ ቁጥር 90 ላይ ተጠቅሰው የቀረቡት እሺ ምስክር እንኳን ደህና መጡ አሁን ለእርሶ ማለት ለምስክሮች ደህንነት ሲባል ኣድራሻዎን እና ሙሉ ስምዎን አይጠቅሱም ስለዚህ የመጀመሪያ ስምዎን ብቻ ይጠቅሳሉ ስምዎ ማን ነው ?
- ማሞ ክፍሌ
- ማሞ ?
- አዎ
- ለምንድን ነው እዚህ የመጡት ?
- ለምስክርነት
- እነ ማን በተከሰሱበት ነው ?
- ያው በስም እከሌ ብዬ መጥቀስ አልችልም በሐምሌ 14/2004 ከቀኑ በግምት 8 ሰዓት አካባቢ
- የተደረገ ድርጊት እሱን ለማስረዳት ነው ?
- አዎ እሱን ለማስረዳት
- ካሉ በኋላ በዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ
- ዋና ጣጅን የመጣሁት ለምስክርነት ነውብለዋል ምንድን ነው የሚመሰክሩት ?

2037 464

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ የምሠሣበትረው ያው ሐምሌ 14 ከቀኑ 8 ሰዓት
- ስንት ዓ.ም ነው ?
- 2004 ከቀኑ 8 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ልዩ ቦታው አንዋር መስኪድ የተባለው አካባቢ ረብሻ ተነስቶ በእዚያ ጉዳይ ነው የመጣሁ
- በእነ ማን ነው ረብሻው የተነሳው ?
- ያው በሙስሊሞች ዙሪያ ነው
- መስኪዱ ውስጥ መስኪዱ አካባቢ ነው ወይስ መስኪዱ ውስጥ እንዴት ነበር እስቲ ቦታው?
- ያው ከውስጥም ጩኸት ይጮሀሉ ከውጪም ጩኸት ነበረ
- ምን እያሉ ነበር የሚጮሁት ?
- አላህ ዋክበር እያሉ ነበር የሚጮሁት
- ሌላስ የሚናገሩት ነገር ነበር ?
- አይ ሌላ ጩኸት ብቻ ነው ያው በጣም በርካት ሕዝብ ስለነበረ መለየት ማወቅ አይቻልም ጩኸቱ ብዙ ነበረ
- ግማሾቹ መስኪድ ውስጥ ሆነው ግማሾቹ ከፊሎቹ ደግሞ ከመስኪድ ውጪ ሆነው ነው ?
- አዎ በቃ አካባቢው
- ለምን ሄዱ እርሶ እዚያ አካባቢ ለምን ሄዱ እዚያ አካባቢ ?
- ለስራ
- ምን ነበር ስራ ?
- ያው የወንጀል መከላከል ስራ
- ምን ስለተፈጠረ ነው ወንጀል ሊከላከሉ እዚያ አካባቢ የሄዱት ?
- ያው ረብሻ ስለተፈጠረ አካባቢው ላይ ያው ሱቆች ተዘግተዋል በርካታ ብዙ ሰዎች ተጎድተዋል እኔ እራሴ ተመትቼአለሁ ሌሎች አባሎችም ተመተዋል
- በቦታው ላይ ረብሻ ነበር ብለዋል እንደዚሁም የተመቱ ሰዎች አሉ ብለዋል ማን ነው እንዚያን ሰው ያን ረብሻ ያስነሳው እና እነዚህ ሰዎች የተመቱት በማን ነው ?
- ያው እዚያ አካባቢ ላይ በሚጮሁት ሰዎች ነው የተመቱትም የተመታነው

2034

465

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ባሉኝ በእዚህ መስኪድ ውስጥ ባሉ ሰዎች ማለት ነው ?
- መስኪድ ውስጥ እና ውጪ ባሉት ሰዎች ማለት ነው
- በምንድን ነው የሚማቱት?
- ያው በተለያየ ድንጋይ ነው አብዛኛው ድንጋይ ነው የሚወረወረው እንጨት ምናምን የተለያየ ነገር ነው
- ወደ ማን ነው የሚወረወረው ?
- በቃ ወደ ፀጥታ አስከባሪው ነው
- ሌላስ ?
- ያው ሌላ ንብረቶችም ተጎድተዋል በእዚያን ሰዓት አሁን መኪና ምናምን ተሰባብረዋል በሚወረወረው ድንጋይ
- በእዚያን ቀን እርሶ በነበሩ ሰዓት የተጎዳ መኪና አለ ?
- አዎ
- ምን ዓይነት መኪና ነው የተጎዳው ?
- አንድ ታርጋውን መያዝ አልቻልኩም የቤት መኪና ቀይ ቅብ የቤት መኪና በጣም ተጎድታለች
- በእዚሁ በተመሳሳይ በተወረወረ ድንጋይ ?
- ትክክል አዎ
- ምን እያሉ ነው ድንጋዩን የሚወረውሩት ?
- አላህ ክበር ነው የሚሉት
- ሌሎችም ተመተዋል እኔም ላይ እኔም ተመትቼአለሁ ብለዋል እርሶም በተመሳሳይ ነው የተመቱት ?
- አዎ እኔም በድንጋይ እዚህ መታጠፊያ /ግልፅ ያልሆነ/
- ምኖት ላይ ?
- እዚህ መታጠፊያዬ ላይ
- ግራ ቀኝ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቀኜ
- የምን መታጠቢያ ?
- የእጇ ማለት ነው
- የቀኝ እጅም ላይ ማለት ?
- አዎ
- ምንድን ነው የሚባል እሱ ?
- ኩርማ
- በምንድን ነው የተመቱት እርሶ ?
- በድንጋይ ነው
- ምን ጉዳት ደረሰቦት ከእዚህ ምት በኋላ ?
- ያው ቁስለት የተወሰነ ስሜት ነው እንጂ በጣም ስብር ምናምን የለኝም
- ታከመው ታል ?
- አልታከምኩኝም
- ከእዚያስ ምን ዓይነት እንቅስቃሴ ነበር እንዴት ቆመ ወይስ ቀጠለ እንዴት ሆነ ከእዚያ ?
- ከእዚያ በኋላ አሸናፊ /ግልፅ ያልሆነ/ አንድ አባላችን በከፍተኛ ሁኔታ ተጎድቶ ስለነበረ እሱን አንስተን ወደ ሕክምና ይዘን ሄድን
- ምኑ ላይ ነበር የተመታው እሱስ ?
- ጨንቅላቱ ላይ ነው
- በምንድን ነው የተመታው ?
- እንግዲህ ያው ረብሻው በጣም እንትን ስለነበር በድንጋይ ነው የተመታሁት ነው ያለው በወቅቱ ለእኛ ሲነግረን
- እሱን ይዛችሁ ወደ ሕክምና ቦታ ሄዳችሁ ?
- አዎ
- መቼ የተጀመረ ነው ይሄ ረብሻ ?
- ማለት

2036 4/67

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከመቼ የጀመረ ነው እዚያ መስኪድ አካባቢ ከመቼ የጀመረ እንዴት የጀመረ ነው ?
- እንግዲህ በእዚያ በፊትም ረብሾች ነበሩ ግን በዋነኝነት እኔ ያጋጠመኝ የነበርኩት በእዚያን ዕለት ብቻ ነው በሌላም ቀኑን አላስታውስም ማታ ላይ እንደዚሁ ረብሻ እንደነበረ ነግረውኛል ሌሎች የተጎዱም አባሎች ሲያወሩ ሰምቼአለሁ እዚያ አካባቢ ላይ ጩኸቱ በርካታ ጊዜ ብዙ ጊዜ ያው አላህክበር የሚለው ጩኸት ብዙ ጊዜ አርብ አርብ ከፀሎት በኋላ ይፈፀም እንደነበረ አውቃለሁ
- ከአርብ ዕለት በኋላ ?
- አዎ
- ሌላስ ምን የሚይዙት ነገር አለ ከአሁን በድንጋይ በዱላ ብለዋል ምን ይዘው ነው አላህ ክበር አላህ ክበር ሲሉ የነበሩት ምን ይዘው ነው ?
- በእዚያን ጊዜ ያው የተለየ ነገር እኔ ምንም አላየሁኝም
- እሺ ከሰሙት ወይም ካዩት ይሄ ረብሻ በማን ነበር የሚቀሰቀስ የነበረው ?
- ያው እዚያ አካባቢ ባሉት ሙስሊም ሕብረተሰቦች ነበር
- እዚያ አካባቢ ባሉት ?
- አዎ
- ዋና ጥያቄ አበቃን የተከበረው ፍ/ቤት
- የተከሣሾች ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ
- እሺ ምስክር አንዋር መስኪድ አካባቢ ሐምሌ 14 እና ከእዚያ በፊት ረብሻ ነበረ ብለው አስረድተዋል እና ረብሻ ያሉትም እርሶ እርሶ አላህ ክበር እየተባለ ይጮህል አላህክበር ማለት እረብሻ ነው እንዴ ከሰላት በኋላ አላህ ክበር ያለ ሰው ረበሸ ማለት ነው መስኪድ ውስጥ አላህ ክበር ስላሉ ነው ረብሸዋል ያሉት ?
- በእዚያን ጊዜ ያው ከእዚያ በፊት የነበረው እንደዚያ ዓይነት ስሜት ነበረ በእዚያን ዕለት ግን አላህክበር እየተባለ ያው ድንጋይ መወራወር መማታት
- ከእዚያ በፊት የነበረው አላህ ክበር ብቻ ነው ሲባል የነበረው ?
- ያው እንደዚያ ከፀሎት በኋላ እንደዚያ ዓይነት ድምፅ ያሰሙ ነበር በከፍተኛ ሁኔታ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የእዚያን ጊዜ ሐምሌ 14 እንደዚያ ሊሆን የቻለው ምናልባት በሩ ስለተዘጋባቸው እና መውጣት ስላልቻሉ ?
- በር አልተዘጋጀም በእዚያን ጊዜ ያው ሕብረተሰቡ ማለት ውጪም አለ ውስጥም ጩኸቱ በከፍተኛ ሁኔታ ነበር ሲሰማ የነበረው
- አስለቃሽ ጭስ የየተኮሰውንስ ያስታውሳሉ ?
- እኔ አላየሁኝም በእዚያን ወቅት አልነበርኩም ምክንያቱም የተመታው ልጅ በጣም ለሕይወቱ አስጊ ስለነበረ እሱን በመኪና አንስተን ወደ ጤና ጣቢያ ይዘን ሄድን
- ፖሊስ በአካባቢው የነበረውን ሁሉ ሲደበድብ የነበረ መሆኑንስ ያስታውሳሉ ?
- ማንም እኔ ዲሞክራት ፖሊስ ነው እዚያ ቦታ ላይ የነበረው በሕግ አምላክ ከማለት ውጪ ምንም ዓይነት ፀረ ዲሞክራሲ የተጠቀመ አባል አልነበረም
- በሕግ አምላክ ብሎ ነው ያስቆመው ማለት ነው እርሶ ረብሻ ያሉትን ነገር ?
- ያው ሲመታ እንዴት እንደቆመ መጨረሻውን ባለውቅም የተመታውን ልጅ ይዤ ወደ ሆስፒታል ሂጃለሁ ወደ ጤና ጣቢያ ማለት ነው እኔ
- ስለዚህ እሱን ሐምሌ 14 የአንዋር መስኪድ በር ክፍት ነበረ ማለት ነው ማንም የዘጋው ሰው የለም ?
- እንግዲህ መጨረሻ ላይ እኔ ከሄድኩ በኋላ ተዘግቶ ሊሆን ይችላል
- አይ እርሶ እሱን እርሶ መቼ ደረሱ እሺ ያሰረዱ ለፍ/ቤቱ መቼ ደረሱ ወደ አንዋር መስኪድ አካባቢ መቼ ደረሱ ?
- እዚያው አካባቢ ነበርኩኝ
- እዚያው አካባቢ ነበሩ ?
- አዎ
- ሲሄዱስ ከተጀመረ ለምሳሌ 8 ሰዓት ጀምረው ነው ይሄ ነገር ብለው አስረድተዋል እና የሄዱትስ እሱን ጉዳት ደረሰበት ያሉት ሰው ሲሄዱ ስንት ሰዓት ነበረ ?
- ቢያንስ የ 10 /15 ደቂቃ ልዩነት ቢኖር ነው ረብሻው ተጀመሮ ልጁ ተመቶ እኛ
- እኮ እርሶ ለ 15 ደቂቃ ብቻ ነው የነበሩት ማለት ነው
- ግምት ነው የእኔ የራሴ ግምት ማለት ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ በግምት ለሁን እርሶ እዚያ የነበሩት ለ 10 ወይም ለ 15 ደቂቃ ብቻ ነው ማለት ነው ?
- አዎ
- ለ 10 እና 15 ደቂቃ ውስጥ ነው ይሄ ሁሉ ነገር ሲፈፀም ያዩት ?
- አዎ እዚያው ነበርኩ በእዚያን ወቅት ያው ልጁ ሲመታ እሱን ይዘን ሄድን
- ከመስኪድ ውስጥ የነበረው ሰው ሰላማዊ ከሆናችሁ ውጡ እየተባለ በማይክሮፎን ጥሪ ሲደረግ ሰምተዋል ?
- አይ አልሰማሁም
- ማለት ከውጪ ያሉ የፀጥታ አካላት ውጪ ሆነው ሰላማዊ ከሆናችሁ ውጡ ተብሎ ሲጠራ አልሰሙም ?
- በእዚያን ወቅት ያው ልጁን ይዤ እኔ ወደ ጤና ጣቢያ ሄጄ በኋላ ነው የመጣሁት ምክንያቱም ልጁን እያሳከምን ነበረ ከሌሎች ጓደኞቼ ጋር ሆነን
- ተጎዳ ያሉት መኪና የቱ ጋር ነው የተጎዳው ተጎዳ ያሉት መኪና የቱ አካባቢ ላይ ነው የተጎዳው የት ጋር የቆመ ነው የሚሄድ መኪና ነበረ ምን ዓይነት መኪና ?
- እየሄደ የነበረ መኪና ነው
- እየሄደ የነበረ ?
- አዎ
- ፖሊስ ያ ነገር እየተከናወነ መኪኖች ያልፉ ነበር ማለት ነው ?
- አይ ያው ረብሻው ሲነሳ በእዚያ አካባቢ የሚመጡት መኪኖች እያለፉ ነበረ
- እና ረብሻ ከመነሳቱ በፊት ነው ማለት ነው መኪናው ጉዳት ያደረሰው ?
- አይደለም በእዚያው ምክንያቱም ወዴት መሄድም አይችሉማ በእዚያን ሰዓት ከብዷቸዋል የግድ ከረብሻው ውስጥ መውጣት ነው መሀል ላይ ነው የነበሩት ከእዚያ ተመታ እንደውም በ 2 ድንጋይ ነው የኋላ መስታወቱ እንዳለ ተመታ ከጎን በኩል ተመታ አስታውሳለሁ
- ማን እንደመታው አይተዋል እንዴ ?
- ማን እንደመታው ያው በጣም በርካታ ሰው ነው የሚወረውሪ ያለው
- አላዩም ?
- እከሌ ብሎ መለየት አይቻልም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የት አካባቢ ነው ትክክለኛው ቦታው መኪናው የተመታው የት አካባቢ ነው ?
- አንዋር መስኪድ
- ግቢ ውስጥ ነው ?
- ንግድ ባንኩ ፊት ለፊት ላይ
- አንዋር መስኪድ ንግድ ባንክ ፊት ለፊት ?
- አዎ
- ንግድ ባንክ ማለት የትኛው ንግድ ባንክ ?
- ከአንዋር መስኪድ ጎን ያለው ማለት ነው
- በጀርባ በኩል ማለት ነው ?
- በጎን በፊት ለፊት እዚህ ከራጉኤል ሰር ማለት ነው
- የአንዋር መስኪድ በሮችን ያውቋቸዋል አይደል ?
- አዎ አውቃቸዋለሁ
- ዋናውን በር ያውቁታል ?
- እንግዲህ ዋናው በር በታች በኩል ያለው ይሁን በእዚህ በኩል ያለው ዞሮ ንግድ ባንኩ
- ንግድ ባንኩ እሺ እኔ ላመላክቶት ወደ ጣና በሚሄድው መንገድ በኩል ማለት ነው ?
- ትክክል በእዚያ በኩል ነው
- ከጣና በኩል እየወረወሩ የሚመጡ ሰዎች አልነበሩም ድንጋይ የሚወረውሩ ሰዎች አልነበሩም ወይም ረብሻ የሚፈፅሙ ሰዎች አልነበሩም ከጣና በኩል?
- ከየአቅጣጫው ነው የሚወረወረው የነበረው
- እኮ ከጣናም ነበረ ማለት ነው ?
- አዎ ከእያቅጣጫው ይወረወር ነበር
- ከጣና ቢሆንስ ከጣና በተወረወረው ድንጋይ ሊሆን ይችላል አይደል የተመታው መኪናው?
- እንግዲህ አሁን ከየት በተወረወረው ድንጋይ
- አይለዩም እርሶ ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- መለየት አልቸልም በእዚያን ረብሻ ላይ ሲመታ ብቻ ካልሆነ በስተቀር እኔም እራሴ የተመታሁትን ከየት አቅጣጫ እንደተወረወረ ሲመታኝ ነው ያየሁት
- እርሶ ተመተውም ስራ ላይ ነበሩ ማለት ነው ?
- ያው ልጁን ይዤ ወደ እኔ በጣም ጉዳቴ መጠነኛ ስለነበረ የተጎዳውን ልጅ በመኪና ይዘን ወደ ጤና ጣቢያ ሄድን
- የተጎው ልጅ ያሉት ምኑን ነው የተጎዳው ?
- ጭንቅላቱን ነው
- ተጎድቶ መቼ ስራ ተመለሰ ?
- እንግዲህ በጣም ለብዙ ጊዜ ሆስፒታል ተኝቶ እንደነበር ነው የማውቀው
- እሱን ማን እንደጎዳው አያውቁም እርሶ ?
- አዎ ማን እንደመታው ያው እዚያው
- ከጣናው በኩልም ሊሆን ይችላል እሱም የተመታው ?
- እዚያው በር ላይ ነዋ ንግድ ባንኩ ፊት ለፊት ነው ጣና እና ንግድ ባንኩ በጣም ይራራቃል
- ትክክል ግን አሁን ከጣና በኩል ድንጋይ የሚወረውሩ ሰዎች እንደነበሩ አረጋግጠውልናል ከጣና በኩል
- እስቲ ነኛ እየተደጋገመ ነው 2ኛ እነኚህ ሰው እኔንም የመታኝን አላውቀውም ሲወረወር ነበር ከሌላ አቅጣጫም ይመጣ ነበረ አቅጣጫውን በትክክል መለየት አልቸልም እያሉ ነው ከእዚህ በላይ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ለምን ይመስሎታል እዚያ ሰው ተሰብስቦ ይሄ ነገር የተፈፀመው ?
- እንግዲህ እኔ ውስጣዊ ችግራቸውን አይ ዶኖ አላውቅም ምናልባት
- ችግር አለባቸው ማለት
- እዚያ ቦታ ላይ የነበረው መወርወር ወዘተ በጣም በርካታ ስለነበረ እንግዲህ ችግራቸው ምን እንደሆነ ምን ፍለጋ እንደሆነ አይ ዶኖ እኔ የማውቀው ነገር የለም
- አሁን የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ከሐምሌ 14 በፊት እዚያው አላህ ክበር እያለ ይሰባሰብ ነበረ ድምፅ ያሰማ ነበረ እነዚህስ ስብሰቦች ለምን ነበሩ ?
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምንድን ነው
- ጠበቃው በራሳቸው ያርሙታል ብለን ስላሰብን ነው መጀመሪያ የመጀመሪያውን ጥያቄ ያለፍነው አሁን ምን ይመስሎታል ተብሎ ኤክስፐርት እንትን ነው እየተጠየቁ ያሉት የግል አስተያየታቸው
- እሱ ተመልሷል ሌላ ካላችሁ
- ይሄኛውም ለምንድን ነው ለምን ይመስሎታል ነው እየተባሉ ያሉት ስለሆነም ምክንያታቸውን ሊያውቁበት የሚችሉት የግል አስተያየታቸውን ሊመሰክሩ አልመጡም በቀጥታ የነበረውን ድርጊት ነው ያዩትን ነው እየመሰከሩ ያሉት ስለሆነም ጥያቄው ያለአግባብ ነው ውድቅ እንዲሆን ነው
- ሰጡበት
- ጥያቄውን አልፈነዋል የተከበረው ፍ/ቤት አልፈነዋል ጥያቄው
- ዋና ሣጅን ቅድም ከቀኑ 8 ሰዓት በሙስሊሞች ዙሪያ ረብሻ ተነሳ ብለዋል እርሶ ከመጀመሪያው ጀምሮ እዚያ እንደነበሩ ነው የገለፁት ምንድን ነው የቀሰቀሰው ረብሻው እንዴት ተነሳ ?
- ያው ጩኸት ነው
- ማለት መነሻው ምንድን ነው ምን ገፋው ሰው እርሶ ሲመጡ መጀመሪያ ከመጀመሪያው ከነበሩ እየጮኸ ነው የደረሱት ወይስ እርሶ ከመጡ በኋላ ነው ጩኸት የተጀመረው ?
- ያው እዚያው እየጮሁ ነበር እኛ ምድብ ቦታችን የተለያየ ነው በእዚያው በሬዲዮ ወደ መስኪድ አካባቢ ችግር አለ የሚል ጥሪ ሲደርስ ወደ እዚያ ቦታ ላይ ስንሄድ ይጮሀሉ ወደ እዚያው ድንጋይ መወርወር ተጀመረ
- እናንተ ስርደርሱ ነው መወርወር የጀመሩት ?
- አይ ያው ጀምረው ነው እኛ የደረስነው
- በማን ላይ ይወረውሩ ነበር ማለት እናንተ ረብሻ መኖሩን ስማችሁ ደረሳችሁ በማን ላይ እናንተ ስትደርሱ በማን ላይ ነበር ?
- ያው በፀጥታ ኃይሉ ላይ ነው
- ከእናንተ በፊት ሌላ ነበረ ነው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዚያ አካባቢ ላይ አዎ አቡ
- የትኛው አሁን የፀጥታ ኃይል ሲሉ ብዙ ነው የትኛው የፀጥታ ኃይል ?
- የፖሊስ ሰራዊት ማለት ነው
- ማለት የአዲስ አበባ አለ የፌዴራል አለ ?
- የአዲስ አበባ ፖሊስ
- በአዲስ አበባ ?
- አዎ የክፍለ ከተማ ማለት ነው
- ዋና ሣጅን ረብሻውን ማን እንዳስነሳ ያውቃሉ ለይተው በግልፅ ?
- ረብሻውን እንግዲህ ያው ሙስሊሙ ሕብረተሰብ እንዳነሳው ነው እኔ የምረዳው በራሴ እንጂ እከሌ ብዬ በግለሰብ ደረጃ ልጠቅሰው የምችለው ሰው የለኝም
- ሙስሊሙ ሕብረሰብ መሆኑን በምን አወቁ ?
- ያው እየጮኸ ድንጋይ ሲወረውር ስለነበር
- ግምት ነው አይደል ?
- አይ በአይኔ ያየሁትን ነው ግምት ሳይሆን
- እኮ ሁሉንም ሕዝብ አንተ ሙስሊም ነህ አይደለህም ብለው ጠይቀዋል አረጋግጠዋል ?
- እንግዲህ ሙስሊም ውስጥ የሚገባው ከሙስሊም ውጪ መስኪድ አካባቢ ሌላ ሰው ይገባ አይመስለኝም አይፈቀድምም
- ቅድም ረብሻው ያስታውሱ እንደሆነ ከመስኪድም ውጪ ነው ብለው ነበር እና ከመስኪድም ውጪ ያለ ሰው ሁሉ ሙስሊም ነው ወይ ይሄንን አረጋግጠዋል ወይ ነው ወይስ ግምት ነው ?
- እንግዲህ እዚያ አካባቢ ላይ አንድ አሁን የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ነው ብለን በአብዛኛው ልንለይ የምንችለው የተለያየ በአለባበስ ቆብ በማድረግ ወዘተ በእዚህ መለየት ይቻላል እዚያ አካባቢ ላይ ያለውን ሕብረተሰብ
- ስለዚህ ይሄንን ረብሻ ያስነሳው ሁሉ እንደዚህ ዓይነት ሰው ነበር ነው የሚሉኝ ?
- አዎ
- ትዕዛዝስ የሰጠ አካል አለ ይሄ ስለመሆኑ ይሄ እንዲደረግ ያውቃሉ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማለት
- ትዕዛዝ እንዲረብሹ እንዲህ ያለ ሰው አለ ያውቃሉ ?
- አይ አላውቅም ማን ትዕዛዝ ይስጥ በራሳቸው ጊዜ ነው ከሚመለከተው አካል ትዕዛዝ ይስጣቸው እሱን የማውቀው ነገር የለም
- ድንጋይ ሁሉም ሰው ነበር የሚወረውረው ?
- ያው ሁሉም ነው ግማሹ ነው ብሎ መፈረጅ አይቻልም
- ያዩትን
- እሱን ቆይ ጠበቃ እሱ ያው ድንጋይ እንዴት እንደሚወረወር ተጠይቆ መልሰዋል ቀደም ሲል በየአቅጣጫው ይወረወር እንደነበር አሁን እሱን ማለት
- ፖሊስሳ ስላደረገው ነገር ኣያውቁም በእዚያ ወቅት ላይ የነበረው የአዲስ አበባ ፖሊስ ብቻ ነበር እዚያ ቦታ ፌዴራል አልነበረም ?
- እኔ በነበርኩበት ሰዓት ያው አዲስ አበባ ፖሊስ
- ተጠይቋል ስለ ፖሊስ
- በእዚህ ሰዓት ሕዝቡ ምን ይል ነበር ሁሉም የኢድማው ደጋፊ ነበር ይሄ ረብሻ የሚሉት ሁሉም አላህ ክበር ነበር የሚለው ወይስ የሚቃወም ነበር አትበሉ የሚል ነበር ?
- አይ አትበሉ ብሎ እዚያ አካባቢ ላይ አሁን ስለረብሻው ሁሉም በእዚያን ሰዓት ሌላውም ሕብረሰብ ሸሽት ነበር ከድንጋዩ ለመሸሽ ነው እንጂ አሁን አትረብሹ ብሎ ወደ እዚያ ቦታ ላይ የሚገባ እከሌ ብሎ ማስቀመጥ አይቻልም ከባድ ስለነበር ረብሻው ማለት ነው
- ምን ያህል ይሆናል ሕዝቡ ?
- በቁጥር ይሄንን ያህል ብሎ ማስቀመጥ ይከብደኛል እኔ
- በግምት ወይስ አይችሉም ?
- አይ በግምት በጣም በርካታ ሕዝብ ነው የመርካቶ እዚያ አካባቢ ላይ በተለይ አሁን ያለን ሰው ይሄንን ያህል ብሎ በቁጥር ማስቀመጥ ከባድ ነው
- ቅድም ጁሉማ ጁሉማ ሁሌ አላክ ክበር ይባላል ብለው ነበር ያኔ አሁን ይሄ ነገር ቀርቷል ?
- አሁን እኔ እዚያ አካባቢ ላይ አይደለሁም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አንድ አራት ወር አካባቢ ከእዚያ ለቅቄአለሁ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስከ 4 ወር ጊዜስ እስከ[illegible]ሩበት ጊዜ ተቋርጧል ይሄ ነገር ?
- አልተቋረጠም አንድ ሁለት ቀን የተለያየ እንደነጭ ጨርቅ ነገር ይዘው እንደዚህ የማውለበለብ ነገሮችን ሁሉ ነበሩ
- ምን ነበር ነጭ ጨርቁ ላይ ያለው አይተውታል ?
- አይ በቃ እኔ ያው በርቀት ሆኜ ነው የነበርኩት እላዩ ላይ ምን ይኑር ምን ይኑር
- ነጩ ጨርቅሳ የምንድን ነው የምን ምልክት ነው ያው እርሶ ፖሊስ ስለሆኑ ያውቃሉ ብዬ አስባለሁ ?
- እኔ የምን ምልክት እንደሆነ እንግዲህ ያው ኃይማኖታቸውን በጥሩ ይሁን በመጥፎ ሊገልፁበት የሚችሉት አይደኖ እኔ የማውቀው ነገር የለኝም የምን መገለጫ እንደሆነ አላውቀውም
- ቅድም አሸናፊን ይዤ ሄድኩ ብለው ነበር እና የት ጤና ጣቢያ ይዘው ሄዱ ?
- የፖሊስ ክሊኒክ አለ መሣለሚያ አካባቢ እዚያ ነው ይዘን የሄድነው
- መሣለሚያ ?
- አዎ
- ጉዳት የደረባት ምን ዓይነት ጉዳት ነው የደረሰባት ታክማ ዳነች ምን ሆነች ?
- ወንድ ነው
- ምን ሆነ እሺ ይቅርታ ?
- ጭንቅላቱ ላይ የተመታው
- ምን ሆነ ከእዚያ ?
- ሆስፒታል እንደተኛ አውቃለሁ
- ከእዚያ ወዲህ ስላለው ነገር አያውቁም ?
- ያው
- እሱም በተደጋጋሚ ተጠይቋል እኮ
- ለማጥራት ብዬ ነው ላጥራው ብዬ ነው ቅድም የተጠየቀውን
- እኮ ያልጠራውን ወይ መርጠ መጠየቅ ነው እንጂ በሙሉ እንዲህ ከሆነ እኮ ሰንት ዓመትም አንጨርስም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምስክር ረብሻውን ካስነሱት ውስጥ የታሰሩ ነበሩ አይደል ?
- በእዚያን ሰዓት ያው ቅድም አስቀምጬዋለሁ ረብሻው ሳይበርድ ነው ልጅቱ ተጎድቶ ስለበረ ልጅቱን ይዤ ወደ ሆስፒታል ሄጃለሁ ከሹፌር ከሌሎች አካላቶች ጋር አንስተን መኪና ላይ ጭነን ማን ይታሰር ማን ይታሰር የታሰረ ምናምን መኖሩን በእዚያን ሰዓት አላውቅም በጣም ቆይቼ ነው ወደ ቦታው የተመለስኩት እኔ
- የስራ አካባቢዬ እዚያ ነው ስላሉ ደግሞ ይከታተላሉ ብለንም ስለምናምን ከእዚያ በኋላ ተይዞ በፍርድ ሂደት ወይም ለፍ/ቤት የቀረበ ሰው ነበር ?
- የማውቀው ነገር የለም
- ሲባል አሁን ለምሳሌ እርሶ እንግዲህ የሚያውቁት ነገር ከሌለ ቢያንስ የሰሙት ነገር አለ ለፍርድ ቀርቦ እንደዚህ ዓይነት ቅጣት ተሰጠው የተባለ የሰሙት ነገር አለ ?
- ምንም የሰማሁት ነገር የለም ያው ለእዚህ በእዚህ ጉዳይ ለምስክርነት እዚህ ቦታ ላይ መምጣቴ እና እነኚህ እዚህ ያሉ አካሎች መቼ ይያዙ በእዚያን ጊዜ ይያዙ ከእዚያ ወዲህ ይያዙ የማውቀው ነገር የለኝም በእዚህ ምክንያት መምጣቴን ነው የማውቀው
- ምስክር ቅድም የተጎደው አሸናፊ ነው ብለው ነበር አሁን ደግሞ ልጅቷ የሚል ነገር አምጥተዋል ምን ማለት ነው ይሄ ?
- ወንድ ነው ብለው አስተካክለዋል በመሀል
- ልጅቷ ያሉት እሱን ነው ?
- ወንድ ነው አይደል ያሉት ?
- ወንድ ነው እኔ ሳልሆን ከእዚያ ነው ልጅቷ የሚል ነገር የተሰነዘረው እንጂ እኔ ወንድ እንደሆነ አሸናፊ አይነቴ ይባላል ኮንስታብል አሸናፊ አይነቴ
- ወንድ ነው የተጎዳው አይደል ?
- ወንድ ነው
- ጨርሰናል
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ ቀጥሉ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ዋና ሣጅን በአካባቢው ላይ የነበሩት ከውጪም ከውስጥም የነበሩት ሙስሊሞች ናቸው ይሄንንም የለየሁት በአለባበሳቸው ነው ብለዋል ከጣና አካባቢ ድንጋይ እየወረወሩ ሲመጡ የነበሩት ሰዎችስ ምን ዓይነት ሰዎች ነበሩ ?
- ያው በአለባበሳቸው ቀሚስ የለበሱ ናቸው በብዛት
- ስለዚህ ተመሳሳይ
- እና ቆብ ያደረጉ ሰዎች ናቸው አዎ
- ከጣና የሚመጡት ከሌላ ቦታ የሚመጡት ተመሳሳይ ?
- አዎ ተመሳሳይነት እምነት ያላቸው
- ተመሳሳይ እምነት ወይም የእዚሁ እምነት ተከታዮች ናቸው ?
- ትክክል
- ሌላው ቦታው ላይ የነበሯችሁት የአዲስ አበባ ፖሊስ የክፍለ ከተማው ፖሊስ ብቻ ነበር አይደል ?
- አዎ በእዚያን
- የክፍለ ከተማ ፖሊስ አስለቃሽ ጋዝ ወይም ጭሽ ትጠቀማላችሁ እንዴ ?
- አንጠቀምም እኛ በጣቢያ ደረጃ ነው ያለነው እንደዚያ ዓይነት ነገር አንጠቀምም
- ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት
- በፍ/ቤቱ ጥያቄ
- ይሄ ጭንቅላቱን ተመታ ያልከው ልጅ አሁን የት ነው ያለው ?
- አሁን እኔ ከእዚያ አንድ 4 ወር ሆኖኛል ከለቀኩኝ
- እስከ መቼ ሕክምናው እስከ መቼ እንደተከታተለ ታውቃለህ ?
- አይ በውል እስከመቼ ብዬ ማስመጥ አልችልም
- ጉዳቱ ከፍተኛ ነበር ?
- አዎ በጣም ከፍተኛ ነበር
- ምን ማለት ነው እንደዚያ ስትል ?
- ይሄ ጭንቅላቱ በጣም ተጎድቶ ነበር

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን መጎዳት ማለት ወይ ተሰብሯል ወይ ምን ሆኗል ?
- በጣም ተሰንጥቆ ነበር ከዛም ተሰንጥቆ ወድቋል ከወደቀበት ነው አንስተን እኮ መኪና ላይ የጫነው በጣም ከፍተኛ ጉዳት
- ምን ደም ይፈሳል ወይ እገለጠት ነው ?
- በጣም ይፈስ ነበረ ደሙ እንደውም ልብሱ እራሱ የፖሊስ ልብስ መሆኑ እራሱ አይለይም ነበር በእዚያን ጊዜ ከደሙ መብዛት የተነሳ ማለት ነው
- እናመሰግናለን ጨርሰሀል
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ
- ምስክር እንኳን ደህና መጡ አሁን ለምስክሮች ደህንነት ሲባል አድራሻዎን እና ሙሉ ስምዎን አይገልፁም የመጀመሪያ ስምዎን ብቻ ይገልፃሉ በፍ/ቤቱ 38ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር በዐቃቤ ሕግ ክስ ላይ የተጠቀሱት ተራ ቁጥር 10 ላይ የተጠቀሱት የመጀመሪያ ስምዎ ማን ነው የራስዎን የመጀመሪያ ስም የራስዎን ስም ብቻ የአባትዎን አይናገሩም የአያትዎን አይናገሩም ?
- ሀይረዲን
- ለምንድን ነው እዚህ የመጡት ?
- ለምስክርነት
- ማን በተከሰሰበት ነው በእነ ማን ላይ ነው ?
- እኔ መስኪድ አስተናጋጅ ነኝ /ግልፅ ያልሆነ/ አስተናጋጅ ነኝ መስኪድ ቁርአን አስተናጋጅ ነኝ
- በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?
- እኔ ሰዎቹን አላውቃቸውም አያውቁኝም
- ምንድን ነው የሚያስረዱት ?
- እኔ ቁርአን አስተናጋጅ ነኝ በ 4 እገባለሁ መስኪዱ በ 4 ይከፈታል ለመክፈት ስመጣ ቅዳሜ
- ቆይ ዝርዝሩን አይደለም በአጠቃላይ ምን ሊያስረዱ ነው የመጡት ?
- እኔ የደረሰብኝ /ግልፅ ያልሆነ/ ለማስረዳት ነው የመጣሁት
- በዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ
- ምስክር መቼ የተፈፀመ ድርጊት ለማስረዳት ነው እዚህ የመጡት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ክስ የተመሰረተው
- መቼ የተፈፀመ ድርጊት ነው ማስረዳት ነው እዚህ የመጡት ?
- ሐምሌ 7 እና 8
- ስንት ዓ.ም ነው ?
- 2004
- እስቲ ከሐምሌ 7ቱ እንጀምር እና ስንት ሰዓት አካባቢ ነው ?
- ከጠዋቱ 4 ሰዓት አካባቢ ነው
- የት አካባቢ ነው ቦታው ?
- መስኪድ አንዋር
- የት ነው ምን ክፍለ ከተማ ነው የሚገኘው አንዋር መስኪድ ?
- ይታወቃል ሌላ አንዋር መስኪድ አለ እንዴ
- የለም ያው አናውቅም እኛ ሊኖር ይችላል ግን ምን ክፍለ ከተማ የሚለውን
- ክፍለ ከተማው አዲስ ከተማ ነው
- አዲስ ከተማ ?
- አዎ
- ለምን ሄዱ እዚህ መስኪድ ?
- እኔ የመስኪድ ሠራተኛ ነኝ
- ሠራተኛ ኖት ?
- አዎ
- ምን የተለየ ነገር አጋጠሞት በእዚያን ቀን ወደ ስራዎ ሲሄዱ ?
- ለስራዬ መጥቼ በራፍ ስደርስ የጠዐ ቡችላ አትገባም ተብዬ ተከለከልኩ ያኔ ተደናብሬ ሸሸሁ
- የቱ ጋር ሲደርሱ ነው መግቢያው ላይ ሲደርሱ ነው ?
- መዝግያው ላይ ስደርስ
- ማን ነው እንደዚህ ያሉት የመስኪዱ ጥበቃዎች ናቸው ወይስ ሌሎች ሰዎች ?
- አይ ተደናብሬ ሸሸሁኝ እኔ እከሌ ብዬ አልልም መስኪዱ ከባድ ጫጫታ ነበር

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተረጋግጠው የእኔን ጥያቄ ተቀብሎኝ በቦታው ላይ ሁል ጊዜ የስራ ቦታዎ ነው አይደል ?
- የስራ መደቤ ያው እዚያው ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- ሁል ጊዜ ሲገቡ ዘበኛ አለው እንዴ መስኪዱ ?
- አለው አዎ
- እነዚያን ጥበቃዎች ያወጣኋቸል መደበኛ ጥበቃዎችን ?
- ጥበቃዎች ጓደኞቼ ናቸው
- ጓደኞችዎ ናቸው ?
- የእዚያን ዕለት የሉም ጥበቃዎቹ የሉም
- የሉም ለምንድን ነው ያልነበሩት በቦታው ጥበቃዎች ?
- በወቅቱ የሉም ያለው መስኪዱን ጠቅላላ የወረረው ሌላ ሰው ነው ወሮት የነበረው
- መስኪዱ በሌላ ሰዎች ተወሮ ነበር ?
- በሌላ ሰው እጅ ነበር ያኔ ጊዜን ቀን
- ጥበቃዎቹ ?
- የሉም በወቅቱ
- ለምን በቦታው እንዳልነበሩ ያውቃሉ ምክንያቱን ?
- በቃ ግርግር ስላለ የሉም እነሱ እኔም ደግሞ ሰላም ነው ብዬ ልከፍት ስገባ ነው አትገባም የጠሀ ብችላ ብዬ ተገፍቼ የወጣሁት
- አሁን ጠሀ ያሏቸው ማን ናቸው ?
- ሰውዬውን አላውቀውም በወቅቱ ለእራሴ ፈርቼ ስለሸሸሁኝ
- አይ
- ለይቼም አላውቃቸውም
- ጠሀ የተባሉት ሰው ማን ናቸው ?
- የመስኪዱ ኢማም ናቸው
- የአንዋር መስኪድ ኢማም ?
- የአንዋር መስኪድ ኢማም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከእሳቸው ጋር አያይዞ ነው ክብሮትን በሚነካ ሰድብ እንትን ?
- ፈራሁኝ ለሕይወቴ ፈርቼ ሸሽቼአለሁ
- ማን ነው የገፈተሮት አያውቋቸውም ?
- ለይቼ አላውቀውም
- ምን ይባል ነበር መስኪዱ በእዚያን ወቅት ግርግር የሚሉት ነገር ምንድን ነው ?
- ግርግር ነበር ምን እንደሚባል እኔ ፈርቼ ሸሽቼአለሁ
- ፈርተው ምንድን ነው የፈሩት ለምን ፈሩ ?
- ተገፈተርኩኝ አትገባም የጠሀ ቡሽላ ተብዬ ተገፈተርኩኝ ፈርቼ ሸሽሁኝ
- እርሶ ብቻ ነው የሚገፈተሩት ወይስ ሌሎች ሰዎች ?
- ብቻ በወቅቱ ብቻ ነው የተገፈተርኩት
- ብቻዎን ነው የሄዱት ?
- አዎ
- ከእዚያ በኋላስ ተመልሰው አልመጡም ?
- እሁድ ተመልሼ መጣሁ አሁንም በድጋሚ በ 4 ሰዓት
- እሁድ ዕለት ?
- አዎ
- የእዚያን ቀን
- ሐምሌ 8 ማለት ነው
- የእዚያን ቀን እስቲ ሐምሌ 7 እንጨርስ እና
- ሐምሌ 7 ቅዳሜ ነው በድጋሚ እሁድ መጣሁኝ
- እስቲ ይኸውሎት አንዴ የእኔን ጥያቄ ያስጨርሱ ቀስ እያሉ ተረጋግተው መመለስ ይችላል እራስዎትን ያረጋጉ እና የእዚያን ቀን ቅዳሜ ዕለት የስራ ቦታዎ ነው እና አትገቡም ሲባሉ ለምን ተናገሩ ሄደው ?
- ለማንም አልተናገርኩም ስገፈተር የጠሀ ቡችላ ብለው ሲወሩብኝ
- ዝም ብሎ ነበር የነበረው መስኪድ ውስጥ የነበረው ሰው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ውስጥ አልገባሁም ማን እንደነበረ ጫጫታ ከባድ ጫጫታ ነበር
- ምንድን ነበር የሚለው ጫጫታው የሚሉት ነገር ?
- ጫጫታውን በደንብ አላዳመጥኩም ስገፈተር ሸሸቼ ወደ ቤቴ ሄጃለሁ
- እሺ በማግስቱ እሁድ መጡ ?
- በማግስቱ እሁድ እንደዚያው በ 4 ሰዓት መጣሁ ልከፍት ስመጣ አሁንም የጠሀ ቡችላ ተባልኩኝ ተገፈተርኩኝ ሸሸሁኝ
- ያውቁታል ማለት ነው እነዚህን ሰዎች ?
- አላውቃቸውም
- እነሱ ግን ያውቆታል ለምን እንደዚያ አሉ ?
- አላውቃቸውም ማንናቸውም ለእኔ ደግሞ አዲስ ነው ይሄ ነገር
- ሌላስ በአካባቢው ምን ተከሰተ በአካባቢው ሌላ ምን ተከሰተ የእዚያን ቀን ?
- ሰኞ ተመልሼ መጣሁኝ ሰኞ ስመጣ ስላም ነው ገብቼ እንደሌላ ጊዜ ቁርአን ከፍቼ አሰናድቼአለሁ
- ሰኞ ሲመጡ ?
- ሰላም ነው
- ሰላም ነበረ ?
- አዎ
- ዋና ጥያቄ አበቃን
- የተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ
- መስቀለኛ ጥያቄ የለንም የተከበረው ፍ/ቤት
- መስቀለኛ ጥያቄ ያልተነሳ በመሆኑ ድጋሚ ጥያቄ አይኖርም በፍ/ቤቱም የተነሳ ጥያቄ የለም እናመሰግናለን መመለስ ይችላሉ
- ጨርሰዋል መሄድ ይችላሉ
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በፍ/ቤቱ 39ኛ ተራ ቁጥር ላይ በዐቃቤ ሕግ ክስ 46 ላይ የተጠቀሱት ምስክር ለምስክሮች ደህንነት ሲባል የመጀመሪያ ስምዎን ብቻ ነው የሚናገሩ አድራሻዎን የአባት ስም የአያት ስም አይናገሩም የመጀመሪያ ስምዎ ማን ይባላል ?
- ከድር
- ከድር ነው አይደል ያሉት ?
- ከድር አደም
- ለምንድን ነው እዚህ የመጡት ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ለምስክርነት ?
- አዎ
- በማን ነው የሚመሰክሩት ?
- እኔ አላውቃቸውም
- ምንድን ነው ልታስረዱ የመጣችሁ ምን ሊመሰክሩ ነው ?
- እኔ አላህ ክበር /ግልፅ ያልሆነ/ በቀኑ 5 ሰዓት ተኩል መጣሁ አላህክበር ሲል ሰማሁ እና ቢቃ ሄድኩ አልገባሁም
- የት ?
- ከግቢው ውጪ
- የት ግቢ ?
- አንዋር መስኪድ
- ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ
- መቼ ነበር ቀኑ ?
- ቅዳሜ ቀን
- ምን ወር የወሩ ስንተኛ ቀን እንደሆነ ያስታውሳሉ ?
- አላስታውስም
- መቼ ነው አምና ነው ዘንድሮ ነው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ዘንድሮ በቃ ዓመቱ ነው ማለት ነው
- ጊዜው ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ አያውቁትም ?
- አላውቀውም አዎ
- ወር ቀን መቁጠር ይችላሉ እንዴ ?
- አልችልም
- አይችሉም ?
- አዎ
- የት ቦታ ስለተፈፀመ ድርጊት ነው የሚያስረዱት ?
- የተፈፀመው አላህክበር ብቻ ሲል ነው
- ቦታው የት ነው ቦታው ?
- አንዋር መስኪድ
- አንዋር መስኪድ ?
- አዎ
- እሺ ለምን ነበር የሄዱት እርሶ ?
- እኔ ካዳሚ ነበርኩኝ ልሰራ ስሄድ ሞልቷል
- ካዳሚ ምን ማለት ነው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ ቁርአን /ግልፅ ያልሆነ/
- ይሄንን ሰራ የት ነው የሚሰሩት ?
- አንዋር
- አንዋር መስኪድ ውስጥ ለስራ ነበር የሄዱት የእዚያን ቀን ?
- አዎ
- ለስራ ሲሄዱ ምን አጋጠሞት ?
- በቃ ሰው ሞልቶ ነበር ግቢው ሁሉ ሙሉ ነበር ያው ረመዳን ዖም ስለሆነ ተመልሼ ሄድኩኝ ደክሞኝ
- ለስራ ነበር የሄዱት ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ሰሩ እራዴ ስራዎትን ?
- ኣይ አልሰራሁም ተመለስኩ
- ለምንድን ነው ያልሰሩት ?
- ሞልቷላ መስኪዱ
- ለምን ነብር የሞላው ?
- እኔ /ግልፅ ያልሆነ/
- ምን ይባል ነበር ?
- አላህክበር ብቻ ነው የሰማሁት
- አላህክበር ማለት እንዴት ነበር ሲሉ የነበሩት ?
- አላህክበር ነው
- ሁሉም ሰው ነው የሚለው ?
- አዎ
- በጩኸት ነበር ሲሉ የነበረው ?
- ጩኸት አልሰማሁም ቁጭ ብለው በእርጋታ ነው
- በእርጋታ ነበር ?
- አዎ
- ስንት ሰዓት አካባቢ ነበር ያሉት ?
- 5 ተኩል ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- 5 ሰዓት ተኩል ?
- አዎ
- ሁል ጊዜ በእዚያን ሰዓት ቅዳሜ ቀን ሰው ለምን ነበር ያ ሰው የተሰበሰበው የእዚያን ቀን የተሰበሰበው ?
- ያው እኔ አላወኩም ለሰላት መስሎኛል በሌላ ጊዜ /ግልፅ ያልሆነ/ አየሁ ተመለስኩ
- ለሰላት 5 ሰዓት ላይ ቅዳሜ ቀን ሰው በእዚያን ሰዓት ይሰባሰባል ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሁልጊዜ 5 ሰዓት 5 ተኩል ይገባል ለሰላት
- ለሰላት ?
- እዎ
- ሁል ጊዜ እንደዚያ ይባላል እንዴ አላህክበር ሁል ጊዜ ይባል ነበር ?
- አይባልም አልተባለም ለእዚያን ቀን ነው
- የእዚያን ቀን ነበር ሲባል የነበረው ?
- አዎ
- የተለየ ሰዎች በመስኪዱ የመጡ ሰዎች ነበሩ ሌላ ?
- ያው ሁሉም /ግልፅ ያልሆነ/ ልዩ ሰው አላየንም
- እስከ ስንት ሰዓት ቆዩ እርሶ በመስኪዱ ?
- እኔ ወዲያው ሄድኩኝ 5 ተኩል መጣሁ ሄድኩ
- ለምን ስራዎትን አልሰሩም ምን ከለከሎት ሰው መብዛቱ ምን ከለከሎት ?
- አዎ ሰው በዛ ሰው /ግልፅ ያልሆነ/
- ሁሌ የሚገባ ሰው ነው ካሉ ሌላጊዜም እንደዚህ ሰው ሲበዛ ይመለሳሉ እንዴ ?
- አይ የእዚያን ቀን አጋጣሚ ሰው ሲበዛ ሄድኩ
- ለምን ነበር እንደዚያ አጋጣሚ ያሉት በምን አጋጣሚ ነው ?
- እኔ እንጃ በምን እንደሆነ ሰው ተሰብስቦ
- ከእዚያ በኋላስ አልሰሙም ምክንያቱን ከእዚያ በኋላ አልሰሙም ?
- በቃ አላህክበር ነው በቃ የሰማሁት ሌላ ነገር
- ይሄንን ነው የሰሙት ?
- አዎ
- ምክንያቱን እንደዚያ የተሰበሰቡበት እና አላህክበር እያሉ ከእዚያ በፊት አይባልም ብለው ነበር የእዚያን ቀን ያንን ሲሉ የነበሩት ለምን እንደሆነ ?
- አላወኩም
- ከእዚያ በኋላ ምክንያቱን አያውቁም ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ይበቃናል ዋና ጥያቄ የተከበረው ፍ/ቤት
- የተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ
- አቶ ከድር ወቅቱ ይሄ አሁን ያሉት ሐምሌ 7 ያሉት ረመዳን ነበር አይደል?
- አዎ
- በረመዳን ረመዳን ማለት የሙስሊሞች ፆም ማለት ነው ?
- አዎ
- በእዚያን ጊዜ አንዋር መስኪድ ሰው በጊዜ ነው አይደል የሚገባው ሁሉም ቀን ?
- አዎ በረመዳን በጊዜ
- ረመዳን ስለሆነ ቦታ ስለሚጠብ ሰው ?
- አዎ በጊዜ ይገባል
- ሁል ጊዜ በጊዜ ይገባል ይሞላል ?
- አዎ
- ግቢው ሰላት አካባቢ ሲደርስ 5 ተኩል ሲሆን መስኪዱን ሞልቶ ግቢውም ይሞላል አይደል?
- አዎ
- ሐምሌ 7 እና 8 ከእዚህ የተለየ ነገር ያዩት የለም ?
- አላየሁም
- እንደሌላው ጊዜ ?
- እኔ 8 አልመጣሁም
- ቆይ ያልተጠየቀውን እየጨመሩ ነው
- ስለዚህ ሐምሌ 7 ከሌላው ጊዜ የተለየ ያዩት ነገር የለም ?
- አዎ ረመዳን ስለሆነ ያው ጥቅጥቅ ብሎ ነው የሚገባው አንጥፎ ነው ቁጭ የሚሉ
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የለንም የተከበረው ፍ/ቤት
- ምስክር እናመሰግናለን ጨርሰዋል ይመለሱ
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ
- በ40ኛ ተራ ቁጥር በዐቃቤ ሕግ ክስ ላይ ተራ ቁጥር 5 ላይ የተጠቀሱ ምስክር እሺ ምስክር ለምስክሮች ደህንነት ሲባል አድራሻዎን የአባትዎን ስም የአያትዎን ስም አይገልፁም የመጀመሪያ ስምዎን ብዎ ይገልፃሉ ?
- አብዱራህማን ሁሴን
- ለምንድን ነው እዚህ የመጡት ?
- እዚህ የመጣሁት እኔ /ግልፅ ያልሆነ/ ተረኛ ነበርኩኝ መስኪድ አንዋር ማለት ነው በእዚያ /ግልፅ ያልሆነ/ ላይ የነበረውን የወቅቱን ሁኔታ ቃል እንድሰጥ ለመስጠት ነው
- በማን ላይ በግለሰብ ላይ የሚመሰክሩት አለ ?
- አዎ
- በማን ላይ ነው ?
- እንግዲህ /ግልፅ ያልሆነ/ ያው እኔ ስመጣ መስኪዱ ሙሉ ነበር በር ገባሁኝ ሁኔታውን አላወኩም
- እኮ ማን ነው ?
- እንትና አቡበከር አህመድ
- አቡበከር ?
- አህመድ
- ሌላ ?
- አህመዲን ጀባል ፣ያሲን ኑሩ ፣ካሚል ሸምሱ
- በእነዚህ ነው ያውቋቸዋል እነዚህን ሰዎች ?
- አላውቃቸውም
- ስማቸውን እንዴት አወቁ ?
- ስማቸውን በእስፒከር ወንድሜ /ግልፅ ያልሆነ/ የሰማዋቸው አላውቃቸውም
- በእዚያ ነው የያዙት በእዚያ ነው የሰሙት ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ካሉ በኋላ በዐቃቤ ሕግ ምስክር ጥያቄ ይቀጥሉ
- ምስክር መቼ የተፈፀመ ድርጊት ሊመሰክሩ ነው የመጡት ?
- እኔ የመጣሁት በ7
- ምን 7 የትኛው ወር ? ሰንተኛ ወር ?
- ሐምሌ
- ሐምሌ ወር በየትኛው ዓ.ም የተፈፀመ ድርጊት ነው መቼ ነው ዓ.ም ?
- ዓ.ም 2004
- የት አካባቢ የተፈፀመ ድርጊትን ነው ?
- አንዋር መስኪድ
- አንዋር መስኪድ ?
- አዎ
- በእዚህ ቀን እርሶ እዚያ ለምን ሄዱ ?
- የጥበቃ ሠራተኛ ስለሆንኩ
- በእዚያው በተቋም በመስኪዱ ማለት ነው ?
- አዎ
- ምን የተለየ ነገር ተከሰተ የእዚያን ቀን ?
- የተከሰተ /ግልፅ ያልሆነ/ ምንም ነገር የለም ያው እንትን ወንድሞቻችን አወሊያ ያሉት ወንድሞቻችን እንትን ጉዳት የደረሰባቸው ጉዳት አድራሾቹ ሕግ ፊት ይቅረቡልን እንደነና ደግሞ ምርጫ በመስኪድ እንዲሆን የመጅሊስ አመራሮች እንዲወርዱልን እንደነና ደግሞ የአሀባሽ አስተምሮት በግድ በላያችን ላይ አይጫንብን የሚሉ እና ይሄንን የመሳሰለ ነው
- ማን ነበር ይሄንን ሲል የነበረው ?
- ከላይ ስማቸው የተለገፀው ተራ በተራ ያንኑ ሁላቸውም ሲያስተጋቡ የነበሩ
- ስማቸውን በምን አወቁ እርሶ ስማቸውን በምን አወቁ ?
- በድምፅ ማጉያ ወንድሜ እከሌ ወንድሜ እከሌ እየተባለ ተራ በተራ ሲናገሩ በእዚያ ነው የሰማሁት በእስፒከር ማለት ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይሄንን ነው
- መልካቸውን አላየሁም ማንነታቸውንም አላውቀውም
- ከእዚያ በፊት አያውቋቸውም ?
- አላውቃቸውም
- ምን ቀን ነበር ሐምሌ ? ?
- ቅዳሜ
- ቅዳሜ ቀን ስንት ሰዓት አካባቢ ነው ሰው ወደ መስኪድ የመጣው ወይም እነሱ ወደ መስኪድ የመጡት ?
- እሱ ቀደም ብሎ ይምጡ ከእዚያ በፊት ከእዚያ በኋላ ይምጡ ያው ኮሚቴዎቻችንን መተዋል መባሉን ነው የሰማሁት እንጂ
- ኮሚቴዎቻችን መጡ ሲል ሰው ሲል ነው የሰሙት ?
- የሰማነው እንጂ እኔ ጥበቃ ቤት ውስጥ ነው ያለሁት
- ጥበቃ ቤት ሆነው ነው እንዴ የሚጠብቁት ለምን ውጪ አልጠበቁም የእዚያን ቀን ?
- ሰው ሙሉ ነዋ ሰው ላይ መረማመድ ስለማይቻል ያው ሁሉ እንደመጣ አንጥፎ ስለተቀመጠ በሰው ላይ መረማመድ ስለማይቻል ያው ያለ ዕድል ጥበቃ ቤት መቀጠጥ ነው
- ሰውስ ምን ይል ነበር እዚያ የተሰበሰበው ሕዝብ ?
- ተክቢራ ያደርገው ነበር አላህ ክበር ነበር የሚለው
- እንዴት ነው ሲሉ የነበሩት ?
- አላህ ክበር ነው ከእዚህ ውጪ የለም ያው ቅድም ያልኳቸው ነገር የሀባሽ አስተምሮ ከላያችን ላይ በግድ መሰሜን የለበትም በሚባልበት ጊዜ ሰው ተክቢራ ይል ነበር
- ተክቢራ አላህክበር ይል ነበር ?
- አዎ
- ስራዎት እንግዲህ እዚያው አንዋር ነው ሙሉ ቀን እዚያ ነበሩ ?
- ነበርኩኝ
- የእዚያን ቀን ሰው እዚያ የተሰበሰበው ለምን ዓላማ ነበረ ?
- ያንን እንትን አወሊያ ወንድሞቻችን ጉዳት /ግልፅ ያልሆነ/

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በእዚህ ይሄ ስለህ አመሊያ ወንድሞቻችን ላይ ጉዳት ደርሷል በሚል ነው ሰው የተሰበሰበው ?
- አዎ በእዚያ ምክንያት ነው
- በረመዳን ፆም በረመዳን ፆም ወቅት በቅዳሜ ቀን ጠዋት ላይ እንደዚያ ሰው ይሰበሰባል እንዴ ?
- አይ ቱሰብስቦ አያውቅም ከእዚህ በፊት
- ተሰብስቦ አያውቅም ?
- አዎ
- እስከ ስንት ሰዓት ቆዩ የእዚያን ቀን እርሶ በእዚያ በመስኪድ በአንዋር ?
- ያው ሙሉ ቀን ነዋ እኔ ጠዋት ገብቼ አድሬ ነው የምወጣው በማግስቱ ማለት ነው
- እሺ ሙሉ ቀን በማይክራፎን ነበር እንዴ ሲናገሩ የነበሩት ?
- አዎ
- መህል ላይ መብራት አልጠፋም ?
- ጠፍቷል
- መብራት ሲጠፋ ከእዚያ ምን ሆነ ?
- ያው ተቋርጦ ነበር እንደገና ጀነሬተር ተነሳ /ግልፅ ያልሆነ/
- ማን ነው ያስነሳው ጀነሬተሩን ?
- ያስነሳውን አላወኩም
- የጀነሬተር ቁልፍ ማን ጋር ነው ያለው ?
- የጥበቃ ኃላፊው ጋር ነው የሚቀመጠው
- የእዚያን ቀን የጥበቃ ኃላፊው ነበር እንዴ ቀርቦ ያንን የጀነሬተሩን ቤቱን የከፈተው ?
- አይ እኔ አላየሁትም የለውም በወቅቱ እሱ
- የጥበቃ ኃላፊው አልነበረም ?
- አዎ
- ከእዚያ በኋላስ የጀነሬተሩን ያለበትን ቤት አይተውታል በምን ቁልፍ እንደተቆለፈ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከእንትን በኋላ /ግልፅ ያልሆነ/ ከስብስባ በኋላ ያው ስራዬ ጥበቃ ስለሆነ ያለውን ነገር ዞሬ ስመለከት ድሮ ከተቆለፈው ቁልፍ ሌላ አዲስ ቁልፍ ተቆልፎ ነው ያየሁት
- የመጀመሪያው ቁልፍ ምን ሆነ ?
- ያንን እንግዲህ እኔ የተገነጠለ መሬትም የለም የወደቀም የለም ግን ቁልፉ አዲስ ተቆልፎ ነው ያየሁት
- እንደጥበቃ አባልነትዎ ከእዚያ በኋላ ያ ቁልፍ ምን ሆነ ሲባል ሰሙ ?
- ምን ሆነ
- ያ ቁልፍ መጀመሪያ ላይ ተቆልፎበት የነበረው ቁልፍ የጥበቃ ኃላፊው ከሌሉ እና ካልከፈቱ የእዚያን ቀን ምን ሆነ ቁልፉ ተቀየረ ?
- እንግዲህ ያኔ ጀነሬተሩን ያስነሳው አካል ከፍቶት ሊሆን ይችላል የሚል ግምት ነው ያለኝ
- በቁልፍ ከፍቶት ነው ወይስ እንዴት ነበር የነበረው ?
- ተሰበረ እንዳልል ሙሉ የተሰበረ ጋን እዚያ ነገር
- አላዩም ?
- አላየሁም በአዲስ ቁልፍ ተቀይሮ ነው
- ከእዚያ በኋላስ በጥበቃ አባል የተነገርዎ ወይም በመስኪዱ አስተዳደር የተነገርዎ ያ ቁልፍ ስለእዚያ ቁልፍ የሰሙት ነገር የለም ከእዚያ በኋላ ?
- ከእዚያ በኋላ ይሄ ቁልፍ እንዴት ነው ብዬ ስጠይቅ አንድ የፅዳት ሠራተኛ ምንድን ነው ያለኝ ይሄ ቁልፍ ከፍት ነበረ ከተጠቀሙ በኋላ ሌላ አዲስ ቁልፍ ገዝተው በምትኩ ቆልፎ አንድ ቁልፍ ለእኔ ሰጥቶ ለጥበቃ አባል እንድሰጥ ለእኔ ሰጡኝ እና አንደኛውን ይዘውት ሄደ የሚል ከፅዳት ሠራተኛው ሰምቼአለሁ
- ሌሎች ንብረቶችስ የእዚያን ቀን ማን ነበር ሲቆጣጠራቸው የነበረው ?
- ምኑን
- ሌሎች ንብረቶች ሌሎች የመስኪዱን ንብረቶች ማን ነበር ሲቆጣጠራቸው የነበረው ?
- ንብረት ሲባል አልገባኝም
- ሌሎች የመስኪዱ ንብረቶች ማለት ለምሳሌ መስኪድ ውስጥ ያሉ ኤምፕሊፋየር እስፒከር እነዚህ እነዚህ ነገሮች ማን ነበር ሲቆጣጠር የነበረው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቀደም ብሎ ወይስ በእዚያን ዕለት
- በእዚያን ዕለት ቀደም ብሎ ማን ነበር የሚቆጣጠረው ?
- በእዚያን ዕለትማ ያው ሰዎቹ ሲጠቀሙበት እንትን የነበረ እኔ ለምሳሌ ከ 2 ሰዓት ተኩል ነው የመጣው በእዚያን ሰዓት ሰው ሞልቷል ማን ማን በቦታው እንደነበረ አላወኩም
- የደረሰ ጉዳት አለ እንዴ በእነዚህ ላይ?
- ምን ንብረቱ ላይ ጉዳት የደረሰ የለም ግን የኦምፒሲፋየር መቀመጫ እንደዚህ ዓይነት ሣጥን ነበር እሱ ማጠፊያው ተገንጥሎ ክፍት /ግልፅ ያልሆነ/
- ማቀፊያው ተገንጥሎ እሱ አይተዋል ?
- አዎ
- እነዚያ ሰዎች በዕለቱ መስኪዱ ላይ መስኪድ ውስጥ ገብተው በማይክራፎን ንግግር ያደርጉ ነበር ብለዋል ማን ፈቅዶላቸው ነበር የመስኪዱ አስተዳደር ፈቅዶላቸው ነው እንዴት ነበር ያንን ንግግር ሲያደርጉ የነበረው ?
- እኔ እንግዲህ ቀደም ብሎ ስለተገባ ማን እንደፈቀደ የፈቀደውን አካል የማውቀው ነገር የለም
- የሚያውቁት ነገር የለም ?
- አዎ
- አሁንም እዚያው መስኪዱ ጥበቃ ነው እየሰሩ ያሉት ?
- አዎ እየሰራሁ ነው ያለሁት
- የእዚያን ቀን ማለት ነው ሐምሌ 7 ሐምሌ 8 ነበሩ እንዴ እርሶ ?
- 7 ነው
- ሐምሌ 7?
- አዎ
- ሐምሌ 7 መስኪዱን ግቢው ላይ ሲጠብቅ የነበረ ማን ነው ማንም ሰው ዝም ብሎ መግባት ይችል ነበር ?
- እንዴት ጥበቃ ሠራተኞች እኛ አለን ሠራተኞቹ ማለት ነው 5 ሰዎች ነን አለን እኛ
- የእዚያን ቀን ይሄንን መደበኛ ስራችሁን እየሰራችሁ ነበር ?
- ያው ሰው ሙሉ ስለሆነ እንቅስቃሴ የለም ተቀምጠናል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሰው ሳይኖር ብቻ ነው የምትጠብቁት ?
- ማለቴ ቦታው በሰው ስለተሞላ መረማመድ እና ተዟዙሮ ማየት ስለማይቻል አንድ ቦታ ተቀምጠናል ማለት ነው
- ቀኑን ሙሉ መስኪዱ ሞልቶ ነበር ውጪም ውስጥም ሰው ነበር ብለዋል ?
- አዎ
- ይሄ ነገር እስከ መቼ ቀጠለ ?
- እስከ 10 ሰዓት ነው
- እስከ 10 ሰዓት ?
- አዎ
- እንዴት ተበተነ ?
- በቃ በራሳቸው ጊዜ ፕሮግራሙ አልቋል ብለው /ግልፅ ያልሆነ/
- ከእዚያ በኋላስ ?
- ከእዚያ በኋላ ምንም ነገር የለም
- ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት
- የተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ
- ምስክር አቶ አብዱራህማን የእዚያን ቀን ጥበቃ ቤት ነበርኩኝ ብለዋል ?
- አዎ
- ጥበቃ ቤትዎ የት ጋር ነው ያለው አሁን ከመስኪዱ እስቲ ለፍ/ቤቱ ያስረዱ ?
- በላኛው በር ማለት ነው ወደ መርካቶ በሚወስደው በር አካባቢ እንዲህ ቆርቆሮ ቤት ማለት ነው
- ከመስኪዱ ከግቢው አጥር አጥሩን ታኮ የተሰራ ቆርቆሮ ነው ?
- አዎ
- እዚያ ውስጥ ሆነው ነው ?
- አዎ
- ተከሣሾቹ የት ጋር ሆነው ነበር የሚናገሩት ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ትልቁ መስኪድ ውስጥ ነው ግለት ነው
- መስኪድ ውስጥ ?
- አዎ
- ትልቁ መስኪድ ውስጥ መሆኑን በምን አወቁ ?
- በእስፒከሩ የድምፅ ማጉያ ያለው ትልቁ መስኪድ ውስጥ ስለሆነ በእዚያ መተላለፉ ስለተላለፈ እዚያ ውስጥ መሆናቸውን አወኩኝ
- ምን ያህል ይርቃል አሁን ያሉበት ቦታ የመስኪዱ አጥር ጥግ ነው ቆርቆሮው እስከዋናው መስኪድ ድረስ ምን ያህል ይርቃል በግምት በሜትሮች አሁን ገምቱ ቢባሉ አንድ ኳስ ሜዳ?
- አንድ ኳስ ሜዳ አይሞላም
- አይሞላም ?
- አዎ
- ቅድም እነዚህ የጠቀሷቸው 4 ሰዎች ይሄንኑ ቃል ቅድም ያሉንን ሲደጋግሙ ያንኑ ቃል ሲደግሙ ነበረ ብለዋል ?
- አዎ
- እስቲ መጀመሪያ ማን ነው የተናገረው ?
- መጀመሪያ የተናገረው አቡበከር ነው
- መጀመሪያ አቡበከር ?
- አዎ
- ሲጀምር ምን አለ አቡበከርን ከእዚያ በፊት ያውቁታል እንዴ ?
- አላውቃቸውም
- አያውቋትም ?
- አዎ
- እንዴት ነው እስቲ ንግግሩ እንዴት ተጀመረ እርሶ ስንት ሰዓት ነው እዚያ የደረሱት ?
- እኔ በጠዋቱ 2 ሰዓት ተኩል አካባቢ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- 2 ሰዓት ተኩል ?
- አዎ
- እርሶ ሲደርሱ ሰው ነበረ ወይስ አልነበረም ?
- ነበረ ሙሉ ነው
- ሙሉ ነው ?
- አዎ
- ግቢውም መስኪዱም ሞልቶ ነበር እርሶ ሲደርሱ ?
- አዎ ሞልቶ በሩ እስከ በሩ እስከ ውጪው በር ድረስ ማለት ነው
- ጥሩ እርሶ ከመጡ በኋላ ነው እነዚህ 4 ሰዎች ተናገሩ ያሉት ?
- አዎ
- ንግግሩን እንዴት ጀመሩ እራሳቸው እኔ አቡበከር ነኝ እያሉ ነው የጀመሩ ?
- አይደለም ቀደም ብሎ እንደአስተዋዋቂ የሚያስተዋውቅ ነበር ወንድሞቻችንን መጥተዋል ብለው አሁን ስለሁኔታው ያብራሩላቸዋል እና አዳምጡ ሲባል ነው ሲናገሩ የነበረው
- ሌሎችንም አያውቋቸውም አይደል በአካል ?
- ማናቸውም አላውቅም
- አያውቋቸውም ?
- አዎ
- ሲገቡም አላዩም ?
- አላየዋቸውም
- ስለዚህ አሁን አቡበከር አህመዲን ያሲን እያሉ የሚጠሯቸው እዚያ በእስፒከሩ ላይ ወንድሞቻችን እየተባለ ስማቸው ስለተጠራ ነው ?
- አዎ ያንን ነው
- እንጂ በቦታው እነሱ ተገኝተው ይናገሩ ወይም በእነሱ ስም ሌላ ሰው ይናገር ማረጋገጥ አይችሉም
- አልችልም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቀጥሎስ መጀመሪያ አቡበከር ተናገረ ቀጥሎ ማን ነው የተናገረው ?
- ቅደም ተከተሉን ይሄንን ያህል ለይቼ እከሌ እከሌ /ግልፅ ያልሆነ/ አልችልም ለምን /ግልፅ ያልሆነ/ ግን ቅድሚያ ወንድማችን አቡበከር እንደዚህ እንደዚህ /ግልፅ ያልሆነ/ ይገልፅላችዋል የሚባለው /ግልፅ ያልሆነ/ የሰማሁት
- ጥሩ ቅደም ተከተሉን አያውቁትም ?
- አዎ
- ይሄ ንግግር ተደረገ አሁን ያሏት ንግግሮች ከእዚያ በኋላ ምን ሆነ ?
- ምንም /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄንኑ እንትን እያሉ ያው ኮሚቴዎች የመጅሊሱ አመራር እንዲወርድልን ምርጫው በሙስሊሙ ሕብረተሰብ እንዲሆን ምርጫው ደግሞ መስኪድ ውስጥ እንዲሆን ከመስኪድ ውጪ ያለው ምርጫ ተቀባይነት የለውም የሚለውን እና የሀባሽ አስተምሮት በጉልበት በላያችን ላይ መጫኑ ይቁም የሚሉትን እንትን ነበር ሲሉ የነበሩ
- አዎ ይሄ ነገር ተባለ ከእዚያ በኋላስ እርሶ በጣም ቆይተዋል እዚያ ቦታ ላይ ይሄ ተባለ ከእዚያ በኋላ ምን ሆነ እነዚህ ተናገሩ ጨረሱ ?
- አዎ
- ከእዚያስ ምን ሆነ ?
- ያው ሕዝቡ ያንንኑ ነው እየደጋገመ ሲል የነበረው ያንኑ እየደጋገሙ ነው ሲሉት የነበረው ተራ በተራ እና ወንድሞቻችን መለቀቅ አለባቸው ጉዳት ያደረሱ ሰዎች ሕግ ፊት መቅረብ አለባቸው የሚል የነበራቸው
- እስከ 10 ሰዓት ይኸው ነበር ሲደጋገም የነበረው ?
- አዎ
- በዕለቱ ሐምሌ 7 ምን ነበር አየሩ ሁኔታ እንዴት ነበር ?
- ካፊያ ምናምን ነበረ በወቅቱ
- ካፊያ ነበር ?
- አዎ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አቶ አብዱራህማን እ... ከጠዋት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ እዚያው ነበሩ አይደል ሁሉንም ነገር ሰምተዋል ?
- አዎ
- አሁን እዚያ ሲናገሩ ነበሩ ያሏቸው ቅድም ስማቸውን ከዘረዘሯቸው ሰዎች ሲያስተምሩ ሙሉ ቀን ሲያስተምሩ ነውየዋሉት ስላሉ ስላማዊ በሆነ መንገድ መጓዝ አለብን ብለው ሲያስተምሩ ነበር አይደል ?
- ተቃውሞ አለ
- ቀጥሉ
- ምስክሩ በዋና ጥያቄ ጥያቄ ሲቀርብላቸውም ሆነ ሲመልሱ ስለጥያቄአቸው ስላማዊነት ወይም ስለትምህርታቸው ዝርዝር ሁኔታ የሚያውቁትን ገልፀዋል ማለት 3ቱን ነጥቦች ገልፀዋል ከእዚህ ውጪ የሰማሁት ነገር የለም ብለዋል ስለሆነም አሁን በመሪ ጥያቄ እየቀረበ ያለው ነገር አንድም በዋና ጥያቄ አልጠየቅንም ምስክሩም አልመለሱም ስለሆነም ጥያቄው ያለአግባብ ነው ውድቅ ሊሆንልን ይገባል
- ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ ጠዋት ጀምረው ገብተው እስኪወጡ ድረስ ማታ ድረስ ቁጭ ብለው ተከሣሾች ቅድም ስማቸውን የዘረዘሯቸው ሰዎች ሲያስተምሩ የነበረውን ነገር ሲሰሙ የዋሉ መሆኑን መስክረዋል ይሄንን አሁን ሲያስተምሩ የነበሩትን ሰምተዋል አይደለም ወይ ብዬ ነው የጠየኳቸው አዎ ብለውኝ ከእዚህ ነው ሲያስተምሩ ይሄንን ሲሉ ተምተዋል ወይ ብዬ ነው የጠኩት አሳቸው ለዐቃቤ ሕግ የተናገሩትን ብቻ አይደለም የምጠይቀው ሲያስተምሩ ከሰሙ ሲያስተምሩ ከሰሙት ውስጥ ነው የምጠይቃቸው ያንን ሰምተው ከሆነ ሰምቼአለሁ ነው አልሰማሁም ከሆነ አልሰማሁም ነው የሚሆነው እና ጥያቄው ዐቃቤ ሕግ በጠየቁትም በመለሱት ላይ የተነሳ ነው
- እሺ የጠበቃ ጥያቄ ትክክል ነው ቀጥሉ ብለናል
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄአችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ይዘን መጓዝ አለብን ብለው ሲያስተምሩ ነበር አይደል ?
- ትክክል .

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥያቄአችንም በሰላማዊ መልኩ ለመንግስት እናቀርባለን ብለው ሲያስተምሩ ነበር አይደል ?
- ትክክል ነው
- ጥያቄአችን ምላሽ እንዲያገኝ ትዕግስት ያስፈልገናል ብለው ሲያስተምሩ ነበር አይደል ?
- ትክክል
- ጥያቄአችን ረጅም ጊዜ ሊወስድ ስለሚችል የፈጀውን ጊዜ ፈጅቶ መልስ እንድናገኝ ከሕዝቡ የሚፈለገው ትዕግስት ጋናት እና ሰላማዊ ትግል ብቻ ነው ብለው ሲያስተምሩ ነበር አይደል?
- ይሄንን እንቃወማለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ትክክል ነው
- ምንድን ነው ተቃውሞ እስቲ
- ነኛ በዋና ጥያቄ ይሄን ሁሉ ቅድም ስለተባለው አጠቃላይ ሁኔታ መስክረዋል አሁን ልክ ይሄ ምርጫ ይመስል ይሄኛውን አዎ አዎ እንዲባል ዓይነት ጥያቄ ቀርቦ ከመስቀለኛ ጥያቄ እና በዋና ጥያቄ መሠረት ባላደረገ መልኩ የሚቀርብ ጥያቄ አግባብ ስላልሆነ ውድቅ እንዲደረግልን ነው የጠየቅነው በፍፁም ይሄንን ነገር አልተናገሩም ይሄ ደግሞ ጥያቄው እራሱ የመስቀለኛ ጥያቄ መሠረት የሌለው እና ውድቅ ይደረግልን
- አልተነሳም ነው ጥያቄው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ ቋንቋ በመግለፅ ምስክሩን ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ በማምጣት አዎ አዎ አማስባል በመሰረቱ ይሄ እኛ ከመጀመሪያም ቢሆን በዋና ጥያቄ ላይ ቅድም ቴዲ ባለው በ3ቱ መሰረታዊ ብለን ባስመስከርናቸው እንጂ ከእዚያ ውጪ ግን አሁን የተነሱት ጥያቄዎት አዎ አዎ በሚያስብል መልኩ የቀረበ ባለመሆኑ ውድቅ እንዲደረግልን ነው በአክብሮት የምንጠይቀው
- አስተያየት ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት መጀመሪያው ነገር እንደዚህ ከቀጠልን አንደማመጥም ፍ/ቤቱን የሰጠውን ብይን ማክበር አለብን አሁን ይሽው ተቃውሞ ሌላኛው ዐቃቤ ሕግ አንስቶት አሁን ነው ብይን የተሰጠበት አሁን አንደገና ጥያቄው ሲቀጥል ተመልሶ ያንኑ እንትን ማንሳት ተገቢም አይደለም እሳቸው ስለሰሙት ነገር ነው ሲሰሙ ደግሞ ጠዋት እስከ ማታ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ድረስ ሲያስተምሩ የነበሩትን ነገር ሰምቼአለሁ ስላሉ ይሄንን ሲያስተምሩ ሰምተዋል ወይ ነው ጥያቄው ይሄንን ነው እየመለሱ ያሉት ጥያቄውንም መልሰውታል ትክክል ነው ብለው

- ብይን ተሰጥቷል ጥያቄው አግባብነት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ነው ያየነው አስቀድሞ የተባለውን መድገም አስፈላጊ አይደለም ከግራ ቀኙ የቀረቡት ክርክር እንዳለ ነው መጀመሪያ ምስክሩ ያው ሲመሰክሩ ሲያስተምሩ ሰምቼአለሁ ብለው በዋና ጥያቄ እና ሲያስተምሩ ሰማሁ ባለው ውስጥ በዋና ጥያቄ የመለሱት መልሶች አሉ አሁን ጥያቄው የቀረበው በእሱ ላይ ተንተርሶ ነው ስለዚህ ጥያቄው መጠየቁ ይቻላል ጥያቄው መሪ ነው መሪ መጠየቅም ይቻላል በመስቀለኛ ጥያቄ ይሄ በሕጉ ላይ በግልፅ የተቀመጠ ነገር ግን መታየት ያለበት መሪ ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል በመስቀለኛ ጥያቄ ሲባል በሕጉ ከመሪ ጥያቄ ውጪ መጠየቅ አትችልም ተብሎ በግልፅ በተቃራኒው የተከለከለ ነገር የለም እናም መስቀለኛ ጥያቄ በሙሉ መሪ መሆን የሕጉ ዓላማ አይደለም በሙሉ መሪ መሆንም የለበትም በአጋጣሚ መምራት ካስፈለገ በጥያቄው መምራት ይቻላል ነው ሁሉም መሪ የሚሆን ከሆነ መጨረሻው ምንድን ነው የሚሆነው የጠያቂው ምስክርነት ነው የሚሆነው የምስክሩ መሆን ቀርቶ ነው ማለት ነው ያ ከሆነ ያልተጠየው በምስክርነት ያልተጠራ ሰው እየመሰከረ ነው ይሄ ደግሞ አግባብነት የለውም ስለዚህ አሁን በሚያነሱት ጥያቄ ላይ ጥያቄው አግባብነት አለው መሪ ብቻ እየሆነ ነው 4/5 መሪ እየጠየቁ ነው መዝግበነዋል እንደዚያ ዓይነት መሪ ማከታተል የስነ ስርዓት ሕጉን ዓላማ የሚያሳካ አይደለም እስካሁን መሪ ጠይቀዋል ሳይመሩ ግን መጠየቅ ይችላሉ አሁን የተጠየቀው አግባብነት አለው ብለን ብይን ሰጥተናል
- አመሰግናለሁ ምርጫችን የመጅሊስ ምርጫችን በመስኪዳችን ብለው ነበር ብለዋል ምን ማለት ነው ይሄ እርሶ እንዴት ነው የተረዱት ?
- ምርጫ መካሄድ ያለበት ከመስኪድ ውጪ ሳይሆን በእምነት ተቋማችን በመስኪድ መሆን አለበት የሚል እንድምታ ይይዛል ማለት ነው
- ለእዚህ ምክንያት ብለው የገለፁት የሚመርጠው ሰው በመስኪድ የሚታወቅ እና ኃይማኖት ያለው ሰው ነው የሚል ነው አይደለም ምክንያታችሁ የሚመርጠው ሰው በመስኪድ የሚታወቅ እና ኃይማኖት ያለው ሰው መሆን አለበት ለእዚህም መስኪድ ውስጥ መሆን አለበት ምርጫው በሚል ነው አይደለም ምክንያት ሲገልፁ የነበረው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይደለም
- ምንድን ነበር
- እኛ ሙስሊሞች ለእምነታችን ይሆናል ብሎ ይወክለናል የሚለውን ሰው ሙስሊም የሆነ ሰው መምረጥ አለበት በሚለው /ግልፅ ያልሆነ/
- በወቅቱ በአካባቢው የፖሊሶች የደህንነት ጥበቃ ሠራተኞች የሆኑ የመንግስት የጥበቃ ሠራተኞች የደህንነት ሠራተኞች የሆኑ ነበሩ ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ጥያቄ እንቃወማለን በዋና ጥያቄ ስለፖሊሶች ስለፀጥታ ሠራተኞች እኛም አልጠየቅንም ምስክሩም አልመለሱም ስለሆነም በዋና ጥያቄ ያልተነሳ ፍሬ ነገር ላይ በመስቀለኛ ጥያቄ የተነሳ ስለሆነ ይሄም ያለአግባብ የቀረበ ጥያቄ ነው እና ውድቅ ይደረግልን
- የተከበረው ፍ/ቤት እኔ እኮ ገና ጥያቄዬን አልጠየኩም ገና እኮ ልጠይቅ እያልኩ ነው እሳቸው ተቃውሞ ብለው ያስቆሙኝ ምንም አልጠየኩም
- አይሰማም
- እኔ ገና ጥያቄዬን አልጠየኩኝም ገና ልጠይቅ ስጀምር ነው እሳቸው ተቃውሞ ብለው ያስቆሙኝ እኔም ግምት ላይ ነው ያቆምኩት ጥያቄዬን እና የትኛው ጥያቄ እንደተቃወሙኝም አልገባኝም የተከበረው ፍ/ቤት እኔ ጥያቄዬን እስክጨርስ እኮ መጠበቅ ነበረበት እኔ ገና ጥያቄዬን አልጠየኩም ወይ ልጠይቅ እና ፍ/ቤቱ ሰምቶት ጥያቄው የሚቀጥል ከሆነ ይቀጥል የማይቀጥል ከሆነ ይተው አንጂ እኔ አልጠየኩም
- ጥያቄዎ ስለ ፖሊስ ምንምን አይደለም
- እኮ ስለፖሊስ ገና ማንሳቴ ነው ከምን አንፃር እንደማነሳው እኮ ምንም አልተጠየቀም ገና ጥያቄዬን አልጠየኩም እሳቸው ሲቃወሙ
- ትተነዋል ነው አሁን
- አይ ልጠይቅ ገና ጥያቄዬን ወይ ልናገር እና ሰምተውት የሚቃወሙ ከሆነ ይቃወሙታል ካልሆነ ደግሞ ፍ/ቤቱ አይጠየቅም ካለ ልተው እኔ ጥያቄዬን ላንሳ
- አሁን ጥያቄው የተነሳደው ምንድን ነው ፖሊሶች እና የፀጥታ ሠራተኞች እዚያ ውስጥ ነበሩ ወይ የሚል ጥያቄ አድርገው ነው የወሰዱት ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ በአካባቢው የ[illegible] መሆኑን አይተዋል ወይ ነው ጥየቄዬ እሳቸው ጠዋት እስከ ማታ ድረስ እዚያው ጋር ነበርኩ ስላሉ
- እኮ እሱን ነው የቁጥጥሙት እኛም የያዝነው ይሄንን ነበር
- ፍ/ቤቱ ተረድቶት ከሆነ እሺ እኔ ያው ጠዋት እስከ ማታ እዚያ ጋር ነበርኩ ብለዋል በጣም ብዙ ሰው ነበር [illegible]ዋል ስለነበረው ሁኔታ ስላስረዱ ያንን ነገር በተመለከተ ፀጥታ ለማስከበር ነበር ወይ ነው ጥያቄዬ
- አሁን ይኸውሎት ሌላ ጥያቄ ከሆነ እኛም አንያዘው እንለፈው በቦታው ፖሊስ የፀጥታ ሠራተኞች እዚያ ውስጥ ነበሩ ወይ የሚል ከሆነ ጥያቄው እነሱ ይሄንን መሠረት አድርገው ነው ያነሱ እና ሌላ ከሆነ እንለፈው
- ይኸው ነው በቃ እሺ
- ይሄ ከሆነ አልተነሳም ሌላ ጥያቄ
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት እሺ በመንግስት እውቅና የተሰጠው መጅሊስ ሙስሊሙን የሚወክል መጅሊስ ሊኖረን እንዲኖረን እንፈልጋለን ብለው ሲያስተምሩ ነበር አይደል ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ጥያቄ እንቃወማለን
- እሺ
- ፍ/ቤቱ በእዚህ ጉዳይ ላይ ሙሉ ጥያቄዎች መሪ ሊሆኑ አይገባም በሚል አሁኑኑ ከእዚህ ጥያቄ በፊት ብይን ተሰጥቶበታል ስለሆነም አንድም ጠበቃው ያሉትን ብቻ አዎ ወይም አይ በማለት እየደጋገሙ እንዲመስክሩ ነው እየተደረገ ያለው ተገቢ ጥያቄ አይደለም ውድቅ ሊሆን ይገባል
- ይሄ የቸሎት አካሄድ ነው መልስ ማሰጠት አያስፈልግም ከተከራካሪ ወገን የተሰጠው ቅድም የተሰጠው ብይን አልተከበረም የሚል ነው ያው እየጠበቅን ነው መሪ ጥያቄ በዝቷል ነው ትክክል ናቸው ስለዚህ ሌላ ጥያቄ
- አስተካክዬ ልጠይቅ እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ስለመጅሊስ ያስተማሩት ምንድን ነው መጅሊስ የመጅሊስ አመራሮች ይውረዱልን ብለዋል ብለዋል ለምንድን ነበር ይውረዱልን ያሉት ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- _ሙስሊሙ ሕብረተሰብ ስላልመረጣቸው በሙስሊሙ ሕብረተሰብ የተመረጠ መጅሊስ የሚወክለን በቦታቸው መተካት አለበት ብሎ ነበረ
- በሙስሊሙ ሕብረተሰብ የተመረጠ መጅሊስ ሊኖረን ይገባል ነበር ይሉ የነበረው ?
- ኣዎ
- አቶ አብዱራህማን በዕለቱ እርሶ 2 ሰዓት ቁኩል አካባቢ ጀምሮ ነበሩ ሰው እንዴት ነበር የሚገባው እርሶ እዚያ በሩ ጋር ጥበቃ ቦታ ላይ ነበሩ ሰው እንዴት ነበር የሚገባው ?
- በብዛት ነበር የሚገባው
- ማለት በሩ ክፍት ነበረ ?
- ክፍት ነው
- እንደመጣ ይገባ ነበር ?
- እንደመጣ ነው የሚገባ
- ሁሉም በሮች ላይ እንዲሁ ነበር ተመሳሳይ ነበር ?
- አዎ የተከፈቱ ከሴቶች ጋር 4 በር ነው በ4ቱም በር ሰዎች ይገቡ ነበር
- እንጂ አትግቡ ብሎ የሚከለክል ሰው ማንም አልነበረም ?
- ማንም ሰው የለም
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ ካላችሁ
- ምስክር እኔ በዕለቱ ነበርኩ ያልከው በላያኛው በር ባለ ወደ መርካቶ በሚወስደው ባለ በር የዘበኛ ቤት ውስጥ ነበርኩ ነው ያልከው ?
- አዎ
- ቅድም ተናገሩ ተከሣሾች ተናገሩ ያሉትን ነገር በማይክራፎን ነው ሰማው ያልከን ?
- አዎ
- ሰው እንዴት ሲገባ እንደነበር ውስጥ ሆነህ እንዴት አየህ ?
- አባባሌ እኔ ስገባ እንደዚያ እዚያው ነው የነበረ ሰው የተከለከለ የለም ሁሉም ይገባ ስለነበረ ያንን ስላየሁት ነው ታግዶም ታገድን ያለ ሰው ስለሌለ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መጀመሪያ ላይ ከእ[illegible]ን ወጥተው ነበር እንዴ እርሶ ከእዚያ ከዘበኛው ቤት ወጥተው ነበር?
- ኧረ እኔ ዘበኛ ውስጥ [illegible]ው ያለሁት
- እና ዘበኛ ቤት ውስጥ ሆነው አሁን ውጪ ስለተደረገ ነገር ነው እየነገሩን ያለው ?
- በሩ ክፍት ነው እኮ እኔ እዚያ ቤት ውስጥ ቢሆን በሩ /ግልፅ ያልሆነ/ ከበሩ ትንሽ ርቀት ነው ያለው ቤቱ ግቢ ነው የጥበቃ ቤት
- ስለዚህ ውጪ በር ጋር የሚፈትሽ ሰው ይኑር አይኑር የሚከለክል ሰው ይኑር አይኑር እርሶ ዘበኛ ቤት ውስጥ ሆነው የሚያውቁበት ሁኔታ አለ ?
- ስለሚታይ እያየሁ ስለሆነ ያው
- ቤት ውስጥ ሆነው ወደ ውጪ ነበር ሲያዩ የነበረው ?
- አዎ በሩ ክፍት ነው የሠራተኛው በር ክፍት ነው ወለል ብሎ ስለተከፈተ እንደዚህ ትይዩ ስለሆነ በፊትም
- በሩ ጋር የነበረው ዘበኛ ማን ነበር በሩ ጋር የነበረው ጥበቃ ማን ነበር ?
- ጥበቃ ሌላ ጥበቃ የለም ማንም ሰው የለም
- ቅድም 5 ነበርን ስላሉ ነው እሺ ሌላ ጥያቄ
- ጥበቃ አባላቶቹ 5 ነን ስለማለት ፈልጌ ነው
- ከጠዋት ጀምሮ ሲያስተምሩ የነበሩትን ትምህርት በዋና ጥያቄ ቅድም ስንጠይቆ እነዚህ 3ቱን ጥያቄዎች መደጋገሞ ጥሩን ሙሉ እነዚህን ሲሉ ነበር ብለዋል በመስቀለኛ ጥያቄ ደግሞ ሲጠየቁ ጥያቄአችን ሰላማዊ ነው ረጅም ጊዜ ቢወስድም ትዕግስት ያስፈልገናል እንደዚህ እንደዚህ የተባሉትን ይሉ ነበር ብለዋል የትኛውን እንውሰድ እርሶ የትኛውን ነው የሰሙት?
- አባባሌ እኔ
- ምንድን ነው ተቃውሞ
- የተከበረው ፍ/ቤት የትኛውን እንውሰድ የትኛው ነው ትክክል ማለት አንደኛው ውሸት ነው የሚል ትርጉም ነው ያለው ይሄ ደግሞ እንደዚህ ዓይነት ምስክሩ እንዲህ ዓይነት ነገር አላሉም እኛም ደግሞ የውሸት የሚል ነገር አላስመሰከርንም ስለዐቃቤሕግ የጠየቁት ውሸት ነው ብለን /ግልፅ ያልሆነ/ እሳቸው የሰሙትን ነው የተናገሩት የትኛውን እንውሰድ የሚል ጥያቄ ሊጠየቁ አይገባም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን ምንድን ነው የምታደርጉት ተቃውሞ አድርጉት አሁን ተቃውሞ ማለት አሁን አስተያየት ምናምን ነው ሆን ተቃውሞ ወይ አልተነሳም ወይ መሪ ነው ወይ እንዲህ ዓይነት ነገር
- የትኛውን እንውሰድ የሚለው ነገር ነኛ ውሸት ነው የሚል ትርጉም ስለሆነ ያለው ተገቢ ጥያቄ አይደለም ጥያቄው እራሱ ሊቆም ይገባል የትኛውን እንውሰድ የሚል ጥያቄ ሊጠየቅ አይገባም የትኛው ነው ውሸት እኮ ነው አንደኛው እውነት ነው አንደኛው ውሸት ነው ማለት ነው እና ተገቢ አይደለም የተከበረው ፍ/ቤት
- ተጨማሪ አለ የተከበረው ፍ/ቤት በመሠረቱ የዐቃቤ ሕግም ሆነ የጠበቃ የትኛውን እንውሰድ የሚል አግራሞት ዓይነት ጥያቄ የሚጠየቀው 2ቱ አሻሚ እና ተመሳሳይነት ወይም ተቃራኒ ባህሪ ያላቸው መልስ ምስክሩ ከመለሰ ነው ግን 2 ፋክቶችን ስለተናገረ ምንም ሳይቃረኑ ወይም አሻሚነት ሳይኖራቸው የትኛውን እንውሰድ የሚል ጥያቄ ምስክሩን ማሳሳት ስለሆነ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ሊጠየቅ አይገባም የጥያቄው ባህሪ ስህተት ነው
- ምላሽ ስጡበት
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት የመጀመሪያውን ተቃውሞ አስመልክቶ የትኛውን እንውሰድ የሚለው ጥያቄ ለፍ/ቤት ግልፅ ካልሆነለት ምናልባት ምስክሩ ግልፅ አልሆነልኝም ሊል ይችላል ፍ/ቤቱም ግልፅ ካልሆነ ለችሎቱም ግልፅ ካልሆነ እንድናስተካክል ሊነገረን ይችላል ነገር ግን አሁን አንደኛም ስነ ስርዓታዊ አይደለም በድጋሚ ጥያቄ ያልተነሳ በመስቀለኛ ጥያቄ ባልተነሳ ነጥብ ላይ ነው እየጠየቃችሁ ያላችሁት በማለት ብቻ ነው ሊቃወሙ የሚገባው ስለሆነም ነኛ የጥያቄው አቀራረብም ስነ ስርዓትን መሠረት ያደረገ አይደለም ሌላው ምስክርን ያሳስታል ተብሏለው የጥያቄው ጥያቄአችን ዝርዝር ነው ያደረግነው በእኛ በዐቃ ሕግ ሲጠቅሱ 3ቱን ነገር ነው የሰማሁት ብለዋል ነገር ግን በመስቀለኛ ጥያቄ በዝርዝር የገለፁዋቸው ነገሮች ሌሉ እኛ ከጠየቅነው ጥያቄ ለእኛ ከመለሱት ነገሮች ሌለ ሰምተዋል ወይ እኛ ወይም ኮንፊርም ስናደርግ ከእነዚህ ውጪ አይሉም ነበር በማለት ደምድመው ነበር እና የትኛውን እንውሰድ ይሄኛውን መደምደሚያ እንውሰድ ወይስ በመስቀለኛ ጥያቄ የተነሱትን እንውሰድ በማለት ነው እየጠየቅን ያለው እና የተነሱት ተቃውሞዎች ያለአግባብ ናቸው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ብይን ሰጥተናል በ[illegible]መሪያ ደረጃ ዐቃቤ ሕግ ጥያቄው ስነ ስርዓታዊ አይደለም የሚለው ነገር ተገቢ አይ[illegible] ምክንያቱም ፍ/ቤቱ ተቀብሎ እያስተናገደ ነው ያለው እሱን ታስተካክላላችሁ [illegible]ያ ውጪ ግን ጥያቄው ምስክሩ መጀመሪያም ዐቃቤ ሕግ ላይ የተነሳ አንድ ነገር አለ በ[illegible]ም ከተከሣሾች የተነሳ አንድ ነገር አለ ስለዚህ በኋላ የተጨመሩትን ሁሉንም ሰምተዋ[illegible]ል ጠበቆችያሉትን ብቻ ነው ወይ ዐቃቤ ሕግ ያለውን ብቻ ነው [illegible]
- እሺ እንታረማለን የ[illegible]በረው ፍ/ቤት ምስክር ጥያቄውን ያስታውሱታል ወይስ ልድገምሎት
- የመቼውን
- አሁን ተቃውሞ የ[illegible]በት ጥያቄ እሺ ልድገምሎት መጀመሪያ ላይ በዋና ጥያቄ ስንጠይቅዎ ሰማሁ ያሉት 3ተ[illegible] ነጥቦች መሠረት ያደረጉ ነገሮች ገልፀዋል ቀኑን ሙሉ ሲደጋግሙ የነበሩት ነገር እነዚህ ናቸው ከእነዚህ ውጪ ሌላ ነገር አላሉም በማለት በዐቃቤ ሕግ ምስክርነት ከገለፁ[illegible]ኋላ በድጋሚ ጥያቄ የዘረዘሯቸው ነገሮች አሉ ጠበቃው ሲጠይቁ አዎ አዎ በማለት ማለት ነው ወይም ትክክል ትክክል በማለት እነዚህ ሁሉንም ነው የሰሙት ወይስ እንዴት ነው ይሄንን እስቲ ይግለፁ ?
- እኔ በመጀመሪያ [illegible]ት እንትን እንደአንኳር በመውሰድ እንጂ በእዚህ ዙሪያ ነው ለማለት በለፈለጉ ነው አ[illegible]ዘርዝር ውስጥ ላለመሥፋት ይሄ ይሄ ነው ለነዚህ ለነዚህ ነው ብለን ይሄ ይሄ ነው በሚል እንኳሩን በመውሰድ ብቻ ነው እንጂ ይሄንን ሰምቼዋለሁ
- ድጋሚ ጥያቄ አብ[illegible]ል
- ያፍ/ቤቱ ጥያቄ
- ጥበቃ ቤት ውስጥ [illegible]ቤ ነበር ብለው ነበር እና ?
- ትክክል
- ሰዎች ሲገቡ ነበር ፍ[illegible]ሻ የለም ክልከላም የለም ብለዋል ?
- ይገባሉ ወይስ አይ[illegible]ም ፍተሻ መኖር አለ ፍተሻ ነበር ግን ሰው ይገባል
- ቆዩ እና በር ውስጥ [illegible]ር ውስጥ ቁጭ ብለዋል እርሶ የዘበኛ የጥበቃ ቤት ውስጥ እዚያ ጥበቃ ቤት ሆነው በሩ ይ[illegible]ል ሰዎች የሚገቡበት በር ?
- አዎ ፊት ለፊት ስለሆነ ይታያል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለነሱ ብር ነው ሁሉም ብር ነው የሚታየው እርሶ ከነበሩበት ሆነው ?
- አንዱ በር
- አንዱ በር ይታያል ?
- አዎ
- [illegible]
- እኔ መልካቸውን አላውቅም እዚያ አካባቢ አይቼአቸው ስለማውላቅ ወጣቶች ናቸው
- ማለት ወንድ ነው ሴት ?
- በወንድ በኩል ስለሆነ ወንዶች
- ወንዶች ናቸው የሚፈትሹ ?
- አዎ
- የጥበቃ ሠራተኞች ናቸው እንዴ ?
- አይደሉም
- አይደሉም ?
- አዎ
- አያውቁትም ?
- አላውቃቸውም
- የጥበቃ ያልሆኑ ሌሎች ሰዎች ናቸው ?
- አዎ
- እናመሰግናለን ጨርሰዋል መመለስ ይችላሉ
- የዛሬውን ችሎት በእዚሁ እናጠናቅቃለን ይሄንን መሠረት አድርገን ትዕዛዝ ሰጥተናል

ትዕዛዝ

- የችሎት ውሎ ከመቅረፀ ድምፅ ወደ ፁሑፍ ተቀይሮ [illegible] ጋር ይያያዝ ብለናል ቀሪ የባቄላ ትግ መለከሎች ለመስማት ቀጠሮ ለ[illegible] ቀን 200[illegible] ተተጽፏል ከጠ ጋ ሰዓት ተኩል ላይ እዚህ እንገናኛለን።

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

4ኛ ወ/ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

የካቲት 13 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች :- ብስራት ተህልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሳሽ :- አቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድምአገኝ ፣ዘረሰናይ ምስግና ፣ቴዎድሮስ ባህሩ ቀርበናል

ተከሳሾች:- እነአቡበክር አህመድ የቀረ ሰው አለ ቁጭ በሉና 21ኛ ነው

ሌሎቹ ቀርበዋል ጠበቆች ከ28ኛ ተከሳሽ በስተቀር ሃሰን ሁሴን መሃመድ አብደላ ሞላልኝ መለሰ ፣ ባህሩ መካንጋ አዲስ መሃመድ ቀርበናል

- የተከሳሾች ጠበቆች ከ28ኛ በስተቀር 5 ጠበቆች ቀርበዋል የ28ኛ እና ሌሎች የተከሳሾች ጠበቆች ከ5 ውጪ ያሉት አልቀረቡም መዝገቡ ያው ለዛሬ የተቀጠመው አንደኛው ቀሪ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች በተያዘው ቀጠሮ መሰረት ለመቀጠል ነው 2ኛ የተከሳሾች ጠበቆች ያላቸውን ውል ለዛሬ እንዲያቀርቡ ተብሏል አንድ ውል ነው ውክልና የትኛው ነው የሚሆነው እንዴት ይታያል የሚለውን ለማንኛውም ለማየት በእጃቸው ያለውን ውል ለዛሬ እንዲያቀርቡ ተብሏል እስቲ ምን ታስተላልፋላችሁ ለወደፊት ይሄ ቼክ እየተደረገ እኛ እንቀጥላለን ቼክ ተደርጉ የሚያመጣው ለውጥ ካለ በኋላ በዛው መሰረት የሚታይ ነው አሁን ትላንት ከተከሳሾቹ ጠበቆች አቶ ተማም አባ ቡልጉ ዛሬ እንዲቀርቡ ትእዛዝ ተሰጥቷቸው ነበር ትእዛዝ የተሰጣቸው በዝግ ችሎት እየታየ ያለውን ችሎቱ ከተቋቋመ ጀምሮ ለምን ለተለያዩ ሚዲያዎች ያስተላልፋሉ ስለሱ ጉዳይ ለማጣራት ዛሬ እንዲቀርቡ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ተብለው ነበር መጥሪያም ከምንጽፍ በጠበቆቹ በኩል ቢደርሳቸው ብለን ያው አድርሰናል በአካልም ነግረናቸዋል በአካልም በስልክም ተብሏል ከተከሳሾች ጠበቆች ጠበቃው ዛሬ አልመጡም ስለዚህ እሱን በተመለከተ ስምንት ሰዓት ላይ ተገቢ ትእዛዝ የሚሰጠው ይሆናል ማለት ነው እስካሁን አልቀረበም ባለው ሌሉቹ ባለው እንቀጥላለን ምናልባት አቃቤ ሕግ 21ኛ ተከሳሽ አልቀረቡም የምትሰጠው አስተያየት ካለህ

- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ያልቀረቡበት ምክንያት ከአቅም በላይ ሆነና የፍ/ቤቱን ቀጠሮ አክብሮ ለመቅረብ የማያስችል መሆኑን ፍ/ቤቱ ካመነበትበእኛ በኩል በእሳቸው ላይ እንደግለሰብ ተሳትፏቸውን የሚያስረዳ ምስክር በዛሬው ከጠዋት በፊት ወይም ዛሬ በሙሉ ቀን ባለው ችሎት የማናሰማ በመሆኑ ምስክር የማሰማቱ ሂደት ቢቀጥ ተቃውሞ የለንም ነገር ግን ያልቀረቡበትን ምክንያት ለፍ/ቤቱ በማረሚያ ቤትም ሆነ በጠበቆቻቸው በኩል በቂ እንትን እንዲረጋገጥልን ነው
- እሺ ማረሚያ ቤለ አንድ ተከሳሽ አልቀረቡም 21ኛ ታመዋል ይባላል የምታውቁት ካለ በምን ምክንያት መምጣት አይችሉም ጥቁር አንበሳ ቀጠሮ አላቸው የእርስዎን ስም እና ማእረጉን ቢነግሩን እና የስራ ድርሻ
- ገብረትንሳኤ ማእረግ ም/ኮማንደር ገ/ትንሳኤ የስራ ኃላፊነት ማረሚያ ቤት ስለዚህ ቀጠሮ ስላላቸው ነው የቀሩት ሕክምና አኬ ለጠዋቱ ቀጠሮ ስላላቸው ነው ጥቁር አንበሳ ተቀብለናል ቁጭ በሉ እሺ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ይቅረቡ
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም
- ምያለሁ
- እሺ ለምስክረነት ነው የመጡት
- አዎ
- ያው አሁን የምንፈልገው የአባቶን ስም ሳይጨምሩ የእርስዎን ስም ብቻ ነው እሱን ይገልፁልናል
- ናስር
- እሺ አቃቤ ሕግ በእኛ ቅደም ተከተል 41ኛ ናቸው በማስረጃ ዝርዝሩ ላይ በ27ኛ ላይ የተጠቀሱት እሺ አቶ ናስር ለምስክርነት ነው የመጡት?
- አዎ
- እነማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በአወልያ ተመርጠናል በሚሉ ኮሚቴዎች ላይ ነው
- እነማን ናቸው እነሱ?
- ያሙ በስም አቡበክር አህመድ ያው ሲያስተዋውቁ የሰማሁትን ነው ያሲን ኑሩ እነዚህን ነው የሰማሁት ሲያስተዋውቁ
- በአካል ያውቁታል አቡበክር እና ያሲንን?
- አላውቃቸውም በአካል
- ሲያስተዋውቁ ነው የሰሙት?
- አዎ በመስኪዱ እስፒከር ሲያስተዋውቁ ሰምቻለሁ
- እሺ ዋና ጥያቄ
- እሺ ምስክር መቼ ነው እራሳቸውን ሲያስተዋውቁ ሰማሁ የሚሉት?
- ሃምሌ 7 ቀን 2004
- የት አካባቢ ነው ቦታው?
- አንዋር መስኪድ ውስጥ
- ስንት ሰዓት አካባቢ ነው ?
- ሲያስተዋውቁ የሰማሁት አራት ሰዓት ተኩል
- ጠዋት ነው?
- አዎ ከጠዋቱ አራት ሰዓት ተኩል ማለት ነው
- ምን ነበረ እያሉ የነበሩት እራሳቸውን አስተዋውቀው ምን አሉ?
- መጅሊስ አይወክለንም ለመንግስት ያቀረብናቸው 3 ጥያቄዎች ይመሉሱ ክላ ሕዝቡ ደግመ የን በመቀበል አላህዋክበር ሲል ሰምቻለሁ
- የት ሆነው ነው ይሄን ሲሉ የነበሩት?
- ያው እኔ በመስኪዱ እስፒከር ነው የሰማሁት እኔ ያው ውጪ ሆኜ ነው የሰማሁት
- የት ውጪ ከመስኪድ ውጪ ነበሩ?
- ከመስኪድ ውጪ ሆኜ
- ለምን ሄደው ነበረ እርስዎ እላ?
- እኔ እላው ሰራተኛ ስለሆንኩኝ ለስራ ነበር
- እሺ ለስራ ነበረ የሄዱት?
- አዎ
- እና መግባት አልቻሉም ወደ ውስጥ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጠዋት ልክ ሁለት ሰዓት ተኩል ስመጣ ያው እኔ በማላውቃቸው ልጆች ግቢው ይፈተሻል ቢያንስ በአንድ በር ላይ ወደ አራት አምስት ሰው አለ ልክ ሁለት ሰዓት ተኩል በቃ እኔ ሳልፈተሽ ሌላጋ ሄድኩኝ ልጆቹ ሰራተኛ መኖር አለመኖሩን ለማጣራት አራት ሰዓት ተኩል ስመጣ ነው የአሁኑን በእስፒክር የሰማሁት
- ጠዋት ለስራ ሁሌ መደበኛ ስራዎ ?
- ለመደበኛ ስራዬ ልገባ ስል
- ጠዋት ሁለት ሰዓት ተኩል ነው የሚገቡት?
- አዎ
- ሌላ ጊዜ ሲገቡ ይፈተሹ ነበረ እንዴ ወይም ሰው ሲገባ ይፈተሻል?
- አይፈተሽም
- ምናች ናቸው ይሄንን ሲፈትሹ የነበሩት?
- እኔ አላውቃቸውም ያው ልጆች ናቸው
- ልጆች ሲባል?
- ወጣቶች ናቸው መሰለኝ
- እዛ መስኪድ ሰራተኛ ናቸው እንዴ?
- አደሉም
- አልፈተሽም ብለው ነው የተመለሱት እንዴት ነው እርስዎ?
- ያው እኔ በወቅቱ መፈተሽ ስላልፈልግኩ ሳልፈተሽ ዝም ብዘለ ነው የሄድኩት ወደራሴ ጉዳይ ማለት ነው አሁን ስገባ ሰራተኞች መግባት አለመግባታቸውን ለማጣራት እንደማንኛውም ሰው ተፈትሼ ገባሁኝ ተፈትሼ ስገባ ያው ጥበቃዎቹ ያው በአንድ ጥበቃ ቤት ተሰባስበው ቁጭ ብለዋል
- አንድ ላይ ነበሩ ጥበቃዎቹ?
- ጥበቃዎቹ አንድ ላይ ተሰባስበው ነው ቁጭ ያሉት
- ሁል ጊዜ እንደዛ ነው የሚቀመጡት?
- አደለም ሌላ ጊዜ በየቢራቸው ነው የሚቀመጡት
- የዛን ቀን ምን ከለከላቸው በየበራቸው እንዳይሆኑ?
- የው ግቢው በተለያየ ሰው ስለተያዘ እዛ ላይ ተሰባስበው ቁጭ ብለው አይቻቸዋለሁ
- ስለተያዘ በአንድ ቤት ተሰባሰቡ ሲባል መደበኛ ስራቸውን እንዳይሰሩ ተከልክለው ነው ወይስ እንዴት ነው ለምንድን ነው?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንግዲህ ያው ቦታው በሌላ ሰው ስለተያዘ እነሱ ተሰባስበው ቁጭ ብለዋል
- እሺ እርስዎ ኃላፊነት አሎት እዛ አወልያ?
- አዎ
- ምንድን ነው ኃላፊነቶ?
- በቃ የሰራተኛ ኃላፊ ነኝ
- የሁሉም ነው ወይስ የጥበቃዎች?
- የጥበቃ እና የጽዳት
- ጥበቃዎቹን አልጠየቁም እንዴ ለምንድን ነው ወደ ስራ ያልሄዱት ብለው?
- አልጠየቅኳቸውም ተሰባስበው ነው ቁጭ ያሉት እኔም ዝም ብዬ ወጣሁኝ
- ለምንድን ነው የተሰባሰቡነው አሉ?
- ያው ቦታው በሌላ ሰው ስለተያዘ የሚሰሩበት ቦታ በሌላ ልጆች ስለተያዘ እነሱ ተሰባስበው ቁጭ ብለዋል
- ምን አደረጉ እርስዎ በሌላ ሰው የተያዘውን ቦታ ለማስለቀቅ ?
- አይ ምንም ያረኩት ነገር የለም
- እስከ ስንት ሰዓት ቆዩ በዛን ቀን መስኪድ?
- እኔ በቃ ጠዋት ሁለት ሰዓት ተኩል ወጣሁኝ ወደ አራት ሰዓት ተኩል ተመልሼ አራት ከዛያ አምስት አካባቢ ተመልሼ ገባሁኝ በስፒከር የአሁኑን ቃል ሰምቼ ደግሞ ተመልሼ ወደነበርኩበት ወጣሁ
- ወዲያውኑ ነው የወጡት?
- ወዲያውኑ ነው የወጣሁት አዎ
- ስለዚህ ቀኑን ሙሉ የተባለውን ነገር አልሰሙማ?
- አዎ ከዛ ውጭ የሰማሁት ነገር የለም
- ሰው እንዴት ነበረ እነሱ ሲናገሩ ሰው አላህዎክበር ይል ነበር ብለዋል ተረጋግቶ ነው ወይስ ስሜታዊ ሆኖ ነው ሰው እንዴት ነበር ሲል የነበረው?
- ሰው ስሜታዊ ሆኖ ነው አላህዋክበር የሚለው
- ለምንድን ነው ስሜታዊ የሆነው?
- እንጃ ይሄንን አላወቅኩኝም
- የሚነገረውን እየሰማ ነበር አላህዋክበር የሚለው ?
- አዎ ያው በእስፒከሩ ድምጽ እየሰማ ያን እየሰማ ነው አላህዋክበር የሚለው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላው በሁሉም በር ነበረ ፍተሻ የነበረው?
- አዎ
- ሌላስ ጥበቃዎቹ በአንድ ክፍል ነበሩ ብለዋል ሌላ የመስኪዱን ንብረት ምናምን ቼክ አርገዋል አርስዎ?
- በወቅቱ እኔ በቃ ከዛ በኋላ ስላልተመለስኩኝ ቼክ አላደረግኩኝም እኔ
- ከዛ በኋላ ቼክ አላደረጉም?
- አዎ
- እሺ በምን ነበረ ሲናገሩ የነበረው?
- በመስኪዱ እስፒከር
- በምን ነበረ የሚሰራው እስፒከሩ?
- እስፒከሩ እኔ በነበርኩበት ሰዓት በመብራት ነበረ
- እርስዎ ከሄዱ በኋላስ?
- ያው ከዛ ውጪ ያለውን ነገር አላየሁም በመብራት
- የሰሙትን አሁን ያዩትን ነገር ነግረውናል የሰሙትንም ለችሎቱ መግለጽ ይችላሉ ከዛን በኋላ አጣርተው የሰሙት ነገር ካለም ለፍ/ቤቱ?
- ከዛ በኋላ ያው በጥበቃዎች ነው የሰማሁት ማብራት ሄደ መብራት ሲሄድ ጀኔሬተር አስነስተው እንደተጠቀሙ ሰምቻለሁ
- ማን ነው ያስነሳው ጀኔሬተሩን?
- ማን እንዳስነሳ አላወቅኩኝም
- ጀኔሬተሩ የት ነው የሚቀመጠው?
- እዛው መስኪድ ግቢ ውስጥ ነው
- ሜዳ ላይነው ወይስ ክፍል አለው?
- ሜዳ ላይ አንድ የሆነ ክፍል አለው ከስኪዱ ትንሽ እራቅ ይላል የሆነ ቤት ተሰርቶለታል
- ቤቱ በር አለው እንዴ?
- አለው አዎ
- ይቆለፋል በሩ?
- ይቆለፋል
- የዛን ቀን ተቆልፎ ነበር እንዴ?
- አዎ ተቆልፏል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማን ከተፈተው ቁልፉን?
- ያው ከጥበቃዎቹ እንደሰማሁኝ ያው ታሰብሮ ነው የተጠቀሙት ነው ሲባል የሰማሁት
- እነዚህ ጥበቃዎቹ ነው የሰበሩት ወይስ ለማስነሳት የሄዱት ሰወች ነው የሰበሩት?
- ለማስነሳት ከዛ ከተሰበሰበው ሕዝብ መሰለኝ
- እንደዛ ነው የሰሙት?
- አዎ
- እሺ ሌላስ መስኪዱ በን ቁጥጥር ስር ነበረ የነበረው በመደበኛ ሰራተኞቹ በመደበኛ አሰጋጆቹ ነው ወይስ በማን ቁጥጥር ስር ነው የነበረው ?
- ያን ቀን ያው ተረኞች ነበሩ ወደ አምስት ተረኞች ነበሩ ከአምስቱ አንድ አልገባም ነበር አራቱ ግን ያው ነበሩ
- ጥበቃዎቹን ነው የሚሉን ?
- ጥበቃዎቹ የሚጠብቁት የመስኪዱን የትኛውን ክፍል ነው?
- ጥበቃዎቹ አጠቃላይ ነው የሚቆጣጠሩት
- ይሄ ውስጡንስ ምናምን ማን ነው የሚመለከተው ማይክራፎን ያለበትን እንደዚሁም ሌሎች የመስኪዱ ንብረቶችን ማን ነው የሚመለከተው?
- የው አጠቃላይ ጥበቃዎችን የሚመለከተው ማይክራፎን ቁልፍ ምናምን በማኡዘኖች ነው የሚኖረው ሙአዚኖች ናቸው ከፍተው የሚጠቀሙበት
- ማን አሉ?
- አዛን የሚሉ ሰወች ማለት ነው ሙአዚኖች ማለት ነው
- ምን ማለት ነው?
- ሰዓት ሲደርስ አላህዋክበር የሚሉት
- እነዛ ሰወች በእለቱ ነበሩ እንዴ በእለቱ እነሱ ነበረ ማይክራፎኑን ሲናገሩ የነበሩት እንዲናገሩ የሰጧቸው?
- አይ እነሱ የሉም አልገቡም እንደገቡ ነው የሰማሁት
- እነሱ አልገቡም ነበር ?
- አዎ
- ስለዚህ በሌሎች ሰወች ነበረ እንትን ሲባል የነበረው ?
- አዎ
- በፍተሻ ወቅት እሚያዝ ነገር ነበር እንዴ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ምን እንዳይገባ ነው ፍተሻ ሲደረግ የነበረው ወይም ደግሞ የተያዘ ነገር አለ እርስዎ ያዩት እየፈተሹ ሲያስቀሩት የነበረ ሲይዙት የነበረ ነገር አለ ?
- አይ የሆነ ሲፈሹ የሆነ እስክሪፕቶ ምናምን ካገኙ እስክሪፕቶ እያወጡ እዛ ያስጠምጡት ነበር እዛ አካባቢ
- እስክሪፕቶ ይቀበሉ ነበር?
- አዎ
- ሌላስ?
- ከዛ ውጭ አልተቀበሉም
- ለምንድን ነው እስክሪፕውን የሚቀበሉት ከውጪ?
- እሱን እንጃ ያወቅኩት ነገር የለም
- እስክሪፕቶ እየተቀበሉ ውጪ ያስቀምጡ ነበር?
- አዎ ሲያስቀምጡ አይቻለሁ
- እሺ ጨርሰናል
- እሺ መስቀለኛ ጥያቄ ካለ
- ሰው ስሜታዊ ነበር ብለዋል ያን ቀን አላህዋክበር ሲል ስሜታዊ ማለት ቁጭ ብሎ ነው የነበረው አደለ ሰው?
- አይ ቆሟል
- ስሜታዊ ነው ሲሉ ማለት እስቲ ይሄን አብራሩ ስሜቱ ተነክቷል ነው ወይስ ሌላ የተለየ አ ክት ያሳይ ነበር?
- ያው ዝም ብሎ በቃ በቆመበት በጣም በጩኸት አላህዋክብር ሲል ሰምቻለሁ
- አሃ ይሄንን ነው ስሜታዊ ያሉት ?
- አዎ
- ሌላ የተለየ ያዩት ነገር የለም ?
- የተለየ ነገር የለም
- ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ?
- የለንም የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ እናመሰግናለን ጨርሰዋል ይመለሱ
- በእውነት ለመመስከር

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በአላህ ስም
- ምያለሁ
- እሺ ለምስክርነት ነው የመጣኸው?
- አዎ
- ስምህን ያው የራስህን ስም ብቻ ነው የምትገግረኝ ከአባትህ ስም ጀምሮ ሌሎቹን አንጠይቅም
- እስቲ ንገረን?
- ነጁ
- ስንተኛ ላይ ናቸው አቃቤ ሕግ
- እሺ አቶ ነጁ ያው እስካሁን በተሰሙት ሊስት 42ኛ ላይ ደርሰዋል በማስረጃ ዝርዝር ላይ የተጠቀሰው 33ኛ ላይ ነው በነማን ላይ ነው የምትመሰክረው
- በነ ያሲን ኑሩ
- ያሲን ኑሩ ሌላስ?
- አቡበክር አህመድ ፣ያሲን ኑሩ፣ ካሚል ሸምሱ
- በሦስት ሰው ላይ ለመመስከር ነው የመጣኸው?
- እና አህመዲን ጀበል
- በአራት ሰው?
- አዎ
- እነዚህ ሰወች በአካል ታውቃለህ?
- አላውቃቸውም
- ምን ሲፈጽሙ ነው ያሉት?
- ሐምሌ 8 ጠዋት እዛ ስ ራ ላይ ነው የነበርነው ስራ ላይ ስንገባ
- አመተ ምረቱ መቼ ነው?
- ሐምሌ ቀን 2004
- ምን ሲያደረጉ ሰመ በአጭሩ ብቻ?
- ጠዋት እየገባን እያለን ማንነታቸውን የማናውቃቸው ወጣቶች ከሃያ እስከ 30 የሚሆኑ እያስፈተሹ እያስገቡ ነበረ
- የት?
- በታላቁ አንዋር መስኪድ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- አቶ ነጁ
- አቤት
- አሁን ስማቸውን የገለጽካቸውን ስትጠየቅ አላውቃቸውም ብለሃል?
- አዎ
- በምንድን ነው ታዲያ ስማቸውን ያወቅከው?
- በስብከት ላይ አሁን እከሌ ሊናገር ነው እየተባ ይወራ ነበር
- ይሄ መቼ ነው?
- ሐምሌ 8
- አመተምረቱስ?
- 2004
- ሰዓቱ?
- ጠዋት እኛ የገባነው ሁለት ሰዓት ነው ግን ፕሮግራሙ የተጀመረው ከአራት ሰዓተ እስከ አራት ተኩል ነው
- እሺ ከሁለት ሰዓት ጀምሮ ምንድን ነው እስቲ የሆነው በዝርዝር ንገረን?
- እና እየተፈተሸን ገባን እኛም እንደማንኛውም ሰው ተፈትሸን ገባን
- ስንት ሰዓት ነው እስቲ?
- ጠዋት ሁለት ሰዓት ነው የገባነው እኛ
- እንደማንኛው ስትል እናንተ ምን ስለሆናችሁ ነው?
- እኛ እዛ ሰራተኛ ነን
- እሺ?
- ተፈትሸን ገብተን የሆነ ልብስ መቀያየሪያ ቤት አለ ገብተን እዛ ቀጭ አልን እሚባለው እና እሚደረገውን እየተከታተልን ነበር
- እስቲ ንገረን እሚደረገውን እና የሚባለውን እስቲ እምታስታውሰውን ያህል በንግግርም በነበረው ሁኔታ ንገን እስቲ?
- ለምሳሌ በአንደኛ ደረጃ ምርጫችን በመስኪዳችን ይሁን አህባሽ የሚባል አዲስ ኃይማኖት ነው አንቀበለውም እንደገና መጅሊስ ይውረድልን እና ለኃይማኖታችን እስከ መጨረሻው ድረስ እንታገላለን መስዋእትነት እንክፍላለን እንደገና ሌላ ደግሞ የሞቱት የ7 ሰወች አስከሬን ይሰጠን

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ?
- እና ፍትህ ሚ/ር እንከሳለን መንግስት ለምንሪ ነዳጅ ያቃጥላል በራሳችን ጊዜ ሄደን-እጅ - እንሰጣለን ከፕሮግራሙ በኋላ ሄደን እጅ እንሰጣለን
- ፍትህ ሚ/ርን እንከሳለን ከሚለው ቀጥል ከዛ ጀምረህ?
- እሺ ከፕርግራማችን በኋላ ሄደን እጅ እንሰጣለን እንደዛ እያሉ ነበር
- አሁን የገለጽካቸውን የዘረዘርካቸውን ማን ነው ይል የነበረው እነዚህን አሁን የነገርከንን በዝርዝር?
- ከ17 ኮሚቴዎች አራቱ ናቸው በተራ በተራ እየወጡ ይሉ የነሩት
- ቅድም እንደገለጽከው ስም እየተዋወቁ እነዚህን ነው ሲናገሩ የነበሩት?
- አዎ
- ስንፈተሽ ነበረ ብለሃል?
- አዎ
- በየተኛው ስንት በር ነው ያው አህን የገለጽከው አንዋር መስኪድ ?
- መስኪዱ ከሴቶችጋር አራት ነው አንዱ የሴቶች በር ዝግ ነበር ሴቶች ግን በአንደኛው በወንዱ በር እየተፈተሹ ነበር የሚገቡት
- አንዱ በር ዝግ ነበር?
- ዝግ ነበር አዎ
- ሦስቱ በር ግን በፍተሻ ነበር የሚገባው?
- አዎ በሁለቱ በር ወንዶች በአንደኛው በር ሴቶች
- እየተፈተሹ ይገቡ ነበር?
- አዎ
- ማን ነበር የሚፈትሻቸው?
- አይ አላውቃቸውም ማንነታቸውን የማላውቃቸው ወጣቶች ናቸው
- ምንድን ነው የሚፈትሹት?
- አይ ስለት ነገር እስክሪፕቶ ምናምን ነገር ይዞ እንዳይገባ ነው
- እስክሪፕቶ?
- አስክሪፕቶ ነገሮች ስለት ያላቸው ነገሮች ማንኛውን ነገር እንዳይገባ ተብሎ እንትን አያሉ ነበር
- ፍተሻ ይደረጋል እንዴ ከዛ በፊት እናንተ ስትሰሩ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይደረግም
- ተደርጉ ያውቃል ?
- አይታወቅም
- ከዛስ ስንት ሰዓተ ላይ አበቃ ፕሮግራሙ?
- ፕሮግራሙ እንግዲህ በግምት አስር ሰዓት ዘጠኝ ከምናምን በቃ እንደዛ ነው ያለቀው
- እንዴት ነበረ ምን ነበረ ሲጠቃለል በምን ተጠቃለለ ?
- ሲጠቃለልማ በቃ አሁን ፕሮግራማችን በሚቀጥለው ጁምአ እዚህ እንገናኝ ተብሎ ነው እ ራትን ያለው
- ሌላ የተፈጠረ ነገር አለ?
- አይ ጄኔራተር ተሰብሯል ምናምን ተብሏል ቅዳሜ እለት ነው የባለው እኛ በሱ ላይ አልነበርንም
- ቅዳሜ ቀን ስንት ማለት ነው?
- በሰባት ነው
- በ7 ጄኔራተር ተሰብሯል ተባለ?
- ተሰብሯል ምናምን ተብሎ ነገረን
- ጄኔራተሩ የት የሚቀመጥ ጄኔራተር ነው ?
- እላይ እንትኑ ላ
- ምን ላይ?
- ከላይኛው በር መግቡያጋ በጉን በኩል የሚቀመጥ ነው ጥግ
- ጄኔራተሩ ተሰብሯል ማለት ምን ማለት ነው እራሱ ጄኔራተሩ ነው ?
- ጄኔራተሩ ቁልፉን ሰብረው ገቡ የጄኔራተሩን በሩን ማለት ነው
- እና አየኸው እንዴ አንተ የተሰበረ አለ አይተሃል ?
- ተሰብሮ ተተክቷል ሲባል ነው እንጂ የሰማሁት ያው ተተክቶ ነው ያየሁት ግን በወሬ ደረጃ ሲነገር ነው የሰማሁት
- በወሬ ደረጃ ተሰብሯል ተብሎ ሰምተሃል?
- አዎ
- እሺ ዋና ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ መስቀለኛ ካለ
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ነጁ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አቤት
- ሲመሰክሩ ፍትህ ሚ/ር እንክሳለን ሄደን እጃችንን እንሰጣለን ሲሉ ነበረ ብለዋል እና ከዛ በፊት ወደዚህ ወደ መስኪዱ ስንመጣ ሊያስተጓጉሉን መንገድ ላይ ሊያስቀሩን የሞከሩ ሰወች ነበር ብለዋል አደል?
- እ?
- ወደ መስኪዱ እንዳንመጣ ሊያግዱን የሞከሩ ሰወች ነበሩ ብየሚል ነገር ተናግረዋል አደል?
- አይ
- ቆይ ቆይ ምስክር
- በዋና ጥያቄ የተከበረው ፍ/ቤት አሁን የተባለውን ጥያቄ አላነሳንም አልተጠየቁም አልመለሱም በዚህ ጉዳይ ላይ
- እ?
- አሁን የተባለውን መንገድ ላይ ሊያግዱን የነበሩ ሰወች
- አልተነሳም ነው?
- አልተነሳም ነው ስለዚህ ጉዳይ አልጠየቅንምም አልተመሰከረምም
- እሺ ምላሽ
- እሺ የተከበረው ፍ/ት እኛ ተነስቷል ነው የምንለው ተነስቷል የምንልበት ምክንያት ሄደን እጃተንን እንሰጣለን የሚል ነገር ተናግረዋል ነው እና የዚህ ምክንያቱን ፈልፍለን አውጥተን ፍ/ቤቱ እንዲረዳልን ነወ ይሄን ጥያቄ እየጠየቅን ያለነው እጃቸውን የሚሰጡት በምን ምክንያት ነው የሚለውን ጥያቄ ለመጠየቅ እየተንደረደርን ነው ስለዚህ ተገቢ ነው ጥያቄው ነው የምንለው
- የመጀመሪያው ጥያቄ አደለም የኛ ጥያቄ አደለም ነው
- ኦኬ ገብቶናል
- እሺ ብይን ሰጥተናል ጥያቄው ተነስቷል አልተነሳም የሚል ነው ክርክሩ ተነስቷል አልተነሳም የሚለውን ጭብጥ ይዘን ነው ያየነው እኛ አሁን በጠበቃው የቀረበው ጥያቄ ጠዋት ወደ መስኪድ ሰወቹ ሲሄዱ የከለከሉ ሰወች እንቅፋት የሆኑ ሰወች ነበሩ አደለም ወይ ነው ጥያቄያቸው ያነሱት አቃቤ ሕግ ይሄን ጥያቄ በዋና ጥያቄ አላነሳንም ብለው ተቃውመዋል ምላሽ ሲሰጡ ጠበናቃው ለዚህ በቀጥታ ተነስቷል አልተነሳም የሚለውን ምላሽ አልሰጡም ምስክሩ ሰወቹን ስትናገሩ ከነበሩት ውስጥ የተናገሩት አንዳቸውም ቋሚ ፕሮግራማችንን ጨርሰን እጃችንን እንሰጣለን የሚል ነገር አለ እና ይሄን ነገር ለማጣራት

ECHN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ነው የሚል ነገር ነው ያነሱት ፍ/ቤቱ ሁለቱ ነገሮች የተለያዩ ሆነው ነው ያገኘነው ፕሮግራማቸውን ጨርሰው እጃቸውን መስጠት ከምን መጣ የሚለው በኋላ የሚታይ ሆኖ አሁን የተነሳው ጥያቄ ግን ጠዋት ወደ መስኪድ ሲሄዱ ለሕዝቡ እንቅፋት የሆነ ነገር አለ ወይስ የለም የሚለው በዋና ጥያቄ ተነስቷል አልተነሳም ነው ኦቤስሲ አልተነሳም ስለዚህ ይሄ አዲስ ጥያቄ ስለሆነ ይሄ ተገቢ አደለም ሌላ ጥያቄ ይቀጥሉ ብለናል

- እሺ አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ነጁ
- አቤት
- ፕሮግራማችንን ጨርሰን ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወይም እሚፈልገን አካል እንሄዳለን ያሉት በምን ምክንያት ነው?
- እሱን እኔ እንጃ
- እንሄዳለን ብቻ ሲሉ ነው የሰማኸው ከዛ በፊት ያለውን አልሰማህም?
- አልሰማሁም አዎ
- ወደ ፕሮግራሙ ሲመጡ ያጋጠማቸው ነገር ነበር እንዴ?
- ይሄ ብይን ተሰጥቷል
- እሺ ትቼዋለሁ የተከበረው ፍ/ቤት
- አስከሬን ይሰጠን 7 አስከሬን ይሰጠን እያሉ ነበረ ብለሃል ?
- አዎ
- የሞተ ሰው አለ እንዴ?
- በ7 እንግዲህ አወልያ ላይ እንግዲህ ያው በተነሳው እረብሻ ሰው ሞቷል ምናምን ተብሎ እንትን ብሎ ነበር
- አሃ በ7?
- የዛን ቀን
- 7 ማለት ?
- ቀኑ
- ወሩንም ጨርስ 7 ማለት ምን?
- ሐምሌ 7 እንግዲህ መጀመሪያ መነሻው
- አመተምረቱ?
- ፀቡ የተነሳው ማለት ነው
- የተነሳበት ቀን በ2004 ማለት ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሐምሌ 8 ምን ቀን ላይ ነበር የዋለው?
- እሁድ ቀን ነው
- ስለዚህ አሁን እርስዎ ፀብ ያሉት ነገር ሐምሌ 7 ነበረ ቅዳሜ ቀን ነበረ የነበረ ማለት ነው?
- ቅዳሜ ቀን ነው ያው
- ሰወቹ ፍተሻ በር ላይ ያረጉ ነበረ ያሏቸው ሰው ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ስለት ነገር ለመከላከል ነው አደል?
- አዎ
- ስለት ነገር እንዳይገባ ሰው ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል ነው አደል?
- እኔ እንደዛ መሰለኝ
- ፕሮግራሙ ሲያልቅ ምንም የተፈጠረ ችግር የለም አደል ሰው በየመጣበት ነው የተበተነው አደል?
- የለም
- የጄኔሬተሩ የሚቀመጥበት በር ቁልፉ ተሰብሯል ሲባል በወሬ ደረጃ ሰሙ እንጂ እርስዎ ያረጋገጡት ነገር የለም አደል?
- አይ አለየሁም
- አላረጋገጡም?
- አላረጋገጥኩም አዎ
- አቶ ነጁ
- አቤት
- ቅድም አሁን ሰማሁ ሲናገሩ እነዚህ በስም የጠቀስናቸው ተከሳሾች ሲናገሩ ሰማሁ ብለው ለፍ/ቤት የገለፁት ነገር አለ?
- አዎ
- የት ሆነው ነበረ የተናገሩት?
- ውስጥ ነው መስኪድ ውስጥ
- የትኛው መስኪድ?
- ዋናው መስኪድ ትልቁ መስኪድ ማለት ነው አንዋር መስኪድ ትልቁ ውስጥ ኢማሙ የሚቀመጥበት
- እርስዎ የት ነበረ የነበሩት የጥበቃ ቤት?
- የጥበቃ ቤት ውስጥ አዎ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የጥበቃ ቤቶ ምን ያህል ይርቃል በግምት የአንድ ኪስ ሜዳ ግማሽ ሜዳ 50 ሜትር በግምት ነው በትክክል ላይለኩት ይችላል?
- አንድ ኬስ ሜዳ ሊሆን ይችላል
- እዛጋ ቤት ውስጥ ነበራችሁ እናንተ?
- አዎ
- ሳወችንም አላውቃቸውም በአካል ብለሃል ?
- አዎ
- በእለቱ ሲገቡ አላየሃቸውም?
- አላየናቸውም ሲገቡ
- ስለዚህ እነሱ ተናገሩ የምትለው በእስፒከር በሰማኸው ነው?
- አዎ
- እንጂ እነሱ ይናገሩ ወይም ሌላ ሰው እነሱን መስሎ ይናገር ማረጋገጥ አትችልም?
- አይ አልችልም አዎ
- ማን ነበር መጀመሪያ የተናገረው?
- አይ እሱን እንኳን አላስታውስም
- እስቲ ሐምሌ 8 እንዴት ነበረ አንተ ጠዋት ሁለት ሰዓት ወይም ሁለት ሰዓት ተኩል አካባቢ ደርሰሃል አየሩ እንዴት ነበር በእለቱ ማለት ዝናብ ነበረ?
- አይ ፀሐይ ነው ጠዋት ነው ፀሐይ ነው
- ሰውስ መስኪድ ውስጥ ብቻ ነበር እንዴ?
- ሙሉ ነው መስኪድ እንዳለ ወጣቶች በቃ እየሞላ እኛም ስንገባ እራሱ በጣ ሊሞላ ነበረ በኋላ አካባቢ ሙሉ ሆነ መስኪዱ እንዳለ
- ግቢውስ?
- ግቢው ነው እኮ መስኪዱም ግቢውም
- ቅድም ሲፈትሹ ነበር ያልካቸው ወጣት ይሁኑ አይሁኑ በምንድን ነው የለየሃቸው?
- በሙሉ ወጣቶች ናቸው
- ማለት ፊታቸውነ አይተህ ነው ወጣት መሆናቸውን ያወቅከው?
- ያው እያየሁ እኮ ነው
- እዛ ፊታቸውን ስታይ ወጣቶች በሚለው አይተህ ነው?
- አዎ

2091 S24

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለኃይማኖታችን መስዋእትነት እንከፍላለን እስከ መጨረሻው እንታገላለን ብለዋል ይሄን ከማለት ውጭ እንዴት እንደሚታገሉ የገለፁት ነገር የለም አደል?
- መሪ ብቻ እያረጉ ነው ጥያቄዎትን መጀመሪያ እያሰቡ ይጠይቁ
- አቶ ነጁ ቅደም ተከተላቸውን የሚያስታውሱ ከሆነ ይንገሩን እስቲ ማን 1ኛ 2ኛ 3ኛ 4ኛ እንደተናገረ?
- ተጠይቋል
- አላስታውስም
- ተጠይቋል እሺ የ7 ሰወች አስከሬን ይለጠን ብለዋል ይሄንን የተናገረው ማን ነው?
- እሱ ያሲን ኑሩ ነው
- አቶ ነጁ
- አቤት
- ቅድም ሲመሰክሩ ምርጫችን በመስኪዳችን ይሁን የአህባሽ አስተሳሰብ አይጫንብን እያሉ ይጠይቁ የነበረው መንግስትን ነው?
- እ
- መንግስትን ነው አደል ምርጫችን በመስኪዳችን ይደረግልን የአህባሽ አስተሳሰብ እንዳይጫንብን ይደረግልን እያሉ ሲጠይቁ የነበሩት መንግስትን ነው አደል?
- አዎ
- ሙሉ ቀን ነበሩ እርስዎ እዛ?
- አዎ
- ከሰዓት በኋላ ላይ አወልያ ሰው ስለመሞቱ ምንም አላረጋገጥንም ሲባል ሰምተዋል?
- አልሰማሁም እሱን
- ሰው ከሞተ በእስልምና ኃይማኖት አስተምሩ የሰላት አልጀናዛ ወይም ሙት ላይ የሚሰገድ ስግደት ይሰገዳል አልተሰገደም አደል?
- የተከበረው ፍ/ቤት
- ትተነዋል ጥያቄውን
- የሞተ ሰው ስለመኖሩ አንተ የምታውቀው ነገር የለም አደል?
- መልሷል እሱን
- ነጁ
- አቤት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ምርጫችን በመስኪዳችን ተብሎ ነበረ
- ላም
- ምርጫው ተካሄደ?
- የት?
- ምርጫ ተካሄደ ወይ ምርጫ ተካሄደ አዲስ አበባ ውስጥ?
- ተካሂዷል
- ስለዚህ ያኔ ይውረድ ያሉት መጅሊስ ወርዷል አደል በዚህ የተነሳ?
- ወርዷል
- ቅደም ስለ ህዝቡ ብዛት ውጭም ውስጥም እንዳለ ተናግረው ነበረ?
- ላም
- ይህ ሕዝብ አሁን ያሏቸው አራት ሰወች መልእክት ሲያስተላልፍ ምንድን ነበረ የሚለው?
- ላላህዋክብር ይላል
- ቅድም መጨረሻ ላይም ነበርኩ ብለዋል እስከ መጨረሻው ሰዓት ነረ እስከ መጨረሻው ሰዓት ከነበሩ ስብሰባውን ሲጨርሱ ትግላችን ሰላማዊ ነው እጅ ለእጅ እንያያዝ ተብሎ ሲባል አልሰሙም ?
- ሰምቻለሁ
- ስለት እንዳይገባ የተከለከለው ለምንድን ነው?
- ተጠይቋል እሱ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ጨርሰናል እናመሰግናለን
- እሺ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ
- አቶ ነጁ
- ላቤት
- ስለት እንዳይገባ ይሁን ወረቀት እንዳይገባ ካሜራ እንዳይገባ እርግጠኛ ነህ የትኛዉ ነው ትክክልኛ?
- በቃ እኔ የትኛው እንደሆነ እርግጠኛ አደለሁም
- ምስክር ቆዩ እሺ ተቃውሞ
- ካሜራ የሚባል ነገር ምስክሩ አልተናገሩም እኛም መስቀለኛ ላይ ዋናም ላይ አልተነሳም እና አዲስ የተከበሩ አቃቤ ሕግ ያነሱት ነው ስለት እና እስክሪፕቶ ብቻ ነው እና ወይ እሚያስተካክሉት ከሆነ

2093 S26

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ አቃቤ ሕግ ምላሽ
- ቅድም ጌልፀዋል..የተከበረው ፍ/ቤት እስክሪፕቶ ስለት እና ሌሎችም ነገሮች እንዳይገቡ ይመስለኛል ብለዋል እንደዚህ ጠቅለል አርጐ ስለተናገረ አሁን የትኛው ነው ስለት ነው እስክሪፕቶ ነው ካሜራ እንዳይገባ ነው ሰው ማስታወሻ እየያዘ እንዳይወጣ ነው የሚለውን ለመጠየቅ ነው
- ስለዚህ ተነስቷል?
- ተነስቷል አዎ የተከበረውፍ/ቤት
- ብይን ተሰጥቷል አቃቤ ሕግ ጥያቄ ሲያቀርቡ ፍተሻ የተደረገው ካሜራ ወይስ ስለት እና እስክሪፕቶ ነው ወይስ ብለው ጥያቄ አቅርበዋል ካሜራ እንዳይገባ ነው ወይ የሚል ጥያቄ አቅርበዋል በጠበቆተ በኩል የተነሳው መቃወሚያ ካሜራ የሚባል አላነሳንም ይሄ ያልተነሳውን ነገር እየጠየቁ ነው ወይ ጥያቄያቸውን የሚያስተካክሉ ካልሆነ አይቻልም ብለው ተቃውሞ አቅርበዋል አቃቤ ሕግ ምላሽ ሲሰጡ እስክሪፕቶ ስለት ብለው አንስተዋል ስለዚህ ተነስቷል የሚል መከራከሪያ አቅርቧል ይሄ ጥያቄ ተነስቷል ወይስ አልተነሳም የሚለውን ነገር ፍ/ቤቱ አይቷል ካሜራ የሚለው ነገር አ ልተነሳም በግልጽ ሁለተኛው በደጋሚ ጥያቄ ላይ እንደዚሁ ድጋሚ ጥያቄ የዋናው ጥያቄ ኤክስቴንሽን ስለሆነ በቀጥታ መርተው መጠየቅ በሕግ የሚፈቀድ አደለም እና ጥያቄያቸውን አስተካክለው መቀጠል ይችላሉ
- ስለት የሚለባለውን እርግጠኛ ነህ አቶ ነጁ ?
- አይ እርግጠኛ አደለሁም
- አንተ ያየኸው ምንድንነው ?
- ፍተሻውን ነው አጠቃላይ እየተፈተሸ ነበር ግን ያው ሕዝቡ ብዙም
- ተይዞ ያየኸው ነገር አለ በፍተሻው?
- እስክሪፕቶ ምናምን ነው በቃ አስቀምጦ የምንገባ የነበረው
- ስለት አላየህም?
- አላየሁም ስለዚህ አስክሪፕቶዎችን ግን ሲቀበሉ አይተሃል?
- እስክሪፕቶ ተቀብሎ እያስቀመጠ ነበር
- ለምን እንደተቀበሉ ታውቃለህ እስክሪፕቶዎችን?
- አላውቅም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መጅሊስ ወርዷል አደለም ወይ ስትባል አሞ ብለሃል መጅሊስ በራሱ አሁን ምርጫውን በራሳቸው በሕገ ደምቡ ምርጫ አድርገው ይውረ ዳበእነሱ ጥያቄ ይውረዱ የምታውቀው ነገር አለ?
- አይ አላውቅም
- የአህባሽ አስተሳሰብ አይጫንብን ነው አህባሽ ይወገድ ነው የተባለው?
- ይወገድ ነው
- እንዴት እንደሚታደሉ ገልፀዋል ወይ ተብለህ ስትጠየቅ አይ አላወቅኩም ብለዋል እስከ ሞት እንታገላለን አላሉም እንዴ?
- ብለዋል
- ተቃውሞ አለ
- ተመልሷል
- ቢመለስም እንቃወማለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ይሽውላችሁ አሁን ተመለሰ በቃ አሁን ከተመለሰ ሚዛን ውስጥ የሚገባ ነው የሚሆነው
- የተከበረው ፍ/ቤት ይስተካከልልን እንዲህ አይነት
- አቃቤ ሕግን ሁለተኛ እንደዚህ መሪ ጥያቄ ነው ጥያቄው ማለት በተቃውሞ ባይቀርብም ጥያቄው መሪ ነው ከተመለሰ በኋላ ስለሆነ ነው
- ድጋሚ ጥያቄ ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- ቆዩ አሁን ይሄኛው ጥያቄ ስለተመለሰ ስለዚህ አናነሳም
- ክቡር ፍ/ቤት ተቃውሚችን ይመዝገብልን እና ወይ ፍ/ቤቱ በብይን አንሰርዝም ብሎ ይለፍ
- አሁን ሕጉ ላይ ያለው ግልጽ ነው ሕግ ላይ ያለው ምንድን ነው የሚነሳው ጥያቄ በተቃራኒ ወገን በተለይ በወንጀል ሕግ ለይ ያለው በተቃራኒ ወገን ተቃውሞ ካልቀረበበት በስተቀር መሪ ጥያቄን ፍ/ቤቱ ብዙ ጊዜም አያስቆምም ሕጉ ላይ የተፃፈው እንደዛ ነው በወንጀለኛ ሕግ በሌሎቹ ከሆነ ይሁን አሁን ተቃውሞ ከተመለሰ በኋላ የተነሳ ስለሆነ ምንም ወደኋላ የምንመልሰው ነገር የለም ስለዚህ ጉዳይ ይዤንን በዚሁ ጨርሰናል አንደኛው በዛ በኩል ያለው ክርክር በድጋሚ ጥያቄ ላይ መምራት ይቻላል የሚል አንድምታ ነው ያለን አቃቤ ሕግ እየሰማን ያለነው ይሄ በድጋሚ ጥያቄ ላይ መምራት ይቻላል አይቻልም የሚለው ነገር የፊሎዞፊ ብዙ መከራከር ይቻላል የፍ/ቤቱ ብይን የሚሰጥበት ግልጽ አቋም አሁን አሁን ጥያቄው ስለተመለሰ ወደዛ ውስጥ ገብተን የምንከራከረው ነገር አደለም መምራት ይቻላል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አይቻልም የሚለው ብዙ ፊሎዞፊ አደለም አሁን ለተያዘው ኢሹ ስላልሆነ ብዙም አስፈላጊ አደለም-አሬዲ ስለተመለሰ ማለት ነው

- የተከበረው ፍ/ቤት ተመሳሳይ ስተት እንዳይደገም አሁንም ምስክሩን ማሳሰቢያ ይስጥልን ተቃውሞ ከተባለ እንዲያቆሙ ወይ ደግሞ የተከበሩ አቃቤ ሕግ ተቃዉሞ ከተባለ ጥያቄያቸውን እንዲያቆሙ ከሁለት አንዱ እንዲሆንል ማሳሰቢያ ይስጥልን እንደከዚህ በፊቱ
- እሱ ግልጽ ነው ማንም ሰው በግራ ቀኝ ተነስቶ ተቃውሞ ካለ ምስክሩ እንዳይመልስ ይከለክላል አሁን እንግዲህ በተነሳው ፍጥነት መልሱን መለሰ ከዚህ በኋላ ምናልባት ተመዝግቦ ይጣልብን ምናምን የምትሉት ነገር ይሽው እየተመዘገበ እኮ ነው እናንተ ተነስታችሁ ተመልሷል ፍ/ቤቱ ይሄንን ነገር አላስተናግድም ካለ ለእናንተ በቂ ነው እያንዳንዷን ነገር እናንተ የምታይዋት መጨረሻ ላይ ምናልባት ይሄ ፍ/ቤት እናንተን የሚስማማ ፍርድ ባይሰጥ ወይም ትእዛዝ ባይሰጥ መጨረሻ ላይ ለይግባኝ ነው እናንተ የምትፈልጉት እሱ ለመሆኑ ደግሞ ይሄ እይተነገረ ነው ይህ ከተነገ ለእናንተ በቂ ነው ቀጥሉ
- የተከበረው ችሎት ምናልባት አሁን በድጋሚ ጥያቄ ከአሁን በኋላም ብዙ ምስክር አለ ስለዚህ ድጋሚ ጥያቄን በተመለከተ የተሳሳተ ነገር የለም አሁን ጠበቃው በገለፁት መልኩ ማለት ነው ድጋሚ ጥያቄ ላይ አሁን የተከበረው ችሎት እንደገለፀው ወደ እንትኑ ለመግባት አደለም እንደገለፀው መርቶ መጠየቅ ይችላል አይቻልም የሚለው ያከራክራል ሕጉ ግልጽ ስላልሆነ ነገር ግን ድጋሚ ጥያቄ በዋና ጥያቄም በመስቀለኛም ጥያቄ አሬዲ ክሊር የሆኑ ፋክቶች ናቸው በድገሚ ጥያቄ የሚመጡት ይሄ ምስክር ከአሁን በኋላ ቢመራም እውነትን ከማጥራት እና ግልጽ ከማድረግ ውጪ እዚህ ምስክር ላይ የሚቀመጥ ወይም ደግሞ የሚነገረው ነገረ አይኖርም ስለዚህ በድጋሚ ጥያቄ ግልጽ ለማረግ እስከሆነ ድረስ አሁን በድጋሚ ጥያቄ መርቶ አይጠየቅም ስተት ነው ተብሎ የሚታለፍ ከሆነ የተከበረው ፍ/ቤት ምናልባት በስነስርዓታዊ አካሄዱ ይቸግረናልግን የተከበረው ችሎት ግን እንዲህ አይነት አቋም የሚወስድ ከሆነ ግን ምናልባት ከንግዲህ ወዲህ ያንን እንተዋለን ስነስርዓቱ ግን ያንን አይልም ያንን አይደግፍም
- ኦኬ ስለዚህ ኢሹ ያው
- አሁን እዚጋ ያለው ነገር ምንድን ነው መምራት አለመምራት የሚለው ነገር ሕጉ ላይ ያለው ክፍተት አለ ግን በመስቀለኛ ጥያቄ ላይ ያልተነሳ ጥያቄ ሁለት ነገር ነው እዚጋ

2096 529

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚመጣው አንደኛ ያልተነሳ ጥያቄ ከመጣ የዋና ጥያቄ ሃሳብ ስለሚሆን እሱ ላይ ሙሉ በሙሉ መምራት አይቻልም

- እሺ መምራት ይቻላል አይቻልም ሲነሳ ተገቢ ብይን እንሰጣለን እሱን እዚሁ እናቆምና በዛ በኩል ያለው ነገር አለ በተከሳሾች የማንጠብቀው ከእናንተ ማጉረምረም ነገር አስፈላጊ አደለም በዛ በኩል ያለው አቁመ አያለ ነው ትክክል ነው ግን ጠበቆች ስላሉ የሚነሳው ጥያቄ ሲነሳ ማጉረምረም መረበሽ ስለሆነ ቃረጋጉ ጥያቄው ይቀጥል ያላችሁን ፊሊንግ በሙሉ ግለፁ እንስማው ከነሱ ይቀጥል
- እሺ እንዴት እንደሚታገሉ ገልፀዋል ወይ ተብለው ሲጠየቁ አልገለፁም ብለዋል በዋና ጥያቄ ስጠይቆት መልስ እስክምናገኝ እንታገላለን ካልተመለሰልኝ እስከ ሞት እንታገላለን ብለዋልነው አደለ ያሉት?
- አዎ
- እሱ ተመልሷል እኮ አቃቤ ሕግ
- እሺ ጨርሰናል
- እሱ ተመልሷል እንደገና ሌላ ጥያቄ መጠየቅ
- ጨርሰል የተከበረው ፍ/ቤት
- የተከበረው ፍ/ቤት
- ምንድን ነው እኛ እኮ እየተናገርን ነው አደለም እኛ እኮ እየተናገርን ነው አቃቤ ሕግ አቁም እያልን ነው እኮ ነው እየተነጋገርን ነው ምን ይሁን ነው የምትሉት
- እኛ እናስስብ የተከበረው ፍ/ቤት
- ቆዩ እስቲ ጀስት በጂላ እንሄዳለን
- ድጋሚ ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ምስክር ጨርሰዋል እናመሰግናለን ይመለሱ
- ምንድን ነው ጠበቃው
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አሁን እዚህ ችሎት ውስጥ ለተፈጠረው ነገር ትልቁ የቅሬታው ምክንያት እኔም የነሱን ያህል ሼህ የማደርገው አቃቤ ሕግ ዛሬ ብቻ ፍ/ቤቱ የሰጠውን 3 ትእዛዝ 3 ጊዜ ነው አሁን የጣሱት እንዲህ አይነት የክርክር አመራር ተገቢ አደለም ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን ማክበር አለብን ከዚህ በፊት የተሰጠን ትእዛዝ አለ ሰዓቱም ያ ነው ፍ/ቤት አንዴ ብይን ከሰጠ ያ ብይን ለአንድ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ተከታታይ ለሆኑ ጉዳዮችም ተመሳሳይ አካሄድ ነው መከተል ያለብን መሪ ጥያቄ መጠየቅ አትችሉም ተብሎ አሁን

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

በዚህኛው ምስክር ብቻ 3 ጊዜ ነው እንዲቆሙ የተደረጉት አቃቤ ሕግ አንዲህ አይነት የክርክር አካሄድ የምንከተል ከሆነ እኛ አምስታችን እንዲህ አይነት ስተት ብንፈጥር ሙሉ ቀን ነው የምንውለው ይሄ የአቃቤ ሕግ ስተት በግልጽ ተነግሯቸው ማስጠንቀቂያም ሊሰጣቸው ይገባል ተግሳጽም ይገባቸዋል እኛ ኃላፊነት እየወሰድን ነው ያለነው አቃቤ ሕግ ጉልበት ነው አሁን እያሳዩ ያሉት አሁን እነሱጋር እየታየ ያለው ነገር ስሜት ውስጥ የሚከታቸው

- በቃ ይበቃናል አሁን እሱ ከሆነ ሌላ ያለ መስሎን ነው
- የተከበረው ችሎት እኛም የምናስበው አለ
- በቃ በቃ አይተነዋል እኮ ሌላ ምንም ንግግር አያስፈልገንም እዚህ ያለውንም እዛ ያለውንም አይተናል አደል ተከሳሾች አሁን እየተከራከሩላችሁ ነው ስለዚህ መቼም ይሄ ሁሉ ተከሳሽ አንድ ቃል አንቀበልም ስለዚህ በጠበቆች
- ቆይ ካሚል እኔ እየተናገርኩ ነው
- መቼ ተሰጣችሁ ስለዚህ ስርዓት አድርግ
- የተከበረው ፍ/ቤት አልጨረስንም እና እንጨርስ አይ ከዛጋ ሳይሆን እሺ ሞላልኝ ስለተናገረው እሱን አልፈዋለሁኝ ሌላው ምንድን ነው ደምበኞቻችን እኛ መግለጽ ያልቻልነውን መግለጽ የሚፈልጉት ነገር አለ ስለዚህ ያን ጊዜ አሁን ተገድቧል እንትናቸው ጠበቆቻችሁ እየተናገሩ ስለሆነ ተብለን መናገር የምንፈልገውን ነገር እየተናገርን አደለም ያሉ ስለሆነ አልፎ አልፎ ኤክሰፕሽናል በሆነ ወይ ማስረዳት ያለባቸው ለፍ/ቤትም ሆነ ለዚህ ችሎት ትክክለኛ ፍትህ ያስገኛል ብለው ያስገኙትን ነገር እንዲናገሩ እንዲፈቀድላቸው ነው እየጠየቅን ያለነው ጠበቆቻችሁ ስላሉ ጊዜ ያራዝማል በሚል እንደዛ ስለተባለ እኛ በምንፈልገው መልክት እየተላለፈልን አደለም ለፍ/ቤቱ ብለዋል በዚህ አግባብ እንዲፈቀድላቸው እሱን ለማመልከት ነው
- የተከበረው ችሎት እኛም እምናመለክተው አለን አሁን ማለት የተከበሩ ጠበቃ እንዳሉት አሁን እየተደረገ ያለው የሕግ ክርክር ነው ስለዚህ በህግ ክርክር ደግሞ ፍ/ቤት ነው ብይን የሚሰጠው እንጂ ክርክሩን ዝም ብሎ ባያዝድ ለማድረግ ተከሳሾቹንም አን ነሰሰሪ እንትን ውስጥ ማስገባት ተገቢ አደለም ተግሳጽም ከሆነ ብይን ስነስርዓታዊ አካሄድ አለ እየተከራከርን ያለነው በስነስርዓት ሕግ ነው በስነስርዓት ሕጉ የሚገድበን ይለም የሚከለክለን የለም ብለን እየተከራከርን እያለ አቃቤ ሕጉ ደጋግመው ሃይላቸውን ጉልበታቸውን እያሳዩ ነው የሚባለው ኦልሞስት ሃራስመንት ነው ተገቢ አደለም እየተከራከርን ነው እሳቸውም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ቁጭ ብለው እየሰሙ ነው ስነስርዓቱ አይከለከለንም መርተን መጠየቅ እንችላለን እያልን ነው ከዛ ውጭ አሁን የተሰየ የተባለ ነገር የለም በዛ መሰረት ጠየቅን ፍ/ቤቱ አቁሙ አልን አቁመናል አሁን እየተደረገ ያለው የሕግ ክርክር ነው አሁን አን ነሰሰሪ ወርዶችን ባይጠቀሙ ተገቢ ነው ስለዚህ የተከበረው ፍ/ቤት እነሱም ይታረሙ

- አሁን ምንድን ነው የተነሳው እንዳለ አለ ኮንሰርን የሚያረገኝ ትንሽ
- እንቀጥላለን የጠዋቱ ያው የነበሩት ዳኞች ያው አልተቀየሩም አቃቤ ሕግ የተጨመረ የለም ከጠዋቱ ተከሳሾች የቀረ የመጣ አለ ከሰዓት መጥቷል ጠዋት የቀረው 21ኛ እሹ ሙሉ ተከሳሾች ቀርበዋል ጠበቆች የተጨመረ ካለ
- ተካ ሮባ ቀርቤያለሁ
- እሺ ሌሎቹ የጠዋቶቹ ናቸው እሺ የአቃቤ ሕግ ምስክር ይቅረብ
- የ28ኛ ተከሳሽ ጠበቃ አህመድ ጀማል ቀርቤያለሁ
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም
- ምያለሁ
- እሺ ለምስክርነት ነው የመጡት?
- አዎ
- እሺ ፊቶን ያው ወደ እኛ ታረጋለህ
- እ?
- ፊቶን ወደኛነው የሚያረጉት ወደዛም ወደዛም መዞር አያስፈልግም ያው በጆሮ ብቻ ማዳመጥ ያው የምንጠይቀው የራሶን ስም ብቻ ነው ወደ አባት አያት ስም አንሄድም ስለዚህ የራሶን የመጀመሪያ ስም ብቻ ይነግሩናል
- አሊ
- እሺ ስንተኛ ናቸው አቃቤ ሕግ ?
- 39ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር
- እሺ ቀርበው በመሰከሩት ዝርዝር 43ኛ ላይ ደርሰናል በማስረጃ ዝርዝሩ 39 ላይ የተጠቀሰ ተብሏል በነማን ላይ ነው የሚመሰክሩት አቶ አሊ?
- እኔ በአቡበክር ፣ አህመዲን ጀበል ፣ ያሲን ኑሩ
- አቡበክርስ ማን ነው የአባታቸው?
- እኔ አላውቀውም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እነኚህ ሦስት ሰወት ሳይ ለመመስከር ነው የመጡት?
- አዎ
- ሦስቱንም ሰወች በአካል ያወቃሉ?
- አላውቃቸውም
- እሺ በምንድን ነው ያወቁት?
- እኔ በመጀመሪያ በታላቁ አንዋር መስኪድ
- ያወቁበትን አጠር አርገው ይንገሩን እና ሌላውን በኋላ እንቀጥላለን በአካል አላወቁም እንዴት አወቁ በአካል ካላወቁ?
- አይ ንግግር በሚያደርጉበት ሰዓት አጠገቤ የነበሩ ሰወች አሁን የሚናገረው እገሌ ነው አሁን የሚናገረው እገሌ ነው በማለት ነው እንጂ እኔ ሰወቹን በአካል አላውቃቸውም
- እሺ ዋና ጥያቄ ይቀጥል
- መጀመሪያ ልግባ
- ቆዩ ቆዩ ቆዩ አቃቤ ሕግ ይጠይቃል የተረዱትን ብቻ ሲጠየቁ ይመልሳሉ
- መቼ ነው አሁን የሚናገረው እገሌ ነው እየተባለ ሲነገር የሰሙት?
- ሐምሌ 8
- ምን ቀን ነበር?
- አሁድ እለት
- ስንት ዓመተምረት?
- ሐምሌ 8 ነው
- ስንት ዓመተምረት ነው?
- 11ኛ ወር 2004
- እሺ የት ነው ቦታው?
- በታላቁ አንዋር መስኪድ
- ስንት ሰዓት አካባቢ ነው ?
- እኔ የገባሁት ጠዋት በግምት እስከ ሁለት ሰዓት ተኩል ይሆናል ብዬ ነው የምገምተው
- ለምን ነበረ በዛ ሰዓት የሄዱት ?
- እዛ ቦታ የሄዱት እኔ በስራ ጉዳይ ነው
- እዛው ነው ሥራዎት መስኪድ ውስጥ?
- እዛ ነው የምሰራው እና አሁን ልገባ ስል ፍተሻ ነበረ

FCLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማን ነው የሚፈትሸው?
- ወጣቶች ናቸው
- ሁል ጊዜ ነበረ እንዴ ከዛን ቀን በፊትፍተሻዎች ነበሩ?
- የለም እኔ አዲስ ነገር ነው የሆነብኝ ፍተሻው ጠዋት ነው አሁን ይሄን ፍተሻ ሳይ ትንሽ ተደናገጥኩ እኔ እና ቆም አልኩና ሁኔታውን ካየሁ በኋላ እንደማንኛውም ሰው እየተፈተሸ ይገባ ነበረ እና እኔም አብሬ እስክሪፕቶ ሞባይሎችንም ያዩ ነበረ ወጣቶቹ ፍተሻ ሲያደርጉ ማለተ ነው
- ምን አርገው ነው የሚያዩት ከፍተው ያዩ ነው ወይስ?
- አዎ ከፈት ያረጉና ያያዩ የኔን ሞባይል ከፈት አረጉና አዩና ሰጡኝ እስክሪፕቶውን ግን ያው ወሰዱት
- ለምንድን ነው የተቀበሉት እስክሪፕቶውን?
- እኔ ለምን እንደሆነ እስክሪፕቶ ይቀበላሉ የማንኛውንም እስክሪፕቶ እየተቀበሉ ይይዛሉ ምክንያቱን አላውቅም ስለዚህ ከዛ በኋላ እኔ እንደማንኛውም ተፈተሸኩና ወደ ሰራተኛ ቦታ አለች እዛ ቦታ ላይ ገባሁኝ ቆርቆሮ ቤት አለች ልክ በሩ ላይ በዚህ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አንዋር ቅርንጫፍ በሚለው በር ነው እኔ የገባሁት እና በዛ እዛችው በር ላይ ገባሁኝ ሕዝቡ ሞልቷል መስኪዱን ወዲያ ማዶ አሻግሬ ስመለከት በሕዝብ ሞልቷል ከዛ በኋላ ብዙ ከቆየን በኋላ ንግግር መደረግ ተጀመረ
- በምን ነበረ ሲናገሩ የነሩት?
- በእስፒከሩ በመስኪዱ እስፒከር
- እሺ በማይክራፎን?
- አዎ በማይክራፎን ነው ማለት ነው
- አሺ
- ከዛ በኋላ ንግግር ሲደረግ አቡበከር
- ማን ማን ነው የተናገረው?
- መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ አይግባ እሱንም አቡበከር መሆኑን ታዲያ እዛ አካባቢ አሁን አቡበከር ነው የሚናገረው በማለት እንጂ እኔ በድምፁ በአካልም አላውቃቸውም
- ያስተዋወቃቸው ሰው ነበረ ሲናገሩ?

ETCLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ እዛ አካባቢ ያለው ሰው በጣም ሞልቷል አሁን አቡበከር ነው የሚናገረው ይላሉ ዝም ብለው እና ይሄንን ሰማሁኝ አሁን አቡበከር ነው እንዴ የሚናገው ምናምን ብዬ ኧም አቡበከር ነው
- ሌላስ ምን ምን ተናገረ እስከ ስንት ሰዓት ቆይ እርስዎ እዛ?
- እዛ ቦታ እስከ አስር በግምት ከጠዋቱ እስከ አስር ብዬ እገምታለሁ
- እሺ ምን ምን ሰሙ ሌላ?
- ሌላ መርጫ በመስኪዳችን ይሆናል አህመዲን ነው ያሲን ኑሩ ደግሞ ለኃይማኖታችን እስከ መጨረሻው ድረስ እንታገላለን የሚለውን እነዚህን ነገሮች ሰምቻለሁ በጆሮዬ ማለት ነው
- እነዚህን ነገሮች ብቻ ነው የተናገሩት?
- የተናገሩት እኔ የማስታውሰው እነዚህን ብቻ ነው
- ከዚህ ውጭ ያለ የሚያስታውሱት ነገር የለም?
- ከዚህ ደግሞ ያው ኃይማኖት አሁን ያልኩትን ብቻ ነው
- ከዚህ ውጪ የሚያስታውሱት ነገር አለ?
- አዎ አስታውሳለሁ አንድ ከጠሩን እኛው እዛው እንሄድላቸዋለን የሚለውን ሰምቻለሁ
- ይሄንን ነው የሰሙት?
- አዎ
- ሌላ የሚናገሩት ነገር በዚህ ላይ ያጠነጠነ ነው ?
- በዚህ መሃከል ላይ አላህዋክብር ይባላል
- ማን ነው የሚለው ይሄንን?
- ሕዝቡ ያስተጋባል
- እንዴት ነበር ሲል የነበረው?
- አይ ንግግር በሚደረግበት ሰዓት አላህዋአክብር ይባላል
- ሰው ምን አይነት ስሜት ውስጥ ነበረ ይሄንን ሲል?
- ሕዝቡ ያው ሞልቷል ያው በጣም በሞራል ነው የሚለው
- አቶ አሊ ከመቼ ጀምሮ ነው እዛ ቦታ መገኘት የጀመሩት ወይም ደግሞ እንዲህ አይነት እንቅስቃሴ የተጀመረው አሁን ያሉትን አይነት?
- እኔ እንቅስቃሴውን የዛን ለታ ነው የማውቀው
- ሞልቶ ነበር ብለዋል አንዋር መስኪድ ነው ማለት አንዋር መስኪድ ነው የሚሰግዱት እርስዎ?

2102 S35

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አም አንዋር መስኪድ ነው
- እርስዎ የስራ ቦታዎት የት ነው?
- አንዋር መስኪድ
- ስለዚህ አሁን ማለት ሞልቶ ነበር ሲሉ እስቲ ይንገሩን ሞልቶ ነበር ማለት?
- ሕዝቡ ሜዳውን በሙሉ ሞልቶታል ግቢውን መስኪድ ውስጡን ሞልቷል
- ከዛ በፊት በነበሩ ስግደቶች እርስዎ በሚያውቁት ?
- በዛን ሰዓት ግን እኔ እንደዛ አይሆንም ነበር ነው
- እንደዛ አይሞላም ነበር?
- አይሞላም ነበር
- ከየት መጣ ታዲያ ይሄ ሁሉ?
- ካየትኛውም ቦታ እየመጣ ሰው ይገባል ብቻ
- እኮ ከየት መጣ በምን እንደመጣ እርስዎ የሚያውቁት ነገር አለ?
- አይ እኔ ይሄንን አላውቅም
- እዛ ሰራተኛ ነኝ ብለዋል ምንድን ነው ምክንያቱ አሁን ለዚህ ለነገሩን መሰብሰብ ምክንያት ወይም ደግሞ ግቢው ለመሙላቱ ምንድን ነው ምክንያቱ?
- ምክንያቱን እኔ አላውቅም
- የሰሙት ነገር የለም ለምንድን ነው እዛ አንዋር መስኪድ እየተሰባሰቡ አሁን ያሉት ነገር እሚናገሩት?
- እኔ ይሄንን አላውቅም ብዙም
- እሺ
- እኔ ደግሞ በሰዓቱ በጣም ከፍተኛ ድንጋጤ ስላለብኝ በጣም ፈራን እኛ ግርግሩን እንደዚህ አዲስ ነገር ስለሆነብን በጣም ፈራን እኛ እንጂ ይሄንን ብዙም እኔ አላውቀውም
- አዲስ ነገር ስለሆነብን ፈራን ማለት ምን ማለት ነው እስቲ ይንገሩን?
- አዲስ ነገር ሆነብን እና እኛ
- ምንድን ነው አዲስ የሆነባችሁ?
- በዛን ሰዓት ሕዝብ መሰብሰቡ
- እኮ ምን ያስፈራችኋል መስኪድ ነው ሰው ቢሰበሰብ ምንድን ነው ችግሩ?
- ፍተሻው አዲስ ነገር ነው እሱ ነው
- ፍተሻው ነው አዲስ ነገር የሆነባችሁ?

2103 536

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፍተሻ እንደዛ አይ ነት በፊት አላውቅም ስለማላውቅ አይቼም ስለማላውቅ ነው
- ሌላ ቅስቀሳ ወይም ማስፈራራት ነገር ነበረ መስኪድ ውስጥ?
- የለም
- ዘበኛ ነኝ እዛ ብለዋል አደል የደረሰ ነገር አለ እንዴ በሰው በንብረት?
- የደረሰ ነገር በንብረት ላይ እኛ መጨረሻ ላይ ከሄድን በኋላ እስኪከሩን እንትን ስናይ እስኪከሩን ሙአዚን ነው እየከፈተ የሚጠቀሙት የነበረው እና የዛን ጊዜ ግን እሱ ቁጭ ተሰብሯል
- የምን ቁልፍ?
- የእስኪከሩ ቁልፍ ሳጥን አለው የአምፕሊፋይሩ መቀመጫ ማለት ነው እና ያንኛውም
- የት ነው የሚቀመጠው?
- አየመጀመሪያ ቦታ ላይ ኢማሙ የሚያሰግድበት ማለት ነው
- እስቲ ተሰበረ ሲሉ ይንገሩን ምንድን ነው የተሰበረው?
- ቁልፏ ይቺ እንትኗ
- ማን ነው የሰበረው ?
- እኛ አናውቅም እንግዲህ በኋላ ነው እኛ እኮ ያየነው
- እኮ በኋላ ስታዩ?
- ከወጣል በኋላ ነው ያንን ነገር ያየነው
- ሰው ከወጣልን?
- አዎ ሰው ከወጣ በኋላ ከመስኪዱ ሰው ወጥቶ ሲሄድ
- ስንት ሰዓት ላይ ?
- አስር ሰዓት ላይ እኛ ገብተን ስናይ የዛን ሰዓት ቁልፏ ተሰብራለች ደግሞ ቅዳሜ የነበሩት እንትኖች ተረኞች ትላንትና ነው የተሰበረው ብለው ኢንፎርሜሽን አጠር አርገው እንትን ያሉን
- እናንተ ጥበቃ አደላችሁም እንዴ ይሄንን መቆጣጠር አትችሉም ንብረት ሲሰበር ወይም ደግሞ ሌላ ነገር ሲደርስ እናንተ ?
- በጣም በሰፊው እዛ ውስጥ መግባት አንችልም እኛ በር ላይ መቆም ብቻ ነው እና በሩን ደግሞ ያው ሌላ ሰው ዛሬ እኛ ሌሎች ስለሆኑ የሚያስተናግዱት እዛ ቦታ ላይ እኛ ለማስተናገድ በጊዜው አልቻልንም
- ንብረት እስኪከር ነው ሌላ ንብረት ላይ የደረሰ ነገር አለ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላ የለም
- ይሄን ነው የሚያውቁት?
- አዎ ይሄን ነው የማውቀው
- እሺ ዋና ጥያቄ አብቅተናል
- እሺ መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ የተከላሽ ጠበቆች
- እሺ አቶ አሊ የዛን እለት ጠዋት የገቡት ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ነው አደል?
- ከሁለት እስከ ሁለት ተኩል በግምት ነው እኔ ሰዓቴን በሰዓቱ አላየሁትም ነበር
- ከዛ ጨርሰው የወጡት ደግሞ ማታ ከአስር ሰዓት በኋላ ነው?
- አይ አድረን ነው እኛ በማግስቱ ነው
- አድረው ነው የወጡት?
- አዎ
- እሺ በዚህ ጠዋት ጀምረው እስከ ማታ ድረስ ያ ሰው ተበተነ እስካሉበት አስር ሰዓት ድረስ ተከሳሾች ቅድም የጠቀሷቸው ሲናገሩ የነበረውን ነገር ሙሉ በሙሉ ሰምተዋል አደል?
- የሰማሁት ይሄንን ብቻ ነው እኔ አሁን የተናገርኩትን
- ይቺን ብቻ ነው የተናገሩት ከዚህ ውጪ ምንም ነገር አልተናገሩም?
- እኔ አልሰማሁትም የዛን ሰዓት እኔ ውስጥም ነው ጩኸትም ስላለ ብዙም አላዳመጥኩም ያዳመጥኳቸውን ነገሮች እነዚህ ናቸው
- እስቲ ቅድም ሲመሰክሩ መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ አይግባ ብለው ተናግረዋል አሉ መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል የሚሉበትን ምክንያት ሲናገሩ አልነበረም?
- መንግስት
- መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ አይግባ ብሎ ሲናገሩ ሰምቻለሁ ብለዋል አደል?
- አዎ
- እና መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገባ ያሉበትን ምክንያት ሲያስረዱስ አልሰሙም?
- አልሰማሁም
- እነሱም አልተናገሩም?
- እኔ ከዛ ወዲህ በደምብ አላዳመጥኩም
- እርስዎ በስንት ሰዓት ነው ይሄን ሲናገሩ የሰሟቸው ?
- ከአራት እስከሚሰገድበት ድረስ ነው ይሄ ንግግር የተደረገው ተራ በተራ እየገቡ
- እሺ ከአራት ሰዓት እስክ መስገድ የሚጀመረው ስንት ሰዓት ነው?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መስገድ ስድስት ከምናምን ነው የሚጀመረው እስከ 7 ያልቃል
- ስድስት ሰዓት ነው የሚጀመረው?
- ሶላት እንደዛ ያልቃል አዎ እሚጀመረው ስንት ሰዓት ላይ ነው?
- መስገድ ስደስት ተኩል
- ስለዚህ እነሱ ከአራት ሰዓት እስከ ስድስት ተኩል ብቻ ነው የተናገሩት?
- ንግግር እስከሚሰገድ ድረስ አዎ
- ከዛ በኋላ ምንም አልተናገሩም?
- ከዛ በኋላ ተሰገደ ከተሰገደ በኋላ ነው
- እነሱ ምንም አልተናገሩም?
- አልሰማሁም
- አልሰማሁም ሳይሆን ተናግረዋል አልተናገሩም ነው እዛው ነበሩ የመጀመሪያውን ሰምተዋል እና ከዛ በኋላ እነሱ አልተናገሩም ካልተናገሩ አልተናገሩም በለኝ ተናግረው ከሆነ ደግሞ ተናግረዋል በለኝ ?
- አልሰማሁም ከዛ በኋላ አላዳመጥኩም እንጂ አልተናገሩም ከዝሁር በኋላ
- መንግስት በሃይማኖታችን ጣልቃ አይግባ ብሎ የተናገረው ማን ነው ከሦስቱ?
- እኔ እንግዲህ ሰወቹ በድምፃቸውም በአካልም አላውቃቸውም እነዚህ እውነተኞም ሊሆኑ ይችላሉ አሁን አቡበክር ነው የሚናገረው ቢለኝ እሱም ላይሆን ይችላል ያ ሰውዬ ዝም ብሎ ሊሆን ይችላል እና ዝም ብሎ ከሰው ነው የሰማሁት እንጂ እዛ ላይ እኔ አላውቃቸውም
- እሺ እነሱ ግን ሲናገሩ
- እስፒከሩ ላይ ግን ሲነገር እንሰማለን
- እሺ መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ አይግባ የሚለውን ነገር የተናገረው ሰው ከመናገሩ በፊት የሚናገረው ማን እንደሆነ ስሙ አልተነገረም አደል?
- እሱ አልተናገረም ሰወቹ አሁን የሚናገረው እገሌ ነው በማለት ነው
- እሺ ምርጫ በመስኪዳችን ብሎ አህመዲን ተናግሯል ብለው ነበር ግን አህመዲን ከመናገሩ በፊት አሁን የሚናገረው አህመዲን ነው ተብሎም አልተነገረም በድምጽ ማጉያው አደል?
- እኔ አልሰማሁም እሱን አላዳመጥኩም አጠገቤ ያሉት ሰወች አጋጣሚ እነሱ ሲናገሩ ነው እንጂ እዛ በእስፒከሩ ላይ ሲዘረዝር እኔ አልሰማሁም
- ምርጫ በመስኪዳችን ብሎ አህመዲን ሲነገር ግን ሰምተዋል ?
- አዎ እሱን ሰምቻለሁ በእስፒከሩ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በእስፒከሩ ስሙ አልተነገረም በእስፒከሩ አልሰሙም?
- በእስፒከሩ ብቻ ነው እኔም የሰማሁት
- እኮ በእስፒከሩ አህመዲን ስሙ አልተነገረም አልሰሙም እሱን አደል?
- እሱን አላዳመጥኩም እኔ እነሱ ላይ አሁን እገሌ ነው የሚናገረው ካሉ በኋላ በዛ ነው እኔ
- ምስክር ቆዩ እስቲ ተመልሷል ይሄ እኮ አጠገቤ ያሉ ሰወች ነገሩኝ ማን ይሁን አለየሁትም ብለዋል
- እሺ ለኃይማኖታችን እንታገላለን ብሎ ያሲን ኑሩ ተናገረ ብለዋል አሁን ለኃይማኖታችን እንታገላለን የሚለውን ነገር ከመነገሩ በፊትም ያሲን ኑሩ ነው አሁን የሚናገረው ተብሎ አልተነገረም አደል?
- አልሰማሁም እኔ እሱን እሱን እንትን አላልኩም እኔ አጠገቤ ያሉትን ሰወች ነው እንጂ ሌላው ጩኸት እና እንትን ስላለ አልሰማሁም
- ከጠርን እዛው ድረስ እንሄድላቸዋለን ሲሉ የጠሩን ያሉት እነማንን ነው ፖሊሶችን ማለታቸው ነው?
- በመንግስት በኩል ከተጠራን እንሄዳለን የሚል ይመስለኛል እኔ በግምት
- እንጂ ማን እንደጠራቸውም አልተናገሩም?
- ጠራን አደለም እኮ ከጠሩን እንሄዳለን ነው
- እኮ ማን ነው የሚጠራን የሚለውንም ነገር አልተናገሩም እነሱ?
- አይ እኔ አልሰማሁም
- እሺ ከዚህ ውጭ ምንም የተነገረ ነገር የለም አደል አሁን ቅድም ያሏቸው ?
- እኔ ከዚህ ውጭ የሰማሁት ያዳመጥኩት ነገር የለም
- እሺ ከዛ በፊት አይፓዷ ክፍት ነች እንዴ
- አቶ አለ ቅድም ፍተሻ ያደርጉ የነበሩት ወጣቶች ናቸው ብለዋል በምን አወቁ ወጣቶች መሆናቸውን?
- ወጣቶችማ መሆናቸውን በአይኔ እያየሁ ነው ወጣት የሆነውን በአይኔ የማየው ነገር ነው
- አሃ ፊታቸውን እያዩ?
- አሃ በር ላይ እየፈተሹን እያስገቡ እንዴት እኔ በአይኔ እያየሁ አደለም እንዴ
- አሃ እርስዎ ቆርቆሮ ቤት ውስጥ ነበርን ስላሉ ፍተሻው የትጋ ነበር የሚካሄደው?
- በር ላይ ነዋ ፍተሻው ቆርቆሮው እኮ ወደ ውስጥ ገባ ብሎ ነው
- እኮ እርስዎ የነበሩበት ቦታ ነው?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አም በሩ አካባቢ ነው
- እናንተ እዛው ቆርቆሮ ቤት ውስጥ ነበራችሁ?
- አም
- እስከ መጨረሻው እዛ ነበራችሁ?
- አም እስከ መጨረሻው
- እስከ አስር ሰዓት?
- አም ሰው እስከሚወጣልን ድረስ የሰገድነውም እዛው
- አሃ ስለዚህ እርስዎ ከነበሩበት ቦታ እንጂ ሌላ ቦታ ፍተሻ ይኑር አይኑር ባይኖ አላዩም?
- አይ ሁሉም ቦታ ተፈተሸ የሚሉ ጓደኞቼ ሲናረሩ እንጂ እኔ በየቦታውማ አልሄድኩም ከዛ ቦታ አልተነቃነቅኩም ሰው እስከሚወጣ ድረስ
- አሃ እርስዎ እና በወቅቱ የነበሩት ጥበቃዎች ናችሁ አደል እዛ ቆርቆዋ ቤት የነበራችሁት?
- አም ተረኞች የነበሩ
- ቅድም ጓደኞቼ የሚሏቸው ?
- ከማይካ ጠጋ ብለው ይመልሱ እሺ ቀጥሉ
- ቅድም ጓደኞቼ ነገሩኝ የሚሉት እነዚህ የጥበቃ ሰራተኞት ናቸው አደል?
- አም
- ስለዚህ ሁላችሁም የጥበቃ ሰራተኞች ወይም የእርስዎ ጓደኞች እስከ መጨረሻው ቆርቆሮ ቤት ውስጥ ከነበራችሁ በየቦታው በየ መግቢያ በሩ ላይ ፍተሻ ይደረግ አይደረግ ከመገመት በስተቀር እንዴት ልታውቁ ትችላላችሁ?
- እኔ እኮ የገባሁበትን ብቻ ነው የማውቀው የሌሎችንማ እንግዲህ አላውቅም በሌላዉ በር ላይ ያለውን አላውቅም አሁን ለምሳሌ እነሱ ሲገቡ ምን ሲሉ
- በቃ በቃ ይበቃል ምስክር
- ጥሩ ቅድም ሰው ይሄ እነያሲን ሲናገሩ ያዳምጥ የነበረው ሰው ምንድን ነው ቁጭ ብሎ ነው ቆሞ ነበር የሚያዳምጣችሁ?
- ቆሞ ነው ሜዳ ላይ ነው ሰው ሜዳውን በሙሉ ቆሞ ነው ያለው
- እስከ አስር ሰዓት ድረስ ቆመ?
- አይ ከተሰገደ በኋላማ እየቀነሰ ሄደ ሰው
- ማለት አሁን እስኪደሰገድ ከሁለት ሰዓት ጀምሮ ነው እርስዎ ያዩት
- ከሁለት ሰዓት ጀምሮ በቃ ሙሉ ነው በቃ ቦታው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከሁለት እስኪሰገድ ድረስም ቆመ?
- አም
- ከዛ ከተሰገደም በኋላ እስከ አስር ሰዓትም ቆመ ?
- አም እዛ መስኪድ እኛ አልገባንም አሁን ወጡ ሲሉን ሄድን መስኪድ ስንገባ ያው አንዳንድ ሰወች የቀሩ ናቸው እስፒከሩን አየን ያው እንደ መሪ ገቢ ሆነን በቃ ይሄ ነው
- አቶ አሊ ፕሮግራሙ ካለቀ በኋላ ሰው በሰላም ነው አደል የተበተነው ?
- አም
- በር ላይ ፍተሻ ይደረግ ነበር ብለዋል የሚፈትሹት ሰወች ለምን ነበር ሲፈትሹ የነበረው?
- ለምን ነበር ሲፈትሹ የነበረው?
- አም
- እኔ እሱን ምክንያቱን አላውቀውም
- እስክሪፕቶ ሲቀበሉ እና ሲያስቀምጡ ነበር ብለዋል እና የት ነበር ?
- ማስቀመጥ ሳይሆን እያንዳንዱ ላይ እስክሪፕቶ መግባት አይችልም እያሉ እኔም እራሴ ከኔ ወስደዋል
- እኮ ወስደው የት ነው ሲያስቀምጡ የነበረው?
- እሱን አላውቅም ከዛ በኋላ የተመለሰ ነገር የለም
- መሬት ላይ የተሰበሰበ እስክሪፕዎችን አላዩም ሲገቡ?
- የተሰበሰ የለም በእጁ ነው ይረከቡናል በቃ መግባት ነው
- እሺ ሞባይል እያሉ ነበር ብለዋል እና የት ነበር የሚያስቀምጡት?
- ማስቀመጥ ሳይሆን እስክሪብቶ መግባት አይችልም እያሉ እኔም እራሴ ከእኔ ወስደዋል
- እኮ ወስደው የት ነው ሲያስቀምጡት የነበረው ?
- አይ እሱን አላውቅም ከዛ በኋላ የተመለሰ ነገር የለም
- መሬት ላይ የተሰበሰበ እስክሪፕቶዎችን አላዩም ሲገቡ?
- የተሰበሰበ የለም በእጁ ነው ይረከቡናል በቃ መግባት ነው
- እሺ ሞባይል እያዩ ነበር አደል?
- ሞባይል ወዲያውኑ ከፈት አርጉ ያዩና ያስረክባሉ
- ሰዉ ሲወጣ እስክሪፕቷችሁን ውሰዱ የሚል ሰው አልሰሙም?
- አልሰማሁም
- ፕሮግራሙ አስር ሰዓት ነው አደለም ያለቀው?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በግምት እንደዛ ይሆናል የሚል ነው ሰዓቱን ስላላየሁት
- ኦኬ እርስዎ ስንት ሰዓት ነው ወደ መስኪድ የገቡት መስኪድ ገብተው አይተዋል እንዴ?
- የእስፒከሩን እንትን
- አዎ?
- አዎ አይቻለሁ በአይኔ ነው ያየሁት እሱን
- ስንት ሰዓት ገብተው አዩ?
- ያው አስር ሰዓት ይሆናል በግምት መጨረሻ ላይ ሰው ከወጣ አስር ሰዓት ይሆናል እዛ ስንገባ ያን እስፒከሩን ምን ጊዜም ፈትሸን ስለ ንብረት መቆጣጠር ስለሚገባን ሌላ ሰው ያ መአዘኖቹ ን ከፍቶ እነደሚገቡ ሳይሆን አሁንም ጀምሮ
- ትክክል አሁን እርስዎ ሰው እስኪወጣ በር ላይ ነው አደልም የሚቆዩት?
- አዎ እኛ ምን ጊዜም በር ላይ ነው የምንቆመው
- በር ላይ ነው የቆዩት ስለዚህ ሰው ወጥቶ ካለቀ በኋላ ነው ገብቶ ያዩት አይደለም ሰው ወጥቶ ካለቀ በኋላ ወይም መስኪዱ ባዶ ሲሆን ነው አደለም ገብተው ለማየት የቻሉት?
- አዎ
- ስለዚህ እርስዎ በገቡበት ሰዓት እና ሰው ወጥቶ ባለቀበት ሰዓት ምን ያህል ሰዓት ክፍተት ነበረ በመሃል የምን ያህል ደቂቃ ወይም የምን ያህል ሰዓት ክፍተት ነበረ?
- ሰው እኮ አለ በሰዓቱ ግን አልፎ አልፎ ሌሎች ሰወች እኮ አሉ
- ሰው እኮ አልፎ አልፎ ይኖራል ግን እርስዎ አሁን ለማለፍም ብዙ ሰው ነበር ስላሉ ለማለፍም የተወሰነ ክፍተት አግኝተው ለመግባትም ጊዜ እስኪያገኙ እና ሰው ወጥቶ የተወሰነ ክፍተት እስኪያገኙ ድረስ ምን ያህል ደቂቃዎች ነበሩ?
- እኛ አሁን እስከሚያልቅ ድረስ ያው እንትን እስከሚል ድረስ ያንን ጠበቅን እንጂ ይሄንን እኔ አላስታውሰውም
- ስለዚህ ሰው ከወጣ በኋላ በመሃል ምን እንደተደረገ አያውቁም አደል?
- አዎ
- ተሰበረ ያሉት የማይክራፎን ስቀመጫ ሳጥን ቁልፍ ነው አደል?
- ሁል ጊዜ ቁልፍ ነው ሙአዚኖች ከፍተዋት ነው
- ቁልፍ ነው ተሰበረ አደል ያሉት?
- አዎ ቁልፍ ብቻ ነው
- ማን እንደሰበረ አያውቁም አደል?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አላውቅም
- አሊ
- አቤት
- ቅድም ሲጠየቁ አቡበክርም አህመዲንም ያሲን ኑሩ እኔ አላውቃቸውም ነገር ግን ሲናገሩ ከጐኔ ያሉት ሰወች ናቸው የነገሩኝ ብለው ነበረ በሌላ መልኩ ደግሞ እዛ ቆርቆሮ ቤት ነበርን ብለዋል የነገሮት ሰወች እዛ ጥበቃ ቤት ውሰጥ የነበሩ ሰወች ናቸው?
- በር ላይ እኮ ነው እኛ ያለነው ያው ጥበቃ በር ላይ ነው በሯ ላይ ሆነን ነው
- ከጐኖ ያሉት ሰወች ነገሩኝ ስላሉ እነማን ናቸው እነዚህ ሰወች እስቲ?
- እኔ አላውቃቸውም ሰወቹን
- ሰወቹን አያውቋቋቸውም?
- አዎ ሰው እኮ በጣም ግጥም ብሎ ሞልቶ አሁን ዝም ብሎ እንደዚህ ነው ምንድን ነው እያለ እየተናገረ ነው እንጂ እኛ ለይተንም በሰዓቱ ደግሞ እኛ እንደዚህ አይነት አላሰብነውም
- ስለዚህ ሰወቹ በደምብ አያውቋቸውም?
- አላውቃቸውም
- የነገሮት ነገር እርግጠኛ መሆኖን ያውቃሉ እንዴ ታዲያ ?
- ሰወቹ እንደዚህ ብለው መናገራቸውን
- አደለም የነገሮት ሰወች እውነት ይንገሮት ሃሰት ይንገሮት እርግጠኛ መሆን ይችላሉ?
- እሱን አላውቀዉም
- ንግግር ሲያደርጉ የት ሆነው እንዳደረጉ ያዉቃሉ?
- መስኪድ ውስጥ ነዋ
- የቱጋ ሁለት መስኪድ ነው ያለው?
- ትልቁ መስኪድ
- ምኑጋ ?
- አወልያ ሶፍ ላይ
- እሚያስተዋውቅ ሰው ኦኬ አልነበረም እሺ ትቼዋለሁ እሱን ቅድም ሕዝቡ አላህዋክበር ይል ነበረ ብለዋል አደለም
- ሕዝቡ
- አዎ
- እ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እነ አቡበክር ሲናገሩ እርስዎ እንዳሉት አላህዋክበር ይል ነበረ ብለዋል ሰው አደል ?
- አዎ ያደርጋል ሰው
- ድጋፍ ነው አደል ይሄ ነገር ?
- እኔ አላውቅም እሱን እንግዲህ ምክንያቱን እኔ እሱን አላውቅም ድጋፍ ነው ግን እኔ አላውቅም
- አዎ ድጋፍ ነው
- እየመለሱ ነው የምስክሩን መልስ ብቻ ነው የምንፈልገው
- ቅድም በተከበሩ አቃቤ ሕግ ሲጠየቁ ከመቼ ጀምሮ እንደዚህ አይነት ነገር እንደተጀመረ አላውቅም ብለዋል አደል ይሄ ነገር ቆሟል አሁን?
- አሁን የለም እንደዚህ አይነት ፍተሻ እና እንትን የለም
- ፍተሻ አደልም እንደዚህ አይነት አላህዋክበር የሚል እንትን አንዋር አካባቢ የለም ?
- አርብ ቀን አለ መሰለኝ እንጃ ደርሶኝ አላውቅም ግን
- አርብ ቀን ነበረ ?
- ነበረ ሲባል እሰማለሁ
- አርብ ብቻ ነው የሰሙት?
- ሌላ ቀን የለም
- ማለቴ አርብ አርብ ቀን የለም ሌላ ጊዜ የምሉት ቀኑን ሳይሆን በተለያየ አርብ ቀን ነው ያለው ወይስ አንድ አርብ ብቻ ነው እርስዎ የሰሙት ነው?
- እኔ እራሴ አልሰማሁም እኮ አሁን በቀደም አሁን ተባለ ተክቢራ ተደረገ ሲባል ነው የሰማሁት እንጂ እኔ የለሁም ተረኛ አደለሁም በሰዓቱ
- ምርጫችን በመስኪዳችን ብለው ነበረ ቅድም ብለዋል አደል ይሄ ምርጫ ተካሄ መስኪድ ያሉት?
- ምርጫው ተካሂዷል
- የፊቶቹ አመራሮች ወርደዋል አደል መጅሊሶች?
- ወርደዋል አዎ
- በሕዝብ ጥያቄ ነው አደል የወረዱት?
- ይሄን እንቃወማለን የተከበረው ፍ/ቤት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይቀይ ከዛ በፊት ተቃውሞ ከቅረቡ በፊት ይዤ ግልጽ ነው ባለፈውም ተናግረናል ይሄ አሁን ምርጫ መደረጉን ምናምን መደረጉ እሱ በጣም ክሊር ነው /ግልጽ ያልሆነ/ በሚዲያ ሁሉ የቀረበ ነው ምንድን ነው ግልጽ ያልሆነው
- /ግልጽ ያልሆነ/ ለመግለጽ ነው እሺ
- ፈታሾች ሲፈትሹ ስለታማ ነገር ያስገቡ ነበር?
- የለም አላየሁም በአይኔ
- መሣሪያስ ያስገቡ ነበር ያሳልፉ ነበር ሲፈትሹ?
- አረ መሣሪያ ምናምን የለም
- እ?
- እየፈተሹ በቃ መግባት የሚገባው መግባት ብቻ ነው
- የሚከለክሉት ሰው አልነበረም?
- የለም
- አቶ አሊ ወቅቱ እርስዎ ያሉት ሐምሌ 8 የፆም ወቅት ወይም እረመዳን ወቅት ነበረ አደል?
- አደለም
- እረመዳን አልነበረም?
- እረመዳን አደለም እሱን አላስታውስም እረመዳን መሆኑን
- ድምጽ ከፍ አድርገው
- አሃ እረመዳን መሆኑን አያስታውሱም?
- እኔ አላስታውስም
- ቅድም ሕዝቡ በዛን ሰዓት እንደዚህ ሞልቶ አያውቅም የሚል ነገር ተናግሯል አንዋር መስኪድ ሁል ጊዜ በሕዝብ የተሞላ አደለም እንዴ ?
- አይ በዛን ሰዓት ማለቴ ነው
- በየትኛው ሰዓት ?
- በሁለት ሰዓት ተኩል ላይ እንደዛ ሕዝብ ሲሞላ አይቼ አላውቅም እስካሁን ድረስ
- ለትምህርትም ለተያየ ነገር በሁለት ሰዓት የሚገባ የለም አንዋር?
- በሁለት ሰዓት እንደዛ የሚሞላ ጊዜም የለም ምናልባች አንዳንድ ጊዜ እረብኢል አወል ከሆነ ነው የመውሊድ ጊዜ ምናልባች እንደዛ ጊዜ ካልሆነ በስተቀር እሱም ደግሞ ቀስ ብሎ አራት ሰዓት ምናምን የሰው እንትን እያለ ነው ቀስ እያለ ነው የሚገባው የዛን ጊዜ ግን ሰው በጣም ብዙ ነው እና አዲስነገር ነው እኔም የዛን ሰዓት የሆነብኝ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ አቃቤ ሕግ
- ቅድም ሲጠየቁ ፍተሻው የት የት ነበረ የሚደረው ሲባሉ እኔ የገባሁበትን በር ነው የማውቀው ብለዋል ሲገቡ አላዩም ሌሎች በሮች ፍተሻ እየተደረገ እንደሆነ ስንት በር ነው ያለው አንዋር መስኪድ ?
- አምስት በር ነው ያለው
- እርስዎ ሲገቡ አላዩም ሌሎች በሮች ፍተሻ እየተደረገባቸው እንደሆነ?
- እኔ አላየሁማ ቀጥታ ከዛ እዛ ቤት ነው የገባሁት እና ሌላ ቦታ ፍተሻ ነበረን ብለው ሌሎቹ ነግረውኛል እንጂ እኔ በየበሩ አልሄድኩም
- ለምሳሌ ሴቶች ከናንተጋ እየተፈተሹ ይገቡ ነበር?
- በዚህ ሴቶች የሉም
- አልነበሩም በእናንተጋ?
- አዎ ወንድ ብቻ ነው በእኛ የምንገባበት ወንዶች ነው ሴቶች በሴቶች ቦታ ላይ ነው
- መጨረሻ ላይ ሲበተኑ በሰላምነው የተበተነው ወይ ስትባሉ አዎ ብለዋል ምን ተብለው ነው መጨረሻ ላይ የተበተነው የተላለፈ መልክት የለም ?
- የተላለፈ መልክት እኔ ይሄንን ያህልነው የማውቀው
- መጨሻ ላይ ሲዘጋ ፕሮግራሙን ሲዘጉ ያስተላለፉት መልእክት የለም ?
- ያው ይሄንን ንግግግ ካደረጉ በኋላ ያው ወደ ስግደት ተሄደ ተሰገደ
- መስክሩ ወደዚህ
- እሺ
- አያስታውሱም?
- አላስታወስኩም
- አሁንስ ቀጥሏል ወይ ሲባሉ አርብ ለታ ተክቢራ ተደርጓል ሲባል ሰምቻለሁ አሉ እዛው እየሰሩ ነው አደል እርስዎ?
- አዎ ተረኛ አልነበርኩም ለማለት ፈልጌ ነው
- አይ አደለም አሁን በተደጋጋሚ ከዛ በኋላ ብዙ ጁምአ ተላልፏል አደል ተደርጓል ?
- እ?
- ብዙ ጁምአ ተደርጓል ከዛ በኋላ አደል አሁን እርስዎ ከነገሩን ከሐምሌ 8 በኋላ?
- አዎ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስቲ አሁን የአርቡ ጥያቄ ምን ይሰራላችኋል የወንጀል ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላም ያው ቅድም ምልባት ስለተባለ ነው እንጂ አሁን እናንተ ምንድን ነው
- እሺ አብቅተናል
- እሺ እናመሰግናለን ጨርሰዋል ይመስሱ
- በእውነት ለመመስከር
- በእግዚአብሔር ስም
- ምያለሁ
- እሺ ለምስክርነት ነው የመጡት የአባቶን ስም ሳይጨምሩ የራሶን ስም ብቻ ነው የሚገልፁልን በዚህ መሰረት ማን እንበል?
- ተስፋዬ
- ስንተኛ ናቸው አቃቤ ሕግ?
- 88ኛ የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ በፍ/ቤቱ በተሰሙት ቅደም ተከተል 44ኛ ላይ ደርሰናል እሺ አቶ ተስፋዬ ለምስክርነት ነው የመጡት?
- አዎ
- እሺ በነማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?
- እኔ በ14/10/2004 ዓ.ም.
- በሰው ላይ ለይተው የሚመሰክሩት ነገር አለ?
- በሰው ላይ የምመሰክረው የለኝም
- 14 ምን?
- 14/10/2004 ዓ.ም. ስለነበረው ሁኔታ
- ሰኔ ነው?
- ሐምሌ
- 14/11 ዓመተምረቱ
- 14/10/2004
- ሐምሌ ነው?
- ሐምሌ
- እሺ አመተምረቱ መቼ ነው ?
- 2004

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ?
- በዛን ጊዜ የነበረውን ሁኔታ ነው እኔ የምመሰክረው
- እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለ
- እሺ ተቃውሞ ምንድን ነው
- አሁን በዚህ ደረጃ ተቃውሞ የለም
- አይ ከጭብጥ አንፃር የምናነሳው
- ቆይ ሌላ አቤቱታ ካሉ
- ጭብጥ ላይ አሁን እሳቸው ስለ 14/11 ስለ ሐምሌ 14 ነው የምመሰክረው ነው ያሉት ተከሳሾች የተከሰሱበት ጉዳይ በሙሉ ሐምሌ 8 ላይ ነው የሚያልቀው ከሐምሌ 8 በኋላ ስለላ ጉዳይ አልተከሰሱም ስለዚህ ባልተከሰሱበት ጉዳይ ላይ ምስክሩ ሊመሰክሩ አይገባም
- ሐምሌ ስንት ነው የሚያልቀው?
- ሐምሌ 8 ላይ ያልቃል የመጨረሻው ሐምሌ 8 ነው የሚያልቀው ክሱ ላይ ያለው አሁን እሳቸው ስለ ሐምሌ 14 ነው የሚመሰክሩት ይሄ ከተሰሱበት ጉዳይ ውጪ ሰለሆነ ምስርነቱ ሊሰማ አይገባም
- እስቲ ምስክር ሁለት ነገር እየተናገሩ ነው እና የትኛው ነው ሐምሌ 14 2004 14/10 ብለዋል ነገር ግን ወሩን ሐምሌ ነው እያሉ ነው 10ኛ ወር ሰኔ ነው የሚታወቀው 11 ሐምሌ ነው የትኛውን ነው ማለት የፈለጉት ግልጽ አርጉ እስቲ አሁን እየተናገሩ ያሉት
- ከተቻለ መረዳት ይቻላል
- እኮ መቼ ነው ትክክለኛ ቀኑ?
- 11ኛ ወር ሐምሌ
- ቀኑ መቼ ነው?
- ቅዳሜ ቀን
- እና ቀኑ መቼ ነው አያስታውሱትም?
- አስታወስኩት እኮ
- እኮ ቅዳሜ ቀን ቀኑ ስንት ቀን ነው?
- 14
- ሐምሌ 14?
- ሐምሌ 14

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስቲ ሐምሌ 8 ያለው ነው በክሱ ላይ ያለው ከክስ ውጪ ነው ምስክሩ
- ክሱ ላይ ያው የተከበሩ ጠበቃ ምናልባት ካላዩም 22ኛ 23ኛ ተከሳሽ ላይም አለ እስክ ሐምሌ 18 ድረስ ለምሳሌ ከጥር 7 ቀን 2004 ዓ.ም. ጽፈናል
- እክሱ ውስጥ የተካተተ ነው እያልክ ነው ሌላ ነገር አለ የምትጨምረው?
- አዎ የተከበረው ፍ/ቤት በግልጽ ክሱ ላይ እኮ ተቀምጧል
- ክሱ አለ በቃ እኛ እናነበዋለን
- አዎ ማለት ካላዩት ምናልባት ስላላዩት ሊሆን ይችላል አለ ቅስቀሳው እስከ ሐምሌ 18
- ቆይ አሁን አትናገሩ ብንለው ምስክሩ እንዳይናገር ቀድሞ መናገር ስለዚህ እኛ እናየዋለን ቀጥሉ እናንተ
- እሺ ምስክሩ ክሱ ላይ ከሌለ ውጪ የተጠራ ነው መሰማት የለበትም አግባብነት የለውም የሚል ቀርቧል በአቃቤ ሕግ በኩል እስከ ሐምሌ 18 ክሳችን ላይ አለ የሚል ነገር ተነስቱቷል በእርግጥም ክሱን ስናየው ከጥር 7 ቀን እስከ 2004 ጀምሮ እስከ ሐምሌ 18 ቀን 2004 የሚል ሌሎችም አሉ ክሱ ላይ ያልተካተቱ ነገሮች ስለዚህ አሁን በተጠቀሰው ቀን ከሆነ ተቃውሞ ቀኑን በክሱ ውስጥ የተካተተ ነው በመሆኑም በዚህ ቀን መቃወሚያ የቀረበው ክሱ በሙሉ ባለማገናዘብ በመሆኑ ክሱ ላይ ያለ ፋክት ነው አሁን የተነሳው ስለዚህ ተገቢነት አለው ይቀጥል በለናል
- እሺ ላጅን ይቀጥሉ የምመሰክርበት ቀን ብለው ሐምሌ 14 ቀን 2004 ብለዋል ምንድን ነው የሆነው በዚህ ቀን?
- በዛ ቀን የሆነው እኛ ሥራ ላይ ነበርን ቅዳሜ ቀን ነው እዚህ አንዋር መስኪድ አካባቢ ችግር አለ ተባልን ከኔጋ የነበሩትን አባሎች ይዤ አንዋር መስኪድ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል አመራን
- ስንት ሰዓት ላይ ነው?
- በግምት ስምንት ሰዓት ይሆናል ከዛ እንደደረስን ግርግር አለ ሁከት ግርግር ነበረ እሱን ተረጋጉ እያልን እያለ እኔ ላይ በሰውነቴ ክፍል 4 ቦታ ላይ በድንጋይ ጉዳት ደርሶብኛል
- እሺ ችግር አለ ተብለን ሄድን አሉ ችግር አለ ብሎ ማን ነው እሪፖርት ያረገላችሁ?
- እዛው ቦታው ላይ የነበረ አሬዲዮ የያዘ
- ምን ብለው እሪፖርት አረጉላችሁ?
- ኃይል ይጨመርልን ሁከት ግርግሩ ጨምሯል ድረሱልን የሚል
- ምን ጨምሯል ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሁከት ግርግሩ ጨምሯል ከአቅማቱን በላይ እየሆነ ነው እና ድረሱልን የሚል
- ሁከት ግርግሩ በምን ምክንያት ተነሳ እናንተ ደርሳችሁ ስታጣሩ ወይም ደግሞ ከዛ በኋላ ባጣራችሁት በምን ምክንያት የተነሳ ነው?
- ያው ኃይማኖታዊ ጉዳይ ነው የሚል
- እዛ በተገኙበት የሰሙት ነገር አለ በተገኙበት ጊዜ የሰሙት ነገር ?
- የሰማሁት ያው አላህዋክበር እየተባለ ዲንጋይ ይወረወር
- ከየት ነው ድንጋይ የሚወረወረው?
- ከግቢ ውስጥ
- ከየት ጊቢ?
- ከአንዋር መስኪድ
- ለምን ነበረ ድንጋይ የሚወረወረው ?
- ሂዱ እናንተ አታስፈልጉም የሚል ድንጋይ ውርወራ ነበረ እኛ ደግሞ ተረጋጉ እንል ነበር
- ማንን?
- ፖሊሶቹን ማለት ነው
- እሺ?
- እና ተረጋጉ እያልን እያለ እኔ ላይ ግራ ደረቴ ላይ እና ቀኝ ጆሮዬ ላይ ጉልበቴ ላይ እና ጣቴ ላይ ጉዳት ደረሰብኝ ከዛ ወደ ህክምና ሄድኩኝ
- እናንተ ላይ ድንጋይ መወርወር የመጣው እናንተ የወሰዳችሁት የኃይል እርምጃ አለ?
- የለም
- ስለዚህ ለምንድን ነው ወደናንተጋ ድንጋይ የተወረወረው ?
- እኛ ተረጋጉ እንል ነበረ እና ተረጋጉ እያልን ባለበት ቅጽበት ነው ይሄ ሁሉ እኔ ላይ ጉዳት የደረሰው
- የትጋ ሆናችሁ ነው ጉዳት የደረሰቦት እርስዎ ?
- በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ባለው በር
- ከአንዋር ምን ያህል ይርቃል?
- አንዋር በሩ ላይ ነው ምናልባት በግምት ማሳየት የሚቻል ከሆነ እንደዚህ ነው በሩ እኛ እዚህ ላይ ነበርን
- እርቀቱ አሁን ከተቀመጡበት እስከ ውጪ ድረስ
- በግምት ስንት ሜትር ይሆናል ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በግምት አንድ ሜትር ሁለት ሜትር ከ1-2 ባለው ይሆናል አዎ
- እሺ ቀጥሉ
- እህ እናንተ ያላችሁት የት ነው ከግቢው ውጪ ነው?
- ውጪ ነው አዎ
- እሺ እርስዎ ላይ ምንድን ነው የደረሰው ጉዳት ይንገሩን እስቲ?
- አንደኛ በቀኝ ጆሮዬ በኩል 2ኛ ግራ ደረቴ ላይ 3ኛ የቀኝ ጣቴ መሃል ጣቴ እና 4ኛ ግራ ጉልበቴ ላይ ነው ጉዳት የደረሰብኝ
- እነዚህ አራት የተለያዩ ድንጋዮች ናቸው ?
- አዎ
- ከማን ነው የተወረወረው አውቀዋል እነማን ናቸው እነዚህን ድርጊት የፈፀሙት ?
- በመልክ አለየሁም ግን ከዛ ከሳርግሩ አካባቢ መሆን ለማየት ችያለሁ
- ምን በጉዳት ደረጃ ምን ደረሰቦት ያን ቀን አሁን ተመታሁ ብለዋ ልበስራ ቀጠሉ ከተመቱ በኋላ?
- ወደ ሕክምና ነው የሄድኩት
- ለምን ?
- ለሕክምና
- እኮ ጉዳት ምን ያህል ጉዳት ማርሶቦታል?
- ያው እንግዲህ በሕክምናው የሚገለጽ ነው የሚሆነው
- እኮ ይንገሩን ምን ያህል ጉዳት አንደደረሰቦት በሕክምና
- እርስዎ የሚያውቁትን እርስዎ የደረሰውን የጉዳት መጠን ይግለፁነው ሌላ ነገር የለም?
- መጠኑ አሁን ጆሮዬ በቀጠሮ ላይ ነው ያለው እስቲል ያመኛል ደረቴ ላይም በተመሳሳይ በክትትል ላይ ነኝ ያለሁት ጉልበቴ እና ጣቴ ላይ ያለው ተሽሎኛል በአሁን ሰዓት
- እስከ አሁን ሕክምና እየተከታተልኩ ነው አሉ?
- አዎ እስከ አሁን ሕክምና እየከታተልኩ ነው
- እሺ ዋና ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ መስቀለኛ ጥያቄ የተከሳሽ ጠበቆች
- ሳጅን አቃቤ ሕጉ ስላሉት ነው ያልኮት ቀኝ ደረቴ ተመቷል ጣቴ ተመቷል ሕክምና ላይ ነኝ ብለው ነበረ ልክ ነኝ ?
- ሕክምና እየተመላለስኩ ነው ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የት ነው የሚታከሙት?
- በግል ሆስፒታል
- የት ?
- ቦታውን
- አም የት ሆስፒታል ካርድ ቁጥሩን ለፍ/ቤቱ ይግለፁ?
- ካርድ ቁጥሩን ለጊዜው አልያዝኩትም
- እሺ የት ሆስፒታል?
- አንደኛው ፖሊስ ሆስፒታል ነው ሁለተኛው በግል እዛው ጣቢያችን አካባቢ ባለ ክሊኒክ ሕክምና እየተደረገልኝ ነው
- እነዚህ ሕክምና የሚያደርጉ አካሎች አጠቃላይ የምርመራውን ውጤት አልነገሮትም?
- አልነገሩኝም በተለይ የቀኝ ጆሮዬ ገና ወደፊት ሌላ የሚሰራ ነገር እንዳለው ገልፀውልኛል
- ፖሊስ ነው የገለፀሎት?
- አዎ
- ካርድ አሎት ወይ ትክክል እዛ?
- አዎ
- ክሊኒኩ የት ነበር አሉ?
- እዛው እኛ አካባቢ አለ ክሊኒክ ፈርስት ኤድ ተደረገልኝ ከዛ በኋላ ወደ ፖሊስ ሆስፒታል ሄድኩልኝ
- ግርግር ነበረ ያሉት አንዋር ምኑን ነው ግርግር ያሉት አላህዋክበር ሲሉ ነበር ነው ያሉት ከዚህ ውጭ ነበር?
- ከዛ ውጪ የነበረው ቅድም እንደገለጽኩት ድንጋይ መወርወር ነበረ በድንጋዩም ተጐድቻለሁኝ እኔ
- ኃይል ተጨምሮ ተጠራን ብለው ነበረ ምን ይዛችሁ ሄዳችሁ እናንተ?
- ምንም መደበኛ የፖሊስ ዱላ ይዘን ነው የሄድነው
- እሺ በዱላው አልተጠቀማችሁም?
- አልተጠቀምንም
- ሰው ተው ብቻ ስትሉት ተወ ሰው ተረጋጋ?
- ተው እያልናቸው እያለ ድንጋዩ እንደተወረወረብኝ ነው ከዛ በኋላ ያለው ሁኔታ እኔ ሕክምና ላይ ስለነበርኩ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተመተው ሄዱ እርስዎ?
- አዎ እኔ ተመትቼ ሄጃለሁ
- በዚህ እለት ፖሊስ ሰወችን መደብደቡን አያስታውሱም አያውቁም?
- አላስታውስም አላውቅም
- ወደ ሰንዳፋም የወሰዳቸውን ሰወች አያውቁም?
- አላውቅም
- በወሬስ ደረጃ አልሰሙም?
- አልሰማሁም
- ሳጅን ጆሮዬ ላይ ጉዳት ደርሷል ብለዋል አሁን ያለመሣሪያ ነው አደል እዚህ እየመሰከሩ ያለው በጆሮ ላይ መሣሪያ አለ እንዴ አሁን?
- የለም
- ተጨማሪ ኃይል መጣልን ብለዋል እና ፌደራል ፖሊስ መጣ?
- እኔ ያልኩት እኛ ጣቢያ መደበኛ ስራ ላይ ነበርን መስመር ላይ የእኛ ልጆች ነበሩ ኃይል ይጨመር ያሉት የእኛ ኃይል እንጂ የፌደራል ፖሊስ አባል አደለም
- መጨመሩን ያውቃል እርስዎ መምጣቱን የፌደራል ፖሊስ ያውቃሉ አያውቁም?
- እኔ አላወቅኩኝም በወቅቱ ቅድም እንደገለጽኩት ጉዳት ደርሶብኝ
- በቃ ይበቃል
- ለአቃቤ ሕግ የሕክምና ማስረጃዎችን ሰጥተዋቸዋል እንዴ?
- ገና ሂደት ላይ እንዳለ ቀደም ብዬ ገልጫለሁ
- ጨርሻለሁ
- ሳጅን እርስዎ እና የእርስዎ ቡድን እዛ ሲደርስ ነው እንትኑ የተጀመረው ወይስ ተጀምሮ ነው የደረሳችሁት ድንጋይ መወርወር ?
- እኛ ስንደርስ ተጀምሮ ነው የደረስነው
- እንጂ ምክንያቱ መንስኤው መጀመሪያ አካባቢ ስላልነበሩ አያውቁም አደል ለምን ወደዚህ ውስጥ እንደተገባ?
- ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ድረሱልን የሚል ነገር ነበር ደረስን ድረሱልን ሲባለ የተጀመረ ጉዳይ ነው
- እኮ እዛም ሄደው መንስኤው ምን እንደሆነ ሰው ድንጋይ ለመወርወር ምን እንደገፋው አልጠየቁም አደል በወቅቱ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለመጠየቅ አልቻልንም
- እሺ ሳጅን ተስፋዬ ጉዳት ደረሰብኝ ካሉ በኋላ ወደ ስራ የተመለሱት መቼ ነው ?
- ልድገመው?
- አዎ
- ወደ ስራ መቼ ተመለሱ?
- እሱን አላስታውሰውም ማስታወሻም አልያዝኩኝም
- አይ ከማስታወሻ ሳይሆን ከሚያስታውሱት በግምት ከምን ያህል ጊዜ በኋላ ነው ወደ ስራ የተመለሱት በነጋታው ስራ ላይ ተገኝተዋል?
- አልተገኘሁም
- እኮ ከምን ያህል ጊዜ በኋላ ወደ ስራ መጡ?
- ከአንድ ከሁለት ሳምንት በኋላ ነው ወደ ስራ የገባሁት
- ሁለት ሳምንት ስራ ላይ አልነበሩም?
- አዎ በግምት እንደዛ ነው
- የሃኪም የእረፍት ፈቃድ ተሰጥቶት ነበር?
- አዎ
- እሺ በወሰቱ ወደዛ ሲመጡ የጉዳት መከላከያ ልብስ አላረጉም ነበር እንዴ?
- አላረግንም
- ያደረጉ ፖሊሶችስ አልነበሩም?
- አላየሁም አጋጣሚ
- እኮ እዛ አካባቢ ላይ ያደረገ ሰው አላዩም ?
- አላየሁም
- ከጣና አቅጣጫ ድንጋይ ሲወረወር ነበረ እንዴ ምክንያቱም ከጣና አንዋር መስኪድ ባንኩ አካባቢ ነው ያሉት እና ከጣና አቅጣጫ የሚወረውሩ ነበሩ?
- ባንኩ አካባቢ ብዬ የገለጽኩት የአንዋር መስኪድ
- አይ ከጣና አቅጣጫ ድንጋይ የሚወረውሩ ሰወች ነበሩ?
- ይቅርታ ልመልስ አንዴ
- እሺ
- እኛ የመጣነው ጣቢያችን አደሬ ሰፈር ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከአደራ ሰፈር ስንመጣ የመጣነው ጉዳዩጋ ለመድፈስ ቅርበት ባለው መንገድ ላይ ነው እኛ የደረስነው በር ላይ ነው ቶሎ ለመድረስ በር ላይ እንደደረስን ቀደም ብዬ የገለጽኩት ችግር እንደነበረ ነው
- ከሃደራ ሰፈር በየት በኩል መጡ?
- በሲኒማ እራስ በኩል መጣሁ
- እኮ አሁን በሲኒማ ራስ በኩል ከመጡ ወደ ባንኩ በየት በኩል ዞረው ሄዱ ማለት ነው?
- በመሃል ማቋረጫ አለች በዛ በኩል ነው
- ጥሩ መሃል ካሉ ጣና ይታያል መቼስ ባንኩጋር ከቆሙ የጣና መንገድ ይታያል እና ከዛ አቅጣጫ የሚወረውሩ ሰወች ነበሩ ?
- አልነበሩም እኛ በር ላይ ነበርን
- ምንም ሰው አልነበረም በዛ አቅጣጫ ?
- እኔ እንግዲህ በር ላይ እንደደረስኩኝ ድንጋዩ ነበረ ከዛ በኋላ ያለው ጉዳት ደርሶብኝ እኔ ወደ ሕክምና ነው የሄዱኩት
- እሺ ከባንኩ እስከ መስኪዱ ያለው እርቀት አንድ ሜትር ሁለት ሜትር ይሆናል ነው ያሉት እስቲ ?
- አደለም እኔ ያን ያልኩት እኛ ከቆምንበት የመስኪዱ በር ነው ቅድም የገለጽኩት
- አሃ በጣም ቀርበዋል ማለት ነው ወደ መስኪዱ?
- አዎ ቅርብ ነበርን
- መስኪዱ ዝግ ነበር ክፍት ነበር?
- እኛ የነበርን ጊዜ ክፍት ነበር
- እሚወጣ እሚገባ ሰው ነበር?
- ያው ግርግሩ ነው እንጂ የሚወጣ የሚገባ አልነበረም
- እኮ ፖሊስ በሩን ስላጠረው መውጣት አልቻሉም ማለት ነው?
- አላጠሩም
- እኮ አሁን አንድ ሜትር እርቀት ላይ ከነበሩ ቆመናል እርስዎም ባልደረቦቼም ቆመናል ብለዋል አንድ ሜትር እርቀት ማለት እርስዎ ከተቀመጡበት እስከ መድረሱ ቢሆን ነው ስለዚህ በሩን አጥራችሁታል ማለት ነው አደል?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኛ ድንጋዩ እየተወረወረ እያለ ተረጋጉ እያልን ነው ያለነው እንጂ ማንም እንዳይወጣ ማንም እንዳይገባ ብለን ትእዛዝ የመስጠትም እንትን የለብንም እንደዛ አላረግንም ደንንም ለማድረግ ጊዜ አልነበረንም
- ብቻ አንድ ሜትር እርቀት ላይ ነበራችሁ?
- ከአንድ ሜትር እስከ ሁለት ሜትር ብዬ ቀደም ብዬ ገልጫለሁኝ
- እሺ ይሄ ግርግር በምን ምክንያት እንደተፈጠረ አያውቁም አደል?
- እሱ ተጠይቋል በምን ምክንያት እንደሆነ ተብሎ ተጠይቋል
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት በወቅቱ አስለቃሽ ጭስ ተተኩሷል አደል?
- አላየሁም
- በወቅቱ አሁን እርስዎ እኔ ላይ ጉዳት ደርሷል ብለዋል ሕዝቡ ላይስ የደረሰ ያዩት ጉዳት አለ ?
- አላየሁም
- ፖሊስ ዝም ብሎ በአፉ ብቻ ነበር ሰውን ሲመልስ የነበረው ተመለሱ ተረጋጉ እያለ ?
- ተረጋጉ እያልን ያለነው እኛ
- ታዲያ ለምን አይረጋጋም በአፉ ብቻ ተረጋጉ እያለ ከሆነ ሰው እማይረጋጋበት ምክንያት ምንድን ነው ?
- እሱን አላወቅኩም
- ከውስጥ ወደ ውጪ የሚገፋቸው ኃይል ይኑር አይኑር አያውቁም?
- አላወቅኩም
- እሺ አመሰግናለሁ
- ላጅን ቅድም እርስዎ መከላከያ ከዱላ በስተቀር ምንም አልያዙም ሲደርሱ ድንጋይ እየተወረወረ ነው የተለመደ ነው እንዴ በአንድ ሜትር እርቀት ድንጋይ በሚወረወርበት ቦታ ላይ መከላከያ ያልያዘ ፖሊስ ተጠግቶ በሚወረወር ድንጋይ ተጠግቶ ተረጋጉ ማለት የተለመደ ነው በዚህ አሰራር?
- እኛጋ የተለመደ ነው እኛ እንደዛ ነው እያደረግን የነበረው
- ድንጋይ እየተወረወረ እያረፈባችሁ ተረጋጉ ?
- አዎ ድንጋይ እተወረወረ ተረጋጉ እያልን የነበርነው እኛ ነን
- እኮ እራቅ ብላችሁ ተረጋጉ ለማለት ምን ከለከሎት በሚወረወር ድንጋይ መሃል ከመግባት?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኛ እንደዚህ አይነት ነገር ይኔን ያህሌ እኔ ላይ ጉዳት ይደርሳል የሚል እምነት አልነበረኝም
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ አቃቤ ሕግ
- የለንም የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ምስክር ጨርሰሃል መመለስ ትችላለህ
- በእውነት ለመመስከር
- በእግዚአብሔር ስም
- ምያለሁ
- ለምስክርነት ነው የመጡት?
- ትክክል ነው አዎ
- ስሞን የአባቶን ስም ሳይጨምሩ የራሶትን ስም ብቻ ነው የሚገልፁልኝ ?
- እሺ ደረጀ እባላለሁ
- ስንተኛ ላይ ናቸው አቃቤ ሕግ
- እሺ በተሰሙት ዝርዝር ያው 45ኛ ላይ ደርሰናል በቀረበው ማስረጃ ዝርዝር 123 ላይ ያሉ ምስክሮች ናቸው አቶ ደረጀ
- አቤት
- በነማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ለምስክርነት ከመጡ ?
- በእለቱ እኔ እነማን እንደሆኑ አላውቃቸውም
- እ?
- በእለቱ እነማን እንደነበሩ አላውቅም ጥቅል ነገር ነው ያየሁት
- እሺ ምንድን ነው ያዩት በአጭሩ ብቻ?
- እኔ በአጭሩ ያየሁት በማሽከርከር ሂደት ውስጥ ባለሁበት ጊዜ
- እ?
- አሽከርካሪ ነኝ
- እሺ?
- በተሰጠኝ መኪና ላይ ለማሽከርከር ለማንቀሳቀስ ባለሁበት ጊዜ በእለቱ የሆነ ትንሽ የእረብሻ እንቅስቃሴ ነበረ
- ከየት ነው?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መርካቶ አካባቢ ማለት ነው
- መንድን ነው የሚባለው ቦታው?
- ልዩ ቦታው አውቶቢስ መናሃሪያ ነው የከተማ አውቶቢስ መናሃሪያ
- የት ያለው?
- አንበሳ ከተማ አውቶብስ መርካቶ አዳራሹ አካባቢ ማለተ ነው ከመስኪድ ጀርባ
- ስለሱ ለማስረዳት ነው የመጡት?
- በትክክል አዎ
- እሺ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ
- እሺ ምስክር መቼ የተፈፀመን ድርጊት ነው የሚያስረዱት ቀኑንያስታውሱታል?
- ቀኑን አስታውሳለሁ አዎ
- ቀኑን ወሩነ አመተምረቱን?
- ወሩ ሐምሌ ወር ነው አመተምረቱ 2004 ዓ.ም.
- የወሩ ስንትኛ ቀን ነው?
- የወሩ 14ኛ ቀን ነው
- እሺ ምን ነበረ ቀኑ?
- አቤት?
- ቀኑን ያስታውሱታል ምን ቀን እንደነበረ የሳምንቱ?
- በትክክል አላስታውሰውም
- እሺ ቅድም በጠቀሱት ቦታ ምንድን ነው የተከሰተው?
- የተከሰተው ለስራ እን ተዘጋጅቼ በማሽከረክረው አውቶቢስ አካባቢ
- ምንድን ነው የሚያሽከረክሩት?
- የከተማ አውቶብስ
- ንብረትነቱ የማን ነው?
- የመንግስት ነው
- የአምበሳ አውቶብስ?
- የአምበሳ አውቶብስ ድርጅት ነው
- እሺ ከዛስ ሰሌዳ ቁጥሩን ይዜንን መኪና ?
- ሰሌዳ ቁጥሩ አዲስ አበባ ኮድ 3 75189 ነው
- እሺ ከዛስ ምን ሆነ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከዚያ በተሰጠኝ ስምሪት ሰመረት ለጉዞ አዘጋጅቼ ጭኜ ለመሄድ ስል እንደወትሮ ከቦታው አልወጣም ለመንቀሳቀስ አልቻልንም ከዛ የሆነ ድምጽ እና ጫጫታ ነገር ተሰማ ከዛ እና እንዳትወጡ ተብለን ተከለከልን በአካባቢያችን ባሉት የቅርብ አለቆቻችን ማለት ነው ከዚህ በኋላ አልወጣንም ሁላችንም ከኔም ሌላ ሌሎች ተጨማሪ መኪናዎች እዛው ቆምን በዚህ መሃል የረብሻው አይነት ወደፊት እና ወደኋላ ሆነ ወዲያ ወዲያ ይሯሯጡ ጀመር
- የሚሮጡ ሰወች ይታዮት ነበር?
- ይታዩኝ ነበር አዎ በሩቁ ማለት ነው
- ያውቋቸዋል ሰወቹን?
- እነ እገሌ ብዬ አላይም ለምን በጣም ብዙ ሰው
- አለባበሳቸውንስ ለይተዋል ?
- አለባበሳቸውንም በጣም ብዙ ናቸው ብዙ ስለሆኑ ማንም ከማንም መለየት በማይቻልበት ደረጃ ነበር
- መደበኛ አለባበስ ነው ወይስ ምን አይነት አለባበስ ነበር?
- አብዛኛው መደበኛ አለባበስ ይመስለኛል
- እሺ ከዛስ?
- ከዛ እረብሻ ወደፊት ወደኋላ ወደኋላ ወደአዳራሽ ወደመርካቶ አዳርሽም ይሄዳሉ መልሶ ደግሞ ወደፊትም ወደ መስኪድ ይሄዱ ነበረ
- ድምጽ ይሰማኝ ነበር ጩኸት ይሰማኝ ነበር ብለዋል እረብሻ አለ ብለዋል ?
- አዎ
- ምን ነበረ የሚለው ይሄ ጩኸቱ ምን ነበረ?
- የብዙ ሰወች ድምጽ ስለሆነ በትክክል ይሄ ነው ብሎ መናገር አይቻልም እስከዚህ ድረስ ነው ይሄንን የማውቀው
- ከዛስ ወደናንተ ቀረበ?
- የኛ መኪናዎች ተሰብስበው ቆመዋል የከተማ አውቶቢሶቹ ማለት ነው እዛው በቆሙበት ድንጋይ መወራወርም ነበረ
- መወራወር ሲሉ ማንና ማን ነው የሚወራወረው ?
- በቃ እነዚሁ ድምጽ ሲያሰሙ የነበሩ ማለት ነው ውርውሪያ እንትን ሲል ያለው አማራጭ መኪናዎችን ወዴት ማድረግ ስለማይቻል እራሴንም ለማዳን ወዳለት ወደ ውስጥ ቢሮዎች ገባሁኝ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ?
- ከዛ ቢኒላ እው በረንዳ ላይ ቆመን ስናይ ያው ድንጋዮች ይወረወራሉ እኔ ይገፍው በነበረው አውቶብስ ላይ የድንጋይ እሩምታ አረፈበት እና የግራ ጐኑ ተመታ
- ምኑ ላይ የብረት አካሉ ነው ወይስ መስታወቱ ላይ?
- የፊት መስታወት አካሉ ላይ 2ኛ ደግሞ ሌላውንም መልሰን ስናይ የቀኝ እስፖኪዮ መስታወቱ የውጭ ሽፋኑም እንዲሁ ስብራት ደርሶበታል
- ከሩቅ በሚወረወር ድንጋይ ነው ወይስ አጠገቡ መጥተው እየወረወሩ ነበር የሚመቱት?
- እኛ በረንዳ ላይ ሆነን ወደፊት ይታየን ነበረ ከመኪናዎቹ አሻግረን ከፊት ያሉት ይታዩን ነበረ ያው ድንጋዩን ሸሽት ማለት ነው
- ወደ ውስጥ ገብተው ምን አዳራሹ በረንዳ ላይ ነበረ የነበሩት?
- የአዳራሹ በረንዳ ማለት ነው ከመኪናዎቹ ከፍ ብለን
- እዛጋ ሆነው መኪናዎቹ ይታያሉ አደል?
- አብዛኛዎቹ ይታያሉ
- እነዚህ መኪኖች አሁን ተሰበሩ በተወረወረ ድንግይ ተሰበሩ የሚሉት ወርዋሪዎቹ ወደ መኪናው ቀርበው ነበር ወይስ ከርቀት ነበረ የሚወረውሩት?
- መንገዱ እና ወርዋሪዎቹ ቅርብ ለቅርብ ነው መውጫችን እና ዋናው ወደ መስኪድ ከመርካቶ ወደ መስኪድ የሚወስደው መንገድ ብዙም ልዩነት የለውም ስለሌለው እዛው ባለበት ወርውረውም ይታያል.
- ከየት የመጡ ሰወች ናቸው እንዲህ እየወረወሩ የመጡት?
- ከየት እንደመጡ ባላውቅም ለፀሎት ወደ መስኪድ ከሄዱት አካባብ ሰወች እንደሆነ ነው የምረዳው
- በምን ተረዱ ይሄንን ከመስኪዱ የወጡት ሰወች ወይም ወደ መስኪድ የሄዱት ሰወች እንደሆኑ በምን ተረዱ ?
- ይሄንን ልረዳ የምችለው መደበኛ ለስራ ከምንወጣበት እንዳንወጣ በቅርብ አለቆቻችንን ቅደምም እንደገለጽኩት ተነግሮን ነበረ
- ለምን?
- መውጣት ምንም መንገዱ ክፍት እንዳልሆነ
- ለምንድን ነው የተዘጋው መንገዱ?
- ለምን እንደተዘጋ አላውቅም ይሄንን

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ቅድም ያሉትን ነገር አንስቼ ልጠይቆት ከየት እንደመጡ ባላውቅም ለፀሎት ወደ መስኪድ ከሄዱት ሰወች እንደሆኑ ተረድቻለሁ ብለዋል ከምን ተነስተው ይሄንን ተረዱ ማለት አሁን አለቃ እንዳትወጡ ተባልን ከሚሉትጋ የሚያገናኘው ነገር የለም አሁን አንዳሉት?
- እኔ የተረዳሁት አንደኛ
- ምንድን ነው መነሻው?
- መነሻው የፀሎት ሰዓት ከነበረበት ሰዓት ጋራ የተያያዘ በመሆኑ ነው
- ምኑጋ ነው የተያያዘው ?
- አቤት?
- ከምኑጋ ነው ተያያዘ የምትሉት?
- ተያያዘ የምንለው የከተማ አውቶብሶቹ መውጫችን በዛው በመስኪዱ አካባቢ ስለሆነ መኪኖቹ እንዳይወጡ የተከለከለው በዚህ ምክንያት ነው
- ሌሎች አውቶብሶች ጉዳት የደረሰባቸው አሉ እርስዎ ቅድም የሰሌዳ ቁጥሩን ከጠቀሱልን ከእርስዎ አውቶብስ ውጪ እርስዎ ከሚያሽከረክሩት አውቶብስ ውጪ በሌሎች ላይ የደረሰ ጉዳት አለ በሌሎች አውቶብሶች ላይ?
- በሌሎችም የደረሱ ቁጥራቸውን በውል ለይቼ የማላውቃቸው ይሄ የኔ ምድብ ስለሆነ ነው የራሴ መኪና ስለሆነ ነው የምለየው ሌሎቹን ባላውቃቸውም የተመቱ መኪኖች አውቃለሁኝ አስታውሳለሁ
- አቶ ደረጄ
- አቤት
- አሁን ይሄ ድንጋይ ሲወረወር የነበረው ማለት ፀብ ነበር በትክክል እርስዎ ያጣሩት ነገር ምንድን ነው ማለት ከሁለት ወገን ነበር ድንጋይ የሚወረወረው ፀብ ነበር እርስዎ ያዩት?
- ፀብ ሳይሆን
- እኮ እሱን ይንገሩን ከሁለት ወገን የሚወረወር ድንጋይ ካልሆነ ከአንድ አቅጣጫ የሚመጣ ነው አደል ፀብ ነው እንዴ ያያችሁት?
- ፀብ አላየሁኝም እንደ ሰልፍ ነገር ድምፁ ጫጫታው እና ወደፊት እና ወደኋላ የሚለው ነገር ነው የሚታየን
- ወደፊት እና?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አንዴ ወደ ወደፊት ይሄዳሉ ወደ መስኪድ ይሄዳሉ ተመልሰው ደግሞ ወደ መርካቶ አካባቢ ወደ አዳራሹ ይመለሱ ነበረ ይህ እንግዲህ ምንድን ነው ከፀሎትብ ጋራ በተያያዘው አካባቢ ያለውን እንቅስቃሴ እንደሚገልጽ ነው የምረዳው
- ከምኑጋር?
- ከፀሎት አድራጊዎች ጋራ እንደሆነ ነው የምረዳው
- ድርጊቱ ከዛጋር የተያያዘ እንደሆነ ነው የተረዱት?
- የተረዳሁት አዎ
- ዋና ጥያቄአብቅተናል
- የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ
- ምስክር እርስዎ የቆሙበት አካባቢ ወደ መስኪድ እና ወደ ምእራብ አቅጣጫ የሚወስደውን አስፋልት ለማየት በሚያስችሎት ቦታ ላይ ነበሩ እንዴ ቆመው ይመለከቱ የነበረው?
- በትክክል አዎ በሁለቱ መሃል አማካይ ነው
- ሀለቱንም አቅጣጫ ማየት ይችላሉ ?
- በሁለቱም አቅጣጫ በሚያሳይ መልኩ ሳይሆን መኪኖቻችን ስምሪት አካባቢ የሁለቱም መንገድ አዋሳኝ አማካኝ ቦታ ላይ ነው ያለው ያ ስለሆነ የተወሰነውን ክፍል ሊያሳይ ይችላል
- ኦኬ መክናው የቆመው በዛ አካባቢ ስለነበረ እርስዎም መኪናው አጠገብ በቅርብ እርቀት ስለነበሩ ሁለቱንም አቅጣጫ ማየት ይችሉ ነበር ?
- የተወሰነውን ክፍል ማየት ይቻላል
- እነዚህ አንድ ጊዜ ወደ መስኪድ ይሄዳሉ ከዛ ወደ አዳራሽ ይመለሳሉ እነዚህ ተመሳሳይ ሰወች ናቸው እንዴ ወደ መስኪድ ይሄዱና ከዛ ተመልሰው ወደ ኋላ ደግሞ ወደ አዳራሽ የሚያፈገፍጉት እነዚህ እርስዎ የሚያዩዋቸው ተመሳሳይ ሰወች ናቸው ?
- የተለዩ ሰወች እንዳልሆኑ ይገባኛል ለምን አንድ እንቅስቃሴ ተመሳሳይ እንቅስቃሴ ያላቸው ናቸው
- ምን ወደኋላ የሚገፋቸው ምንድንነው ፖሊስ ነበረ እንዴ አድማ በታኝ?
- ፖሊሶች በቅርብ አይታዩንም እነዚሁ የሚጮሁት ሰወች ናቸው ሲታዩን የነበረው
- ምንድን ነው ወደኋላ እንዲያፈገፍጉ የሚያደርጋቸው
- ይህ እንቅስቃሴ አይታየኝም ወደፊት ምን እንደሚወስዳቸው እና ወደኋላ ምን እንደሚወስዳቸው አላውቅም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሰወቹ ፊታቸው መነሻቸው ቅድም ያሉት እንግዲህ ወደመስኪዱ አካባቢ የሚሄዱ ከሆነ መነሻቸው እኮ መስኪድ ሊሆን አይችልም ከመስኪድ የመጣ ሰው ወደ ምእራብ ወደ አዳራሽ ነው የሚሄደው ወደ መስኪድ የሚሄድ ሰው ግን ከመስኪድ ሊሆን ይችላል ተብሎ እንዴት ሊገመቱ ይችላሉ?
- ይህ የኔ ግምት አውቶብሱ ለመውጣት ባለመቻሉ ምን ጊዜም የሁል ጊዜ መውጫችን ዋና በራችን በመሆኑ ነው መስኪዱ እና ፀሎት ብሚደረግበት ሰዓት ሁል ጊዜ ዘውትር አቁመን ልክ ፀሎቱ ሲያልቅ እንደምንወጣ ስለምረዳ ነው
- እንጂ ከመስኪዱ ቀጥታ ወጥቶ ወደናንተ መጥቶ የወረወረ ሰው ሳይሆን ወደ መስኪድ ሄዶ ወደ ኋላ የሚያፈገፍግ ሰው ነበረ ያዩት አደል?
- በዚህ ሂደት ውስጥ ነው አዎ እንደገና ወደኛም እንትን ያሉት
- እሺ አቶ ደረጀ በወስስቱ ሰው ጭነው ነበረ እንዴ?
- አቤት በደምብ አይሰማም
- ሰው አልጫኑም ነበር አደል?
- ሰው ጭነን አራግፈናል
- እንጂ በዛ ወቅት ሰው ጭናችሁ አራገፋችሁ እንጂ አውቶቢስ ውስጥ ሰው አልነበረም
- የተወሰኑ መኪናዎች
- እርስዎ የሚነዱት አውቶቢስ ሰው አልነበረም ማለት ተሳፋሪ አልነበረም አደል?
- ወርደዋል አዎ
- ተሳፋሪ አልነበረም ባዶ ነበረ?
- አልነበረም ተመለሱ ስለተባልን አውርደናቸዋል
- እሺ አለቆቻችሁ አትንቀሳቀሱ እዛው ቆዩ ካሏችሁ ከምን ያህል ደቂቃ ወይም ሰዓት በኋላ ነው ድንጋይ ውርወራ የተጀመረው አንደ ሰላሳ ከዛ በላይ ወይስ እንዴት ነው ?
- ያው እንደዚሁ አካባቢ ነው ከስምንት እስከ ዘጠኝ ባለበት ሰዓት ውስጥ ነው
- አይ ሰዓቱ ሳይሆን አሁን አለቆቻችሁ አትንቀሳቀሱ እዚሁ ቆዩ ካሏችሁ በኋላ ድንጋይ እስከተወረወረበት ጊዜ ድረስ 30 ደቂቃ ነው አንድ ሰዓት ነው ምን ያህል ቆያችሁ ያድንጋይ እስኪወረወር ?
- ከአንድ ሰዓት በላይ ይሆናል
- ከአንድ ሰዓት በላይ እዛ ከቆያችሁ በኋላ ድንጋይ መወርወር ተጀመረ?
- አዎ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ አለቀቻችሁ እዛው ቆዩ ሲሏችሁ ድንጋይ ውርወራ አልነበረም አደል ከአንድ ሰዓት በኋላ ስለሆነ ማለት ነው ድንጋይ ውርወራው ያተጀመረው?
- መንገዱ ስላልተከፈተ አልወጡም መኪናዎች በሙሉ አልወጡም ብዙ መኪናዎች አልወጡም እና ያው እዛው ተፋፍገው ቆመዋል
- እሺድንጋይ ውርወራ ካለ በኖርማል ሁኔታ አውቶብስ ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ተብሎ ስለሚገመት በጀርባ በኩል በአዳራሽ በኩል አውቶቢሱን ማሸሽ አትችሉም ነበር እንዴ አንድ ሰዓት ሙሉ ድንጋይ እስኪወረወር ለምን መጠበቅ አስፈለገ ?
- ጉዞቿውን አገልግሎት ለመስጠት ሁሉም እንደተዘጋጁ አጠቃላይ የመውጫ በራችን ቀድሜ እንደገለጽኩት የመውጫ በራችን በሱ አቅጣጫ ስለሆነ አብዛኛው የኔ የጉዞ አቅጣጫ ወደ ሰንዳፋ ስለነበረ በዛው አቅጣጫ ነው መውጣት ያለበት እና የኔንም መሰሎች እንደዛ ስለሆነ ሁሉም መኪኖች ስላልወጡ እንደዚህ አይነቱ ትእዛዝ ውስጥ /ግልጽ ያልሆነ/
- እርስዎ የሚነዱት አውቶብስ ደረሰበት ያሉት ጉዳት በግጭት ቢሆን ምን ያህል ዋጋ ያስወጣል የደረሰው ጉዳት ጥገናው ምን ያህል ዋጋ ያስወጣል ?
- ይህን
- ተቃውሞ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ቆይ ምስክር
- እህ
- የምንቃወምበት ምክንያት እኚህ ምስክር በወቅቱ ይዘውት ስለነበረው ተሽከርካሪ አምበሳ አውቶቢስ ስለደረሰበት ጉዳት ነው የደረሰበት ጉዳት ደግሞ የጮኑ የአውቶብሱ መስታወት እስፖኪዮ የተለያዩ እነኚህን ጉዳቶች በዝርዝር ገልፀዋል ከዚጋር በተያያዘ ግን እያንዳንዱን ግምት እሳቸው መካኒክ አደሉም ወይም ደግሞ በዚህ እውቀት ያላቸው የሰለጠኑ ባለሙያ ሆነው አደለም እሳቸው ያሽከርካሪ ባለሙያ ናቸው ከዚጋር በተያያዘ በተጓዳኝ የመካኒክ እና የመገመት ስራ አገልግሎት ስለሚሰጡ ያን ጭብጥ አሲዘን አደልም እያስመሰከርን ያለነው ስለዚህ አምበሳ አውቶቢስ እሱ የተጠየቀውን በማስረጃ መግለጽ አያይዘናል ያን ብቻ ማየት ይበቃል እና ይሄ ጥያቄ ውድቅ እንዲደረግልን በአክብሮት እጠይቃለሁ
- መልስ ስጡበት
- እሺ አናመሰግናለን የተከበረው ፍ/ቤት የተከበሩ አቃቤ ሕግ ያቀረቡትን ብቻ የመቀበል ግዴታ የለብንም በእርግጥ የተከበሩ አቃቤ ሕግ ይጠቅመናል ያሉትን ማስረጃ አቅርበዋል ይሄንን እኛም አይተናል ግን አሁን እኚህ ምስክር እስካሁንም የቀረቡት ምስክሮች ያዩትን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ያተረዱትን የሚያውቁትን እንዲመሰክሩ እንየተጠየቁ ነው እኔም አዲስ ጥያቄ አደለም ጀየጠየቅኩ ያለሁት የተከበረው ፍ/ቤት ስለሚያውቁት አውቶቢስ ስለሚነዱት ልለሚያሽከረክሩት አውቶቢስ የደረሰበት ጉዳት መጠን ነው ይሄንን ደግሞ ማስረዳት ለክርክሩ በጣም መሰረታዊ ነገር ስለሆነ ይሄንን እንዲያስረዱ ይፈቀድልን ነው እሚያውቁት አላውቀውም ካሉ እኮ አናስገድድም የተከበረው ፍ/ቤት ካወቁ ይመልሱልን

- እሺ ብይን ሰጥተናል
- አውቶቢሱ ላይ የደረሰው ጉዳት ምን ያክል ነው የሚል ጥያቄ ቀርቧል ምስክሩ የሙያ ምስክር አደሉም ይሄን ማወቅ አይችሉም የሚል መቃወሚያ ቀርቧል ካወቁ ነው የሚገልፀው የሚልነገርም በዚህ ተነስቷል ፍ/ቤቱም ምስክር ይሄን መመለስ ይችላሉ አይችሉም የሚለውን አይቷል አሁን ምስክሩ የተጠየቁት የግል የራሳቸውን ግምት ባወቁት እንዲያስቀምጡ የራሳቸው ግምት አደለም የተፈለገው ምስክሩ የሙያ ምስክር አደለም ይታወቃል ነገር ግን ተጐዳ የተባለው አውቶቢስ ዋጋው ምን ያክል እንደሆነ የሚያውቁ ከሆነ ቢገልፁ የሙያ ምስክር እንጂ ማንኛውም ምስክር ይሄን ግምት አይገልጽም የሚለው ክርክር የማያስኬድ ስለሆነ የሚያውቁ ከሆነ የተጠየቀውን ጥያቄ መልሱ ተብሎ ብይን ተሰጥቷል
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ደረጀ እስቲ እርስዎ የሚያሽከረክሩት አውቶቢስ ላይ የደረሰው እስፖኪዮ ላይ እና ሌላ መስታወቱ ላይ ደረሰ ያሉት ጉዳት ምን ያህል ወጪ ያስወጣል እንደው እርስዎ እራሶ ቢያስጠግኑት ምን ያህል ወጪ ያስወጣል ?
- ጥያቄውን ለመመለስ በእውነቱ ይሄ የሙያ እንትን አይፈቅድልኝም
- የሚያውቁት ከሆነ ነው ?
- አላውቀውም ግምቱን አላውቅም
- አውቶቢሱ ላይ መስታወቱ ስንት መስታወት ነው የተሰበረው ?
- ዋናውን ትልቁ የፊት መስታወት ነው የግምባር መስታወት ነው
- እሺ ቅድም መጨረሻ ላይ አቃቤ ሕግ ከጠየቁት ጥያቄ ወደ ጠየቆት ጥያቄ እንሂድ
- እነዚህ እሚወረውሩ እና እየደረሱ የሚመለሱ ሰወች ከፀሎትጋ አገናኝተው ተናግረዋል እና እዛ ቦታ ላይ ፀሎት ይደረጋል እንዴ እርስዎ አውቶቢስ የሚያቆሙበት ወይም አውቶብስ የሚያንቀሳቅሱበት ቦታ ላይ ፀሎት ይደረጋል እንዴ?
- እዛ ቦታ ላይ አይደረግም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያው ግምቶት እንጂ ምንም ማስረጃ የሎትም አደል ለነዚህ ሰወች ፀሎት ይሁን ምን ይሁን ግምት ነው የእርስዎ ግምት ነው አደል?
- የኔ ግምት ነው አዎ ትክክል
- ከምእራብ አካባቢ የሚመለጡ ሰወችስ አልነበሩም ድንጋይ የሚወረውሩ ወይም ወደ መስኪድ አቅጣጫ የሚሄዱ ሰወች ወይም የእርስዎ አውቶቢስ ላይ ድንጋይ ከወረወሩ ሰወች ከምእራብ አቅጣጫስ የመጡ ሰወች አልነበሩም ?
- በትክክል የአገራችን ዋና መገበያያ ቦታ ስለሆነ የተሰነው ክፍል ድረስ ሰው ሊንቀሳቀስ ይችላል ግን ይሄኛው የፀሎት አካባቢ
- ከምእራብ አይ ከምእራብ አካባቢ ሰወች አልመጡም ወይ እርስዎ አሁን
- ምእራብ የሚሉትን እስቲ ግልጽ አርገው
- አቅጣጫ ለመግለጽ እንጂ ከምእራብ አካባቢ አይታየኝም ልገልጽም አልችልም
- ምእራብ የምለው እኮ ምእራብ ሆቴል ለማለት ነው ለምሳሌ ሃደሬ ሰፈር አለ የእርስዎ የስራ አካባቢ ስለሆነ ያውቁታል ብዬ ነው ምእራብ ሆቴል አለ እሱን ተሻግሮ የንግድ ባንክ አለ እሱን ተሻግሮ ወደ ሰባተኛ የሚወስድ መንገድ አለ ከነዚህ የመንገድ አቅጣጫ ሰወች አልመጡም ወይ ?
- እኔ በስራ ላይ ስለነበርኩ ከዚህ አቅጣጫ የሚመጣ ሰው ምንም ሊታየኝም ላይም አልችልም ስራ ላይ እንደሆነ ገልጫለሁኝ
- በወቅቱ አካባቢዎ ላይ ፖሊሶች አይተዋል እንዴ?
- ቅድም ተጠይቆ ተመልሷል
- እርስዎ ደረስ እያሉ የሚመለሱ ሰወች ነበሩ ብለዋል እንግዲህ ፀጥታ ለማስከበር የተተኮሰ ጥይት የሰሙት ነገር አለ የጥይት ድምጽ ሰምተዋል?
- የጥይት ድምጽ አልሰማሁኝም
- አስለቃሽ ጭስስ?
- መከላከያ የያዙ ፖሊሶች ብቻ የድንጋይ መከላከያ የያዙ ብቻ እና እንዲሁ ፀጥታ አስከባሪ ፖሊሶች አይቻለሁ
- የት አካባቢ አዩ?
- እኔ ልክ ካለሁበት መናሃሪያ አቅጣጫ ቅያስ ወደታች ወደ [illegible] ተራ በሚለው አቅጣጫ ሁሉ ወደ ውስጥ ይታየናል
- ጆንያ ተራ ያሉት ወዴት ነው?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጆንያ ተራ ማለት ከአውቶብስ መናሃሪያው ግራ ቀኝ ሳይሆን ፊት ለፊት ትይዩ መንገድ በሌለበት አቅጣጫ በቂ የመኪና መጓጓዣ ከእግረኛ በስተቀር ሌላ ማንቀሳቀስ የማይችል አቅጣጫ አለ
- እሺ የእርስዎ አለቃ አትንቀሳቀሱ ሲሉ ችግር ሊፈጠር እንደሚችል ያውቁ ነበረ ማለት ነው?
- ይህ ጥቅል ትእዛዝ እንጂ በተናጠል ለኔ የተሰጠኝ ትእዛዝ አደለም
- እኮ አትንቀሳቀሱ ያሉት ችግር ሊፈጠር ይችላል በሚል ነው አደል?
- ሌሎች ስላልወጡ ባለመውጣታቸው ለኔም ያው እንደማንኛውም
- ጥያቄዬን አልመለሱልኝም የእርስዎ አለቃ አሁን መደበኛ ስራ ላይ ነው ያሉት እርስዎም ሆኑ ሌሎች ያውቶቢስ ሹፌሮች መደበኛ ስራዎቻቸውን እየሰሩ ነው ስለዚህ አሁን አትንቀሳቀሱ አትውጡ ሲሉ ችግር ሊፈጠር ይችላል የሚል እውቀት ነበራቸው ወይ ነው ነበራቸው አደል?
- ይሄ ከኔ ግንዛቤ ውጪ ስለሆነ አላውቅም
- እሺ እንደዚህ በኖርማል ሁኔታ አትውጡ ተብላችሁ ታውቃላችሁ አንዴ ዝም ብለው ለሁሉም አውቶቢሶች አትውጡ ተብሎ ያውቃል እንዴ ?
- ከዛ ቀን ሌላ ውጪ አትውጡ ተብላችሁ ታውቃላችሁ ወይ ?
- በትክክል ፀሎት እስካለለቀ ጊዜ ድረስ በትራፊክ ፖሊሶቻችን አማካኝነት ባሉት የከተማ ትራፊክ ፖሊሶች አማካኝነት እንዳንወጣ የግድ ይታገዳል
- ትራፊኮች አደሉም ትራፊኮች ሳይሆን በአለቆቻችን ነው ተሰጠን ያሉት አደል ?
- በአለቆቻችን አልተገለፀም እኔ ሌላ ጊዜ አልሰማሁኝም
- እ?
- በሌላ ጊዜ ሲገለጽ አልሰማሁኝም አዎ
- እሺ ትራፊኮች ናቸው እንዴ በዛ ቀን አትውጡ ብሎ ያስቆሟቸው ?
- እንዴት?
- አሁን በአለቆቻችን አደለም እያሉ ነው የተከበረው ፍ/ቤት እየደባለቁ ነው ምስክሩ
- ሌላ ጊዜ አሁን አርብ ሊሆን ይችላል
- አንደርስታንድ እንደራረግ እና ምስክሩ የሚሉት በአለቆቻችን ነው ያን ቀን የተነገረው ሌላ ጊዜ ግን በፖሊሶች ነበር በአለቆቻችን ሌላ ቀን ተነግሮን አያውቅም ነው ከዚህ ተነስተው ጥያቄውን ያቅርቡ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ ከዚህ ቀን ውጪ በአለቆቻችሁ ተነግሮ አያውቅም አሉ ይሄን መልሰውታል?
- ከተመለሰ ወደሌላ ለምን
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ባልደረቦቼ
- ምስክር ቅድም የእርስዎ አውቶቢስ በድንጋይ እሩምታ እንደተመታ ነግረውናል የተመታበት ድንጋይ ምንድን ነው ተራ የተገኘ ድንጋይ ዝም ብሎ ድንጋይ ነው የተመታው የድንጋዩ አይነት ከአካባቢው ያገኙትን ሰወች እያነሱ ነበር የሚመቱት?
- የድንጋዩን አይነት ለይቼ እኔ አላየሁኝም
- ማለት አሁን ተመቶ ከዛ ድንጋዩ መሬት ይወድቃል የወደቀውንም ድንጋይ እሩምታ ስለሆነ አላዩትም እንዴ?
- እሩምታ ስለሆነ ምን አይነት እንዴት አይነት ምን እንደሆነ መለየት አይቻልም ለምን ብዙ ድንጋዮች ናቸው የተወረወሩት ግማሹ መኪና ላይ ያረፈ ግማሹ ያላረፈም የተወሰነ ግዜ ተወርውረዋል
- አዎ የኔ ጥያቄ መኪናው ላይ ያረፈው ድንጋይ መኪናውን ይመታና መሬት ይወድቃል ያ የወደቀውን ድንጋይ እርስዎ በኋላ መጥተው የመኪናዎ መጐዳት ሲያዩ የድንጋዩን አይነት አላዩትም እንዴ ጐምበስ ብለው መሬት
- ወርደው አይተዋል የተወረወረውን ድንጋይ?
- እኔ መኪና ውስጥ አልነበርኩኝም ከመኪናው ወጥተን ወደ ውጪ ነን በረንዳ ላይ ሆነን ነበር ስንከታተል የነበረው
- እኮ አሁን ድንጋይ ተወረወረ የሆነ ቦታ ላይ እኮ ቆሟል አደል ውርወራው ?
- አዎ
- ከዛ በኋላ እርስዎ ወደ መኪናው ሄደው የደረሰውን ጉዳት ለማየት አልሄዱም እንዴ?
- ሁላችንም አይተናል በደረሱት አውቶቢሶች
- አሁን ሲሄዱ እዛጋ ሲደርሱ የተወረወረው ድንጋይ ይኮ አካባቢውን አቆሽሾት ብዙ ድንጋይ እዛ ወድቆ አላዩም እንዴ?
- በትክክል አዎ
- ያ ድንጋይ ዝም ብሎ ድንጋይ የሚወረውር ሰው አንስቶ የወረወረው ድንጋይ ዝም ብሎ የተገኘ ድንጋይ ነው ለደል የተሰየ ድንጋይ ነበረ እንዴ?
- የተሰየ ድንጋይ አይመስለኝም ያው ተመሳሳይ በዛ አካባቢ ሊገኝ የሚችል ድንጋይ ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥሩ መስታወት አሁን በድንጋይ እሩምታ ተመታ ከዛ መስታወቱ እዛው ተሰነጣጥቆ ባሱ ላይ ቀረ ወይስ ወደ መሬት አረገፈ?
- የኔ የተወሰነ ክፍል ተሰነጠቀ
- ተሰንጥቆ እዛው ባሹ ላይ ነበር?
- አዎ ባሱ ላይ ነበር
- ውርወራው እንዴት ቆመ ታዲያ አሁን ሲወረወር ነበረ እርስዎ እያዩ ነው እንዴት ቆመ ውርወራው ?
- አሁን ጥያቄውን አልሰማሁትም?
- የድንጋይ ውርወራው እንዴት ቆመ መቼ ቆመ የሚለውን
- ቅድም እንደገለጽኩት ወደ ፊት እና ወደ ኋላ እየሄዱ ስለነበረ እኔ እንደማንኛውም ከመኪና ከአካባቢዬ መኪና አካባቢ ሆኜ መጠበቅ ስለነበረብኝ አካባቢዬ መኪና አካባቢ ሆኜ መጠበቅ ስለነበረብኝ እዛው እየጠበቅኩኝ ነበረ እንዴት እንደቆመ አላየሁኝም እኔ
- ምስክር የሚሸሹ ሰወች ነበሩ ብለዋል እየመቷቸው ነው የሚሸሹት ምን ሆነው ነበረ የሚሸሹት?
- ለምን ወደፊት እንደሚሄዱ እና ወደኋላ ለምን እንደሚሄዱ አላውቅም ስራ ላይ ስለነበርኩኝ ይሄንን አላውቅም
- ሲሸሹ ነው ያዩት?
- መሸሽ ሳይሆን ይጮሃሉ ይናገራሉ ወደፊት ይሄዳሉ አንዴ ወደኋላ ይመለሳሉ በምን ምክንያት እንደሆነ ግን አላውቅም
- እሺ የነበሩት ፖሊሶች መከላከያ ለብሰው ነበረ ብለሃል መከላከያ ማለት ይሄ ድንጋይ እንዳይመታቸው መስታወት የሚመስለውን ነገር ነው?
- በትክክል አዎ
- የነበሩት ፖሊሶች ምን አይነት ልብስ የፌደራል ልብስ የለበሱ ናቸው ወይስ ኖርማል የፖሊስ ልብስ የለበሱ ነበሩ ማለት እንደዛ መከላከያ የለበሱት የትኞቹ ፖሊሶች ናቸው ፌደራል ፖሊሶች ናቸው ወይስ ይሄ ከላይ ሰማያዊ እና ሱሪ የሚያረጉት ናቸው የትኛውን ልብስ የለበሱ ነበሩ ነው ወይስ ሁለቱንም የለበሱ ነው የነበሩት?
- ሁለቱንም አይቻለሁኝ እነዛ ግን ወደዚህ ብዙም አላየሁኝም እኔ
- ሁለቱም የለበሱት ግን ነበሩ እዛው?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሁለቱንም የለበሱት ሳይሆን ዱላ ይዘው የተወሰኑ ፖሊሶች ነበሩ እሱን እዛ እኛ አካባቢ አንዳ ይታያሉ አንዱም አይታዩም እነሱም
- እሺ ሌላው ድንጋዩ እንትኖችን ለመምታት ተብሎ የተወረወረ ነው ወይስ ሰወቹ ላይ ሲወረወር የነበረው ድንጋይነው አውቶብሶችን የመታው ?
- የተወሰነው ክፍል ኃይል ወደ አውቶብሶቹ ዞሮ ወርውሯል
- ሰው አልነበረም ወደዛ እሚያመልጥ ሰው ወይም ፖሊሶቹን የሚሸሹ ሰው ሌላ ሰው አልነበረም?
- ቅድምም ለመግለጽ ሞክሬያለሁኝ በድንጋይ ውርዋሮ ምክንያት ሁላችንም አቁመን ግማሾቻችን በየበረንዳው ላይ ነበርን ተሳፋሪዎችንም አውርደናል ብያለሁኝ
- ስለዚህ ሆነ ብሎ ይወርወር ለሰው የተወረወረ ይምታው አያውቁም እርስዎ?
- በረንዳው ሊያሳየን ስለሚችል ከመኪናዎቹ ጀርባ ሆነን ሊያሳይ ስለሚችል ክፍታ ያለው ቦታ ስለሆነ ሊያሳየን ስለሚችል የተወሰነው ክፍል ወደዚህ ሆኖ ነው ወደ አውቶብሶቹ ሆነው ሲወረውሩ ነው እንግዲህ እኔ እንደተረዳሁኝ
- ሰው አልነበረም በዛ በአውቶብሶቹ መካከል እሚሯሯጥ?
- /ግልጽ ያልሆነ/ ብያለሁ በድጋሚ ለ3ኛ ጊዜ
- አይ የወረዱትን አደለም እያልኩ ያለሁት ድንጋይ እየወረወሩ ያሉት ወይ ወደ አውቶብሶቹ አካባቢ የሄደ ወይ የሚሸሽ ሰው እዛ አካባቢ አልነበረም ወይም ፖሊሶቹ አልነበሩም ሌላ ሰው አልነበረም?
- ብዙዎቻችን ጥግ ጥግ ይዘናል በመጠለያ የፀሐይ መጠለያ
- እኮ አይተው ከሆነ የሚሮጥ ሰው በአውቶብሱ መካከል የሚሮጥሰው ካለ እሱን ነው
- እኔ አላየሁኝም ሙሉ በሙሉ አቁመናል እኛ አውቶብሶቹን
- አቶ ደረጀ ቅድም ቀኑን ሲጠየቁ ሐምሌ 14 ቀን 2004 ብለው ነበረ ሰዓቱ ስንት ሰዓት ላይ እንደሆነ ግን አልገለፁም ስለዚህ ስንት ሰዓት ነው ሰዓቱ?
- እሱ ብዙ ጊዜ ተጠይቋል
- ሰዓቱ አልተጠየቀም
- ከስንት ሰዓት በላይ ነው አንድ ሰዓት ነው ከዚህ ሰዓት ከዚህ ሰዓት እሳቸው ሲጠይቁት ነበር
- በመስቀለኛም ተጠይቆ ነው የተመለሰው በዋና አልተጠየቀም
- የእርስዎ መኪና አውቶብስ ምን ነበረ አይነቱ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የአውቶብሱ አይነት አሁን አዲሱ የገባው ለአገራችን የገባው ቢሾፍቱ የሚባለው አውቶብስ ነው
- መርካቶ ሲሰሩ መርካቶ መስመር ላይ ሲሰሩ ብዙ ጊዜ ሕዝብ የሚበዛው ምን ምን ቀን ነው
- ፀሎት ባሉት መሰረት ማለት ነው አንዋር መንገዳችሁ ስለሆነ?
- በሁሉም ቀን ይኖራል ሰው
- የተለየ የሚበዛበት ቀን ይኖራል ሰው?
- የተለየ እኔ ይሄ ነው ብዬ
- አርብ እለት ለምሳሌ ያህል አይበዛም ጁምአ ማለተ ነው?
- የፀሎት ቀን ትክክል አርብ እለት ይበዛል አልፎ አልፎ
- ሐምሌ 14 የሚሉት ጁምአ ቀን ነው?
- በእለቱ እለቱን ትዝ አይለኝም ጁምአ ይሁን ቅዳሜ ይመስለኛል እኔ
- ሐምሌ 14 በምን አስታወሱ አመት ሊሆነው ነው በምን አስታወሱ?
- በትክክል ብዙ ጊዜ ቋሚ ማስታወሻ የእለት የምንመዘግብበት ማስታወሻ አለኝ ይበልጥ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት ማስታወሻ መያዝ ስለነበረብኝ በማስታወሻዬ ስለመዘገብኩኝ ነው
- መኪናው እንደተሰበረ እርስዎ ምን አደረጉ?
- አቤት
- የመኪናዎ መስታወት እንደተሰበረ እርስዎ ምን አደረጉ?
- የግድ ለቅርብ አለቃዬ ማሳወቅ ብቻ ነው እንጂ ሌላ ምንም የማደርገው ነገር የለም
- ስንት ሰዓት ላይ አሳወቁ ለአለቃዎ?
- ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ይመስለኛል
- እሺ እርስዎ ብዙ ቆዩ እዛ ወይስ ሄዱ ከዛ በኋላ?
- አልሄድንም እዛ ሁላችንም ቆየን የኔ ጉዳት ስለደረሰበት ወዴትም አልሄድኩኝም
- እሺ ሌሎቹ ወደ ሰንዳፋ ሲሄዱ አይተዋል አደለ ?
- አቤት አቤት
- ሌሎቹ ወደ ሰንዳፋ ሲሄዱ አይተዋል ወይ እያሉ ነው እኛ በዋና ጥያቄ አልጠየቅንም ስለ ሰንዳፋ ጉዳይ ምስክሩ የመሰከሩት ስለ ንብረት ጉዳት ነው
- ስጡበት መልስ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ እዛው ነበርኩ ብለዋል እዛው እስከ ስንት ሰዓት ነበሩ ስል ሰዓቱን ገልፀውልኛል ከዚህ በኋላ ወደ ሰንዳፋ እነዚህን እረበሹ የተባሉትን ክፍል ይዛችሁ

ECN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሄዳችኋል ወይ አልኩኝ ስለዚህ እኔ የጠየቅኩት እሳቸው እዛ በመኖራቸው ነው ይሄ ነገር ደግሞ የግድ በአቃቤ ሕግ ሊነሳ አይገባም እዛ ስላሉ ከዚህ በኋላ ይዛችሁ ሄዳችሁ ወይ ነው ጥያቄው?

- እሳቸው የያዙት ባስ ቁጥሩ ወደ ሰንዳፋ ስለሆነ
- ቆይ ይሄ ነው ጥያቄው አደል?
- አዎ
- በቃ እሱ ከሆነ አልተነሳም ሌላ ጥያቄ
- እነዚህ እረብሻ አድርገዋል ወይም ፈጽመዋል የተባሉት ሰወች መጨረሻ የት ሄዱ?
- ምንድን ነው መቃወሚያው ?
- በብይን ታለፈ እኮ አሁን ወዴት ሄዱ በተመለከተ እዛ ቆሜ ነበር ሰንዳፋ ሄደዋል ወይ አልሄዱም በተመለከተ እሳቸው አይመሰክሩም በዋና ጥያቄም እኛ አላስመሰከርናቸውም እኛ ያስመሰከርናቸው የንብረት ጉዳት ሲያሸክረክሩት የነበረው መኪና ላይ ስለደረሰው የንብረት ጉዳት ነው
- ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት እኔ ሰወቹ የት ሄዱ ነው ያልኩት ስለእሳቸው እኮ አልጠየቅንም ሰወቹ የት ሄዱ የፍ/ቤቱን ብይን ተቀበልኩኝ ያን አጠይቅ ተባለ የእሳቸውን ተውኩት ነገር ግን ከዚህ በኋላ እንደዚህ እረበሹ የተባሉትን ሰወች የት ወሰዳችሁ የት ሄዱ ነው ያልኩት ስለሰወቹ ነው የጠየቅኩት ይሄን ደግሞ በዋና ጥያቄ አቃቤ ሕጉ አንስተው ስለ እሩጫ ስለ እረብሻ ብዙ ነገር ተነስቷል እና የሚያያዝ ነገር ነው
- እሺ ብይን ሰጥተናል ጥያቄው ሲወረውሩ የነበሩ ሰወች የት ሄዱ በሚል ነው የያዘው ፍ/ቤቱ ሲወረውሩ የሚሉ ሰወች የት ሄዱ የሚለው ጥያቄ አግባብ ነው በፊትም ተነስቶ ስለነበረ ነገር ግን የት ሄዱ ሲባል ቅድም ተጠይቆ ጥያቄው ድጋሚ ነው ድጋሚ የሚሆነው ለምንድን ነው ይሄ ፀብ እንዴት በረደ የት ሄዱ ሲባል እኔ ምንም የማውቀው ነገር የለኝም በርዷል የሚል ጥያቄ መልሰዋል ከዚህ ተነስተው ያልተነሳ ካለ ነው የት እንደሄዱ አላውቅም እንዴት እንደበረደ አላውቅም ነው ያሉት ቅድም
- እርስዎ የያዙት አውቶብስ ስንት ቁጥር ነበር?
- ቁጥሩን
- የማን ነው የአውቶብሱ ነው?
- ቀድም ጠቅሰዋል ምናልባት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሰሌዳውን አደለም የጠየቅኩት እኔ
- እህ
- የአውቶብስ ቁጥር አለ አደለም እንዴ ከዚህ እስከዚህ ይሄዳል የሚለውን ቁጥር
- ይቻላል ለመግለጽ እሞክራለሁ ለኔ ግልጽ ነው
- እሺ ስንት ነው የጐን ቁጥር አለው
- የጐን ቁጥር ሳይሆን በዚህ የምትሄድ 63 ቁጥር ምናምን የሚባል አለ አውቶብስ አደል የከተማ አውቶብስ ነው
- ትክክል ነው
- ስለዚህ እሱ ቁጥር ስንት ነው ነው ጥያቄው?
- 89 ነው
- 89 ቁጥር አውቶብስ የት ነው የሚሄደው?
- ሰንዳፋ
- ቅድም ሰው ጣና ደርሰዋል ብለው ነበረ እርስዎም የቆሙት አዳራሽ አካባቢ ነው ከአንዋር መስኪድ እስከ አዳራሹ በጣም እረዥም አደል እንዴ ልክ ነኝ እርቀቱ ከአንዋር መስኪድ እስከ አዳራሽ ወይም ልደት ኬክ ቤት እናንት እስከምትቆሙበት ቦታ ድረስ ቢያንስ ሃምሳም ስድሳ ሜትር አይሆንም ወይም መቶ?
- በሜትር መግለጽ ባይቻልም
- እርዝመቱን እስቲ ይንገሩን?
- የእኛ የከተማ አውቶብስ መናሃሪያ በመስኪድ እና በአዳራሽ አማካይ ዳርቻ መንገድ ላይ ነው ብዬ ገልጫለሁ
- እኮ እሱ እርቀት እጅግ እረዥም አደለም ወይ ነው ?
- አሁንም የመስኪድ አቅጣጫ ብዬ ገለጽኩኝ እንጂ መስኪድ ይታያል ማለትም አደለም
- አይ ጥያቄዬን ሰምተውት ከሆነ እረዥም ነው አይደለም ነው?
- እረጅም ነው በሜትር መግለጽ አይቻልም
- ስለዚህ ቅድም ወጡ ያሉት ሰወች ከአንዋር እስከዛ ድረስ መምጣታቸውን ይከታተሉ ነበር ወይም ከአንዋር መነሳታቸውን በምን አወቁ?
- በትክክል የኔ የመጫኛ አቅጣጫ የ89 ቁጥር አቅጣጫ ልክ አስፋልቱ ዳሩ ላይ ስለሆነ ነው ስለዚህ ግራ ቀኝ ማየት ይቻላል ለምን መውጣት ስለተከለከለ
- ከመስኪድ ከራሱ ከግቢ ሲወጡ ያዩዋቸው ሰወች ናቸው?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከመስኪድ አቅጣጫ
- እንጂ ከመስኪድ የወጡ አደሉም ?
- የሚል አገላለጽ የለኝም አዎ
- ሕዝቡንስ መገመት ይችላሉ ቁጥሩን ቅድም ሲሮጥ የነበረው ምን ያህል ሕዝብ ነው መገመት ይችላሉ ?
- ይሄን ያህል ብዬ መገመት አልችልም
- ምን ያህል ይሆናል መገመት አይችሉም?
- መገመት አልችልም
- ሃምሳ ሺ መቶ ሺ?
- አይ እሱን ጥያቄ እለፉት
- ሁሉም ሕዝብ ነበረ ድንጋይ የሚወረውረው?
- ለኔ መታየት በሚችለው ደረጃ የተወሰነ ክፍል ወደኛ አቅጣጫ ወርውረዋል
- ወደ አውቶብሱ?
- አዎ
- ወደሌላስ ሲወረውሩ አይተዋል?
- እሱም ተመልሷል እኮ ባካችሁ አትደጋግሙ
- የተከበረው ፍ/ቤት ይኖራል
- ካለ ጠይቁ ግን አሁን ችግሩ አትደጋግሙ አሁን ቅድም ያለውን ነገር
- እሺ አቶ ደረጀ የመጨረሻ አንድ ጥያቄ ልጠይቆት ይህ ሁሉ ነገር ከሆነ በኋላ የናንተ አውቶብሶች ስራ ስንት ሰዓት ጀመሩ አስር ሰዓት ?
- የኔ አውቶብስ
- የእርስዎ ሳይሆን እዛው ስምሪት ለምሳሌ 89 ቁጥርነው ያሉት እና ሌሎች 89 ቁጥሮች እና ለሎችም ባሶች ስንት ሰዓት እንቅስቃሴ ጀመሩ?
- አብዛኛው ክፍል ወደ ግቢ አቅጣጫ እንድናመራ ነው ወደ መናሃሪያቸው ወደ ማደሪያ እንትናቸው እንድንሄድ ነው የታዘዙት
- እሺ ከዛ በኋላ ወደ ስራ የተሰማራ አ ውቶቢስ አልነበረም ማለት ነው ?
- ይኑር አይኑር እርግጠኛ አደለሁም ወደ ግቢ ሁላችንም ለመሄዳችን ወደ ግቢ አቅጣጫ ስለሄድን የኔም ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ
- እሺ በቃ ይኑር አይኑር ካላወቁ ይበቃል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እናንተ ወደ ግቢ ስትመለሱ እርስዎ እረብሻ ያሉት ነገር ቆሞ ነበር አደል?
- እሱ እኮ ተመልሷል ቢዝርዝር እራሶ ጠይቀው ለራሶ ነው የተመለሰው በፊት ፀቡ እንዴት በረደ ተብሎ እንዴት እንደቆመ
- አይ እነሱ ሲመለሱ ፀቡ ቆሟል ወይ የሚለውን
- እነማን ሲመለሱ
- አሁን ወደ ስራ አልተሰማራንም ተመለስን ወደ ማደሪያችን አሉ አውቶብሶቹ እና ሲመለሱ ቆሞ ነበረ ወይ ነው ጥያቄዬ
- ንቀሳቀሳችኋል እንዴ እናንተ ?
- ተንቀሳቅሰን ወደ ግቢ እንድንሄድ ታዘናል አዎ
- እሺ ሌላ ጥያቄ ቀጥሉ
- እሺ ሲጀምሩ ምስክርነቶን መርካቶ አካባቢ ትንሽ እረብሻ ነበር ብለዋል እረብሻው ትንሽ ነበረ ማለት ነው?
- እሱም ተመልሷል ለምዘና በቂ ነው
- ይቅርታ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ደረጄ ቅድም ፌደራል ፖሊሶችን አይቼ ነበረ ብለዋል ቁጥራቸው ምን ያህል ይሆናል ?
- የመቁጠር ኃላፊነቱ ምን ያህል እንደሆነ አላውቅም አልቆጠርኩኝም
- ብዛታቸው መገመት አይችሉም ?
- መገመትም አስቸጋሪ ነው ለምን ሲንቀሳቀሱ
- በቃ ይበቃል
- ጨረሳችሁ
- ጨረስን አዎ
- ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ አቃቤ ሕግ
- እሺ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- አቶ ደረጄ አሁን በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ ከአንዋር መስኪድ አቅጣጫ ስለሆነ ነው እንጂ ከአንዋር መስኪድ ይውጡ አይውጡ ግምት ነው ብለዋል እናንተ ተጠልላችሁ ለረጅም ሰዓት ቆማችኋል አደል ?
- አዎ
- መኪናችሁም ላይ ንብረታችሁ እናንተ የምታሽከረክሩበት መኪናችም ላይ ጉዳት ደርሷል ይሄ ነገር በምን ምክንያት ነው ተብሎ ይጠየቃል ዝም ብሎ በተሰማዉ ቦንብ ዘይቤ አደል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ምክንያቱ ምንድን ነው ተብሎ ይጠየቃል እና አልጠየቃችሁም ወይ ምንድን ናቸው እነዚህ ሰወች ምንድን ነው ምክንያታቸው እንደዚህ ንብረት ላይ ጉዳት ሊማድረስ ምክንያታቸው ምንድን ነው ብላችሁ አልጠየቃችሁም?

- መቃወሚያ አለን
- ምንድን ነው መቃወሚያው?
- እኛ የፀቡን ምክንያት አልጠየቅንም ምስክሩን በምን ተነሳ ጉዳዩ እረብሻው በምን ተነሳ አልጠየቅነውም እኛ ባላነሳነው ጥያቄ የተከበሩ አቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ ሊያነሱ አይችሉም ስነስርዓትም አይፈቅድላቸውም
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት በአንዋር መስኪድ እና በእናንተ መሃከል የነበረው እርቀት ምን ያህል ነው ሰወቹ ከአንዋር መስኩድ ሲወጡ አይተዋል ወይ በትክክል እየተባለ ያለው እነዚህ ሰወች አይተዋል ወይ በትክክል እየተባለ ያለው እነዚህ ሰወች ወይም ደግሞ ድንጋይ ንብረቱ ላይ ጉዳት አድርሰዋል እየተባሉ ያሉት ሰወች ከመስኪዱ ውጪ ናቸው የሚለውን ነው በመስቀለኛ ጥያቄ ለማስመስከር የተፈለገው ስለዚህ አሁን ምክንያቱ ምንድን ነው ተብሎ ሲጠየቅ እሳቸው የሚመልሱት መልስ እነማን ናቸው የሚለውን ነገር በትክክል ይለያል ግልጽ ያደርጋል ያብራራል ስለዚህ ተገቢ ነው ከነሱ መስቀለኛ ጥያቄ ተነስተን ነው እየጠየቅን ያለነው ነው
- እሺ መስቀለኛ ጥያቄው ላይ እኛ በያዝነው በዓፍነው እንትን ላይ የጠቡ ምክንያት ምን ነበር ተብሎ አልተነሳም የተነሳው ነገር አቃቤ ሕግም ቅድም እንዳነሱት ሰወቹ ከመስኪድ ውጭ የሆኑ ከውስጥ ይሁኑ አናውቅም ማለት የት ይሁኑ ያውቃሉ አያውቁም የሚል ጥያቄ ነው የተነሳው ስለዚህ እርስዎ ይሄን መሰረት አድርገው ይጠይቁ መጨረሻ ላይ በተደረረው ሰወች የት ነበሩ በሚል ነው
- እሺ አቶ ደረጀ በግልጽ እስቲ ይንገሩን ሰወቹ በትክክል ከየት ነው የወጡት ?
- በትክክል ከዚህ ቦታ ነው ለማለት የፀሎት ሰዓት ከመሆኑ አኳያ በመገመት ካልሆነ በስተቀር ከዚህ ቦታ ብዬ መግለጽ አልችልም
- እኮ የፀሎት ሰዓት ከመሆኑ ብለው በመሆኑ ከዚህ ተነስቼ ገመትኩኝ የሚሉት ምንድን ነው ግምቶትን እኮ ነው አሁን ግልጽ አርገው ለፍ/ቤቱ [illegible] ቅድምም ግምቴን ሲሉ ከፀሎት የሚወጡ ይመስሉኛል ብለውናል አደል
- አዎ ትክክል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ ይሄን ግምቶትን በደምብ አብራርተው ይሄን ግምት የወሰዱበትን ሁኔታ እንዲነግሩን ነው የፀሎቹ ስለሆነ የምን ፀሎት ለምሳሌ ?
- የመ·ስሊም ሕብረተሰብ ፀሎት ብዬ ነው የምገምተው
- ከዛ ፀሎት ጋር የተያያዘ ነው የሚል ግምት ነው የወሰዱት ?
- ብዬ ነው የማስበው አዎ ትክክል ግምት ነው
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ እናመሰግናለን ጨርሰሃል
- እሺ አመሰግናለሁ
- እሺ የዛሬውን ምስክር መስማት በዚሁ ጨርሰናል ትእዛዝ ተሰጥቷል

ትእዛዝ

- 1ኛ ዛሬ የተሰሙት የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ተገልብጦ ከመዝገቡጋር እንዲያያዙ ትእዛዝ ተሰጥቷል 2ኛው አቶ ተማም ማለት ነው አልመጡም አደለም ከዚህ በፊት እንዲመጡ ተብሎ አልመጡም ስለዚህ በነአቡበከር አህመድ መዝገብ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ችሎት ቀርበው የሚያስረዱት ነገር ስላለ በፌደራል ፖሊስ በኩል መጥሪያ ደርሷቸው ለ15/6/2005 ለአርብ ጠዋት ሦስት ተኩል እዚህ ችሎት እንዲቀርቡ ታዟል መጥሪያው ለፌደራል ፖሊስ ይተላለፍ ተብሏል ቀሪውን የአቃቤ ሕግ ምስክር ለመስማት ነገ ሦስት ተኩል ላይ ቀጠሮ ተይዟል በተለመደው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

4ኛ ወ.ችሎት

የመ.ቁ 124754

14/6/05 ዓ.ም

ዳኞች:- ብስራት ተልዕቀ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሣሽ:- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ አቶ ብርሃኑ ወንድማገኝ አቶ ቴዎድሮስ ጌታቸው አቶ ዘረሰናይ ምስግና

ተከሣሾች:- እነ አቡበከር አህመድ የቀረ ሰው ካለ 21ኛ ተከሣሽ አልቀረቡም ማረሚያ ቤት መምጣት አልቻለም 21ኛ ተከሣሽ

ጠበቆች ሀሰን ሁሴን፣ ተካ ዳባ፣ መሐመድ አብደላ ፣ ባህሩ መካንጋ እና አዲስ መሐመድ የ 28ኛ ተከሣሽ ጠበቃ አህመድ ጀማል

- ጠበቆች የቀረቡት ሰማቸውን በመቅረፀ ድምፅ አስመዝግበዋል እሺ ዐቃቤ ሕግ 21ኛ ተከሣሽ አልቀረበም የተለየ ነገር ካለ
- ያው የተለየ ነገር የለም ቢያንስ ለጠዋቱ /ግልፅ ያልሆነ/ የተለየ የለም በአጠቃላይ ጭብጡ ላይ ነው የሚያስረዱት ያው ጠበቆቻቸው ስላሉ መቀጠል እንችላለን እሳቸው ላይ ፕሮሰናል የሚያስረዳ የለም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጠበቆች 5 ቀርበዋል የ 28ኛ እንደዚሁ ለብቻው 6 ጠበቆች ቀርበዋል ሌሎቹ አልቀረቡም ዐቃቤ ሕግ ምስክሩ ይቅረብ
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ
- ለምስክርነት ነው የመጡት አይደል ?
- አዎ
- ስምዎን የአባትዎን ስም ሳይጨምሩ የራስዎን ስም ብቻ ይገልፁልናል
- ሚፍታህ
- ስንተኛ ላይ የተጠቀሱ ናቸው ዐቃቤ ሕግ
- 126
- 46ኛ ላይ ደርሰናል በተሰሙት ልክ በማስረጃ /ግልፅ ያልሆነ/ 126 ላይ የተጠቀሱት ምስክር ቀርበዋል በእነ ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ቶ ሚፍታህ ?
- እኔ ባለፈው መኪናዬ ላይ በተሰበረው ነው በአንበሳ አውቶቢስ ላይ በደረሰ ጉዳት ነው
- መቼ ነው ?
- በ 14/11/
- ዓ.ም ?
- 2004
- ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- ምስክር ሊመሰክሩ የመጡበትን ነገር በዝርዝር ያስረዳሉ ከጊዜው ይጀምራሉ ጊዜውን ያስታውሳሉ ?
- ጊዜውን አዎ
- መቼ ነው ?
- ጊዜው ሐምሌ 14 ነው 11ኛ ወር 2004 ዓ.ም ነው
- ስንት ሰዓት ነው ?
- ሰዓቱ ወደ 8 ሰዓት
- ቀን ነው ለሊት ?
- ከቀኑ 8 ሰዓት አካባቢ ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የት ?
- መርካቶ ተርሚናል
- እርሶ አሁን በጠቀሱት ጊዜ እና ቦታ ምን እያደረጉ ነበር ?
- እኔ 30 ቁጥር ላይ እየጫንኩ ነበረ አውቶቢስ ሰውን ማለት ነው
- ከየት ወዴት ?
- ከመርካቶ ሱሉልታ በቃ ሱሉልታ እየጫንኩ እያለ እኔ ሰው በር ከፍቼ ነው እየጫንኩ ትኬተር እየቆረጠ ነው ከእዚያ ረብሻ ከእዚያ ከመስኪዱ አካባቢ በጣና እኛ እንደውም 30 ቁጥር የሚጭነው ጫፍ ነው የእኛ ነው መጀመሪያ ከእዚያ እየጫነ እያለ ረብሻ መጣ እኔ ወረድኩኝ
- ከየት መጣ ረብሻ ?
- ከመስኪድ ከጣና አካባቢ
- ምን መስኪድ ?
- ከአንዋር
- ከአንዋር መስኪድ ?
- ከአንዋር መስኪድ
- አንዋር መስኪድ ጋር ሲመጣ እኔ ከመኪና ወረድኩ ምንድን ነው ብዬ ጠየኩ አይ ከመስኩድ የሚመጡ እየተረበሸ ነው ተባልኩ በሰው ከእዚያ በኋላ ረብሻው እየባሰ መጣ ወደ እዚህ ወደ እኛ
- እንዴት በምን መልኩ ነበር ረብሻው ?
- ድንጋይ ውርወራ አለ ሁሉ ማለትም ከእኛ በፊት የነበሩ ሕንፃዎች አካባቢ ምናምን እየተመታ ስለነበር እኛ አሁን ከእዚያ ልንወጣ ስንል እንትኖች እንዳትወጡ አሉን ቆምን በቃ እዚያ
- ከእዚያስ ?
- ከእዚያ በኋላ ወደ እኛ አካባቢ መጡ የእኛን አውቶቢስ እኔ ፊት ነው ያለው የእኔ እንደውም ፊቱ ላይ 4 ቦታ ነው ምናምን መስታወቱን መቱት
- በምን ?
- በድንጋይ
- ምን ሆነ ?

2444 581

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተሰባበረ /ግልፅ ያልሆነ/ መስታወት አዲስ መኪና ማለት ነው
- የአውቶቢሱ የፊት መስታወት ብቻ ነው የተሰበረው ?
- አዎ የእኔ አዎ
- ሌላ ያዩት አለ እንዴ የእኔ የሚሉት ሌላስ አለ የተሰበረ ?
- ሌላ
- የእኔ የፊት መስታወቱ ነው የተሰበረው አሉ ?
- አዎ
- ሌላስ ያዩት አለ ወይ ሌላ የተሰበረ አለ እንዴ ?
- ሌላ የለም /ግልፅ ያልሆነ/
- ይሄ ረብሻ የምን ረብሻ ነው እነ ማን ናቸው የሚረብሹት ?
- እኔ ረብሻውን ከመስኪድ መምጣታቸውን ነው ከመስኪድ አካባቢ መጡ አላህክበር እያሉ መጡ ከእዚያ በኋላ እኔ መስታወቴ ሲመታ እኔ ወደ ኋላ ሄድኩ በቃ
- አላህክበር ከማለት ውጪ ሌላ የሚናገሩት ነገር ነበር ?
- እኔ አልሰማሁም
- አልሰሙም የእርሶ መኪና የተመታው ሆን ተብሎ ነው ወይስ እንዴት ነው የተመታው ?
- አዎ ሆን ተብሎ ነው ማለትም እኔ ዳር ነው ያለሁት ያኛው ዋናው መንገድ በቃ ያ ዋና መንገድ ወደ ጣና መውሰጂያ ነው የእኔ ጫፍ ነው የሌሎችም አውቶቢሶች ነበሩ በቃ ከእዚያ ድንጋይ ይዘዋል እየተወራወሩ ነበረ
- ለምን ተመታ አውቶቢሱ ለምን ተመታ ?
- ያው የመንግስት ነገር በመሆኑ ይሁን እንደዚህ ይመስለኛል እኔ
- እስቲ ወደ እዚህ እያዩ እንደዚህ
- የመንግስት ነገር በመሆኑ ይመስለኛል እንጂ
- ሰው ጭኖ ነበር አውቶቢሱ ?
- አዎ ጭኜ ነበር ልክ ረብሻው እየመጣ እያለ ገና የእኔ መኪናው ከመመታቱ በፊት አስወረድኳቸው ውረዱ ውረዱ ብለን
- እነዚህ ድንጋይ ይወረውሩ የነበሩ ሰዎች ረብሻ ላይ የነበሩ ሰዎች በምን መንገድ ይሆናሉ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በግምት ከ 200 ይበልጣል በቃ 200 ሁለተ መቶ ብላይ ይሆናል
- ቅድም ሲጠየቅ ስትመልስ ከአንዋር መስኪድ አካባቢ ነው የመጡት ብለሀል ?
- አዎ
- እንዴት አወክ ?
- ጫፍ ነኝ እኔ እኮ ላለሁ እኮ እኔ እራሴም እኮ ጫፍ ነው አንዋር መስኪድ እኮ ይታይሀል ቢቃ በእዚያ በጣና በኩል ይታያል እንደዚህ ያው መንገድ ነው ሌላ መንገድ የለም
- የእዚያን ቀን ከ 8 ሰዓት በፊት ረብሻ ነበር ?
- አልሰማሁም /ግልፅ ያልሆነ/
- የሰማኸው ነገር የለም ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አንተ በወቅቱ ይዘኸው የነበረው የአንበሳ አውቶቢስ መኪና ታርጋ ቁጥሩን ታስታውሳለህ ?
- ታርጋው 76592
- ኮዱስ ?
- 3
- አዲስ አበባ ነው ?
- አዎ
- ዋና ጥያቄ አበቃ
- የተከሣሾች ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ
- አቶ ሚፍታህ ዐቃቤ ሕግ ሲጠይቆት ሲመልሱ ረብሻው እየባሰ ሲመጣ ውርውራ ነበር ብለዋል ደግሞ ልንወጣ ስንል እንትኖች እንዳትወጡ አሉን ነው እንትኖች ያሏቸው ምኖችን ነው ?
- ማለትም ስምሪቶች ማለት ነው መኪናው ከወጣ አደጋ ይደርስበታል የሚል ግምት አለ ረብሻው እየመጣ ስለነበረ ያው ቆይ እስቲ ተባልን
- ከኃላፊዎቻችሁ ማለት ነው አትውጡ የተባለው ?
- ኃላፊዎቻችን ናቸው አዎ የስምሪት ኃላፊዎች አሉ
- አትውጡ ያሏችሁ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ማለትም አዎ ረብሻው ውጪ ስለሚሰበር እዚያ አካባቢ ይነካል የሚል ግምት ስለሌላቸው ቆዩ አሉ
- አጠር እያደረጉ ይመልሱልን ጥያቄውን ብቻ ማለት ነው ኃላፊዎቻችሁ ወይም ስምሪቶች አትውጡ እንዳላቸሁ ነው ወዲያው ድንጋይ ውርወራ የተጀመረው ?
- አዎ ቆመን እዚያው ቆመን አዎ
- ወዲያኑ ነው ድንጋዩ መወርወር የተጀመረው ?
- አዎ ወዲያውኑ ነው
- ምንም ምን ያህል ደቂቃ የሚሆን ልዩነት ?
- የ 4 ደቂቃ እና የ 3 ደቂቃ ልዩነት
- 4 ደቂቃ 3 ደቂቃ ልዩነት ውስጥ ?
- አዎ
- ወዲያውኑ ድንጋዩ /ግልፅ ያልሆነ/
- ወዲያውኑ /ግልፅ ያልሆነ/ ተጀመረ አዎ
- እርሶ ይሄንን በደንብ ያስታውሳሉ ?
- አዎ
- ድንጋይ ይዘዋል በእየተወራወሩ ነበር ብለዋል አሁን መወርወር እና መወራወር ልዩነት አለው 2 ወገን ሆነው ነበር ማለት ውርወራ የነበረው ከእዚህ የእናንተ አውቶቢሶች ካሉበት ወገን እና ከሌላ ወገን የሚወረውር ነበር ?
- አዎ በእዚያ በኩል ፖሊሶች አሉ
- ፖሊሶች ይወረውሩ ነበሩ ?
- አይወረውሩም ፖሊሶች ያው እነሱን ሲያባርሯቸው ሂዱ ሲሉ ያው ከእኛ አካባቢ እያገለሉዋቸው እየመጡ እያሉ ይሄንን /ግልፅ ያልሆነ/
- የሕዝቡ ነው እነዚህ 200 ሰዎች ናቸው በእናንተ አቅጣጫ የነበሩት ወይስ ፖሊሶች ናቸው ?
- አዎ
- በእናንተ አቅጣጫ የነበሩት ?
- በእኛ አቅጣጫ የነበሩ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- 200 የሚሆኑ ሰዎች ናቸው ?
- አዎ
- ፖሊሶች ከሌላ አቅጣጫ ነው የነበሩት ?
- አዎ እነሱ ከእዚያ በኩል ገና እየመጡ
- ይሄ ነገር እንደተፈፀመ ወደ ስራ ተሰማራችሁ ወይስ ?
- እኔ ወደ ግቢ ነው የሄድኩት
- ሌሎችስ ወደ ስራ የተሰማሩ አሉ ?
- አይ እሱማ ወደ ግቢ ነው ሂዱ የተባለው
- ከእዚያ በኋላ ስራ አልሰራችሁም ?
- አልሰራንም
- አውቶቢሶች ስራ ላይ አልተሰማሩም ?
- አዎ
- ከመስኪድ አቅጣጫ ያሏቸው ሰዎች እርሶ የት ላይ ሆነው ነው ያዩዋቸው ?
- እኔ ጫፍ ላይ በቃ ማለትም ግፋ ቢል 4 ሜትር 5 ሜትር ይሆናል በቃ ጫፉ ነው እንደዚህ መንገድ ነው
- እኮ አሁን ከጣና አቅጣጫ ነው ያሉት እና ይሄ የእርሶ ግምት ነው እንጂ ከመስኪዱ ይውጡ አይውጡ አያውቁም አይደል ?
- አይ ሰውም ጠይቄአለሁ እኮ ረብሻው ከመስኪድ እንደተከሰተ ከየት ነው ጩኸቱ ምናምን ስል ከመስኪድ አካባቢ ሲባል
- አሁን የምንጠይቆት ነገር የእርሶን መኪና የመታው ድንጋይ ከመስኪድ የወጣ ሰው ይሁን አይሁን ማወቅ አይችሉም አይደል ?
- ያው ከመስኪድ አካባቢ ከፖሊሶች እንደዚህ አባረዋቸው የመጡ ሰዎችን
- ጥያቄዬን ግልፅ ላድርግሎት አሁን እርሶ ያሉት የአውቶቢስ ተርሚናል ጋር ነው ብለዋል ?
- አዎ
- በአውቶቢስ ተርሚናል እና በመስኪዱ መሀል ምን ያህል ርቀት አለ 200/300 ሜትር በላይ?
- 200 ሜትር

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከ 200 ሜትር በላይ ነው አይደል ?
- 200 ሜትር /ግልፅ ያልሆነ/
- ስለዚህ እርሶ አሁን ከ 200 በላይ ርቀት ላይ ቆመው አንድ ሰው ከመስኪድ ይምጣ አይምጣ ሊያውቁ አይችሉም አይደል ግምት ነው ይሄ ?
- ግምት
- ግምቶት ነው እንጂ እነዚህ ሰዎች ከመስኪድ ይምጡ አይምጡ አያውቁም ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ይሄንን እስቲ አንዴ ያረጋግጡልን ከመስኪድ ይምጡ አይምጡ አያውቁም አይደል ?
- ይሄ ተመልሷል
- አልተመዘገበም ስላሉኝ ነው ባልደረቦቼ አልተሰማንም ስላሉኝ ነው
- ይሄ ሳይሆን ቅድም እኮ መልሰውታል ድጋሚ ነው የጠየቁት ቅድም መልሰዋል ሰዎች ነግረውኛል ጠይቄ
- ለምን የተከበረው ፍ/ቤት 2ኛውስ አይመዘገብም ሰዎች ነረውኛል ያለው ብቻ ሳይሆን ግምቴ ነው የእርሶ ግምት ነው
- ይሄ ተመልሷል እሱ በሚያውቀው ከሰው ጠይቄ ተነግሮኛል ብለው ምላሽ
- ፖሊሶቹ እየሸሹ ነበር የሚመጡት ብለዋል እየደበደቧቸው ነበር ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ እነሱ እየተጠጓቸው ሲያባርሯቸው እየወረወሩ ነው እነዚያ የሚሸሹት
- ምንድን ነበር ፖሊሶቹ ምን ለብሰው ነበር ?
- የፖሊስ ልብስ ነዋ
- የፖሊስ ልብስ የፌዴራል የፖሊስ ልብስ ነው ፌዴራሎች ናቸው ወይስ ኖርማል የፖሊስ ልብስ የለበሱ ?
- ኖርማል ፖሊስ
- የፌዴራል ፖሊስ ልብስ የለበሰ አላዩም ?
- ፌዴራል ፖሊስ ከእዚያ በኋላ መጣ
- ከእዚያ በኋላ ምን አደረጉ ምን የተጠቀሙት ነገር ነበረ ድምፅ የሰሙት ለመከላከል ያንን ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምንም ያው መከላከያ የያዙት /ግልፅ ያልሆነ/ እዚያ ፖሊስ መከላከያ /ግልፅ ያልሆነ/ እንትን የሚሉ ነበሩ
- መከላከያ ማለት ምንድን ነው ?
- ይሄ ምንድን ነው ድንጋይ መከላከያ
- ሌላ
- ፖሊሶች እነዚያ እነሱ መጡ ከእዚያ በቃ
- ጭሽ ምናምን መተኮሱን አላዩም ወይ አልሰሙም እርሶ የአስለቃሽ ጭሽ መተኮሱን አላዩም አልሰሙም እርሶ ?
- ሽጭ ተተኩሷል መጀመሪያማ
- የአስለቃሽ ጭሽ ?
- አዎ ወደ እዚያ /ግልፅ ያልሆነ/
- ከእዚያ በኋላ ነው ልጆቹ እየሸሹ የመጡት ?
- ሰው ሸሸ በቃ ሸሸ ሄደ
- ሌላስ ተኩስ ድምፅ አልሰሙም ?
- አልሰማሁም
- የአስለቃሽ ጭሱን ብቻ ነው የሰሙ እና ያዩት ?
- አዎ
- አቶ ሚፍታህ ሰው እንግዲህ አሁን ቅድም እንደነገሩን ፖሊስ አለ ረባሾቹ አሉ ፖሊስ አሁን ከአንዋር እርሶ እስካሉበት ፖሊሱ ያለው ጣና ጋር ነው ረባሾቹ እና በፖሊስ መካከል ያለውን ርቀት ስላዩ ፖሊስ ጣልቃ ገብቶ ከእዚያ ወደ እዚህ የሚያባርራቸው የት ጋር ደርሶ ነበር አንዋር መስኪድ ገብቶታል ጥያቄው አንዋር መስኪድ አለ ?
- አዎ
- ወደ አንዋር ደግሞ ድንጋይ የሚወረውር ሰው ድንጋይ ወርዋሪዎች ከእዚያ ደግሞ ፖሊስ አለ አሁን ሰዎቹ ፊታቸውን መጀመሪያ ወደ አንዋር አድርገው እየወረወሩ ፖሊስ እያሳደዳቸው ነው አይደል ?
- ወደ እዚህ ወደ እዚያ እንዲሸሹ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወደ ኋላ እናንተ ?
- አዎ ወደ እዚያ ወደ አስፋልቱ ወደ ምዕራም አካባቢ እንዲሂዱ ማለት ነው
- ወደ ምዕራብ እንዲሄዱ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እነሱ ፊታቸውን ወደ አንዋር አድርገው ከፖሊስ ጋር ተፋጠው ነበር ?
- አዎ
- ፖሊሶቹ የት ደርሰው ነበር ወደ ኋላ እየገፉ ?
- በቃ እኛ ጋር አካባቢ እኛ ንብረት አካባቢ ሲደርስ አንበሳ አውቶቢሶች ጋር ሲደርስ ቆሙ በቃ
- የለም መጀመሪያ አሁን እርሶ ወደ አንዋር ሲያዩ ፖሊሶቹ የት ጋር ደርሰው ነበር እርሶ አይኖ ሲያዩ ጣና ጋር ደርሰው ነበር ፖሊሶቹ ?
- ፖሊሶቹ እንትኖቹ እኛ አካባቢ እንዳሉ እነዚያ ወደ ጣና ጋር
- ፖሊሶቹ ጣና ጋር ነበር ?
- አዎ እንደዚያ
- ስለዚህ ድንጋይ ወርዋሪዎቹ ወደ አንዋር እየሄዱ የቆሙ ማለት እናንተ ጋር አሁን ባስ ማቆሚያው ጋር አለ ከእዚያ ምን ያህል አልፈው ወደ ፖሊሶች ተጠግተዋል
- ምን ያህል
- ማለት አልፈው አሁን ልደት ኬክ ቤት አለ ?
- አዎ
- የእናንተ ማቆሚያ አለ ?
- አዎ
- ከእዚያ ቀጥሎ ሕንፃዎች አዲስ የተሰሩም አሉ ጣና ከመድረስዎ በፊት ?
- አዎ
- ስለዚህ እነዚህ ድንጋይ ወርዋሪዎቹ ወደ አንዋር በሚሄደው አቅጣጫ ድንጋይ እየወረወሩ የት ጋር አልፈው ሄደው ነበር እርሶ እዚያው ስለነበሩ ወደ ፖሊሶቹ ምን ያህል ተጠግተው ነበር ?
- ግፋ ቢል ከ 50 ሜትር በቃ 60 /70 ሜትር ይሆናል
- ስለዚህ እርሶም ያዩዋቸው ፊታቸው ወደ አንዋር አቅጣጫ ሆነው ነው ያዩዋቸው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወደ አንዋር አዎ
- እንጂ ከአንዋር ወደ ኤዚህ ሲመጡም አላዩም ?
- አይ መጀመሪያማ ወደ አንዋር ነበር እኔ ሳያቸው እኮ ወደ አንዋር ዞረዋል ወደ እዚያ ነበሩ
- ፊታቸውማ ወደ አንዋር እኮ ነው ችግር የለውም እርሶ በአይንዎ ማየት በጀመሩበት ጊዜ በአንዋር አቅጣጫ ወደ ምዕራብ ፊታቸውን አዙረው የሚያሳድዱ ፖሊሶች አሉ ?
- አዎ
- ከእዚህ ደግሞ ወደ አንዋር አቅጣጫ ድንጋይ የሚወረውሩ ሰዎች አሉ ?
- አዎ
- እርሶ ያዩት ይሄንን ነው ?
- አዎ
- አሁን ድንጋይ የሚወረውር ሰው አለ ወደ 200 የሚሆን እርሶ እዚያ ጫፍ ላይ እንዴት ቆሙ ማለት እራስዎ ላይ እኮ አደጋ ሊደርስ ይችላል እንዴት ሊቆሙ ቻሉ ?
- እየቀረበ ሲመጣ ቢሮ አለች እዚች ጫፏ ላይ እንደዚች አጠገባችን ጋር እንዲህ ሰምሪት ቢሮ አለ በቃ ወዲያውኑ በሩ ተከፈተልን ልክ ድንጋዩ ሲያርፍ ገባን እኛ
- ስለዚህ ምን አስከምን ድረስ አይተው ነው የገቡት ምን ምን ካዩ በኋላ ነው የገቡት ?
- በቃ ልክ መስታወቱ መመታት ሲጀምር
- አውቶቢሱ ?
- አዎ ልክ ሲያርፍበት በቃ ወዲያውኑ እኛ ገባን ከእዚያ ፖሊሶቹ እንደገና እንትን ሲሉልን ወጣን በቃ
- ጥሩ በእዚያን ዕለት ከምዕራብ አቅጣጫ እስከ 7ኛ አቅጣጫ ወደ አንዋር አሁን ባሉት መልክ አላህ ክበር እያለ ወይም በሌላ መልክ የሚመጣ ሰው አልነበረም ?
- ነበረ
- ከእዚያ አቅጣጫ ሲመጣ ነው ያዩት ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ምናልባት ከምዕራብ አቅጣጫ የሚለው መነሻ በኋላ ለመመዝገብ አስቸጋሪ ስለሚሆን መነሻውን አስተካክሉት ወይም ምዕራብ ሆቴል ?

2151 589

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ምዕራብ ሆቴል ማለቴ ነው ምዕራብ ሆቴል የ 7ኛ መንገድ አለ
- አዎ አውቀዋለሁ
- ከእዚያ ወደ እዚያ የሚመጣ ነው
- ቀጥሉ
- አሁን አደጋው ድንጋይ መኪናው ላይ አረፈ መስታወቱ ምን ሆነ ተሰበረ አሉ ?
- አዎ
- ተሰብሮ ማለት አንዳንድ ጊዜ ስብርብር ብሎ እዚያው ተሰነጣጥቆ ይቆማል ወይስ መሬት ረገፈ?
- እንደውም ይሄ መኪና አዲሱ መኪና ነው ድንጋጉ በስቶት ገባ ከቅርበቱ አንፃር አዎ በስቶ እስከነመስታወት እንደዚህ ቦጭቆት ገባ ዳሽ እንትኑ ላይ
- ያቺ የተቦጨቀችውን ቦታ ይዞ ገባ ነው ?
- አዎ
- አንድ ድንጋይ ነው ?
- ሌላው በቃ ሰነጣጠቀው
- ሰነጣጠቀው ?
- አዎ
- ከእዚያ አደጋው ከበረደ በኋላ መኪናው ሄደዋል እርሶ ?
- አዎ
- አሁን አካባቢው በድንጋይ ውርወራ ቆሸሾ ነበር አይደል ምን ዓይነት ወርዋሪዎቹ ተራ ድንጋይ ነበር የሚወረውሩት ወይ የተለየ ድንጋይ ነበረ ወይ ያገኙትን ነበር የሚወረውሩት ?
- ያገኙትን ድንጋይ ነው
- ያገኙትን ነው እንጂ አሁን ይሄ ኮብል እስቶን ምናምን እንደዚህ ነገር አላዩም ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- መንገድ ላይ የተሰራ ?
- አዎ
- አቶ ሚፍታህ እርሶ አውቶቢሱን በድንጋይ የመታውን ሰው አይተዋል እንዴ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አላየሁም
- አላዩም አይደል-?
- አዎ
- አውቶቢሱ ከተመታ በኋላ ነው ተመልሰው መጥተው ያዩት ?
- አዎ
- መመታቱን ያረጋገጡት ?
- ያው ብዛት ስለነበራቸው ግማሹ አትምታ ይላል ግማሹ ምታ ይላል በለው በለው ሲባባል አንድ ድንጋይ ሲያርፍ በቃ እኛንም ሊመቱን ነው ብለን በቃ ገባን
- ስለዚህ አሁን ከገቡ በኋላ ወጥተው አውቶቢሱን ሲያዩ ነው መመታቱን ያወቁት ማለት ነው ?
- አዎ
- ስለዚህ አውቶቢሱ ሆን ተብሎ ይመታ በአጋጣሚ ይመታም አያውቁም አይደል ካላዩ ?
- ያው ሆን ተብሎ ነው መጀመሪያ አልተመታም ነበረ በኋላ ላይማ ያው
- መጀመሪያማ ምንም ነገር ስለሌለ ሊመታ አይችልም በኋላ ላይ ግን ግርግር ስለነበረ በግርግሩ ውርወራ መወራወር ነበረ ስላሉ በውርወራው ሂደት አንዱ ለአንዱ የወረወረው አውቶቢሱ ላይ አርፎ ሊሆን ይችላል አይደል
- ቆይ ቆይ እስቲ ይሄ ተመልሷል እኮ እየገደሙ ነው እርሶ ግማሹ ምታ ምታ ይላል ግማሹ አትምታ ይላል አንዱ ሲመጣ እኔ ወደ ቤት ገባሁ ነው ያሉ ይሄ ተመልሷል እስከእዚህ ያለው ማለት ከእዚህ በኋላ ያለው
- የተከበረው ፍ/ቤት አሁን እኔ መጠየቅ የፈለኩት
- እንዴት እንደተመታ አታውቅም አይደለም ወይ
- አዎ ኢንቴንሽን ጋር የተያያዙ ነገሮች
- ይሄው እኮ መለስ እኮ ግማሹ ምታ ይላል ግማሹ አትምታ ይላል
- እሳቸው ሆን ተብሎ ይመታ አይመታ በቦታው ስላልነበሩ አያቁም የሚለውን ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- ያሉትን ነገር እኮ ግማሹ ምታ ይላል ግማሹ አትምታ ይላል
- እሱን ለማጣራት ነበር የተከበረው ፍ/ቤት
- ምታ አትምታ የተባለው አውቶቢሱን ነው ወይስ ሌላ ነገር ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አውቶቢሱን ነው እንጂ
- ኢንቴንሽን ከእዚህ ነው ኢንፈር የሚደረገው
- እርሶ ሲመታ አልነበሩም ?
- አዎ
- እኮ ታዲያ
- ምታ ሲባልማ እኔ ነበርኩኝ የእዚያን ጋር
- እና ምታ ሲባል ዝም ብለው እያዩ ነበር ?
- ታዲያ ቆሜ ስለነበረ ምታ ምናምን ግማሹ በጣም ብዙ ሕዝብ ስላለ ድንጋይ እየተወራወረ ስለሆነ ከእዚያ ልክ ሲያርፍ ገባሁ
- ይሄ አውቶቢስ እርሶ ስራ የሚሰሩበት አውቶቢስ ነው ሰው ምታ አውቶቢሱን ምታ ሲል እርሶ ዝም ብለው ቆመው እያዩ ነበር ?
- አዎ አትችላቸውማ ያው ሕዝብ እያለ አትችልም መከላከል አትችልም
- አስለቃሽ ጭሽ ተተኩሶ ነበር ብለዋል ከየት ነው የተተኮሰው ?
- ከእዚያ ያው እነሱን ሲያባርሩ ማለት ነው ወደ እዚህ ጋር እንትን ሲሏቸው እነሱን ለመበተን ወደ እዚህ
- በአስለቃሽ ጭሱ የተጎዱ ሰዎች የሚያለቅሱ ወይ የወደቁ ሰዎች ነበሩ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ወዴት ነበር ወደ መስኪዱ አቅጣጫ ነበር ተኩሰ ?
- አይ ወደ እዚህ ወደ እኛ ጋር አካባቢ
- ወደ እናንተ ወደ ነበሩበት ?
- አዎ ወደ ተርሚናሉ ጋር
- ወደ አውቶቢሱ ተርሚናል ?
- አዎ
- /ግልፅ ያልሆነ/ ሁኔታ እንዴት ነበር ይሄንን ሊያስረዱን ይችላሉ ማለት ሰውን ለመሸሽ ከመተኮስ ወይም ጭሽ ከመተኮስ ውጪ ሌላ የተጠቀሙት ኃይል የለም ?
- ሌላ የለም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እርሶ የነበሩበትን አካባቢ ብቻ ነው አይደል የሚያውቁት ?
- አዎ
- ሌላ ቦታ ስለመኖር አለመኖር አያውቁም አይደል ?
- አላውቅም
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ
- ምስክር አሁን በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ አውቶቢሱን የመታውን ሰው አይተዋል ወይ ሲባሉ አላየሁም ብለዋል አይደለም ያውቁታል ወይ አውቶቢሱን የመታው ሰውሲባሉ አላውቀውም ብለዋል አይደለም ?
- አውቶቢሱ የመታውን አላውቀውም
- ጥሩ አውቶቢሱን የመታው ሰው ግን እርሶ በመልክም በአካልም ባያውቁትም ቅድም 200 ካሏቸው ሰዎች ውስጥ ነው አይደለም ?
- አዎ 200 ይሆናሉ ያው
- ስለዚህ ይረብሹ ከነበሩት ሰዎች ውስጥ ነው ?
- አዎ
- አስለቃሽ ጭስ ነበረ ብለዋል እንዲሁ በተመሳሳይ ረብሻም ስለተነሳ እኛም ሕዝቡን አውርደናል ብላችዋል ምን ያህል ሕዝብ ነው እናንተ ያወረዳችሁት የጫናችሁትን ታስታውሳላችሁ ?
- ግፋ ቢል እስከ እኔ እስከ 80 እየጫንኩ እያለ ነው ገና እየጫንኩም ነው ደግሞ በእዚያ ላይ
- ምን ያህል ሰው ጫናችሁ በግምት የሚያታውሱት ከሆነ ?
- እስከ 80
- 80 ሰው ?
- አዎ
- ትኬት የቆረጠ ማለት ነው ?
- አዎ
- ለምን አወረዳችዋቸው ?
- በቃ ይጎዳሉ የሚል ግምት ነበረን እኛ ማለትም እየባሰ ሲመ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምኑ ?
- ሰው ይጎዳል የሚል -
- ረብሻው በጣም ስለበዛ ነው ?
- አዎ
- ሰውን ያወረዳችሁት ?
- አዎ እየመጡ ስለሆነ ስለሚበዛ ሰው ደግሞ እየወጣ ስለነበረ እኛ ደግሞ ወዲያኑ በሩን ከፍቼ ውረዱ ብዬአቸው ወረድኩኝ
- ድንጋዩ ማለት ባሱ የተሰበረው ለፖሊሶች የተወረወረ ነው ለባሱቹ ?
- ለባሱ
- የባሱ የተወረወረ ?
- እዚያ ላይ
- ፖሊሶች ላይ የተወረወረ ድንጋይ አይደለም ባሶች ያረፈው ?
- ያረፈው አይደለም አዎ
- ቀጥታ ባሶቹ ላይ የተወረወረ ድንጋይ ነው ?
- አዎ
- ቅድም ዋና ጥያቄ ላይ ሲጠየቁ ቀጥታ ይታየኛል 30 ቁጥር የሚቆመው ጫፍ ላይ ስለሆነ ከአንዋር መስኪድ ቀጥታ እንደሆነ ይታየኛል ብለዋል በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ በግምት ብለዋል የትኛውን እንውሰድ በቀጥታ ታይቶታል ወይስ ግምት ይመስሎታል ከአንዋር መስኪድ?
- ከአንዋር መስኪድማ ይታያል እኮ
- በቀጥታ ይታዮታል ?
- ይታያል ሲመጡ ይታያል
- ከመስኪዱ ሲወጡ ማለት ነው ?
- ሲወጡ አይደለም አቅጣጫ ያንን ያህልማ አይታይም እንደዚያ አይታይም ግን ከመስኪድ አካባቢ እንደሚመጡ ይታወቃል በቃ መንገዱ እንደዚህ ክፍት ነው
- መንዱ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- /ግልፅ ያልሆነ/ መንገድ ነው ይታያል
- መንገዱ ክፍት ነው ?
- አዎ
- ከእዚያ እንደሚመጡ ?
- ወደ እዚህ ፖሊሶች ሲያባርሯቸው ፖሊሶቹ ሲያባርሯቸው ወደ እዚህ ወደእዚህ እየመጡ እየሸሹ እያሉ ነው እንትን ያሉት
- ስለዚህ በእርግጠኝነት ከአንዋር መስኪድ እንደሆነ ማረጋገጥ ይችላሉ ?
- አዎ
- ጨርሰናል
- እናመሰግናለን
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- ለምስክርነት ነው የመጡት አይደል ?
- አዎ
- ስምዎን ያው የአባትዎን ስም ሳይጨምሩ የስራዎን ስም ብቻ ይነግሩናል
- ኮንስታብል በየነ ኃይሉ ኪዳነማሪያም
- ስንተኛ ናቸው ዐቃቤ ሕግ ?
- 58ኛ የተከበረው ፍ/ቤት
- በመሰክሩት ሊስት 47ኛ ላይ ደርሰናል በክሱ ዝርዝር 58 ላይ የተጠቀሱ እሺ ኮንስታብል በየነ ለምስክርነት ነው የመጡት እና እነ ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?
- የምመሰክረው /ግልፅ ያልሆነ/ መርካቶ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በ 01/02/03
- ቀበሌው ነው ?
- አዎ አደሬ ልዩ ስሙ ባዩሽ የሚባል መስኪድ እዚያ እኔ በወቅቱ ስራ ላይ ነበርኩኝ ስራ ላይ እያለሁ
- መቼ ነበር ቀኑ ?
- ቀኑ በ 6/11ኛ ወር 2004

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- 2004 ምን አዩ በእዚያን ቀን አስቲ አጠር አድርገው ይንገሩን ምን አይተው ነው 6/ዘ ነው አይደል ያሉት ቀኑ?
- አዎ
- ምን አዩ በእዚያን ቀን ባዩሽ መስኪድ ብለዋል ?
- አዎ
- ምንድን ነው ያዩት ?
- ያየሁት እኔ ስራ ላይ ነበርኩ ስራ ላይ እያለሁ እዚያ ሰዓቱ 5 ሰዓት ገደማ ነው ከለሊቱ ማለት ነው
- ዐቃቤ ሕግ ቀጥሉ
- ምስክር በ 6 ያሉት ምን 6 ነው ?
- ቀን ነው 6
- እኮ ምን 6 ወሩ ምንድን ነው ?
- ዘኛ ወር
- እሺ ዘኛ ወር ሐምሌ 6 ስንት ዓ.ም ነው ?
- 2004
- 2004 ዓ.ም ከምሽቱ 5 ሰዓት ነው ብለዋል ?
- አዎ
- የት አካባቢ ነው ?
- አደሬ ሰፈር ባዩሽ መስኪድ
- ባዩሽ መስኪድ ክፍለ ከተማው የት ነው ?
- አዲስ ከተማ
- ቀበሌውን ያውቃሉ ?
- ቀበሌው 01/02/03
- አሁን በጠቀሱት ጊዜ እና ቦታ እርሶ ምን እያደረጉ ነበር ?
- እያሉ የነበሩ
- እርሶ ምን እያደረጉ ነበር እርሶ እራስዎት ምን እያደረጉ ነበረ በግልጽ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ ስራ ላይ ነኝ
- -ስራ ላይ ነበሩ ?
- አዎ
- ጥሩ ስለዚህ ምን እንዳዩ ምን እንደተፈጠረ እስቲ ይንገሩን ?
- የተፈጠረው በእዚያን ወቅት መነሻው ኣላህክበር ነው የሚሉት እዚያ መስኪድ አለ እንዳልኳችሁ
- በምን ?
- ባዩሽ መስኪድ የሚባል አለ
- በምንድን ነው የሚሉት በምንድን ነው አላህክበር የሚሉት መጀመሪያ የሰሙት ምንድን ነው?
- በቃ እንደዚህ ተሰብሰቦ በቃ አላህክበር እያሉ ለእንትን ደግሞ ለመንግስት
- ወደ እዚያ እንመጣለን መጀመሪያ እርሶ አሁን በጠቀሱት ጊዜ እና ቦታ ከምሽቱ 5 ሰዓት ስራ ላይ ነበሩ ?
- አዎ
- ስራ ላይ ሆነው መጀመሪያ ምን ሰሙ ?
- ጩኸት
- ምን ዓይነት ጩኸት ?
- አላህክበር እያሉ
- በምን በአፍ ነው ?
- በአፍም ከውስጥ በማይክራፎን እየሰማሁ ነው
- በማይክራፎን ከምን ውስጥ?
- አዎ ከውስጥ ከመስኪዱ
- ከመስኪድ ውስጥ?
- አዎ
- ጥሩ ከእዚያስ ?
- ከእዚያ ሌሎችም ደግሞ ከውጪም አሉ ብዛት ያላቸው እንትኖች ሆነው
- እርሶ ተጠጉ ሲሰሙ ድምፁን ወደ መስኩዱ ተጠጉ ወይስ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ አልተጠጋሁኝም እዚያ ውጪ ላይ ነኝ
- ውጪ ላይ ኖት ?
- አዎ
- እኮ መስኪዱ ያለበት አካባቢ ነበሩ መጀመሪያ ?
- መስኪዱ አካባቢ ሳይሆን በቃ እዚያ አካባቢ ስራ ቦታዬ ስለሆነ ስራ እያከናወንኩ እያለሁ ድምፁ ይሰማል ማይክራፎን አለ ከእዚያ ብዙ ሰውም ስላለ ጩኸት ምናምን ሲሰማ በ 5 ሰዓት ላይ ደግሞ ምን ተፈጠረ ምናምን ብለን እዚያ ፀጥታ እያስከበርን እያለን ከእዚያ ወደ እኛ አካባቢ ለመምጣት ሞከሩ ወደ ፖሊሶች ማለት ነው
- ምን ይሉ ነበር የሚናገሩት ነገር ነበር ?
- እነሱ የሚሉት
- አዎ ቅድም አላህክበር ይሉ ነበር ብለዋል ሌላ የሚናገሩት ነገር ነበር ?
- ነበር አዎ
- ምን ይላሉ ?
- አላህወደ ፊት እንጂ ወደ ኋላ አይልም እኛ ፖሊሶች አንፈራም ፖሊስ የመንግስት ሌባ ነው ሌላ ደግሞ ወንድሞቻችን እኮ አወሊያ ላይ እያለቁ ነው የሚል ድምፆች ምናምን እያሰሙ ነበር
- በምን ይሄንን በማይክራፎን ነው ?
- እንደዚያ የሚሉ እነዚህ በማይክራፎን ሳይሆን በውጪ ላይ ያሉ
- ውጪ ያሉት ?
- ብዛት ያላቸው እንትኖች ናቸው
- ከእዚያስ ተጠጋችሁ ወደ ሰዎቹ ?
- አልተጠጋንም
- ጥሩ ምን ሰማችሁ አሁን ከጠቀሱን ነገር ሌላ ምን ምን ሰማችሁ ከእዚህ አሁን ከነገሩን ሌላ ምን ሰማችሁ ?
- በቃ እንደዚህ ነው የሰማነው በቃ ጩኸት ነው ሰማነው
- ምንድን ነው የሚፈልጉት ምን ይሁን ነው የሚሉት ?
- ምን ይሁን አይሉም ግን በቃ አላህክበር እያሉ ዝም ብለው በቃ ጩኸት ምናምን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይሁንልን የሚሉት ነገር ነበር ?
- ይሁንልን የሚል ነገር አልሰማሁም
- ጥሩ ከእዚያ ምን አደረጋችሁ ?
- ምን እናደርጋለን ምንም አላደረግንም በእዚያ ወቅት
- አኮ ምን ተፈጠረ ከእዚያ በኋላ ወደ ቤት ሄዳችሁ በቃ ?
- ወደ ቤት አልሄድንም
- ታዲያ ?
- አላህክበር እያሉ እየጮሁ እየጮሁ እየዞሩ ምናምን እዚያ አካባቢዋ
- ምናምን ምናምን
- ሲረብሹ
- ይኸውህ ምስክር ቆይ አዳምጥ ይሄ ምናምን ምናምን የምትለው አይቀረፅም አሁን አንተ ቦታው ስለነበርክ ታውቃለህ ግን እኛ አሁን አናውቀውም
- ነበርኩኝ በስነ ስርዓት ነበርኩ
- ስለዚህ ምናምን ምናምን የሚለውን ተወው እና ንገረን ምናምን ምናምን ሳይሆን እንዲህ ይሉ ነበር እንዲህ ይሉ ነበር ብለህ ከመጀመሪያው ጀምሮ አሁን የሰማኸውን ተናገርክ በማይክራፎን አላህክበር አሉ ብጥብጥ ነበር እዚያው አካባቢ ነበርን ከእዚያስ ምን ሆነ ?
- ይሄን ነግሬአሁ ከእዚህ በፊት ቀደም ብዬ ነግሬአለሁ
- ተቃውሞ አለኝ
- ምንድን ነው ተቃውሞ ?
- የተከበረው ፍ/ቤት የተከበሩ ዐቃቤ ሕግ ምስክሩ ያልተናገሩትን ነገር ከእዚህ ቀጥለው ተናገሩልኝ በሚል ዓይነት ሁኔታ ብጥብጥ በሚል እየነገሯቸው እና ይሄ ግልፅ የሆነ መሪ ነው መባል የለበትም አግባብም አይደለም አላሉም እሳቸውም
- ምላሽ ስጡበት
- ምኑን ነው ያላሉት የተከበረው ፍ/ቤት እኔ አሁን እሳቸውን ያሉትን ነው የደገምኩት እና ግልፅ ይሁን መጀመሪያ መቃወሚያው
- ብጥብጥ የሚለውን ይመስለኛል ያነሱት ብጥብጥ አላሉም ነው ጥያቄው እንደዚያ ነው
- ችግር የለውም መሰረዝ ይችላል ችግር የለውም የተከበረው ፍ/ቤት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አስተካክሉ
- እሺ ምስክር አላህክበር ይባል ነበረ ውስጥ የነበሩ ሰዎች በማይክራፎን ውጪ ያሉ ሰዎች አወሊያ ወንድሞቻችን እያሉቁ ነው ይሉ ነበር ብለዋል ከእዚያ በኋላስ ምን አሉ ?
- ከእዚያ በኋላ እንደዚህ እያሉ እያሉ እኛን ደግሞ ፀጥታ አስከባሪዎች ነን ፀጥታ እያስከበርን እያለን ምን ተፈጠረ ምናምን ብለን እኛ ምን ሆናችሁ ነው እስቲ የፈለጋችሁት ነገር ጠይቁን እና የምንችለው ነገር እንርዳችሁ ምናምን ስንላቸው አያገባችሁም እኛ ፖሊስ አንፈራም እንተ የመንግስት ሌባ ነህ እያሉ ድንጋይ ጠርሙስ ምናምን እየወረወሩ ወደ እኛ ሊጠጉ እየሞከሩ እኛ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይጠጉብን የራሳችን እንትን እያልን ከለላ
- አሁን እሱ ነው ችግሩ እንትን የምትለዋ ነገር ምን አላችሁ እናንተ ስትሸሹ ወዴት የት ደረሳችሁ?
- የትም አልደረስንም እኛ ባለንበት ቆመን የሆነ ጉዳት እንዳይደርስ ሕዝብ ላይ ሰላም የሚፈልግ ሕዝብ አለ እዚያ መኖሪያ የተኛ ሕዝብ አለ እነሱ እነሱ እንዳይረበሹ እሱን ለማስረገብ ለማረጋጋት ነው የምንሞክረው እንጂ ሌላ ነገር ምንም አላደረግንም
- እኮ አሁን ቀላል ጥያቄ ነው ከእሱ በኋላ እስከመጨረሻው ድረስ እየሆነ ያለውን እና እንዴት እንደተጠናቀቀ እሱን ይንገሩን ?
- በቃ መጨረሻ ላይ በራሳቸው ጊዜ በቃ ተበተኑ ጠፉ
- እሺ ድንጋይ ጠርሙስ ይወረወር ነበር ብለዋል ?
- አዎ
- የደረሰ ጉዳት ነበር ?
- እኔ እራሴ ደርሶኛል
- ምን ሆንክ አንተ ?
- እኔ ቅድብ አይኔ ላይ ጉዳት ደርሶብኛል
- ምን ሆንክ ?
- ቅድብ አይኔ ቀኝ አይኔ አካባቢ
- ምን እኮ ምን ተደረክ ?
- ተመትቼአለሁ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በምን ?
- በወቅቱ ድንጋይ ይሁን ጠርሙስ ይሁን አላውቀውም ግን ደም ፈስሼ ተጎድቼአለሁ
- ምንህ ላይ ተመታህ ?
- ቀላል ጉዳት ደርሶብኛል
- ምንህ ላይ ተመታህ ?
- ቅንድብ አይኔ ቀኝ አይኔ ቅድብ አይኔ አካባቢ
- የትኛው ነው ቀኝ እና ግራ ?
- ቀኝ
- በቀኝ በኩል ?
- አዎ
- ከእዚያ ምን ሆነ የተመታው ቦታ ?
- ደማ
- ከእዚያስ ምን አደረክ ?
- ምንም አላደረኩም በቃ እዚያ አጠገባችን የሆነ ክሊኒክ አለ የሕዝብ ክሊኒክ አለ እዚያ እርዳታ ተደረገልኝ ከእዚያ /ግልፅ ያልሆነ/ ከተደረገልኝ በኋላ ተመልሼ እንደገና ነገሩ ስላልበረደ እነሱን ለማስበረድ እንደገና ተመልሰን ስራዬ ቀጠልን
- እነዚህ አሁን እዚያ ከባዩሽ መስኪድ ውስጥ እና ውጪ የነበሩ ሰዎች ያልካቸው ብዛት ነበራቸው ?
- አዎ አሉ
- ምን ያህል ይሆናሉ በግምት ?
- ብዙ ናቸው
- ብዙ ማለት ?
- እኮ ብዙ ናቸው
- መገመት አትችልም
- በግምት
- ፖሊስ ነህ አንተ መገመት አትችልም 100 ሺህ 100 ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያው ብዛት አላቸው ከተባለ ይበቃል
- ወዴት ነበር መሄድ የሚፈልጉት ለምንድን ነው እናንተ ላይ ድንጋይ የሚወረውሩት ?
- የትም መሄድ አልፈለጉም ዝም ብለው እዚያ እየተንሸካለሉ በቃ ዝም ብሎ ቀደም ብዬ የገለፅኳቸውን ቃላት እየገለፁ ድንጋይ ምናምን ጠርሙስ እና እየወረወሩ ሲሸከረከሩ የሚታዩ የነበረው የመሩት ነገር አልነበረም
- እናንተን ለምን መቷችሁ ታዲያ ምን አደረጋችዋቸው ለምን መቷችሁ ?
- ለምን መቷችሁ አልጠየቅናቸውም ለምን መታችሁን ብለን
- አሁን ከጠቀስካቸው ነገሮች ሌላ የተናገሩት የምታስታውሰው ነገር የለም እነዚያ የተሰበሰቡ ሰዎች ይናገሩ የነበሩት ነገር ቅድም የነገርከን አለ አወሊያ ወንድሞቻችን አለቁ እኛ ፖሊስ አንፈራም ያልካቸው ነገሮች አሉ ?
- አዎ
- ከእዚያ ውጪስ የሚሉት ነገር ነበር ምን ይሁንልን ነው የሚሉት ?
- በቃ አላህክበር የሚል ድምፅ ያሰማሉ ድምፃችን ይሰማ አላህክበር
- ድምፃችን ይሰማ
- እኛ አላህ ነው የምንፈራው እንጂ ፖሊስን አንፈራም የሚል ድምፅ እያሰሙ
- ድምፃችን ይሰማ ምን ዓይነት ድምፅ ?
- አላውቅም ምን ዓይነት ድምፅ እንደሆነ አያወጡትም ነበር በእዚያን ጊዜ ብቻ ድምፃችን ይሰማ የሚል ድምፅ ነው የሚሰማው
- ኮንስታብል እኔ ላይ ቅንድቤ ላይ ጉዳት ደርሶብኛል ብለሀል በእኔ ላይ ቅንድቤ ላይ ጉዳት ደርሶብኛል በምን እንደተመታሁ አላውቅም ብለሀል ?
- አዎ
- ከአንተ ጋር ምን ያህል ሰው ነበረ የእናንተ አባሎች ማለት ነው ምን ያህል ነበራችሁ ?
- ነበርን አለን እኛ ባልደረቦቼ የጎዱ ቀላል ጉዳት የደረሰባቸው
- እሱን እስቲ ንገረን እሱን ንገረን በምን ያህል ሰው ላይ ጉዳት ደረሰ ምንድን ነው ጉዳት የደረሰባቸው ቀስ በል እና እያስታወስክ ረጋ ብለህ ንገረን ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ እኮ እነግርሀለሁ በወቅቱ እኔ ጋር አጠገቤ የነበሩ ሌሎችም ነበሩ ጉዳት የደረሰ ግን አጠገቤ የነበሩ አባሎች ጉዳት የደረሰባቸው ግርማይ
- ግርማይ
- አዎ ኮማንደር ግርማይ ማለት ነው ኮንስታብል አንበሳዬ መርካ ኮንስታብል ቡሸራ ኤፔሳ እንዲሁም እኔ በየነ ጎይሉ
- እነዚህ ምን ምንድን ነው የደረሰባቸው ?
- ጉዳት ደርሶባቸው እነሱ
- ምን ጉዳት ደረሰባቸው አንተ ላይ ቅንድብህ ላይ ጉዳት እንደደረሰብህ እነሱ ላይ አጠገቤ ስለነበሩ ስላልከን ነው ?
- አዎ
- ምን ምን ጉዳት ደረሰባችሁ ?
- ኮንማደር ግርማይ ማለት አይኑ እሱም ቀኝ አይኑ ነው ጉዳት ደረሰበት አንበሳዬ መርካ ደግሞ አናቱ ላይ ጭንቅላቱ ላይ ነው ቡሸራ ኤፔሳ ደግሞ ፊኛው እዚህ ሆዱ ላይ ነው ጉዳት የደረሰበት
- ምን ሆኑ ታዲያ ወዲያው ይሄ ጉዳት ሲደርስባቸው ምን ሆኑ ?
- በቃ አሁን ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት እኔ የሄድኩበትን ክሊኒክ አለ እዚያ አጠገባችን እዚያ ሄደን እርዳታ ተደረገልን እርዳታ ከተደረገልን በኋላ ተመልሰን ወደ ስራችን ገባን
- ንብረት ላይ የደረሰስ ጉዳት አለ ?
- ንብረት ላይ የደረሰ በእዚያን በወቅቱ አልነበረም
- አላየህም ?
- አዎ
- እዚያው ሲሸከረከሩ ነበር ብለሀል ?
- አዎ
- ምን ማለት ነው ሲሸከረከሩ ማለት ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የምልህ እዚያ ደርሰው እዚያም ደርሶ እዚያ ማለት የመሩት ነገር የለም እዚያ መስኪዱ ላይ እንደዚህ እየተሸካለሉ እየዞሩ የትም አልሄዱም ማለቴ ነው መስኪዱ ላይ እየተሸከረከሩ እንደዚህ ይዞሩታል አላህክበር እያሉ
- እያሉ ?
- አዎ
- መጨረሻ ላይ በምን ተጠናቀቀ ?
- መጨረሻ ላይ በቃ በራሳቸው ጊዜ ሰዓት እየፈጀ እየፈጀ ሲሄድ በራሳቸው ጊዜ
- ስንት ሰዓት ላይ ተጠናቀቀ ?
- በእዚያን ጊዜ ሰዓት ብዙ እንትን አልልም አለይልህም ግን በግምት ወደ 8 ተኩል ወደ 9 ሰዓት ምናምን
- 8 ተኩል አካባቢ ?
- አዎ በራሳቸው ጊዜ አበረዱ እኛም
- በእዚህ ተጠናቀቀ ?
- አዎ
- ኮንስታብል እነዚህ ሰዎች ችግራቸው ከማን ጋር ነው ?
- አላውቅም
- ከማን ጋር ተጣልተው ነው እናንተ የሄዳችሁት እዚያ ከማን ጋር ስለተጣሉ ነው የሄዳችሁት እናንተ ?
- ከማንም እንደተጣሉ አናውቅም እኛ እኔ በወቅቱ ስራ ላይ ነው ያለሁት አዲስ አበባ ፖሊስ ነኝ ስራ ላይ ነኝ ፖሊስ ምን ጊዜ እስታንድ ባይ ነው ስራ ነው
- ጥሩ ቅድም ስትመሰክር እናንተ የመንግስት ሌቦች ናችሁ ብለውናል እኛ ፖሊሶችን ብለሀል ?
- አሉን አዎ
- ምን ማለት ነው እንደዚያ ?
- አላውቅም ለምን እንደሆነ አላውቅም ትርጉም አላውቅም አልተረጎሙትም
- አማርኛ ትችላለህ አይደለ ?
- አዎ እችላለሁ በስነ ስርዓት

2166 604

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥሩ
- ግልፅ እኮ ነው ዐቃቤ ሕግ_ ከእዚህ በላይ
- ያው ማለት እኛ የተከበረው ፍ/ቤት የያዝነው ጭብጥ ነኛ
- እኮ ምክንያቱን አናውቅም አሉ ወይ ሌላ ጥያቄ ካላችሁ በሌላ መንገድ መጠየቅ ነው ይሄንን እኮ 3 ጊዜ ተጠይቆ 3 ጊዜ መለሱ
- ይሁንልን የሚሉት ነገር ነበር እናንተ በሄዳችሁበት በወቅት ?
- አልነበረም
- እሱም ተጠይቋል ዐቃቤ ሕግ
- ዋና ጥያቄ አበቃ
- መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ የተከሣሾች ጠበቆች
- ኮንስታብል በየነ
- አቤት
- በአወሊያ ወንድሞቻችን አለቁ እያሉ ነበር ብለዋል ?
- በትክክል
- ወንድሞቻችንን አለቁ ብለው ነው እንዴ የተሰባሰቡት የነበረው ?
- አላውቅም
- ከእዚህ ጋር በተያያዘ ፖሊስ ያጣራልን ያሉት ነገር የለም ?
- አቤት
- አንድ ጉዳት ሲደርስ ፖሊስ ነው አይደል የሚጠየቀው አወሊያ እየተደረገ ያለውን ነገር ፖሊስ ያጣራልን ብለው አልጠየቁም ?
- አላሉንም እንደዚያ አላሉንም ፖሊስ ያጣራልን የሚል ድምፅ አላሰሙም
- እኮ አሁን ለምሳሌ ድምፃችን ይሰማ እያሉ ነበር ?
- አዎ የሚል ድምፅ ሰምቼአለሁ
- ያው መንግስት ይሰማልን ነው አይደል ሌላ አካል የለም መቼስ ድምፅ የሚሰማ መንግስት ይሰማልን ነው ሲሉ የነበሩት እንደዚያ ነው አይደል ?
- እሱ የራስህ አማርኛ ሊሆን ይችላል እንደዚያ ብዬ አልፈታውም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ምን ማለት ነው እርሶ የተረዱት አሁን አንድ ሰው ድምፃችን ይሰማ ሲል ምን ማለቱ ነው በእዚያ ሁኔታ የነበረው ድምፃችን ?
- አላውቅም
- ቆይ ምስክር ጥያቄው ለማን ነው ድምፃችን ይሰማ የሚሉት ለማን ነው ?
- ለማን እንደሆነ አላውቅም እኔ ለራሴ
- በቃ ሌላ ጥያቄ
- በወቅቱ የነበረው የአየር ሁኔታ እንዴት ነበር ዝናብ ነበረው አይደል ዝናብ ነበረ አይደል ዘንቧል አይደል ?
- ዝናብ አልነበረም
- በመሀል አልዘነበም ምንም ?
- አልዘነበም
- በማይክራፎን ሲናገሩ ሰማሁ ብለዋል እና እነዚህን 3 ነገሮች ብቻ ነው ወይስ ጥያቄአችን ሰላማዊ ነው የሚሉ ነገሮችም ሲናገሩ ነበር ?
- አልሰማሁም ጥያቄአችን ሰላማዊ ነው የሚል ቃላት አልሰማሁም
- ከእኔ ጋር የነበሩ ሌሎች የተጎዱ አሉ ብለዋል ከእዚያ ቀን በኋላ ወደ ስራ ተሰማርተዋል ስራ አብረው ነበሩ ?
- አቤት
- ይሄ ነገር ከሆነ በኋላም ስራ ላይ ነበሩ አሁን ቅድም ሲያስረዱ እዚያው የነበረ ክሊኒክ የተወሰነ እርዳታ አደረገልን ከእዚያ ወደ ስራ ሄድን ብለዋል ?
- አዎ
- በነጋታውም ከእዚያ ቀንም በኋላ በነበረው ስራ ላይ ነበሩ አይደል እርሶም እነሱም ስራ ላይ ነበሩ አይደል ?
- በማግስቱ ነው የምትለው ወይስ በወቅቱ ?
- በወቅቱ ነበሩ ?
- አዎ ነበሩ
- በማግስቱም ከእዚያ በኋላ ወደ ስራቸው ነው አይደል የተሰማሩት ?

2168 606

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በማግስቱ ወደ ሆስፒታል ነው የሄድነው
- አሁን ይሄ ነገር ያደረሱባቸው ሰዎች ምን ሆኑ ?
- አላውቅም
- ለፍርድ ስለመቅረባቸው ያውቃሉ ?
- አላውቅም
- የእርሶን አይወቁ እሺ የኮማንደር ግርማ ወይም የኮንስታብል አንበሴ ይሄንን ድርጊት ፈፀሙባቸው ተብሎ ለፍርድ የቀረቡ ሰዎችን አያውቁም ?
- አላውቅም
- እዚያው ላይ ሲሸከረከሩ ነበር ብለሀል እና አልወጡም ነበረ ከመስኪድ እናንተ እንዲወጡ የተጠቀማችሁት ነገር አልነበረም እናንተ እንዲወጡ የተጠቀማችሁት ነገር አልነበረም ከመስኪድ ?
- በፍፁም
- ተጨማሪ ኃይል እንዲመጣላችሁ አልጠየቃችሁም ነበር ?
- በፍፁም አልጠየቅንም
- ፌዴራል ፖሊስ አልመጣም ነበር በወቅቱ ?
- አላውቅም
- ነበሩ አይደል በቦታው እርሶ ?
- ነበርኩኝ አዎ
- እኮ ተጨማሪ ኃይል ይምጣልን ብላችሁ ፌዴራል ፖሊስ መጥቶ አስለቃሽ ጭሽ ተተኩሶ ነው ሕዝቡ የወጣው ይሄንን አያውቁም እርሶ ?
- አላየሁም
- ጥያቄው ተመልሷል ጠበቃ ጠይቀውት በቀጥታ መለሰ እኮ አላየሁም /ግልፅ ያልሆነ/
- ከእዚያ በኋላ ተበተነ ሰው በየቤቱ ሄደ ተይዞ ?
- አዎ ከጊዜ በኋላ ከሰዓታት በኋላ
- እኮ ከሰዓታት በኋላ ተበተነ ?
- አዎ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እናንተ የተወሰነ የተያዘ ሰው አልነበረም ጣቢያ ወስዳችሁ ያሳደራችሁት ሰው አልነበረም ?
- አላውቅም
- አላውቅም ነው አልነበረም ነው ?
- አላውቅም አልያዝንም
- አልነበሩም እንዴ እርሶ በቦታው ?
- ነበርኩኝ ይኸው ነበርኩ ስለነበርኩኝ እኮ ነው እየነገርኩሽ ያለው
- አዎ ከነበሩ ያን ቀን ልክ ሰው ከተበተነ በኋላ ፖሊስ ጣቢያ የሄደ ታስሮ ያደረ ሰው ነበረ አልነበረም ?
- አልነበረም አልያዝንም አላሰርንም
- አላሰራችሁም ያደረም ሰው የለም ?
- የለም
- መብራት አልጠፋም ?
- መብራት አልጠፋም
- አልጠፋም ?
- አዎ
- ጨርሻለሁ
- ቅድም ኮንስታብል ቅድም የስራ ቦታዎም እዚያው አካባቢ እንደሆነ ገልፀዋል እዚያ አካባቢ ሲሉ ምን ማለትዎ ነው የት ጋር ?
- እዚያ አካባቢ ማለቴ ብቻ አይደለም አዲስ አበባ ፖሊስ ነው የምሰራው አዲስ አበባ ፖሊስ ደግሞ የትም ቦታ ቀጠና ይመድበኛል የትም ቦታ ገብቼ እሰራለሁ በቃ ፀጥታ አስከባሪ ነኝ ፀጥታ አስከባሪ እስከሆንኩ ድረስ የትም ቦታ እየዞርኩኝ እየሰራለሁ
- ምስክር ይኸውሎት ምስክር ሲጠየቁ ጥያቄውን ብቻ ይመልሱ ነኛ ይረጋጉ ምናልባት ባህሪዎ ሊሆን ይችላል ብለን ነው እና አንዳንዴ ለመቆጣት ይላሉ እሱን ቀስ ብለው ተረጋግተው ይመልሱ
- እሺ ተቀብዬአለሁ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ምንድን ነው አሁን የጠየኮት በዕለቱ ከሰር አሁን ከመስከሩት ጋር በተያያዘ አላህክበር የሚለውን የት ጋር ሆነው ነው አሁን ጣቢያው ጋር ሆነው ነው ሰምተው የመጡት የትጋር ነበሩ ለማለት ነው መጀመሪያ አሁን ይሄንን ነገር ቅድም ያልተለመደ ነው ብለው ወደ እዚህ ጉዳይ እንዲመጡ ያደረጎት
- ግልፅ ነው ግልፅ ነው ቀጥሉ መልሱን የት ሆነህ ነው የሰማህ የመጀመሪያ ?
- እኔ የነበርኩበት እዚያ አካባቢ
- እኮ እዚያ አካባቢ ማለት ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ነው ?
- ፖሊስ አለ ፖሊስ ጣቢያ አለ አዎ
- ፖሊስ ጣቢያ ሆነው ?
- መርካቶ ፖሊስ ጣቢያ
- ጥሩ መርካቶ ፖሊስ ጣቢያ ሆነው ድምፅ አላህክበር የሚለውን ድምፅ ሰሙ ፖሊስ ጣቢያው እርሶ የነበሩበት መርካቶ ፖሊስ ጣቢያ ከባዩሽ አሁን ካሉት መስኪድ ምን ያህል ይርቃል ?
- በግምት ነው በግምት እንጂ አልሰፈርኩትም ግን በግምት መናገር
- የሚያውቁት ከሆነ በግምት ?
- አዎ
- በግምት ?
- ከ 150 እስከ 200 ሜትር ይሆናል
- ይሆናል ?
- አዎ በግምት
- አሁን ፖሊስ ጣቢያ ሆኖ አንድ ሰው የፖሊስ ጣቢያው የግቢ በር ላይ ሆኖ ቀጥታ ወጥቶ ባዩሽን ማየት ይችላል እንዴ ?
- አዎ ይቻላል
- በመሀል ሌሎች ቤቶች የሉም ?
- ይታያል
- ብሎኮች የሉም ሌሎች ብሎኮች ?
- ቤቶች አሉ ግን ይታያል ቅያሶች አሉ ይታያል በስነ ስርዓት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቀጥታ ከእናንተ ፖሊስ ከመርካቶ ፖሊስ ?
- አዎ
- ባዩሽ ይታያል ?
- ይታያል
- ጥሩ ባዩሽ ጋር ሌሎች መስኪዶች የሉም በእዚያ ዙሪያ ?
- የሉም እሱ ብቻ ነው የማውቀው እኔ
- በባዩሽ ዙሪያ መስኪዶች የሉም ?
- አላውቅም እሱ ብቻ
- በወቅቱ በባዩሽ ሌሎች መስኪዶች ላይ አዛን አልነበረም እንዴ ?
- አላውቅም እኔ የእዚያን ጊዜ ስለነበርኩ ነው የእዚያን ጊዜ ነው የምነግርህ
- አይደለም እርሶ አዛን በሚሰሙ ጊዜ ይሄ ጥሪ በሚሰሙ ጊዜ ከአንድ ከባዩሽ መስኪድ ብቻ ነው ወይስ ከሌሎች መስኪዶች
- ሌሎች አላውቅም
- ቆይ አዛን አይደለም የሆነ አላህክበር የሚል ድምፅ ሰምተን ጨኸት ሰምተን ጨኸቱ ምን ዓይነት ነው ሲባል አላህክበር የሚባል ሰማሁ ነው ያሉት ስለዚህ
- እኔ እንትን ብዬ ነው
- አዛን የሚለው
- ማለት አላህክበር የሚለውን እርሶ የሰሙት ከአንድ መስኪድ ብቻ ነው የተባለው ወይስ ከሌላ ከሁሉም ከሌላ አቅጣጫ ?
- የተባለው ሳይሆን እኔ እኮ ነው ያየሁት የሰማሁት እኮ እየነገርኩ
- ቆይ ቆይ ምስክር እዚያ ብቻ ነው የሰሙት ሌላ ሰምተዋል ?
- በቃ ይሄ ብቻ ነው የሰማሁት ከእዚያ መስኪድ ብቻ
- ሌላ ጥያቄ
- ኮንስታብል ባዩሽ መስኪድ የት ነው የሚገኘው ባዩሽ መስኪድ ትክክለኛው ቦታው የት ነው የት ነው የሚገኘው ? ቀስ ብለው ያስረዱኝ ?
- ማለት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቦታውን ንገሩን ባዩሽ መስኪድ ያሉት የቱ ጋር ይገኛል ?
- አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ
- አይደለም ቦታው መንገድ ዳር ነው መሀል ነው ?
- መሀል ነው
- ምን እስቲ ከዋና መንገድ ምን ያህል ይገባል ?
- አቤት
- ከዋና መንገድ ምን ያህል ይገባል ባዩሽ መስኪድ ሲሄዱ በየት አቅጣጫ ?
- ዋና መንገድ ስትለኝ ምን ዋና መንገድ ነው ማንም ዋና መንገድ ሲባል ወይም
- ምስክር 1ኛ እያዳመጡ 2ኛ ቀስ ብለው መልሷን ብቻ ለምሳሌ መንገድ የተጠየቁት መንገድ ዳር ነው ስላሉ የትኛው መንገድ እንግዲህ መንገድ ዋና ሊሆን ይችላል ላይሆን ይችላል የሚያውቁትን ብቻ ?
- እኮ እሱን ቼክ ለማድረግ እሱን እጠየኩ ያለሁት
- ቆይ ዋና መንገድ አለ እዚያ የለም ዋና መንገድ አለ ?
- ዋና መንገድ የለም
- ዋና መንገድ የለም ?
- የለም
- ስለዚህ ምን ዓይነት መንገድ ነው ያለው ?
- በቃ ቅያሶች አለ አይደለም የሰፈር ቅያስ መንገድ
- ቅያስ መንገድነው ያለው?
- የውስጥ የውስጥ መንገድ እሱ እሱ አለው
- ከእዚህ ተነስታችሁ
- በበርበሬ ተራ ነበር የሄዱት ወደ ባዩሽ መስኪድ ሲሄዱ በበርበሬ ተራ ነው የሄዱት በዋናው በተከለኃይማኖት ነው የሄዳችሁት ?
- አዎ ዋና መንገድ አለ እሱ አንድ
- እሱ አለ አይደለም ?
- አዎ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከበርበሬ በረንዳ ስትወርዱ በቀኝ ነው በግራው በኩል ነው የሚገኘው ?
- ወዴት ስትሄድ በርበሬ መንገድ
- ወደ ታች እወርዳለሁ ከበርበሬ በረንዳ
- ወደ መስኪዱ ስትሄዱ በበርበሬ ተራ በኩል ነው የሄዳችሁ እና መስኪዱ በየት በኩል ነበር ?
- እዚያ ጋር አይደለም ያለነው በወቅቱ አሁን እያልከው ያለኸው በርበሬ ተራ አይደለም ያለነው
- በየት ሄዳችሁ እኮ ነው ?
- አወከው አይደለም መስኪዱ ካወከው ከመስኪዱ ወደ ላይ ነው
- ወዴት ወደ ላይ ?
- መርካቶ ፖሊስ ጣቢያ የሚባል አለ ወይም የሕዝብ ክሊኒክ አለ እዚያ ጋር እዚያ አካባቢ ነን ያለው ፀጥታ የምናስከብረው እኛ
- እሺ መስኪዱ ዙሪያው ምን አለ ?
- ምን አለ ማለት
- ያዩትን ንገሩኛ ?
- በቃ /ግልፅ ያልሆነ/ የቤት መኖሪያ
- ታጥሯል አጥር አለው ? መስኪዱ አጥር አለው አጥር አለው ወይ ነው ጥያቄው ?
- አናጣ አልገባኝም
- ቆይ አንዴ እንትን ነው አሁን አንዳንድ ጊዜ እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ሊከሰቱ ይችላሉ ግን ምንድን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ በእያንዳንዱ መልስ ላይ ሰው እየሳቀ ከሄደ ወደ እዚያ ነው የሚያስበው ስለሚመሰክረው ሌላ ነገር ነው ስለዚህ ፀጥ ብላችሁ አዳምጡ ቀጥሉ
- /ግልፅ ያልሆነ/ መስኪዱ አለው ወይ መስኪዱ ወይስ ሱቆች አሉ ምግብ ቤት አለ ምንድን ነው ሜዳ ላይ ብቻውን ነው ያለው መኖሪያቤት ነው የትኛው ነው ?
- መኖሪያ ቤቶች አሉ
- ሱቅ አለው ?
- ሱቆችም አነስተኛ ሱቆች ምናምን ምናምን አሉ
- ፊት ለፊቱስ ምን አለ ሜዳ የለም ?
- ማለት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- መስኪዱ ፊት ለፊት ምን አለ ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ማለት ከቅድም ጀምሮ ስለመስኪዱ አካባቢ ነው እየቱጠየቁ ያሉት በትክክል አሁን ነበሩ አልነበሩም ለማለት ከሆነ የእሳቸውን የታአማኒነት ጥያቄ እየተጠየቁ ከሆነ ኤግዛክትሊ ቦታው የት አሁን እኛ አራሱ እኔ አሁን እራሱ አላውቀውም ግልፅም አይደለም አሁን መስቀለኛ ጥያቄ እየተጠየቀ ያለው በግልፅ ምን እየተጠየቁ እንደሆነ አላወቅንም አሁን አቅጣጫዎቹን ቦታዎቹን ዙሪያ ምን አለ ሱቅ የለም ወይ እንዲህ የለም ወይ የሚባለው ነገር ኤግዛክትሊ ቢጠየቁ ለእኛም ግልፅ እየሆነልን አይደለም የእሳቸው እዚያ ቦታ ነበሩ አልነበሩም ከሆነ ለእኛም ግልፅ በሚሆን ለእሳቸውም ግልፅ በሆነ መልኩ ቢቀርብላቸው እና ቢጠየቁ በእዚያ መልኩ
- ሌላው የተከበረው ፍ/ቤት ከእዚህ ጋር ከቅድም ጀምሮ የምታዘበው ነገር አለ አሁን ዋናው የእዚህ ጥያቄ ምን እንደሆነ ያው መገመት ይቻላል መስኪዱን ያውቃሉ ወይስ አያውቁም የሚል ነው ግን አጠቃላይ አንዳንዴ ከእዚያም ያልፍ እና የሌላ የሙያ ጥያቄ ዓይነት ማለት የቦታ አቅጣጫ የክፍል ምን እዚያ ውስጥ እንደምህንድስና ዓይነት አገባብ ይመስላል እና ግን ኤግዛክትሊ እንትን የሚጠይቁትን በግልፅ ቦታ ከሆነ መስኪድ ነው መስኪድ ከሆነ ፀጥታ አስከባሪ ናቸው ለሊት ሊሆን ይችላል የሄዱት ቀን ሊሆን ይችላል ሕግ ማስከበር ነው ሕግ ለማስከበር ደግሞ የሚሄድ ለሰከንድ ወይም ተለወሰነ ሰዓት አስከብሮ ይመለሳል አጠቃላይ እውቀት ይኖራቸዋል ማለት እራሳቸው ናቸው የሚያውቁት እና እንትኑ በጣም ባይበዛ ለማለት ነው አመሰግናለሁ
- መልስ ልስጥበት የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ይሄ ማሳሰቢያ እና አካሄድ ስለሆነ መልስ መስጠቱ እንትን አይደለም ጥያቄው በመሰረቱ ችግር የለበትም ችግር የሆነው መደጋገማችሁ ነው እያንዳንዷን ጥያቄ አሁን በእዚህ አሁን አለ የለም የሚለውን ነገር ለማረጋገጥ ነው ትክክል ነው ጥያቄው በመሰረታዊነት ችግር የለውም ነገር ግን በጣም ጫፍ ወርዶ ጊዜ የሚወስድ መደጋገም ነው ያለው ስለዚህ ዋናውን ዋናውን ነገር ምስክሩ ሊያስረዳልን ይችላል የምትሉትን ነገር ቀጥሉ
- ኮንስታብል ሰዓቱ ለሊት ነበር ብለዋል በእዚህ ለሊት በሆነ ሰዓት ቅድም ሲመስክሩ ግማሹ ሰላማዊ ሰው ነበረ ግማሹ አላህክበር ይል ነበር ብለዋል የትኛው ሰው ነበር የሚበልጠው እርሶ እንዳዩት ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በወቅቱ ሰላማዊ ሰው የሚባል እኮ ሁሉም ተኝቶ እኮ ነው ያለው /ግልፅ ያልሆነ/ ማረፊያ ሰዓት ነው አርፎ ተኝቶ ነው ያለው አላህዋክበር የሚል ብቻ ድንጋይ እና ጠርሙስ የሚወረውር
- በቃ ምስክር
- ሁሉንም ሰው ይታዮት ነበር ለሊት ከሆነ ለሊት ነው ብለዋል ጨለማ ነው ብለዋል ?
- አዎ 5 ሰዓት ላይ
- ስለዚህ ይታዮታል ሁሉም ሰው ሁሉም ሰው አላህክበር ነበር የሚለው ?
- አዎ የውጪ መብራት አለ እኮ
- እኮ ሁሉም ሰው ነበር አላህ ክበር የሚለው ?
- አዎ ሁሉም ሰው ነው የተሰበሰበም ሁሉም ሰው ነው አላህክበር የሚል
- ፖሊስ ላይ ቅድም አደጋ ደረሰ ብለው ነበር እና የደረሰውን አደጋ ማን እንዳደረሰው ያውቃሉ ለይተው ?
- ቀደም ብዬ ገልጬአለሁ
- እኔ የጣየኮትን መልሱ
- ነግሬአለሁ በቃ
- ቆይ ቆይ ይሽውለት አሁን ቅድም ለዐቃቤ ሕግ ነግረዋል አሁን እሳቸው ሲጠይቁ እሱን በትክክል ጥያቄውን ሰምተው ካለ የለም የጉዳት መጠን ከሆነ የጉዳት መጠኑን እሱን መንገር ብቻ ነው
- እሺ
- እኮ ማን እንዳደረሰ ያውቃሉ ወይ ?
- ማን እንዳደረሰ
- አዎ ጉዳቱን አያውቁም አይደል ?
- አላወቅም አዎ
- እርሶ ሲደርሱ ድንጋይ እየተወረወረ ነው የደረሱት ወይ ሰላማዊ እያሉ ነው የደረሱት ?
- ድንጋይ ሲወረወር ነው የደረስኩት
- መጀመሪያም ፖሊስም ሳይኖር ድንጋይ ይወረወር ነበር ፖሊስ ከመጣም ድንጋይ ይወረወር ነበር እንዴ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፖሊስ ሳይደርስ ደረሰ አልደረሰ ሲጀምር እኛ ይዩን አይዩን አላወቅም ሲጀመር እና ድምፅ እያሰሙ ነው ብዬአለሁ ቀደምብዬ ገልፀዉልሀለሁ አላህዋክበር እያሉ ድምፃቸን ይሰማ እኛ ፖሊስ አንፈራም አላህ ነውየምንፈራው እንጂ አላህ ወደ ፊት እንጂ ወደ ኋላ አይልም እነዚህን ቃላቶች ሲወረውሩ በጆሮአችን እንሰማለን
- አይ ድንጋዩን ነው እኔ ያልኮት እሱን ቃላት ወረወሩ ?
- አዎ
- ድንጋይ ይወረውሩ የነበሩት በእዚህ ጊዜ ነው ወይስ እናንተ ከመጣችሁ በኋላ ነው ጥያቄዬ ?
- በቃ በእዚያ ወቅት ነው በቃ አላህክበር እያሉ ድንጋይ እና ጠርሙስ ይወረውራሉ
- ወዴት ነበር የሚወረውሩት እናንተ ሳትደርሱ ?
- ወደ እኛ ነው የሚወረውሩ
- ስለዚህ የወረወሩት እናንተ ከደረሳችሁ በኋላ ነው ?
- አዎ
- ጨረሳችሁ
- ቆይ
- ኮንስታብል በየነ እርሶ አላህክበር ተብሎ እዚያ ቦታ ላይ ሲደርሱ ቀድሞት ሌሎች ፖለሶች ደርሰዋል ?
- ይድረሱ አይድረሱ አላወቅም በወቅቱ ፖሊስ አባሎች ከእኔ በፊት የደረሱ ሊኖሩ ይችላሉ ግን አላወቅም
- ቅድም ያስረዱ ነገሩ የሆነው ከ 5 ሰዓት እስከ 8 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው ብለዋል እርሶ ሙሉን ሰዓት ነበሩ እዚያው ?
- አዎ ከተመታሁኝ በኋላ የተወሰነ ሰዓት ለእዚያ ክሊኒክ እንትን ሄጄ እንትኑን ደመን ለማስጠረግ እና ለማሻሸግ
- እዚያው አካባቢ ቅርብ ነው አይደል ?
- አዎ ቅርብ ነው ክሊኒኩ ቅርብ ነው
- እዚያ አካባቢ ላይ የሚባሉ ነገሮች በሙሉ በደንብ ይሰማዎት ነበር አይደል እዚያ አካባቢ ላይ ያሉ ድምፆች በሙሉ በደንብ ይሰማዎት ነበር አይደል ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የእነዚያ የአላህክበር የሚሉ ድምፅ
- አዎ ?
- አዎ ይሰማል አዎ
- አላህክበር አላህን እንጂ ፖሊስ አንፈራም ድምፃችን ይሰማ ቅድም የዘረዘሯቸው ነገሮች ከእነዚህ ውጪ ምንም ነገር አልተገሩም አይደል ?
- አዎ
- ይሄንን ብቻ ነው የተናገሩት ጨርሻለሁ የተከበረው ፍ/ቤት
- ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ ዐቃቤ ሕግ
- ጉዳቱን ማን አደረሰው ማን እንዳደረሰው ያውቃሉ ወይ ተብለው በመስቀኛ ሲጠየቁ አላውቅም ብለዋል ኮንስታብል በየነ ቅድም ደግሞ ሲነግሩን ተረጋጉ ስንላቸው እናንተ የመንግስት ሌቦች ናችሁ እያሉ ቅድም አሁን የዘረዘሯቸውን የተናገሩ ሰዎች ነበሩ ብለዋል ታዲያ ጉዳቱን ማን ነው ያደረሰው ከየት በኩል ሌላ ሰው ነበር እንዴ ከእነሱ ውጪ ?
- ከእነሱ ውጪ ማንም አልነበረም
- ታዲያ ጉዳቱ ከየት ነው የደረሰው ?
- ጉዳቱ የደረሰው ከእነሱ ነው
- እነሱ እነ ማን ናቸው ?
- አዎ እነሱ አላውቃቸውማ ከእዚያ
- እኮ እነሱ ማለት ?
- በወቅቱ ማን እንዳደረሰ እኔ እራሴ ጉዳት ደርሶብኛል
- ቆይ ምስክር ጥያቄው በግለሰብ ደረጃ ነው ለይቼ አላውቅም እያልክ ያለኸው በግለሰብ ደረጃ ማን እንደሆነ ለይቼ አላውቅም ወይስ ከመስኪድ የወጡ ሰዎች አይደሉም ነው ?
- አይደለም በግለሰብ ነው አሁን ለምሳሌ እኔ ጉዳት ደርሶብኛል አይደል ጉዳት ያደረሰብኝ አካል
- ከየት በመጣ ሰው ነው የደረሰብህ ነው ጥያቄው ?
- ከእነዚያ ከእነዚያ ረብሻ
- እነዚያ አናውቃቸውም እነሱን በትክክል አናውቃቸውም እኛ እነዚያ በእናንተ ላይ ጉዳት ያደረሱት ሰዎች ከየት የመጡ ናቸው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከአንዲያ ከአንዲያ ከመሰከሪያ ቢሮ
- ሥዩሉ
- ቅድም መባራት ጠፍቷል ወይ አልጠፋም ሰትል አልጠፋም ብለሀል አንተ ወደ ሕዝመግ በሄድክበት ሰዓት ያጥፋ አያጥፋ የምታውቀው ነገር አለ ወይም አንተ ?
- እዚያው ነዋ ከለኔኩ አዚያ ነው
- እኮ አንተ ያለህበት አካባቢ መበራት ላይጠፋ ይችላል በሌላ በኩል መበራት ጠፍቶ ይሆን አያውን የምታውቀው ነገር የለም አለ ?
- አልጠፋም ሰንድ እኮ አልቀየሁም ቢሮ አዚያ ወዲያው ሕዝመግ ተደረገልኝ ተመልሼ ወደ ስራዬ ገባው
- ከእዚህ አውን ቅድም ከዘረዘርከሻው ውጪ ሰለመባሉ አልሰማሁም ነው አልተባለም ነው ቅድም ከተባለት ውጪ አውን ከነገርከን አንተ ከምታስታውሰው ንቁዝ ውጪ ሰለመባሉ አላስታውሰም አልሰማሁም ነው አልሰማሁም ነው አላስታውሰም ነው ?
- አኔ አላስታውሰም እንጂ በአዚያን ወቅት ብዙ ቃላት ሲወጣ ነበር የማስታውሳቸው ታላላች አውን የገለፅኩሻው
- ኧረ ምሰከር ቀይ አላምጠ ወደ አዚህ አደላመጣችሁ
- ሌላ ከአዚህ ውጪ
- ድጋሚ ጥያቄ አበቅቀናል
- ምሰከር እናመሰግናለን ጨርሰሻል
- አንድ አጭር ምሰከር ካላቸው
- በእውነት ለመመሰከር በእግዚአብሔር ስም ምያለህ
- ለምሰከርነት ነው የመጣኸው ?
- ትክክል
- ስምህን የአባትህን ስም ሳትናገር የራስህን ስም ትገረናል ?
- ሂንው
- ሰንተኛ ናቸው ወይቤ ሕግ ?
- ፡፡፡ ላይ ደርሰናል በተሰሙት ሥልፅ ያልሆነ/ 89 ላይ በማስረጃ ዝርዝሩ ላይ የተጠቀሰ ምሰከር ለምሰከርነት ነው የመጣኸው ዛሬ አይደል በእነ ማን ላይ ነው የምትመሰክረው ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ በሰዓቱ ሌላ በሰዓቱ እኔ ሌላ ግቢ ውስጥ ነበርኩኝ
- በሰዓቱ ማለት ?
- በ 14/11ኛ ወር
- በ 14/11ኛ ወር ?
- ትክክል
- ዓ.ም ?
- 2004
- ምን አዩ እስቲ አጠር አድርገው ይንገሩን እና ወደ ዝርዝሩ ሳይገቡ ወደ ዝርዝር ሳትገባ አጠር አድርገህ ንገረን ?
- አይ በሰዓቱ ጣቢያ ውስጥ ነበርኩኝ እና ከእዚያ ኃይል ጨምሮ ተበሎ ስልክ ሲደወል ከጣቢያ ነው የወጣነው ከጣቢያ እንደወጣሁ ልክ ጣና ጋር ስደርስ ድንጋይ ውርወራ ነው የነበረው በእዚያን ሰዓት ላይ ከእዚያ በተወረወረ
- ለእኛ ይበቃል ዋና ጥያቄ ዐቃቤ ሕግ
- ኮንስታብል ምንድን ነው· አሁን በገለፅከው· ጊዜ ምንድን ነው· የተመለከትከው· ወይም የተረዳኸው· ?
- እዚያው· ቦታ ላይ ስደርስ ድንጋይ ውርወራ ነው· የነበረው· የሆኑ ቃላቶችም ነበሩ የሚናገሩት ድምፃችን ይሰማ
- እስቲ ቦታውን ንገረን ቦታው· የት ነው· ?
- መጀመሪያ የደረስኩት ጣና ነው· ከጣና 7ኛ ስደርስ ነው /ግልፅ ያልሆነ/ 7ኛ ጋር ነዉ
- ቦታው· ምን ተበሎ ነው· የሚታወቀው· በስም ?
- ቦታው· 7ኛ ወይም አማኑኤል ታክሲ ተራ
- እናንተ ከየት ጣቢያ ናችሁ ?
- መርካቶ
- መርካቶ ጣቢያ ?
- አዎ
- ስንት ሰዓት ነው· ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጉዳት /ግልፅ ያልሆነ/ የደረሰብኝ 9 ሰዓት ላይ ነው
- አይ እኔ ጣቢያ ነበርኩ ያልክበት ሰዓት ስንት ሰዓት ነው ኃይል ጨምሩ ተብለን ?
- ጁማ ሰዓት ላይ ነው ወደ 7 ሰዓት አካባቢ
- 7 ሰዓት አካባቢ ንገረን እሺ ማን ነው ማለት እኛ ጣቢያ ነበርን ?
- 7 ሰዓት ከቀኑ ነው ?
- ቀን ላይ አዎ
- እኛ ጣቢያ ነበርን ኃይል ጨምሩ ተብለን ሄድን ነው ያልከን ?
- ትክክል
- ማን ነው ይሄንን ያላችሁ ከየት ነው ?
- ከእዚያ ከመስኪድ አካባቢ ነው ስልክ ተደውሎ በጣቢያ ስልክ
- ተደውሎ ?
- አዎ
- ምን ስለተፈጠረ ነው ኃይል ጨምሩልን የተባለው ?
- ያው ድንጋይ ውርወራ እና ድምፃችን ይከበር እየተባለ ድንጋይ ውርውራ ስለነበረ በእዚያ ቦታ ነው ኃይል ጨምሩ ተብሎ የወጣነው እኛ
- እናንተ ስትደርሱ ድንጋይ እየተወረወረ ነበር ?
- አዎ ጣና ጋር ድንጋይ ውርወራ ነበር
- አንተ ከመድረስህ በፊት ድንጋይ መወርወር ተጀምሯል ?
- አዎ
- ንገረን እያስታወስክ አንተ ከደረስክ በኋላ የሆነውን ?
- የሆነው እኔ ከደረስኩ በኋላ ጣና አካባቢ ነው የደረስኩት ከጣና እስከ 7ኛ ያው ድንጋይ ውርወራ ነበረ በእዚያን ሰዓት ላይ ከእዚያ በኋላ አማኑኤል ታክሲ ተራ መውረጃውጋር ድረስ መንገድ ሁሉ ተዘግቶ በድንጋይ ተከትሮ ነበረ
- በምን ?
- በድንጋይ እና በጎማ ያ መንገድም የማስከፈት ስራ ነው የሰራነው
- በድንጋይ እና ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በድንጋይ እና በጎማ
- በጎማ ?
- አዎ
- ማን ነው የሸፈነው ወይም አሁን ያልከው የከተረው ?
- ያው ድንጋይ ሲወረውሩ የነበሩ ብዙ ናቸው እዚያ በእዚያን ሰዓት መለየትም አልቻልንም ከእዚያ ከመሀል በተወረወረ ድንጋይ ነው እኔም እግሬ ላይ የተመታሁት
- ምንድን ነው ማለት መነሻው ምንድን ነው እነዚህ ሰዎች አሁን ድምፃችን ይሰማ ብለው ድንጋይ እየወረወሩ ነው የተባሉት ሰዎች መነሻቸው ምንድን ነው ምክንያታቸው ?
- መነሻው እንግዲህ ከእዚህ በፊት ከእዚያ በፊትም የሆነ ሁከት ነበረ በ 6 በእዚያ ምክንያትም እኛ እስታንድ ባይ ነው የነበርነው ኪዙ ምን እንደሆነ አላወቅንም ከእዚያ በፊት የነበረውን
- እኮ እርሶ ደርሰዋል ምን ሲባል ሰምተዋል ለምሳሌ ?
- በቃ ያ ሲባል ነው እኔ የሰማሁት ድምፃችን ይሰማ በሚለው እና ድንጋይ ሲወረወር ነው እኔ የደረስኩት
- የደረስከው ?
- አዎ
- ምን ያህል ሰዓት ቆይተህል እዚያ ?
- እስከ 12 ሰዓት ከምናምን ድረስ እዚያ ነበርኩ
- ከስንት ሰዓት እስከ ሰዓት ?
- ከ 7 ሰዓት ከወጣሁበት ሰዓት ጀምሮ
- ከ 7 እስከ 12 ድምፃችን ይሰማ ብቻ ነው ሲባል የነበረው ?
- ድምፃችን ይሰማ ቃላችን ይከበር እየተባለ ድንጋይ ነበር ሲወረወር የነበረው
- እኮ አሁን ይኸውልህ እያስታወስክ ከ 7 ሰዓት ጀምሮ እስከ 12 ሰዓት አንድ ቃል ብቻ አይባልም አይደል ?
- አዎ የተለያዩ ቃላቶች አሉ /ግልፅ ያልሆነ/
- አዎ አኮ እነሱን እያስታወስክ ቀስ ብለህ ንገረን ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሲናገሩ የነበሩት በሰዓቱ ድምፃችን ይከበር ታላችን ይሰማ መንግስት ሌባ ምናምን እያሉ ብዙ ታላቶች
- ቆይ ቆይ ምስክር አሁን የሚያስታውሱትን ቀስ በለው ሲጠየቁ እሱን ነው የሚመስክሩ አሁን ምናምን ምናምን የሚለው ወረቀት ነው የሚያበዛው እንጂ ሌላ ምክንያት የለውም ስለዚህ በትክክል ያሉትን ሊያስታውሱ የሚችሉትን ብቻ ቀጠሉ
- ይቀጥሉ ኮንስታብል
- እሺ ያው በሰዓቱ ሲሉ የነበሩ ድምፃችን ይከበር ታላችን ይሰማ
- እኮ እሱን ብለዋል ሌላ ?
- እና መንግስት ሌባ የሚለው መፈክር ነበረ መንግስት ሌባ
- መንግስት ሌባ ?
- አዎ እየተባለ ድንጋይ ወርወራ እንደዚያ ነው የነበረው
- ከእናንተ ጋር ምንድን ነው ድንጋይ መወራወር ውስጥ ያስገባቸው ምንድን ነው ?
- ከእዚያ በፊት የነበረው ሂደት አላወኩም እኔ
- እናንተ ከደረሳችሁ በኋላ ምን አደረጋችሁ ?
- ምንም አላደረግንም የድምፅ ማጉያ ነበረ ተረጋጉ የሚለውን ነው እንትን ስንል የነበረ
- በምንድን ነው ተረጋጉ ስትሏቸው ?
- በድምፅ ማጉያ
- በድምፅ ማጉያ ?
- አዎ
- ምን እያደረጉ ስለነበር ነው ተረጋጉ የምትሏቸው ?
- ያው ድንጋይ ወርወራ እና ጩኸት ነው በቃ
- ጩኸት ?
- አዎ
- ጩኸት ማለት ?
- ይሄ ድምፃችን ይሰማ በሚለው
- የሚል ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ድምፃችን ይሰማ እያሉ ነበር ሲፈሙሁ የነበረው እና ድንጋይ ሲወረውሩ የነበሩት
- ስንት ሰዓት አበቃ ?
- ያበቃው ወደ 12 ሰዓት አካባቢ ነው ያበቃው ከእዚያ በኋላ ነው እኔ ከምሸቱ 2 ሰዓት አካባቢ ሕክምና ሄጀአለሁ በእዚያን ሰዓት
- ከ 7 ሰዓት እስከ 12 ሰዓት ላይ አብቅቷል ?
- አዎ
- እንዴት አበቃ 12 ሰዓት ላይ ?
- ያው ቦታው የገበያ ማዕከል ስለሆነ ነጋዴውም የሰው ኃይሉም ወደ የቤቱ ስለሚሄድ በእዚያ ምክንያት ነው የቀነሰው ይመስለኛል
- እየቀነሰ ሄዷል ?
- አዎ
- አንተ ላይ ምንድን ነው ጉዳት የደረሰው ?
- ግራ እግሬ ላይ ከጉልበቴ በታች ነው የተመታሁት
- ግራ እግሬ ላይ ከጉልበቴ በታች ?
- አዎ
- በምን ተመታህ ?
- በድንጋይ
- ማን ነው የመታህ ?
- አላወኩትም እዚያ መሀል ላይ
- አይ በስም በአካል ላትለየው ትችላለህ ከየት በመጣ ድንጋይ ነው የተመታኸው ነው ?
- ያው በእዚሁ ጉዳይ ነው 7ኛ አደባባይ አካባቢ ነው የተመታሁት ድንጋይ ሲወረወር
- እኮ በምን ምክንያት ነው የተመታኸው ማለት ቆመህ ምንም ነገር ካላደረጋችሁ የፖሊስ አባል ናችሁ አይደል ?
- ያው ቦታው
- ደንብ ልብስ ለብሳችዋል አይደል ?
- አዎ ለብሰናል

2784 622

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ደንብ ልብስ ለብሳችሁ ድንጋይ እንዴት ይወረወርባችዋል እንዴት ትመታላችሁ ነው ?
- እዚያ ጩኸቱን እኛ ለማረጋጋት ነው የወጣነው ኃይል ጨምሩም ሲባል የወጣነው ለእዚያ ነው
- እኮ አሁን እናንተ ለማረጋጋት ኃይል ተጨምራችሁ ነው የሄዳችሁት ?
- አዎ
- ኃይል ተጨምራችሁ ስትሄዱ የኃይል ተግባር ስለፈፀማችሁ ነው ምን ስላደረጋችሁ ነው
- የኃይል ተግባር አልፈፀምንም
- ስለዚህ እናንተ ላይ ድንጋይ ለምን ተወረወረ ?
- ያው መጀመሪያም ድንጋይ ሲወረወር ስለነበር ድንጋዩ
- የመጀመሪያውን አይደለም አንተ ከደረስክ በኋላ ኃይል ማለት ረብሻው ስለተስፋፋ ነው አይደል እናንተ የተጠራችሁት ?
- ትክክል
- ከተጠራችሁ በኋላ እናንተ ያደረጋችሁት ነገር ካለ ንገረን ወይ ዝም ብላችሁ ቆማችሁ የተመታችሁበት ምክንያት ምንድን ነው ከ 7 እስከ 12 ሰዓት ዝም ብላችሁ የምትቆመበት ምክንያት አይኖርም ?
- መልሱ ይሄንን
- ስለዚህ ምንድን ነው እናንተ ልትመቱበት የቻላችበት ምክንያት ነው ?
- እኛ ሁከቱን የማብረድ ስራ ነው ስራሰራ የነበረ ከእዚያ መሀል በተወረወረ ድንጋይ ነው የተመታነው
- ሁከቱ እንዴት ነው አስቲ
- ቆይ ይኸው ምስክር ጥያቄው ግልፅ ነው ጥያቄው እናንተ እዚያ ሄዳችሁ ምንም አላደረጋችሁም ግን በድንጋይ ተመታችዋል ለምን ምንም ሳታደርጉ ለምን ተመታችሁ ነው ጥያቄው ይሄ ነው ለምን ተመታችሁ እናንተ ?
- እኛ ሁከቱን ለማብረድ ነው በቃ ከያቅጣጫው ነበርነው ሁከቱን ለማብረድ ስንሯሯጥ ነበረ ስራ ላይ ነበርን
- ሌላ ጥያቄ
- ዋና ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ፍ/ቤት
- የተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ኮንስታብል ዋጋው እርሶ ጣና አካባቢ እንደደረሱ ኃይል ይጨመር ከተባለ በኋላ ጣና አካባቢ እንደደረሱ ገልፀው ልናል በየት በኩል ኢድርገው ነው ጣና የደረሱት ?
- በምዕራብ በኩል
- ከምዕራብ ሆቴል?
- አዎ
- ከምዕራብ ሆቴል ተነስታችሁ ጣና ይሄ ገበያው አዳራሽ ነው አይደል ጣና የሚሉት ?
- የገበያ ማዕከሉ አዎ
- ይሄ ገበያው ይሄ ባንክ ምናምን ያለበት ?
- አዎ
- በምዕራብ ሆቴል አካባቢ እናንተ በርከት ብላችሁ ነው አይደል የሄዳችሁት ?
- ትክክል
- በእግር ነው በመኪና ?
- በእግር ነው
- በእግር ስትሄዱ መንገዱ ነፃ ነው ?
- መንገዱ ጨቼት ነበረ የመሬጫህ እና አልፎ አልፎ ድንጋይ የመወርወር ሁኔታ ነበረ ከእዚያ በኋላ ነው
- ማለት አሁን ከምዕበራ የተነሳችሁት ከምዕራብ ሆቴል ነው ወይስ ከጣቢያችሁ ነው ?
- ከምዕራብ ነው የተነሳነው
- ቆይ ጠበቃ አሁን ምዕራብ ሆቴል ተነስተው ጣና ገቢያ ላይ ደርሰዋል ስለዚህ እሱ ላይ ተነስታችሁ ጠይቁ ወደ ኋላ ወደ ምዕራብ
- ሂደቱን ሲሄዱ መንገዱ ላይ እየበተናችሁ ነው የሄዳችሁት ወይስ ቀጥታ አልፎ አልፎ ከነበረው ሰው ውጪ ዝም ብላችሁ እናንተ ሄዳችሁ ጣና ጋር ደረሳችሁ ?
- ምንም አልበተንም አልፈን ጣና ጋር ስንደርስ ከእዚያ ድንጋይ ውርወራ ነው የተጀመረው
- ጥሩ አሁን ከምዕራብ ሆቴል ወደ ጣና ጋር ደረሳችሁ ከእዚያ በኋላ ድንጋይ የተወረወረው በምዕራብ ሆቴል በኩል የሚመጣ ሰው ነው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ ከኋላ ያለውን አዕድታችሁ እየገፋችሁ እየገፋችሁ ሄዳችሁ እና 7ኛ አካባቢ ሲደርሱ ጉልበትዎን እንደተመቱ ነግረውናል ?
- ትክክል
- ጉልበትዎን ተመቱ እና ስራ ላይ ቀጠሉ አይደል እርሶ ?
- አዎ ስራ ላይ ነበርኩኝ
- ከእዚያ ረብሻው ከበረደ በኋላ ወደ ሆስፒታል የሄዱት 2 ሰዓት ላይ ነው ከምሽቱ 2 ሰዓት ነው አይደል ረብሻው 12 ሰዓት ላይ አካባቢ ቆመ እርሶ ከእዚያ በኋላ ወደ ሆስፒታል ሄዱ ?
- አዎ
- ሆስፒታል ሄደው ምን ያህል ቆዩ ?
- ሆስፒታል ብዙም አልቆየሁም ያው የተመታሁት ትንሽ ቁስል ስለነበረ ታሸገ
- ወዲያው ታሸገ እና ?
- ተመልሼ አዳር በእዚያው አዳር ነው የቀጠልነው ወደ ስራ ማለት ነው ስራ ነው የገባነው
- በማግስቱ ስራ ገቡ ?
- አዎ በእዚያው ማታም ስራ ነበርን አዳር ነበርን እስታንድ ባይ ሆነን ነው ያደርነው
- ምስክር ቅድም ሲመሰክሩ ይሄንን ላቆየው እና ከአንዋር መስኪድ እስከ 7ኛ ምን ያህል ይርቃል ከአንዋር መስኪድ እስከ 7ኛ ድረስ ርቀቱ ምን ያህል ይሆናል ?
- እንግዲህ ርቀቱ ይሄንን ያህል ብሎ መገመት የተወሰነ ይከብዳል
- በሚያውቁት ፍ/ቤቱ እንዲረዳ በሚያውቁት ምን ያህል ይርቃል ?
- ቢያንስ ከ 10 ደቂቃ እስከ
- 30 ?
- አይፈጅም 10 ደቂቃ ቢፈጅ ነው
- 10 ደቂቃ በመኪና ነው ?
- በእግር
- በእግር ይህ ማለት እስከ 2 ኪሎ ሜትር 3 ኪሎ ሜትር ይሆናል ?
- እሱ ስለኪሎ ሜትር መገመት ያስቸግራል
- ከአንዋር መስኪድ እስከ አማኑኤል ምን ያህል ይርቃል ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በምዕራብ በኩልም በታችኛው ወደ ሲኒማ ራስ በሚወርድም ከየአቅጣጫው ነው ድንጋይ ውርወራ የነበረው
- በሲኒማ ራስ ?
- በሲኒማ ራስም በጣና ወደ ምዕራብ በሚወስድው መንገድም በላይ በአዲስ አበባ ገቢያ ማዕከል በራጉኤል በኩልም ድንጋይ ውርወራ ነበረ
- እናንተ ከሁሉም አቅጣጫ ነበር የሚወረወርባችሁ ወይስ የሆነ ወደ ኋላ የሚሸሹበት የምታፈገፍጉበት ክፍት ቦታ ነበራችሁ ድንጋይ ሲወረወር አሁን ከራጉኤል በኩል ከሲኒማ ራስ በምዕራብ አቅጣጫ ድንጋይ ተወረወረ ከእዚያ እናንተ ድንጋዩን ለመሸሽ ወዴት ነበረ የምታፈገፍጉበት ሁኔታ ነበረ ማለት ድንጋይ የማይመጣበት አቅጣጫ ነበረ ?
- ድንጋይ በተለያየ አቅጣጫ ነው የሚመጣው ስትሄድ የመሸሽ ሁኔታ አለ ስትቆም ደግሞ መልሶ የመምጣት ሁኔታ ነው ነበረው በሰዓቱ
- ስለዚህ አሁን ወደ ከጣና ወደ አንዋር የሚወስደው አካባቢ አለ ቀጥታ መንገድ ያውቁታል አይደል ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ስለዚህ ወደ እዚያ ለማፈግፈግ የሞከራችሁበት ሁኔታ አለ ?
- አይ እዚያው ነው የቆምነው አዲስ አበባ የገቢያ ማዕከል ጋር ቆምን ከየአቅጣጫው ድንጋይ ሲወረወር የነበረው
- ምንን ከለላ አደረጋችሁ አሁን ከየአቅጣጫው ድንጋይ ከተወረወረ እናንተ መሀል ላይ ገባችሁ?
- እኛ መሀል ላይ ነበርን እንደከለላ የምንጠቀመው ይሄ የግንቦችን እንትን ነው ግንቦችን ነው እንደከለላ የምንጠቀም የነበረው
- የጣናን ግንብ ማለትዎ ነው ?
- የአዲስ አበባ የገቢያ ማዕከሉ የፎቁ ግንብ እንደከለላ ስንጠቀም የነበር እዚያ አካባቢ የተጎዱ ልጆች አሉ በሰዓቱ
- ከእዚያ እናንተ አሁን እየገፋችሁ ሰውን ወደ ምዕራብ ሆቴል ወደ 7ኛ እየገፋችሁት ነው የሄዳችሁት ወይስ ምንድን ነው ?
- ትክክል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሱ የእኛ ስራ ስላልሆነ እሱን ብዙም አናወቀውም
- የቦታ ክርክር /ግልፅ ያልሆነ/ እሱን አሳጥሩት እና
- የተከበረው ፍ/ቤት የማሳየው ነገር ስላለ ነው
- የሚጠይቁትን ፋክት ጠይቁታ /ግልፅ ያልሆነ/ ክርክር እኮ አይደለም
- እርሶ የቱ ጋር ነው ተመታሁ ያሉት ?
- 7ኛ ጋር
- 7ኛ ጋር ከመስኪድ የወጣ ሰው ብቻ አይደለም አይደል የሚኖረው 7ኛ ጋር ከሌላም ጋር የመጣ ወይም የአካባቢውም ነዋሪ አለ አይደለ ?
- የአካባቢ ነዋሪ ሊኖሩ ይችላል ሲወረወር የነበረው ዞሮ ዞሮ ሁከቱ መነሻው ያ ነው የመጀመሪያው
- ከአማኑኤል ታክሲ መያዣ እስከ አንዋር መስኪድ ድረስ ሙስሊሞች ብቻ አይደለም አይደል የሚኖሩት ?
- የሚኖሩት ሙስሊሞች ብቻ እንዳልሆኑ ይታወቃል ሙሉ መርካቶ ገበያ ማዕከልም ስለሆነ
- የድምፅ ማጉያ ተጠቅመናል ብለዋል በድምፅ ማጉያ ምን ምን ነበረ ሲባል የነበረው ?
- በእኛ ድምፅ ማጉያ ነው ?
- አዎ
- ተረጋጉ የማለት የማረጋጋት እና ተረጋጉ እየተባሉ ነው ሲነገር የነበረው
- በቃ ይኸው ብቻ ነው ?
- አዎ
- ለምሳሌ አህመዲን ጀባልን ይዘነዋል ብንፈልግ እንገድለዋለን ብንፈልግ እንሰቅለዋለን የሚል ንግግር አልነበረም ?
- አልሰማሁም ይሄንን ቃል
- ይሄንን እርሶ ተጀምሮ እስኪያልቅ የድምፅ ማጉያው ጋር ነበሩ ?
- የድምፅ ማጉያው ብዙ ጊዜ ከአንድ ሰው ጋር ስለማይሆን
- እኮ እርሶ አሁን የስራ አካባቢዎ የድምፅ ማጉያ ወይም በድምፅ ማጉያ መናገር አይደለም አይደል ከድምፅ ማጉያ ርቀው ሊገኙ የሚችሉባቸውን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያው ካልሰመ አልሰመም በቃ አልሰማንም በሚል ያዘት እኮ እንዲህ ዓይነት ነገር መቼም ቢሆን አልሰማሁም አለ ይበቃል
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እርሶ የሸፈኑት አካባቢ ከየት እስከ የት ነበረ ?
- ከጣና ከተነሳሁበት እስከ ተጎዳሁበት ድረስ
- የተጎዱት ማለት ?
- 7ኛ
- እሺ እርሶ ባሉበት አካባቢ ወይም ቅድም ሲመሰክሩ የፖሊስ አባላት የኃይል ተግባር መፈፀማቸውን አላውቅም ብለዋል እርሶ ከሸፈኑት ውጪ ያሉ አካባቢዎች ላይ የኃይል ተግባር ይፈፅሙ አይፈፅሙ አያውቁም አይደል ?
- አላወኩም
- ጎማ ደርድረው መንገዱን ዘግተውታ ብለዋል የቱ ጋር ነው ጎማ የተደረደረ የነበረው ?
- 7ኛ ታክሲ ተራው ጋር
- 7ኛ ታክሲ ተራ ?
- አዎ
- መስኪድ ውስጥ ያለ ሰው ጎማ ሊይዝ አይችልም አይደል ?
- መስኪድ ውስጥ አይደለም መንገድ ላይ ነው የተደረደረው መጀመሪያ
- እዚያው የአካባቢው ሰው ሊሆን ይችላል አይደል ይሄንን ያደረገው ?
- የአካባቢው መነሻ ከምን አንፃር በሚለው ደግሞ ስንሄድ መጀመሪያ የተነሳው ነገሩ በነገር ስለሆነ በእዚያ ምክንያት ነው
- እኮ አሁን ይሄንን ጎማ ሊደረድር የሚችል ሰው
- እስቲ መጀመሪያው አልገባንም መስኪድ ውስጥ ያለ ሰው ጎማ መያዝ አይችልም ምን ማለት ነው እስቲ ግልፅ አድርጉልን ?
- ትተነዋል ጥያቄውን
- ተጨማሪ ኃይል መጣልን ብለሀል ተጨማሪ ኃይል የእናንተ እስታንድ ባይ የነበረ የእናንተ ሰው ነው ወይስ ሌላ ፈዴራል ፖሊሶች ናቸው የመጡት ?
- የእኛ እስታንድ ባይ ግቢ ውስጥ የነበርን ልጆች ነን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሉላ ፌደራል ፖሊስ አልነበረም ?
- ፌደራሎች አላየሁም
- አላየህም ?
- አዎ
- ከመጀመሪያ እስከ መፈክረሻ አላየህም ?
- አላየሁም እኔ ወደ 7ኛ ነው ቀጥታ የሄድኩት
- እኮ ከ 7 ሰዓት እስከ 12 ሰዓት አልነበረም
- ይበቃል እኮ አሁን አላየሁም ካለ ጥያቄውን ጠይቃችሁ አላየሁም ካለ 3 ጊዜ ከተናገረ ምንድን ነው ከእዚያ
- አይ አጠያየቁ የተለያየ ስለሆነ ለእዚያ ነው እሺ አስለቃሽ ጭስስ ነበር ?
- እኔ በነበርኩበት አላየሁም
- እስከ 12 ሰዓት ግን ነበርክ አንተ ?
- አዎ
- አንተ የተመታኸው 7ኛ ላይ ነው ብለሀል 7ኛ ላይ እዚያ 7ኛ አካባቢ ሲወረውሩ የነበሩ ሰዎች ነው የመቱህ ?
- አዎ
- 7 ሰዓት ጣና አካባቢ ደርሷል ከእዚያ ሰውን እነዚህ ድንጋይ የሚወረውሩትን ቢያንስ እስከ ምዕራብ ድረስ እንዴት እንደገፏቸው ቢነግሩን ልክ ከጣና እስከ ምዕራብ 7 ሰዓት እርሶ ደርሰዋል ድንጋይ የሚወረውር አለ እናንተ ይሄንን ለመበተን ከድምፅ ማጉያ ጀምራችሁ ተጠቅማችሁ ምዕራብ ሆቴል እስኪደርስ ድረስ እንዴት እንዳደረጋችሁት በወቅቱ ስለነበረው ሁኔታ እስቲ ይንገሩን ?
- እስከ እዚያ እስከምደርስ ሰዓት የነበረው ሁኔታ ስንከተላቸው ይሸሻሉ ስንቆም ይመጣሉ ስንከተላቸው ይሸሻሉ የነበረው ሁኔታ
- በእዚህ ሂደት ድንጋዩን ወደ እናንተ ነበር የሚወረውሩት ?
- ትክክል
- በእናንተ ላይ ያርፋል ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ በእኛ ላይ ነው ምዕራብ ጋር 2 ልጆች ተጎድተዋል ከእዚያም እራሱ የተሰባበረ ብዙ ፎቅ አለ እራሱ እዚያ
- አዎ ምዕራብ እስኪደርሱ እናንተ ላይ ወረወሩ እናንተ እየሸሹ እየመጡ እናንተ ስትቆሙ እያሉ እየገፋችሁ ሄዳችሁ እንጂ ከእናንተ ውጪ በሌላ ላይ ያደረሱት ነገር አለ በወቅቱ እርሶ ያዩት ?
- የድር ተራ ገበያ ማዕከል መስታወቱ እራሱ ብዙ መስታወት ተሰብሮ እንደአዲስ ነው መስታወት የተቀየረው
- ድር ተራ ማለት ሱቆች ማለት ነው ?
- ሱቆች አዎ የገቢያ ማዕከል
- ሱቆች ተሰበሩ ?
- አዎ
- ከእዚያ ውጪ እርሶ እያዩ እዚያ ጋር የደረሰ ነገር የለም ?
- እኔ እያለሁ ድንጋይ የሚወረወረው ወደ እኛ ነበር በታ እኛ ላይ ጉዳት ከመድረስ እና ከመስታወት መሰበር ያየሁት ነገር የለም
- ኮንስታብል አሁን መጨረሻ ላይ ከመለሱት ጥያቄ ልነሳ እና እኛ ስንደርስ ይሸሻሉ እናንተ ስትመለሱ ደግሞ ወደ እናንተ ይመጡ ነበር አይደል ?
- ትክክል
- አልሸሸም ያለውን ሰው ምን ታደርጉት ነበር ትመቱት ነበር አይደል ?
- ያልሸሸ የለም ይሸሻሉ
- አይ ባይሸሽ ለምሳሌ ?
- ባይሸሽ ያጋጠመን ነገር
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለን
- ምንድን ነው መቃወሚያ አሁን የተከበሩ ጠበቃ የሚያነሱት ጥያቄ እንትን ነው ኤሉሽን ነውእና ልክ አይደለም ይሄ ደግሞ ቀደም ብሎ ፍ/ቤት ብይን ሰጥቶበታል አፕኒየን ባይሆን ኖሮ ምን ታደርግ ነበረ ሸሽቷል ብሎ መስክሯል ሸሽቷል አልሸሹም ነው ክርክሩ መሆን ያለበት እንጂ ባይሸሹ ግን ደርሳችሁ ትመታችዋቸው ነበር ወይ ማለት አግባብነት ያለው ጥያቄ አይደለም እና እንዲታለፍ
- ልመልስ የተከበረው ፍ/ቤት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥያቄው ይስተካከል የመቱት ሰው አለ ወይ አለ የመታኸው ሰው ?
- የለም የመታሁት
- የመታችሁት ?
- የመታሁት የለም
- ቀጥሉ ሌላ ጥያቄ
- ሌሎች ጓደኞችስ ስላለመምታቱ ያውቃሉ ?
- የመታ የለም
- አይተዋል ስለራስዎ ማወቅ ይችላሉ ስለሌሎቹ ?
- እኔ ጋር ከነበሩት ጋር የተወሰኑ የነበሩት አያቹአቸዋለሁ እኔ ጋር
- ማንንም አልመቱም ?
- አልመቱም
- ቅድም የጁማ ሰዓት ነበር ብለዋል ይሄ ቀን አርብ ዕለት ማለትዎ ነው ስለሚመዘገብ ?
- አርብ ይሁን ቅዳሜ ይሁን አላስታወስኩትም ቅዳሜ እንደዚህ 7 ሰዓት ላይ ጠበቀው የተሰበሰቡበት ጊዜ ስላለ
- ይሄንን ቃል ነው ያልኩት ስለእዚች ቀን ነው ?
- አርብ ይሁን ቅዳሜ ይሁን አላወኩትም
- ቀኑን አያወቁትም ?
- አዎ ዕለቱን አላስታወስኩትም ቀኑ ግን በ 14 መሆኑን ነው የማስታወሰው
- ጁማ ስላሉ ብዬ ነው ቅድም እሺ
- ሁሌ ጁማ ሰዓት ላይ 7 ሰዓት ላይ ስለሚሰበሰቡ
- ድንጋይ የተወረወረው እናንተ ስትደርሱ ነው ወይስ ከእናንተ በፊትም ድንጋይ ውርወራ ነበር ?
- ከእዚያ በፊት ድንጋይ ውርወራ ስለነበር ታይል
- እሱ እኮ ቅድም በብዛት ተጠይቆ ብዙ ምላሽ ተሰጥቶበታል
- በእዚህ መነሻ ልቀጥል ነበረ እንደመግቢያ ነገር /ግልፅ ያልሆነ/
- እኮ ስትጠይቁ ጥያቄውን ዋናውን ጠይቁ ምክንያቱም ምስክሩ ያለው ነገር እኛም ግልፅ ነን እናንተም ግልፅ ናችሁ ወረቀት እና ጊዜ ነው የሚጨርሰው በኋላ እኮ ይሄንን ወረቀት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የምንመረምረው እኛ ስለሆንን በጣም ያስቸግረናል ይሄንንም አስቡልን ስለዚህ ጥያቄውን ብቻ ጠይቁ መልሱን ብቻ ከምስክሩ እንስማ

- ቅድም ከሰሙት ነገር ውስጥ የማስታወሰው ብለው ድምፃችን ይሰማ የሚል ነገር አለ ብለው ነበረ ትግላችን ሰላማዊ ነው ሲሉስ ሰምቶው ነበር አይደል ቅድም በዐቃቤ ሕግ ሲጠየቁ ድምፅችን ይከበር ብለው ነበር ብለዋል ያስታወሳሉ ይሄንን አይደል ?
- ድምፃችን ይከበር እያሉ ሲጮሁ እንደነበር አስታወሳለሁ
- ትግላችን ሰላማዊ ነው ሲሉስ ሰምተዋል አይደል ?
- እሱን አልሰማሁም ብዙ ጊዜ ድምፃችን ይከበር ነበር ድምፃችን ይሰማ የሚለውን ነው
- ይበቃል
- 7ኛ መስኪድ አለ የተመቱበት ቦታ ?
- አይ 7ኛ መስኪድ እንዳለ አላውቅም
- የተመቱበት ቦታ የለም መስኪድ ?
- ትክክል
- ተጨማሪ ኃይል ሆናችሁ ስትሄዱ ስትጠሩ ምን ይዛችሁ ሄዳችሁ ?
- ምንም አልያዝንም
- ቦዶ እጅ ነው የሄዳችሁት ?
- ባዶዬን ነበር ከግቢ ውስጥ ቢሮ ነው የምንሰራው ግቢ ውስጥ ነበርን በባዶ እጃችን ነው የወጣነው
- ሰውን ታዲያ የምታስሮጡት በምን ነበረ ቅድም ስናሯሩጥ ነበር ብለሀል ሰዎችን በምን ነበር የሚሮጡት ባዶ እጅ /ግልፅ ያልሆነ/?
- ትክክል ባዶ እጃችን ነበር እኛ ከግቢ ነው የወጣነው መከላከል ኃይል የምንሰራው እስታፍ ነበር የምንሰራው ስንወጣ በቦዶ እጅ ነው የወጣነው
- ስለዚህ ምንም አልያዛችሁም ?
- ምንም አልያዝንም ስንሮጥ ይሮጣሉ ስንቆም ይቆማሉ ይመለሳሉ
- እስታንድ ባይ የሆነ ሰው ባዶ እጁን ነው የሚሆነው ቅድም እስታንድ ባይ ነበርኩኝ ብለዋል እና ስትወጡ ኃይል ጨምሩ ሲባል እስታንድ ባይ ስትሆን ባዶ እጅ ነው የምትሄደው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቢሮ ውስጥ ስለነበርን እኛ ቢሮ ውስጥ ምንም አንይዝማ ለእዚያ ነው
- እስታድ ባይ አልነበርክማ ?
- አሁን ጥያቄው ፖሊስ ስለሆኑ ያንን ጨኸት ሰምታችሁ በተጨማሪ የመጣችሁ ስለሆነ እሱን ለመከላከል ምን ይዛችዋል ነው ጥያቄው ?
- ምንም አልያዝንም ከቢሮ ነው የወጣነው እኛ በሰዓቱ
- ምንም የያዛችሁት ነገር የለም ?
- አልያዝኩም
- ቀጥል
- ምስክር የመጨረሻ አንድ ጥያቄ ልጠይቆት ቅድም እርሶ ከተናገሩት ድንጋይ ሲወረውሩ የነበሩት ብዙ ናቸው ለይተን አናውቃቸውም ብለዋል መስኪድ አካባቢ ደግሞ ሲባል የነበረው ብለው ድምፃችን ይሰማ ድምፃችን ይከበር የመሳሰለ የመሳሰሉትን ነገር ተናግረዋል በእዚህ መሀል የሙስሊሞቹ ጥያቄ የተናገሩት ከሆነ እስከ 7ኛ ድረስ ደግሞ ጎማ ደርድረው ይሄንን የመሰለ ነገር ከተፈጠረ በሙስሊሞቹ ጣልቃ ገብቶ የሆነ ረብሻ ለመፈፀም ያሰበ አካል ይኑር አይኑር ማረጋገጥ ይችላሉ ?
- እሱን አላውቅም
- ሊኖር ይችላል አይደል ?
- አይ አላውቅም ካሉ ይበቃል ግልፅ እኮ ነው ይሄ
- ጨርሰናል
- ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ
- አዎ አለን የተከበረው ፍ/ቤት ኮንስታብል ጉዳት ከደረሰብኝ በኋላ በድጋሚ እስታንድ ባይ ሆኜአለሁ ብለሀል ለምኑ ነው እስታንድ ባይ የሆናችሁት በድጋሚ ?
- ምናልባት እንደዚያው ብጥብጥ ሊነሳ ይችላል የሚለውን ነገር ስላሰቡ ስራም አዳር ነበርን በእዚያው አዳር ገባን
- ተመሳሳይ ብጥብጥ እንዳይኖር በሚል ነው ?
- አዎ
- ከሕክምና ወደ እስታንድ ባይ ማለት ቀጥላችሁ ያደራችሁት ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- አሁን መጨረሻ ላይ የተጠየቁትን ጎማ የደረደሩት ከመ/ስሊፃቹ ቅድም ተናግረዋል ከሚሉት ሰዎች ውጪ ሌላ የፖለቲካ ነገር ሲናገር የነበረ ሰው ነበር ከእናንተ ጋር ?
- ከእኛ ጋር ማንም የለም
- በአለባበሳቸውስ ?
- ያው አለባበስ ብዙ መርካቶ ስለነበር ብዙ ነው ድንጋይ ወርወረውም ከአቅጣጫው ስለነበር በቃ የፊቱን ይዘን
- ጎማ የተደረደረበት አካባቢ ድምፃችን ይሰማ ይከበር የሚል ጩኸት ነበር ?
- አዎ ጩኸቱ እንደዚያ ነው
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- በፍ/ቤቱ ጥያቄ
- እናንተ እስታንድ ባይ ሆናችሁ ስትመጡ በእጃችሁ ምንም ነገር የያዛችሁት ነገር የለም ?
- ከቢሮ ነው የወጣነው
- እኮ ከቢሮ ስትወጡ የሆነ ጩኸት የሆነ ፀጥታ ልታስከብሩ ነው የምትወጡት በባዶ እጅ ማስከበር ይቻላል እንዴ ?
- ያው እኛ አጋጣሚ ቢሮ ውስጥ ስለነበር የምንሰራው ሁሌም የተለመደ ስለሆነ ሁሌ አርብ አርብ እስታንድ ባይ ምናምን ስለሚባል ቢሮ ስራ የሚሰራው ቢሮ ስራ የሚሰራው ቢሮ መደበኛ ነው የሚሰራው መርማሪ የመርማሪ ስራውን ነው የሚሰራው የመረጃም የመረጃ ስራ ነው የሚሰራው ዱላ የሚይዝ የለም እዚያ አጋጣሚ ውጡ ሲባል ሁሉም ዝም ብሎ ነው የወጣው
- የፖሊስ ዩኒፎርም ለብሳችዋል ?
- አዎ
- እናመሰግናለን ጨርሰዋል
- አሁን ያው ምሳ ሰዓት እየደረሰ ስለሆነ 8 ሰዓት ላይ እንገናኛለን::
- ችሎቱን እንጀምራለን የዐቃቤ ሕግ ምስክር ቀጣዩ ይቅረብ /ግልፅ ያልሆነ/ ተከሣሽ አለ የለም ያው የ ነኛ ብቻ አልመጡም እሺ ጠበቃ አንድ ተቀንሷል የ 28ኛ እና ሌላ ስለዚህ ያላችሁ አስመዝግቡ ያላችሁ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሀሰን ሁሴን ፡ መሐመድ አብደላ ፣ ባህሩ መካንጋ፣ እና አዲስ መሐመድ
- ፣ ለሱ ቀርበዋል ዐቃቤ ሕግ የጠዋቶቹ አልተለወጡም ቃለ መሀላ ይፈፅም ምስክር ፈሰሚል
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ
- የእርሶ ስም ያው የአባትዎን ስም ሳይጨምሩ የራስዎን ብቻ ?
- ናስር
- አቶ ናስር ስንተኛ ናቸው ዐቃቤ ሕግ 49ኛ ላይ ደርሰናል በተሰሙት በማስረጃ ግርግር ይ
- ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት አቶ ናስር ?
- አይ እኔ ማንም ላይ ሳይሆን እኔ የሰማሁት በ 7 /ዘኛወር ሐምሌ ላይ አለ የአንዋር መስኪድ ሠራተኛ ነኝ
- ስንት ዓ.ም ነው ?
- ዘኛ ወር በ 7 ሐምሌ 7
- ዓ.ም ?
- 2004 ነዋ
- የት መስኪድ ነው ያሉን ?
- አንዋር መስኪድ ሠራተኛ ነኝ
- አንዋር መስኪድ እሺ ለእኛ ይበቃናል ዐቃቤ ሕግ ያሉት ዋና ጥያቄ
- ሀጂ እስቲ አሁን የገለፁትን
- ምስክር ፊትዎን ወደ እኛ አድርገው በእዚያም በእዚያም ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል ያው የሚያውቁትን ይመሰክራሉ
- አሁን በገለፁት በሐምሌ 7/2004 ምንድን ነው ያዩት ?
- አሁን ያው የስራ ተግባሬ ያው መስለም ላይ ካዲም ስለሆንኩ ለመግባት ወደ ስራዬ ስመጣ
- የት መስኪድ ?
- አንዋር መስኪድ
- አንዋር መስኪድ ?
- ሰገባ መልካቸው ምንም በማይታወቅ ብዛት ባላቸው ሰዎች አላህከበር በሚሉ ሰዎች ጋር ስጓጓ ፍተሻ ላካሂድ አሉኝ እና እኔ በማንም እወቅና በሌለው ልፈተሸም እኔም ድርም ያው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የመስኪዱ ፊተሸ ነበርኩኝ ዛሬ ግን በእናንተ አልፈተሸም አላውቃችሁም ብዬ ወደ ኋላ ተመልሸአለሁ

- መስኪድ ፈተሻ ነበርኩ መስኪድ /ግልፅ ያልሆነ/
- ያው አውቃለሁ እፈትሻለሁ አንዳንድ ጊዜ ስካደም ሳይሆን የሚገባውን አስተናግዳለሁ እኔ እንደዚህ ዓይነት ነገር አይቼ አላውቅም አዲስ ነገር ነው ስገባ እንደዚያ ከታች እላይ ድረስ የሚፈተሸው ነገር እኛ አናደርግም ካዲም ማለት ካልሰ አውጡ ሞባይል አውጡ ቁርአን እየሰጠን ነው እንጂ እንደዚህ ያለ ነገር ኢንነሳም አላውቅም የመጀመሪያ ጊዜ ነው በቃ እውቅና በሌለው ሰው አልፈተሸም ብዬ ወደ ኋላ ሄጀለሁ 2 ሰዓት ተኩል ነበር
- አዲስ ነገር ሆነብኝ ያሉት ነገር እሱ ምንድን ነው አዲስ ነገር የሆነቦት ?
- በቃ ጨቸቱ አላህክበር የሚለው በጣም ያለው ረብሻው እራሱ ከሌላ ጊዜ የተለየ ነገር ነዋ የሆነብኝ
- ምንድን ነው መነሻው የረብሻው ?
- እኔ መነሻ አላውቅም የማውቀው ነገር የለም እኔ ያኢዚያ ቀን ያው እንዳለ ገቢቶ ግራማፎን ላይ የሚናገር ሰው ነበር የሚናገረውም ሰው ምንድን ነው የሚለው በአወሊያ መስኪድ የተቀለመውን ደማችንን በአንዋር መስኪያ የአወሊያ ደማችን በአንዋር መስኪድ እንደግመዋለን እንቀልመዋለን
- ምን ማለት ነው ?
- በአወሊያ የፈሰሰው ደማችን በአንዋር መስኪድ እንቀልመዋለን
- ምን እናደርገዋለን ?
- እንቀልመዋለን
- ምን ማለት ነው ?
- የማውቀው ነገር የለም እኔ
- ሰምተው ነው ሲባል ?
- የሰማሁት ነው በቃ ይቸው ነው
- ስንት ሰዓት ላይ ነው ሰዓቱ ?
- 2 ሰዓት ተኩል
- ማን ነው ይሄንን ያለው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን ይሄንን በሚሉበት ጊዜ እኔ ወደ ኋላ ሄጄ ከአንድ ግለሰብ ጋር ምንድን ነው ይሄ ነገር ማን ነው እንዲህ የሚናገረው በምል ጊዜ አቡበከር አህመድ ነው የ 17 ኮሚቴ ዋና ሊቀመንበር ነው ሲለኝ ነው የሰማሁት እንጂ ሰውዬው አቡበከር አህመድ መልኩንም አላወቀውም በአይኔም አይቼውም አላወቀውም ይሄንን ሲለኝ ጊዜ በኋላ በእዚያችው ሰዓት የአንዋር መስኪድ ካዲሞች ኢማሞች /ግልፅ ያልሆነ/ ሠራተኞች በአጠቃላይ ስራችሁ ግቡ እና ስራችሁን ጀምሩ መስኪዱን ከዛሬ ጀምረን እኛ ነን የተቆጣጠርነው እና ከዛሬ በኋላ ካልገባችሁ በቦታው ላይ ሰው እንተካበታለን እና የራሳችን ሠራተኛ እንቀጥራለን ብሎ ሲናገር እኔ በጣም በቁጣ መንፈስ እንዴት ሊያፈናቅሉኝ ነው በሚል ሰበብ ጠይቄ ነበር
- ማን ነው ይሄንን የሚለው ?
- ማን ነው ብዬ በምል ጊዜ አቡበከር አህመድ ነው የቀባለው እንጂ እኔ መልኩን አላወቀውም በማራማፎን ነው ውጪ ወደ ምንጣፍ ተራ አካባቢ ከግቢ ውጪ የሚሰማው ሀገር ሁሉ እየሰማሁ ነው ሀገር ሁሉ እያየሁ አይደለም እንዴ ምን አዲስ ነገር ነው እሱ ነገር እስካሁን ድረስ እንደዚያ ነው እኔ የሰማሁት በመቀጠል ደግሞ በማግስቱ በ 8 ደግሞ አሁንም በ 2004 በእዚያው ሰዓት ድንገት እዚያ ላይ ልግባ ብዬ በምመጣበት ሰዓት
- ስንት ሰዓት ነው ?
- በእዚያው ሰዓት በ 2 ሰዓት ተኩል መጣሁ አሁንም በማግስቱ ልገባ መጣሁ ስራዬ ቦታ
- ቆይ እስቲ ወደ ማግስቱ ሳንሄድ በ 7
- በ 7
- ስንት ሰዓት ላይ አለቀ ፕሮግራመ ?
- ቀን በመሉ ዋለ በታ
- እስከ ሰዓት እርሶ ቆዩ ?
- እኔ 2 ሰዓት ተኩል ገባሁ እና በታ ተመለስኩ አልገባሁም 4 ቀን ድረስ እኔ አቋርጠናለ እኛ ስራ አቋርጬለሁ እኔ አንገባም በታ ቦታው ተወስዷል እኛ
- ለምንድን ነው የማትገቡት ?
- እነሱ አልከለከሉንም እኛ ግን አንገባም ምክንያቱም በማናውቀው ሰው ስር ገብተን እኛ ከእነሱ ጋር ውዝንብር ስለሚፈጠር አንገባማ እኛ እኛ መደበኛ ሠራተኞች ነን ስለዚያ እኔ የማላውቀው ቦታ አልገባም ሰውም አዲስ ነው ንግግሩም አዲስ ስለሆነብኝ አልገባም እኔ ስራዬን አቀማለሁ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስቲ አሁን ያ'ከሰሉት ሀጂ እኛ አሁን እዚያ ቢታው ላይ አልነበረም ?
- አዎ
- ሁኔታው አዲስ ነገር ስለሆነብኝ አልገባሁኝም የሚሉት ድሮ ምን ስለነበረ ነው አሁን ምን ስለተፈጠረ ነው የሚለውን ዘርዘር አድርገው ይንገሩን እነዚህ ሰዎች ምንድን ነው የፈጠሩት እርሶ ከሚያውቁት ከተለመደው ማለት ነው ?
- የፈጠሩት ጩኸት ነው አላህክበር ነው ሁሉም አፉ አንድ ዓይነት ነው የተለየ ነገር የለም ሁሉም ንግግሩ አንድ ነው የማውቀውም ሰው እከሌ እከሌ የሚባል ነገር የለም በሺህ ቤት የሚቆጠር ሰው ነው እሱን እንዴት አድርጌ ዘርዝሬ መናገር እችላለሁ
- ስንት ዓመት ነው የሰሩት እርሶ ?
- እኔ 38 ዓመት ወደ 40ኛ ይገፍአለሁ
- 40 ዓመት ሰርተዋል ?
- አዎ
- 40 ዓመት መሉ ሲሰሩ እንዲህ ዓይነት ነገር ገጥሞት ያውቃል ?
- በዕድሜ ልኬም ወደ ፊትም ላየው አልፈልግም እንደዚህ ያለው ነገር
- እንደዚያ ?
- አዎ
- በ 8 ምን ተፈጠረ በ 8 በማግስቱ ያሉት ?
- በ 8 መጅሊስ ሌባ መጅሊስ ይውረድ እኛ እውቅና አልሰጠነውም እኛ ያልመረጥነው መጅሊስ ነው ይውረድ ፖሊስ ሌባ አላህክበር ነው በቃ በማግስቱ ከእዚያ ሌላ የሰማሁት ነገር የለም
- በ 8/11 እንደዚሁ እርሶ እስከ ስንት ሰዓት ቆዩ ?
- በቃ እኔ በኔ መስኪድ ወደ 4 ሰዓት ድረስ /ግልፅ ያልሆነ/ ነገሩ እየበዛ እየጨመረ እየጨመረ ሲሄድ ምንም መቆሚያ ስለሌው ከተማው ቀውጢ ስለሆነ በኔ ሰፈር የሚባል መስኪድ አለ ፒያሳ ሄጄ እዚያ ሰግጄ እቤቴ ገባሁ
- ለምን ወደ ቤትዎ ሄዱ ?
- በቃ እኔ መስማት አልፈለኩማ በቃ ጆሮዬ ሊሰማ አልቻለም ከምችለው በላይ ነው እራሴ በቃ አዲስ ነገር ስለሆነ በጣም ፈርቼዋለዋ እኔ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፈርተው ወደ ቢሂን መስክድ ሄዱ ?
- አዎ 4 ቀን ድረስ አልገባሁም ሰራ
- አንዋር መስክድ ምን ከእዚያ ውጪ አሁን ከሚሉት ፊቴቪት እና ረብሻ ውጪ ሌላ የተፈጠረ ነገር አለ እንዴ ?
- በር የአስተዳደሩ የአባስ በር ተሰብሯል በሩ ተገንጥሏል የነበለው ሰውዬውም አላውቅም በሩ ተገንጥሎ አይቼዋለሁ
- መቼ ነው የተገነጠለው ?
- እሱ በእዚያው አካባቢ ነው የሆነ ቀኑን አላውቀውም የእዚያ ቀን አይደለም በሩ ያው እንደዚህ ውዝንበር ነበር ሳምንት በሙሉ ነበር በእዚያ ጊዜ የአባስ ቢሮ ተሰብሯል አባስም ውስጥ ነበር ያው
- አባስ ምንድን ናቸው ?
- አስተዳደር ነው
- አስተዳደር ?
- አዎ
- የአንዋር መስኪድ ?
- አዎ
- ማን ነው የሰበረው ተባለ የሰሙት ነገር ?
- ማን እንደሆነ አላውቅም ወላሂ አላውቅም /ግልፅ ያልሆነ/
- የተሰበረው ምንድን ነው ?
- የተሰበረ መስኮቱ ተሰብሯል አዲስ መስታወት ነው የገባው አዲስ መስታወት ነው የገባለት ተሰብሯል መስታወቱ
- የትኛው ?
- የላኛው ቢሮ የአባስ ቢሮ
- የት ያለው ?
- የላኛው ይሄ በላይ ደረጃ ላይ ያለው ቢሮ
- የት መስኪድ ያለው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አንዋር መስኪድ ያለው ነዋ
- አባስ ምንድን ናቸው ?
- አስተዳደር ነው
- መስታወቱ ተሰብሯል ?
- መስታወቱ ተሰብሯል መዝያውም እንትን ብሎ ውስጥ ነበር እሱን ስለሚፈልጉት ና ውጣ ሲሉት በቃ አይ አሁን ደረስኩ እኔ በምደርስበት ሰዓት የእዚያ ቀን ፖሊስም ተመቶ ነበር አጋጣሚ ይሄ አጅንዳው ላይ የሌለ ነገር ነው መገኘበ ላይ በእዚህ ክሱ ላይ የለም አሁን እናንተ አልፋችሁ ሌላ የምትጠየቁኝ እንጂ የእዚያን ቀን የ 2 እና የ 7 እና የ 8 አሁን የምናገረው እኔ
- ይንገሩን ?
- አልፈን ከሄድን ብዙ ስለሚያመጣብኝ ወንጀል ነው ደግሞ ሌላ ነገር አታናግሩኛ
- አይደለም ይኸውሎት ምስክር በእዚህ ዙሪያ ላይ የሚያውቁትን ይጠየቃሉ ከፀቃቤ ሕግም ከእዚያም ሊጠየቁ ይችላሉ የተጠየቁትን ምላሽ የሚያውቁት ከሆነ የሚያውቁትን የሚያውቁት ከሆነ አላውቀውም የሰሙት ከሆነ ሰምቼአለሁ ምንም ችግር የለም የሚያውቁትን ነገር ይመስክሩ
- በቃ ተሰብሯል /ግልፅ ያልሆነ፣
- ሲጠየቁ እዚያ ሲጠየቁ የተጠየቁትን የሚያውቁት ከሆነ ይመልሳሉ ?
- በታ ተሰብሯል የሰበረውን አላውቅም
- ሀጂ ሌላስ የተሰበረ ነገር አለ ከእዚያ ወጪ ከመስኮት ?
- አንድ መዝግያ በአዲሱ መስኪድ ላይ መስኪዱ ተገንጥሎ መጥቶ ወይራው ላይ አምነሁለው አቀመው ታል ገንዘለው አምጥተውት እሱ አንድ መስኪድ አዲስ መስኪድ አለ ፊት ለፊት ከእዚያ መስኪድ ያለውን መዝጊያ ገንጥለው አምጥተውት መዝግያ ቢሮው ላይ ወደራው ላይ አቀመው ታል እሱንም ማን እንደሆነ አላውቅም ቆሞ ቆሞ ነው ያየሁት
- መጅመሪያ ማን ነው ያሰራው ?
- መስኪዱ ነዋ
- አዲስ መስኪድ የሚሉት አንዋር መስኪድ ውስጥ ያለ ነው ?
- አንዋር መስኪድ ያለ ነው ይለያል ለየት ያለ ነው ፈነጠር በሉ የታሰፈ መስኪድ ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተሰራ ?
- አዎ
- የእሱን በር ተገንጥሏል ?
- እሱ አንድ በር ተገንጥሎ እንደውም ተገንጥሎ ወጥቶ ወይራው ጋር ነው የቆመው አንድ በር ብቻ ግን ማን እንደሆነ አላውቀውም ቆሞ ነው ያየሁት እንጂ አላየሁትም ማን እንደሆነ
- አሁን መስኮት ነግረውናል በርም ተገንጥሏል ብለዋል ሌላስ ?
- ሌላ በቃ የማውቀው ነገር የለም በእዚሁ ላይ
- ቅድም ፖሊሶቹም የተመቱ አሉ ነው ያሉት ?
- ቀደም ሲል እሱ የነበረው ከሣምንቱ በፊት ያው አንዋር መስኪድ መቼ ጤና አለው
- ይቸውሎት ቆይ ሀጂ ይቸውሎት አሁን የሚያውቁትን እንዳለ ማለት ነው ወይ የሰሙትን ወይ የሚያውቁትን በሞላ ነው የሚነግሩን እሺ አሁን ስለዚህ ፖሊስ ተመቷል ያሉት የሰሙት ከሆነ ሰምቼ ነው ጊዜውንም እያስታወሱ ማለት ነው ?
- ሰምቼ በእዚያው ሣምንት አካባቢ ላይ ፖሊስ የ 4ኛ ፖሊስ ሊገላግል ገቡቶ ተመቷል ተብሏል ፖሊሱም አላየሁትም በቦታው የለሁም ወሬ ነው የሰማሁት
- ተመቷል ፖሊስ
- ሣምንት አካባቢ ማለት ከምን ተነስተነው ነው ከየትኛው ጅምሮ ሣምንትን ?
- ይሄኛው ረብሻ ከመምጣቱ በፊት አሁን እናንተ ጋር የምትጠይቂኝ አንድ ነገር ልንገራችሁ እናንተ ጋር ያለው መዝጉበ ላይ የለም ይሄ ቃሌ
- ቆይ ቆይ ይቸውሎት አሁን እኛ ጋር መኖር አለመኖሩ አይደለም እኛ የምንፈልገው ዐቃቤ ሕግ የሚጠይቀውን ጥያቄ እንድትመልሱ ነው እንጂ አሁን እዚህ ጋር ስለመኖሩ ምንም የሚያስጨንኖት
- በቃ ዐቃቤ ሕግ የሚጠይቀኝ ያለውን ነው የሌለውን ሊጠይቀኝ አይችልም
- ይቸሎት ይችላል እርሶ ደግሞ የሚያውቁትን መመለስ አለቦት ?
- በቃ ጨረስኩ
- አይደለም እየሰሙን ነው ?
- አዎ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እየተጠየቁ ነው ይሄ ፍ/ቤት የተቀመጠው እርሶ በሚናገሩት ነው የሚወሰን ስለዚህ አሁን የሚያወሩትን አልናገርም የሚያወሩት ነገር እንዳለ ይሰማናል ይታያል ያንን የሚያወሩትን ደግሞ መናገር ግዴታ አለቦት
- ተናግሬአለሁ በቃ
- ከሣምንት በፊት ፖሊሶች ተደብድበዋል ?
- እሱን ብዬአለሁ /ግልፅ ያልሆነ/
- ቆይ ቆይ እስቲ አዳምጡ እዚያ መስኪድ ውስጥ አንድ ቀን ጤና አድሮ አያውቅም ብለዋል አይደል ?
- አዎ
- ለምን ይሄንን መልሱ እንጂ ?
- አሁንም ጤና አይደለም ዛሬም ጤና አይደለም
- በፊት የነበረውን በፊት የነበረው ምንድን ነው ችግሩ ?
- ችግሩ የማውቀው ነገር የለም እኔ ከአወሊያ የመጣ ነገር
- ምክንያቱን የማያውቁ ከሆነ
- 17 ኮሚቴ ተበሎ የመጣ በአወሊያ የማውቀው ነገርየ የለም
- አዳምጡ አዳምጡ ቆይ አዳምጡ ምክንያቱን የማያወቁት ከሆነ ምንድን ነው ጤና የለውም ተበሎ የታመመው ነገር ምንድን ነው እሱን ንገሩን ?
- በቃ ከአወሊያ የተነሳ ረብሻ ነው ተበሎ ነው የመጣው ወደ እኛ አንዋር መስኪድ ያመጣው ከአወሊያ 17 ኮሚቴ ተበሎ የተባሉ ሰዎች ናቸው ያመጡት ተበሎ ነው የመጣው እኛ ጋር
- እሺ ሀጂ አሁን ያሉት ረብሻ ከአወሊያ የመጡ ኮሚቴ ያመጡት ነው ተበሎ ነው የተነገሮት ?
- አዎ
- እንደዚያ ነው የሰሙት እርሶ ?
- አዎ
- ሌላ የሚያስታውሱት ነገር አለ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የማስታውሰው የለም ሌላ በቀን በቀንማ የማስታውሰው ብዙ አለኝ በቀን በቀን የማስታውሰው መናገር አለብኝ በቀን በቀን ሁል ጊዜ የማስታውሰው አለ በቀን በቀን ሁሉ የማስታውሰው አለ አዲስ ነገር
- ይኸውሎት አሁን የምንነግሮት ያዳምጡናል አሁን የምንነግሮት የተጠየቁትን የሚያስታውሱት ከሆነ እና የሚያውቁት ከሆነ የመመለስ ግዴት አለቦት የማያውቁት ከሆነ አይገደዱም ያዳምጡ መጀመሪያ ያዳምጡ ነኛ ጥያቄውን የመወሰን የእርሶ አይደለም እዚህ ውስጥ አለ የለም የእርሶ አይደለም እርሶ ብቻ የሚጠየቁትን የሚችሉትን መመለስ የማይችሉትን ደግሞ አላስታውስም ማለት
- እሺ
- እንጂ አሁን በእዚህ ፍ/ቤት ነው የሚመሩት አሁን እርሶ እየመሩ ነው
- እሺ ሀጂ የማስታውሰውን ሁሉ ልናገር ወይ ብለዋል ተናገሩ ተበለዋል አሁን ይናገሩ ?
- ይሄ በየዕለቱ ያለውን ነገር መንግስት በጠራራ ፀሀይ እያየው
- መቃወሚያ አለ
- ምንድን ነው መቃወሚያ
- መቃወሚያችን ዐቃቤ ሕግ እሳቸው የሚያስታውሱትን ሁሉ ነገር እንዲዘከዝኩ አይደለም በጭብጡ ላይ ያስያዘው እና በክሱ ላይ ያለውን ነገር ነው ማስመስከር ያለበት ስለዚህ ፍ/ቤት ይሄንን ነገር ተናግሯል ብሎ የሚያውቁትን ሁሉ ተናገሩ ከማለት ይልቅ ባስያዘው ጭብጥ መሠረት ይጠይቅ ነው ካለበለዚያ እኮ ምንም መቆሚያ የሌለው ነገር ነው
- አሁን እኮ ፍ/ቤቱ ነው የፈቀደው
- ገባኝ የተከበረው ፍ/ቤት
- ይኸውሎት አሁን ሲመሰከር አሁን ዐቃቤ ሕግ ጋር እኛ የገባን ባነሱት ነገር ላይ ባነሱት ጭብጥ ላይ እየጠየቁ ነው ብለን ነው እያሰብን ያለነው
- አይደለም አሁን
- እዚያ ላይ ሲወጡ ጥያቄው ተጠየቆ ሲወጣ እና ሲመለስ ከክሱ ላይ ከሌለ እናንተ መቆጣጠር ነው እዚያ ላይ ከሌለ ግን በእዚህ ጉዳይ ላይ አሁን በጠየቅነው ጉዳይ ላይ የሚያስታውሱት ነገር ካለ ይጨምሩ ነው ያሉ ስለዚህ ስህተት የለውም
- ይንገሩን ሀጂ የሚያስታውሱትን ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የማስታውሰው የለኝም በቃ ጨርሻለሁ
- ቅድም አስታውሳለሁ እኮ ብለውን ነበር ?
- እናንተ እኮ የማስታውሰው እኔ ዛሬ እዚህ መጣሁ እንጂ እኔ የእዚያ ሠራተኛ ነኝ ብያችዋለሁ በቀን ቀን ሁል ጊዜም በቃ መስኪድ ላይ ሁል ጊዜም ረብሻ ነው የማስታውሰው እኛ ሰላም የለንም ነው በቃ መስኪድ ላይ ሁሌም ረብሻ ነው የማስታውሰው ምንድን ነው እሱን በየቀኑ መዝግቤ እይዛለሁ እንዴ ይሄ የመንግስት ጉዳይ ስለሆነ እኔ የምሰራው ስራ የእኔ ስራ እንጂ በቀን በቀን መዝግቤ እዚህ ፍ/ቤት እመጣለሁ ብሎ የሌለው ነገር /ግልፅ ያልሆነ/
- ስለዚህ እርሶ እዚያ ሠራተኛ ሆነው በነበሩበት ጊዜ ከተለመደው ውጪ ሲረበሽ እና ባልተለመደ ሁኔታ
- እሱ ተጠይቋል ዐቃቤ ሕግ እሱ ተጠይቆ ቅድም መልሰው ታል ሌላ ጥያቄ
- ጨርሰናል
- ምስክር ቅድም መስታወት ተሰበረ የቢሮ መስታወት ተሰበረ በር ተገነጠለ ብለዋል ይሄንን ያደረገውን አላየሁትም ብለዋል አይደለም ?
- አዎ ብዬአለሁ
- ከማን ወገን ያሉ ሰዎች ናቸው ይሄንን ያደረጉት ?
- አሁን በተነሳው ተያያዥነት
- ተቃውሞ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ምንድን ነው ተቃውሞ
- የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ በሰጡት ምስክርነት ወገን ምናምን የሚሉት ነገር አላነሱም ዐቃቤ ሕጉ ናቸው ወገን ብለው እየጨመሩ ያሉት ጥያቄው ተስተካክሎ ይጠየቅ መሪ ነው የሚሆነው ያለበለዚያ
- ፍ/ቤቱም እንዳዳመጠው ቅድም ምስክሩ ባልደረባዬ ሲጠየቁ 17ቱ ኮሚቴዎች ከአወሊያ ይዘው የመጡት ነገር አንዋር ላይ ሲደረግ የነበረው ብለው ሲናገሩ ነበር እና ተሰበረ መስታወት ተሰበረ በር ተገነጠለ ብለው መስክረዋል ማን ነው ይሄንን ያደረገው ስላላዩት ትክክለኛውን ሰው ከየትኛው ወገን ያለ ነው ብለን የጠየቅነው እና ስለኮሚቴም ሲመሰክሩ ነበር በሩ ስለመሰበሩ ሲመሰክሩ ነበር ማን ነው የሰበረው ብሎ መጠየቅ አግባብነት ያለው እና ውድቅ ይደረግ መቃወሚያው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/